## ማውጫ

ክፍል 17 ........ 1
ንግድና ኢንዱስትሪ ........ 1
ሀ/ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ ........ 1
አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓ.ም ........ 1
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ........ 1
ደንብ ቁጥር 392/2009 ........ 34
ስለንግድ ምዝገባና ፈቃድ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 34
ደንብ ቁጥር 246/2003 ........ 66
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ተመኖች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 66
ለ/ ስለፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ........ 70
አዋጅ ቁጥር 847/2006 ........ 70
የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ........ 70
ደንብ ቁጥር 332/2007 ........ 107
የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 107
ሐ/ ስለ ልዩ ልዩ የንግድ ህጎች ........ 124
የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 246/1954 ዓ.ም ........ 124
ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ስለሚላክ ዝባድ የወጣ ደንብ ........ 124
አዋጅ ቁጥር 181/1992 ........ 129
ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅትን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ለማስተላለፍ የወጣ አዋጅ ........ 129
አዋጅ ቁጥር 103/1990 ........ 130

## የፍትህ ሚኒስቴር


የካፒታል እቃ ኪራይ ንግድ ስራ አዋጅ ........ 131

ደንብ ቁጥር 309/2006 ዓ.ም ........ 142

ስለካፒታል እቃዎችና ስለካፒታል እቃ ኪራይ ስምምነቶች ምዝገባና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 142

አዋጅ ቁጥር 261/1994 ዓ.ም ........ 148

በአፍሪካ የእድገትና የተጠቃሚነት ሕግ መሠረት የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ምርቶችን ወደ አሜሪካ ሀገር ስለመላክ የወጣ አዋጅ ........ 148

አዋጅ ቁጥር 372/1996 ዓ.ም ........ 156

የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ........ 156

ደንብ ቁጥር 126/1998 ........ 179

የወጪ ንግድ ሽልማት አሰጣጥ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 179

አዋጅ ቁጥር 759/2004 ........ 183

ስለ ማስታወቂያ የወጣ አዋጅ ........ 183

አዋጅ ቁጥር 813/2006 ዓ.ም ........ 204

ስለ ንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ የወጣ አዋጅ ........ 204

አዋጅ ቁጥር 1147/2011 ........ 231

በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ ........ 231

አዋጅ ቁጥር 1205/2012 ........ 274

የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽንን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ........ 274

መ/ ኢንዱስትሪ ልማት ........ 300

አዋጅ ቁጥር 886/2007 ........ 300

የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ........ 300

ደንብ ቁጥር 417/2009 ........ 321

ስለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 321

ሠ/ ስለምርት ገበያ ........ 345

አዋጅ ቁጥር 550/1999 ........ 345

የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 345

አዋጅ ቁጥር 551/1999 ........ 362

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........ 362

ደንብ ቁጥር 178/2002 ........ 379

የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 379

ደንብ ቁጥር 377/2008 ........ 396

የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 396

ክፍል ሃያ ........ 409

ኢንቨስትመንት፣ አምሮአዊ ንብረት እና ጥራትና ደረጃዎች ........ 409

ሀ/ ኢንቨስትመንት ........ 409

አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ........ 409

የኢንቨስትመንት አዋጅ ........ 409

ደንብ ቁጥር 473/2012 ዓ.ም ........ 439

የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ........ 439

ደንብ ቁጥር 270/2005 ........ 443

ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 443

ደንብ ቁጥር 162/2001 ........ 468

ስለመስኖ ልማት ኢንቨስትመንት ማበረታቻ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 468

ለ/ አምሮአዊ ንብረት ........ 471

አዋጅ ቁጥር 123/1987 ........ 471

የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ፣ ........ 471

ደንብ ቁጥር 12/1989 ........ 489

የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራ እና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ. 489

አዋጅ ቁጥር 410/1996 ........ 518

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ........ 518

ደንብ ቁጥር 305/2006 ........ 547

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የሚያስገኙ ሥራዎች ለመመዝገብ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 547

አዋጅ ቁጥር 501/1998 ........ 553

የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ........ 553

ደንብ ቁጥር 273/2005 ........ 574

ስለንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 574

ሐ/ ጥራትና ደረጃዎች ........ 602

የመንግሥት ማስታወቂያ ቁጥር 6/1934 ዓ.ም ........ 602

አዲሱን ደንበኛ ሰዓት በኢትዮጵያ ስለመከተል የወጣ ማስታወቂያ ........ 602

የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 431/1965 ዓ.ም ........ 603

የሚዛንና የመሥፈሪያ ደንብ ........ 603

የደንብ ቁጥር 13/1982 ........ 613

የደረጃዎች ማኅተም እና የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 613

ደንብ ቁጥር 476/13 ........ 628

የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ........ 628

ክፍል ሃያ አንድ ........ 632

የባንክ እና መድህን ስራ ........ 632

ሀ/ የባንክ ስራ ........ 632

## የፍትህ ሚኒስቴር


አዋጅ ቁጥር 97/1990 ዓ.ም ........ 632

በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ........ 632

አዋጅ ቁጥር 592/2000 ........ 635

ስለባንክ ሥራ የወጣ አዋጅ ........ 635

አዋጅ ቁጥር 626/2001 ........ 675

አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ........ 675

አዋጅ ቁጥር 718/2003 ........ 698

የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ........ 698

ለ/ የመድህን ስራ ........ 723

አዋጅ ቁጥር 746/2004 ........ 723

የመድን ሥራን አዋጅ ........ 723

አዋጅ ቁጥር 799/2005 ........ 765

ስለተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የወጣ አዋጅ ........ 765

## ክፍል 17

## ንግድና ኢንዱስትሪ

### ሀ/ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ

## አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓ.ም

## የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ

የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ፍትሀዊ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ በማድረግ የንግዱን ማህበረሰብ እና ህብረተሰቡ ከንግዱ ሥርዓት የሚጠብቀውን አገልግሎት እንዲያገኝ የሕግና የአሠራር ክፍተቶችን በመድፈንና እርካታን በማሳደግ በአገሪቱ ሁለንተናዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ማድረግ በማስፈለጉ፤

የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ፈቃድ አሰጣጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ የንግድ ሥርዓቱ ለመረጃ አያያዝ አመቺ እንዲሆን፣ ሕገወጥ እንቅስቃሴ ለመግታት የሚያስችል፣ ለመንግስት፣ ለህብረተሰብ እና የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የንግድ ሥርዓቱ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት እና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት በማድረግ የአገሪቱን ራዕይ ለማሳካት እንዲቻል አገሪቱ ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሕግ እንዲኖራት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "የንግድ ሕግ" ማለት የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ነው፤

2. "ነጋዴ" ማለት ንግድን የሙያ ሥራው አድርጎ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት በንግድ ሕጉና በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን ማንኛውንም ሥራዎች የሚሰራ ሰው ነው፤[1]
3. "የንግድ ሥራ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተተረጎመው መሠረት ነጋዴ የሚሰራው ማንኛውንም ሥራ ነው፤
4. "አገልግሎት" ማለት ደመወዝ ወይም የቀን ሙያተኛ ክፍያ ያልሆነ ገቢ የሚያስገኝ ማንኛውም አገልግሎት የመስጠት ንግድ ሥራ ነው፤
5. "የአገር ውስጥ ንግድ" ማለት እንደአግባቡ በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ዕቃ በጅምላ ወይም በችርቻሮ መሸጥን ወይም አገልግሎት መስጠትን ወይም ቁም እንስሳትን ከአምራች ገዝተው ወይም አደልበው ለገበያ የሚያቀርቡትን የሚያካትት ነው፤
6. "የውጭ ንግድ" ማለት ለሽያጭ የሚሆኑትን የንግድ ዕቃዎች እና አገልግሎቶችን ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ መላክ ወይም ከውጭ አገር ወደ ሀገር ውስጥ የማስመጣት ንግድ ሥራ ነው፤
7. "የንግድ ወኪል" ማለት ከነጋዴው ጋር እንዲሠራ በውል የተቀጠረ ሳይሆን ነጋዴ ሆኖ ራሱን የቻለ ሥራ ሊሠራ በተወሰነ ሥፍራ በነጋዴው ስምና ምትክ ውል እንዲዋዋል ውክልና የተሰጠው ሰው ነው፤
8. "የንግድ ዕቃዎች" ማለት ገንዘብና ገንዘብነት ካላቸው ሰነዶች በስተቀር ማናቸውም የሚገዙ ወይም የሚሸጡ ወይም የሚከራዩ ወይም በሌላ ሁኔታ በሰዎች መካከል የንግድ ሥራ የሚከናወንባቸው የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎች ናቸው፤
9. "የንግድ እንደራሴ" ማለት መኖሪያው የወካዩ የንግድ ማህበር ወይም ነጋዴ ጽሕፈት ቤት ባለበት አገር ያልሆነና ከንግድ ማህበሩ ወይም ከነጋዴው ጋር በተዋዋለው የሥራ ውል መሠረት በንግድ ማህበሩ ወይም በነጋዴው ስምና ምትክ ሆኖ ነጋዴ ሳይሆን የንግድ ማስፋፋት ተግባር የሚያከናውን ሰው ነው፤
10. "የንግድ ስም" ማለት አንድ ነጋዴ ለንግድ ሥራው የሚጠቀምበት እና በህብረተሰቡ ዘንድ በግልጽ የሚታወቅበት ስም ነው፤
11. "የንግድ ድርጅት ስም" ማለት አንድ የንግድ ድርጅት ለንግድ ምዝገባ የሚጠቀምበት፣ በመዝጋቢው መሥሪያ ቤት እና በሦስተኛ ወገኖች የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑ የሚታወቅበት ስም ነው፤

[1] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

12.“የፀና የንግድ ሥራ ፍቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በበጀት ዓመቱ የተሰጠ ወይም የታደሰ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ያለቅጣት የሚታደስበት ጊዜው ያላለፈበት የንግድ ሥራ ፈቃድ ነው፤

13.“ኢንዱስትሪ” ማለት ማንኛውም የንግድ ተግባር ሆኖ በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ ወይም በሌሎች መሣሪያዎች የንግድ ዕቃዎችን ወይም የንግድ ዕቃዎችን ለማምረት የሚያገለግሉ ግብአቶችን የማምረት ሥራን፣ የኢንጂነሪንግ አገልግሎትን፣ ሌላ ማንኛውም የአገልግሎት መስጠት ሥራን እና የምርምር ሥርጸት ሥራን ያጠቃልላል፤

14.“የማምረት ሥራ" ማለት በኢንዱስትሪ የሚከናወን የመቀመም፣ የመለወጥ፣ የመገጣጠም ወይም የማሰናዳት ሥራን ወይም የግብርና ልማት ወይም የማዕድን ፍለጋና ልማት ወይም የማምረት ሥራን ያካትታል፤

15. “የኢንጂነሪንግ አገልግሎት” ማለት ለኢንዱስትሪ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ወይም የኤሌክትሪክ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ መሳሪያዎችን መጠገን፣ ማደስ ወይም የግንባታ ማማከር፣ የግንባታ አስተዳደር፣ የመሣሪያ ተከላና ማማከር አገልግሎት፣ የኢንጂነሪንግ ማማከር የቅድመ ዲዛይን አገልግሎት፣ የኢንጂነሪንግ ዲዛይን አገልግሎት፣ የቁጥጥር አገልግሎትን ወይም የመሳሰሉትን ያካትታል፤

16. “የአገር ውስጥ ባለሀብት” ማለት ካፒታሉን በንግድ ሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም እንደ ሀገር ውስጥ ባለሀብት እንዲቆጠር አግባብ ባለው አካል የተፈቀደለት የውጭ ሀገር ዜጋ ነው፤

17.“የውጭ ባለሀብት” ማለት ካፒታሉን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት በኢንቨስትመንት አዋጁ መሠረት በተፈቀደለት የንግድ ሥራ ዘርፍ ላይ ኢንቨስት ያደረገ የውጭ ሀገር ዜጋ ወይም ሙሉ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ወይም ከሀገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ድርጅት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ ሀገር ዜጋ ወይም ድርጅት ነው፤

18. “ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ” ማለት ማንኛውንም ንግድን የሚመለከት የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ድርጊት ነው፤

19.“የግብርና ልማት” ማለት ማንኛዉንም የዕፅዋት ልማት ወይም የእንስሳትና ዓሣ ልማት ወይም እንስሳት ተዋፅኦ የማልማት ንግድ ሥራ ነዉ፤

20.“የንግድ ምዝገባ” ማለት በንግድ ሕጉ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደረግ ምዝገባ ነው፤

21.“መዝጋቢ መሥሪያ ቤት” ማለት የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ስም ምዝገባን የሚያከናውን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ነዉ፤

22.“አስመጪ” ማለት የንግድ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስመጣ ሰው ነው፤

23.“ላኪ” ማለት የንግድ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ሀገር የሚልክ ሰው ነው፤

24.“ልዩ የምዝገባ መለያ ቁጥር” ማለት ለግለሰብ ነጋዴ፣ ለንግድ ማኅበር ወይም ለእንደራሴ በሚመለከተው አካል የሚሰጥ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ነው፤

25. “ጅምላ ነጋዴ” ማለት የንግድ ዕቃዎችን ከአምራች ወይም ከአስመጭ ገዝቶ ለቸርቻሪ ወይም ለመንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ወይም ለህብረት ሥራ ማህበራት በጅምላ የሚሸጥ ማንኛዉም ሰዉ ነዉ፤

26.“ችርቻሮ ነጋዴ” ማለት የንግድ ዕቃዎችን ከአምራች፣ ከአስመጭ ወይም ከጅምላ ሻጭ ገዝቶ ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ የሚሸጥ ማንኛዉም ሰው ነዉ፤

27.“የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት” ማለት በመንግሥት የልማት ድርጅትነት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ሁሉም አክሲዮኖቹ በፌዴራል መንግስት የተያዘ የንግድ ድርጅት ነው፤

28.“የክልል መንግስት የልማት ድርጅት” ማለት በክልል መንግስታት ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ሁሉም አክሲዮኖቹ በክልል መንግሥታት የተያዘ የንግድ ድርጅት ነው፤

29.“መሠረታዊ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት” ማለት በገበያ ላይ እጥረት በመፈጠሩ ምክንያት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ ውድድር ሊያስከትል የሚችል ከሸማቾች የየዕለት ፍላጎት ጋር የተገናኘ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሆኖ፣ በሚመለከተው አካል መሠረታዊ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ተብሎ በሕዝብ ማስታወቂያ የሚገለጽ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው፤

30.“የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት ሚኒስቴሩ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት ለተወሰኑ አግባብነት ላላቸዉ የንግድ ሥራዎች በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ተገቢው ብቃት መሟላቱን በማረጋገጥ ከሚመለከተዉ የሴክተር መሥሪያ ቤት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

31.“የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት” ማለት ነጋዴዎች የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በየደረጃው በሀገሪቱ ሕግ መሰረት የሚያቋቁሙት ምክር ቤት ነው፤

32.“የዘርፍ ማህበራት” ማለት በአምራችነት ወይም በአገልግሎት ሰጪነት በአንድ ዓይነት የንግድ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችን ወይም ፆታን መሠረት በማድረግ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ንግድን ለመደገፍ የተደራጁ ማህበራት ናቸው፤

33.“የፍራንቻይዝ ስምምነት” ማለት ዕዉቅና ባገኘዉ ምርት ወይም አገልግሎት ንግድ ስም ተጠቅሞ፣ ዕዉቅና ባገኘዉ ምርትና አገልግሎት ባለቤት መሪነት የሥራዉን ባህሪና ልምድ ለመካፈል በፍረንቻይዘርና በፍረንቻይዚ መካከል ለጥቅም ተብሎ የሚደረግ ስምምነት ነዉ፤

34.“የኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰጥባቸው የንግድ ሥራዎችን ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ የያዘ ሀገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው በሚኒስቴሩ የሚወጣ መመሪያ ነው፤[2]

35.“ንብረት" ማለት የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሆኖ የአዕምሯዊ ፈጠራ ንብረት መብትን ይጨምራል፤

36.“አስተዳደራዊ እርምጃ” ማለት አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚወሰድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ እሽጋ ፣ እገዳ፣ ስረዛ ወይም መሰል እርምጃዎችን ያካትታል፤

37.“በተመሳሳይ ደረጃ የሚደረግ ግብይት” ማለት የጅምላ ነጋዴ ከጅምላ ነጋዴ ወይም የችርቻሮ ነጋዴ ከችርቻሮ ነጋዴ ጋር የሚያደርገው የግብይት ዓይነት ነው፤

38.“አግባብ ያለው የሴክተር መሥሪያ ቤት” ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ወይም ተመሳሳይ ተግባራትን የሚያከናውን አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ነው፤

39.“ኩባንያ” ማለት ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ነው፤

40.“ሆልዲንግ ኩባንያ” ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ኃላፊነታቸዉ የተወሰነ የንግድ ማህበራትን ያቀፈ፣ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው እና በሆልደሩ የሚመራ ኩባንያ ነዉ፤

[2] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

41.“የጠረፍ ንግድ” ማለት ከኢትዮጵያ ድንበር አዋሳኝ በሆኑ ሀገሮች በሁለትዮሽ ስምምነት ወይም በተናጠል ውሳኔ በድንበር አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ወይም ነጋዴዎች ሚኒስቴሩ በጠረፍ ንግድ መመሪያ በሚወስነው መሠረት ከሀገሪቱ ድንበር ባሻገር ጭምር በልዩ ሁኔታ የሚነግዱበት የንግድ ሥራ ዓይነት ነው፤

42. “የበጀት ዓመት” ማለት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለው ጊዜ ወይም ነጋዴው በሚያቀርበዉ የፀደቀ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ላይ ወይም በሌላ ሁኔታ የወሰነውን ጊዜ መሠረት ያደረገ ዓመት ነዉ፤

43.“ተቆጣጣሪ” ማለት የንግድ ሥራዎች ሕግን ተከትለው ስለመተግበራቸው እንዲቆጣጠር አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚመደብ ሰው ነው፤

44.”አግባብ ያለው ባለስልጣን” ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፤”[3]

45.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[4]

46.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

47.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

48.በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በአንቀጽ 21(4) ከተመለከቱት የንግድ ሥራዎች በስተቀር በነጋዴዎች፣ በዘርፍ ማህበራት፣ በንግድ እንደራሴዎች እና በማንኛውም ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ በሚገኝ ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. <u>አግባብ ያለው ባለሥልጣን ተግባር እና ኃላፊነቶች</u>

1. ሚኒስቴሩ ሀገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው ማዕከላዊ የንግድ መዝገብ እና የንግድ ስም መዝገብ በዚህ አዋጅ መሠረት ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤ ለህዝብ ክፍት እንዲሆንም ያደርጋል፡፡

[3] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(3) ተሻሻለ፡፡
[4] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(4) ተሻሻለ፡፡

2. ሚኒስቴሩ የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ስም ምዝገባ ያከናውናል፡፡
3. ንግድን የሚያስተዳድሩ የክልል አካላት እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከሚኒስቴሩ በሚሰጥ ውክልና መሠረት የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ስም ምዝገባ ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡
4. ሚኒስቴሩ የመዘገበውን የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ስም ምዝገባ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ ያስገባል፤ ንግድን የሚያስተዳድሩ የክልል አካላት እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በውክልና የመዘገቡትን መረጃ ወደ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ያስተላልፋሉ፡፡
5. ሚኒስቴሩ በተለየ ሁኔታ ሕጋዊ ሰውነት መብት ለሚሰጣቸው እና ልዩ የምስክር ወረቀት ለሚሰጣቸው አካላት ይህንኑ የሚያረጋግጡ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
6. ሚኒስቴሩ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የዘርፍ ማህበራትን መዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ንግድን የሚያስተዳድሩ የክልል አካላት በክልል ደረጃ የሚቋቋሙ የዘርፍ ማህበራትን መዝግበው የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፡፡
7. ሚኒስቴሩ በፌደራል ደረጃ ፈቃድ ለሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ መደቦች የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ንግድን የሚያስተዳድሩ የክልል አካላት በክልል ደረጃ ፈቃድ ለሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ መደቦች የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣሉ፡፡
8. አግባብ ያለው ባለስልጣን ለሚመለከታቸው አካላት እና ጥያቄ ለሚያቀርቡ ለሌሎች ሰዎች እንደአስፈላጊነቱ ንግድ ነክ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡
9. ሚኒስቴሩ የኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል ወይም እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡
10. ሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ሥራ መደቦች ከሚመለከታቸው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ይለያል፤ መስፈርቶች እንዲዘጋጅላቸዉ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥም ያስተባብራል፤ በራሱ ሥልጣን ሥር ለሚውሉ የንግድ ሥራ መደቦች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
11. አግባብ ያለው ባለስልጣን አዋጁን፣ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተላልፈው በሚገኙ ሰዎች ወይም ነጋዴዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ሕጋዊ እርምጃዎች በሌሎች አካላት እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡

12.አግባብ ያለው ባለስልጣን ነጋዴዎች በሰጣቸው የምስክር ወረቀቶች ላይ የተገለፁ ተግባራትን በትክክል ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆናቸው ቅድመና ድህረ ፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

13.አግባብ ያለው ባለስልጣን ለንግዱ ማህበረሰብ እና ለሚመለከታቸው አካላት የአቅም ግንባታ እና ሌሎች ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

14.አግባብ ያለው ባለስልጣን ይህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንብና መመሪያዎች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆናቸውን የሚከታተሉ ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፡፡

15.ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሰጣቸው ውክልናዎች አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

16.አግባብ ያለው ባለስልጣን በሥልጣኑ ሥር የሚውሉ የዚህ አዋጅ፣ የደንቡና የመመሪያውን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ያደርጋል ወይም ያስተገብራል፤ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

17.የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን የኢንፎርሜሽን መገናኛ ቴክኖሎጂ አውታሮችን በመጠቀም ተገልጋዮች ወደ አገልግሎት ሰጪው በአካል ሳይቀርቡ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሰራሮችን እና ሥርዓቶችን በሀገር አቀፍ ደረጃ ይዘረጋል፤ ተፈፃሚ እንዲሆንም ያደርጋል፤[5]

## ክፍል ሁለት

## ስለንግድ መዝገብ

5. **በንግድ መዝገብ ስለመመዝገብ**

1. ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ ላይ ሳይመዘገብ ማንኛውንም ዓይነት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው ዋና መስሪያ ቤቱ ባለበት ሥፍራ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም ሰው በተለያዩ ክልሎች የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን ቢሠራም በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡

[5] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(5) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

4. በተለያዩ ሥፍራዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት የሚከፍት ማንኛውም ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት የመጀመሪያ ምዝገባ በተመዘገበበት ቦታ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን ማስመዝገብና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ሥፍራ ላለው መዝጋቢ መሥሪያ ቤት ወዲያዉኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
5. በንግድ ሕግ መሠረት ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ ሲመዘገብ የድርጅት ስሙ ከሌላ ነጋዴ ጥቅም ጋር የማይጋጭ መሆኑን በማረጋገጥ በንግድ መዝገብ ውስጥ መግባት አለበት፡፡
6. በንግድ ማህበራት መመስረቻ ጽሑፎችና መተዳደርያ ደንቦች እንዲሁም ማሻሻያዎች እና ለውጦቻቸው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ አካላት ውስጥ በሚቋቋሙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰነዶችን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሙያተኛ በመመደብ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤[6]
7. የንግድ ማህበር መስራቾች ወይም አባላት የመመስረቻ ጽሁፎቻቸውን ወይም መተዳደሪያ ደንቦቻቸውን ከመፈራረማቸው በፊት የንግድ ማህበሩ ስም በሌላ ነጋዴ ያልተያዘ መሆኑን በቅድሚያ ለመዝጋቢው መስሪያ ቤት በማመልከት ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
8. በንግድ ሥራ ተሰማርቶ የነበረ ግለሰብ ነጋዴ ወራሾች እና የትዳር ጓደኛ በንግድ ሥራው ለመቀጠል የንግድ ማህበር ለማቋቋም ያልፈለጉ ከሆነ ከወራሾቹ አንዱ ወይም የትዳር ጓደኛው ከሌሎቹ ወራሾች እና/ወይም የትዳር ጓደኛ በሚሰጠው ውክልና መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገብ ይችላል፡፡
9. በንግድ ማህበር ውስጥ በዓይነት የሚደረግ መዋጮን ግምት የንግድ ማህበሩ መስራቾች ወይም አባላት ባደረጉት ስምምነት የተወሰነ መሆኑ በመመስረቻ ጽሁፉ ወይም በመመሥረቻ ጽሁፉ ማሻሻያ ውስጥ መጠቀስ አለበት፡፡
10. በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ አካላት ውስጥ በሚቋቋሙ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሙያተኛ በመመደብ ሥራው እንዲሰራ ያደርጋል፤[7]

6. <u>የንግድ ምዝገባ ስለማከናወን</u>

1. ለንግድ ምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የሚጠየቁትን ሰነዶች

[6] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(5) ተሻሻለ፡፡
[7] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(5 መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

በማያያዝ የንግድ ሥራው ይጀምራል ተብሎ ከሚታሰብበት ቀን አስቀድሞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. ማናቸውም ለመዝጋቢው አካል በንግድ መዝገብ ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ መዝጋቢው መሥሪያ ቤት የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ምዝገባ በማከናወን የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ወዲያውኑ ለአመልካቹ ይሰጠዋል፤ ሆኖም የምዝገባ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ውድቅ በማድረግ ምክንያቱን ገልፆ ለአመልካቹ በጽሁፍ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በማዕድን ዘርፍ የሚሰማሩ የውጭ ነጋዴዎች፣ የፌደራል መንግስት ልማት ድርጅቶች፣ የንግድ እንደራሴዎች፤ የውጭ አገር ነጋዴዎች፣ በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር ነጋዴዎች፣ ተቋቁሞ የሚገኝ የንግድ ድርጅቶችን ገዝቶ ባለበት ሁኔታ ንግድ ለማካሄድ የሚፈልግ የውጭ አገር ነጋዴ፣ በሌሎች ሕጎች የንግድ ሥራ እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው ማህበራት፣ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት እንዲሁም በሚኒስትሩ ታምኖበት የተፈቀደላቸው የውጭ አገር ንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚኒስቴሩ ይመዘገባሉ፡፡
4. በክልል መንግስታት የሚቋቋሙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በተዋረድ በክልል የሚቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት ንግድን በሚያስተዳድሩ የክልል አካላት ይመዘገባሉ፡፡
5. ሚኒስቴሩ ፈቃድ በሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ መስክ መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ ለመመዝገብ በቀጥታ ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል፡፡
6. ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማህበር በንግድ መዝገብ እንዳይመዘገብ በሕግ መሠረት የሚቀርብ መቃወሚያ በንግድ መዝገብ ከመመዝገብ ያግደዋል፡፡

7. <u>የንግድ ምዝገባ ስለሚፀናበት እና የንግድ ማህበራት ሕጋዊ ሰውነት</u>
    1. የንግድ ማህበራት የሕግ ሰውነት የሚያገኙት በምዝገባ ይሆናል፡፡
    2. የግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማህበራት ሲመሰረቱ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለሚሰጣቸው ሰዎች አግባብ ያለው ባለስልጣን ተደራሽ የሆኑ የኢንፎርሜሽን መገናኛ ቴክኖሎጂ አውታሮችን በመጠቀም የምዝገባና ፈቃድ መረጃዎቻቸውን ይፋ ያደርጋል፤[8]

[8] 25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(7) ተሻሻለ፡፡

3. የንግድ ማህበራት መዝገብ ለሕዝብ ክፍት መሆን ይኖርበታል፤ ሦስተኛ ወገኖችም መዝገቡን መመልከት ይችላሉ፡፡
4. ማንኛውም የንግድ ምዝገባ የሚፀናው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አመልካቹ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ነው፡፡

8. **<u>የምዝገባ መረጃዎችና ሰነዶችን ስለማስተላለፍ</u>**

1. ንግድን የሚያስተዳድሩ የክልል አካላት ወይም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ መሠረት የንግድ ምዝገባ እንዳከናወኑ የምዝገባ መረጃዎችን ሚኒስቴሩ ለዚሁ ዓላማ በሚያዘጋጀው የመረጃ ቋት አማካይነት ወዲያዉኑ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተላለፈለትን እና ራሱ የመዘገባቸውን መረጃዎች ወዲያዉኑ በማዕከላዊ የንግድ መዝገብ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

9. **<u>የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር</u>**

1. መዝጋቢው መሥሪያ ቤት ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ማህበር እና የንግድ እንደራሴ በንግድ መዝገብ ከመግባቱ በፊት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሰጠው ግብር አስከፋዩን አካል በደብዳቤ ይጠይቃል፡፡
2. ግብር አስከፋዩ አካል በምስረታ ላይ ላለው የንግድ ማህበር ወይም የንግድ እንደራሴ የሰጠውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመዝጋቢው ያሳውቃል፡፡
3. መዝጋቢው መሥሪያ ቤት ከግብር አስከፋዩ አካል የሚሰጠውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምዝገባ ማመልከቻ ላቀረበው ነጋዴ ወይም የንግድ እንደራሴ በልዩ የምዝገባ መለያ ቁጥርነት በመዝገብ ያስገባል፡፡

10. **<u>የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ</u>**

1. ማንኛውም የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ በንግድ ሕጉ መሠረት መዘጋጀቱን በማረጋገጥ መዝጋቢው አካል መመዝገብ አለበት፤[9]
2. የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ለማስመዝገብ የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ መዝጋቢው አካል ተቀባይነት ያገኘበትን ቀንና በንግድ መዝገብ ስለገባው ለውጥ ወይም ማሻሻያ በዝርዝር በመግለፅ ለአመልካቹና ለሚመለከታቸው አካላት

[9] 25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(9) ተሻሻለ፡፡

በጽሁፍ ማረጋገጫ መስጠት አለበት፤ ይህ የጽሁፍ ማረጋገጫ ካልተሰጠ በስተቀር የቀረበው የምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ በንግድ መዝገብ እንደገባ አይቆጠርም፡፡

3. መዝጋቢው አካል ያለአግባብ ተለውጧል ወይም ተሻሽሏል ብሎ የሚያምንበትን የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ መሰረዝና ይህንኑ አመልካቹ እንዲያውቀው በዝርዝር በጽሁፍ መግለፅ ይችላል፡፡
4. በዚህ አዋጅ ለንግድ ምዝገባ የተቀመጡ መስፈርቶች እንዳስፈላጊነቱ በንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
5. [10]

11.<u>የንግድ ምዝገባን ስለመሰረዝ</u> [11]

1. በንግድ ሕጉ ምዝገባን ስለመሰረዝ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው፦
   ሀ) ነጋዴው የንግድ ሥራውን በማናቸውም ምክንያት የተወ እንደሆነ፣
   ለ) ነጋዴው ንግዱን መነገድ እንደማይችል አስተዳደራዊ እርምጃ ሲወሰድበት ወይም በፍርድ ቤት ሲወሰን፣
   ሐ) ነጋዴው ሀሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ አቅርቦ የተመዘገበ እንደሆነ፣
   መ) ነጋዴው ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ፣

   መዝጋቢው መሥሪያ ቤት የንግድ ምዝገባውን ሊሰርዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) መሠረት የንግድ ምዝገባው የተሰረዘበት ነጋዴ በማንኛውም ጊዜ ያንኑ የንግድ ምዝገባ መልሶ ማስመዝገብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) መሠረት የንግድ ምዝገባ ስረዛ ከመደረጉ በፊት መዝጋቢው መስሪያ ቤት ነጋዴው መቃወሚያ ሐሳብ ካለው እንዲያቀርብ በተመዘገበው አድራሻው በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ነጋዴው ደብዳቤው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ መቃወሚያ ሀሳብ ካላቀረበ ወይም ነጋዴው ያቀረበው መቃወሚያ ሀሳብ የሕግ መሠረት የሌለው ከሆነ ወይም በተመዘገበው አድራሻ ሊገኝ ካልቻለ የንግድ ምዝገባው ይሰረዛል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ) ወይም (መ) ምክንያት የንግድ ምዝገባ የተሰረዘበት ነጋዴ እንደገና እንዳይመዘገብ የሚከለከል አስተዳደራዊ ቅጣት

---

[10] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(8) መሰረት ተሰረዘ፡፡

[11] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(10) መሰረት አንቀጽ 11 (1) (ሠ)፣ (2) እና (8) ተሰርዘው ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (7) ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 6 ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ ከሌለ በስተቀር የተሰረዘውን የንግድ ምዝገባ እንደገና ሊመዘገብ የሚችለው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡

6. ማንኛውም ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ምዝገባ ስረዛ የሚፀናው አግባብ ያለው ባለስልጣን ስረዛውን ተደራሽ በሆነ የኢንፎርሜሽን መገናኛ ቴክኖሎጂ አውታርን ተጠቅሞ ካሳወቀበት ከአንድ ወር በኋላ ነው፡፡ የግለሰብ ነጋዴ በሆነ ጊዜ ስረዛው ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤[12]

## 12.ምትክ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ነጋዴ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ በተመለከተው መስፈርት መሠረት ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፡፡

## 13.የመረጃ ቅጅ ስለመስጠት

1. በንግድ መዝገብ ውስጥ የሰፈረው ዝርዝር ቅጅ፣ ከመዝገቡ የሚውጣጣ ማስረጃ፣ ተፈላጊው ማስረጃ ዝርዝር መዝገቡ ላይ አለመኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም የንግድ ምዝገባው የተሰረዘ ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን ለመዝጋቢው አካል በጽሁፍ ማመልከት አለበት፡፡
2. መዝጋቢው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለቀረበ ማመልከቻ አግባብ ያለውን ክፍያ በማስከፈል መሰጠት ያለበትን መረጃ ወዲያውኑ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለድርጅትና ንግድ ስሞች[13]

## 14.ስለደርጅት ስም ምዝገባ[14]

1. የግለሰብ ነጋዴ የሕግ ስም የግለሰቡን ስም የአባቱን እና የአያቱን ስም የሚያካትት ይሆናል፤ ስሙ ቀደም ብሎ በሌላ ተመሳሳይ ስም ባለው ግለሰብ የተመዘገበ ሲሆን፣ የቅድመ አያትን ስም በመጨመር፣ እስከ ቅድመ አያት ስም ድረስ በሌላ ተመሳሳይ ስም ባለው ግለሰብ የተያዘ ሲሆን፣ የእናት ስም ተጨምሮ ይመዘገባል፤ የእናት ስም

[12] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(12) ተሻሻለ፡፡
[13] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(13) ተሻሻለ፡፡
[14] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(13) ተሻሻለ፡፡

በሌላ ተመሳሳይ ስም ባለው ግለሰብ የተያዘ ከሆነ ሌላ መለያ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

2. የህብረት የሽርክና ማህበር ስም የንግድ ሥራ ዘርፉን በማመልከት በንግድ ሕጉ መሠረት ይሰየማል፡፡
3. ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት ሽርክና ማህበር ስም የንግድ ሥራ ዘርፉን በማመልከት በንግድ ሕጉ መሠረት ይሰየማል፡፡
4. የአክሲዮን ማህበር ስም የንግድ ሥራ ዘርፉን በማመልከት በንግድ ሕጉ መሠረት በአባላቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡
5. የኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም የንግድ ሥራ ዘርፉን በማመልከት በንግድ ሕጉ መሠረት በአባላቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡

15.<u>ስለንግድ ስም ምዝገባ</u>[15]

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባ በሚያደርግበት ቦታ የንግድ ስሙን ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ በሚያወጣበት ቦታ የንግድ ስሙን ማስመዝገብ አለበት፡፡
3. የንግድ ድርጅት ስም በዚህ አዋጅ ለንግድ ስም የተደነገጉትን መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ በንግድ ስምነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡
4. አመልካቹ የውጭ አገር የንግድ ማህበር ከሆነ በተመዘገበበት አገር የተረጋገጠ የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ ከማመልከቻው ጋር ለመዝጋቢው መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡
5. የንግድ ድርጅት ስም በንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ የሚመዘገብ ሲሆን የንግድ ስም የራሱ የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ በንግድ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ላይ የሚመዘገብ ነው፡፡
6. የንግድ ስም ምዝገባ ማመልከቻ ለዚሁ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት እና በደንቡ የተገለፁትን ሰነዶች በማካተት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

[15] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(13) ተሻሻለ፡፡

**16.<u>የንግድ ስም እንዳይመዘገብ የሚያደርጉ ምክንያቶች</u>**

1. መዝጋቢው አካል በሚከተሉት ምክንያቶች የንግድ ስም እንዳይመዘገብ ያደርጋል፡-[16]
   ሀ) እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ፣ ሌላ የንግድ ስም ወይም የንግድ ድርጅት ስም ጋር አንድ ዓይነት ወይም በሚያሳስት ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ፤
   ለ) እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ከመንግሥት ተቋማት፣ ከሃይማኖት ተቋማት፤ ከፖለቲካ ፓርቲ፣ ከብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች፣ ነገዶች እና ጎሳዎች መጠሪያ፣ ከሌላ ማንኛውም ዓይነት ማህበር፣ ከመንግሥታት ህብረት ድርጅቶች ተቋማት ወይም ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ስሞች ጋር አንድ ዓይነት ወይም በሚያሳስት ሁኔታ ተመሳሳይ ከሆነ፤
   ሐ) እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም የንግዱን ዘርፍ ዓይነት የማያመለክት ከሆነ፤
   መ) እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ብሎ ያልተመዘገበ ቢሆንም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቅ ወይም ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ሆኖ ስሙን ለመጠቀም የተሰጠ ፈቃድ የሌለ ከሆነ፤
   ሠ) እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ከመልካም ፀባይ ወይም ሥነ- ምግባር ጋር ተቃራኒ መሆኑ ሲረጋገጥ፡፡
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ነጋዴው በንግድ ስምነት ለረዥም ጊዜ ሲታወቅበት የኖረ ሆኖ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት የንግድ ስሙ እንዳይመዘገብ የተከለከለ እና ያልተመዘገበ ከሆነ አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚወስነው መሠረት ሊመዘገብ ይችላል፤
3. ለዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ዝርዝር አፈፃፀም ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ስለንግድ ስም የተገለፁት ለድርጅት ስምም ያገለግላሉ፤[17]

**17.<u>የንግድ ስም በንግድ ስም መዝገብ የመግባት ውጤት</u>**

1. የንግድ ስም በመዝገብ መግባት የንግድ ስሙን ለመጠቀም መብት የሚሰጥ ተቀዳሚ ማስረጃ ነው፡፡

---

[16] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(14) መሰረት የአዋጁ አንቀጽ 16 (1) (ሐ) ተሰርዞ፤ ከፊደል ተራ (መ) እስከ (ረ) ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከፊደል ተራ (ሐ) እስከ (ሠ) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

[17] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(15) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

2. አንድ የንግድ ድርጅት ስም ወይም የንግድ ስም ቀድሞ የተመዘገበ መሆኑ ብቻ በንግድ ሥራ ጠባዩ ፈፅሞ ለማይመሳሰል የንግድ ሥራ እንዳይመዘገብ ሊከለከል አይችልም፡፡

18.<u>የንግድ ስም ምዝገባ ስረዛ</u>

1. መዝጋቢው መሥሪያ ቤት የንግድ ስም ምዝገባን በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፦

   ሀ) የንግድ ስሙን ያስመዘገበው ነጋዴ እንዲሰረዝ ሲጠይቅ፤

   ለ) የንግድ ስሙ በማታለል ወይም በስህተት የተመዘገበ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

   ሐ) የነጋዴው የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ በዚህ አዋጅ መሠረት ሲሰረዝ፤

   መ) የንግድ ስም ምዝገባው በፍርድ ቤት ውድቅ መሆኑ ሲወሰን፣

   ሠ) በዚህ አዋጅ መሠረት በንግድ ስሙ ላይ ለውጥ ሲደረግበት፤

   ረ) የንግድ ማህበሩ ሕጋዊ ሰውነቱን ሲያጣ ወይም ሲፈርስ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) መሠረት የንግድ ስም ስረዛ ከመደረጉ በፊት መዝጋቢው መስሪያ ቤት ነጋዴው መቃወሚያ ሐሳብ ካለው እንዲያቀርብ በተመዘገበው አድራሻው በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. ነጋዴው ደብዳቤው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ መቃወሚያ ሀሳብ ካላቀረበ ወይም ነጋዴው ያቀረበው መቃወሚያ ሀሳብ የሕግ መሠረት የሌለው ከሆነ ወይም በተመዘገበው አድራሻ ሊገኝ ካልቻለ የንግድ ስሙ ከመዝገብ ይሰረዛል፡፡
4. የንግድ ስም መዝገቡ በሚሰረዝበት ጊዜ የቀድሞው የንግድ ስም ተጠቃሚ የስረዛ ማስረጃ እንዲሰጠው ካመለከተ መዝጋቢው መስሪያ ቤት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ይሰጠዋል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) መሰረት የንግድ ስም ምዝገባው የተሰረዘበት ነጋዴ በማንኛውም ጊዜ ያንኑ የንግድ ስም መልሶ ማስመዝገብ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) ወይም (ሐ) መሠረት የንግድ ስም ምዝገባ የተሰረዘበት ነጋዴ እንደገና እንዳይመዘገብ የሚከለከል አስተዳደራዊ ቅጣት ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ ከሌለ በስተቀር የተሰረዘውን የንግድ ስም ምዝገባ እንደገና

ሊመዘገብ የሚችለው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

19.<u>የንግድ ስም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ስለማድረግ</u>

ቀደም ብሎ ያስመዘገበውን የንግድ ስም ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ማመልከቻ ለሚያቀርብ ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

20.<u>ምትክ የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

ምትክ የንግድ ስም ምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከቻ ለሚያቀርብ ማንኛውም ነጋዴ በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣው ደንብ ስለምትክ የንግድ ምዝገባ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለንግድ ሥራ ፈቃድ

21.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን</u>

1. በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎችና በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ከተደነገገው በስተቀር አግባብ ያለው ባለሥልጣን የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ሚኒስቴሩ በመመሪያ በሚዘረዝረው የኢትዮጵያ ንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደቦች መሰረት ይሆናል፡፡
3. አግባብ ያለዉ ባለሥልጣን እና ሌሎች ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸዉ አካላት የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲሰጡ በፈቃዱ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደቡን ስያሜና መለያ ቁጥር በግልጽ መጥቀስ ይኖርባቸዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አካላት በዚህ አዋጅ እና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ለሚከተሉት የንግድ ሥራዎች የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣሉ፡-
   ሀ) የማዕድን ፍለጋ እና ልማት ሥራዎች፤
   ለ) የውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ አገልግሎትን ሳይጨምር በልዩ ልዩ ውሃ ነክ አገልግሎት ሥራዎች፤
   ሐ) የባንክ፣ የመድን እና የማይክሮ ፋይናንስ ንግድ ሥራዎች፤
   መ) የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቶች ሥራ እና ሌሎች የበረራ ሥራዎች፤

ሠ) የሬድዮ አክቲቭ ቁሶችና የጨረር አመንጪ መሣሪያዎችን የመጠቀም የንግድ ሥራ፤

ረ) የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት፤

ሰ) የኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ ወይም መሸጥ የንግድ ሥራ፤

ሸ) የጦርና ተኩስ መሣሪያዎች ጥገና፣ ዕድሳትና የፈንጂዎች ሽያጭ ሥራ፤

ቀ) የባህርና የሀገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት የንግድ ሥራ፤

በ) የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ንግድ ሥራ፤

ተ) የብሮድካስቲንግ አገልግሎት ሥራ፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን ያላቸው የመንግሥት አካላት፣ የንግድ ፈቃድ ሲሰጡ እና ሲያድሱ በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

6. በአዋጁ ወይም በሌሎች ሕጎች ወይም በውክልና ስልጣን የንግድ ሥራ ፈቃድ ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላት የንግድ ሥራ ፈቃድ መረጃዎችን ሚኒስቴሩ ለዚህ ዓላማ ባዘጋጀው የመረጃ ቋት የንግድ ሥራ ፈቃዱ እንደተከናወነ ማስተላለፍ አለባቸው፤[18]

22.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማውጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ሥራ መሥራት አይችልም፡፡

2. በዚህ አዋጅ መሠረት የንግድ ሥራ ለመስራት የፀና የንግድ ሥራ ፍቃድ ያወጣ ሰው ለተመሳሳይ የንግድ ሥራ ለሚከፍተው ቅርንጫፍ ተጨማሪ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያወጣ አይገደድም፡፡

3. የማምረት የንግድ ሥራ ፍቃድ ያለው ነጋዴ ያመረታቸውን ምርቶች ብቻ በሚያመርትበት አድራሻ ወይም በሌላ ባስመዘገበበት አድራሻ በጅምላ ለመሸጥ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጣ አይገደድም፡፡

4. የማምረት የንግድ ሥራ ፍቃድ ያለው ነጋዴ ያመረታቸውን ምርቶች በችርቻሮ መነገድ አይችልም፤ ሆኖም በልዩ ሁኔታ በችርቻሮ የሚነግድባቸውን ምርቶች ዓይነት በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

---

[18] በ25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(16) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

5. ማንኛውም የአስመጪነት የንግድ ፈቃድ ያለው ነጋዴ ያስመጣቸውን ምርቶች ለአስመጪነት የንግድ ፈቃዱን ሲያወጣ ባስመዘገበበት አድራሻ በጅምላ ለመሸጥ ተጨማሪ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያወጣ አይገደድም፡፡
6. ማንኛውም የአስመጪነት ንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው ነጋዴ ያስመጣቸውን ምርቶች በችርቻሮ መነገድ አይችልም፤ ሆኖም ከንግዱ ባሕሪይ እና ከአገር ጥቅም አንጻር በልዩ ሁኔታ በችርቻሮ የሚነግድባቸውን ምርቶች በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

23.**<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

በንግድ ሥራ መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የተመለከቱትን አስፈላጊ ሰነዶች በማያያዝ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማመልከት ይኖርበታል፡፡

24.**<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት</u>**

1. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡት ደንብ እና መመሪያዎች መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ሊሟሉ የሚገባቸው መሥፈርቶች መሟላታቸውንና ሊሰራ ያቀደው የንግድ ሥራ በሕግ ያልተከለከለ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ማመልከቻው በዚህ አዋጅ እና በደንቡ ወይም በመመሪያዎች መሠረት ተሟልቶ ባለመቅረቡ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን አግባብ ያለው ባለስልጣን ሲያረጋግጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. በንግድ ስራ ተሰማርቶ የነበረ ግለሰብ ነጋዴ ወራሾች እና/ወይም የትዳር ጓደኛ በንግድ ሥራው ለመቀጠል የንግድ ማህበር ለማቋቋም ያልፈለጉ ከሆነ ከወራሾቹ አንዱ ወይም የትዳር ጓደኛው በሌሎቹ ወራሾቹ እና/ወይም የትዳር ጓደኛው በሚሰጠው ውክልና በዚህ አዋጅ ስለ ንግድ ምዝገባ በተደነገገው መሠረት በንግድ መዝገብ ከተመዘገበ በኋላ በወኪሉ ስም የንግድ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

25.**<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ መብት</u>**

ማንኛውም የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

1. ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንብና መመሪያ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ንግድ ነክ ድንጋጌዎችን በማክበር በተሰጠው የንግድ ፈቃድ መስክ ወሰን የንግድ ሥራዎች የማካሄድ፤
2. ለተመሳሳይ የንግድ ሥራ ለሚከፍተው ቅርንጫፍ ተጨማሪ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያወጣ ያለመገደድ፤
3. ስለ ንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መረጃ የማግኘት፤
4. በዚህ አዋጅ መሠረት የንግድ ምዝገባን፣ የንግድ ስምን እና የንግድ ፈቃድን የመለወጥና የማሻሻል፤
5. በአዋጁ፣ አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንብ እና በመመሪያው የተፈቀዱ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን፡፡

## 26.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ ግዴታዎች</u>

የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፦

1. የንግድ ፈቃድ የተሰጠባቸውን የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን በአንድ ሥፍራ ወይም ግቢ ውስጥ አጣምሮ መሥራት በተጠቃሚው ሕዝብ ጤንነትና ደህንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ እነዚህን ሥራዎች በተለያዩ ሥፍራዎች ወይም ግቢዎች በተናጠል የማካሄድ፤
2. የንግድ ዕቃዎቹንና የአገልግሎቶቹን የዋጋ ዝርዝር በንግድ ቤቱ በግልጽ ሥፍራ በሚታይ ቦታ የማመልከት ወይም በንግድ ዕቃዎች ላይ የመለጠፍ፤
3. የንግድ ሥራው ጠባይ የሚጠይቃቸውን ግዴታዎች የማክበር፣ ደረጃዎችን የማሟላት እና የመሥራት፤
4. የንግድ ሥራ ፍቃዱን በንግድ ቤቱ ውስጥ በግልጽ በሚታይ ቦታ የማስቀመጥ፣ ወይም የንግድ ቤቱ ቅርንጫፍ ከሆነ የመዝጋቢው አካል ማህተም የተደረገበት የንግድ ሥራ ፍቃድ ፎቶ ኮፒ በንግድ ቤቱ ውስጥ በግልጽ በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ፤
5. የንግድ ፈቃዱን ለሌላ ለማንኛውም ሰው እንዲገለገልበት ወይም በመያዣነት እንዲይዘው ወይም እንዲያከራየው አሳልፎ ያለመስጠት፤
6. በአስተዳደራዊ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የንግድ ድርጅቱ እንዲፈርስ ወይም የግለሰብ ነጋዴ ንግዱን እንዳያካሂድ ሲወሰንበት የተሰጠውን የንግድ ሥራ ፈቃድ በሥራ ላይ ያለማዋል፤

7. የአድራሻ ለውጥ ሲያደርግ ለውጡን በአንድ ወር ጊዜ ውሰጥ ለመዝጋቢው መሥሪያ ቤት የማሳወቅ፤
8. አክስዮን ማህበር እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሆነ በየበጀት ዓመቱ በኦዲተር ሂሳቡን የማስመርመር እና ሪፖርት የማቅረብ፤
9. ስለንግዱ በሚመለከታቸው አካላት የሚጠየቀውን ማንኛውንም መረጃ  የመስጠት፤
10. በተመሳሳይ ደረጃ ግብይት ያለመፈፀም፤ እና
11. አግባብ ባለው ባለስልጣን የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን እና በሕግ የተደነገጉ ሌሎች ግዴታዎችን የማክበር፡፡

27. **የንግድ ሥራ ፈቃድን ስለማሳደስ** [19]

1. የንግድ ሥራ ፍቃድ በየበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ታህሳስ 30 ቀን ወይም ካስመዘገበው የበጀት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 6 ወራት ዉስጥ መታደስ አለበት፡፡
2. ኃላፊነታቸው የተወሰነ የንግድ ማህበራት ካስመዘገቡት ካፒታል ሦስት አራተኛውን እና ከዚያም በላይ የከሰሩ ከሆነ ካፒታላቸው ከአንድ አራተኛ በላይ እንዲሆን በማድረግ ፍቃዳቸውን ማሳደስ ይችላሉ፤
3. የንግድ ሥራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚፈልግ ነጋዴ ለዕድሳት የተዘጋጀውን ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ከተመለከቱት ሰነዶች ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው የፍቃድ ማሳደሻ ጊዜ ውስጥ ነጋዴው የንግድ ፈቃዱን ካላሳደሰ ከጥር 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ላለው ጊዜ ከፍቃድ ማሳደሻው በተጨማሪ ፈቃድ ማሳደሱ ለዘገየበት ለጥር ወር ብር 2,500 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) እና ለሚቀጥለው እያንዳንዱ ወር ብር 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ቅጣት በመክፈል ፈቃዱን ያሳድሳል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) በተደነገገው መሠረት በቅጣት የማሳደሻ ጊዜ ውስጥ ያልታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ አግባብ ባለው ባለስልጣን ይሰረዛል፡፡
6. በቅጣት የማደሻ ጊዜ ውስጥ ያላደሰ ማንኛውም ነጋዴ በቅጣት የማደሻው ጊዜ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብር 20,000 በመክፈል ማደስ ይችላል፤

[19] 25/77(2011) አ. 1150 አንቀፅ 2(17) መሰረት ንዑስ አንቀፅ 2፣ 6 እና 7 ተሻሻሉ፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ያልታደሰ ንግድ ፈቃድ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ያንኑ ፈቃድ መልሶ ማውጣት የሚቻለው በቅጣት የማሳደሻ ጊዜው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ያለምንም ተጨማሪ ቅጣት እንደአዲስ መውሰድ ይችላል፣

28.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወቅቱን ጠብቆ በዚህ አዋጅ መሠረት ከታደሰ እና እስካልተሰረዘ ድረስ የፀና ይሆናል፡፡
2. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 27(6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተሰጠበት ወይም የታደሰበት የበጀት ዓመት ካበቃ በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተገቢው ክፍያ ተፈጽሞ ያልታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ የፀና አይሆንም፡፡

29.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድን ስለማገድ</u>

1. የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ፦
   - ሀ) የንግድ ሥራውን የጤናና የጽዳት አጠባበቅ፣ የአካባቢ እንክብካቤ፣ የአደጋ መከላከያና የንግድ ዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን የጥራት ደረጃ ካጓደለ፣
   - ለ) በዚህ አዋጅ የነጋዴ ግዴታዎች በሚል የተቀመጡትን የጣሰ ከሆነ፣
   - ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚጠይቃቸውን መረጃዎች በትክክልና በወቅቱ ያላቀረበ ከሆነ፣
   - መ) የተሰጠው ወይም የታደሰው የንግድ ሥራ ፈቃድ በሀሰተኛ ሰነድ ወይም ማስረጃ ተደግፎ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ወይም
   - ሠ) ፈቃዱን ከተሰጠበት ዓላማ ውጭ ሲገለገልበት ከተገኘ፣ ወይም
   - ረ) ባስመዘገበዉ የንግድ ፈቃድ አድራሻ ያልተገኘ ከሆነ፣
   - ሰ) የንግድ ሕጉን፣ የአዋጁን፣ አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ የደንብና የመመሪያ ድንጋጌዎችን የጣሰ ከሆነ፣

   አግባብ ያለው ባለሥልጣን የንግድ ሥራ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡
2. የንግድ ሕጉን፣ የአዋጁን፣ በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንብና የመመሪያዎችን ድንጋጌ በመጣስ የንግድ ፈቃዱ የታገደ ከሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት አግባብ ያለው አካል የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የንግድ ፈቃድ ሲታገድ የንግድ ድርጅቱ ወዲያውኑ አግባብ ባለው አካል ይታሸጋል፡፡

3. በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ሲታገድ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፈቃዱ የታገደበትን ምክንያት እና አሳማኝ በሆነ ጊዜ ውስጥ ጉድለቶቹን እንዲያስተካክል ሊወስድ ስለሚገባው እርምጃ ለባለፈቃዱ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡
4. ነጋዴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ካስተካከለ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በንግድ ሥራ ፍቃዱ ላይ የተጣለው ዕግድ ተነስቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
5. የብቃት አረጋጋጭ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫዎችን ሲያግዱና ሲያሳውቁ ያለምንም ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ የንግድ ሥራ ፈቃዱ ይታገዳል፡፡

## 30.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>

1. የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ፦
   ሀ) የንግድ ሥራውን በራሱ ፍቃድ የተወ እንደሆነ፣
   ለ) የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ወይም የታደሰው ፈቃድ በሀሰተኛ ሰነድ ወይም ማስረጃ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
   ሐ) የንግድ ሥራ ፈቃዱን ፈቃዱ ከተሰጠበት ዓላማ ዉጭ ሲገለገልበት ከተገኘ፣
   መ) በዚህ አዋጅ መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለንግድ ፈቃዱ ዕገዳ ምክንያት የሆኑትን ጉድለቶች ያላስተካከለ ከሆነ፣
   ሠ) የኪሳራ ውሳኔ የተወሰነበት ከሆነ፣
   ረ) በዚህ አዋጅ መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃዱን ያላሳደሰ ከሆነ፣ ወይም
   ሰ) የንግድ ምዝገባው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰረዘበት ከሆነ
   አግባብ ያለው ባለሥልጣን የንግድ ስራ ፈቃዱን ይሰርዛል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) መሠረት በራሱ ፍቃድ የንግድ ሥራውን የተወ እና ፈቃዱን በማሳደሻ ጊዜ ውስጥ የመለሰ ነጋዴ ያንኑ ፈቃድ በማንኛውም ጊዜ መልሶ መውሰድ ይችላል፤ ሆኖም የንግድ ሥራ ፍቃዱን በንግድ ሥራ ፈቃድ ያለቅጣት ማሳደሻ ጊዜ ውስጥ ያልመለሰ ከሆነ ያንኑ የንግድ ሥራ ፍቃድ መልሶ መውሰድ የሚችለው የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለቅጣት የማደሻ ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡
3. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) ፣ (ሐ) እና (መ) በተገለፁት ምክንያቶች ፈቃዱ እንዲሰረዝ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እንደ

አስፈላጊነቱ ነጋዴው ባስመዘገበው አድራሻ በደብዳቤ ተጠርቶ መቃወሚያ ሀሳብ ካለው በጽሁፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ነጋዴው ያቀረበው መቃወሚያ ሀሳብ በቂ ሆኖ ካልተገኘ ወይም ደብዳቤው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ መቃወሚያ ሀሳቡን በጽሁፍ ካልሰጠ ፈቃዱ ይሰረዛል፤ በዚህ ሁኔታ ፍቃዱ የተሰረዘበት ነጋዴ ያንኑ የንግድ ፍቃድ መልሶ ማውጣት የሚችለው ከሁለት ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

4. የንግድ ሥራውን በፈቃዱ የተወ ነጋዴ ያለቅጣት የፈቃድ ማዳሻ ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ካልመለሰ፣ ባሰረዘው የንግድ ሥራ ፍቃድ መስጫ ውስጥ በተዘረዘሩት የንግድ ሥራ ዓይነቶች ፍቃድ ማውጣት የሚችለው ያለቅጣት የፈቃድ ማሳደሻ ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው፤
5. የንግድ ፈቃዱን ተመላሽ የሚያደርግ ወይም የተሰረዘበት ነጋዴ ያንኑ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደ አዲስ ለማውጣት ሲመጣ ተመላሽ በተደረገው ወይም በተሰረዘው የንግድ ሥራ ፈቃድ ለሰራበት ጊዜ የግብር ክፍያ ስለመፈጸሙ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፤
6. የብቃት አረጋጋጭ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫዎችን ሲሰርዙና ሲያሳውቁ ያለምንም ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ የንግድ ሥራ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

31.<u>ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማግኘት</u>

1. የንግድ ሥራ ፍቃድ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ነጋዴ በአዋጁ መሠረት በወጣ ደንብ ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች በማሟላት ማመልከቻ ሲያቀርብ ምትክ የንግድ ሥራ ፍቃድ ምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፡፡
2. ፈቃዱ የተበላሸበት ነጋዴ ምትክ እንዲሰጠው ሲያመለከት የተበላሸውን የንግድ ፈቃድ ይመልሳል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ የቀረበለት አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹ የንግድ ሥራ ፍቃዱ ስለመጥፋቱ ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ወይም ፖሊስ እንዲያቀርብ አድርጎ በደንቡ የተመለከተውን ክፍያ በማስፈጸም ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

32.<u>የንግድ መደብር ሲተላለፍ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ</u>

1. የንግድ መደብር ለሌላ ሰው በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስ ወይም በመሰል ማንኛውም ሁኔታ ሊተላለፍ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የንግድ መደብር ማስተላለፍ የሚችለው በነጋዴው ወጪ አገር አቀፍ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ታትሞ ወጥቶ ተቃዋሚ ካልቀረበ ወይም የዕግድ ትዕዛዝ ካልወጣበት ከአንድ ወር በኋላ ይሆናል፡፡
3. የንግድ መደብሩ ከመተላለፉ በፊት የቀድሞዉ ባለፈቃድ በንግድ ሥራ ፈቃዱ ለሰራበት ጊዜ የግብር ክሊራንስ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡
4. አግባብ ያለው ባለሥልጣን አስፈላጊ መረጃዎችን በማጣራት እና የቀድሞውን የንግድ ሥራ ፍቃድ ተመላሽ በማድረግ የንግድ መደብር ለተላለፈለት ሰው ተመሳሳይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
5. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ በተገለፀው መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ምክንያቱን ገልፆ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

33.<u>ስለንግድ እንደራሴነት</u>

1. የንግድ እንደራሴ ሆኖ ለመሰራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በሚኒስቴሩ በንግድ መዝገብ ተመዝግቦ የንግድ እንደራሴነት ልዩ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. የንግድ እንደራሴነት ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በአዋጁ መሠረት በወጣ ደንብ ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች በማሟላት ከማመልከቻው ጋር በማያያዝ ማቅረብ አለበት፡፡
3. የንግድ እንደራሴነት ልዩ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፣

   ሀ/ የወካዩን ምርቶችና አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የማስተዋወቅ፣

   ለ/ ወደፊት ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ እንዲችል የሚረዱ የገበያ ጥናትና የንግድ የማስፋፋት ሥራ የማካሄድ፤ እና

   ሐ/ የኢትዮጵያን የውጭ ንግድ ምርቶችን ወካይ ድርጅቱ በሚገኝበት አገር የማስተዋወቅ ተግባራት የማከናወን መብት ይኖረዋል፡፡

4. የንግድ እንደራሴ በወካዩ ስም ለደንበኞቹ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ማቅረብ ወይም ከደንበኞቹ ጋር ውል መዋዋል አይችልም፡፡
5. የንግድ እንደራሴ ከወከለው ነጋዴ ውጭ ለሌሎች ነጋዴዎች በማንኛውም መልኩ መሥራት አይችልም፡፡
6. ማንኛውም የንግድ እንደራሴነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በአዋጁ መሠረት በወጣ ደንብ ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች በማሟላት የንግድ እንደራሴነት ልዩ ምስክር ወረቀቱን ማሳደስ አለበት፡፡
7. በዚህ አዋጅ የንግድ ሥራ ፈቃድ ምትክ ስለማግኘት፣ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ለንግድ እንደራሴነትም እንደአግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

34.<u>ስለ ሆልዲንግ ኩባንያ</u>

1. በንግድ ሕጉ መሠረት ሆልዲንግ ኩባንያ መመስረት የሚፈልጉ ኃላፊነታቸዉ የተወሰነ የንግድ ማህበራት የንግድ ዉድድርን በማያዛባ ሁኔታ መወደንና በሚኒስቴሩ ዘንድ ቀርበው መመዝገብ ይኖርባቸል፡፡
2. ሆልደር ኩባንያው ከሶስተኛ ወገኖች ለሚመነጩ ማናቸውም ኃላፊነቶች በአንድነት እና በተናጠል ከቡድኑ ኩባንያ አባላት ጋር ኃላፊ ነዉ፡፡
3. ሆልደሩ ኩባንያ የቡድን አባላትን ጨምሮ የተጠቃለለ ዓመታዊ ሂሳብ እና ሌሎች መረጃዎችን መያዝ አለበት፤ አግባብ ያለዉ ባለስልጣን ሲጠይቅም ማቅረብ አለበት፡፡
4. የሆልዲንግ ኩባንያው አባላት ከቡድኑ ሲወጡ ወይም ወደ ቡድኑ ሲቀላቀሉ ለመዝጋቢዉ አካል በማሳወቅ አስቀድሞ የተሰጠዉ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት መለወጥ አለበት፡፡
5. ሆልደር የሆነዉ ኩባንያ የራሱንና የቡድን አባል ማህበራትን ዝርዝር መረጃዎች ይዞ በመቅረብ በአዋጁ መሠረት በወጣ ደንብ የሚወሰኑትን መስፈርቶች በማሟላት የመመዝገብ እና የሆልዲንግ ኩባንያ ምዝገባ ልዩ የምስክር ወረቀት የማዉጣት ግዴታ አለበት፡፡
6. የሆልዲንግ ኩባንያዎች የምዝገባ መስፈርት በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

**35.ስለ ጠረፍ ንግድ**

1. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፍቃድ በሚኒስቴሩ ወይም ሚኒስቴሩ ውክልና በሚሰጣቸው አካላት ይሰጣል፡፡
2. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፍቃድ በሚኒስቴሩ ወይም በጠረፍ ንግድ ስምምነቶች ወይም በተናጠል ውሳኔ በተወሰኑ ምርቶች ላይ ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፡፡
3. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ፍቃድ አሰጣጥ መስፈርት በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

**36.ስለ ውጭ ንግድ ትርዒት**

የውጭ የንግድ ትርዒት ይሁንታ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**37.ስለ ፍራንቻይዝ ምዝገባ**

1. የፍራንቻይዝ ምዝገባ መስፈርት በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ በተወሰነው መሠረት ይፈፀማል፡፡
2. ፍራንቻይዚው በፍራንቻይዘሩ ደረጃ መሠረት መስራት አለበት፡፡
3. ተገልጋዮች ከፍራንቻይዘሩ የሚያገኙትን ዓይነት ምርት ወይም አገልግሎት ከፍራንቻይዚው ማግኘት አለባቸው፡፡

**38. ስለ ብቸኛ አስመጭና አከፋፋይ**

1. ብቸኛ አስመጭ ወይም አከፋፋይ ሆኖ መስራት የተከለከለ ነዉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከሥራው ባሕሪ እና አገራዊ ጥቅም አንጻር ብቸኛ አስመጭ ወይም አከፋፋይ ሆኖ መሥራት የሚቻልባቸው የንግድ ሥራ መስኮችን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**39.የንግድ ወኪል ተግባራት**

የንግድ ወኪል የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የወካዩን ምርት ለገበያ የማስተወወቅ፤
2. የሀገራችንን ምርቶች ለዉጭ ሀገር ገበያ የማስተዋወቅ፤
3. ዓለም አቀፍ ጨረታ ላይ በሕግ ተወክሎ በወካይ ምትክ ሆኖ በጨረታ ላይ የመሳተፍና አፈጻጸሙን የመከታተል፤
4. በወካይ ነጋዴ ስም ውል የመዋዋል፡፡

## 40.ስለዉጭ ሀገር የንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች

1. የዉጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤቶች የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን ሊከፍቱ የሚችሉት በተመሰረቱበት አገር የተሰጣቸውን የሕጋዊ ሰውነት ማስረጃ፣ መተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ጽሁፍ እንዲሁም የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ዝርዝር መግለጫ በማቅረብ በሚኒስቴሩ ተፈቅዶ ሲመዘገቡ ይሆናል፡፡ሆኖም ከውጭ ሃገር በኢንቨስት መንት የገቡ የራሳቸውን ማህበር ሲያቋቁሙ በሃገር አቀፍ ደረጃ ኢንቨስትመንትን ለማስተዳደር በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡
2. የዉጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሀገር ዉስጥ ያሉ የንግድና ዘርፍ ምክር ቤቶች ከሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት ጋር ተመሳሳይ ተግባራትን ብቻ ማከናወን ይችላሉ፡፡
3. የዉጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሀገር ዉስጥ ከተቋቋሙ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ጋር በትብብርና በጋራ መደጋገፍ ይሰራሉ፡፡

## 41.ስለ ንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ

የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው በተመሳሳይ ወቅት ከአንድ በላይ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ መሆን አይችልም፡፡

## 42.ስለ ብቃት ማረጋገጫ

1. ይህን አዋጅ ተከትሎ በወጣው ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ለሚያስፈልጋቸው የንግድ ሥራዎች ሊሟሉ የሚገባቸውን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች አግባብነት ያላቸው የሴክተር መስሪያ ቤቶች በመመሪያ ይወስናሉ፡፡
2. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ እና መመሪያ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸዉ የመንግሥት አካላት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣሉ፡፡
3. የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠበት አድራሻ ወይም መስፈርት ለዉጥ የተደረገ ከሆነ በአዲሱ አድራሻ ወይም መስፈርት መሠረት ተደርጎ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፡፡
4. የብቃት ማረጋገጫ እንደሚያስፈልጋቸው በመመሪያ ለተወሰኑ የንግድ ሥራዎች ማንኛውም ሰው የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለንግድ ሥራ ፈቃድ በቅድመ ሁኔታነት የማይጠየቅባቸውን የንግድ ሥራ መደቦች ይወስናል፡፡
6. ሴክተር መሥሪያ ቤቶች የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ሲያዘጋጁ በዘርፉ የተሰማሩ የነጋዴዎች አደረጃጀቶችን ማማከር አለባቸው፡፡

43.**ወጪና ገቢ ዕቃዎችን ስለመወሰን**

1. ሚኒስቴሩ ለብሔራዊ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚኒስትሮች ምክር ቤትን በማስፈቀድ አንዳንድ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ክልከላ ለመጣል ይችላል፡፡
2. የአስመጪነት ወይም የላኪነት ንግድ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ከውጭ ሀገር ዕቃ እንዲያስገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር ዕቃ እንዲልኩ በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሚኒስቴሩ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

44.**አገልግሎቶችና መለዋወጫዎች አቅርቦትና ቁጥጥር**

1. የእርሻ፣ የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን በመኪና ኃይል የሚሰሩ ዕቃዎችንና ተሽከርካሪዎችን ከውጭ አገር አስመጥቶ የሚሸጥ ነጋዴ ወይም ወኪል የእነዚሁ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እስከሚያቆምበት ጊዜ ድረስ፦
   ሀ) መሥራታቸው ካላቆመ ወይም ከሌላ ምንጭ በበቂ ሁኔታ የሚገኙ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ጊዜ ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ከሚወስነው አነስተኛ የክምችት መጠን ባላነሰ ሁኔታ መለዋወጫዎችን በመደብሩ ውስጥ ይይዛል፣ ለሽያጭም ያቀርባል፤
   ለ) በማናቸውም ጊዜ ተገቢ በሆነ ዋጋ የተሟላ የማደስ አገልግሎት ለገዥዎች ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ባልፈፀመ ነጋዴ ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፣ በወንጀልም ይቀጣል፡፡

45.**ስለ ተቆጣጣሪ**

1. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚመድባቸው ተቆጣጣሪዎች ወደ ንግድ ድርጅቶች ለቁጥጥር ተግባር ሲሄዱ ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ እና ቁጥጥር ለማድረግ

አግባብ ካለው ባለስልጣን የተሰጠ የተቆጣጣሪነት ልዩ መታወቂያ ማሳየት አለባቸው፡፡

2. ተቆጣጣሪዎች ወደ ንግድ መደብሮች ለቁጥጥር ተግባር መሄድ ያለባቸው በመንግስት የሥራ ሰዓት ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስት የሥራ ሰዓት ውጪ ወደ ንግድ ድርጅቶች ለቁጥጥር ሥራ የሚሄዱ ከሆነ አግባብ ካለው ባለስልጣን ይህንኑ የሚያስረዳ ደብዳቤ መያዝ አለባቸው፡፡

46.<u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተላልፎ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ አግባብ ያለው አካል በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በተመለከተው መሠረት አስተዳዳራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

47.<u>በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ</u>

1. በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንብና መመሪያ በሚሸፈን በማናቸውም ጉዳይ ላይ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚወስናቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን አግባብ ላለው ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ በ 10 ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. አግባብ ያለው ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ የቀረበውን አቤቱታ ሰምቶ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤ ሆኖም ግን በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ የበላይ ኃላፊው ውሳኔውን ያላሳወቀው እንደሆነ ቅሬታ አቅራቢው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
3. አግባብ ባለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት በሕግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

48.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

የንግድ ሕጉን፣ አዋጁን እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን በማስፈፀም ሂደት ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**49.<u>ስለቅጣት</u>**

1. ሀሰተኛ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የእንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ያዘጋጀ ወይም ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም ሰው የንግድ ሥራ ሲያካሂድባቸው የነበሩ የንግድ ዕቃዎች፣ የአገልግሎት መስጫ ወይም የማምረቻ መሣሪያዎች መወረሳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺ) እስከ ብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከ7 (ሰባት) ዓመት እስከ 15 (አሥራ አምስት) ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፤
2. የፀና የንግድ ሥራ ፍቃድ ሳይኖረው በንግድ ሥራ ተሰማርቶ የተገኘ ማንኛውም ሰው ወይም በንግድ ሥራ ፍቃዱ እንዲሰራ ከተፈቀደለት የንግድ ሥራ ውጭ ሲሰራ የተገኘ ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ሲካሄድባቸው የነበሩ የንግድ ዕቃዎች እና የአገልግሎት መስጫ እና የማምረቻ መሣሪያዎች መወረሳቸው እንደተጠበቁ ሆነው ከብር 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺህ) እስከ ብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከ7 (ሰባት) ዓመት እስከ 15 (አሥራ አምስት) ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፤
3. ሐሰተኛ መረጃ በማቅረብ በንግድ መዝገብ የተመዘገበ ወይም የንግድ ስሙን ያስመዘገበ ወይም የንግድ ሥራ ፍቃድ ወይም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ያወጣ ወይም የንግድ ሥራ ፍቃዱን ወይም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀቱን በሐሰተኛ መረጃ ያሳደሰ ወይም ለማውጣት ወይም ለማሳደስ ሙከራ ያደረገ ማንኛውም ሰው ወይም ነጋዴ ያለአግባብ ያገኘው ጥቅም መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከብር 60,000 (ስልሳ ሺህ) እስከ ብር 120,000 (መቶ ሃያ ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከ7 (ሰባት) ዓመት እስከ 12 (አሥራ ሁለት) ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፤
4. የንግድ ሥራ ፍቃዱን እንዲጠቀምበት በሽያጭ፣ በኪራይ፣ በስጦታ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ ማንኛውም ነጋዴ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ) እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) የገንዘብ መቀጮ እና ከ5 (አምስት) ዓመት እስከ 10 (አሥር) ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት የሚቀጣ ሲሆን አሳልፎ የሰጠው ለውጭ አገር ዜጋ በሆነ ጊዜ ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ) እስከ ብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከ7 (ሰባት) ዓመት እስከ 15 (አሥራ አምስት) ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

5. የንግድ ሥራ አድራሻ ለውጥ በአዋጁ መሠረት በወጣው ደንብ በተመለከተዉ የጊዜ ወሰን ውስጥ ለመዝጋቢው መስሪያ ቤት ያላስታወቀ ማንኛውም ነጋዴ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ) እስከ ብር 10,000 (አስር ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና እስከ ሦስት ወር በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤
6. በንግድ መዝገቡ ላይ ማሻሻያ ሊያስከትል የሚችል ለውጥ አድርጎ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት በ 30 ቀናት ውስጥ ለመዝጋቢው መሥሪያ ቤት ያላስታወቀ ማንኛውም ነጋዴ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ) እስከ ብር 10,000 (አስር ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤
7. ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ለሚካሄድ የቁጥጥር ሥራ አግባብ ያለው አካል የሚልካቸው ሠራተኞች ወይም ተቆጣጣሪዎች የሚጠይቁትን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ የማይሆን ወይም በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ ተግባራቸውን የሚያስተጓጉል ማንኛውም ነጋዴ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ) እስከ ብር 10,000 (አስር ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል::
8. የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር 10,000 (አስር ሺ) እስከ ብር 30,000 (ሠላሳ ሺ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

50.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 51(1) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተጀመሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 (እንደተሻሻለ) መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

51.**ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

1. የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡
2. በዚህ አዋጅ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ልማድ ወይም አሰራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

52.**ደንብና መመሪያ ስለማውጣት**

1. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም ሚኒስቴሩ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

53. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም.**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዝዳንት**

## ደንብ ቁጥር 392/2009

## ስለንግድ ምዝገባና ፈቃድ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ[20]

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 52(1) መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 392/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ነዉ።
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

### ክፍል ሁለት

### የንግድ ድርጅት ስምና የንግድ ስም በንግድ

### መዝገብ ስለመመዝገብ፤ ስለማሻሻል፤ ስለምትክ ምዝገባና ስለስረዛ መስፈርቶች

3. **የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ስለማስመዝገብ**

የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ለማውጣት የሚቀርብ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 14(1) የተመለከቱ መረጃዎች በማመልከቻ ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

4. **የንግድ ማህበራት የንግድ ድርጅት ስም ስለማስመዝገብ**

1. የንግድ ማህበራት የንግድ ድርጅት ስም ለማስመዝገብ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-
   ሀ) የንግድ ድርጅት ስሙን እንዲያፀድቅ የተመረጠው የአንድ አባል የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
   ለ) ያልፀደቀ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ፤

---

[20] በበ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(2) መሰረት በደንቡ በየትኛውም ቦታ ላይ " አመልካቹ የዋና ሥራ አድራሻና የቅርንጫፍ የሥራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንኑ የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ "የሚለው ተሰርዞ " አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ" በሚል ተተክቷል፡፡

ሐ) ለድርጅታቸው መጠሪያ የመረጡት ሶስት አማራጭ ስሞች፡፡

2. መዝጋቢው አካል ባደረገው ማጣራት አመልካች ያቀረባቸው ሶስቱ አማራጭ ስሞች በሌላ ድርጅት የተያዙ ከሆነ ሌሎች አማራጭ ስሞችን እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡

5. **የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማውጣት**

የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
2. የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
3. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ ሁሉም መስራቾች ተስማምተው የሰጡት የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፤ የወኪሉ እና የወካዩ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም የፀና ፓስፖርት ዋናው እና ፎቶ ኮፒ፤
4. የንግድ ምዝገባ እና የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ፤
5. የንግድ ስሙን ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት የቆየ ከሆነ ከአካባቢው አስተዳደር ሲገለገልበት የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማረጋገጫ ደብዳቤ።

6. **ስለምትክ የንግድ ስም ምስክር ወረቀት**

ምትክ የንግድ ስም ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የአመልካቹ የፀና መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
2. የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
3. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ የወኪሉ እና የወካዩ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የተበላሸው የንግድ ስም የምስክር ወረቀት፤
5. የንግድ ስም የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፡፡

7. **የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል**

የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ለማሻሻል ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው:-

1. የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
2. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ዋናዉንና ፎቶ ኮፒ፤
4. በንግድ ማኅበር የንግድ ስም እንዲሻሻል ሲጠየቅ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ስለመሻሻሉ ለዚህ በተዘጋጀ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታርን በመጠቀም ያሳውቃል፡፡[21]

8. **የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ**

የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. የአመልካቹን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
2. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
4. የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ዋናዉንና ፎቶ ኮፒ፤

9. **ስለግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት**

1. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-
   ሀ) አመልካቹ ዋና የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
   ለ) የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች

[21] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

ፎቶ ኮፒ፣

ሐ) አመልካቹ ዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፣

1) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

2) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

3) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ በአካባቢዉ የመስተዳድር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

መ) ለንግድ ስራዉ የመደበዉ ካፒታል መጠን መግለጫ፣

ሠ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፣

ረ) አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሁም ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የንግድ ሥራ አድራሻ የአመልካቹ የንግድ ሥራ አድራሻው ነው ተብሎ ይወሰዳል፣[22]

2. ግለሰብ ነጋዴ በውክልና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ለማውጣት ሲፈልግ ወኪሉ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የውክልና ማስረጃ ሠነድ ማቅረብ አለበት፣[23]

10. <u>የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው።

1. የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ፣
2. የንግድ ማህበሩን የስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣

[22] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(3) ተሻሻለ፡፡
[23] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(4) ተሻሻለ፡፡

3. በመመስረት ላይ ያለ ከሆነ በሁሉም መስራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ዋና እና ከዋናው ጋር የተመሳከረ ቅጂ፤
4. ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጅዎች፤
5. አመልካቹ የዉጪ ሀገር ዜጋ ከሆነ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የግለሰቡ የታደሰ ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
6. በሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ውስጥ አባል የሆነ የውጪ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው አካል ከሆነ፡-
   ሀ) ከተቋቋመበት አገር ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፤
   ለ) አዲስ በሚቋቋመው ማህበር ውስጥ ለመግባት መወሰኑን የሚያሳይ በአገሩ ሕግ መሠረት የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ ወይም ደብዳቤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፤
   ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፡
   መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ እና በንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት የሚቋቋም የንግድ ማህበር ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ የቅርንጫፍ አድራሻ ማረጋገጫ፤
7. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤
   ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም
   ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየዉ ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ በአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
8. የዓይነት መዋጮ በሚኖርበት ጊዜ የመዋጮው ባለቤትነት የንግድ ምዝገባው ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ የሽርክና ማህበሩ ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበሩ እንደሚተላለፍ የሚያረጋግጥ በአመልካቹ የተፈረመ ማረጋገጫ፤

9. የአዕምሯዊ ፈጠራ ንብረት መዋጮ በሚኖርበት ጊዜ በሰነዶች አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፤
10. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

11. <u>የአክሲዮን ማኅበር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

የአክሲዮን ማኅበር መሥራቾች የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የአክሲዮን ማህበሩ ስራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
2. የአክሲዮን ማህበሩን ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸዉ ፎቶግራፎች፤
3. ማመልከቻ በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋናው እና ፎቶ ኮፒ የተወካዩ እና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናዉ እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የአክሲዮን ማህበሩ በመመስረት ላይ ያለ ከሆነ በሁሉም መስራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ዋና እና ከዋናው ጋር የተመሳከረ ቅጂ፤
5. በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ዋናና ቅጅዎች፤
6. በአክሲዮን ማህበር ውስጥ የዉጭ ሀገር ዜግነት ያለው ግለሰብ አባል የሚገኝ ከሆነ ከሚመለከተዉ መስሪያ ቤት የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የፓስፖርቱ ዋና እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤
7. በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ አባል የሆነ የውጭ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት የሚገኝ ከሆነ፡-
   ሀ) ከተቋቋመበት አገር ሕጋዊ ሰዉነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፤
   ለ) አዲስ በሚቋቋመው አክሲዮን ማህበር ውስጥ ለመግባት መወሰኑን የሚያሳይ በአገሩ ሕግ እና በኢትዮጵያ የሰነዶች አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ-ጉባዔ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፤
   ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፤
   መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ እና በንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት የሚቋቋም የንግድ ማህበር ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ የቅርንጫፍ አድራሻ ማረጋገጫ፤

8. አመልካቹ በዋና የስራ አድራሻና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለዉ ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፤
   ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም
   ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
9. ከተፈረመ የአከሲዮን ሽያጭ ቢያንስ አንድ አራተኛ ገንዘብ ተከፍሎ በዝግ ሂሳብ ለመቀመጡ የባንክ ማስረጃ፤
10. የአዕምሯዊ ፈጠራ ንብረት መዋጮ በሚኖርበት ጊዜ በሰነዶች አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፤
11. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

12. <u>የመንግስት የልማት ድርጅት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

የፌዴራል ወይም የክልል መንግስታት የልማት ድርጅቶች የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. ድርጅቱ የተቋቋመበት ሕግ፤
2. የስራ አስኪያጁ የምደባ ደብዳቤ፤
3. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ እና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
5. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
6. የልማት ድርጅቱ የዋና የስራ አድራሻ እና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንን የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ፤
   ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

7. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

13. <u>የንግድ እንደራሴ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

1. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፤

ሀ) የእንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

ለ) የእንደራሴዉን ማንነት በግልፅ የሚያሳዩ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

ሐ) ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የእንደራሴውና የወካዩ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

መ) ወካዩ ነጋዴ በተቋቋመበት አገር ወይም በሚሰራበት አገር የተመዘገበ ሕጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

ሠ) ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ እና ለሥራ ማስኪያጃ የሚሆን ቢያንስ 100ሺ (አንድ መቶ ሺ) የአሜሪካን ዶላር ወደ አገር ውስጥ በወካዩ ስም ወይም በእንደራሴው ስም ለማስገባቱ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፤[24]

ረ) እንደራሴው በወካዩ ነጋዴ በእንደራሴነት የተሾመበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ማስረጃ ዋና ቅጅ፤

ሰ) አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤

1) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም፤

[24] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(5) ተሻሻለ፡፡

2) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

3) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

ሸ) ወካዩ የንግድ ማህበር ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ ሀ-ሰ ከተመለከቱት በተጨማሪ የተረጋገጡ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ወይም ድርጅቱ የተቋቋመበት ተመሳሳይ ሰነድ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ማስረጃ፤

ቀ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፤

2. የንግድ እንደራሴ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በውክልና ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

14. <u>በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነዉ የሚገቡ የውጭ አገር የንግድ ድርጅቶች የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት</u>

በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር ንግድ ድርጅቶች የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የስራ አስኪያጁ ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
2. የስራ አስኪያጁ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ የተነሳው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
3. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁን ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የማህበሩን ሕጋዊ ሰውነት የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፤
5. ማህበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ለመክፈት መወሰኑን እና ስራ አስኪያጅ ስለመመደቡ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፤
6. ጨረታውን ከሰጠው አካል የጨረታ ስምምነት ሰነድና የይመዝገብልኝ የድጋፍ ደብዳቤ፤
7. የስራ ቦታ አድራሻ የሚያሳይ ሰነድ፤
8. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

15.**<u>በሌሎች ሕጐች እንዲነግዱ የተፈቀደላቸዉ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት</u>**

በሌሎች ሕጎች አግባብ ባላቸው የመንግሥት አካላት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. አግባብ ካለው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፤
2. ስለሚነግዱበት የንግድ ስራ ዓይነት፣ የካፒታል ምንጭ እና መጠን፣ ስለትርፍ አጠቃቀም፣ የማህበሩ አስተዳደር እና መሰል ጉዳዮችን ያካተተ አግባብ ካለው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ ደብዳቤ፤
3. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናዉ እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
5. ማመልከቻዉ በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የስራ አስኪያጁ የፀና የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
6. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤
   ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም
   ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየዉ ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
7. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፤

16.**<u>የዘርፍ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት</u>**

የዘርፍ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤
2. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ሲሆን የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅና ፎቶ ኮፒ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የፀና የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናዉ እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጅ፤
5. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤
   ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም
   ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው መንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገቻ፤
6. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

17.<u>**በውጭ አገር የተቋቋሙ የንግድ ምክር ቤቶች የቅርንጫፍ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት**</u>

በውጭ አገር የተቋቋሙ የንግድ ምክር ቤቶች የቅርንጫፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. ከአገራቸው ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ወይም ኤምባሲዎቻቸው ወይም ከንግድ ምክር ቤቶቻቸው ወይም ከአገራቸው አግባብ ካለው አካል ምዝገባዉ የተፈቀደ ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
2. በተቋቋሙበት አገር የተሰጠ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፤
3. ቅርንጫፍ ለመክፈት ያመለከተው ንግድ ምክር ቤት ለሚቋቋመው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የመደበዉ ስራ አስኪያጅ ሕጋዊ ደብዳቤ፤

4. የንግድ ምክር ቤቱን ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳዉ ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸዉ ፎቶግራፎች፤
5. የአመልካቹ የስራ አድራሻ ማረጋገጫ የኪራይ ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤
6. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፤

18.<u>የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል</u>

የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሻሻል በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
2. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. ማሻሻያው የሚደረገው በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሆነ የማኅበሩ አባላት ማሻሻያ ያደረጉበትን ሠነድ ለማርጋገጥ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ፤ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ ሠነድን ለማርጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የማኅበሩ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ እና የአድራሻ ማሻሻያ ቅፅ ላይ በመሙላት በፊርማው ያረጋገጠው በቅፁ የተመለከተው አድራሻ የንግድ ሥራ አድራሻው፤[25]
5. ግለሰብ የሆነ የውጭ ሀገር ዜጋ በነባር የንግድ ማህበር ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ከሆነ የኢንቨስትመንት ይሁንታ፤
6. በነባር የንግድ ማህበር ውስጥ አባል ሆኖ የሚገባው የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጂ፣ የሕጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀት ወይም ተመሳሳይ ሰነድ እና አዲስ በሚቋቋመው ማህበር ውስጥ እንዲገባ ሥልጣን ባለው የማህበሩ አካል መወሰኑን የሚያሳይ አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ሰነድ አረጋጋጭ

[25] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(6) ተሻሻለ፡፡

የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ ወይም ደብዳቤ እና እንዲሁም ማህበሩ የዉጭ አገር ማኅበር ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም አባል ሆኖ አክሲዮን እንዲገዛ የተፈቀደ ደብዳቤ፤

7. ማሻሻያዉ ስለግለሰብ ነጋዴ የስራ አድራሻ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

19.<u>ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
2. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ የመታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የተበላሸውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
5. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተዉ አካል የተሰጠ ማስረጃ፡፡

20.<u>ስለ ምትክ የንግድ እንደራሴ ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

ምትክ የንግድ እንደራሴ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፤

1. የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
2. የእንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናዉ እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. ማመልከቻዉ በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ፣ የወኪሉና እንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የተበላሸውን የንግድ እንደራሴ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤
5. የንግድ እንደራሴው የምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፤

## 21.የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ[26]

1. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅፅ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው:-

   ሀ) የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

   ለ) ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤

   ሐ) የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ፤

   መ) የንግድ ማኅበር ከሆነ የማኅበሩን ስረዛ ቃለ ጉባኤ (ዋናውን) እና የኦዲት ሪፖርት፡፡

2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት መሰረዙን ለዚህ ተግባር ያዘጋጀውን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታር በመጠቀም ያሳውቃል፡፡

## 22.የንግድ እንደራሴ ምዝገባ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማስረዝ

የንግድ እንደራሴውን ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማስረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናዉ እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
2. ማመልከቻዉ በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፤ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. የእንደራሴው ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
4. ቀደም ሲል የተሰጠው የንግድ እንደራሴው ልዩ የምስክር ወረቀት ተመላሽ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

[26] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(7) ተሻሻለ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የንግድ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት፣ ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለመተካት እና ስለመሰረዝ

### 23.ስለግለሰብ ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

1. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

   ሀ) የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤

   ለ) የግለሰቡን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

   ሐ) የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

   መ) አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፤

   ሠ) አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፣

   1) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም

   2) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

   3) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

   ረ) የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፤

2. ግለሰብ ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀትን በውክልና ለማውጣት ተወካዩ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡[27]

[27] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(8) ተሻሻለ፡፡

## 24.የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

የሽርክና ማህበራት እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
2. የስራ አስኪያጅ ወይም የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. የንግድ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳዉ ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
4. ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ፤
5. አመልካቹ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ግለሰብ ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማረጋገጫ እና የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤
6. በሽርክና ማህበራትና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ውስጥ አባል የሆነ የውጭ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው ከሆነ፤

   ሀ) ከተቋቋመበት አገር ሕጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፤

   ለ) በንግድ ማህበሩ ውስጥ ለመግባት የተወሰነበት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፤

   ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፤

   መ) የንግድ ማኅበሩ ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የንግድ ሥራ አድራሻው፡፡ ይህ አመልካቹ በቅፁ የተመለከተው አድራሻ ቅርንጫፍ የንግድ ሥራ አድራሻው ነው ተብሎ ይወሰዳል፤[28]
7. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፣

   ሀ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም

[28] በ26/11(2012) ዶ.461 አንቀፅ 2(9) ተሻሻለ፡፡

ለ) ለንግድ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀቀ የኪራይ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

8. የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡፡

25.**<u>የአክሲዮን ማኅበር የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት መሟላት ያለባቸዉ መስፈርቶች</u>**

የአክሲዮን ማኅበር መሥራቾች የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
2. የስራ አስኪያጅ ወይም የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤
3. የአክሲዮን ማህበሩን ስራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳዉ ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
4. ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ በሁሉም መስራች አባላት የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ሰነድ ዋናው እና የተረጋገጠ ቅጅ፤
5. የተረጋገጠ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጂ፤
6. በአክሲዮን ማህበር ውስጥ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ግለሰቦች በሚኖሩበት ጊዜ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ይሁንታ ማረጋገጫ እና የፀና ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤
7. በአክሲዮን ማህበር ውስጥ አባል የሆነ የውጭ ሀገር የሕግ ሰውነት ያለው አካል ከሆነ፤

ሀ) ከተቋቋመበት አገር ህጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ማረጋገጫ ሰነድ፤

ለ) በንግድ ማህበሩ ውስጥ ለመግባት የተወሰነበት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ፣

ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፤

መ) የንግድ ማህበሩ ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ የቅርንጫፍ አድራሻ ማረጋገጫ፤

8. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፣
   ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም
   ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
9. የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡፡
10. የአክሲዮን ድርሻ ሰርተፊኬት ናሙና እና የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ፡፡

26. <u>**የመንግስት የልማት ድርጅት የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት**</u>

የመንግስት የልማት ድርጅት የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
2. የተቋቋመበት ሕግ፣
3. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፤
4. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
5. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
6. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የተወከለበት ደብዳቤ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
7. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤
   ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፣ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ በአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

8. የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡፡

27.<u>**የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት**</u>

የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. የእንደራሴው የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤
2. የእንደራሴውን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
3. የእንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤
4. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጂ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የእንደራሴው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤
5. ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ እና ለሥራ ማስኬጃ የሚሆን ቢያንስ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር በእንደራሴው ስም በአገር ውስጥ ስለማስቀመጡ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፤
6. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤

   ሀ) ለጽህፈት ቤት የሚጠቅምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ወይም

   ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜው ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ውል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ውል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢው የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤

7. የንግድ እንደራሴው የሚያከናውናቸው ተግባራት መግለጫ፤
8. አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ የንግድ እንደራሴነት ልዩ የምስክር ወረቀት እንደተሰጠው አግባብ ካለው የመንግስት አካል የመኖሪያ እና የሥራ ፈቃድ አውጥቶ ለማቅረብ ግዴታ የገባበት ጽሁፍ ማረጋገጫ፡፡

28.**<u>በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር ድርጅቶች የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት</u>**

በዓለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው የሚገቡ የውጭ አገር ድርጅቶች የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
2. የሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
3. የሥራ አስኪያጁ ፓስፖርት ዋናው እና አሰፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፤
4. የሥራ ቦታ አድራሻ መግለጫ፤
5. ጨረታውን ከሰጠው አካል የጨረታ ስምምነት ሰነድና የይመዝገብልኝ የድጋፍ ደብዳቤ፤

29.**<u>በሌሎች ሕጎች እንዲነግዱ የተፈቀደላቸው ማህበራት የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት</u>**

በሌሎች ሕጎች አግባብ ባላቸው የመንግስት አካላት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው ማህበራት ወይም የንግድ ድርጅቶች የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣
2. የሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
3. የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፣

4. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ እና የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፣
5. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤
   ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋጫ ወይም
   ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ በአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
6. የንግድ ስራ ፈቃድ የተጠየቀበት የስራ መደብ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ለሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡፡

30.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማደስ</u>

የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማደስ በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የግብር ክሊራንስ፤
2. የንግድ ማኅበር ከሆነ የኦዲት ሪፖርት፤[29]
3. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤
4. ማመልከቻው በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የንግድ ማህበር ሲሆን በሁሉም መሥራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ እና የወኪሉ እና የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
5. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፣

[29] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(10) ተሻሻለ፡፡

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ፤ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ በአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፡፡

31.<u>የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማደስ</u>

የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸ፡-

1. ከሚመለከተዉ አካል የተሰጠ የግብር ክሊራንስ፤
2. የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
3. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ እና የእንደራሴው እና የተወካዩ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤ማህበር ከሆነ በማህበሩ ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ፤
4. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፣

ሀ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋንጫ፤ ወይም

ለ) ለጽሕፈት ቤት የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየዉ ከሆነ ጊዜው ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ  የኪራይ ዉል፤ የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢዉ የመስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፡፡

5. በሚታደስበት በጀት ዓመት 100,000 (አንድ መቶ ሺ) የአሜሪካ ዶላር በእንደራሴዉ ስም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባቱ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፣

6. የንግድ እንደራሴዉ የዉጭ አገር ዜጋ ከሆነ ለዘመኑ የታደሰ የስራ እና የመኖሪያ ፈቃድ፡፡

## 32. የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል

የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማሻሻል ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘዉ መቅረብ አለባቸው፡-

1. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
2. የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፤
3. ማሻሻያው የሚደረገው በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሆነ የማኅበሩ አባላት ማሻሻያውን ያደረጉበት ሠነድን ለማረጋገጥ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ፤ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅፅ ላይ ማኅበሩ የንግድ ሥራ አድራሻዬ ነው ብሎ የሞላው እና በፊርማው ያረጋገጠው የንግድ ሥራ አድራሻ የአመልካቹ የንግድ የሥራ አድራሻ ነው ተብሎ ይወሰዳል፤[30]
4. ግለሰብ የውጭ ሀገር ዜጋ በነባር የንግድ ማህበር ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን፣
5. አዲሱ አባል የሕግ ሰውነት ያለው አካል ከሆነ የዚሁ አዲስ አባል የመመስረቻ ጽሁፍና ደንብ ዋና ቅጅ የመቋቋሚያ የምስክር ወረቀት ወይም ተመሳሳይ ሰነድ እና አዲስ በሚቋቋመው ማህበር ውስጥ ለመግባት ስልጣን ባለው የማህበሩ አካል መወሰኑን የሚያሳይ አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ ወይም ደብዳቤ እና ማህበሩ የዉጭ ሀገር ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና አክሲዮን እንዲገዛ በሚኒስቴሩ የተሰጠ ፈቃድ፣
6. የንግድ ሥራ ፈቃድ ማሻሻያ የተጠየቀበት የስራ መደብ ቀደም ብለው በነበሩት ውስጥ ያልተካተተ እና የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተዉ የሴክተር መስሪያ ቤት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣
7. ማመልከቻዉ በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም የጸና የፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፣

[30] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(11) ተሻሻለ፡፡

8. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በ 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፡፡

33. <u>ስለምትክ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት</u>

ምትክ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያያዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የተበላሸዉ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፣
2. የመደበኛ እድሳት ጊዜው ያለፈበት ምስክር ወረቀት ከሆነ ክሚመለክተው አካል የግብር ክሊራንስ፣
3. የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣
4. የስራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣
5. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ እና የስራ አስኪያጁን እና የተወካዩን የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፣ ማህበር ከሆነ በሁሉም መሥራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ፡፡

34. <u>ምትክ የንግድ ልዩ የምስክር ወረቀት</u>

ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. የተበላሸውን የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት፡
2. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣
3. የእንደራሴውን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ ባለፉት 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣
4. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ እና የወካዩ እና የንግድ እንደራሴዉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ማህበር ከሆነ በሁሉም መስራች አባላት ተፈርሞ የተሰጠ የውክልና ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ፣
5. የመደበኛ እድሳት ጊዜው ያለፈበት ምስክር ወረቀት ከሆነ ከሚመለክተው አካል የግብር ክሊራንስ፣

35.<u>የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ</u>

የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. ቀደም ሲል የተሰጠ እና የሚሰረዝ የንግድ ሰራ ፈቃድ፤
2. የንግድ ስራ ፈቃድ መሰረዢያ የግብር ክሊራንስ፤
3. የስራ አስኪያጁ የታደስ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የስረዛው ጥያቄ የቀረበው በወኪል ከሆነ በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ፤
5. ለንግድ ስራ ፈቃዱ የወሰደው የንግድ ስም ምዝገባ ሰርተፊኬት፡፡

36.<u>የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ</u>

የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የእንደራሴው ልዩ የምስክር ወረቀት፤
2. የንግድ እንደራሴው የገቢ ግብር ክሊራንስ፤
3. የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. የስረዛው ጥያቄ የቀረበው በወኪል ከሆነ በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

37.<u>የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. የሆልዲንግ ኩባንያ ስለመመስረቱ ሰነዱን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ፤
2. የሆልዲንግ ኩባንያው የቡድን አባላት የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ ዋናው እና ፎቶ ኮፒ፤
3. የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤

4. የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፡፡

38. **<u>የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እድሳት</u>**

የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምስክር ወረቀትን ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘዉ መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የሆልዲንግ ኩባንያው የቡድን አባላት የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ፤
2. የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤
3. የሆልዲንን አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
4. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ የተወካዩ እና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፣

39. **<u>ስለሆልዲንግ ኩባንያ ምትክ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>**

የሆልዲንግ ኩባንያ ምትክ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የተበላሸውን ልዩ የምስክር ወረቀት፣
2. የሆልዲንግ ኩባንያው ልዩ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣
3. የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፣
4. የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፡፡

40. **<u>የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል</u>**

የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማሻሻል ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘዉ መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. ከአባላቱ መካከል በማናቸውም ምክንያት ከቡድኑ ሲወጡ ወይም ሌላ አዲስ የቡድን አባል ወደ ቡድኑ ሲገባ በሠነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ፤
2. የሆልዲንን ኩባንያው ልዩ የምስክር ወረቀት፤

3. የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጁ የፀና የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፣
4. የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤

41.**<u>የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ</u>**[31]

1. የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅፅ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

   ሀ) የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት፣

   ለ) የሆሊዲንግ ስምምነት ስለመፍረሱ ሰነድ ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ፣

   ሐ) የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገጾች ፎቶኮፒ፡

2. የሆልዲንግ ስምምነቱ ስለመፍረሱ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀውን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታር በመጠቀም ይፋ ያደርጋል፡፡

42.**<u>ስለጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>**

የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የአመልካቹን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
2. የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ፤

   ሀ) ለንግድ ሥራ የሚጠቀምበት ቤት የአመልካቹ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም

   ለ) ለንግድ ሥራ የሚጠቀምበት ቤት ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜዉ ያላለፈበት በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የፀደቀ የኪራይ ዉል የመንግስት ቤት ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ዉል፣

---

[31] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(12) ተሻሻለ፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ከተመለከቱት ማስረጃዎች አንዱን ማቅረብ ካልቻለ ስለሚሰራበት አድራሻ በአካባቢዉ የመስተዳድር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣

4. ለንግድ ስራዉ የመደበዉ ካፒታል መግለጫ፤
5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፡፡

43.<u>የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ</u>

የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
2. ማመልከቻዉ በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ የወኪሉና የስራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
3. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ፤
4. የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ስረዛ ውሳኔ ቃለ ጉበዔ ዋና ቅጅ እና የኦዲት ሪፖርት፡፡

44.<u>ስለጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት</u>

የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማውጣት በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የጠረፍ ንግዱ በሚካሄድበት የአካባቢ አስተዳደር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እና ነዋሪ ስለመሆኑ የሚገልፅ ማረጋገጫ፤
2. የጠረፍ ንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት በሚመለከተዉ አካል የጠረፍ ንግድ እንዲነግድ የተፈቀደለት ስለመሆኑ የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
3. የግለሰቡን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሣው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸዉ ፎቶግራፎች፤
4. የግለሰቡ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፤
6. ግለሰቡ ስለሚሰራበት አድራሻ ከአካባቢው አስተዳደር አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፡፡

## 45. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማደስ

የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማደስ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. ከሚመለከተው አካል የግብር ክሊራንስ፤
2. ከሚመለከተው የአካባቢ አስተዳደር የንግድ ስራው እንዲቀጥል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤
3. የግለሰቡን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
4. የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፡፡

## 46. ስለምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የተበላሸውን የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፤
2. ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ፤
3. የመደበኛ ዕድሳት ጊዜው ያለፈበት የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ምትክ የተጠየቀበት ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የግብር ክሊራንስ፡፡

## 47. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ

የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የተሰጠ የጠረፍ ንግድ ልዩ ስራ ፈቃድ፤
2. ከሚመለከተው ባለስልጣን የተሰጠ የግብር ክሊራንስ መረጃ፤
3. የአመልካቹ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፡፡

## 48. የፍሬንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት

የፍሬንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. በሠነድ አረጋጋጭ የፀደቀ የፍሬንቻይዚንግ ውል ዋናውና የተረጋገጠ ፎቶ ኮፒ፤
2. የፍሬንቻይዘሩ (ውል ሰጪ) የተመዘገበበትን ምስክር ወረቀት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ፤
3. የፍሬንቻይዚ (ውል ተቀባይ) የፀና ንግድ ስራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፤

4. የፍሬንቻይዚ ሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
5. የፍሬንቻይዚ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፤
6. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፡፡

49.**<u>የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማደስ</u>**

የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማደስ በሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡-

1. የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤
2. የፍሬንቻይዚ ሥራ አስኪያጁ የፀና ንግድ ስራ ፈቃድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፤
3. የፍሬንቻይዚ ሥራ አስኪያጁን ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ግዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤
4. የፍሬንቻይዚ ሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፣
5. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፡፡

50.**<u>ምትክ የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማግኘት</u>**

ምትክ የፍሬንቻይዚንግ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የተበላሸውን የፍሬንቻይዚ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፤
2. የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ከሚመለከተዉ አካል የተሰጠ ማስረጃ፤
3. የፍሬንቻይዚዉን ሥራ አስኪያጅ ማንነት በግልፅ የሚያሳይ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፤

4. ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፡፡

51.<u>**የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ**</u>

የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የፍራንቻይዘሩና የፍራንቻይዚ ውል ማፍረሻ ስምምነት ሰነድ፤[32]
2. የፍሬንቻይዚ ልዩ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤
3. ማመልከቻዉ በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ዋና ቅጅ እና ፎቶ ኮፒ፣ የወካዩ እና የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊው ገፆች ፎቶ ኮፒ፡፡

52.<u>**አምራቾች ወይም አስመጪዎች በችርቻሮ መሸጥ የሚችሏቸው የምርት ወይም የእቃ ዓይነቶች**</u>

1. አምራቾች ወይም አስመጪዎች በችርቻሮ መሸጥ የሚችሏቸው የምርት ወይም የእቃ ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-
   ሀ) በሞተር ኃይል የሚሰሩ የማምረቻ ማሽኖች፤
   ለ) በሞተር ኃይል የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች፤
   ሐ) የቢሮ እና የቤት መገልገያ ዕቃዎች፤
   መ) የሙዚቃ መሳሪያዎች፤
   ሠ) ሶፍትዌሮች፤
   ረ) ብስክሌቶች፤
   ሰ) አሳንሰር እና የተንቀሳቃሽ ደረጃዎች፤
   ሸ) የህክምና መሣሪያዎች፤
   ቀ) ለምርምር የሚውሉ ኬሚካሎች፤
   በ) ሬንጅ፡፡
2. አምራቾች ብቻ በችርቻሮ መሸጥ የሚችሏቸው የምርት ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-
   ሀ) ዳቦ እና ጣፋጭ ምግቦች፤

[32] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(13) ተሻሻለ፡፡

ለ) የሲሚንቶ እና የሴራሚክ ዉጤቶች፡፡

3. አምራቾች ወይም አስመጪዎች ከምርት ባህሪያቸው የተነሳ ለችርቻሮ ሽያጭ አስገዳጅነት ያላቸው ምርቶች በችርቻሮ ሊሸጡ ይችላሉ፤[33]

52.በዚህ ደንብ ስለመታወቂያ እና ፓስፖርት የተነገሩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንጃ ፈቃድ እና ከመሥሪያ ቤቶች የሚሰጡ መታወቂያዎችን በማቅረብም አገልግሎት ይሰጣል፡፡[34]

53.<u>መመሪያ ስለማዉጣት</u>

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ሚኒስቴሩ መመሪያዎችን ማዉጣት ይችላል፡፡

54.<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸዉ ደንቦችና አሰራሮች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም የተለምዶ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

55.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመስከረም 4 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

[33] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(14) ተሻሻለ፡፡

[34] በ26/11(2012) ደ.461 አንቀፅ 2(15) አንቀጽ 52 በኋላ አዲስ አንቀጽ 53 ተጨምሮ ከአንቀጽ 53 እስከ አንቀጽ 55 ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 54 እስከ አንቀጽ 56 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

## ደንብ ቁጥር 246/2003

## የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ተመኖች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 62 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ተመኖች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 246/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "አዋጅ" ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ነዉ፤[35]
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ።[36]

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   በዚህ ደንብ የተመለከቱት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ተመኖች ተፈፃሚ የሚሆኑት በንግድ ሚኒስቴር እና ሚኒስቴሩን በመወከል በክልል ቢሮዎች ወይም በሌሎች የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚሰጡ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ነው።

4. **የአከፋፈል ሁኔታ**

   1. በዚህ ደንብ የተመለከቱት የአገልግሎት ክፍያዎች በተናጠል እና አገልግሎቶቹ በተጠየቁ ጊዜ መከፈል አለባቸው።
   2. ለንግድ ፈቃድ ማውጣት ወይም እድሳት የሚፈፀሙ ክፍያዎች ለእያንዳንዱ የንግድ ፈቃድ አይነት ለየብቻ መከፈል አለባቸው።

5. **የክፍያ መጠን**

   በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈፀሙ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ በተቀመጡ ተመኖች መሠረት ይከፈላሉ፡-

---

[35] በ22/101(2008) አ.980 ተሻሯል፡፡

[36] ለአቻ ትርጓሜ 22/101(2008) አ.980 አንቀፅ 2ን ተመልከት፡፡

## የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች የክፍያ ተመኖች

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን (በብር) |
|---|---|---|
| 1. | የአገልግሎት መጠየቂያ የማመልከቻ ቅጽ | 2 |
| 2. | የንግድ ምዝገባ | 100 |
| 3. | የንግድ ምዝገባ ዕድሣት | 100 |
| 4. | የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ | 80 |
| 5. | የምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 6. | የንግድ ምዝገባ ስረዛ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 7. | የንግድ ምዝገባ በመዝገብ የሰፈረው ዝርዝር ቅጂ ወይም የተውጣጣ መረጃ ቅጂ ወይም በንግድ መዝገብ ያልተመዘገበ ለመሆኑ ወይም የንግድ ምዝገባው የተሰረዘ ለመሆኑ ማረጋገጫ | 100 |
| 8. | የንግድ መደብር ቅርንጫፍ አድራሻን ለመዝጋቢው መሥሪያ ቤት ለማሳወቅ | 50 |
| 9. | የንግድ ስም ምዝገባ ማጣሪያ | 25 |
| 10. | የንግድ ስም ምዝገባ | 100 |
| 11. | የንግድ ስም ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ | 80 |
| 12. | ምትክ የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 13. | የንግድ ስም ምዝገባ ስረዛ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 14. | የንግድ ፈቃድ ለማውጣት | 100 |
| 15. | የንግድ ፈቃድ ዕድሣት | 100 |
| 16. | በንግድ ፈቃድ ላይ ስለሚደረግ ለውጥ ወይም | 80 |

| | | |
|---|---|---|
| | ማሻሻያ | |
| 17. | ምትክ የንግድ ፈቃድ | 50 |
| 18. | የንግድ ፈቃድ ስረዛ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 19. | የማስፋፊያና የማሻሻያ ፈቃድ | 100 |
| 20. | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት | 250 |
| 21. | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት ዕድሣት | 250 |
| 22. | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት ለውጥ ወይም ማሻሻያ | 100 |
| 23. | ምትክ የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት | 100 |
| 24. | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት ስረዛ ማረጋገጫ | 100 |
| 25. | ህዝቡ አክስዮን ለመግዛት በመፈረም ለሚቋቋም የአክሲዮን ማኅበር መስራቾች ለሚሰጥ ፈቃድ | 100 |
| 26. | በውጭ ሀገር የኢትዮጵያን የንግድ ትርኢት ለማዘጋጀት ለሚሰጥ ፈቃድ ወይም የውጭ ሀገር መንግሥት ወይም ድርጅት በሚያደረገው የውጭ ሀገር የንግድ ትርኢት ኢትዮጵያ ተካፋይ እንድትሆን ተሳታፊዎችን ለማስተባበር ለሚሰጥ ፈቃድ | 300 |
| 27. | በውጭ ሀገር በሚዘጋጅ የንግድ ትርኢት የግል ተሳትፎ ለማድረግ ለሚሰጥ ፈቃድ | 100 |
| 28. | በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚዘጋጅ ውጭ ሀገር ምርት የንግድ ትርኢት ፈቃድ | 300 |

| | | |
|---|---|---|
| 29. | በሀገር ውስጥ በሚዘጋጅ የንግድ ትርዒት ውስጥ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር ነጋዴ የግል ተሳትፎ ለማድረግ ለሚሰጥ ፈቃድ | 100 |

6. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ለ/ ስለፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ

## አዋጅ ቁጥር 847/2006

## የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ

በግል እና በመንግስት ዘርፍ ባሉ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የተሟላ፣ ግልጽና በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ወጥ የሆነ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ህግ መኖሩ ያልተማከለ የነበረውን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ በማማከል ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የሚያጎለብት በመሆኑ፤

የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ምሶሶዎች ለመደገፍ፣ የፋይናንስ ቀውስና የድርጅቶችን ውድቀት ስጋት እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን አሉታዊ የኢኮኖሚ ውጤቶች ለመቀነስ ከድርጅቶች የሚገኘውን የፋይናንስ መረጃ አቅርቦት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብን በኃላፊነት የሚመራ እና የሚቆጣጠር አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ አዋጅ "የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "የሂሳብ ዓመት" ማለት የሪፖርት አቅራቢው አካል የሀብትና ዕዳ መግለጫ በሚወጣበት ቀን የሚያበቃው ዓመት ነው፤ ሆኖም የሪፖርት አቅራቢው አካል በተቋቋመበት ወይም በተመሠረተበት ጊዜ ምክንያት ወይም የሪፖርት አቅራቢው አካል የሀብትና ዕዳ መግለጫ የሚዘጋጅበት ቀን በመለወጡ ምክንያት በዚያ ቀን

የሚያበቃው ጊዜ ከዓመት የሚያጥር ወይም የሚረዝም ከሆነ ይኸው ረጅም ወይም አጭር ጊዜ የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሣብ ዓመት ሆኖ ይቆጠራል፤

2. “የኦዲት ድርጅት” ማለት በቦርዱ የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፤
3. “የሀብትና ዕዳ መግለጫ የሚወጣበት ቀን” ማለት ሪፖርት አቅራቢው አካል የሀብትና ዕዳ መግለጫው የሚወጣበት ቀን እንዲሆን የሚመርጠው ማንኛውም ወርና ቀን ነው፤
4. “የተመሰከረለት ኦዲተር” ማለት የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ በኢንስቲትዩቱ እንደተመሰከረለት ኦዲተር የተመዘገበና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤
5. “የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ” ማለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ በኢንስቲትዩቱ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ የተመዘገበና የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤
6. “ኩባንያ” ማለት በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመና የሕግ ሰውነት የተሰጠው የንግድ ማህበር ነው፤
7. “ዳይሬክተር” ማለት በማንኛውም ስያሜ ቢጠራም ለአንድ ሪፖርት አቅራቢ አካል የበላይ ኃላፊ የሆነ ሰው ወይም የበላይ ኃላፊ ከሆኑት ሰዎች መካከል አንዱ ነው፤
8. “የሂሳብ መግለጫ” ማለት ቦርዱ በሚያወጣቸው ደረጃዎች የሚወሰን ሆኖ በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻም ሆነ ከዚያ በፊት የሚዘጋጅ የሀብትና ዕዳ፣ የትርፍና ኪሳራ፣ የሀብት ለውጥ፣ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫዎች እና በነዚህ ላይ የቀረቡ የማብራሪያ ማስታወሻዎችን ይጨምራል፤
9. “ኢንስቲትዩት” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ነው፤
10. “የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ” ማለት በአንድ የኩባንያዎች ቡድን ስር ያሉ ግንኙነት ያላቸው ኩባንያዎችን የተናጠል የሂሳብ መግለጫዎች በማጠቃለል የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫ ነው፤
11. “ፐብሊክ ኦዲተር” ማለት የህዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ኦዲተር ሆኖ እንዲሰራ በቦርዱ ፈቃድ የተሰጠው የተመሰከረለት ኦዲተር ነው፤
12. “የውጭ ሀገር ኩባንያ” ማለት በንግድ ሕጉ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ከኢትዮጵያ ውጭ የተቋቋመ ኩባንያ ነው፤

13. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[37]

14. "የሂሳብ ሙያ ማህበር" ማለት ዓላማው የአባላቱን የሙያ ብቃት መቆጣጠር እና የሂሳብ ሙያን ማሳደግ የሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 መሠረት ቦርዱ እውቅና የሰጠው ወይም የተቀበለው የሂሳብ ባለሙያዎች ማህበር ነው፤

15. "የሽርክና ማህበር" ማለት በንግድ ሕጉ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

16. "የመንግስት መሥሪያ ቤት" ማለት አግባብ ባለው ሕግ ለመንግስት መሥሪያ ቤት በተሰጠው ትርጉም የሚካተት ወይም በተቋቋመበት ሕግ የመንግስት መሥሪያ ቤት ተብሎ የተሰየመ ማንኛውም አካል ነው፤

17. "የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል" ማለት የሥራውን ዓይነት ወይም ባህሪ፣ የሀብቱን መጠን ወይም የሠራተኛውን ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦርዱ በየጊዜው ከህዝብ ጥቅም ጋር ከፍተኛ ትስስር አለው ብሎ የሚወስነው ሪፖርት አቅራቢ አካል ሲሆን በተለይም የሚያወጣውን የግዴታ ምስክር ወረቀት ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለግብይት ማዋል የሚችል ማንኛውንም ኩባንያን፣ ባንኮችን፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን እና ማንኛውንም ሌሎች የፋይናንስ ተቋማትን እንዲሁም የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፡፡

18. "ሪፖርት አቅራቢ አካል" ማለት የመንግስት መሥሪያ ቤቶችንና ጥቃቅን ድርጅቶችን ሳይጨምር ማንኛውም በሕግ የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ያለበት አካል ነው፤

19. "ጥቃቅን ድርጅቶች" ማለት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ በሚያስቀምጠው መሥፈርት መሠረት እንደ ጥቃቅን ድርጅቶች የሚቆጠሩ ድርጅቶች ናቸው፤

20. "አነስተኛ ወይም መካከለኛ ድርጅት" ማለት የሕዝብ ጥቅም ላለበት አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17 በተሰጠው ትርጓሜ የማይሸፈን ሪፖርት አቅራቢ አካል የሆነ እና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ውጪ ያለ ድርጅት ነው፤

21. "ደረጃዎች" ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከቱት የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ እና የኦዲት ደረጃዎች ማለት ነው፤

22. "የኩባንያዎች ቡድን" የሚለው ሀረግ ቦርዱ በሚያወጣቸው ደረጃዎች የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

---

[37] በ25/8(2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

23.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

24.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋሙ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ማናቸውም ሪፖርት አቅራቢ አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ቦርዱን ስለማቋቋም</u>

4. <u>የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ</u>

1. የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይቋቋማል፡፡
2. ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብና አዘገጃጀትና የኦዲት ሥራዎችን በተመለከተ ደረጃዎችን እና የአፈጻጸም መመሪያዎችን ያወጣል፣ መከበራቸውን ያረጋግጣል፡፡

ለ) የፋይናንስ ሪፖርትና የኦዲት ደረጃዎችን ለማስጠበቅ አስፈላጊውን ምርመራ ወይም ማጣራት ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የህዝብ ጥቅም ባለባቸው አካላት እና በፐብሊክ ኦዲተሮች ላይ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

ሐ) ዓላማውና ተግባሩ ከቦርዱ ዓላማና ተግባር ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተያያዥነት ካለው ማንኛውም ዓለም አቀፍ ተቋም ጋር አብሮ ይሰራል ወይም የተቋሙ አባል ወይም ተባባሪ ይሆናል፤

መ) ሪፖርት አቅራቢ አካላትን የህዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ መለየት የሚያስችል መስፈርት ያወጣል፣ ይመዘግባል፤

ሠ) ፐብሊክ ኦዲተሮችን መዝግቦ ፈቃድ ይሰጣል፤

ረ) ያወጣቸውን ደረጃዎች ለሚያሟሉ የሀገር ውስጥ የሂሳብ ሙያ ማህበራት አክሬዲቴሽን ይሰጣል፣ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት በውጭ ሀገር ለተቋቋሙ የሂሳብ ሙያ ማህበራት እውቅና ይሰጣል፤

ሰ) የሪፖርት አቅራቢ አካላትን የሂሳብ መግለጫዎች ተቀብሎ ይመዘግባል፤

ሸ) የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎችን ለማስጠበቅ የሂሳብ መግለጫዎችን አጥጋቢነትና ትክክለኛነት ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፤

ቀ) የህዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በገለልተኝነት መመርመር የሚያስችል የምርመራና የዲሲፕሊን ሥርዓት ያቋቁማል፤

በ) ከኢንስቲትዩቱ ጋር የሚኖረው የዲሲፕሊን ኃላፊነቶች ማቀናጀት የሚያስችል ስርዓት ይመሰርታል፤

ተ) የሂሳብ ሙያ ማህበራትን በበላይነት ይቆጣጠራል፤

ቸ) ፐብሊክ ኦዲተሮች፣ የኦዲት ድርጅቶች እና ከእነርሱ ጋር በቅርበት የሚሰሩ ሰዎች ሥራቸውን በሚመለከት ተፈጻሚነት ባላቸው ደረጃዎች መሠረት ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ የጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ያከናውናል፤

ኀ) ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰነው ተመን መሠረት ክፍያ ያስከፍላል፤

ነ) በዚህ አዋጅ፣ ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ በሚወጡ ደንቦች እና በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ቅጣት ይጥላል ይሰበሰባል፤

ኘ) ከፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ፣ ከሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሥራ እና ከድርጅቶች አመራር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በሚመለከት መንግሥትን ያማክራል፡፡

አ) የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

ከ) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የፋይናንስ ሪፖርት እና የኦዲት ደረጃዎች</u>

### <u>ምእራፍ አንድ</u>

### <u>የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች</u>

5. <u>ተፈጻሚነት የሚኖራቸው የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች</u>

1. የሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ መግለጫ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ቦርዱ ያጸደቃቸው ወይም ማስተካከያ ወይም ማሻሻያ ያደረገባቸው አለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች ቦርድ ወይም እሱን የሚተካ አካል ያወጣቸው ወይም አለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች ቦርድ ወይም እሱን የሚተካ አካል ያወጣቸው፡-

ሀ) አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች፤ ወይም

ለ) የመካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶች አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች፤

ሐ) ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚያገለግል አለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች፤

ተፈጻሚ ይሆናሉ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የተጠቀሰውን አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መከተል አለበት፡፡
3. ቦርዱ በሚያወጣው የሂሳብ ሪፖርት ደረጃዎች ማንኛውም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ወይም አነስተኛ ወይም መካከለኛ ድርጅት ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ፣ የኩባንያዎች ቡድን የሂሳብ መግለጫ ወይም ሌላ የሂሳብ ሪፖርት ሲያዘጋጅ በአነስተኛ መከተል የሚገባውን የሂሳብ አመዘጋገብ፣ የመለኪያ፣ የአቀራረብ እና የማሳወቅ መስፈርቶች መዘርዘር አለበት፡፡

6. <u>**በውጭ ሀገር የተቋቋመ ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ መግለጫዎች**</u>

በውጭ ሀገር የተቋቋመ የማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ መግለጫ፡-

1. ሪፖርት አቅራቢው አካል የተቋቋመበት ሀገር ሕግ የሚጠይቃቸውን መስፈርቶች የጠበቀ መሆኑን፤ እና
2. ሪፖርት አቅራቢው አካል የተቋቋመበት ሀገር ሕግ የሚጠይቃቸው መስፈርቶች በዚህ አዋጅ ከተቀመጡት መስፈርቶች ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይ መሆናቸውን፤
   ቦርዱ ሲያረጋገጥ የሂሳብ መግለጫው በዚህ አዋጅ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆኑትን የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች ጠብቆ የተዘጋጀ እንደሆነ ይቆጠራል።

7. <u>**በውጭ ሀገር የተቋቋመ የኩባንያዎች ቡድን የሂሳብ መግለጫዎች**</u>

በውጭ ሀገር የተቋቋመ የኩባንያዎች ቡድን የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ፡-

1. የሪፖርት አቅራቢው አካል የተቋቋመበት ሀገር ሕግ የሚጠይቃቸውን መስፈርቶች የተከተለ መሆኑን፤ እና
2. የሪፖርት አቅራቢው አካል የተቋቋመበት ሀገር ሕግ የሚጠይቃቸው መስፈርቶች በዚህ አዋጅ ከተቀመጡት መስፈርቶች ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይ መሆናቸውን፤
   ቦርዱ ሲያረጋገጥ የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ በዚህ አዋጅ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆኑትን የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች ጠብቆ የተዘጋጀ እንደሆነ ይቆጠራል።

8. **<u>የሂሳብ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ</u>**

   1. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሂሳብ ሪፖርቱን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።
   2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ሪፖርት አቅራቢ አካላት በሌላ ሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ያለባቸውን የሂሳብ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አያስቀርም፡፡
   3. በሌሎች ሕጎች መሠረት ሥልጣን ለተሰጠው የመንግስት መሥሪያ ቤት የሚቀርብ የሂሳብ ሪፖርት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለቦርዱ የቀረበው የሂሳብ ሪፖርት ኦሪጂናል ቅጂ መሆን አለበት፡፡

9. **<u>የተናጠልና የተጠቃለሉ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት የማስደረግ ግዴታ</u>**

   1. የማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ዳይሬክተር የሪፖርት አቅራቢውን የሂሳብ መግለጫ እንዲሁም ሪፖርት አቅራቢው አካል የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ማቅረብ የሚጠበቅበት ከሆነ የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ኦዲት መደረጉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
   2. የተናጠሉም ሆነ የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ኦዲት መደረግ እና የኦዲት ሪፖርቱ መዘጋጀት ያለበት ቦርዱ በሚያፀድቀው አለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች ወይም በውጭ ሀገር ለተቋቋሙ ሪፖርት አቅራቢ አካላት በዚህ አዋጅ ከተቀመጡት መስፈርቶች ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይ እስከሆነ ድረስ በተቋቋሙበት ሀገር ተፈጻሚ በሆነው የኦዲት ደረጃዎች መሠረት መሆን አለበት፡፡

10. **<u>የሪፖርት አቅራቢ አካላትን የሂሳብ መግለጫ ኦዲት ማድረግ ስለሚችሉ ኦዲተሮች</u>**

ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሚያቀርበው ነጠላም ሆነ የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ኦዲት መደረግ ያለበት፡-

   1. ሪፖርት አቅራቢው አካል በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የተቋቋመ ወይም የተመሠረተ ኩባንያ ከሆነ በንግድ ሕጉ ወይም እንደአግባብነቱ በሌሎች ሕጎች መሠረት በሚሰየም ኦዲተር፤
   2. ሪፖርት አቅራቢው አካል የተቋቋመበት ወይም የተመሰረበት ሌላ ማንኛውም ሕግ ስለኦዲተር አሰያየም የሚደነገግ ከሆነ በዚሁ ሕግ መሠረት በተሰየመ ኦዲተር፤

3. ሪፖርት አቅራቢው አካል የተቋቋመበት ወይም የተመሠረተበት ሕግ ስለኦዲተር አሰያየም የተለየ ድንጋጌ የሌለው ከሆነ በንግድ ሕጉ ወይም የተመሳሳይ ድርጅቶችን የኦዲተር አሰያየም በሚደነግጉ ሌሎች ሕጎች መሠረት በተሰየመ ኦዲተር ይሆናል፡፡

11. <u>የሂሳብ መግለጫዎች ምዝገባ</u>

1. የማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ዳይሬክተር እንደ አግባብነቱ የሪፖርት አቅራቢውን የተናጠል ወይም የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ መፈረም ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር 20 የሥራ ቀናት ውስጥ የሂሳብ መግለጫው እና በሂሳብ መግለጫው ላይ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት ቅጂዎች ለምዝገባ ወደ ቦርዱ መላካቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. በውጭ ሀገር የተቋቋሙ ወይም የተመሠረቱ ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሂሳብ መግለጫዎቻቸውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማስመዝገብ አለባቸው።
3. የሪፖርት አቅራቢ አካላት መግለጫቸውን ለቦርዱ በሚያስመዘግቡበት ጊዜ የሚጠየቀውን የምዝገባ ክፍያ መክፈል አለባቸው።
4. ማንኛውም መብት ወይም ጥቅም ያለው ሰው መብት ወይም ጥቅም እንዳለው ሲረጋገጥና የሚጠየቀውን ክፍያ ሲከፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ለምዝገባ ለቦርዱ የተላከውን የሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ መግለጫና የኦዲት ሪፖርት ማየት ወይም ቅጅውን መውሰድ ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የኦዲት ደረጃዎች</u>

12. <u>ተፈጻሚ የኦዲት ደረጃዎች</u>

1. በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ኦዲተሮች ቦርዱ ያጸደቃቸውን ወይም ማስተካከያ ወይም ማሻሻያ ያደረገባቸውን አለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል ያወጣቸውን አለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች መጠቀም አለባቸው።
2. ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር የሙያ ስራውን ሲያከናውን፦
   ሀ) የህዝብ ጥቅም ላለባቸው አካላት የኦዲትና የማረጋገጫ አገልግሎት ሥራዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ቦርዱ ያስቀመጣቸው በአነስተኛ መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ማሟላት፤ እና

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና የሙያ ሥነ ምግባር ደንቦችን ማክበር አለበት፡፡

3. ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር የሙያ ሥራውን ሲያከናውን ቦርዱ ለተመሰከረላቸው ኦዲተሮች ባወጣቸው የተለዩ የኦዲት ደረጃዎች ያስቀመጣቸውን አነስተኛ መስፈርቶች ማክበር አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ደረጃዎችን የመቀበል፣ የማስማማት እና የማሻሻል ስነስርዓት

### 13. ምክክር

1. ቦርዱ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ እና ኦዲት ደረጃዎችን ከመቀበሉ፣ ከማስማማቱ ወይም ከማሻሻሉ በፊት ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማድረግ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ እና የኦዲት ደረጃዎችን ሲያወጣ አግባብነት ካለው ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ጋር ሊመካከር ይችላል፡፡

### 14. የህዝብ አስተያየት

1. ቦርዱ ማንኛውንም ደረጃ ሲያወጣ ወይም ሲያሻሽል የምክክሩ አንድ አካል አድርጎ በመውሰድ የህዝቡን አስተያየት መቀበል እንዲቻል በቦርዱ ድረገጽ እና ሀገር አቀፍ ሥርጭት ባላቸው ከሁለት ባላነሱ ዕለታዊ ጋዜጣዎች ላይ ቢያንስ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ማስታወቂያ በማውጣት እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ህዝቡ በደረጃዎቹ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ መጋበዝ አለበት፡፡
2. አስተያየት መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቦርዱ የሚያወጣው ማስታወቂያ ከሚቀይበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በሚቆጠሩ 60 ቀናት ውስጥ አስተያየቱን በጽሑፍ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. ቦርዱ ደረጃዎችን ለማውጣት ወይም ለማሻሻል ሲወስን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተሰጡትን የህዝብ አስተያየቶች ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡

### 15. ደረጃዎችን ይፋ ስለማድረግ

1. ቦርዱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያጸድቃቸውን ደረጃዎች "የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ እና የኦዲት ደረጃዎች ይፋ ማስታወቂያ"

የሚል ስያሜ ያለው ማስታወቂያ በድረገፁ ላይ በማውጣት ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲያውቋቸው ማድረግ አለበት፡፡

2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው በተጨማሪ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ከሁለት ባላነሱ ዕለታዊ ጋዜጣዎች ላይ ቢያንስ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ማስታወቂያ በማውጣት እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ደረጃዎቹን ህዝቡ እንዲያውቃቸው ማድረግ አለበት፡፡

16.<u>**የደረጃዎች ማስታወቂያ ይዘት**</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 መሠረት የሚወጣው ማስታወቂያ የሚከተሉትን በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፡--

1. የወጡትን አዳዲስ ደረጃዎች ወይም በሥራ ላይ ባሉት ደረጃዎች ላይ የተደረጉትን ማሻሻያዎች፤
2. ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በሥራ ላይ እንዳይውሉ የተደረጉትን ወይም የተሰረዙትን ደረጃዎች፣
3. አዳዲስ ደረጃዎች እና በደረጃዎች ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች ሥራ ላይ የሚውሉበትን ቀን እና የሚመለከታቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት፡፡

17. <u>**ቦርዱ የሚያወጣቸው ደረጃዎች ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር ያለመጣጣም**</u>

ቦርዱ በአለም አቀፍ ደረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን በመከተል ደረጃዎችን ሳያሻሽል፣ ለጊዜዉ ስራ ላይ እንዳይውሉ ሳያደርግ ወይም ሳያነሳ በመቅረቱ ምክንያት ቦርዱ ባወጣቸው ወይም ባሻሻላቸው የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ እና የኦዲት ደረጃዎች እና በአለም አቀፉ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ እና የኦዲት ደረጃዎች መካከል ልዩነት ከተፈጠረ ቦርዱ የተፈጠረውን ልዩነትና አለም አቀፍ ደረጃዎቹን ላለማሻሻል ለጊዜው በሥራ ላይ እንዳይውሉ ለማድረግ ወይም ላለማንሳት የወሰነበትን ምክንያት ለባለድረሻ አካላት በዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ፈቃድና አክሬዲቴሽን ስለመስጠት

### 18.ለፐብሊክ ኦዲተር ፈቃድ ስለመስጠት

1. በንግድ ሕጉ ወይም በሌላ ማንኛውም ሕግ የተደነገገው ቢኖርም፣ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርዱ እንደ ፐብሊክ ኦዲተር እንዲሰራ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር የህዝብ ጥቅም ላለባቸው አካላት ኦዲተር ሆኖ መሾም ወይም ሌላ ማንኛውንም የኦዲት አገልግሎት መስጠት አይችልም።
2. ማንኛውም የኦዲት ሙያ ሥራ ምሥክር ወረቀት ያለው ሰው ፐብሊክ ኦዲተር ሆኖ ለመሥራት ማመልከት ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያ ደረሰኝ እና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ከሚገለጽ መረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።
4. ቦርዱ የቀረበለትን ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ አመልካቹ፡-

   ሀ) በኢንስቲትዩቱ የተሰጠ የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ያለው መሆኑን፤

   ለ) የኦዲት ድርጅት አባል ወይም ሠራተኛ ከሆነ እና ድርጅቱ አግባብ ያለው የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት እንዳለው ማስረጃ ያቀረበ እንደሆነ፤

   ሐ) ቦርዱ የሚያወጣው መመሪያ የሚያስቀምጣቸውን መሥፈርቶችን ያሟላ መሆኑን፤ እና

   መ) ቦርዱ በሚወስነው የገንዘብ መጠን የሙያ መድን ዋስትና ያቀረበ መሆኑን፤ ካረጋገጠ በኋላ የህዝብ ጥቅም ላለበት አካል ኦዲተር ሆኖ መሥራት የሚያስችል ፈቃድ ይሰጠዋል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የተሰጠ ፈቃድ የሚቆይበት ጊዜ በቦርዱ ይወሰናል፡፡
6. ቦርዱ የኦዲተሩን ስምና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በፐብሊክ ኦዲተሮች መዝገብ ላይ ይመዘግባል።

### 19.ፈቃድን ስለማሳደስ

1. ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር የፈቃድ አገልግሎት ጊዜው ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት ቦርዱ በሚያወጣው ፎርም እና አኳኋን የጽሑፍ ማመልከቻ በማስገባት ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፡፡

2. አመልካቹ የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶቹን ጠብቆ መገኘቱን ሲያረጋግጥ ቦርዱ ፈቃዱን ያድስለታል፡፡
3. ቦርዱ የአንድ ፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የቀረበን የፈቃድ ዕድሣት ማመልከቻ ሳያይ የፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜ ካለፈ ማመልከቻውን አይቶ እስኪወስን ድረስ የፈቃዱ እና ምዝገባው አገልግሎት የሚቀጥል ሆኖ ፍቃዱን ሊያድስ የፈቃዱና ምዝገባ ጊዜ ካለቀበት ቀን ጀምሮ እንደታደሰ ይቆጠራል።
4. አመልካቹ፡-
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (4) የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፣ ወይም
   ለ) የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ እንዲሠራ የተሠጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከተወሰደ ከታገደ ወይም ከተሠረዘ፤

   ቦርዱ የፐብሊክ ኦዲተሩን ፈቃድ እና ምዝገባ ማደስ የለበትም፡፡

20.<u>**ፈቃድን ስለመሰረዝ**</u>

ፐብሊክ ኦዲተር ሆኖ እንዲሠራ ፈቃድ የተሠጠው ሰው ፈቃዱን እንዲያገኝ ያስቻሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (4) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች የተጓደሉ እንደሆነ ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

21.<u>**በፀደቀ የኦዲት ድርጅት ስም ስለመሥራት**</u>

1. ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር በራሱም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር በሽርክና ቦርዱ ስሙን ባላፀደቀው የኦዲት ድርጅት ስም እንደ ኦዲተር ሆኖ መሥራት አይችልም።
2. በራሱ ስም ወይም ከሌሎች ጋር በሽርክና በኦዲት ድርጅት ስም መሥራት የሚፈልግ ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር ቦርዱ የሚያወጣውን ፎርምና ሥነ ሥርዓት በመከተል በጽሑፍ ማመልከት ይኖርበታል።
3. ከሌሎች ሰዎች ጋር በሽርክና በኦዲት ድርጅት ስም የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ፐብሊክ ኦዲተር የኦዲት ድርጅቱን ስም ለማስመዝገብ የሚያቀርበው ማመልከቻ አንድ አካል አድርጎ ከሽሪኮቹ ውስጥ ፐብሊክ ኦዲተር የሆኑትን ካልሆኑት ለይቶ ለቦርዱ መግለጽ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የክፍያ ደረሰኝ፣ ቦርዱ በሚወስነው የገንዘብ መጠን ከተገባ የሙያ መድን ዋስትና ማስረጃ እንዲሁም የኦዲት ድርጅቱ በሥራ ላይ ከሚያውለው የጥራት ማረጋገጫ አሠራር እና በቦርዱ መመሪያ መሠረት ከሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎች ጋር መቅረብ አለበት፡፡
5. ቦርዱ በኦዲት ድርጅቱ የቀረበው ስም ወይም የስም ለውጥ፤-
   ሀ) ቦርዱ ቀድሞ ካፀደቀው ሌላ የኦዲት ድርጅት ስም ጋር አንድ ከሆነ፤
   ለ) ከሌላ የኦዲት ድርጅት ስም ጋር በጣም የተቀራረበ ከመሆኑ የተነሳ ሊያምታታ የሚችል ከሆነ፤
   ሐ) በቦርዱ ዕይታ መሠረት የሚያሳስት ወይም የህዝብን ጥቅም የሚፃረር ከሆነ፤ ወይም
   መ) የንግድ ህጉን የሚቃረን ከሆነ፤

   እንዲፀድቅ የቀረበውን የኦዲት ድርጅት ስም ወይም የስም ለውጥ አያፀድቅም፡፡
6. በዚህ አንቀጽ መሠረት ስሙ የፀደቀ የኦዲት ድርጅት የነባር አባል መልቀቅና አዲስ አባል መቀበልን ጨምሮ ሽሪኮቹን በሚመለከት የሚደረግን ማንኛውም ለውጥ ለቦርዱ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

22. <u>ያልተፈቀደለ የኦዲት ስራ ስለመስራት</u>

1. ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር ወይም የኦዲት ድርጅት ምዝገባው በቦርዱ የታገደ ወይም እንደፐብሊክ ወይም እንደተመሠከረለት ኦዲተር ሆኖ እንዳይሠራ የታገደን ሰው ከኦዲት ሥራ ጋር በተያያዘ መቅጠር አይችልም።
2. ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር፡-
   ሀ) ሽርክናን በሚመለከት የኦዲት ድርጅቱን ሽሪኮች ስምና ማዕረግ፤
   ለ) የኦዲት ድርጅቱ አርማ ያለው ወረቀት የሚጠቀም ከሆነ የወረቀቱን ቅጅ፤
   ሐ) የኦዲት ድርጅቱ ሥም ከክልላዊ ወይም አለም አቀፋዊ የኦዲት ኔትወርክ ስም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ወይም የኔትወርኩን ስም የሚያካትት ከሆነ ወይም የኦዲት ድርጅቱ ባለዓርማ ወረቀት ወይም ሌላ ማንኛውም ሰነድ የክልል ወይም የአለም አቀፍ ኦዲት ኔትወርክ አካል መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ፣ ከክልላዊው ወይም አለም አቀፋዊው ኔትወርክ ጋር ያለውን ትስስርና ግንኙነት ዓይነት፤ ለቦርዱ አስቀድሞ ካላሳወቀ በስተቀር በኦዲት ድርጅት ስም የኦዲት ሥራ መሥራት አይችልም።

23.<u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት እንደፐብሊክ ኦዲተር የተመዘገበ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) እርሱ ወይም የእርሱ ኦዲት ድርጅት እንደፐብሊክ ኦዲተር ሆኖ በሚሠራበት ስም፣ አደረጃጀት ወይም አድራሻ የሚኖርን ለውጥ ለቦርዱ፣ ለኢንስቲትዩቱ እና እንደፐብሊክ ኦዲተር በመሆን ለሚሠራለት ማንኛውም ሰው ለውጡ በተደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፤

ለ) ፐብሊክ ኦዲተር ሆኖ ራሱ ወይም ድርጅቱ የሚሠራለት ወይም እንዲሠራለት ለመሾም የፈለገ ማንኛውም ሰው ሲጠይቀው ጥያቄው በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት አለበት፡-

1) የሚሠራበትን ማንኛውም የኦዲት ድርጅት ስም ወይም የራሱ ማዕረግ፤
2) ሽሪክ ሆኖ የሚሠራበትን የማንኛውንም የሽርክና ማህበር የሥራ ቦታ፤
3) የሽሪኮቹን ሙሉ ስም፤
4) ዜግነቱን፤
5) ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ከሆነ ስሙን እንዲሁም የአባቱንና የአያቱን ስም፣ የውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ የመጀመሪያ ስሙን ወይም የስሙን የመጀመሪያ ፊደል እና አሁን የያዘውንና የቀድሞ የቤተሰብ ስሙን፤ እና
6) መደበኛ የሥራና የመኖሪያ አድራሻውን፡፡

2. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በሽርክና የሚሠሩ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው መረጃ በኦዲት ድርጅቱ ስም ሊተላለፍ ይችላል፤ ይህም በሚሆንበት ጊዜ እያንዳንዱ የሽርክና ማህበሩ አባል የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንዳሟላ ተደርጎ ይቆጠራል።

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ “የቀድሞ የቤተሰብ ስም” የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን አያካትትም፡-

ሀ) ጉዲፈቻን በተመለከተ ጉዲፈቻ ከመደረጉ በፊት የነበረውን የቤተሰብ ስም፤

ለ) ማንኛውንም ሰው በተመለከተ ዕድሜው 18 ዓመት ከመሆኑ በፊት ወይም ከ20 ዓመት በፊት ጀምሮ የተለወጠ ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የቤተሰብ ስም፣ ወይም

ሐ) ያገባች፣ የፈታች ወይም ባሏ የሞተባትን ሴት በተመለከተ ከማግባቷ በፊት የነበራትን የቤተሰብ ስም።

24.<u>የሂሳብ መግለጫና ሪፖርትን ስለመቆጣጠር</u>

1. ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት የቀረቡለት የሂሣብ መግለጫዎችና ሪፖርቶች ይህንን አዋጅ ጠብቀው የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሂሣብ መግለጫዎችን እና ሪፖርቶቹን ሊመረምር ይችላል፡፡
2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሂሣብ መግለጫና ሪፖርት ሲመረምር፡-

   ሀ) ከማንኛውም የሪፖርት አቅራቢው አካል የስራ ኃላፊ ወይም ዳይሬክተር፤

   ለ) የሪፖርት አቅራቢውን አካል የሂሣብ መግለጫና ሪፖርት ካዘጋጀ ሠራተኛ፤ ወይም

   ሐ) የሪፖርት አቅራቢውን አካል መግለጫና ሪፖርት ኦዲት የማድረግ ኃላፊነት ካለበት ፐብሊክ ኦዲተር፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም የኦዲት ድርጅት፤ ተጨማሪ መረጃና ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

25.<u>የኦዲተሮችን ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ስለማከናወን</u>

1. ቦርዱ ወይም ቦርዱ በጽሑፍ የሚወክለው የሌላ ሀገር የሂሣብ ሙያ ተቆጣጣሪ ድርጅት፣ አህጉራዊ ወይም ከፍለ አህጉራዊ የሂሣብ ሙያ ማህበር ወይም ሌላ አለም አቀፍ የሂሣብ ሙያ ማህበር የኦዲተሮችን የሥራ ጥራት መመርመር ይችላል፤ ለዚህም ዓላማ፡-

   ሀ) በኦዲተሩ፣ በሸሪኩ፣ በተቀጣሪው ወይም ከእርሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ባለው ሰው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለውን መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀትና ማህደር፣ ሠነድና መዝገብ ለመመርመርና ፎቶ ኮፒውን መውሰድ፣ ወይም አጭር ማስታወሻ መያዝ ይችላል፤

   ለ) ከኦዲተሩ ወይም ከሸሪኩ ወይም ከተቀጣሪው ወይም ከእርሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ካለው ሰው ማንኛውንም መረጃ ወይም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር ሸሪኩ፣ ተቀጣሪው ወይም ከእርሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው በቦርዱ ወይም ቦርዱ በጽሑፍ በወከለው ሰው ሲጠየቅ በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለው መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀት፣ ማህደር ወይም ሠነድ ማቅረብ አለበት፡፡

26. <u>ለሂሣብ ሙያ ማህበራት አክሬዲቴሽን እና ዕውቅና ስለመስጠት</u>

1. ቦርዱ እንደ ሂሳብ ሙያ ማህበር አክሬዲቴሽን እንዲሠጠው ማመልከቻ ለሚያቀርብና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች ለሚያሟላ ማንኛውም ድርጅት ዕውቅና ይሰጣል፡፡
2. ማንኛውም ድርጅት እንደ ሂሣብ ሙያ ማህበር አክሬዲቴሽን ለማግኘት ለቦርዱ አጥጋቢ በሆነ አኳኋን፡-

   ሀ) ቦርዱ የሚያወጣውን የሂሳብ እና ኦዲት ሙያ ዕድገት እና የአባላቱን የሙያ ብቃት መለኪያ መሥፈርት የሚያሟላ፣

   ለ) በቦርዱ ተቀባይነት ያለው አባላቱ ተከታታይነት ባለው የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና መሳተፋቸውን የሚያረጋግጥበት ተገቢ ሥልት ያለው፣

   ሐ) የአባላቱን ዲሲፕሊን መከታተልና መቆጣጠር የሚችልበት ዘዴ ያለው፣

   መ) ቦርዱ በሚያወጣው ፎርም መሠረት አባላቱን መዝግቦ የሚይዝ፣ እና

   ሠ) ቦርዱ በየጊዜው የሚያወጣቸውን ሌሎች መስፈርቶች የሚያሟላ፣

   መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የሂሣብ ሙያ ማህበር የተሰጠውን አክሬዲቴሽን ይዞ መቀጠል እንዲችል ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ቢያንስ በዓመት አንዴ ቦርዱን በሚያረካ አኳኃን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩትን የአክሬዲቴሽን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘቱን ማሳየት አለበት፡፡
4. ቦርዱ የሚያወጣቸውን መስፈርቶች ለሚያሟሉ በውጭ ሀገር ለተቋቋሙ የሂሳብ ሙያ ማህበራት ተቀባይነት ይሰጣል፡፡

27. <u>የህዝብን ጥቅም ማስጠበቅ</u>

1. ቦርዱ ማንኛውም የሂሣብ ሙያ ማህበር፡-

   ሀ) የህዝብ ጥቅምን የመጠበቅ ግዴታዎቹን መወጣቱን፣

   ለ) ከፍተኛ የሙያ እና የሥራ አፈጻጸም ደረጃውን መጠበቁንና ማራመዱን፣ እና

   ሐ) የሂሣብ ሙያን ማሳደጉን እና በመመሥረቻ ደንቡና በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ሌሎች የህዝብ ጥቅም ዓላማዎችን ማሳካቱን፣

   ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. ማንኛውም የሂሣብ ሙያ ማህበር የሂሳብ ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ፦
   ሀ) የህዝብ ጥቅም የማስጠበቅ ግዴታውን በመወጣት ረገድ ያከናወናቸውን ተግባራት የሚገልጽ ዓመታዊ ሪፖርት፤ እና
   ለ) ቦርዱ ባወጣው መመሪያ ባስቀምጣቸው የክዋኔ መለኪያዎች መሠረት ያከናወነውን ሥራ አፈጻጸም ምርመራና ግምገማ ሪፖርት፤

   ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የሂሣብ ሙያ ማህበር፡-
   ሀ) ከፍተኛ የሙያ ደረጃ የመጠበቅ፤
   ለ) የሂሣብ ሙያን የማሣደግ፤ ወይም
   ሐ) ሌሎች በዚህ አዋጅ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ የተመለከቱትን የህዝብ ጥቅምን የመጠበቅ ግዴታዎችን እየተወጣ ካልሆነ ወይም ካልተወጣ፤

   የሂሣብ ሙያ ማህበሩ ኃላፊነቱን በብቃት መወጣት የሚያስችለውን አሠራር እና ስነስርዓት መዘርጋቱን እስኪያረጋግጥ ድረስ ቦርዱ የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት አክሬዲቴሽኑን ሊያግድ ይችላል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የህዝብ ጥቅምን የመጠበቅ ግዴታ" ማለት ማንኛውም የሂሣብ ሙያ ማህበርና አባላቱ ቦርዱ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው አኳኋን ለደንበኞቻቸው ብቻ ሳይሆን ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚጠበቅባቸውን ተግባር በመወጣት ረገድ ያለባቸው ኃላፊነት ነው፡፡

28. <u>አክሬዲቴሽንን ስለመሰረዝ</u>

1. ማንኛውም የሂሳብ ሙያ ማህበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (3) በተደነገገው መሠረት የዕገዳ ትዕዛዝ በተላለፈለት በ30 ቀናት ውስጥ ለዕገዳው ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን ካላረመ ቦርዱ አክሬዲቴሽኑን ሊሰርዝ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ የሂሣብ ሙያ ማህበርን አክሬዲቴሽን ለመሰረዝ ሲወስን፡-
   ሀ) የሙያ ማህበሩ አክሬዲቴሽን የሚሠረዝበትን ምክንያት በመግለጽ ዕውቅናው ሊሠረዝ እንደሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለሚመለከተው የሂሳብ ሙያ ማህበር ይሰጣል፤
   ለ) ማህበሩ አክሬዲቴሽን ሊሠረዝብኝ አይገባም የሚልባቸውን የመቃወሚያ ምክንያቶች እንዲያቀርብ ከ21 ቀናት ያላነሰና ከ30 ቀናት ያልበለጠ ጊዜ ይሰጠዋል።

3. ቦርዱ የሂሳብ ሙያ ማህበሩ አክሬዲቴሽን መሠረዝ የህዝብ ጥቅምን፣ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ሙያን ወይም የማህበሩን አባላት ጥቅም በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል ብሎ ካመነ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ አክሬዲቴሽን ሳይሰረዝ እንዲቆይ ሊወሰን ይችላል፡፡
4. የማንኛውም የሂሣብ ሙያ ማህበር አክሬዲቴሽን፡-
   ሀ) ማህበሩ ህልውናውን ሲያጣ፤ ወይም
   ለ) ተገቢውን ክፍያ በቦርዱ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይከፍል ሲቀር፤

   ወዲያውኑ ያበቃል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የኦዲተሮች አሰራር ደረጃዎች

### 29. የኦዲተሮች ሪፖርትና አስተያየት

1. ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል እንደፐብሊክ ኦዲተር ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር በመሆን የሚሠራ ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) የኦዲት ሥራውን ከማናቸውም ዓይነት ተጽእኖ ነጻ ሆኖ ካላከናወነ፤
   ለ) የሪፖርት አቅራቢውን የሥራ እንቅስቃሴ እና የሂሳብ አመዘጋገብ እንዲሁም ሃብት እና ዕዳ በትክክልና በተሟላ ሁኔታ የሚያሳይ ተገቢ የሆነ የሂሳብ መዝገብ ከሌለ፤
   ሐ) ሥራውን በአግባቡ እንዲያከናውን ያስፈልጋል ብሎ የሚያምንበት ማንኛውንም መረጃ፣ ደረሰኞች እና ሌሎች ሰነዶች ካላገኘ፤
   መ) ኦዲትን በሚመለከት ሪፖርት አቅራቢው አካል የሚተዳደርበት ሕግ የሚያዘውን በሙሉ ካልጠበቀ፤
   ሠ) እንደ ሪፖርት አቅራቢው አካል የሥራ ባህሪ ተገቢውን ዘዴ በመጠቀም በሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መግለጫ እና አባሪዎች ላይ የሚታየው ፋይዳ ያለው ንብረትና ዕዳ በእርግጥም ስለመኖሩ ካላረጋገጠ፤
   ረ) እንደ ሪፖርት አቅራቢው አካል የሥራ ባህሪ የሚቻለውን ያህል የኦዲት ሥራ አከናውኖ የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መግለጫና አባሪዎች እውነተኛና ትክክለኛ መሆናቸውን ካላረጋገጠ፤ እና

ሰ) ባረጋገጠበት፣ ሪፖርቱን ባቀረበበት ወይም አስተያየቱን በሰጠበት ዕለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 የተመለከተው ጉልህ ጥፋት ተገቢ ነው ብሎ በሚያምንበት መልኩ መስተካከሉን ካላረጋገጠ፤

በስተቀር ከሪፖርት አቅራቢው አካል ጋር የሚገናኝ ማንኛውም የሂሳብ መግለጫና አባሪ ሁኔታው እንደሚጠይቀው የሪፖርት አቅራቢውን አካል የሥራ እንቅስቃሴ፣ የሥራውን ውጤትና በዚህ የሂሳብ መግለጫና አባሪ የተመለከቱትን ጉዳዮች ትክክለኛነት፣ ያሳያል፣ አጥጋቢ ነው ወይም በትክክል ያመላክታል ብሎ ማረጋገጫ መስጠት ወይም ሪፖርት ማድረግ ወይም አስተያየት መስጠት የለበትም፡፡

2. የማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ኦዲተር የሪፖርት አቅራቢው አካል በሚያቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት እራሱን ወይም ኃላፊዎቹንና ዳይሬክተሩን በሚመለከት በሕግ መሠረት እንዲገልጽ ከሚጠበቅበት ማንኛውም መረጃ ጋር በተያያዘ በሪፖርቱ የገለጸው ከሕጉ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## 30. አስተያየት ስለሚሰጥበት ጊዜ

1. ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ፐብሊክ ኦዲተር በኦዲተርነቱ ያከናወነውን ማንኛውንም ሥራ በሚመለከት የሚሰጠው ማረጋገጫ፣ የሚያቀርበው ሪፖርት ወይም የሚገልጸው አስተያየት ሥራውን ካጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አራት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
2. ኦዲተሩ ያከናወነውን ሥራ በሚመለከት ጉድለት የሌለበት ማረጋገጫ፣ ሪፖርት ወይም አስተያየት መስጠት፣ ማቅረብ ወይም መግለጽ ካልቻለ ጉድለት ያለበትን ማረጋገጫ፣ ሪፖርት ወይም አስተያየት ከነምክንያቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ መስጠት፣ ማቅረብ ወይም መግለጽ ያለበት ሆኖ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ጉድለት የሌለበት ማረጋገጫ ሪፖርት ወይም አስተያየት መስጠት፣ ማቅረብ ወይም መግለጽ ያልቻለበትን ማናቸውንም ምክንያት በዚሁ ማረጋገጫ ሪፖርት ወይም አስተያየት ውስጥ ማካተት ይችላል፡፡

## 31. ጉልህ ጥፋት

1. ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ፐብሊክ ኦዲተር በመሆን የሚሰራ ሰው በሥራው ሂደት ጉልህ ጥፋት መፈጸሙን ሲያረጋግጥ ወይም መፈጸሙን እንዲያምን የሚያደርግ ምክንያት ሲኖረው በአፋጣኝ፡-

ሀ) የተፈጸመውን ጉልህ ጥፋት በዝርዝር በመግለጽ ለሪፖርት አቅራቢው አካል ኃላፊዎችና ለሁሉም የቦርዱ አባላት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከቱትን ሰዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ማሰታወቂያው እንደደረሳቸው በጽሑፍ እንዲያረጋግጡና አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ እንዲወስዱ መጠየቅ አለበት፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ጉልህ ጥፋት" ማለት ማንኛውንም ሪፖርት አቅራቢ አካል በማስተዳደር ወይም በመቆጣጠር ሂደት ሕግን በመተላለፍ በማድረግ ወይም ባለማድረግ በማንኛውም ሰው የተፈጸመ የማጭበርበር ወይም የስርቆት ተግባር፣ ወይም በሪፖርት አቅራቢው አካል፣ በሸሪኩ፣ ባለአክስዮን ወይም አበዳሪ ወይም በሪፖርት አቅራቢው አካል ላይ የገንዘብ ጥቅም ባለው ሌላ ማንኛውም ሰው የተጣለን እምነት የማጉደል ተግባር፣ ወይም የሪፖርት አቅራቢውን አካል፣ የሥራውን አካሄድ ወይም አመራር በሚመለከት በማንኛውም ሕግ እንደ እምነት ማጉደል የሚቆጠር በሪፖርት አቅራቢው አካል ወይም በባለአክሲዮኖቹ ወይም በሸሪኮች ወይም አበዳሪዎች ወይም በሪፖርት አቅራቢው አካል ላይ የገንዘብ ጥቅም ባለው ሌላ ማንኛውም ሰው ላይ ጉልህ የገንዘብ ኪሳራ ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ተግባር ነው፡፡

3. የተመሰከረለት አዲተር ወይም ፐብሊክ ኦዲተር ባገኘው መረጃ መሠረት ጉልህ ጥፋት አለመፈጸሙን ወይም በመፈጸም ላይ አለመሆኑን ወይም የሪፖርት አቅራቢው አካል የስራ ኃላፊዎች ወይም የቦርዱ አባላት ጉልህ ጥፋቱን ለማረም አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰዳቸውን ካላረጋገጠ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት የሰጠው ማስታወቂያ በተላከ በ30 ቀናት ውስጥ ስለተፈጸመው ጉልህ ጥፋት አስፈላጊ ነው ብሎ ከሚያምንበት ተጨማሪ መረጃ ጋር ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበለትን ማንኛውንም መረጃ ለፍትህ ሚኒስቴር[38] ወይም አግባብነት ላለው ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን፣ ለሪፖርት አቅራቢው አካል ሸሪኮች፣ ባለአክሲዮኖች፣ አበዳሪዎች ወይም በሪፖርት አቅራቢው አካል ላይ የገንዘብ ጥቅም ላለው ሌላ ማንኛውም ሰው ሊገልጽ ይችላል፡፡

[38] በ25/8 (2011) አ. 1097 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ በሚል ይነበብ፡፡

5. ማንኛውም ኦዲተር ጉልህ ጥፋት መፈጸሙን ወይም እየተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

32. <u>ከመክሠር በፊት የተገኘ ጉልህ ጥፋት</u>

አንድ የሪፖርት አቅራቢ አካል የመሸጋገሪያ ወይም የመጨረሻ የመክሰር ወይም የሂሳብ ማጣራት ሂደት ውስጥ ከመግባቱ በፊት የዚህ ሪፖርት አቅራቢ አካል ኦዲተር በመሆን የሚሠራ የተመሠከረለት ኦዲተር ወይም ፐብሊክ ኦዲተር፡-

1. የሪፖርት አቅራቢው አካል ከስራል በተባለበት ወይም በተዘጋበት ዕለት ወይም ከዚያ በፊት በሪፖርት አቅራቢው አካል የሥራ ሂደት ጉልህ ጥፋት መፈጸሙን ወይም በመፈጸም ላይ መሆኑን፤ ወይም
2. ተፈጽሟል ወይም እየተፈጸመ ነው ብሎ ማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖረውና ይህ ጉልህ ጥፋት በሪፖርት አቅራቢው አካል ወይም በሸሪኮቹ፣ በባለአክሲዮኖች፣ በአበዳሪዎች ወይም በሪፖርት አቅራቢው አካል ላይ የገንዘብ ጥቅም ባለው ሌላ ማንኛውም ሰው ላይ ከፍተኛ የገንዘብ ኪሣራ ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል መሆኑን፤ ወይም
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) በተደነገገው መሰረት ሪፖርት አቅራቢው አካል ከሥራል በተባለበት ወይም ከተዘጋበት ዕለት በፊት ስለ ጥፋቱ ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑን፤

   ካረጋገጠ ስለ ጥፋቱ በዝርዝር በመግለጽ ወዲያውኑ እንደ ጊዜያዊ ባለአደራ ወይም እንደ ባለአደራ ወይም እንደ ጊዜያዊ ሂሣብ አጣሪ ወይም የሂሣብ አጣሪ በመሆን ለተሾመው ሰው ሪፖርት ማቅረብ እና የዚህን ሪፖርት ቅጅ ለሪፖርት አቅራቢ አካል ኃላፊ እና ለቦርዱ መላክ አለበት፡፡

33. <u>ስለ ኦዲተር ነጻነት</u>

1. ማንኛውም የተመሠከረለት ኦዲተር ወይም ፐብሊክ ኦዲተር ሥራውን ሲያከናውን፡-
   ሀ) ቦርዱ ወይም ኢንስቲትዩቱ የሚያወጣውን የስነ ምግባር ደንብ የሚፃረር ማንኛውንም ተግባር መፈጸም፤ ወይም
   ለ) እንደ ኦዲተር በእይታም ሆነ በአዕምሮ ነፃነቱን በሚጎዳ ማንኛውም ተግባር ላይ መሳተፍ፤

   የለበትም፡፡

9. ማንኛውም የተመሠከረለት ኦዲተር፣ ፐብሊክ ኦዲተር ወይም ሸሪኩ ወይም እሱ የቀጠረው ማንኛውም ሰው ወይም በእርሱ ቅርብ ክትትል ወይም ቁጥጥር ሥር የሚሠራ ማንኛውም ሰው ለአንድ ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሣብ አመዘጋገብና አያያዝ ኃላፊ ከሆነ፣ ከተመዘገበው ሂሣብ በመነሣት የሂሣብ መዝጊያ ምዝገባ ከማከናወን፣ በሂሣብ ማስተካከያ ምዝገባ ከመርዳት ወይም የሃብትና ዕዳ መግለጫዎች፣ የሌሎች ሂሣቦች መግለጫዎች ወይም ሌሎች የሂሣብ ሰነዶች ከማዘጋጀት በስተቀር ከሪፖርት አቅራቢው አካል ሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ ማረጋገጫ ሲሰጥ ወይም ሪፖርት ሲያቀርብ የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መዝገብና የሂሳብ አያያዝ በራሱ ወይም በሸሪኩ ቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ሥር በሚሠራ ሰው ሃላፊነት መከናወኑን ማመልከት አለበት፡፡
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ ለአንድ ሪፖርት አቅራቢ አካል እንደ ሂሣብ ባለሙያና እንደ ኦዲተር ሆኖ መሥራት የሚፈቀድለት ተደርጎ መተርጎም የለበትም፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን የሚተላለፍ ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር በቦርዱ የዲሲፐሊን ችሎት ክስ ቀርቦበት በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት ድንጋጌዎች መሠረት የዲሲፐሊን እርምጃ ይወሰድበታል።
12. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን የሚተላለፍ ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር በኢንስቲትዩቱ የዲሲፐሊን ችሎት ክስ ቀርቦበት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው የኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሰረት የዲሲፐሊን እርምጃ ይወስድበታል።
13. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ፡-

ሀ) “የአእምሮ ነጻነት” ማለት አንድ ኦዲተር ታማኝ፣ ገለልተኛና ጥንቁቅ ሆኖ መሥራት የሚያስችለውን ሙያዊ አቋም ከሚሸረሽር ተጽእኖ ነጻ ሆኖ አስተያየት መስጠት የሚያስችለው የአእምሮ ሁኔታ ነው፤

ለ) “የእይታ ነጻነት” ማለት አንድ እውቀቱ ያለውና ምክንያታዊ የሆነ ታዛቢ የአንድ ኦዲት ድርጅት ወይም የኦዲት ቡድን አባል ታማኝነት፣ ገለልተኝነትና ጥንቃቄ ተሸርሽሯል ብሎ እንዲያምን ምክንያት የሚሆን ማንኛውንም ጥርጣሬ የሚጋብዝ ሁኔታ ወይም ድርጊት ማስወገድ ነው።

14. <u>ኦዲተርን ስለሚያጋጥም የጥቅም ግጭት</u>

ማንኛውም ኦዲተር ወይም የኦዲት ድርጅት በኦዲተርነት ከሚያገለግለው ሪፖርት አቅራቢ አካል ጋር የጥቅም ግጭት ሊኖረኝ ይችላል ወይም የሙያ ነጻነቴን የሚያሳጣ ሁኔታ አለ ብሎ ሲያምን የሪፖርት አቅራቢ አካሉን ሂሣብ ከመመርመር ራሱን ማግለል አለበት፡፡

15. <u>በኦዲተሮች ስለሚፈፀም የሙያ ጥፋት</u>

1. በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሰረት ፐብሊክ ኦዲተር ወይም የተመሰከረለት ኦዲተር በመሆን የተመዘገበ ማንኛውም ሰው፦

   ሀ) እንደ ፐብሊክ ኦዲተር ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለአንድ ሪፖርት አቅራቢ አካል ያለበትን ግዴታ በሚጠበቅበት ጥንቃቄና የሙያ ብቃት መወጣት ሳይችል ቢቀር፣ ወይም

   ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ በቀረበ መነሻ የሚሆን ማስረጃ ላይ በመመስረት በሥራው ቸልተኛ ሆኗል ብሎ ማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር፣ ሙያውን በሚገባ ጥንቃቄና ብቃት መወጣት ባልቻለበት ወይም ቸልተኛ በሆነበት ጉዳይ በወንጀል ተጠያቂ ወይም የተከሰሰ ወይም ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ቢሆንም ባይሆንም ቦርዱ በዚህ አዋጅ በክፍል ሰባት መሠረት ጉዳዩን ሊመረምር፣ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሰረት እንዲመረመር ለኢንስቲትዩቱ ሊመራ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበለት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ካገኘው በዚህ ሰው ላይ በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት የተመለከተውን ስነ ሥርዓት በመከተል በዚህ አዋጅ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነውን ተገቢውን ቅጣት ሊወስንበት ይችላል፡፡

3. አስተያየቱን የገለጸው ወይም ማረጋገጫውን የሰጠው ወይም ሪፖርቱን ወይም መግለጫውን ያዘጋጀው ወይም መግለጫውን፣ ሂሣቡን ወይም ሰነዱን ያረጋገጠው ከቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ ሃሳብ፣ በቸልተኝነት ወይም ለማጭበርበር በማሰብ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሰረት ፐብሊክ ኦዲተር ወይም የተመሰከረለት ኦዲተር በመሆን የተመዘገበ ማንኛውም ሰው መደበኛ ሥራውን ሲያከናውን በገለጸው አስተያየት

ወይም በሰጠው ማረጋገጫ ወይም ባዘጋጀው ሪፖርት ወይም መግለጫ፣ ወይም ባረጋገጠው መግለጫ፣ ሂሣብ ወይም ሰነድ ምክንያት ሊከሰስ አይችልም፡፡

## ክፍል ሰባት

## ሕግ ማስከበር

16. **የመመርመር ሥልጣን**

1. ቦርዱ ተገቢው የሙያ ብቃት ያላቸው ሰዎች እርሱን በመወከል የሚከተሉትን ጉዳዮች በሚመለከት የምርመራ ሥራ እንዲያከናውኑ ሊፈቅድ ይችላል፡-

   ሀ) በፐብሊክ ኦዲተር ላይ የሚቀርብን ማንኛውንም የእምነት ማጉደል ተግባር፣ የቸልተኝነት፣ የሙያ ስነምግባር ጥፋት ወይም የማንኛውንም ተነቃፊ ተግባር ቅሬታን፤

   ለ) በፐብሊክ ኦዲተር የሚፈጸምን የሙያ ስነምግባር መተላለፍን፤

   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 መሠረት ቦርዱ እንዲያውቀው የተደረገ ማንኛውንም ጉልህ ጥሰትን፤

   መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሠረት ማቅረብ የሚገባውን ማንኛውንም ሪፖርት ወይም ሰነድ አለማቅረብን፤

   ሠ) ፐብሊክ ኦዲተር ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችለውን ብቃት ይዞ መቆየት አለመቻልን፣

   ረ) ማንኛውንም ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የመተላለፍ ተግባርን፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በሚመለክት ቦርዱ እራሱ ምርመራ የሚያካሂድ ከሆነ የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው መርማሪውን ይሾማል።

3. የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ለተመርማሪው ኦዲተር ወይም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ስለቀረበበት ቅሬታ ይዘት ማሳወቅ አለበት፡፡

4. መርማሪ ሹሙ ማንኛውንም ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪዎች ተጥሰዋል በሚል የሚቀርብን ቅሬታ፣ ያልተገባ ተግባር ክስ ወይም ሌላ ማንኛውም ክስ ለመመርመር የሚከተሉትን ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ) ክሱ ወይም ቅሬታው በቀረበበት የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ወይም በቀድሞው ወይም በአሁኑ ፐብሊክ ኦዲተር ወይም የህዝብ ጥቅም ባለበት አካል ኃላፊዎች ወይም በኦዲተሩ ሸሪክ፣ ሠራተኛ ወይም ከኦዲተሩ ጋር የሥራ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች እጅ ወይም ቁጥጥር ስር የሚገኙን መዝገብ፣ ሰነድ ወይም መረጃ መመርመር ወይም እንዲቀርብለት መጠየቅ፤

ለ) የዚህ ዓይነቱን መዝገብ፣ ሰነድ ወይም መረጃ ይዞ ማቆየት ወይም ቅጂውን ማስቀረት እና በቀረበው ቅሬታ ወይም ክስ ላይ ለሚከናወን ምርመራ ወይም ስሚ በማስረጃነት መጠቀም፣

ሐ) ለቀረበው ክስ ወይም ቅሬታ መሠረት ስለሆነው ድርጊት መረጃ ያለውን ማንኛውንም ሰው መጠየቅ፤ እና

መ) ለማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት የቀረበን የሂሳብ መግለጫና ሪፖርት ማየት፡፡

5. ማንኛውም ሰው የተጠየቀውን ጥያቄ መመለስ ወይም ማስረጃ መስጠት ሊያስወነጅለኝ ይችላል ብሎ የሚያምን ከሆነ ጥያቄውን ያለመመለስ ወይም የተጠየቀውን ማስረጃ አለመስጠት ይችላል፡፡

6. ሕጉ መረጃ ይፋ እንዲሆን በሚያዘው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ፐብሊክ ኦዲተሩ ወይም ሸሪኩ ወይም ሠራተኛው ወይም ከኦዲተሩ ጋር የሥራ ግንኙነት ያለው ሰው፣ የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ወይም የእርሱ ኃላፊዎች የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ማንኛውንም መረጃ እንዲያቀርቡ የሚያስገድድ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡-

ሀ) በንግድ ሕጉ ወይም በሥራ ላይ ባለ ሌላ ሕግ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ማንኛውንም መረጃ፤ እና

ለ) አንድ ሰው እንደ ሕግ ባለሙያነቱ የተቀበለው ወይም የተሰጠው ጥበቃ የሚደረግለት መረጃ፡፡

17.<u>የሕግ መተላለፍን በተመለከተ ለቦርዱ ስለሚቀርብ ሪፖርት</u>

በሌላ ሕግ የተመለከተ ድንጋጌ ቢኖርም የማንኛውም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ተቆጣጣሪ የሆነ የመንግስት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ የሚጥስ ተግባር በቀድሞው ወይም በሥራ ላይ ባለው ፐብሊክ ኦዲተር ተፈጽሟል ብሎ እንዲያምን የሚያስችል ግልጽ ማስረጃ ሲኖር ድርጊቱ እንዲመረመር ይህንኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

18.<u>ክስ ስለመመስረት</u>

1. መርማሪ ሹሙ ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ የሚጥስ ተግባር ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ጥሰቱን በፈጸመው ፐብሊክ ኦዲተር፣ የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ላይ ክስ እንዲመሰረት ለቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከመርማሪ ሹሙ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡
3. የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ክስ ለመመስረት ከወሰነ በምርመራ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ያልነበሩ ከመካከላቸው አንዱ የሕግ ባለሙያ የሆነ ሶስት የቦርዱን ሠራተኞች በክስ ሰሚነት ይሰይማል።
4. ክሱ የቀረበበት የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በክሱ ሂደት በጠበቃ አማካኝነት መከራከር ይችላል፡፡

19. <u>የዲሲፕሊን ክስ ስነስርዓት</u>

1. የክስ ሰሚዎች ከተከራካሪ ወገኖች በአንዳቸው ጠያቂነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 ለተመለከተው የክስ ስሚ፤-
   ሀ) በመሰማት ላይ ካለው ክስ ጋር የተያያዘ ጠቃሚ መረጃ ሊሰጥ ይችላል ብሎ የሚያምንበትን ሰው ወይም ለክሱ አግባብነት ያለው ማንኛውንም መዝገብ፣ መረጃ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ነገር ይዟል ወይም በቁጥጥሩ ሥር አለ ብሎ ለሚገምተው ሰው መጥሪያ በመስጠት በመጥሪያው ላይ በተመለከተው ቦታ እና ጊዜ እንዲቀርብ በማድረግ ሊመረምሩ ወይም የተጠቀሱትን ሰነዶች ወይም ሌሎች ማስረጃዎች እንዲያቀርብ ሊያደርጉ ወይም የቀረቡትን ሰነዶች ወይም ሌሎች ማስረጃዎች ለምርመራ ሊይዙ ይችላሉ፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት መጥሪያ የደረሰው ሰው ቃለ መሃላ እንዲፈጽም ያደርጋሉ ወይም የማረጋገጫ ቃሉን ይቀበላሉ፤ የሚቀርብለትን ጥያቄ እንዲመልስ እና በእጁ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለን ማንኛውንም መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርብ ያደርጋሉ፡፡

2. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ሰው ስለቀረበበት ክስ ይዘት የማወቅ እና በራሱ ወይም በጠበቃው አማካኝነት ቀርቦ ማስረጃውን የማቅረብ፣ ምስክሮቹን በመጥራት ቀጥተኛ ጥያቄ መጠየቅና እና ለከሳሽ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት ይኖረዋል።

3. ማንኛውም ሰው በክስ ሰሚዎች ፊት እንዲቀርብ ወይም ማንኛውንም መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚሰጠው መጥሪያ ቦርዱ በሚወስነው ፎርም መሠረት የሚዘጋጅ እና ከክስ ሰሚዎች በአንዱ መፈረም ያለበት ሆኖ የመጥሪያ አሰጣጥ ስርዓቱ በመደበኛ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ መጥሪያ በሚደርስበት ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

4. በአግባቡ ቃለ መሃላ ፈጽሞ ወይም የማረጋገጫ ቃሉን ሰጥቶ በሕግ አግባብ ለቀረበለት ጥያቄ ሀሰተኛ መልስ የሰጠ ወይም እውነት አለመሆኑን እያወቀ በማናቸውም ጉዳይ ላይ ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ ምስክር በወንጀል ሕጉ መሠረት በሀሰት በመመስከር ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5. ማንኛውም ሰው በማስረጃነት የቀረበን የአንድ ሰነድ ቅጂ የሰነዱ ትክክለኛ ቅጂ አለመሆኑን የማስረዳት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም የዲሲፕሊን ምርመራ ወይም ክስ አንድ ሰነድ በትክክል የተፈጸመ መሆኑን ወይም የሰነዱን ይዘት ወይም ቃል ወይም ትክክለኝነት ለማስረዳት የሚቀርብ የዋናው ሰነድ ቅጂ እንደ ዋናው ሰነድ በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

20. <u>ያለመቅረብ</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው በአግባቡ መጥሪያ ደርሶት ያለበቂ ምክንያት በመጥሪያው ላይ በተመለከተው ቦታ እና ሰዓት ባይገኝ ወይም ክስ ሰሚዎች ሳይፈቅዱለት ወይም ሳያሰናብቱት በክሱ ምርመራ ወይም ስሚ መገኘቱን ቢያቋርጥ ወይም በምስክርነት ቃለ መሃላ ለመፈጸም ወይም የማረጋገጫ ቃል ለመስጠት ፈቃደኛ ባይሆን ወይም ያለበቂ ምክንያት በምርመራ ወይም በመሰማት ላይ ያለውን ክስ በሚመለከት በሕግ

አግባብ የቀረበለትን ማንኛውም ጥያቄ የእውቀቱን ወይም ያመነበትን ያህል ለመመለስ ፍቃደኛ ሳይሆን ቢቀር ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን በእጁ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለን ማንኛውንም መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ ሳያቀርብ ቢቀር አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2. በመደበኛ ፍርድ ቤት ለምስክርነት ወይም ማንኛውንም መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርብ መጥሪያ ለደረሰው ሰው በሕግ የተሰጡ መብቶች በዚህ አዋጅ መሠረት ለምስክርነት ወይም ማንኛውንም መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርብ መጥሪያ ለደረሰውም ሰው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

21.**<u>የቅጣት አወሳሰን</u>**

1. ክስ ሰሚዎች በክሱ ስሚ ሂደት የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከመረመሩ በኋላ ተከሳሽ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ መተላለፍ ወይም አለመተላለፉን ይወስናሉ።
2. ክስ ሰሚዎች ተከሳሹ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ ተላልፏል ብለው ካመኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 እና 43 መሠረት የቅጣት ውሳኔ ይሰጣሉ።
3. ተከሳሹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 መሠረት ይግባኝ ካላቀረበ በስተቀር በክስ ሰሚዎች የተሰጠ ውሳኔ የቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

22.**<u>በፐብሊክ ኦዲተር እና የኦዲት ድርጅት ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ</u>**

ክስ ሰሚዎች ክስ የቀረበበት ፐብሊክ ኦዲተር ወይም የኦዲት ድርጅት ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ ተላልፏል ብለው ከወሰኑ እንዳስፈላጊነቱ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ እርምጃዎች ሊወስዱ ይችላሉ፡-

1. ለፐብሊክ ኦዲተሩ ወይም ኦዲት ድርጅቱ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤
2. ፐብሊክ ኦዲተሩ ወይም የኦዲት ድርጅቱ ማሟላት የሚጠበቅበትን መስፈርት እንዲያሟላ ማዘዝ፣
3. ፐብሊክ ኦዲተሩ ወይም የኦዲት ድርጅቱ ሸሪኮች ወይም ተቀጣሪዎች ጥራት ያለው የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚያስችላቸውን አቅም እንዲገነቡ የሚያስፈልጋቸውን ስልጠና እንዲወሰዱ ማዘዝ፤
4. የፐብሊክ ኦዲተሩን ወይም የኦዲት ድርጅቱን ፈቃድ ማገድ፤

5. የፐብሊክ ኦዲተሩን ወይም የኦዲት ድርጅቱን ፈቃድ መሠረዝ፣
6. በፐብሊክ ኦዲተሩ ወይም በኦዲት ድርጅቱ ላይ ከብር 25 ሺ ያልበለጠ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት መጣል፡፡

23. <u>በሪፖርት አቅራቢ አካላትና በእነርሱ ዳይሬክተሮች ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ</u>

1. ክስ ሰሚዎች ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡትን ማናቸውንም የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ እና የኦዲት ደረጃዎች ወይም መመሪያዎች የሚጠይቁትን አላሟላም የሚል ውሳኔ ላይ ሲደርሱ ማስጠንቀቂያ ሊሰጡ ወይም የሂሳብ መግለጫውን ወይም ሪፖርቱን ወይም ሁለቱንም በቶሎ እንዲያስተካክል ትዕዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ትዕዛዝ የተሰጠው ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ትዕዛዙ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የሂሳብ መግለጫውን ወይም ሪፖርቱን አስተካክሎ ለቦርዱ እና ለሚመለከተው የመንግስት መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ መሠረት ባይፈጽም ክስ ሰሚዎቹ ከብር 10,000 ያልበለጠ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ሊጥሉበት ወይም አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ጉዳዩን ለሚመለከተው የመንግስት አካል ሊመሩት ይችላሉ፡፡
4. ክስ ሰሚዎች የማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ዳይሬክተር ሆን ብሎ ሪፖርት አቅራቢው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) በተደነገገው መሠረት እንዳይፈጽም ማድረጉን ወይም የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መግለጫ ወይም ሪፖርት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲዛባ ያደረገ መሆኑን ሲደርሱበት፡-

   ሀ) በዳይሬክተሩ ላይ ከብር 10,000 ያልበለጠ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ሊጥሉበት ይችላሉ፣

   ለ) ዳይሬክተሩ የሪፖርት አቅራቢው ወይም የሌላ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ዳይሬክተር ሆኖ እንዳይሰራ ከአንድ ዓመት ላላነሰ እና ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያግዱት ወይም በዳይሬክተርነት ለመስራት ብቁ አይደለም ብለው ሊወስኑበት ይችላሉ፣ ሆኖም በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ቦርዱ የሚወስድበት አስተዳደራዊ እርምጃ ዳይሬክተሩን በፍትሐ ብሔርም ሆነ በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ከመሆን አያድነውም፣

ሐ) አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ጉዳዩን ለሚመለከተው ሌላ የመንግስት አካል ሊመሩ ይችላሉ፡፡

5. ክስ ሰሚዎች የማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) በተደነገገው መሠረት እንዳይፈጽም ወይም የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መግለጫ ወይም ሪፖርት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲዛባ ሆን ብሎ ያደረገው ዳይሬክተር ፐብሊክ ኦዲተር መሆኑን ሲደርሱበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ከተቀመጡት አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተጨማሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 መሠረት ቅጣት ይጥሉበታል፤ ዳይሬክተሩ የተመሰከረለት ኦዲተር ከሆነ ደግሞ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ከተቀመጡት እርምጃዎች በተጨማሪ አስፈላጊውን የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወስድ ጉዳዩን ለኢንስቲትዩቱ ወይም ለሚመለከተው የሂሳብ ባለሙያዎች ማህበር ይመራሉ፡፡

24.**የወንጀል ጥፋቶች**

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚያዝ መዝገብ ወይም ማንኛውም የዚሁ መዝገብ ቅጂ ውስጥ ለማጭበርበር በማሰብ የሀሰት ወይም የተሳሳተ መረጃ ያስገባ፣ እንዲገባ ያደረገ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፤

ለ) ራሱ ወይም ሌላ ማንኛውንም ሰው በማጭበርበር እንደተመሰከረለት ኦዲተር፣ እንደ ተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንደ ፐብሊክ ኦዲተር እንዲመዘገብ ያደረገ ወይም እንዲመዘገብ ለማድረግ የሞከረ እንደሆነ፤

ሐ) ለራሱ ወይም ለሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውንም ጥቅም፣ የተለየ አስተያየት ወይም ልዩ መብት ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ እያወቀ እና ሆን ብሎ መሠረታዊ ይዘቱ ሀሰተኛ የሆነ መግለጫ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤

መ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ያለን ክስ ሰሚ፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ሌላ ማንኛውንም የቦርዱ ኃላፊ ወይም የቦርዱን ሥራ ሆን ብሎ ያሰናከለ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከብር 20,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት ባልበለጠ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሚወሰንበት ጠቅላላ የገንዘብ ቅጣት ከብር 50,000 ሳይበልጥ ጥፋቱ ለሚቆይበት ለእያንዳንዱ ቀን ብር 1,000 መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
4. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተጠየቀውን መረጃ የደበቀ ወይም መረጃ ወይም ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ የማንኛውም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ዳይሬክተር፣ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከብር 20,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
5. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለጥራት ማረጋገጫ ዓላማ ቦርዱ ወይም ኢንስቲትዩቱ ሲጠይቀው መረጃ የደበቀ ወይም በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለን ማንኛውንም መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ የማያቀርብ ወይም ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ፐብሊክ ኦዲተር ወይም የተመሰከረለት ኦዲተር፣ ሸሪኩ፣ ሠራተኛው ወይም ከተፈቀደለት ወይም ከተመሰከረለት ኦዲተር ጋር የሥራ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
6. አንድን ሪፖርት አቅራቢ አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተደነገገው መሠረት እንዳይፈጽም ወይም የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መግለጫ ወይም ሪፖርት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲዛባ ሆን ብሎ ያደረገ፣ ወይም ሆን ብሎ ትክክል ያልሆነ ወይም በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሳስት የሂሳብ መግለጫ ወይም የሂሳብ ሪፖርት እንዲያዘጋጅ ወይም እንዲያቀርብ ሌላውን ሰው የሚረዳ፣ የሚገፋፋ፣ የሚያደፋፍር፣ የሚያግባባ ወይም የሚያነሳሳ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከብር 20,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

7. ሕጋዊ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ሥራ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው በሂሳብ ሙያ የሰራ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከብር 25,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
8. በማድረግ ወይም ባለማድረግ ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም የሙያ ስነምግባር ደንብን በመጣስ የሚፈጸም ማንኛውንም ሌላ ጥፋት ከብር 20,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ያስቀጣል፡፡

25. <u>**መልሶ ስለመመዝገብ**</u>

1. ኢንስቲትዩቱ ወደ አባልነት መመለሱን በጽሑፍ ሲያስታውቀው ቦርዱ ከኢንስቲትዩቱ ተሰርዞ የነበረውን ሰው መልሶ በመዝገቡ ውስጥ ያሰፍራል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 መሠረት ፍቃዱ የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው በድጋሚ ለመመዝገብ ለቦርዱ ማመልከቻ ማስገባት ይችላል፡፡ ለዚህ ዓላማ የአንቀጽ 18 እና 21 ድንጋጌዎችም በተመሳሳይ መልኩ ለምዝገባ እንደሚያመለክት ሰው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

26. <u>**በቦርዱ የሚጣልን ቅጣት እና የአገልግሎት ክፍያ ስለማስፈጸም**</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ ሊከፈል የሚገባ ማንኛውም ክፍያ እንደ ዕዳ ተቆጥሮ ቦርዱ እንዲከፈለው ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርዱ የተጣለ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንደተወሰነ የገንዘብ ቅጣት ተቆጥሮ ለቦርዱ እንዲከፈል ሊታዘዝ ይችላል፡፡ ለዚህም ዓላማ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይም የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጠው የቃለ መሃላ ማረጋገጫ ቅጣቱ በሕግ አግባብ የተጣለ ስለመሆኑ እንደበቂ ማረጋገጫ ተወስዶ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ በተጣለበት አንቀጽ መሠረት ገንዘቡ እንዲከፈል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በጉዳዩ ላይ የቀረበው ይግባኝ ከመታየቱ ወይም ይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከማለፉ በፊት ፍርድ ቤቱ እንዲህ ዓይነቱን ትዕዛዝ አይሰጥም።

27.**ይግባኝ**

ክስ ሰሚዎች በሰጡት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በውሳኔው ቅር የተሰኘበትን ምክንያት ከሚደግፍ የፍሬ ነገር፣ የሕግ፣ የሂሳብ አያያዝ እና የኦዲት ደረጃዎች ትንተና ጋር ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 48 መሠረት ለሚሰየመው የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

28.**ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ**

1. ሚኒስትሩ በክስ ሰሚዎች በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው የሚያቀርበውን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥ ሦስት አባላት ያሉት የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይሰይማል።
2. የይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የይግባኙ ማመልከቻ በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. የይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ይግባኝ የሚሰማበትን ስነሥርዓት ይወስናል።
4. የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 መሠረት የቀረበን ይግባኝ መርምሮ የክስ ሰሚዎች የሰጡትን ውሳኔ ካፀና ይግባኙን ለማየት የተደረገውን ወጪ በሙሉ ወይም በከፊል ይግባኝ ባይ እንዲከፍል ሊያዝ ይችላል፡፡
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ መሠረት በይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

29.**በይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሕግ ትርጉም ረገድ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት በይግባኙ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ እንዳይፈጸም ካላዘዘ በስተቀር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
3. የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሕግ ትርጉም ረገድ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ ውድቅ የሚያደርግ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የህግ ትርጉም መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ይመልሳል። የይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም በፍርድ ቤቱ የተሰጠውን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 30. የጥቅም ግጭት

1. በቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እንዲያገለግል የታጨ ማንኛውም ሰው ቦርዱ መወሰን በሚችልባቸው ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ጥቅም ማግኘት የሚችል ከሆነ የጥቅሙን ዓይነትና መጠን በአባልነት ለሚያጨው አካል በግልጽ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ድምጽ በሚሰጥበት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ጥቅም የሚያገኝ ከሆነ የጥቅሙን ዓይነትና መጠን ለዳይሬክተሮች ቦርድ በግልጽ በማሳወቅ በጉዳዩ ላይ ድምጽ ከመስጠት እራሱን ማግለል አለበት፡፡
3. ማንኛውም የቦርዱ ሠራተኛም ሆነ አማካሪ ቦርዱ በሚያያቸው ማናቸውም ጉዳዮች ላይ የግል፣ ሙያዊ ወይም የስልጣን ጥቅም ያለው ከሆነ ወይም የእሱ የቅርብ ቤተሰብ አባላት ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ጥቅም ያላቸው ከሆነ ይህንኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።
4. የቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚቀርቡትን የጥቅም ግጭት ማሳወቂያዎች ተቀብሎ በመመርመር በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የውሳኔውን ሪፖርት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ያቀርባል።
5. በቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የተሰየመ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገውን ካላሟላ በስተቀር በስሙም ሆነ በሌሎች ሰዎች ስም ምንም ዓይነት የኦዲት ወይም የማረጋገጥ አገልግሎት መስጠት የለበትም፡፡
6. ማንኛውም የቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የስራውን ባህሪ እና ስፋት ለዳይሬክተሮች ቦርድ በግልጽ ሳያሳውቅ ከቦርድ አባልነት ሥራው ውጪ በሌላ ማንኛውም ትርፍ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መሰማራትም ሆነ መቀጠል የለበትም፡፡
7. ማንኛውም የቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይም የቦርዱ ሰራተኛ በኃላፊነቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በሚኖረው ወይም በሚፈጥር ማንኛውም ሥራ ላይ መሳተፍ ወይም መቀጠል የለበትም፡፡

8. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የቅርብ ቤተሰብ" ማለት ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ባል፣ ሚስት፣ ልጅ፣ እናት፣ አባት፣ ወንድም ወይም እህት ነው፡፡

31. <u>ምስጢር ስለመጠበቅ</u>

1. ማንኛውም የቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ በቦርዱ የሚቋቋመው የአማካሪዎች ኮሚቴ አባል፣ የቦርዱ ሰራተኛ ወይም ቦርዱን የሚያገለገል አማካሪ ሥራውን ወይም ኃላፊነቱን ሲጀምር ቦርዱ ያፀደቀውን ምስጢር የመጠበቅ ቃለ መሃላ መፈፀም አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው የቦርዱን ወይም ቦርዱ የሚወክለውን ሰው ፈቃድ በጽሁፍ ሳያገኝ ከሥራው ጋር በተገናኘ እና በሥራው አጋጣሚ ያወቀውን የማንኛውንም ሰነድ፣ ግንኙነት ወይም ሌላ መረጃ ይዘት ይፋ ማድረግ ወይም ላልተፈቀደለት ማንኛውም ሰው መግለጽ አይችልም።

32.<u>መረጃን በመገናኛ ዘዴዎች ይፋ ስለማድረግ</u>

1. ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን መረጃ የሚይዝ መጽሔት በተወሰነ ጊዜ ልዩነት ያሳትማል።
2. ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን መረጃ ለህዝብ የሚገልጽበት ድረ ገጽ እና የኤሌክትሮኒክስ መጽሔት ሊኖረው ይችላል፡፡
3. ቦርዱ የሚያዘጋጀውን ወቅታዊ መጽሔት፣ ድረ ገጹን፣ የኤሌክትሮኒክስ መጽሔቱን ወይም ዕለታዊ ጋዜጣን በመጠቀም በዚህ አዋጁ አንቀጽ 48 መሠረት የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች ይፋ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

33.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

34. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 ድንጋጌ ቢኖርም አቅማቸውንና ዝግጁነታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሪፖርት አቅራቢ አካላት በዚህ አዋጅ መሠረት መፈጸም የሚጠበቅባቸውን ጊዜ የመወስን ሥልጣን በዚህ አዋጅ ለቦርዱ ተሰጥቶታል። ሆኖም

ይህ ጊዜ በማናቸውም ሁኔታ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር አምስት አመት መብለጥ የለበትም፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 የተደነገገው ቢኖርም፣ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት፡-

ሀ) ለማንኛውም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል የኦዲት እና የማረጋገጥ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው አዋጁ ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የምዝገባ ማመልከቻ ካቀረበ በዚህ አዋጅ መሠረት ፐብሊክ ኦዲተር ሆኖ ለመሥራት የሚፈለገውን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር የስድስት ዓመት ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል፡፡

ለ) በራሱም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር በሽርክና በኦዲት ድርጅት ስም ለማንኛውም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል የኦዲት እና የማረጋገጥ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው አዋጁ ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ስም እንዲጸድቅለት ማመልከቻ ካቀረበ በዚህ አዋጅ መሠረት በኦዲት ድርጅት ስም ለመሥራት የሚፈለገውን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር የስድስት ዓመት ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሳይመዘገብ አገልግሎቱን እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው ወይም ድርጅት ለማመልከቻ ማቅረቢያ ከተፈቀደው የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ የተቀመጠውን የምዝገባ መሥፈርት ካላሟላ ከስድስት ዓመት በኋላ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል፡፡

35. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ) የፌዴራል ዋናው ኦዲተር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (16) እና (17)፣ እና

ለ) በግል የሚሠሩ ኦዲተሮች እና የሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሠጣጥ ደንብ ቁጥር 4/2002፡፡

2. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡-

ሀ) በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ውስጥ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብን የሚወስኑ ድንጋጌዎች፣

ለ) የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 27፣ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ (2) እና አንቀጽ 34፤

ሐ) የምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (8)፤

መ) የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 8(ሀ)፤

ሠ) የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 (በአዋጅ ቁጥር 693/2003 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 18፣ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (2) እና አንቀጽ 59፤

ረ) የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (3)፣ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1)፤

ሰ) የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) እና አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (1)፤ እና

ሸ) የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (1) እና አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ (3) ፡፡

3. ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

36. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 26 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

## የፍትህ ሚኒስቴር

**ደንብ ቁጥር 332/2007**

**የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 5 እና 35 እና በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 4(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 ነው፤
2. "ድርጅት" ማለት የሂሣብ ሙያ አገልግሎት ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ በቦርዱ የተመዘገበ ድርጅት ነው፤
3. "ባለሙያ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት እንደተመሠከረለት የሂሣብ ባለሙያ ወይም እንደተመሠከረለት ኦዲተር በቦርዱ የተመዘገበ እና እንደ አግባብነቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤
4. በአዋጁ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**ክፍል ሁለት**

**የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ**

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የቦርዱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **የቦርዱ ዓላማዎች**

ቦርዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በሪፖርት አቅራቢ አካላት የሚቀርቡ የፋይናንስ እና ተያያዥነት ያላቸውን ሪፖርቶች አዘገጃጀት እና አቀራረብ ጥራት ማስጠበቅ፤
2. የኦዲተሮች እና የሂሳብ ባለሙያዎችን የሙያ ደረጃ ማስጠበቅ፤
3. የሂሳብ አያያዝና የኦዲት አገልግሎትን ጥራት ማስጠበቅ፤
4. የሂሣብ ሙያ የህዝብ ጥቅምን ማስጠበቁን ማረጋገጥ፤
5. የሂሳብ እና ኦዲት ባለሙያዎችን የሙያ ነፃነት ማስከበር፤

6. **የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ለቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ 4 የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ተጨማሪ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ዓለም አቀፍ የሂሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ወይም እርሱን የሚተካው አካል ከሚያወጣው የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ጋር የተጣጣመ የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችና የተመሰከረላቸው ኦዲተሮች የሚመሩበት የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፤ ይፋ ያደርጋል እንዲሁም በየጊዜው ይገመግማል፤
2. የባለሙያዎችን ማመልከቻ ስለመቀበል ወይም ውድቅ ስለማድረግ፣ ባለሙያዎችን ስለማገድ ወይም ከባለሙያዎች ዝርዝር ስለመሠረዝ፤ ፈቃድ ስለማደስ እና ሌሎች ባለሙያዎችን የሚመለከቱ መመሪያዎች ያወጣል፤
3. የራሱን የፈተና እና የብቃት መሥፈርት መመሪያዎች ያወጣል፤
4. የሂሣብ ሙያን እና የባለሙያዎችን አቅም ለማጎልበት ከአገር ውስጥና ውጭ ሀገር ካሉ አግባብነት ካላቸው ባለሥልጣኖች፣ ማህበራት፣ የህብረተሰብ ተቋሞች ወይም አካላት ጋር ይነጋገራል፣ ይመካከራል፣ ግንኙነት ያደርጋል ወይም ይተባበራል፤
5. ዓላማውና ተግባሩ ተመሳሳይ ከሆነ ማናቸውም አለም አቀፍ አካል ጋር ይተባበራል ወይም የዚህ አይነቱ አካል አባል ወይም ተባባሪ አባል ይሆናል፤
6. በባለሙያዎች እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በግልግል ወይም በዕርቅ መፍትሄ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፣

7. በሂሣብ ሙያ ላይ ተጽዕኖ ባላቸው በሥራ ላይ ባሉ ወይም ረቂቅ ህጎች ላይ የማሻሻያ ሃሣብ ያቀርባል፤
8. የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችን ለመመዝገብ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይሰጣል፤ ወይም የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
9. በኢትዮጵያ ውስጥ የሂሳብ እና ኦዲት ሥራ ሙያን ይወክላል፤
10. እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር በመሆን በቦርዱ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ የብቃት መሥፈርቶችን በማውጣት በእነዚሁ መሥፈርቶች መሠረት ባለሙያዎችን መዝግቦ ይይዛል፤
11. ለባለሙያዎች ለሚሰጡ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ፕሮግራሞች መሥፈርት ያወጣል፣ ሥልጠና ይሰጣል ወይም ሥልጠና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤
12. በራሱ አነሳሽነት ወይም ከሌላ ሰው በሚቀርብ ጥያቄ ወይም ቅሬታ መሠረት በተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ወይም በተመሰከረላቸው ኦዲተሮች የሚፈጸም የሥነምግባር ደንብ ወይም የዚህን ደንብ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ ድንጋጌዎች መተላለፍን አስመልክቶ የቀረበን ክስ ይመረምራል፤ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤
13. የላቀ የኦዲት ሥራ ጥራት መኖሩን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት በሥራ ላይ ያውላል፤
14. ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች የሚሠሩ ኦዲተሮችን የሥራ ጥራት ይመረምራል ወይም እንዲመረመር ያደርጋል፤
15. የሂሣብና የኦዲት ሙያን የሚመለከቱ አለም አቀፍና የሀገር ውስጥ መረጃዎችን በየጊዜው በመከታተል ለባለሙያዎች እና ለሌሎች ሰዎች ያሰራጫል፣
16. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>የቦርዱ አቋም</u>

1. ቦርዱ፦

ሀ) የዳይሬክተሮች ቦርድ

ለ) በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

ሐ) አስፈላጊው ሠራተኞች፤ ይኖሩታል፡፡

2. ቦርዱ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ የሚያግዙትን የተለያዩ የአማካሪ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል።

8. **<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት</u>**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከግሉ ዘርፍና ሙያውን ከሚወክሉ የሙያ ማህበራት የተውጣጡ 12 አባላት ይኖሩታል።
2. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚመረጡት አብዛኞቹ ሰዎች በሂሳብ ሙያ እና ለሙያው ቀረቤታ ካላቸው የትምህርት መስኮች ይሆናሉ፡፡

9. **<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን</u>**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ለሌላ ሦስት ዓመት በአባልነት በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል።
3. ለሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመናት ያገለገለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ከኃላፊነት ከተነሳ ከሦስት ዓመታት ቆይታ በኋላ በድጋሚ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ሊመረጥ ይችላል።

10. **<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር</u>**

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የቦርዱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤
2. ለመንግሥት የሚቀርበውን የቦርዱን በጀትና የሥራ ፕሮግራም እና ሪፖርት ይመረምራል፤
3. ቦርዱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚጠየቁ የክፍያ ተመኖች ለመንግሥት ከመቅረባቸው በፊት ይመረምራል።

11. **<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ</u>**

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከአባላቱ መካከል ቢያንስ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት ሲጠይቁ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።
2. በማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም የአባላቱ ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የቦርዱ ዋና ዳይሬክተር በስብሰባ ላይ እንዳይገኝ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካልወሰነ በስተቀር ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በማናቸውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል።
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

12.<u>ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አባልነት ብቁ አለመሆንና ከአባልነት ስለመሰናበት</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) በማንኛውም ጊዜ በሙስና፣ በስርቆት፣ በማጭበርበር፣ አስመስሎ በመስራት፣ በሀሰት በመመስከር፣ ወይም በማናቸውም የእምነት ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፤
   ለ) ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በማንኛውም ሕግ መሰረት የገንዘብ ቅጣት አማራጭ በሌለው ከስድስት ወር ባላነሰ የእስራት ቅጣት በሚያስቀጣ ወንጀል ተግባር የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈበት ከሆነ፣
   ሐ) በአባልነት ቢሾም የጥቅም ግጭት የሚያስከትልበት ከሆነ፣
   መ) በሌላ ማናቸውም ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ባለአደራ ለማገልገል በሕግ ብቁ ካልሆነ፣ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ ሊሆን አይችልም።
2. ማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ይሰናበታል፡-
   ሀ) በራሱ ፈቃድ ከአባልነት ለመሰናበት ለሚኒስትሩ የጽሑፍ ማመልከቻ ሲያቀርብ፤
   ለ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ያወጣውን የአባላቱን የሙያና የሥነምግባር ደንብ ጥሶ ሲገኝ፤
   ሐ) በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አብላጫ ድምጽ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት አልተወጣም ተብሎ ሲወሰን፤ ወይም
   መ) በአስራ ሁለት ተከታታይ ወራት ውስጥ ከተደረጉ ስብሰባዎች ቢያንስ በግማሹ ላይ ካልተገኘ፡፡

13.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የቦርዱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የቦርዱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) የቦርዱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የቦርዱን ዓላማ በማስፈፀም ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል
   ሐ) የቦርዱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በዳይሬክተሮች ቦርድ ከታዬ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም፤ ተግባራዊ ያደርጋል
   መ) ለቦርዱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤
   ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ቦርዱን ይወክላል፣
   ረ) የቦርዱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በዳይሬክተሮች ቦርድ ከታየ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለቦርዱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለቦርዱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

14.<u>የበጀት ምንጭ</u>

የቦርዱ የበጀት ምንጭ፦

1. መንግሥት ከሚመድብለት ዓመታዊ በጀት፤ እና
2. ከሌሎች ምንጮች ይሆናል።

15.<u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ቦርዱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የቦርዱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## ባለሙያዎችን ስለመመዝገብ፣ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት እና ስለመቆጣጠር

### 16.ስለመመዝገብ

ቦርዱ የባለሙያዎችን ስምና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች የያዘ መዝገብ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፡፡

### 17.የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ስለመመዝገብ

1. በሂሣብ ሙያ አግባብነት ያላቸው የብቃት መስፈርቶችን የሚያሟላና ቢያንስ የሦስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ማንኛውም ሰው እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ለመመዝገብ ቦርዱ በሚያወጣው ፎርምና ሥርዓት መሠረት ማመልከት ይችላል።
2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያና በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰኑ መረጃዎች ጋር እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።
3. ቦርዱ፡-

   ሀ) የኢትዮጵያ ዜግነት ያለውን ወይም ኢትዮጵያዊ ካልሆነ የሥራ ፈቃድ ያለውን ወይም የሥራ ፈቃድ ከማቅረብ ግዴታ በሕግ ነፃ የተደረገን፤

   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ ነዋሪ የሆነን፤

   ሐ) መልካም ሥነ ምግባር ያለውና እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል በማንኛውም ሀገር ጥፋተኛ ሆኖ ያልተገኘን፤

   መ) በቂ የሂሣብ ሙያ እውቀትና ክህሎት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጠውን ፈተና ወይም ምዘና ያለፈን፤ እና

   ሠ) ተገቢውን ክፍያ የከፈለን፤

   አመልካች ስምና አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ሌሎች መረጃዎች በተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ይመዘግብዋል፡፡
4. ቦርዱ አንድ ሰው እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ መሥራት እንዲቀጥል ለመፍቀድ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት የመውሰድ ግዴታን እንዲያሟላ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

## 18. የተመሰከረላቸውን ኦዲተሮች ስለመመዝገብ

1. ኦዲተር በመሆን ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ እንደተመሰከረለት ኦዲተር እንዲመዘገብ ቦርዱ በሚያወጣው ፎርም እና ሥርዓት መሠረት ለቦርዱ በጽሑፍ ማመልከት ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያ እና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰኑ መረጃዎች ጋር መቅረብ አለበት፡፡
3. ቦርዱ አመልካቹ፡-

   ሀ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ መሆኑን፣

   ለ) ቦርዱ ባወጣው መመሪያ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን፣

   ሐ) ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት ለመውሰድ ዝግጅት ማድረጉን፣

   መ) እንደተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ ለመስራት የሚያስችል ብቃት ያለውና ቦርዱ ባወጣው መመሪያ የሚጠየቀውን ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት በፈጸመበት እና በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻውን ባቀረበበት ጊዜ መካከል አንድ ዓመት ያለፈ መሆኑን፣ እና

   ሠ) ቦርዱ በሚወስነው ጊዜና አኳኋን መሠረት ለጥራት ማረጋገጫ ምርመራ እራሱን ያዘጋጀ መሆኑን፣

   ሲያረጋግጥ የአመልካቹን ስምና ሌሎች መረጃዎች በተመሰከረላቸው ኦዲተሮች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደተመሰከረለት ኦዲተር ይመዘግበዋል፡፡
4. ቦርዱ አንድ ሰው እንደተመሰከረለት ኦዲተር መስራት እንዲቀጥል ለመፍቀድ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርትና ስልጠና የመውሰድ ግዴታን እንዲያሟላ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

## 19. የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች እና የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ስላለመመዝገብ፣

1. ቦርዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ወይመ 18 መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት፣

   ሀ) እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመዝገብ የቀረበው አመልካች፡-

   1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች ካላሟላ፣

   2) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ እንዲሠራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ ወይም፣

3) በሌላ ማንኛውም ምክንያት እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

አመልካቹን እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ አይመዘግበውም፡፡

ለ) እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ የቀረበው አመልካች፡-

1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች ካላሟላ፣

2) የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ እንዲሠራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ፣ ወይም

3) በሌላ ማንኛውም ምክንያት እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

አመልካቹን እንደተመሰከረለት ኦዲተር አይመዘግበውም፡፡

2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበን ሰው ላለመመዝገብ ሲወስን ምክንያቱን በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

3. ቦርዱ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር ስላልመዘገበው ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ሊያስቀይር በሚችል የሕግና የፍሬ ነገር ትንታኔ በማስደገፍ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት ቅሬታውን በጽሑፍ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4. የዳይሬክተሮች ቦርድ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 20. ድርጅቶችን ስለመመዝገብ

1. ማንኛውም የሂሳብ ሙያ አገልግሎት ወይም የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ድርጅት ቦርዱ እንዲመዘግበው ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ሥርዓት መሠረት በጽሑፍ መቅረብ አለበት፡፡

3. ቦርዱ፡-

ሀ) ሁሉም የድርጅቱ ሽሪኮች በቦርዱ የተመዘገቡ መሆኑን፣

ለ) ድርጅቱ እና እያንዳንዱ ሽሪክ አባል በተናጠል ቦርዱ የሚያወጣውን የሙያ ስነምግባር ደንብ ለማክበር በጽሑፍ ግዴታ የገቡ መሆኑን፣

ሐ) ድርጅቱ ቦርዱ በሚወስነው የገንዘብ መጠን የሙያ መድን የገባ ወይም ሌላ ዓይነት የገንዘብ ዋስትና የሚያቀርብ መሆኑን፣

ሲያረጋግጥ የአመልካቹን ድርጅት ስም እና ሌሎች መረጃዎች በድርጅቶች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደ ድርጅት ይመዘግበዋል፡፡

4. የድርጅት ምዝገባን በሚመለከት ለሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ የዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) እና (4) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

21.<u>የምዝገባ እና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት፣</u>

1. ቦርዱ አንድን ግለሰብ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም አንድን ድርጅት እንደ ድርጅት ሲመዘግብ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
2. ቦርዱ አንድን ሰው እንደተመሰከረለት ኦዲተር ሲመዘግበው የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
3. የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት አመልካቹ ተገቢውን ክፍያ ሲፈጽም ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም መሠረት ይሰጣል፡፡
4. በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት፣

   ሀ) እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ራሱን የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ብሎ መጥራት እና "ሲ.ፒ.ኤ." የሚለውን ምህጻረ ቅል መጠቀም ይችላል፣

   ለ) እንደተመሰከረለት ኦዲተር የተመዘገበ ሰው ራሱን የተመሰከረለት ኦዲተር ብሎ መጥራት እና "ሲ.ኤዩ." የሚለውን ምህጻረ ቃል መጠቀም ይችላል፡፡
5. የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ሆኖ የሚቆየው የምስክር ወረቀቱን የያዘው ሰው ምዝገባ እስከፀና ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ ምዝገባው የተሰረዘ ወይም የታገደ ማንኛውም ሰው የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ለቦርዱ ወዲያውኑ መመለስ አለበት፡፡

22.<u>ምዝገባን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ</u>

1. ቦርዱ በሚከተሉት ምክንያቶች አንድን የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት ምዝገባ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ እና ከመዝገብ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

   ሀ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅቱ

የተመዘገበው በማጭበርበር ወይም በማስመሰል መሆኑን ሲደርስበት፣

ለ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ ማንኛውንም የቦርዱን መመሪያ የማያከብር ሲሆን ወይም የሚጥስ ተግባር መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣

ሐ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ አባል ከሆነበት ሌላ የሂሳብ ሙያ ማህበር የታገደ ወይም የተሰረዘ ሲሆን፣

መ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ አዋጁን ወይም ይህንን ደንብ ተላልፎ ከተገኘ፣

ሠ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ ከእምነት ማጉደል ጋር በተያያዘ ወንጀል በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ጥፋተኛ ሆኖ የገንዘብ ቅጣት አማራጭ በሌለው እስር ከተቀጣ ወይም ድርጅቱ የገንዘብ ቅጣት ከተጣለበት፣

ረ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ በሕግ ችሎታ ያጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሰ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መስጠቱ ሲረጋገጥ፣

2. ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲሰርዝ የምስክር ወረቀቱን የያዘውንም ሰው ከባለሙያዎች መዝገብ ይሠርዘዋል፡፡
3. ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲያግድ የምስክር ወረቀቱ ለታገደበት ጊዜ የምስክር ወረቀቱን የያዘውንም ሰው ከባለሙያነት ያግደዋል፡፡
4. ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ይህንኑ ከሁለት በማያንሱ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ዕለታዊ ጋዜጣዎች ለሶስት ተከታታይ ቀናት በማውጣት ህዝብ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

23. **<u>የምዝገባ የቆይታ ጊዜ እና እድሳት</u>**

1. ቦርዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የሚሰጠው የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል፡፡

2. ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ስርዓት መሠረት የጽሑፍ ማመልከቻ በማስገባት የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ማሳደስ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ስርዓት መሠረት የጽሑፍ ማመልከቻ በማስገባት የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ማሳደስ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያ እና ቦርዱ በመመሪያ ከሚወስነው መረጃ ጋር መቅረብ አለበት፡፡
5. ቦርዱ፡-

ሀ) አመልካቹ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት እንደአግባብነቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ያድስለታል፣

ለ) አመልካቹ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት፡-

1) እንደአግባብነቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፣ ወይም
2) በሌላ ማናቸውም ምክንያት እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን አያድስለትም፡፡

ሐ) አመልካቹ የተመሰከረለት ኦዲተር በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ያድስለታል፣

መ) አመልካቹ የተመሰከረለት ኦዲተር፡-

1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፣ ወይም
2) የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ እንዲሰራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ፣ወይም

3) በሌላ ማናቸውም ምክንያት እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፣

የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን አያድስለትም፡፡

6. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የአንድን አመልካች የምስክር ወረቀት ላለማደስ ሲወስን የምስክር ወረቀቱን የማያድስበትን ምክንያት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

24. <u>ያለምስክር ወረቀት መሥራትን ስለመከልከል</u>

ማንኛውም ሰው ቦርዱ የሚሰጠው ሕጋዊ የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ወይም የምስክር ወረቀቱ በሚፈቅደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በእራሱም ሆነ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር በሽርክና ወይም በማኅበር እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር መሥራት ወይም እራሱን ማቅረብ አይችልም፡፡

25. <u>የስም ወይም የሌላ መረጃ ለውጥ</u>

ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት በተመዘገበው ስሙ ወይም ሌላ መረጃ ላይ ለውጥ ሲኖር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለውጡ በተደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

26. <u>የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ስለማከናወን፣</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 25 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ወይም ቦርዱ በጽሑፍ የሚፈቅድለት የሌላ ሀገር የሂሣብ ሙያ ተቆጣጣሪ ድርጅት፣ አህጉራዊ ወይም ክፍለ አህጉራዊ የሂሣብ ሙያ ማህበር የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ሥራ ጥራት መመርመር ይችላል፡፡ ለዚህ ዓላማ፡-

   ሀ) በኦዲተሩ፣ በሸሪኩ፣ በተቀጣሪው ወይም ከእርሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ባለው ሰው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለውን መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀትና ማህደር፣ ሰነድና መዝገብ መመርመርና ፎቶ ኮፒ መውሰድ፣ ወይም አጭር ማስታወሻ መያዝ ይችላል፣

   ለ) ከኦዲተሩ፣ ከሸሪኩ ወይም ከተቀጣሪው ወይም ከኦዲተሩ ጋር የሥራ ግንኙነት ካለው ሰው ማንኛውንም መረጃ ወይም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር፣ ሸሪኩ፣ ተቀጣሪው ወይም ከሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው በቦርዱ ወይም

ቦርዱ በጽሑፍ በወከለው ሰው ሲጠየቅ በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለው መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀት፣ ማህደር ወይም ሰነድ ማቅረብ አለበት፡፡

27.**<u>መረጃን ይፋ ስለማድረግ፣</u>**

1. ቦርዱ፡-

ሀ) የሂሳብ ዓመቱ ባለቀ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከሁለት በማያንሱ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ዕለታዊ ጋዜጣዎች ለሦስት ተከታታይ ቀናት ዓመታዊ የባለሙያዎችን ስም ዝርዝር በማውጣት ይፋ ማድረግ አለበት፣

ለ) ለህዝብ ይፋ በሆነ መዝገቡ እና በድረ-ገጹ ወቅታዊውን የባለሙያዎች ስም ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

2. የባለሙያዎችን መዝገብ ተገቢውን ክፍያ ከፍሎ ማየት ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው አመቺ በሆነ ማንኛውም ጊዜ ክፍት ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች የያዘ ሪፖርት በየጊዜው ያወጣል፡፡
4. ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን መረጃ የያዘ ኤሌክትሮኒክ መጽሔት የሚያወጣበት ድረ-ገጽ ይኖረዋል፡፡
5. ቦርዱ ከባለሙያዎች እና ከሚያከናውናቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች በሪፖርቱ ወይም በድረገጹ፣ በኤሌክትሮኒክ መጽሔቱ ወይም በዕለታዊ ጋዜጣ ይፋ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ትምህርት እና ፈተናዎች</u>

28.**<u>የሙያ ብቃት መስፈርቶች እና የትምህረት ፕሮግራም ይዘቶች፣</u>**

ቦርዱ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ የመንግስት እና የግል ዘርፍ ፍላጎቶችን ማሟላት በሚያስችል አኳኋን የሙያ ብቃት መስፈርቶችን እና የትምህርት ፕሮግራም ይዘቶችን ያዘጋጃል፡፡

29.**<u>የፈተና አስተዳደር እና የጥራት ማረጋገጫ፣</u>**

የቦርዱ የሙያ ብቃት መስፈርቶች ከፍተኛ ጥራትና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥና ከልምድ ልውውጥ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻል ቦርዱ

በፈተና እቅድ ረገድ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል እውቅና ካላቸው የሂሳብ ሙያ ማህበራት ጋር ጥምረት በመፍጠር በትብብር ይሰራል፡፡

## ክፍል አምስት

## የዲሲፕሊን ክስ

### 30.በቦርዱ ስለሚታይ የዲሲፕሊን ክስ

1. በአዋጁ ከአንቀጽ 36 እስከ 42 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከመርማሪ ሹሙ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሣብ ወይም ቦርዱ በራሱ ተነሳሽነት ባገኘው መረጃ መነሻ አዋጁ ወይም ይህ ደንብ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጣ መመሪያ ወይም የሙያ ስነምግባር ደንብ በተመሠከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ በተመሠከረለት ኦዲተር ወይም በድርጅት ተጥሷል ብሎ እንዲያምን የሚያስችል ምክንያት ሲኖር ጥሰት በፈጸመው ሰው ላይ ክስ በመመሥረት ጉዳዩን በአዋጁ አንቀጽ 38(3) መሠረት ለሚሰየሙ የክስ ሰሚዎች ይመራል፡፡
2. የክስ ሰሚዎች የቀረበውን ማስረጃ ከሰሙ በኋላ ክሱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተረጋግጧል ብለው ካመኑ፣ በተከሳሹ ላይ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የቅጣት ውሳኔ ያስተላልፋሉ፣-

   ሀ) ተከሳሹ ተግሳጽ ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው፣

   ለ) የተከሳሹ የሙያ ሥራ ወይም የምዝገባ ምሥክር ወረቀት እንዲወሰድ፣

   ሐ) ተከሳሹ ለተወሰነ ጊዜ ከሙያው እንዲታገድ፣

   መ) የተከሳሹ ስም ከመዝገብ ላይ እንዲሠረዝ፣

   ሠ) ተከሳሹ ከብር 25ሺ ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሙያ ሥራ ወረቀቱ የታገደ ወይም ስሙ ከመዝገቡ የተሠረዘ ግለሰብ ወይም ድርጅት እራሱን እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት ማቅረብ አይችልም፣ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱም እገዳው ለሚፀናበት ጊዜ ወይም በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት ስሙ ተመልሶ መዝገብ ላይ እስኪሰፍር ድረስ እንደተሠረዘ ይቆጠራል፡፡
4. የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት ተከሳሽ ይግባኝ የጠየቀ ቢሆንም፣ የክስ ሰሚዎች የይግባኙ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ ውሳኔው እንዳይፈጸም ካልወሰኑ በስተቀር ተከሳሹ እንዲታገድ ወይም ስሙ ከመዝገብ እንዲሠረዝ እና የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱ

እንዲወሰድ ወይም እንዲታገድ የክስ ሰሚዎች የሰጡት ውሳኔ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 31. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በዚህ ደንብ የተደነገገው ቢኖርም፣ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት-

   ሀ) ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ ሥራም ሆነ የኦዲት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው ይህ ደንብ ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የምዝገባ ማመልከቻ ካቀረበ በዚህ ደንብ መሠረት የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ ለመሥራት የሚፈለገውን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር ከአምስት ዓመታት ያልበለጠ ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል፣

   ለ) በራሱም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር በሽርክና በድርጅት ስም ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሣብ ወይም የኦዲት ሥራ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው ደንቡ ከፀናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ድርጅቱ እንዲመዘገብለት ማመልከቻ ካቀረበ በዚህ ደንብ መሠረት ድርጅቱ ለመመዝገብ ማሟላት የሚፈለግበትን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር ከአምስት ዓመታት ያልበለጠ ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሳይመዘገብ አገልግሎቱን እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው ወይም ድርጅት በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ ደንብ እና ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ ቦርዱ የሚያወጣውን መሥፈርት ካላሟላ ከአምስት ዓመት በኋላ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል፡፡

### 32. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቦርዱ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡

### 33. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ሀ) የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን በድጋሚ ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 121/1998 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

ለ) ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

34. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 6 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ሐ/ ስለ ልዩ ልዩ የንግድ ህጎች

### የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 246/1954 ዓ.ም

### ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ስለሚላክ ዝባድ የወጣ ደንብ

### የሕግ ክፍል ማስታወቂያ

*ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር የሚወጡትን ዕቃዎች ለመቆጣጠር በ1934 ዓ.ም በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ*

1. ይህን ደንብ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስትር[39] ያወጣው ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር የሚወጡትን ዕቃዎች ለመቆጣጠር በቁጥር 15/1934 ዓ.ም በወጣው (በኋላ በተሻሻለው) አዋጅ በ2ኛው አንቀጽ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡
2. ይህ ደንብ "ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ስለሚላክ ዝባድ የወጣ የ1954 ዓ.ም ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡
3. በቁጥር 53/1936 ዓ.ም የወጣው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ፣ በቁጥር 101/1939 ዓ.ም የወጣው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ፣ በቁጥር 113/1940 የወጣው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ፣ በቁጥር 133/1942 ዓ.ም የወጣው የሕግ ክፍል ማስታወቂያና እንዲሁም በቁጥር 135/1942 ዓ.ም የወጣው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ በዚህ ተሽረዋል፡፡
4. በዚህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ፤
   - ሀ) "ሥልጣን የተሰጠው ላቦራቶሪ" ማለት ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የሚወጣውን ዝባድ ለመመርመርና በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሰውን የምስክር ወረቀት ለመስጠት ከንግድና እንዱስትሪ ሚኒስትር ሥልጣን የተሰጠው ላቦራቶሪ ማለት ነው፡፡
   - ለ) "ዝባድ" ማለት መልኩ ከብጫነት ወደ ጠይምነት የሚሄድ ከጥርኝ የሚወጣ ወፍራም ቅባት ነው፡፡
   - ሐ) "ሲቪቶን" ማለት በዝባድ ውስጥ የሚገኝ የሳይክሎሄፕታዴሴየስ ክፍል የሆነ ኦርጋኒክ ኮምፓውንድ ነው፡፡ እርሱም የዝባድ ዋናው ክፍል ነው፡፡
   - መ) "ላኪ ነጋዴ" ማለት የንግድና የእንዱስትሪ ሥራዎችን ስለማስመዝገብ በ1954 ዓ.ም በቁጥር 184 በወጣው አዋጅ መሠረት በንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ተመዝግቦ የውጭ ንግድ ሥራ እንዲሠራ ከንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ፈቃድ የተሰጠው ማናቸውም ሰው ማለት ነው፡፡

[39] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የንግድ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

5. ሀ) ማናቸውም ዝባድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተወሰነው አኳኋን ካልተመረመረ፣ ካልተጠቀለለና ካልታሸገ፤

   ለ) ተመርምሮ በዝባዱ ውስጥ የሚገኘው ሲቬቶን ቢያንስ በመቶ አርባ (40) ሆኖ ካልተገኘና፤

   ሐ) ሠንጠረዥ "ለ" ተብሎ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ፎርም የሆነ የምስክር ወረቀት ላኪው ነጋዴ ከሚያቀርበው የጉምሩክ ዴክላራሲዮን (መግለጫ) ጋር ተያይዞ ካልተገኘ በቀር ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ወደ ውጭ አገር ሊወጣ አይችልም፡

6. ከዚህ በላይ በ5ኛው አንቀጽ የተጻፈው ግዴታ ያልተፈጸመበት ዝባድ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት እንዳይወጣ የገንዘብ ሚኒስቴር[40] የጉምሩክ መሥሪያ ቤት መከልከል አለበት፡፡

7. ሀ) ዝባድ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ለማውጣት የሚፈልግ ማናቸውም ላኪ ነጋዴ ለማውጣት ያሰበውን መላውን ዝባድ ሥልጣን ለተሰጠው ላቦራቶሪ ለምርመራ ማቅረብ አለበት፡፡ ሥልጣን የተሰጠው ላቦራቶሪም ከቀረበለት ከመላው ዝባድ ውስጥ ለዓይነት ያህል በሚወስደው ዝባድ ላይ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ "ሀ" የተወሰኑትን ምርመራዎች ከፈጸመ በኋላ በዝባዱ ውስጥ በሚገኘው ሲቬቶን መጠን መሠረት ዝባዱን በደረጃ ይመድበዋል፡፡

   ለ) በውስጡ ከመቶ ሃምሳ (50) በላይ ሲቬቶን የሚገኝበት ዝባድ አንደኛ ደረጃ ተብሎ ይመደባል፡፡ በውስጡ ከመቶ አርባ (40) እስከ መቶ ሃምሳ (50) የሚሆን ሲቬቶን የሚገኝበት ዝባድ ሁለተኛ ደረጃ ተብሎ ይመደባል፡፡ በውስጡ ከመቶ አርባ (40) ያነሰ ሲቬቶን የሚገኝበት ዝባድ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር እንዲወጣ ስለማይፈቀድ ለባለቤቱ ይመለስለታል፡፡

   ሐ) ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር እንዲወጣ ከላቦራቶሪው የተመሰከረለት ዝባድ በልዩ መያዣ ይጠቀለልና እዚያው ከላቦራቶሪው ውስጥ እንዳለ በናይሎን ክረጢት ከተከተተ በኋላ በከረጢቱ ላይ መለያ ምልክት ይደረግበታል፡፡ ቀጥሎም ላቦራቶሪው ከረጢቱን ያሽግና በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ በደረሰኝ ያስቀምጠዋል፡፡

[40] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

መ) ምርመራውን የፈጸመው ላቦራቶሪ መርምሮ ለተስማማበት ለያንዳንዱ ክፍል ዝባድ በአምስት ቅጅ የሆነ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ ከአምስቱ ቅጅ ውስጥ ላቦራቶሪው አንዱን እራሱ ያስቀርና ዋናውን እና ሶስቱን ቅጅዎች ለላኪው ነጋዴ ይሰጠዋል፡፡ ላኪው ነጋዴም አንዱን ቅጅ ለራሱ አስቀርቶ ዋናውን ከሚያስፈልጉት ሌሎች ሰነዶች ጋር አያይዞ ዝባዱን ለሚቀበለው (ለሚገዛው) ወይም ለባንኩ ይልክለታል፡፡ የቀሩት ሁለቱ ቅጂዎች ግን ላኪው ነጋዴ ከሚያቀርበው የጉምሩክ ዴክላራሲዮን ጋር ለጉምሩክ መሥሪያ ቤት ይቀርባሉ፡፡

8. ሀ) ሥልጣን የተሰጠው ላቦራቶሪ ለመረመረው ዝባድ የሚከተለውን ዋጋ እንዲያስከፍል ተፈቅዶለታል፡፡

    1) እስከ 20 ኪሎግራም ለሚሆን ................................... የኢ.ት/ብር 30.00
    2) ከ20 ኪሎግራም በላይ እስከ 30 ኪሎግራም ለሚሆን ......... የኢ.ት/ብር 40.00
    3) ከ30 ኪሎግራም ለሚበልጥ ....................................... የኢ.ት/ብር 45.00

ለ/ በዚህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ በ7ኛው አንቀጽ የተጠቀሰውን መያዣና ከረጢት የሚያቀርብ ላቦራቶሪው ነው፡፡ ዋጋውን ግን የሚከፍለው ላኪው ነጋዴ ነው፡፡

9. እያንዳንዱ ላኪ ነጋዴ ለመርማሪው ላቦራቶሪ የሚያቀርበው ዝባድ በሚመረመርበት ጊዜ ራሱ ወይም በደንብ ሥልጣን የተሰጠው ወኪሉ ለመገኘት መብት አለው፡፡

10. ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 30 ቀን 1954 ዓ.ም**

**እንዳልካቸው መኰንን**

**የንግድና እንዱስትሪ ሚኒስትር**

**ሠንጠረዥ (ሀ)**

ቀን ----------------------

የዝባዱ ጥቅል ተራ ቁጥር ------------------------------------------------------

አቅራቢው ------------------------------------------------------------------------

1. ጠቅላላ መልክና ሽታ ------------------------------------------------------------
2. የማይክሮስኮፕ ምርመራ -------------------------------------------------------
3. ዝባዱ ከመቀዝቀዙ በፊት የተደረገ ምርመራ፤

   ሀ/ የሳፖኒፊኬሽን ቁጥር -----------------------------------------------------

   ለ/ የኮምጣጣነት ቁጥር ------------------------------------------------------

   ሐ/ የኤስተር ቁጥር ----------------------------------------------------------

   መ/ የአሴቶን ቁጥር ----------------------------------------------------------
4. ዝባዱ ከቀዘቀዘ በኋላ የተደረገ ምርመራ፤

   ሀ/ የሳፖኒፊኬሽን ቁጥር -------------------------------------------------------

   ለ/ የኮምጣጥነት ቁጥር --------------------------------------------------------

   ሐ/ የኤስተር ቁጥር ------------------------------------------------------------

   መ/ የአሴቶን ቁጥር ----------------------------------------------------------
5. የሲቪቶን መጠን --------------------------------------------------------------
6. ደረጃ፤ -------------------------------------------------------------------------

**ሠንጠረዥ (ለ)**

**ዝባዱ ወደ ውጭ አገር ሊወጣ ተገቢ መሆኑን የሚያረጋግጥ**

**የምስክር ወረቀት**

እኔ ----------------------- ----------------------------------------

(ስም) (የተፈቀደለት ላቦራቶሪ ስም)

(ማዕረግ) ------------------------------------------------------------------------------------

ከዚህ በታች የተዘረዘረው ዝባድ በእኔ ወይም በእኔ ተቆጣጣሪነት ተመርምሮ በደረጃ የተመደበ መሆኑን፤ ዝባዱም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ሊወጣ ተገቢ መሆኑንና ደረጃው ከዚህ እንደሚከተለው መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

የሲቪቶኑ መጠን፤ ----------------------------------------------------------------------------

ደረጃው፤ ---------------------------------------------------------------------------------------

**የፍትህ ሚኒስቴር**

**የዝባዱ ሁኔታ፤**

**(ክብደት፣ የከረጢት ቁጥር፣ የመለያ ምልክቶችና የተረፈው)**

**-----------------------------** **------------------------------------**

**(ቀን)** **(ስም)**

## አዋጅ ቁጥር 181/1992

## ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅትን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ለማስተላለፍ የወጣ አዋጅ

ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅት በከፊል ወደ ግል ይዞታ የተዛወረና ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተለወጠ በመሆኑ፤

ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት በማቋቋሚያ አዋጁ ተሰጥቶት የነበረውን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅትን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ለማስተላለፍ የወጣ አዋጅ ቁጥር 181/1992 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የሞኖፖሊ መብት መተላለፍ**

   1. ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶችን ለመግዛት፤ ለመቀመም፤ በፋብሪካ ሠርቶ ለማውጣት፤ ለመሸጥ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ወደውጭ ለመላክ ለብሔራዊ የትምባሆ ድርጅት በማቋቋሚያው አዋጅ ቁጥር 37/1985[41] በአንቀጽ 2 እና 9 ድንጋጌዎች መሠረት ተሰጥቶት የነበረው የሞኖፖሊ መብት በዚህ አዋጅ ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ተላልፏል፡፡

---

[41] ይህ አዋጅ ብሔራዊ ትንባሆ ደርጅትን ማቋቋሚያ ሲሆን በተጠቃለሉ ህጎች ውስጥ አልተካተተም፡፡ ሆኖም አንቀፅ 2 እና 9 ተፈፃሚነታቸው እንዲቀጥል ተደረገ በመሆኑ እንደማጣቀሻ ያገለግሉ ዘንድ ከአዋጁ ውስጥ ተወስደው እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣

   1.“ትምባሆ” ማለት ቅጠሎቻቸው ለመጤስ፣ ለመታኘክና ሱረት ለመሆን የሚጠቅሙ “ኒኮቲኒያ” ተብለው የሚታወቁት ልዩ ልዩ ተክሎች ናቸው፡፡

   2.“የትምባሆ ውጤቶች” ማለት ሲጃራ፣ሲጋራ፣ ሲጋሪሎስ፣ ሱረት፣ የሚታኘክና የፒፓ ትምባሆ እንዲሁም የትምባሆ ተረፈ ምርቶች ሁሉ ማለት ነው፡፡

9. **ልዩ ሥልጣን**

   ድርጅቱ ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶችን ለመግዛት፣ ለመቀመም፣ በፋብሪካ ሠርቶ ለማውጣት፣ ለመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ወደ ውጭ ለመላክ ብቸኛ ሥልጣን አለው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር የተላለፈውን የሞኖፖሊ መብት ለማስከበር አግባብ ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 37/1985 አንቀጽ 10-13 ድንጋጌዎች[42] ተፈጻሚነት ይቀጥላል፡፡

3. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአሥር ዓመታት ጸንቶ ይቆያል።

**አዲስ አበባ ህዳር 8 ቀን 1992 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጲያ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**አዋጅ ቁጥር 103/1990**

[42] ይህ አዋጅ ብሐራዊ ትንባሆ ደርጅትን ማቋቋሚያ ሲሆን በተጠቃለሉ ህጎች ውስጥ አልተካተተም፡፡ ሆኖም አንቀፅ 10 እስከ 13 ተፈፃሚነታቸው እንዲቀጥል ተደረገ በመሆኑ ከአዋጅ ውስጥ ተወስደው እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

10. **ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን**

ድርጅቱ በሚያቀርበው አስተያየት መሠረት ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ሌሎች ባለሥልጣኖች ከውክልና ፈቃድ እንዲሰጡ ሥልጣን ካልሰጣቸው በስተቀር፣ ድርጅቱ ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶች ከውጭ ለማስመጣት ወደ ውጭ ለመላክ ለመሸጥ፣ ለማዘጋጀትና በፋብሪካ ሠርቶ ለማውጣት ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡

11. **ክልከላ**

ማንም ሰው በድርጅቱ ወይም በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በተመደቡ ባለሥልጣኖች ፈቃድ ሳይሰጠው፣ ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶች ከውጭ ለማስመጣት ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለማዘጋጀት፣ በፋብሪካ ሠርቶ ለማውጣት ወይም ለመሸጥ አይችልም፡፡

12. **የመያዝ ሥልጣን**

በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የተመደቡ ወይም ሥልጣን የተሰጣቸው ተቆጣጣሪዎች ወይም ሠራተኞች

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ባልተሰጠው ማንኛውም ሰው እጅ ትምባሆ ወይም የትምባሆ ውጤቶች ካገኙ፣ እነዚህኑ ዕቃዎች መያዝ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተያዙትን ዕቃወች በሚመለከት አግባብ ያለው ፍ/ቤት ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ዕቃዎቹን ይዘው ይቆያሉ፡፡

13. **ቅጣት**

ይህን አዋጅ የሚጥስ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በተሰጠው ፈቃድ የተመለከቱትን ግዴታዎች የማይፈጽም፣ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

ጉዳዩን የሚያየው ፍርድ ቤት ከማንኛውም ሌላ ቅጣት በተጨማሪ ከሕግ ውጭ ተይዘው የተገኙትን ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶች ለመንግሥት እንዲወረሱ ሊያዝ ይችላል፡፡

## የካፒታል እቃ ኪራይ ንግድ ስራ አዋጅ

በልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ለመሳተፍ ፍላጐት፡ ዕውቀትና ሙያ ኖሯቸው በካፒታል እጥረት ምክንያት መንቀሳቀስ ላልቻሉ ባለሀብቶች አማራጭ የገንዘብ አቅርቦት ምንጮች ማቋቋም የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

አሁን ባሉት የገንዘብ ተቋማት መፍትሔ ሊገኝለት ያልቻለውን ክፍተት የካፒታል ዕቃ አከራዮች ሊሸፍኑት ይችላሉ ተብለው በመታመኑ፤

የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራን በሚመለከት በሥራ ላይ ያሉት ሕጐች የተሟሉ ሆነው ባለመገኘታቸው፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**[43]

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ማከራየት" ማለት አከራይ አንድን የካፒታል ዕቃ በፋይናንስ ኪራይ ወይም በአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ወይም በዱቤ ግዥ ስምምነት መሠረት ያለምንም መያዣ በየተወሰነ ክፍለ ጊዜ የሚፈጸም ክፍያ እየተቀበለ ተከራዩ ለተወሰነ ጊዜ ለምርትና ለአገልግሎት መስጠት ዓላማ እንዲጠቀምበት የሚፈቀድበት በዓይነት የሚደረግ የፋይናንስ አቅርቦት ነው፤
   2. "የኪራይ ስምምነት ወይም ስምምነት" ማለት በዚህ አዋጅ ውስጥ እንደተተረጐመው የፋይናንስ ኪራይ፣ የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ወይም የዱቤ ግዢ ማለት ነው፤
   3. "የፋይናንስ ኪራይ" ማለት አከራዩ፤

      ሀ) ቀደም ሲል ይዞት የሚገኘውን የካፒታል ዕቃ ወይም

[43] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8, 10 እና 13 በ19/60(2005) አ.807 አንቀጽ 2(1) እና 2(2) የተሻሻሉ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 14, 15 እና 16 አዲስ ተጨምረዋል፡፡

ለ) በተከራዩ መራጭነት አቅራቢ ተብሎ ከሚጠራው ሦስተኛ ወገን የሚገዛውን የካፒታል ዕቃ፣ ተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በየተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አከራይ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ ዓይነት ነው፤

4. "የዱቤ ግዢ" ማለት አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሠረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቀድበት፣ እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራዩ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበትና ተከራዩ የመጨረሻውን ክፍያ እንደፈጸመም በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያውኑ የሚያገኝበት የኪራይ ዓይነት ነው፤
5. "የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ" ማለት በአከራዩ እጅ የሚገኝ አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ተከራዩ በሁለት ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ኪራይ በመክፈል ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲጠቀምበት የሚከራይበት የኪራይ ዓይነት ነው
6. "ተከራይ" ማለት በኪራይ ስምምነት መሠረት ለተወሰነ ጊዜ አንድን የካፒታል ዕቃ ኪራይ እየከፈለ ለመጠቀም ከአንድ አከራይ ላይ የሚከራይ ሰው ነው፤
7. "አከራይ" ማለት በኪራይ ስምምነት መሠረት ለተወሰነ ጊዜ አንድን የካፒታል ዕቃ ኪራይ እየተከፈለው አንድ ተከራይ እንዲገለገልበት የሚያከራይ ሰው ነው፤
8. "የካፒታል ዕቃ" ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ማንኛውም መሳሪያ ወይም ማሽን ሲሆን አክሰሰሪዎችን ይጨምራል፤
9. "አቅራቢ" ማለት ከአከራይ ወይም ተከራይ ሌላ ሆኖ የካፒታል ዕቃዎችን በመሸጥ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
10. "የኢንቨስትመንት ሕግ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 ወይም ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 ወይም ሁለቱም ነው፣
11. "ሊሰረዝ የማይችል ስምምነት" ማለት በሕግ አፈጻጸም ወይም በስምምነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሊሠረዝ የማይችል የኪራይ ስምምነት ነው፡

12. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
13. “ሚኒስቴር” ማለት የንግድ ሚኒስቴር ነው[44]፤
14. “የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ” ማለት የፋይናንስ ኪራይ እና የዱቤ ግዢን ያጠቃልላል፡
15. “ዋና ስራ አስፈጻሚ” ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የአንድን አከራይ የእለት ተእለት ስራዎች በዋና ኃላፊነት ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤
16. “ዳይሬክተር” ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የአንድ አከራይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው።።

## ክፍል ሁለት

## የፈቃድ አሰጣጥ፣ የኪራይ ስምምነት ባህሪያትና የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች

### 3. የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ንግድ ስራ ፈቃድ[45]

1. የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ንግድ ሥራ የሚካሄደው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ በተሰጠው አከራይ ይሆናል፡፡
2. የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ሊሰራ አይችልም።
3. ሚኒስቴሩ የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 4. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ፈቃድ

1. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ የሚካሄደው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጠው አከራይ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ተጨማሪ ፈቃድ ሳያስፈልገው በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ላይ ሊሰማራ ይችላል፡፡
3. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ንግድ ሥራ ሊሰራ አይችልም።
4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፡-

   ሀ) የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው

---

[44] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የንግድ እና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[45] ቀድሞ አንቀጽ 3 የነበረው በ19/60(2005) አ.807 አንቀጽ 2(3) ተሰርዞ በአዲስ አንቀጽ 3 እና 4 የተተካ ሲሆን ከአንቀጽ 4 እስከ 19 የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 5 እስከ 20 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

መስፈርቶች፤

ለ) በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ኩባንያ ዳይሬክተሮች እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ማሟላት ስላለባቸው የብቃትና ችሎታ መስፈርቶች፤

ሐ) በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ የተሰማራ ኩባንያ ሊይዝ ስለሚገባው የካፒታል መጠንና መጠባበቂያ፤እና

መ) ለአጠራጣሪ ሂሣቦች ስለሚያዘው መጠባበቂያና ለቋሚ ንብረቶች ስለሚደረግ የእርጅና ቅናሽ፤መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ አሰራሩ ለአደጋ ያልተጋለጠ፣ አስተማማኝና ጤናማ መሆኑን ለማረጋገጥ፡-

ሀ) ሪፖርቶች በኩባንያው በየጊዜው እንዲቀርብለት ማዘዝ፤

ለ) በኩባንያው ላይ በማናቸውም ጊዜ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በቦታው ተገኝቶ ቁጥጥር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ፤

ሐ) የኩባንያውን ዳይሬክተር ወይም ዳይሬክተሮች ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚ ከሥራ ማገድ ወይም ማሰናበት፤ እና

መ) ማናቸውንም ሌላ አግባብነት ያለውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤ ይችላል፡፡

6. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ስልጣን ባለው መንግስታዊ አካል ፈቃድ ተሰጥቶት በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ 12 ወራት ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

5. <u>የኪራይ ስምምነቶች አጠቃላይ ባህሪያት</u>

ማንኛውም የኪራይ ስምምነት ቢያንስ የሚከተሉትን ይይዛል፡

1. የኪራይ ዓይነቱን፤
2. የካፒታል ዕቃውን ለመለየት የሚያስችል በቂ መግለጫ፣ የካፒታል ዕቃውን ሙሉ ዋጋ እና በኪራይ ስምምነቱ መሠረት የሚከፈለውን ጠቅላላ ኪራይ፣
3. የእያንዳንዱ ኪራይ መጠን፣ ጠቅላላው ኪራይ የሚከፈልበት ጊዜና እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ የሚደረግበት ቀን ወይም ቀኑ የሚወሰንበት ዘዴ፤ ተከራዩ በውሉ መሠረት በተወሰነው ቀን ኪራዩን የሚከፍል መሆኑን፤

4. ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ሦስተኛ ወገኖች በካፒታል ዕቃው ላይ ጉዳት ቢያደርሱበት ተከራዩ የማሠራት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ድንጋጌ፤
5. ተከራዩ የካፒታል ዕቃው በተላለፈለት ጊዜ አገልግሎቱን የሚቀንስ ጉድለት ያለበት ሆኖ ካገኘው ስምምነቱን አቋርጦ የካፒታል ዕቃውን የመመለስ መብት ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ ድንጋጌ፤
6. በአከራዩና በካፒታል ዕቃ አቅራቢው መካከል ከተደረገ የሽያጭ ውል የሚመነጩ መብቶችንና ጥቅሞችን ለተከራዩ ለማስተላለፍ አከራዩ የገባው ቃል፤
7. ተከራዩ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ በስምምነቱ በተገለጸው ሁኔታ በተከራየው የካፒታል ዕቃ ላይ ሁከት የማይደረግበት የባለይዞታነት መብት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ቃል፤
8. ተከራዩ በካፒታል ዕቃው ሲጠቀም በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ሞት፥ የአካል ጉዳት ወይም የንብረት ጉዳት አከራዩ እንደአከራይነቱ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን የሚያሳይ ቃል።

6. <u>የኪራይ ስምምነቶች ልዩ ባህሪያት</u>

1. የፋይናንስ ኪራይ ስምምነትን በሚመለከት፤

ሀ) ተከራዩ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ የካፒታል ዕቃውን ለአከራዩ እንደባለአደራ ብቻ ሆኖ ይይዛል፤ በካፒታል ዕቃው ላይም ምንም ዓይነት ባለቤትነት መብት አይኖረውም፤

ለ) ስምምነቱ ውል የተገባበት ሙሉ ዋጋ በኪራይ ተከፍሎ የሚሸፈንበትና ሊሠረዝ የማይችልበት ስምምነት ይሆናል፤

ሐ) የስምምነቱ ጊዜ ሲያበቃ ሁለቱ ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን የመግዛት ምርጫ ሊኖረው ይችላል፤ ካልተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ለአከራዩ ይመልሳል፤

መ) ተከራዩ ለካፒታል ዕቃው መድን የመግባትና ተገቢውን እድሳት የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ መገለጽ ይኖርበታል።

2. የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ስምምነትን በሚመለከት፤

ሀ) ተከራዩ የተከራየው የካፒታል ዕቃ የአከራዩ ንብረት ሆኖ የሚቆይና የስምምነቱ ጊዜ ሲያበቃ ሁለቱ ወገኖች በሚስማሙበት መሠረት ስምምነቱ እንደገና

እንዲራዘም ወይም ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን እንዲገዛ ካልተስማሙ በስተቀር ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ለአከራዩ የሚመልሰው ይሆናል፤

ለ) ስምምነቱ አለጊዜው በመቋረጡ ምክንያት በሌላው ወገን ላይ ጉዳት ያደረሰው ወገን ለደረሰው ጉዳት ካሳ የሚከፍል ሆኖ፣ ተከራይም ሆነ አከራይ ስምምነቱን የመሰረዝ መብት ይኖራቸዋል፤

ሐ) አከራይ ለካፒታል ዕቃው መድን የመግባትና ተገቢውን እደሳ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ መገለጽ ይኖርበታል።

3. የዱቤ ስምምነትን በሚመለከት፤

ሀ) እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተፈጸመ ቁጥር ለከፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ የባለቤትነት መብት እንዲሁም የመጨረሻው የኪራይ ክፍያ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ የካፒታል ዕቃው ሙሉ የባለቤትነት መብት ለተከራዩ የሚተላለፍለት ይሆናል፡

ለ) ስምምነቱ በማናቸውም ወገን አለጊዜው በሚቋረጥበት ጊዜ ከስምምነቱ የሚመነጭ የባለቤትነት መብቶችና ጥያቄዎች እልባት የሚያገኙበትን ሁኔታ ሁለቱ ወገኖች በስምምነቱ ያካትታሉ፤

ሐ) ተከራዩ ለካፒታል ዕቃው መድን የመግባትና ተገቢውን እደሳ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ መገለጽ ይኖርበታል።

7. <u>ኪራይን ስላለመከፈልና ሌሎች ጥፋቶች</u>

1. ተከራዩ ኪራዩን በወቅቱ ባይከፍል ወይም ስምምነቱን የሚጥስ ሌላ ጥፋት ቢፈጽም ተከራዩ የፈጸመው ጥፋት ሊወገድ የሚችል ከሆነ በስምምነቱ መሠረት እንዲፈጽም አከራዩ የ30 ቀን ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፡፡

2. ተከራዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ጥፋቱን ባያስወግድ አከራዩ ስምምነቱን መሠረዝ፣ የካፒታል ዕቃውን ወደ ይዞታው መመለስና ለደረሰበት ጉዳት ካሣ መጠየቅ ይችላል፡፡

3. ተከራዩ ኪራዩን በወቅቱ ያልከፈለ እንደሆነ ጥፋቱ የተወገደ ወይም ያልተወገደ ቢሆንም እንኳ አከራይ ውዝፉን ኪራይ ከወለድና ካሣ ጋር ማስከፈል ይችላል።

8. <u>በተከራየው የካፒታል ዕቃ ላይ ስላሉ ጉድለቶች</u>

1. ስምምነቱ በተደረገበት ወቅት በተከራዩ ለታወቀ የካፒታል ዕቃ ጉድለት አከራዩ ኃላፊነት የለበትም፡፡

2. አከራዩ የካፒታል ዕቃውን ለተከራዩ ባስረከበበት ወቅት ያወቀውን ወይም ሊያውቀው የሚገባውን ጉድለት ለተከራዩ ሳያሳውቀው ቀርቶ በካፒታል ዕቃው ጉድለት ምክንያት በተከራዩ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
3. በኪራይ ስምምነቱ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር፤ ተከራዩ በሰጠው ዝርዝር የመምረጫ መስፈርት መሠረት አከራይ የካፒታል ዕቃውን እስከገዛ ድረስ ዕቃው ለተፈለገው ዓላማ አገልግሎት ለመስጠት ጉድለት ያለበት ወይም የማይስማማ ሆኖ ቢገኝ በኃላፊነት አይጠየቅም።
4. ተከራዩ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ በኪራይ ስምምነቱ መሠረት ወይም ተቀባይነት ያለውን ሥርዓት ወይም አጠቃቀም በመከተል የማይገለገልበት ከሆነና የተከራዩ አጠቃቀም በካፒታል ዕቃው ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ አከራዩ ለተከራዩ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱን ለመሠረዝና የአከራየውን የካፒታል ዕቃ ወደ ይዞታው ለመመለስ መብት አለው።

9. <u>ስለመክሰር</u>

1. በኪራይ ስምምነቱ መሠረት ተከራዩ ግዴታውን እስከተወጣ ድረስ አከራዩ እንደከሰረ በፍርድ ቤት ቢወሰን እንኳን የከሰረውን አካል በሕግ የሚተካ አካል በስምምምነቱ ግዴታዎችና ሁኔታዎች መሠረት ይቀጣል።
2. የተከራዩ መክሰር በፍርድ ቤት ቢወሰንም በተከራየው የካፒታል ዕቃ ላይ አከራዩ ያለውን የባለቤትነት መብት አያሳጣውም፤ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

10. <u>ስለጉዳት ካሣ</u>

1. ስምምነቱ በተከራዩ በሚሠረዝበት ጊዜ ተከራዩ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ ለአከራዩ እንዲመልስ ተገቢው ማሳሰቢያ ተሰጥቶት ካላስረከበ አከራዩ የካፒታል ዕቃውን ወዲያውኑ ወደ ይዞታው የመመለስና ለደረሰበት ጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብት አለው፡፡
2. የሚከራየው የካፒታል ዕቃ ከአከራይ ወደ ተከራይ ከመተላለፉ በፊት በተከራይ ጥፋት ምክንያት በአከራይ ላይ ማናቸውም ጉዳት ቢደርስበት፣ አከራይ በቅን ልቦና እስከፈጸመና በተከራይ ጥያቄ የካፒታል ዕቃውን ለመግዛት ወጪ የደረሰበት እስከሆነ ድረስ ተከራይ በአከራይ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ መክፈል አለበት።

3. የፋይናንስ ኪራይን እና የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይን በሚመለከት ተከራዩ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ የስምምነቱ ጊዜ ሲያልቅ ሳይመልስ የቀረ እንደሆነ በስምምነቱ ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር አከራዩ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ ወደይዞታው የመመለስና ለደረሰበት ጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብት አለው።

11. **መብትን ስለማስተላለፍ**

ተከራዩ በስምምነቱ መሠረት በካፒታል ዕቃው በሰላም ለመጠቀም ያለውን መብት እስካልተጋፋ ድረስ አከራዩ በኪራይ ስምምነቱ መሠረት ያገኘውን መብት ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ የተናጠል መብት አለው፡፡

12. **በሦስተኛ ወገኖች የሚቀርብ ጥያቄ**

1. በካፒታል ዕቃው ላይ መብት አለኝ በማለት በሦስተኛ ወገን የሚቀርብ ማንኛውም ክስ በአከራዩ ላይ መቅረብ አለበት።
2. የተከራዩን አበዳሪዎች ጨምሮ ሌሎች ሦስተኛ ወገኖች በካፒታል ዕቃው ላይ ከሚያቀርበቸው ጥያቄዎች ይልቅ አከራዩ ያለው የባለቤትነት መብት ምንጊዜም ቅድሚያ ይሰጠዋል።
3. ተከራዩ በካፒታል ዕቃው በሰላም እንዳይጠቀም በሦስተኛ ወገኖች የሚደርስበትን ችግር ወይም ሁከት ለአከራዩ ማሳወቅ አለበት።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተገለጸው መሠረት ተከራዩ አከራዩን ሳያሳውቅ የቀረ ወይም የዘገየ እንደሆነ አከራዩ ለሚያወጣው ወጪና ለሚደርስበት ጉዳት ኃላፊ ይሆናል።
5. ሦስተኛ ወገን በአከራዩ ላይ በሚያቀርበው ክስ ምክንያት የካፒታል ዕቃው ዋጋ የቀነሰ እንደሆነ ተከራይ በአዲሱ ዋጋ መሠረት ኪራይ እንዲቀንስለት ወይም ስምምነቱ እንዲሰረዝ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

13. **የኪራይ ስምምነት መቋረጥ**

1. ማንኛውም የኪራይ ስምምነት በስምምነቱ በተገለጸው ቀን ይቋረጣል።
2. በኪራይ ስምምነቱ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር በተከራዩ መሞት ወይም ችሎታ ማጣት ምክንያት ስምምነቱ አይቋረጥም።
3. የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ስምምነት ዘመን ሲያበቃ ተከራይ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ እንደያዘ ቢቀርና አከራይም እንዲመለስለት

ባይጠይቅ ከተዋዋዮቹ ወገኖች አንደኛው ስምምነቱ እንዲቋረጥ እስከሚጠይቅ ድረስ በመጀመሪያ የተገባው የኪራይ ስምምነት እንደተራዘመ ይቆጠራል።

14. **ተከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ግዴታ መፍጠር የሌለበት ስለመሆኑ**

1. ተከራዩ በተከራየው የካፒታል ዕቃ ላይ ማናቸውንም የክፍያ ወይም ሌላ ግዴታ መግባት አይችልም።
2. የክፍያ ወይም ሌላ ማናቸውም ግዴታ በካፒታል ዕቃው ላይ በተከራዩ የተገባ እንደሆነ፣ ይኸው ግዴታ ዋጋ የሌለው ይሆናል።
3. በካፒታል ዕቃው ላይ በአከራዩ የተገባ ግዴታን ወይም የሚጠየቅ ግብርን የሚችለው አከራዩ ነው።

15. **የካፒታል ዕቃውን ስለመያዝና ስለመጠበቅ**

1. ተከራዩ የካፒታል ዕቃው በእጁ እስካለ ድረስ በጥንቃቄ ይይዛል፣ ይጠብቃል።
2. ተከራዩ ያለአከራዩ ፈቃድ የካፒታል ዕቃውን አጠቃቀም ሁኔታ መቀየር አይችልም።

**ክፍል ሦስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

16. **ማበረታቻዎች**[46]

1. አከራይ ለኪራይ ተግባር የሚውሉ የካፒታል ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ በሚያስገባበት ጊዜ በኢንቨስትመንት ሕጉና በዚሁ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን የኢንቨስትመንት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የመሆን መብት አለው።
2. “የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም አቅራቢ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ከውጭ አገር ለሚያስገባው የካፒታል ዕቃ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ የመሆን መብት አለው፡፡
3. በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ለተገዛ የካፒታል ዕቃ ክፍያ ለአከራይ በሚፈፀምበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ አይከፈልበትም።

17. **ስለ እርጅና ቅናሽና በገቢ ላይ ስለሚጣል ግብር**

[46] 19/60(2005) አ.807 አንቀጽ 2(5) ተሻሻለ፡፡

1. የፋይናንስ ኪራይን እና የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይን በሚመለከት አከራይ የካፒታል ዕቃው ባለቤት በመሆን የካፒታል ዕቃዎቹ የእርጅና ቅናሽ ከሚገኘው የኪራይ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡ ሆኖም የዱቤ ግዥ ስምምነትን በሚመለከት የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለተከራዩ ይሆናል፡፡
2. በኪራይ ስምምነት መሠረት አከራይ የሚያገኘው ኪራይ እንደገቢ ይቆጠራል።
3. በተከራይ የሚከፈል ኪራይ እንደመደበኛ ወጪ ተቆጥሮ ለግብር ዓላማ ከተከራይ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይሆናል፡፡

**18. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ የሚኒስቴሩ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥልጣንና ተግባር</u>**[47]

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፡-
   ሀ) የካፒታል ዕቃ ምዝገባና ቁጥጥርን የሚመለከት ደንብ፤ እና
   ለ) ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ደንቦችን፤ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ የካፒታል ዕቃ ስምምነቶች፣ ማሻሻያዎች፣ ለውጦች እና የተቋረጡ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶችን ይመዘግባል።
3. ሚኒስቴሩ ተከራዩ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ የመመለስ ግዴታ ቢኖርበትና ባይመልስ የካፒታል ዕቃው ለአከራዩ መመለሱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አግባብ ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤ ለአፈጸጸም እንዲረዳው ፖሊስን ሊያዝ ይችላል፡፡
4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ መሠረት የካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**19. <u>የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>**

በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሕግ እና የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በኪራይ ስምምነት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

[47] በ19/60(2005) አ.807 አንቀጽ 2(6) ተሻሻለ፡፡

20.**<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከየካቲት 26 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 26 ቀን 1990 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

## ደንብ ቁጥር 309/2006 ዓ.ም

## ስለካፒታል እቃዎችና ስለካፒታል እቃ ኪራይ ስምምነቶች ምዝገባና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 ዓ.ም አንቀጽ 5 እና በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 ዓ.ም (በአዋጅ ቁጥር 807/2005 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 18 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች ምዝገባና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 309/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

   1. "አዋጅ" ማለት የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 (በአዋጅ ቁጥር 807/2005 እንደተሻሻለ) ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከቱት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነት" ማለት የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ወይም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ስምምነት ነው፤
   4. "መዝጋቢ አካል" ማለት ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት ሚኒስቴሩ ሲሆን በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት አግባብ ያለው የክልሉ አካል ነው፤
   5. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ፡ የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
   6. "ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ" እና "አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ" የሚሉት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/2003 አንቀጽ 2 (1) እና (2) የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤

7. "ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ" ማለት ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተቀመጠውን የሰው ኃይልና ጠቅላላ ሃብት ደረጃ በማለፍ ወደ መደበኛ ኩባንያነት በመሸጋገር ላይ ያለ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
8. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>ስለካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ</u>

1. በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ለተከራዮች የሚያቀርባቸውን የካፒታል ዕቃዎች የማስመዝገብ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የካፒታል ዕቃን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ መዝጋቢ አካሉ ባዘጋጀው ቅጽ ላይ ተሞልቶና ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-
   ሀ) አስመዝጋቢው በሚመለከተው አካል የተሰጠውን የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ ንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የካፒታል ፋይናንስ ንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ፈቃድ፤
   ለ) የካፒታል ዕቃውን ለመለየት የሚያስችል መግለጫ፤
   ሐ) አመልካቹ የካፒታል እቃው ባለቤት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤
   መ) መዝጋቢው አካል የሚጠይቃቸው ሌሎች ሰነዶች፡፡
3. መዝጋቢው አካል የቀረበውን ማመልከቻ መርምሮ ትክክለኛ ሆኖ ሲያገኘው የካፒታል ዕቃውን በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 (1) መሠረት ይመዘግበዋል፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀትም ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተደረገ የካፒታል ዕቃ ምዝገባ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

4. <u>የካፒታል ዕቃ ምዝገባን ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

1. የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት ማንኛውም ህገወጥ ድርጊት ተፈፅሟል ተብሎ ሲገመት ምዝገባው ሊታገድ ይችላል፡፡ የእገዳው የጊዜ ገደብ ከ30 ተከታታይ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የካፒታል ዕቃ ባለቤት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘው በህገወጥ ወይም በተጭበረበረ መንገድ መሆኑን መዝጋቢው አካል ሲያረጋግጥ ምዝገባውን ይሰርዘዋል፡፡

3. የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠበት የካፒታል ዕቃ ሙሉ በሙሉ መውደሙ ሲረጋገጥ ምዝገባው ይሰረዛል፡፡ ባለቤቱም የካፒታል ዕቃው በወደመ ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለመዝጋቢው አካል በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

5. <u>**ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት**</u>

የካፒታል ዕቃ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበሳሸበት ሰው ለመዝጋቢው አካል ሲያመለክትና መዝጋቢው አካል ሲያምንበት አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልቶ ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

6. <u>**ስለካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነት ምዝገባ**</u>

1. በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ከማንኛውም ተከራይ ጋር የገባውን የካፒታል እቃ ኪራይ ስምምነት እና የስምምነቱን መሻሻል፣ መለወጥ ወይም መቋረጥ የማስመዝገብ ኃላፊነት አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነትን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ መዝጋቢ አካሉ ባዘጋጀው ቅጽ ላይ ተሞልቶና ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) የካፒታል ዕቃ ኪራይ ውሉ ቅጂ፤

ለ) የካፒታል ዕቃው ምዝገባ ምስክር ወረቀት፤ እና

ሐ) መዝጋቢው አካል የሚጠይቃቸው ሌሎች ሰነዶች፡፡

3. መዝጋቢው አካል የስምምነቱ ይዘት አግባብ ካላቸው የአዋጅና የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሲያረጋግጥ ስምምነቱን ይመዘግባል።
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተመዘገበ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ያልተመዘገበ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነት ወይም የስምምነቱ መሻሻል፣ መለወጥ ወይም መቋረጥ የህግ ውጤት አይኖረውም፡፡

7. <u>**የምዝገባ አገልግሎት ክፍያ**</u>

1. የካፒታል ዕቃ ወይም የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነት ለማስመዝገብ ለሚኒስቴሩ የሚከፈል የምዝገባ አገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል፡፡

2. የካፒታል ዕቃ ወይም የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነት ለማስመዝገብ ለክልል መዝጋቢ አካል የሚከፈል የምዝገባ አገልግሎት ክፍያ አግባብ ባለው የክልሉ አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡

8. **ቁጥጥርና የብቃት ምርመራ ስለማድረግ**

1. መዝጋቢው አካል በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ለጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በተከራዩት የካፒታል ዕቃዎች ላይ የአጠቃቀም ቁጥጥርና የብቃት ምርመራ እንዲደረግ ያስተባብራል፡፡
2. የካፒታል ዕቃ አከራዮችና ተከራዮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በሚደረገው የቁጥጥር ወይም የብቃት ምርመራ ውጤት መሰረት የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች የመተግበር ግዴታ ይኖርባቸዋል።

9. **የመዝጋቢው አካል ሥልጣንና ተግባር**

የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ መዝጋቢው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለተከራዮች የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎችን በዓይነት፣ በመጠን፣ በአምራች፣ በስሪት ዘመንና በመሳሰሉት በመለየትና በአምራች የተሰጧቸውን መለያ ቁጥሮች በመጥቀስ ይመዘገባል፤
2. ስለተመዘገቡት የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች የመረጃ ስርዓት ይገነባል፣ የተሟላ፣ የተናበበና የተቀናጀ አገራዊ መረጃ ይይዛል፤
3. የተመዘገቡ የካፒታል ዕቃዎች መለያ ቁጥሮች የተቀየሩ ወይም የተሠረዙ አለመሆናቸውን ይቆጣጠራል፤
4. የካፒታል ዕቃዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 (1) መሠረት ለሚደረግ ምርመራ የሚቀርቡበትን ቦታና ጊዜ ወይም ባሉበት ቦታ እንዲመረመሩ ይወስናል፤ የምርመራ ሂደቱን ያስተባብራል፤
5. የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች ምዝገባ ለማከናወን የአንድ መስኮት አገልግሎት ለሚሰጥ አካል ወይም ሌላ አግባብ ላለው አካል እንደአስፈላጊነቱ ውክልና ይሰጣል፤
6. የካፒታል ዕቃ ምዝገባ የሚታገድበት ወይም የሚሰረዝበት ሁኔታ ሲያጋጥም በማስረጃ በማጣራትና በማረጋገጥ ምዝገባውን ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤ እንደ

አስፈላጊነቱም በሚኒስቴሩ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

7. ከካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

10.**<u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>**

1. ሚኒስቴሩ በሚዘረጋው የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት የክልል መዝጋቢ አካላት የተሟላ የምዝገባ መረጃ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋሉ።
2. ማንኛውም መዝጋቢ አካል ስለካፒታል ዕቃ ምዝገባ መረጃ ለሚጠይቅ ሰው ተገቢውን መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
3. ተከራዮች በእጃቸው የሚገኙትን የካፒታል ዕቃዎችን በተመለከተ ሲጠየቁ ወይም በሚዘረጋው ሥርዓት መሰረት በየወቅቱ ለመዝጋቢ አካሉ መረጃ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

11.**<u>የተከለከሉ ተግባራት</u>**

የሚከተሉት የተከለከሉ ተግባራት ናቸው፡-

1. በዚህ ደንብ መሠረት የሚጠየቁ መረጃዎችን አለመስጠት ወይም የተሳሳቱ መረጃዎችን መስጠት፤
2. የተመዘገበን የካፒታል ዕቃ ድጋሚ እንዲመዘገብ ማድረግ፤
3. የካፒታል ዕቃን መለያ ቁጥር መቀየር ወይም መሠረዝ፤
4. አዋጁን፣ ይህንን ደንብ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን የሚጥስ ድርጊት መፈጸም፡፡

12.**<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

ከዚህ ደንብ መውጣት በፊት የተመዘገቡ የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች በዚህ ደንብ መሠረት እንደተመዘገቡ ይቆጠራሉ።

13.**<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## የፍትህ ሚኒስቴር

### የምዝገባ አገልገሎት የክፍያዎች ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | የክፍያ መጠን (በብር) |
|---|---|---|
| 1 | ለማመልከቻ ቅፅ | 2 |
| 2 | ለካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ | 100 |
| 3 | ለካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ ዕድሳት | 100 |
| 4 | ለምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት | 50 |
| 5 | ለካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ ስረዛ | 80 |
| 6 | ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል ምዝገባ | 100 |
| 7 | ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል ማሻሻያ ምዝገባ | 80 |
| 8 | ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል መቋረጥ ምዝገባ | 100 |

## አዋጅ ቁጥር 261/1994 ዓ.ም

## በአፍሪካ የእድገትና የተጠቃሚነት ሕግ መሠረት የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ምርቶችን ወደ አሜሪካ ሀገር ስለመላክ የወጣ አዋጅ

የአሜሪካ መንግሥት አ.ኤ.አ ሜይ 18 ቀን 2000 ዓ.ም የአፍሪካ የዕድገትና የተጠቃሚነት ሕግ ያወጣ በመሆኑ፣

ይህ የሕግ ሰነድ የተመረጡ ከሠሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ወደ አሜሪካ አገር የሚልኳቸውን ምርቶች ከቀረጥ እና ከኮታ ነፃ ለማስገባት የሚያስችላቸው ስለሆነና ኢትዮጵያም የዚሁ ሕግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከተመረጡት ከሠሀራ በታች ከሆኑ አገሮች ውስጥ አንዷ በመሆኗ፤

በዚሁ ሕግ መሠረት የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርቶችን ያለ ቀረጥና ኮታ ወደ አሜሪካ ለመላክ የኢትዮጵያ መንግሥት የተስማማ በመሆኑና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አምራቾችና ላኪዎችም በዚሁ ስምምነት መሠረት እንዲሠሩ ለማድረግ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "በአፍሪካ የዕድገትና የተጠቃሚነት ሕግ መሠረት የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ምርቶችን ወደ አሜሪካ ሀገር ስለመላክ የወጣ አዋጅ ቁጥር 261/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "በአፍሪካ የዕድገትና የተጠቃሚነት ሕግ" ማለት (ከዚህ በኋላ "አዕተሕ") እ.ኤ.አ ሜይ 18 ቀን 2000 በአሜሪካ መንግሥት የተደነገገው "አፍሪካን ግሮውዝ ኤንድ ኦፖርቹኒቲ አክት" ነው፤
   2. "ሥልጣን የተሰጠው ሹም" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ የተደነገጉትን እንዲያስፈጽም በኢትዮጵያ የጉምሩክ ባለሥልጣን[48] የተወከለ ሠራተኛ ነው፤
   3. "በአዕተሕ የሚሸፈኑ ጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት" ማለት ከዚህ በታች ከምድብ 1 እስከ ምድብ 9 የተዘረዘሩት ናቸው፤

[48] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 21(ሀ) መሰረት የጉምሩክ ኮሚሽን በሚል ይነበብ፡፡

ምድብ 1.በአሜሪካ አገር ከተመረቱ ድርና ማግ በዚያው አገር ተመርቶና ለስፌት በሚያመች መልክ ተቆራርጦ የተዘጋጀ ጨርቅን በመጠቀም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሃራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ አገሮች የተሰፉ አልባሳት፡፡

ምድብ 2. ድርና ማጉ በአሜሪካ ሀገር የተሠራ፣ ጨርቁም በአሜሪካ አገር የተሠራና እዚያው አሜሪካ አገር ተቆራርጦ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሃራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ ሀገሮች የተሰፉ አልባሳት ሆነው፣ አልባሳቱ የአሜሪካንን አንድ ወጥ የታሪፍ ሥርዓት ንዑስ ርዕስ 9802.00.80 ሊያሟሉ የሚችሉ፣ ነገር ግን የመጥለፍ ፤ የስቶን ወይም የኢንዛይም ወይም የአሲድ እጥበት ፣ የቋሚ ተኩስ፣ የመቀቀል ፣ የማንጣት ፣ የማቅለም፣ በስክሪን የማተም እና ሌሎች ይህን የመሳሰሉ ሥራዎች የተከናወኑባቸው አልባሳት፤

ምድብ 3. አሜሪካ አገር ከተመረተ ድርና ማግ በአሜሪካ የተሠራ ጨርቅን በመጠቀም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሀራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ ሀገሮች ተቆራርጦ በተጠቃሚው አገር ውስጥ፤ በአሜሪካ በተሠራ ክር የተሰፉ አልባሳት፡

ምድብ 4. በአሜሪካ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሀራ በታች ከሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ ሀገሮች በተመረተ ድርና ማግ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሀራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ ሀገሮች ሙሉ በሙሉ የተሠራ ጨርቅን በመጠቀም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሃራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ ሀገሮች ሙሉ በሙሉ የተሰፉ አልባሳት፡፡

ምድብ 5. ከየትኛውም አገር በተገኘ ጨርቅ በዕድገታቸው ዝቅተኛ በሆኑ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሃራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ ሀገሮች ሙሉ በሙሉ የተሰፉ አልባሳት፡፡

ምድብ 6. በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሃራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ በአብዛኛው ከካሽሚር ሱፍ የተሠሩ እና በአሜሪካ አንድ ወጥ የታሪፍ ሥርዓት በንዑስ ርዕስ 6610.10 ሥር የሚመደቡ በልብስነት የተመረቱ ሹራቦች፤

ምድብ 7. 50 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ሱፍ ከሆነና 18.5 ማይክሮን ውፍረት ወይም ከዚያ በላይ የቀጠነ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ከሠሃራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ በልብስነት የተመረተ ሹራብ፡፡

ምድብ 8. ከሠሃራ በታች በሚገኙ ተጠቃሚ የአፍሪካ አገሮች ሙሉ በሙሉ የተሰሩት አልባሳት ጨርቅ ወይም ጨርቁ የተሠራበት ድርና የተሰፉበት ማግ በአሜሪካን አገር ወይም ከሠሃራ በታች በሚገኝ ተጠቃሚ የአፍሪካ አገር ያልተሠራ ቢሆንም፣ ከእነዚህ ጨርቆች ወይም ድርና ማግ የተሰፉት አልባሳት በሰሜን አሜሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ስምምነት አባሪ 401 መሠረት የተጠቃሚነት መብት ያለው፣ ወይም አሜሪካ ውስጥ ለንግድ በበቂ መጠን አለመኖሩ የተረጋገጠ፡፡

ምድብ 9. ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በሚደረጉ ውይይቶች የሚወሰኑ በእጅ የተሠሩ፣ የተፈተሉ፣ ወይም ባሕላዊ የሆኑ አልባሳት፡፡

4. “ባስሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፤[49]
5. ተጠቃሚ” ማለት ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) መሠረት ልዩ ምዝገባ ያደረገ አምራች ወይም ላኪ ማለት ነው፤
6. “ሰርቲፊኬት” ማለት በአዕተሕ መሠረት የሚሰጥ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ምርት የአምራች ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፤
7. “መስፈርቶችን ስላለማሟላት” ማለት የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርቶችን ወደ አሜሪካ አገር ለመላክ የዚህ አዋጅ እና የአዕተሕን ድንጋጌዎችና መስፈርቶች በተለያዩ ዘዴዎች መጣስ ወይም መተላለፍ ነው፤
8. “የዋጋ መግለጫ ሰነድ” ማለት ከሻጩ ለገዥ የሚሰጥ ዋጋን የሚገልጽ ሰነድ ነው፤
9. “ሚኒስቴር” ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤[50]
10. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ሰው ነው፤
11. “አቅጣጫ ማስቀየር” ማለት የአዕተሕ ተጠቃሚ ለመሆን ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ሀገር የሚላከን የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርት አሜሪካ ከመድረሱ በፊት በሌላ ሦስተኛ ሀገር ክልል ውስጥ የንግድ ተግባር እንዲፈጸምበት ማድረግ ነው፤
12. “ሐሰተኛ መረጃን መጠቀም” ማለት የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርትን ወይም ከምርቱ ማናቸውም አካል (ክፍል) ጋር በተገናኘ የአምራች ሀገር አመልካችነትን፣

[49] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 21(ሀ) መሰረት የጉምሩክ ኮሚሽን በሚል ይነበብ፡፡
[50] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

አፈበራረክ፣ የአመራረት ሂደትን ወይም መገጣጠምን በተመለከተ ሐሰተኛ መረጃ መጠቀም ነው፡፡

13.“የይለፍ ማስረጃ” ማለት ሥልጣን በተሰጠው ሹም አማካኝነት በዋናው የዋጋ መግለጫ ሰነድ ላይ የሚደረግ ሕጋዊ ማኅተም ነው።

3. **<u>አስፈጻሚ አካል</u>**

ይህንን አዋጅ የማስፈጸም ኃላፊነት ለባለሥልጣኑ የተሰጠ ሲሆን፤ በተለይም ባለሥልጣኑ፣

1. የይለፍ ማስረጃ የመስጠት፤
2. የአምራች ሀገር የምስክር ወረቀት የማረጋገጥ፤ እና
3. በአፅተሕ መሠረት መረጃ የመያዝና ሲጠየቅ መስጠት፤

ኃላፊነት አለበት፡፡

4. **<u>የተጠቃሚ መብት</u>**

በዚህ አዋጅ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ተጠቃሚ በአፅተሕ መሠረት ጨርቃ ጨርቅንና አልባሳትን ከቀረጥና ከታክስ ነጻ ወደ አሜሪካ የመላክ መብት አለው፡፡

5. **<u>የይለፍ ማስረጃ ስለማስፈለጉ</u>**

ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ በተገቢ ሁኔታ የተሰጠ የይለፍ ማስረጃ ሳይኖረው ማንኛውንም የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ምርቶችን በአፅተሕ መሠረት ወደ አሜሪካ ሀገር መላክ አይችልም።

6. **<u>ለይለፍ ማስረጃ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

1. ማንኛውም በአፅተሕ መሠረት ለጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ምርቶች የሚቀርብ የይለፍ ማስረጃ ጥያቄ የሚከተሉትን በማሟላት ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፤

   ሀ/ የዋጋ መግለጫውን ዋና ቅጅ እና ሁለት ፎቶ ኮፒዎች፣ እና

   ለ) የሰርቲፊኬቱን ሦስት ቅጂዎች፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ከተቀበለ በኋላ፤

   ሀ) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አመልካቹ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፤

ለ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማመልከቻው (የአ.ዕ.ህ.ተን) እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች አሟልቶ ሲገኝ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የይለፍ ማስረጃ ይሰጣል፡፡

3. ባለሥልጣኑ ጥያቄውን ካልተቀበለው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

7. <u>ስለ ምዝገባና መግለጫ</u>

1. ማንኛውም ተጠቃሚ፤

ሀ) በሚኒስቴሩ ልዩ ምዝገባ ማድረግ፤

ለ) ለእያንዳንዱ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ጭነት የኤክስፖርት መግለጫ ፎርም ሞልቶ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤ እና

ሐ) የማምረት ተግባሩን ባቋረጠ ወይም ማምረቻውን ጊዜ ልዩ ምዝገባው እንዲሰረዝ ማድረግ፣ አለበት።

2. ከባለሥልጣኑ በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ አሜሪካ አገር ከቀረጥና ኮታ ነፃ ለመላክ የሚያስችል ሠርቲፊኬትና ኤክስፖርት መግለጫ ፎርምን ማተም ወይም ማሳተም አይችልም።

8. <u>የይለፍ ማስረጃ ስለመከልከል</u>

ባለሥልጣኑ፤

1. የሚላኩት የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ምርቶች የዚህን አዋጅ እና (የአዕተህን) ድንጋጌዎች የሚያሟሉ ሆነው ካልተገኙ፤

2. የተጠቃሚው የመዛግብት አያያዝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የሰፈረውን የሚያሟላ ሆኖ ካልተገኘ፤የይለፍ ማስረጃ አይሰጥም።

9. <u>ሰነድና መዛግብት ስለመያዝ</u>

1. ማንኛውም ተጠቃሚ የሚከተሉትን የተሟሉ ሰነዶችና መዛግብት በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ ቋንቋ አዘጋጅቶ መያዝና ቢያንስ ለ10 ዓመታት መጠበቅ አለበት፤

ሀ) የምርት መዛግብት፣

ለ) ምርት ለማምረት የተጠቀመባቸውን ግብአቶች ዓይነት፣ መጠንና ምንጭ፣

ሐ) ለማምረት የተጠቀመባቸውን የማምረቻ መሣሪያዎች ዓይነት፣ መለያ እና ብዛት፣

መ) በምርት ሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ብዛት፣

ሠ) በአ.ዕ.ተ.ሕ መሠረት የተላከውን የምርት መጠን፣ እና

ረ) ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ አስፈላጊ መረጃዎችን፤

2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚገኘው ማናቸውም ሰነድና መረጃ በሚስጥር መያዝ አለበት።

10. <u>የተከለከለ ተግባር</u>

መስፈርቶችን ያለማሟላት፣ የምርትን አቅጣጫ ማስቀየር እና ሀሰተኛ መረጃ መጠቀም ለማንኛውም ተጠቃሚ በጥብቅ የተከለከሉ ተግባራት ናቸው።

11. <u>ስለመፈተሽ</u>

1. ሥልጣን የተሰጠው ሹም ወይም የእርሱ ተወካይ በማንኛውም ተገቢ በሆነ ሰዓት መታወቂያውን በማሳየት በተጠቃሚው መሥሪያ ቤት በመግባት፤

ሀ) ከሀሰተኛ መረጃ መጠቀም ጋር የተያያዙ ጥቆማዎችን ለማጣራት፤

ለ) የአዕተሕ እና የዚህን አዋጅ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ፣

ፍተሻ ማድረግ ይችላል፡፡

2. ሥልጣን የተሰጠው ሹም ወይም ተወካዩ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ፍተሻ ከአሜሪካ መንግሥት የጉምሩክ አገልግሎት ተወካይ ጋር በመሆን ሊያካሂድ ይችላል።

3. ማንኛውም ተጠቃሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የሰፈሩትን ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት መከልከል አይችልም።

12. <u>ስለፈቃድ መሠረዝ</u>

1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ የሠፈሩትን ድንጋጌዎች ያላከበረ ተጠቃሚን የንግድ ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የንግድ ፈቃዱ የተሠረዘበት ተጠቃሚ የንግድ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ተጠቃሚ አይሆንም።

3. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የንግዱ ፈቃዱ ለተሠረዘበት ማንኛውም ተጠቃሚ ወይም የንግድ ድርጅቱን ለወረሰ ወራሽ ወይም በዚሁ ተጠቃሚ ባለቤትነት ለተያዘ ሌላ ድርጅት ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በሚኖሩት አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ማንኛውም የንግድ ፈቃድ አይሰጠውም፡፡

13. <u>ቅጣት</u>

ማኛውም፡-

1. መስፈርቶችን ያላሟላ፣ ሀሰተኛ ማስረጃ የተጠቀመ ወይም የምርቱን አቅጣጫ ያስቀየረ፤
2. የይለፍ ማስረጃ ለማግኘት ካቀረበው ማመልከቻ ጋር በተያያዘ በተጨባጭ ሁኔታ ሀሰተኛ የሆነ፣ የተሳሳተ፣ ያልተሟላ ወይም አሳሳችነት ያለው ወይም ከትክክለኛው ምንጭ ያልተገኘ ሰነድ ወይም መረጃ ያቀረበ፣
3. በሀሰተኛ መረጃ የይለፍ ማስረጃ መገኘቱን ወይም የይለፍ ማስረጃ እንዲሰጥ የቀረበው መረጃ ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ይህንኑ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ያላሳወቀ፤
4. የይለፍ ማስረጃን ወደ ሀሰተኛነት የቀየረ፣ የለወጠ ወይም እንዲህ ያለውን ተግባር ተመሳጥሮ የሠራ፣ ወይም እንዲቀየር፣ እንዲለወጥ ወይም እንዲሠራ ያደረገ፤
5. በአዕተሕ መሠረት የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ምርቶችን በሚያመርቱ ወይም በሚልኩ ተቋማት ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚደረግ ፍተሻን የከለከለ፤
6. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አግባብ ያላቸውን መዛግብትና መረጃ ያልያዘ ወይም ለመያዝ ቸልተኝነት ያሳየ፤
7. የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ወይም ሚኒስቴሩ ወይም ባለሥልጣኑ ያወጣቸውን የሕዝብ ማስታወቂያዎች ወይም መመሪያዎች የተላለፈ፤

ሰው ወንጀሉ የተፈፀመበትን ንብረት ዋጋ ሶስት እጥፍ የንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

14. <u>ደንብ ስለማውጣት</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

15. <u>የሕዝብ ማስታወቂያ ወይም መመሪያዎች ስለማውጣት</u>

እንደአስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ ወይም ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሕዝብ ማስታወቂያ ወይም መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ።

16. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ 11 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 11 ቀን 1994 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

## አዋጅ ቁጥር 372/1996 ዓ.ም

## የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በሀገሪቱ የግብርና ምርት ውጤቶች አቅርቦት ከፍላጎት በጣም ሲልቅ ገበሬው ምርቱን በርካሽ ዋጋ ከሚሸጥ ምርቱን ለዕቃ አስቀማጮች በደረሰኝ የሚያስረክብበት እና መልሶ የሚረከብበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤ ሥርዓቱ በዕቃ አስቀማጩ እና በአደራ ሰጪው መካከል በሕግ ፊት የፀና ውል ለመደረጉ ማረጋገጫ ስለሚሆን፣ አስቀማጩ በማከማቻ ባስቀመጠው ምርት ላይ ያለውን መብት ለገዥዎች ማስተላለፍ ከፈለገ ደረሰኙን በማስረከብ ብቻ ሽያጭ የሚፈፀምበትን ሥርዓት መመሥረት ለአምራቹ ጠቀሜታ ስላለው፣ በተለይም ይህ ዓይነቱ ሥርዓት ዕቃውን ወይም የግብርና ምርት ውጤቱን በማከማቻ ቤት በማስቀመጥ የተቀበለውን ደረሰኝ መያዣ በማድረግ ከባንክ ወይም ከመሰል አበዳሪ ተቋማት ለመበደር ስለሚያስችል፣ ሥርዓቱ የግብርና ምርቶችን የዋጋ ውጣ ውረድ አደጋዎችን ለመከላከል፣ በደረጃ ላይ የተመሠረተ የተቀላጠፈ የግብርና ምርቶች ግብይት ለማስፈንና የንግድና ፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን እንዲስፋፉ ስለሚረዳ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 372/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የማሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ፦

   1. "የግብርና ምርት" ማለት ማኒስትሩ ወይም ሚኒስቴሩ የሚሰይመው አካል በተለያዩ ጊዜያት የግብርና ምርት ነው ሲል የሚወስነው ምርት ማለት ነው ፡፡
   2. "ዕቃ አስቀማጭ" ማለት በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሠነድ የግብርና ምርት ውጤቶችን ጨምሮ ዕቃዎችን ተቀብሎ የሚያስቀምጥና ለአደራ ሰጭው ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ከአደራ ሰጭው መብት ለተላለፈለት ሰው ዕቃዎቹን መልሶ ለማስረከብ ግዴታ የሚገባ ሰው ማለት ነው፤

3. “አደራ ሰጭ” ማለት ዕቃ በሌላ ጊዜ ለመውሰድ ፣ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ ለአበዳሪ ተቋም ወይም ለሌሎች ሰዎች በመያዣነት ለመስጠት በማሰብ በራሱ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ዕቃውን በዕቃ ማከማቻ ቤት የሚያስቀምጥ ሰው ማለት ነው፤
4. “የዕቃ ማከማቻ ውል” ማለት ዕቃ እየተቀበለ በማከማቻ ቤት ለማስቀመጥ አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ የተሰጠው ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ለአደራ ሰጭው ወይም ከእርሱ ዕቃውን ለገዛው ወይም ዕቃውን በመያዣነት ለተቀበለው ሰው ጥቅም ሲል ዕቃውን ተቀብሎ ለማስቀመጥ ግዴታ የሚገባበት ውል ማለት ነው፤
5. “ማስረከብ” ማለት አደራ ሰጭው የዕቃዎቹን ባለይዞታነት በራሱ ፈቃድ ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሚያስተላልፍበት፣ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱም ዕቃዎቹን ለአደራ ሰጭው፣ ከእርሱ መብት ለተላለፈላቸው ወይም የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙን በመያዣነት ለተቀበሉ ሰዎች መልሶ የሚያስረክብበት ሂደት ማለት ነው፤
6. “ሰነድ” ማለት አንድን ፍሬነገር በመረጃነት ለማስቀረት ሲባል በፊደል፣ በአኃዝ፣ በምልክት ወይም ከእነዚህ ከአንዱ በላይ በሆነ መንገድ ፍሬነገሩ የሚገለጽበት ወይም የሚብራራበት ማስረጃ ማለት ነው፤
7. “የሸቀጥ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ” ማለት በዘወትር የንግድና የፋይናንስ አሠራርና ልማድ ሰነዱን የያዘው ሰው ሰነዱንና በሰነድ የተመለከቱትን ዕቃዎች ለመቀበል፣ ይዞ ለማቆየት ወይም ለሌላ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት የሚያገኝበት በጽሑፍ የተመዘገበ ማስታወቂያ፣ መለያ ወይም መግለጫ ማለት ነው፤
8. “የኤሌክትሮኒክ ሰነድ” ማለት በኤሌክትሮኒክ፣ በማሳያ፣ ወይም በመሰል ዘዴዎች የወጣ፣ የተላከ፤ የደረሰ ወይም የተቀመጠ ሰነድ ማለት ሲሆን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ፤ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት፣ በቴሌግራም፣ በቴሌክስና በቴሌኮፒ የወጣ መረጃን ይጨምራል፤
9. “ተተካኪ ዕቃዎች” ማለት በተፈጥሮ ባህሪያቸው ወይም በልማዳዊ የንግድ አሠራር ዕርስ በእርሳቸው ሊለዋወጡና ሊተካኩ የሚችሉ ዕቃዎች ማለት ነው፤
10. “ዕቃዎች” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የዕቃ ማከማቸት ውል ሊደረግባቸው የሚችሉ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ማለት ነው፤

11. “አምጭ (ያዥ)” ማለት በስሙ ወይም ላዘዘለት ተብሎ የተሰጠውን፤ ስሙ ተጽፎ ወይም ሳይጻፍ በጀርባ ፊርማ የተላለፈለትን፤ ወይም በእጁ በማድረግ ብቻ መብት የሚያገኝበትን የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የያዘ ሰው ማለት ነው፡፡
12. “የቅን ልቦና ያዥ” ማለት በሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ፣ በደረሰኙ ወይም በደረሰኙ በተመለከቱት ዕቃዎች ላይ አስቀድሞ ስለነበረ የይገባኛል ጥያቄ የሚያውቀው ነገር ሳይኖር አንድን የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ዋጋ ሰጥቶ የተቀበለ አምጭ ማለት ነው፤
13. “የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ” ማለት በጀርባ ተፈርሞበት ወይም ሳይፈረምበት በመስጠት ከአንዱ ወደ ሌላው ሊተላለፍ የሚችል የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ማለት ነው፤
14. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደአገባቡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፤[51]
15. “ሰው” ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤
16. “የዋስትና ጥቅም” ማለት አደራ ሰጭው ለባለዕቃ ማከማቻው ወይም ለሌላ ሦስተኛ ወገን አንድ የታወቀ ግዴታ ለመወጣት ሲል ከገባው የዋስትና ግዴታ የሚመነጭና የዋስትናው ተጠቃሚዎች በአደራ ሰጭው ስም በዕቃ ማከማቻ ቤቱ በተቀመጡት ዕቃዎች ላይ የሚኖራቸው መብት ማለት ነው፡
17. “ሲስተም ፕሮቫይደር” ማለት በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኝ ሆኖ በሥራ አመራር፣ በኤሌክትሮኒክ መረጃ አቅርቦትና አያያዝ፣ እንዲሁም በኮምፒዩተር አሠራር በሚደገፉ የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች አማካኝነት የሚደረጉ ግንኙነቶች ስለሚካሄዱበት መንገድ ለባለዕቃ ማከማቻዎች አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ማለት ነው፤
18. “የዕቃ ማከማቻ ቤት” ማለት በባለዕቃ ማከማቻው ሕጋዊ ይዞታና ቁጥጥር ሥር ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ዕቃ የሚከማችበት ሕንጻ ወይም ተለይቶ የተከለለ ሥፍራ ማለት ነው፤
19. “ባለዕቃ ማከማቻ ቤት” ማለት የሙያ ሥራው በማድረግና ጥቅም ለማግኘት ሲል የሌሎች ሰዎችን ዕቃዎች እየተቀበለ በማስቀመጥ ንግድ ሥራ የተሠማራ ሰው ማለት ነው፤

[51] በ25/82011) አ.1097 አንቀፅ 9(6) መሰረት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

20.“የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ” ማለት ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሌላ ሰው ዕቃ መረከቡ የተረጋገጠበት በዚህ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀ የጽሑፍ ማስረጃ ማለት ሲሆን የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝንም ይጨምራል።

21.“የማገቻ መብት” ማለት ያልተከፈሉ ወይም ቀሪ የማከማቻ ቤት ሂሣቦችን ጨምሮ ዕቃውን ለማስቀመጥ፣ ለማዘጋጀትና ለመጠቅለል ለማጓጓዝ፣ መድን ለመግባት፣ ለጉልበትና ሙያ ሥራ እና ለሌሎች ዕቃውን በአግባቡ ለመያዝ ወይም ለመሸጥ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተደረጉ ወጪዎችን ክፍያ አስመልክቶ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ተመልክቶ በማከማቻ ቤት በተቀመጠ ዕቃ ወይም ከዚህ ዕቃ ሽያጭ በተገኘው ሂሣብ ላይ እራሱን የማከማቻ ሰነዱን በመያዣነት የተቀበሉ ባለገንዘቦችን ጨምሮ ከማንኛውም የአደራ ሰጪ ወይም ከእርሱ መብት የተላለፈለት ባለገንዘብ ያለው የተሻለ የቅድሚያ መብት ነው፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ አዋጅ ዓላማ፡

1. ማንኛውም ሰው ዕቃውን በተለይም ደረጃ የወጣለትን የግብርና ምርት በዕቃ ማከማቻ ቤቶች በማስቀመጥ የያዘውን ደረሰኝ በመያዣነት በመስጠት ገንዘብ ለመበደር እንዲችል ለማድረግ፡
2. በዕቃ አስቀማጮችና በአደራ ሰጪዎች መካከል በሕግ ፊት የፀና ውል ለመመሥረትና ሥርዓቱንም በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር ለማስቻል፣ እና
3. የተደራጀና የተሳለጠ የግብርና ምርቶች የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

1. በልዩ ሕጎች የተመለከተ ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ አዋጅ ከዕቃ ማከማቻ ውሎች በሚመነጩና ከእነርሱም ጋር ተያያዥነት ባላቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. አግባብነት ያላቸው የ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔርና የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ በማሟያነት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ስለማውጣት

5. **የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ለማውጣት ስለሚችሉ አካላት**

   1. በመንግሥት በኩል ተገቢው ማበረታቻ እየተደረገላቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የዕቃ ማከማቸት ንግድ ሥራ ለመሥራት የንግድ ፈቃድ ያወጡና ምዝገባ ያደረጉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ለማውጣት ይችላሉ፤
   2. በዚህ አዋጅ መሠረት የዕቃ ማከማቻ ንግድ ሥራ ለመሥራት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያወጣና ለዚህም ምዝገባ ያደረገ ማናቸውም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም አክሲዮን ማኅበር ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ለማውጣት ይችላል፡፡

6. **የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ፎርም**

   1. ዕቃዎችን ለማስቀመጥ የተቀበለ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት አደራ ሰጭው ሲጠይቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተገለጸው ፎርም መሠረት የተዘጋጀ አንድ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ የሆኑ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች አውጥቶ ይሰጠዋል፤
   2. አንድ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሚከተሉትን ዝርዝር ፍሬ ነገሮች መያዝ አለበት፣
      ሀ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የወጣው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት መሆኑን የሚያመለክት መግለጫ፣
      ለ) የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን ስም፣ አድራሻና የምዝገባ ቁጥር፣
      ሐ) የዕቃ ማከማቻ ቤቱን ወይም ዕቃዎቹ የተቀመጡበትን ሌላ መገኛ ቦታ የሚያመለክት መግለጫ፣
      መ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የወጣበትን ቀን፣
      ሠ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙን የቅደም ተከተል ተራ ቁጥር፣
      ረ) የዕቃ አስቀማጩን ወይም በስሙ ዕቃ የተቀመጠለትን ሰው ስምና አድራሻ ፣
      ሰ) የዕቃ ማስቀመጫ ክፍያውን ተመን፣
      ሸ) በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የተመለከቱትን ዕቃዎች ዓይነት ፤ የጥራት ፣ ደረጃና መጠን፣
      ቀ) በዕቃ ማከማቻ መጋዘን ዕቃው ገቢ በሚሆንበት ዕለት የዕቃው የዋጋ ግምት፣
      በ) ዕቃዎቹ በማከማቻ ቤቱ የሚቆዩበትን የጊዜ ገደብ፣

ተ) በቅድሚያ የተከፈለውን የአገልግሎት ሂሣብ እና ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዕቃዎቹ ላይ ሊኖረው የሚችለውን የማገቻ ወይም የዋስትና ጥቅም ወሰን የሚያሳይ መግለጫ፣

ቸ) ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ እንደተጠየቀ ዕቃዎቹን ለማስረከብ ግዴታ እንደገባ የሚያመለክት ማረጋገጫ እና

ኀ) የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን ፊርማ፤

3. ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃዎቹን በማስረከብና በጥንቃቄ ይዞ በማቆየት ረገድ ያለበትን ግዴታ አስመልክቶ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ በደረሰኙ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወገኖችን ግንኙነት በተሻሻለ ሁኔታ የሚገልጽ ተጨማሪ ፍሬ ነገር ማስገባት ይቻላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩትን ፍሬ ነገሮች በደረሰኙ ያልገለጸ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ይህን ባለማድረጉ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፡፡ ይሁንና በዚህ ጉድለት ብቻ ደረሰኙ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አይደለም ተብሎ ግምት አይወሰድበትም ።

5. አንድ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በዚህ አዋጅ እንደተደነገገው ከአንዱ ወደሌላው እንዲተላለፍ የሚደረግበትን አሠራር ሊያመለክት የሚችል መግለጫ የሚሰጥበት በቂ ክፍት ቦታ ሊኖረው ይገባል ፣

6. አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ በተጠየቀበት ጊዜ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመጠየቅ አንድን ደረሰኝ ጠቅላላ ዋጋቸው፣ የአገልግሎት ክፍያቸውና የመቆያ ጊዜያቸው ከፊተኛው ደረሰኝ ጋር እኩል በሆነ በርካታ አነስተኛ ደረሰኞች ለመተካት፣ ወይም አነስተኛ ደረሰኞችን አንድ ላይ በማጠቃለል በከፍተኛ ደረሰኝ ለመቀየር ይችላል፡፡

7. <u>የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሕጋዊ አቋም</u>

   1. በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ለአደራ ሰጭው የተሰጠ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በባለዕቃ ማከማቻ ቤቱና በአደራ ሰጭው መሀል በሕግ ፊት የሚፀና ውል ለመደረጉ ማረጋገጫ ነው፤
   2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ስለውሎች በጠቅላላውና በተለይም ስለአደራ ውሎች የተመለከቱት አግባብ ያላቸው

ድንጋጌዎች የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ተዋዋይ በሚሆኑ ወገኖች መሀል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ይህን አዋጅ በማሟላት ተፈፃሚ ይሆናሉ ፡፡

8. <u>ተደራራቢ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ስለማውጣት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠፋ፣ የተሰረቁ ወይም የተበላሹ ደረሰኞችን ለመተካት ካልሆነ በስተቀር አስቀድሞ የዕቃ ማከማቻ ደረስኝ ለወጣላቸው ዕቃዎች ሌላ ደረሰኝ ማውጣት አይቻልም።
2. የመጀመሪያው የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ ወይም ከእርሱ መብት የተላለፈላቸው ሰዎች በዕቃዎቹ ላይ የነበረውን መብት እንደያዙ ይቆያሉ፤
3. ተደራራቢ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን አውጥቶ የሰጠ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ይህን በማድረጉ ምክንያት በተከታታዮቹ የደረሰኙ አምጭዎች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፤
4. ተደራራቢ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች በተሰጡበት ተመሳሳይ ዕቃ ላይ የመጀመሪያውን አምጭ መለየት ካልተቻለ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ለሁሉም አምጭዎች በግል ኃላፊነት ይኖርበታል፤

9. <u>የተለወጡ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች</u>

1. በሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ ያለ ክፍት ቦታ የተሞላው ይህን ለማድረግ ሥልጣን በሌለው ሰው ቢሆንም እንኳ የደረሰኙ የቅን ልቦና ያዥ በደረሰኙ የተመለከቱትን ዕቃዎች በተመለከተ ሙሉ መብት ይኖረዋል፤
2. ሥልጣን በሌለው ሰው በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ የተደረገ ሌላ ማናቸውም ለውጥ ደረሰኙ በመጀመሪያው ግዴታ መሠረት በባለዕቃ ማከማቻ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የማድረግ ውጤት ብቻ ይኖረዋል።

10. <u>የጠፉ የተሰረቁና የተበላሹ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች</u>

1. አንድ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሲጠፋ፣ ሲሰረቅ፣ ወይም ተበላሽቶ ጉዳት ሲደርስበት አምጭው ይህንኑ እንዳወቀ በ24 ሰዓት ውስጥ ሁኔታውን በጽሑፍ ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ መግለጽ አለበት፤
2. የጠፋ የተሰረቀ ወይም የተበላሸ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ ነበርኩ የሚል ሰው በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የተገለጹት ዕቃዎች እንዲሰጡት ወይም ምትክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት ያለመዘግየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማመልከት አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱም በትዕዛዙ ምክንያት ጉዳት ሊደርስበት

ለሚችል ሰው ካሣ የሚሆን በቂ ዋስትና እንዲያስይዝ በማድረግ በአቤቱታው መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥለት ይችላል፡፡ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በተሰጠ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከዋስትናው መብት አገኛለሁ የሚል ወገን ካልመጣ ዋስትናው በራሱ ቀሪ ይሆናል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ማስታወቂያ የደረሰው ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በጠፋው የዕቃ ማከማቻ ደረስኝ መነሻነት ለሚጠይቅ ሰው ዕቃውን ያስረከበ እንደሆነ በዚህ አድራጎቱ ጉዳት ለሚደርስበት ሰው ኋላፊ ይሆናል፡፡

11.<u>**በፍርድ አፈጻጸም ስለሚሰጥ ማስከበር ትዕዛዝ**</u>

የዕቃ ማከማቻ ደረስኝ በባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ስም ሳይሆን በሌላ ሰው ስም ወጥቶባቸው በዕቃ ማከማቻ ቤት እንዲቀመጡ የተደረጉ ዕቃዎች በባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕዳ ወይም በእርሱ ላይ በሚሰጥ የመክሰር ውሳኔ መነሻነት በፍርድ አፈጻጸም እንዲከበሩ አይደረግም።

12.<u>**ተጻራሪ የሆኑ የይገባኛል ጥያቄዎች**</u>

በዕቃ ማከማቻ ደረስኝ መብት አለን ወይም በደረሰኙ የተመለከቱት ዕቃዎች ይገቡናል በማለት የተለያዩ ሰዎች ጥያቄ ሲያቀርቡና ከእነዚህ ሰዎች ለየትኛው ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ለማወቅ ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ አጠራጣሪ በሚሆንበት ጊዜ በቂ ጊዜ ወስዶ ትክክለኛውን ባለመብት እስኪያረጋግጥ ወይም ይኸው እንዲረጋገጥ የኃላፊነት ይውረድልኝ አቤቱታ ለፍርድ ቤት እስከሚያቀርብበት ጊዜ ድረስ ዕቃውን የማስረከብ ግዴታውን እንዲወጣ አይገደድም።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የባለዕቃ ማከማቻ ቤት መብትና ግዴታዎች</u>

13.<u>**የማስረከብ ግዴታ**</u>

1. አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አውጥቶላቸው ተቀብሎ ያስቀመጣቸውን ዕቃዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተደነገገው መሠረት የማስረከብ ግዴታ አለበት፤
2. የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የሚተላለፍ ሲሆን አደራ ሰጭው ዕቃውን የሚረከበው፡-
   ሀ) ለባለዕቃ ማከማቻው መወጣት ያለበትን ዕቃውን ከዕግት ነፃ የማድረግ ግዴታ ሲወጣ፣

ለ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙን ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በመስጠት፣

ሐ) ዕቃውን መረከቡን በጽሑፍ ሲያረጋግጥ፤ ነው።

3. የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የማይተላለፍ ሲሆን አደራ ሰጭው ዕቃውን የሚረከበው፤

   ሀ) ለባለዕቃ ማከማቻው ቤት መወጣት ያለበትን ዕቃውን ከዕግት ነፃ የማድረግ ግዴታውን ሲወጣና

   ለ) ዕቃውን መረከቡን በጽሑፍ ሲያረጋግጥ ነው።

4. አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃውን ለማስረከብ ያልፈቀደ ወይም ያልቻለ እንደሆነ ያልፈቀደበት ወይም ያልቻለበት በቂ ሕጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ይህም ምክንያት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ መሆን አለበት፡፡

   ሀ) ዕቃውን ትክክለኛ መብት ላለው ጠያቂ ያስረከበ መሆኑን፣

   ለ) ዕቃውን የማገት ሕጋዊ መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ሲል ወይም ዕቃውን የማስቀመጥ ግዴታውን በሕግ መሠረት ካቋረጠ በኋላ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃዎቹን የሸጠ ወይም በማናቸውም መንገድ ያስወገደ ሲሆን፣ ወይም

   ሐ) ፍርድ ቤት ወይም በአግባቡ የተቋቋመ የግልግል ሸንጎ ሕጋዊ ነው ብሎ በሚወስነው ሌላ ማናቸውም ምክንያት፤

5. በቅንልቦና እና በመስኩ የተለመደውን አሠራር በትክክል በመከተል በዚህ አዋጅ መሠረት ዕቃ የተቀበለ፣ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሰጠና ዕቃዎችን መልሶ ያስረከበ ወይም በሌላ መንገድ ያስወገደ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ዕቃውን እንዲከማች የሰጠው ሰው ዕቃውን ለመስጠት፣ ዕቃውን የተረከበውም ሰው ለመረከብ የሚያስችል ሥልጣን ባይኖረውም እንኳ ይህንን በማድረጉ በኃላፊነት አይጠየቅም።

14. <u>ጥንቃቄና ትጋት</u>

1. አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዕቃ ማከማቻ ቤቱ ውስጥ ለማከማቸት የሚረከባቸውን ዕቃዎች በአግባቡ የመያዝና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፤

2. የሥራው ባህርይ የሚጠይቀውንና ማንም ሰው በእርሱ ቦታ ቢሆን ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ምክንያት የተከማቹት ዕቃዎች ቢጠፉ ወይም ቢበላሹ ለሚደርሰው ጉዳት ባለማከማቻ ቤቱ ኃላፊ ነው፤

3. የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን የውል ግዴታ መጠን በማከማቻ ቤቱ ካስቀመጣቸው ዕቃዎች ትክክለኛ ዋጋ አሳንሶ የሚወስን የውል ቃል በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ ላይ መጻፍ ውጤት አይኖረውም፤
4. ተቀብሎ ባስቀመጣቸው ዕቃዎች ላይ የመለወጥ ነገር በመታየቱ ሳቢያ ተጨማሪ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ይህንኑ በጽሑፍ ለአደራ ሰጭው ማስታወቅ አለበት፡፡

15.<u>ባለመረከብና አሳስቶ በመግለጽ ስለሚደርስ ኃላፊነት</u>

አንድ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥልጣን በተሰጠው ወይም ከነገሩ አካባቢ ሁኔታ ሲታይ ሥልጣን የተሰጠው በሚመስል የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ወኪል ወይም ሠራተኛ መፈረሙ ከተረጋገጠ ዕቃዎቹ በሙሉ ወይም በከፊል በማከማቻ ቤቱ የተቀመጡ ወይም ዓይነታቸው ወይም መጠናቸው በደረሰኙ ከተሰጠው መግለጫ የተለየ ቢሆንም እንኳ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የደረሰኙ የቅን ልቦና ባለይዞታ ለሆነው ሰው ሙሉ ኃላፊነት አለበት፡፡

16.<u>ስለማደባለቅ</u>

1. አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ከአደራ ሰጭው ግልጽ ፈቃድ ሳያገኝ የተቀበለውን ማናቸውንም ዕቃ በማከማቻ ቤቱ ካሰቀመጣቸውና በዓይነትና በጥራት ተመሳሳይ ከሆኑ ሌሎች ዕቃዎች ጋር መደባለቅ የለበትም፤
2. ዕቃዎቹን በቀላሉ ለመለየትና ጥያቄ በቀረበ ጊዜም ያለችግር ለማስረከብ ይረዳ ዘንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በእያንዳንዱ ደረሰኝ የተመለከቱትን ዕቃዎች ለየብቻ ማስቀመጥ አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተገለጸው ቢኖርም አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ተተካኪ ዕቃዎች በዓይነት፣ በጥራትና በደረጃ ተመሳሳይ ከሆኑ ከሌሎች ተተካኪ ዕቃዎች ጋር ማደባለቅ ይችላል፡፡ እንዲህም በሆነ ጊዜ እንዲደባለቁ የተደረጉትን ዕቃዎች የሚያሳዩ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች አምጭዎች የዕቃዎቹ የጋራ ባለንብረት እንደሆኑ ይቆጠራሉ፤ በያዙት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የተመለከተውን ዕቃም የመጠየቅ መብት አላቸው።

17.<u>የዕቃ ማከማቻ ስምምነት የቆይታ ጊዜ</u>

1. በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ ላይ የተመለከተው ጊዜ ሲያበቃ፣ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃው በስሙ ለተቀመጠለት ሰው፣ ለሕጋዊ ወኪሉ ወይም በዕቃው ላይ ሕጋዊ

መብት እንዳለው ለማወቅ ለማናቸውም ሰው ተገቢውን ማስታወቂያ በመስጠት ያለበትን አገልግሎት ሂሣብ ከፍሎ ዕቃውን እንዲረከብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

2. ዕቃው የሚቀመጥበት ጊዜ ያልተገለጸ ሲሆን ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃዎቹን ከተቀበለ ከአንድ ዓመት በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መብቱ ሊሰራበት ይችላል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ተቃራኒ የሆነ ደንብ ከሌለ ወይም በውሉ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በቀር ዕቃው ሊበላሽ ወይም የዕቃው ዋጋ እርሱ በዕቃው ላይ ካለው የማገቻ መብት በታች ሊወርድ እንደሚችል ባለዕቃው ማከማቻ ቤቱ ማስረዳት ከቻለ ተገቢውን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ዕቃውን የመሸጥ መብት አለው፡፡ እንዲህም በሆነ ጊዜ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ስለማካካሻ ሽያጭ የተደነገጉት ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ፣
4. ዕቃውን ሲረከብ ባላወቀው እና ከዕቃው ዓይነት ወይም ባህርይ በሚነሱ ችግሮች የተነሳ በሰው ወይም በንብረት ላይ አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል የተረዳ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ተገቢውን ማስጠንቀቂያ በዕቃ ላይ መብት አለን ለሚሉ ሁሉ በመስጠት ዕቃውን በግልጽ ጨረታ ወይም በግል ሊሸጠው ይችላል፡፡ ተገቢውን ጥረት አድርጎ ዕቃው አልሸጥ ካለው ዕቃውን በሌላ አመችና ሕጋዊ መንገድ እንዲወገድ ማድረግ ይችላል፡፡ ይህን በማድረጉም ኃላፊነት አይኖርበትም፤
5. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃ የሸጠ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የራሱን የማከማቻና ሌሎች መሰል ክፍያዎች ከሽያጩ ዋጋ ላይ ቀንሶ የተረፈውን ለባለ መብቱ ተቀማጭ አድርጎ ማቆየት አለበት፡፡

18.<u>የባለዕቃ ማከማቻ ቤት የማገቻ መብት</u>

1. ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የማገቻ መብቱን በዚህ አዋጅ መሠረት ሊጠቀም ይችላል፤
2. ዕቃውን በገዛ ፈቃዱ ለአደራ ሰጭው ያስረከበ ወይም አጥጋቢ ምክንያት ሳይኖረው ዕቃውን ያላስረከበ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት ሊያገኝ የሚችለውን የማገት መብት ያጣል።

19.<u>የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን የማገቻ መብት ተግባራዊ ስለማድረግ</u>

1. ሊከፈለው የሚገባው ማናቸውም ሕጋዊ ክፍያ እስኪደረግለት ድረስ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ባስቀመጠው ዕቃ ላይ የይገባኛል ጥያቄ የማንሳትና ዕቃውንም አግቶ የማቆየት መብት አለው፤
2. ይህንን መብቱን ተግባራዊ ለማድረግም በማከማቻ ቤቱ ከተቀመጡት ዕቃዎች መሀል ለሚጠየቀው ክፍያ የሚመጥኑትን ያህል በአካባቢው የንግድ አሠራር ተቀባይነት ባለው መንገድ በጨረታ ወይም በግል ሊሸጣቸው ይችላል፤
3. ይሁንና ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተመለከቱት መብቶች ለመሥራት ከዚህ በታች ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡-
   ሀ) ለመብቱ መሠረት የሆኑት የዕቃ ማከማቻ ቤት የአገልግሎት ክፍያና ሌሎችም ሂሣቦች የመክፈያ ጊዜ የደረሰ እንዲሆን ያስፈልጋል፤
   ለ) በዕቃው ላይ መብት አለን ለሚሉ ሰዎች ሁሉ ተገቢው ማስታወቂያ እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል፤
   ሐ) የሚላከው ማስታወቂያ የተጠየቀውን ክፍያ መጠን፣ ታግተው ያሉትን ዕቃዎች የሚያሳይ መግለጫ፣ ክፍያ የሚደረግበትን የተቆረጠ የጊዜ ገደብ እንዲሁም በተባለው ጊዜ ክፍያ ካልተፈጸመ ዕቃዎቹ በጨረታ ወይም በግል የሚሸጡ መሆናቸውን የሚያመለክት ማስገንዘቢያ የሚያካትት መሆን ይኖርበታል፤
   መ) መብቱ ተፈጻሚ የሚሆነው በዕቃ አከማቹ ዘንድ ከተቀመጡና በይዞታውም ሥር ካሉ ዕቃዎች ለሚጠየቁ ክፍያዎች ብቻ ነው፤
   ሠ) የማገት መብቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ለይገባኛል ጥያቄው ምክንያት በሆነው በአንድ የተለየ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በተመለከቱት ዕቃዎች ላይ ወይም ከእነዚህ ዕቃዎች ሽያጭ በተገኘ ገንዘብ ላይ ብቻ ነው። መብቱ በባለዕቃ ማከማቻው ይዞታ ሥር በሚገኙ በሌሎች የአደራ ሰጭው ዕቃዎች ተፈጻሚ አይሆንም፤
4. በሚሸጠው ዕቃ ላይ መብት አለኝ የሚል ሰው የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን የአገልግሎት ሂሣብና ሌሎች ተገቢ ወጭዎችን የሚሸፍን ክፍያ በማድረግ ሽያጩን ማስቆም ይችላል፡፡ እንዲህም ሲሆን ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ ላይ የተመለከቱትን የውል ቃላትና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አድርጎ ዕቃውን ይዞ ይቆያል፤

5. የማገቻ መብቱን ተግባራዊ የሚያደርግ ማንኛውም ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ ይሆናል፤
6. አግባብነት ያላቸው የግዴታዎች ሕግ ድንጋጌዎች የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ለማሟላት ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት

## የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ስለማስተላለፍ

### 20.ስለማስተላለፍ

1. አንድ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሚተላለፍ ወይም የማይተላለፍ ሊሆን ይችላል፤
2. ማናቸውም የማይተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በላዩ ላይ "የማይተላለፍ" የሚል ቃል የያዘ መሆን አለበት። ይህ አነጋገር ካልተመለከተበት ደረሰኙ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ይሆናል፤
3. ከማይተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሚመነጩ መብትና ግዴታዎች ለሦስተኛ ወገን የሚተላለፉት ሽያጭን ወይም መደበኛ የመብት ማስተላለፍን በሚመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ብቻ ነው፤
4. የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በጀርባ ፊርማ እና በቀጥታ በመስጠት ለሦስተኛ ወገኖች ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ የተጻፈና የደረሰኙን ትልልፍ የሚገድብ ቃል ውጤት አይኖረውም፤
5. ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደረሰኙ ላይ ፊርማን ብቻ በማኖር፣ ላምጪው የሚል ቃል ጽፎ በመፈረም፤ ወይም የተቀባዩን ስም ጽፎ በመፈረም የተቀመጠ የጀርባ ፊርማ ውጤት ይኖረዋል። ደረሰኙ ስም ተጽፎበት በጀርባ ፊርማ በሚተላለፍበት ጊዜ እንደገና ፊርማን ብቻ በማኖር፣ ላምጪው የሚል ቃል ጽፎ በመፈረም ወይም የተቀባዩን ስም ጽፎ በመፈረም በጀርባ ፊርማ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ቀጣይ ትልልፎችም በተመሳሳይ መንገድ ሊደረጉ ይችላሉ፤
6. ትክክለኛውን የማስተላለፍ አሠራር ተከትሎ በተሠራ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ መብት የተላለፈለት ሰው በደረሰኙ ላይ በተመለከተው ዕቃ ላይ ሙሉ መብት ይኖረዋል። ደረሰኙን በቅን ልቦና የያዘ ሰውም በደረሰኙ ላይ ያለው መብት ቀደም ሲል ከነበሩ ከማናቸውም መብቶችና መቃወሚያዎች ነፃ ይሆናል፡፡

### 21.ሌሎች ከዕቃ ማከማቻ ደረስኝ ማስተላለፍ የሚመነጩ መብቶች

1. የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ጀርባ ፊርማ ለሌላ ያስተላለፈ ሰው ከእርሱ በፊት ደረሰኙን በጀርባ ፊርማ ያስተላለፉ ሰዎች ወይም ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ለፈጸመው ጥፋት (ጉድለት) ኃላፊነት የለበትም፤
2. የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የተላላፈለት ሰው በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት በደረሰኝ ሊገለጽ ይገባው የነበረ ፍሬ ነገር አለመገለጹን ካወቀ ይኸው እንዲገለጽለት በጀርባው ፊርማ ደረሰኙን ያስተላለፈለትን ሰው በማናቸውም ጊዜ ሲጠይቀው ይችላል፡፡

## 22.ዋቢ ስለማለፍ

የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ዋጋ ተቀብሎ ያስተላለፈ ሰው፣

1. የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ እውነተኛ ስለመሆኑ፣
2. የደረሰኙን ሕጋዊነትና ያለውንም ዋጋ የሚያሰናከል ምንም ዓይነት ሁኔታ ለመኖሩ የማያውቅ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም
3. ያደረገው ማስተላለፍ ደረሰኙን እና በላዩ የተመለከቱትን ዕቃዎች በተመለከተ ትክክለኛና ተፈፃሚ ስለመሆኑ ዋቢ ነው፡፡

## 23.ቀሪ ስለሚሆኑ መብቶች

1. ከባለዕቃ ማከማቻ ቤትነት ሥራው በተደራቢ ተተካኪ ዕቃዎችን ለመሸጥ ፈቃድ ካለው ሰው በተለመደው የንግድ ሥራ አካሄድና በቅን ልቦና እነዚህን ዕቃዎችን ገዝቶ የተረከበ ሰው በዕቃ ላይ ከዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የመነጨ መብት ካለውና ደረሰኙ በአግባቡ ከተላለፈለት ሰው ጥያቄ ነፃ ነው፤
2. እንደዚህ ዓይነቱን የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ዋጋ ሰጥቶ የተላለፈለት ሰው የሚኖረው መብት ደረሰኙን ያስተላለፈለት ሰው በሚኖረው መብት ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል፡፡

## 24.የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን በመያዣ ስለመስጠት

1. አንድ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ የሆነ ሰው ደረሰኙን መያዣ በመስጠት ከባንክ ወይም ከተፈቀደለት መሰል አበዳሪ ተቋም ገንዘብ ለመበደር ይችላል፤
2. ተበዳሪው ብድሩን የመክፈል ግዴታውን ካልተወጣ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የያዘ ባንክ ወይም አበዳሪ ተቋም መያዣውን ለሦስተኛ ወገኖች ማስተላለፍ አይችልም፣

3. በመክፈያው ጊዜ ተበዳሪው ብድሩን ያልከፈለ ከሆነ ባንኩ ወይም አበዳሪ ተቋሙ ለተበዳሪው ተገቢውን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በማስጠንቀቂያው የተመለከተው የክፍያ ጊዜ ካለፈ ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ በደረሰኙ የተመለከተው ዕቃ እንዲሸጥ ለማድረግ ይችላል፤
4. የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የማገቻ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃው እንዲሸጥ ያደረገ ባንክ ወይም አበዳሪ ተቋም በደረሰኙ መያዣነት ከተበዳሪው የሚፈለገውን ያልተከፈለ ዕዳና በሽያጩ ምክንያት ያወጣውን ወጭ ተቀናሽ አድርጎ ተራፊውን ለተበዳሪው ይሰጣል፤
5. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን አስፈላጊ ሁኔታዎች ያልፈጸመ ባንክ ወይም አበዳሪ ተቋም ይህን በማድረጉ ምክንያት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ከደረሰ ኃላፊ ይሆናል፤
6. የማይተላለፉ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች በመያዣ የሚሰጡበት አሠራርና ውጤት ስለመያዣ ውሎች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

25.<u>ዕቃው ሳይኖር ደረሰኝን ስለማስተላለፍ</u>

የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ወጥቶለት በዕቃ ማከማቻ ቤት የሚገኝን አንድ ዕቃ ከሸጠ ወይም መያዣ ከሰጠ በኋላ፣ ወይም ራሱን የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙን ከሸጠ ወይም መያዣ ከሰጠ በኋላ፣ ያንኑ ደረሰኝ በይዞታው ሥር አድርጎ ያቆየ ሰው መልሶ አስቀድሞ ስለተደረገው ሽያጭ ወይም መያዣ ምንም ዕውቀት ለሌለው ሦስተኛ ወገን ደረሰኙን ዋጋ ተቀብሎ ያስተላለፈ እንደሆነ ደረሰኙ በቅን ልቦና የተላለፈለት ሰው መብት የፀና ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>በዕቃ ማከማቻ ቤቶች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር</u>

26.<u>ለምዝገባ ስለማመልከት</u>[52]

1. በዚህ አዋጅና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/89 እና በፌዴራል መንግሥት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 13/89 ላይ የተቀመጡ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ማናቸውም የአክስዮን ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ፣ ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ለሚኒስቴሩ ወይም ሚኒስቴሩ ለዚሁ ተግባር ለሚወክለው ሌላ ተቆጣጣሪ አካል

[52] በአንቀፅ 26፣ 27፣ 35፣ እና 37 ላይ የተጠቀሱት አዋጅ ቁጥር 67/1989 እና ደንብ ቁጥር 13/1989 ተሽረዋል፡፡ (22/101(2008) አ.980 እና ደንብ ቁጥር 392/2009ን ተመልከት)፡፡

የዕቃ ማከማቻ ቤት ሥራ ለመሥራት በንግድ መዝገብ እንዲመዘገብ ማመልከት ይችላል።

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን አቤቱታ አቅራቢው ከሌሎች ጉዳዮች በተለይ የሚከተሉትን መለኪያዎች ማሟላት አለበት፤
   ሀ) እጅግ ቢያንስ ብር አንድ ሚሊዮን የሚደርስ የተጣራ ወረት ያለውና በአስተማማኝ የገንዘብ አቅም ላይ የሚገኝ መሆኑን ማሳየት፣
   ለ) የሚረከባቸውን ዕቃዎች በአግባቡ ለመመዘን፣ ለመቀበል፣ ደረጃ ለመስጠት፣ ለማስቀመጥ፣ ንጽሕናቸውን ለመጠበቅና ሲፈለጉም መልሶ ለማስረከብ የሚያስችል አስፈላጊ በሆኑ ቁሳቁሶች የተደገፈ ቋሚ የዕቃ ማከማቻ ቤት እንዳለው ወይም እንደተከራየ የኪራዩም ዘመን ቢያንስ ለአሥራ ሁለት ወራት ፀንቶ የሚቆይና ከዚህም በኋላ ለሌላ አሥራ ሁለት ወር እንደሚታደስ ማረጋገጫ ማቅረብ እና
   ሐ) በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት የሚረከባቸውን ዕቃዎች በአግባቡ ለመያዝ፣ ደረጃ ለማውጣትና ለመጠበቅ የሚችሉና ተገቢው የሙያ ሥልጠናና የሥራ ልምድ ያላቸው ሠራተኞች እንደቀጠረ ማሳየት።
3. የኅብረት ሥራ ማኅበራት የዕቃ ማከማቻ ቤት ንግድ ሥራ ለመሥራትና ለመመዝገብ ሊያሟሉ የሚገባቸውን መስፈርቶች ሚኒስቴሩ በመመሪያ ይወስናል፤

27.<u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

ሚኒስቴሩ ወይም ለዚሁ ተግባር በሚኒስቴሩ የሚወከል አካል፣

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 ለተገለጹት በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጣቸው አካላት የዕቃ ማከማቻ ቤቶችን ሥራ ለማካሄድ የሚያስችል የንግድ ሥራ ፈቃድ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/89 እና በፌዴራል መንግሥት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 13/89 እና በዚህ አዋጅ መሠረት ይሰጣል፣
2. ከሥራው ስፋት ወይም ፈቃድ ከተሰጠበት ሥራ ልዩ ባህርይ በመነሳት ለዕቃ ማከማቻ ቤቶች ደረጃና መደብ ይሰጣል፣
3. አስፈላጊ የሙያ ብቃት ማስረጃ ለሚያቀርቡ ግለሰቦች በዕቃ ማከማቻ ቤቶች የሚቀመጡ የግብርና ምርት ውጤቶችን ለመቆጣጠር፣ ለመለየት፣ ደረጃ

ለመስጠት፣ ለመመዘን ወይም ናሙና ለማውጣት የሚያስችል የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የግብርና ምርት ውጤቶችን ደረጃ የመስጠት ሥራ የሚያካሂድ ሰው የግብርና ምርት ውጤቶችን ደረጃ ለማውጣት በቅድሚያ የኢትዮጵያ ደረጃዎችና ጥራት ባለሥልጣንን ውክልና ማግኘት አለበት፡፡

28.<u>ምዝገባን ይፋ ስለማድረግ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የማከማቻ ቤቱን ዋና መሥሪያ ቤት፣ በድርጅቱ ሥር ያሉ የዕቃ ማከማቻ ቤቶች የሚገኙባቸውን ሥፍራዎች፣ እንዲሁም በተሰጠው ፈቃድ መሠረት የሚያስቀምጣቸውን ዕቃዎች ዓይነት የፋይናንስ አቋሙንና ሌሎችም አስፈላጊ መረጃዎችን በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚሰራጭ ጋዜጣ ላይ እንዲታተም ያደርጋል፡፡ መግለጫውም ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በተመዘገበ በ30 ቀን ውስጥ በጋዜጣ መውጣት አለበት፡፡

2. ማናቸውም የተመዘገበ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ሥራውን በሚያካሂድባቸው ቅጥር ግቢዎች ሁሉ ግልጽ በሆነ ሥፍራ ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገቡን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ መግለጫ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

29.<u>ሰነዶችንና መዛግብትን ስለመያዝ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ያስቀመጣቸውንና ወጭ የተደረጉትን ዕቃዎች ዝርዝር የሚያመለክቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ ሰነዶችንና መዝገቦችን በእሳት ሊቃጠል በማይችል የተቆለፈ ሰንዱቅ ውስጥ መያዝና ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

2. በተለይም የሚከተሉትን ሰነዶችና መረጃዎች በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፤

   ሀ) ወጭ ያደረጋቸውን የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችና ቅጂዎቻቸውን፣ እንደዚሁም ደረሰኞቹ ወጭ የተደረጉላችውን ሰዎች ስምና አድራሻ የሚያሳይ መዝገብ፤

   ለ) የተመለሱለትንና እንዲሰረዙ ያደረጋቸውን የዕቃ ማከማቻ የሚመለከት መዝገብ፤

   ሐ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን በመመለስ በማከማቻ ቤቱ የተቀመጡትን ዕቃዎች የተረከቡ ሰዎችን ስምና አድራሻ የሚያመለክት መዝገብ፤

መ) መያዣ መስጠትን ጨምሮ ወጭ በተደረጉ ዕቃ ማከማቻ ሰነዶች ላይ ስለተደረጉ የትልልፍ ስምምነቶች የደረሱትን ማስታወቂያዎችና የትልልፉ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን ስምና አድራሻ የሚያሳይ መዝገብ እና

ሠ) በዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሚገኙትን በየቀኑ ወደ ዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሚገቡትንና ከዚያም የሚወጡትን ዕቃዎች የሚያሳይ ዕለታዊ መግለጫ፣

3. አደራ ሰጭው ከእርሱ መብት የተላለፈለት ሰው፣ መያዣ ተቀባዩ ወይም ሌላ ማንኛውም ሕጋዊ መብት ያለው ሰው ዕቃውን ሲረከብ ተመላሽ የሚያደርጋቸው የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች ወዲያውኑ መሠረዝ አለባቸው።

4. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚመዘገቡ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቶች ሁሉ አግባብ ባላቸው ሕግጋት በተደነገገው መሠረት ተገቢ የሂሣብ መዝገቦችን የመያዝና በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይም የሂሣብ መዝገቦቻቸውን የማስመርመር ግዴታ አለባቸው።

30.<u>የአገልግሎት ታሪፍን ይፋ ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም ባለዕቃ ማከማቻ ቤት እያንዳንዱ የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት በጀመረ በሰላሣ ቀናት ውስጥ በዕቃ ማከማቻ ቤቱ ለሚቀበላቸው ዕቃዎች የሚያስከፍለውን ታሪፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ማድረግ አለበት። በዚህ መልክ በጋዜጣ እንዲታተም የተደረገው ታሪፍ በሁሉም የዕቃ ማከማቻ ቤቶች ግልጽ በሆነ ሥፍራ በቋሚነት መለጠፍ ያለበት ሲሆን በታሪፉ ከሚገለጹት ፍሬነገሮች መሐል ዕቃዎችን ለመቀበል፣ ለማስቀመጥ፣ ወጭ ለማድረግና ለዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ዝግጅት የሚከፈል ሂሣቦች ሊኖሩበት ይገባል፤

2. ማንኛውም ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በጋዜጣ ላይ እንዲታተም ካደረገው ታሪፍ የበለጠ ታሪፍ ለማስከፈል አይችልም፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ሁኔታዎች በሚያስገድዱበት ጊዜ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ተጨማሪ የክፍያ ታሪፎች እንዲታተሙ ማድረግ ይችላል። ቀደም ሲል ወጭ ተደርገው ያልተመለሱ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች ወጭ ሲደረጉ በነበረው ታሪፍ ብቻ የአገልግሎት ክፍያ ይጠየቅባቸዋል።

31.<u>ዋስትናና መድን</u>

1. ማንኛውም ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም ፈቃዱ እንዲታደስለት የሚፈልግ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ለደንበኞቹ፡ የሚገባቸውን ግዴታዎች በብቃት ለመወጣት የሚያስችለውን ዋስትና ወይም ሌላ ማረጋገጫ ለሚኒስቴሩ ወይም ሚኒስቴሩ ለዚሁ ተግባር ሲባል ለሚወክለው ተቆጣጠሪ አካል አቅርቦ ማስመዝገብ አለበት፡፡ የዋስትናው ወይም የማረጋገጫው ዓይነትና የግዴታው መጠን ሚኒስቴሩ ወይም እርሱ የሚወክለው አካል በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
2. ማንኛውም ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያወጣቸው የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች አስፈላጊውን የመድን ሽፋን መግዛት አለበት፡፡

## 32.አድልኦ ስላለማድረግ

1. የሚቀርቡለት ዕቃዎች በዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሚቀበላቸው ዕቃዎች ዓይነት እስከሆኑና ሲቀርቡም በአግባቡ የተያዙ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ማንኛውም በቂ ሥፍራ ያለው ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ዕቃዎቹን ተቀብሎ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፤
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በሆኑ ወይም አገልግሎቱን በሚጠይቁ ሰዎች መሀከል በአገልግሎቱ አሰጣጥም ሆነ በአገልግሎት ክፍያ ረገድ ልዩነት ማድረግ የለበትም፡፡

## 33.ደረጃ ስለማውጣት

1. አግባብ ባላቸው ሕጎች ስለብሔራዊ ደረጃ አሰጣጥና ቁጥጥር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ውስጥ በማስገባትና ከሚመለከታቸው የመንግሥት የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ጋር በመነጋገር ሚኒስቴሩ በተመዘገቡ የዕቃ ማከማቻ ቤቶች ለሚቀመጡ የግብርና ምርት ውጤቶች ደረጃ ለመስጠት ወይም እንዲሰጥ ለማድረግ ይችላል፤
2. በተመሳሳይ መንገድም በዕቃ ማከማቻ ቤቶች የሚቀመጡ የግብርና ምርት ለሚቆጣጠሩ፣ ለሚመድቡ፣ ደረጃ ለሚሰጡ፣ ለሚመዝኑና ናሙና ለሚያወጡ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት መመዘኛ ለማውጣትና የምስክር ወረቀት ለመስጠት ወይም እንዲሰጥ ለማድረግ ይችላል።

## 34.በዕቃ ማከማቻ ቤቶች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

1. ሚኒስትሩ ወይም ሚኒስቴሩ የሚወክለው አካል በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠውን ማናቸውንም የዕቃ ማከማቻ ቤት ለመቆጣጠር ወይም ቁጥጥር

እንዲረግበት ለማድረግ ሥልጣን አለው፡፡ በተለይም ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሚቀበላቸውን የግብርና ምርት ውጤቶች የሚረከብበትን፣ የሚያከማችበትን፣ የሚይዝበትን፣ በየደረጃቸው ወይም በሌላ አኳኋን እየለየ የሚመድብበትን፣ የሚመዝንበትንና ደረጃ የሚሰጥበትን አሠራር ይመረምራል፡፡

2. ሚኒስቴሩ የማንኛውንም ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የሂሣብ መዝገቦችን፣ ሌሎች መዝገቦችንና ሰነዶችን ለመመርመር ወይም ምርመራ እንዲደረግባቸው ለማዘዝ ይችላል።
3. ሚኒስቴሩ ወይም የእርሱ ተወካይ የግብርና ምርት ውጤቶች ለመቆጣጠር፣ ለመመደብ፣ ደረጃ ለመስጠት፣ ለመመዘን ወይም ናሙና ለማውጣት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ሥራቸውን የሚያካሂዱበትን መንገድ ለመመርመር ወይም እንዲመረመር ለማድረግ ይችላል፡፡

35.<u>**የፈቃድ የቁጥጥርና የአገልግሎት ክፍያዎች**</u>

1. ሚኒስቴሩ ወይም የእርሱ ተወካይ ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቶች የግብርና ምርት ውጤቶችን ለመቆጣጠር፣ ለመመርመር፣ ደረጃ ለመስጠት፣ ለመመዘን ፣ ወይም ናሙና ለማውጣት ፈቃድ ሲሰጥ፣ የፈቃዱ ደረጃ ከፍ ሲደረግ፣ ወይም ፈቃዱ ሲታደስ በፌዴራል መንግሥት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 13/89 መሠረት የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈል ያደርጋል፣
2. እንደዚሁም ሚኒስቴሩ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ድርጅቱ እንዲመረመርለት ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ ሊከፈል የሚገባውን የአገልግሎት ሂሣብ ለመተመንና ለመሰብሰብ ይችላል፡፡

36.<u>**በተተካኪ ዕቃዎች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥርና ስለሚሰጣቸው ደረጃ**</u>

ዓይነታቸው አንድ ሆኖ እርስ በርስ ሊተካኩ የሚችሉ ዕቃዎችን ተቀብሎ የሚያስቀምጥ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የሚረከባቸውን ዕቃዎች ከሌሎች ተተካኪ ዕቃዎች ጋር ከመደባለቁ በፊት ዕቃዎቹ ፈቃድ ባለው ደረጃ ሰጪ ታይተው ትክክለኛ መሆናቸውን እንዲረጋገጥ ማድረግ አለበት፡፡

37.<u>**ፈቃድ ስለማደስ**</u>

በዚህ አዋጅ፣ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/89 እና በፌዴራል መንግሥት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 13/89 መሰረት ሚኒስቴሩ ወይም ተወካዩ ለባለእቃ ማከማቻ ቤቶች፣ የግብርና ምርት

ውጤቶችን ለሚቆጣጠሩ፣ ለሚመድቡ፣ ደረጃ ለሚሰጡ ለሚመዝኑና ናሙና ለሚያወጡ ባለሙያዎች የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ እንዲታደስ ያደርጋል።

38.<u>ፈቃድ ስለማገድና ስለመሠረዝ</u>

1. ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ ሚኒስቴሩ ወይም ለዚህ ተግባር በሚኒስቴሩ የተወከለ ተቆጣጣሪ አካል የአንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሠረዝ ማድረግ ይችላል።
   ሀ) ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዚህ አዋጅ የተመለከተውን የካፒታል መጠን መጠበቅ አለመቻሉ ሲረጋጋጥ፣
   ለ) ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ባሉት የዕቃ ማከማቻ ቤቶች ወይም ከእነዚህ ውስጥ በከፊሎቹ ላይ ያለውን ቁጥጥር በሙሉ ወይም በከፊል መልቀቁ ሲረጋገጥ፣
   ሐ) የዕቃ ማከማቻ ቤቱ ድርጅት እየፈረሰና ንብረቱም እየተጣራ መሆኑ ወይም ወደ መፍረስና ንብረት ማጣራት ሊያደርሱ የሚችሉ አሳማኝ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣ ወይም
   መ) ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ሥራውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ችሎታና አቅም የሌለው መሆኑ በበቂ ሁኔታ ሲረጋገጥ፣ ወይም
   ሠ) ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዚህ አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ በሚወጡ ደንቦች የተቀመጡትን ክልከላዎች የጣሰ መሆኑ ወይም በማናቸውም መንገድ ቢሆን እነዚህን ሁኔታዎች አለማክበሩ ሲረጋገጥ፣
2. የአደራ ሰጭዎችን፣ ከእነርሱ መብት የተላለፈላቸውን ሰዎች፣ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን መያዣነት የያዙ ባለገንዘቦችን ወይም ሌሎች ሕጋዊ ጥያቄ ማንሳት የሚችሉ ሰዎችን መብት ለመጠበቅ ሲባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሠረዘበት ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የዕቃ ማከማቻ ቤቱንና በውስጡ የተቀመጡትን ዕቃዎች ያለመዘግየት ለሚኒስቴሩ ወይም ሚኒስቴሩ ለዚህ ተግባር ሲባል ለሚወክለው አካል የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስም ተረካቢው አካል አስተዳደራዊ ስራዎችን ብቻ እያከናወነ ይቆያል፡፡
3. አንድ የግብርና ምርት ውጤቶችን ለመቆጣጠር ለመመደብ፤ ደረጃ ለመስጠት፤ ለመመዘን ወይም ናሙና ለማውጣት የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ይህን ሥራ መሥራት ማቆሙ፣ የሙያው ሥነምግባር የሚጠይቃቸውን ደንቦች የጣሰ መሆኑ፣

እርሱ በማይጠበቅ ተግባር ውስጥ መሳተፉ፣ በማናቸውም ምክንያት ሥራውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ችሎታና ብቃት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ሚኒስቴሩ ወይም ለዚህ ተግባር ሲባል በሚኒስቴሩ የሚወከል ተቆጣጣሪ አካል ፈቃዱ እንዲ ታገድ ወይም እንዲሠረዝ ሊወስንበት ይችላል፤

4. ሚኒስቴሩ ወይም የእርሱ ተወካይ የአንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የግብርና ምርት ውጤቶች ተቆጣጣሪ መዳቢ፣ ደረጃ ሰጪ፣ መዛኝ፣ ወይም ናሙና አውጭ የሥራ ፈቃድ ለዘለቄታው እንዲሠረዝ ከመወሰኑ በፊት አጥፍቷል የተባለው ጥፋት በጽሑፍ እንዲገለጽለትና በቂ ጊዜ ተሰጥቶት በጉዳዩ ላይ የራሱን ምላሽ እንዲሰጥበት ወይም መቃወሚያ እንዲያቀርብበት ዕድል ሊሰጠው ይገባል፤
5. ፈቃድ ለመሠረዝ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በሚሆንበት ጊዜ ሚኒስቴሩ ወይም የሚኒስቴሩ ተወካይ ውሳኔውና ለውሳኔው መሠረት የሆኑት ምክንያቶች በመገናኛ ብዙኃን ለሕዝብ እንዲገለጹ ማድረግ አለበት፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 39.የታክስና ሌሎች የኢንቨስትመንት ድጋፎች

በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ተቃራኒ ድንጋጌዎች ቢኖሩም በተለይ የግብርና ምርት ውጤቶችን በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀብለው ለማከማቸት በሚያስችሉ የዕቃ ማከማቻ የንግድ ሥራ ዘርፎች የሚሰማሩ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር ባለሃብቶች አግባብ ባላቸው ኢንቨስትመንት አዋጅ ድንጋጌዎች ልዩ ትኩረት በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት ሥራ መስኮች ለተሰማሩ ኢንቨስተሮች በሚሰጠው ድጋፍ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡

### 40.የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች

ሚኒስቴሩ ወይም የእርሱ ተወካይ በሚያወጣው ሥርዓት መሠረት በሚኒስቴሩ በሚሰየም አካል (ሲስተም ፕሮቫይደር) የሚዘጋጅ የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በባለዕቃ ማከማቻ ቤቶች ወጭ እየተደረገ ለአደራ ሰጭዎች ወይም ከእነሱ መብት ለሚተላለፍላቸው ሰዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 41.ናሙና የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ ወይም የእርሱ ተወካይ በባለዕቃው ማከማቻ ቤቶች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የናሙና የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች ሊያወጣ ይችላል፡፡

42. <u>ግልግል</u>

ከዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች ወይም ከዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች ትልልፍ የሚነሱ ማናቸውም ክርክሮች በአንድ ወይም በሦስት የግልግል ዳኞች ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ተዋዋዮች ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

43. <u>ቅጣት</u>

ሚኒስቴሩ የሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የተላለፈ በሌሎች ሕጎች በተደነገገው መሠረት ይቀጣል፡፡

44. <u>ሥልጣንን በውክልና ስለመስጠት</u>

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ተግባርና ኃላፊነቶቹን ለሌላ የመንግሥት አካል ወይም የዚህን አዋጅ አፈጻጸም ለማረጋገጥ ታስቦ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ለሚቋቋሙ የምዝገባና የቁጥጥር አካላት በሙሉ ወይም በከፊል በውክልና ለመስጠት ይችላል፡፡

45. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልገውን ደንብ ለማውጣት ይችላል፡፡

46. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

1. በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 2806 እስከ ቁጥር 2824 ጭምር ያሉት ደንጋጌዎች የተተኩ ስለሆነ ተሽረዋል፡፡
2. ማናቸውም ሕግ ደንብና የሥራ መመሪያ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣም እስከሆነ ድረስ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

47. <u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት 3 1996 ዓም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 3 ቀን 1996 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

**<u>ደንብ ቁጥር 126/1998</u>**

**<u>የወጪ ንግድ ሽልማት አሰጣጥ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀጽ 47 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

“ይህ ደንብ የወጪ ንግድ ሽልማት አሰጣጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 126/1998” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

1. "የወጪ ንግድ ቀን" ማለት በወጪ ንግድ አፈጻጸም የተሻለ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ሰዎች ሽልማት እንዲሰጥበት በየዓመቱ በሚኒስቴሩ የሚወሰን ቀን ነው፤
2. "ላኪ" ማለት የኢትዮጵያ የወጪ ምርቶችን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ማለት ነው፤
3. "ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ" ማለት በዓለም አቀፍ ገበያ የሚፈለጉ የወጪ ምርቶች ማሟላት ያለባቸው የጥራትና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ስታንዳርድ ነው፤
4. "የወጪ ምርት ግብዓት" ማለት ልዩ ትኩረት ለተሰጣቸው የወጪ ምርቶች በግብዓትነት የሚያገለግልና በሀገር ውስጥ የሚመረት ምርት፣ ማሽኒያ ፣ ኬሚካል ወይም አክሰሰሪ ነው፤
5. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
6. "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡[53]

3. **የወጪ ንግድ ሽልማት የመስጠት ዓላማ**

የወጪ ንግድ ሽልማት የመስጠት ዓላማ በወጪ ንግዱ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች ለሚደርጉት ጥረትና ለሚያስመዘግቡት ውጤት ዕውቅና በመስጠት ለማበረታታትና በውጤት ላይ ያተኮረ የውድድር መንፈስ በመፍጠር የወጪ ንግዱን እንቅስቃሴ ቀጣይነት ይበልጥ ማጠናከር ይሆናል፡፡

4. **የወጪ ንግድ ሽልማት መቋቋም**

1. የሚከተሉት የወጪ ንግድ ሽልማቶች በዚህ ደንብ ተቋቁመዋል፡-

    ሀ) የላቀ የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሽልማት፤

    ለ) አዲስ የወጭ ምርት ሽልማት፤

    ሐ) የወጪ ምርት ገዢ ሽልማት፤

    መ) የወጪ ምርት ግብዓት አቅራቢ ሽልማት፤

    ሠ) የወጪ ንግድ ድጋፍ ሰጪ ሽልማት፡፡

[53] በ25/08(2011) አ.1097 አንቀጽ 9(7) መሰረት የንግድ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሽልማቶች ዓይነትና ይዘት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ፡፡

5. **<u>ለወጪ ንግድ ሽልማት ብቁ ስለመሆን</u>**

1. የላቀ የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሽልማት በማንኛውም የወጪ ንግድ ዘርፍ የተሻለ የውጪ ምንዛሪ ገቢ ለሚያስመዘግቡ ላኪዎች ይሰጣል ፡፡
2. አዲስ የወጪ ምርት ሽልማት የኤክስፖርት ስብጥርን ከማስፋት አኳያ ቀድሞ ውጪ ገበያ ያልገቡ ምርቶችን ለውጪ ገበያ በማቅረብ የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ ላኪዎች ይሰጣል ።
3. የወጪ ምርት ገዢ ሽልማት ኢትዮጵያ ወደ ውጪ የምትልካቸውን ምርቶች በመግዛት የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ ገዢዎች ወይም ለወኪሎቻቸው ይሰጣል፡፡
4. የወጪ ምርት ግብዓት አቅራቢ ሽልማት የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ የወጪ ምርት ግብዓት አቅራቢዎች ይሰጣል፡፡
5. የወጪ ንግድ ድጋፍ ሰጪ ሽልማት በወጪ ንግዱ ዘርፍ ለተሰማራው የንግዱ ኅብረተሰብ ድጋፍ በመስጠት የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ የመንግሥትና የግል ተቋማት ይሰጣል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሽልማት የሚገባቸውን ተወዳዳሪዎች ለመምረጥ የሚያስችሉ ዝርዝር መስፈርቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

6. **<u>መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>**

የወጪ ንግድ ሽልማት ተወዳዳሪዎችን የሚመርጥ ኮሚቴ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አግባብነት ካላቸው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አካላት ተውጣጥተው የሚሰየሙ አባላት የሚገኙበት ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

7. **<u>የወጪ ንግድ ሽልማት ስለመስጠት</u>**

የወጪ ንግድ ሽልማት የወጪ ንግድ ቀን በየዓመቱ በሚከበርበት ጊዜ ይሰጣል፡፡

8. **<u>የወጪ ንግድ ሽልማት ተሸላሚዎች ጥቅሞች</u>**

የወጪ ንግድ ሽልማት ተሸላሚዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት የሚከተሉት ጥቅሞች ይጠበቁላቸዋል፡፡

1. በመሳሪያ ኪራይ ወይም በፋናንስ ኪራይ ሥርዓት የቅድሚያ ተጠቃሚ የመሆን፤

2. የዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ለማሟላትና ማረጋገጫ ለማግኘት በሚደረጉ ጥረቶች በወጪ መጋራት ስርዓት ድጋፍ የማግኘት፣
3. በወጪ ንግድ ብድር ዋስትና ሥርዓት ለማይሸፈኑ የግብርና ምርቶችም በሥርዓቱ ተጠቃሚ የመሆን፣
4. በውጭ ሀገር በሚዘጋጁ የንግድ ኤግዚቢሽኖች ለመካፈል በወጪ መጋራት ሥርዓት ድጋፍ የማግኘት፣
5. በሀገር ውስጥ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ምርቶችን ለማቅረብ የቦታ ኪራይ ክፍያ ድጋፍ የማግኘት፣
6. በሚኒስቴሩ በሚታተሙ መጽሔቶች፣ ብሮሸሮች፣ ኒውስሌተሮችና ዌብሳይት ድርጅቶቻቸውንና ምርቶቻቸውን የማስተዋወቅ፣
7. በመንግሥታዊ ተቋማት በሚሰጡ ሥልጠናዎች ቅድሚያ የማግኘት፣
8. በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በሚቋቋም የክብር መዝገብ የመመዝገብ፣
9. ያገኟቸው ሽልማቶች በመገናኛ ብዙሀን እንዲገለጹላቸው የማድረግ፣
10. ወደ ሀገር ውስጥና ወደ ውጭ ሀገር በሚደረጉ የንግድ ተልእኮዎች ተሳትፎ ቅድሚያ የማግኘት፣
11. የሕዝብ በዓላት አከባበር ሥርዓቶችና በመንግሥት የሚደረጉ ግብዣዎች በሚካሂዱባቸው ሥፍራዎች ልዩ ክብር ለሚሰጣቸው እንግዶች በሚዘጋጀው ቦታ የመቀመጥ፣
12. ወደ ውጭ ሀገር ሲጓዙና ሲመለሱ ልዩ ክብር በሚሰጣቸው እንግዶች ደረጃ የመስተናገድ ፡፡

9. <u>የወጪ ንግድ ሽልማት ማስፈጸሚ በጀት</u>

የወጪ ንግድ ሽልማት ማስፈጸሚያ ወጭ ከመንግሥት በሚመደብ በጀትና ከስፖንሰርሽፕ በሚገኝ የፋይናንስ ምንጭ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

10. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡

11. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 12 ቀን 1998**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 759/2004

## ስለ ማስታወቂያ የወጣ አዋጅ

ማስታወቂያ ሕብረተሰቡ በምርት ግብይት ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽእኖ በማሳደር ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

አገሪቱ በገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት የምትመራ ከመሆኑ አንጻር ገበያው ጤናማ በሆነ ውድድር እንዲመራ በማድረግ ረገድ ማስታወቂያ ከፍተኛ አስተዋፆ የሚያደርግ በመሆኑ፤

ማስታወቂያ በሥርዓት ካልተመራ የሕብረተሰቡን መብትና ጥቅም እንዲሁም የአገርን ገጽታ ሊጎዳ የሚችል በመሆኑ፤

## የፍትህ ሚኒስቴር

የማስታወቂያ ወኪሎች፣ የማስታወቂያ አሰራጮች እና የማስታወቂያ አስነጋሪዎችን መብት እና ግዴታን በግልጽ መወሰን በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ማስታወቂያ" ማለት የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ እንዲስፋፋ ወይም ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት ወይም አላማ እንዲተዋወቅ በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የንግድ ማስታወቂያ ሲሆን የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያንና የግል ማስታወቂያን ይጨምራል፤
2. "የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ" ማለት መገናኛ ብዙሃንን፣ የውጭ ማስታወቂያን፣ የቴሌኮምን፣ የፖስታ፣ የኢንተርኔት ድረ ገፅ እና የፋክስ አገልግሎቶችን፣ ሲኒማን፣ ፊልምን፣ ቪዲዮን እና መሰል የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ይጨምራል፤
3. "የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ" ማለት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በመገናኛ ብዙሃን የሚሠራጭ መልዕክት ነው፤
4. "የግል ማስታወቂያ" ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የእፋልጉኝ ማስታወቂያ፣ የሃዘን መግለጫ እና ሌላ መሰል ማስታወቂያን ያካትታል፤
5. "የማስታወቂያ ሥራ" ማለት ማስታወቂያ ማዘጋጀትንና ማሰራጨትን፣ የፕሮሞሽን አገልግሎትን እና ከማስታወቂያ ጋር ተያያዥነት ያለውን ሌላ ሥራ የሚያካትት ሥራ ነው፤
6. "የማስታወቂያ ወኪል" ማለት በማስታወቂያ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
7. "የማስታወቂያ አሰራጭ" ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የአየር ጊዜ፣ የሕትመት ሽፋን ወይም መሰል አገልግሎት በመስጠት ማስታወቂያ

የሚያሰራጭ ሰው ነው፤

8. “የማስታወቂያ አስነጋሪ” ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት ማስታወቂያ የሚተዋወቅለት ሰው ነው፤

9. “መገናኛ ብዙሃን” ማለት የሕትመት መገናኛ ብዙሃን እና የብሮድካስት አገልግሎትን ያካትታል፤

10. “የሕትመት መገናኛ ብዙሃን” ማለት በጠቅላላው ኅብረተሰብ ወይም በአንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል እንዲነበብ ታስቦ የሚሰራጭ ማንኛውም ሕትመት ሲሆን ጋዜጣን፣ መጽሔትን፣ የማስታወቂያ መፅሀፍ ወይም የሎው ፔጅን፣ የስልክ ቁጥር ማውጫ ወይም ግሪን ፔጅን ያካትታል፤

11. “የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ነው፤

12. “የውጭ ማስታወቂያ” ማለት፡-

   ሀ) በቢልቦርድ፣ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የሚሰራጭ፤

   ለ) በሕንጻ ወይም በማናቸውም ስትራክቸር ወይም በትራንስፖርት ተሽከርካሪ ላይ የሚፃፍ ወይም የሚለጠፍ፤

   ሐ) በተንጠልጣይ ነገር፣ በፖስተር፣ በስቲከር፣ በብሮሸር፣ ሊፍሌት ወይም በራሪ ወረቀት የሚሰራጭ፤

   መ) በድምጽ ካሴት፣ በድምፅ ማጉያ መሳሪያ የሚሰራጭ፤ ወይም

   ሠ) በሌላ መሰል ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ፤

   ማስታወቂያ ነው፡፡

13. “በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም” ማለት ፕሮግራሙን ለማሰራጨት ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተከፈለበት ወይም የክፍያ ቃል የተገባበት ፕሮግራም ነው፤

14. “ስፖንሰር” ማለት ፕሮግራምን ወይም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ስፖንሰር የሚያደርግ ሰው ነው፤

15. “በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያ” ማለት ከሁለት ደቂቃ የበለጠ ጊዜ የሚወስድና ለብሮድካስተሩ ክፍያ የፈፀመ ሰውን ምርት፣ አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት በፕሮግራም መልክ ተዘጋጅቶ በብሮድካስት አገልግሎት

የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነው፤

16. “ተካታች ማስታወቂያ” ማለት ብሮድካስተሩ ገንዘብ የተቀበለበትን ወይም ጥቅም ያገኘበትን የማንኛውንም ሰው ምርት፣ አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት በተዘዋዋሪ ለማስተዋወቅ በፅሁፍ፣ በድምጽ ወይም በምስል ከአንድ ፕሮግራም ጋር የተካተተ ማስታወቂያ ነው፤

17. “ተጓዳኝ ማስታወቂያ” ማለት በቴሌቪዥን መስኮት ወይም ስክሪን ከሚሰራጨው ፕሮግራም ጋር አልፎ አልፎ በተጓዳኝ መስኮት የሚታይ ማስታወቂያ ነው፤

18. “የአፀፋ ማስታወቂያ” ማለት የዚህን አዋጅ ድንጋጌ በሚጥስ ማስታወቂያ የተነሳ በህዝብ ዘንድ የተፈጠረውን የተሳሳተ አመለካከት ለማቃናት ወይም ለጉዳት የተጋለጠውን ወገን መብት ለማስጠበቅ የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነው፤

19. “ፕሮግራም” ማለት በድምፅ ወይም በምስል ወይም በሁለቱ ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ በብሮድካስት አገልግሎት የሚቀርብ ስርጭት ነው፤

20. “የዜና እና የወቅታዊ ጉዳዮች ዘገባ” ማለት አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊ ወይም አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እና ወቅታዊ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማኅበራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት በብሮድካስት አገልግሎት የሚቀርብ ዜና፣ ዘገባ፣ ማብራሪያ፣ ትርጓሜ፣ አስተያየት፣ ሐተታ ወይም ትንታኔ ነው፤

21. “እለታዊ የስርጭት ጊዜ” ማለት ከንጋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ባሉት 24 ሰዓታት የሚተላለፍ የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት ነው፤

22. “ሎተሪ” ማለት የሽልማት አሸናፊው በእድል፣ በእጣ አወጣጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ የሚታወቅበት ጨዋታ ወይም ድርጊት ሲሆን አግባብ ባለው ሕግ የተመለከቱትን ጨዋታዎችና ድርጊቶች ያካትታል፤

23. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

24. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ነው፤

25. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል

ነው፤

26.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሠራ የማስታወቂያ ወኪል፣ የማስታወቂያ አሰራጭ እና የማስታወቂያ አስነጋሪ፤
2. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚዘጋጅና በሚሰራጭ ማስታወቂያ፤
3. በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖር ሰው አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በውጭ አገር በተቋቋመ የኢንተርኔት ድረ ገፅ ላይ በሚሰራጭ ማስታወቂያ፤
4. አገር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ በሚገባ እና ዋነኛ አትኩሮቱ በአገር ውስጥ ጉዳዮች ላይ በሆነ ማናቸውም የውጭ አገር ጋዜጣ ወይም መፅሄት አማካኝነት በሚሰራጭ ማስታወቂያ፤ እና
5. በአገር ውስጥ ተዘጋጅቶ በውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎት ወደ አገር ውስጥ በሚሰራጭ ማስታወቂያ።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በማስታወቂያ ሥራ ስለመሰማራት</u>

4. <u>በማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት</u>

1. ማንኛውም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ግለሰብ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመና በካፒታሉ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ ድርሻ የሌለበት የንግድ ማኅበር በማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ በማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት ይኖረዋል፡፡

5. <u>የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ ስለማውጣት</u>

1. በማስታወቂያ ወኪልነት ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የመንግስት አካል የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ማስታወቂያ አሠራጭ ማስታወቂያ በማዘጋጀት ሥራ ላይ ለመሰማራት አግባብ ካለው የመንግስት አካል የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ

ማውጣት አለበት፡፡

3. ማስታወቂያ በማዘጋጀት ሥራ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን የማስታወቂያ ሥራውን ከመገናኛ ብዙሃን ሥራው በተለየ አደረጃጀት ማከናወን አለበት።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ምርቱ፣ አገልግሎቱ ወይም ሌላ መልዕክት እንዲተዋወቅለት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልገው የራሱን ማስታወቂያ አዘጋጅቶ ማሰራጨት ወይም ማስታወቂያውን አዘጋጅቶ በማስታወቂያ አሰራጭ አማካኝነት እንዲሰራጭለት ማድረግ ይችላል፡፡ በማስታወቂያው ላይም ማንነቱን እና አድራሻውን በግልፅ ማካተት አለበት፡፡
5. ማንኛውም በውጭ አገር ተዘጋጅቶ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ሊደረግ የሚችለው በማስታወቂያ ወኪል አማካኝነት ነው፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ፈቃድ የሚሰጥ አግባብ ያለው የመንግስት አካል ባለፈቃዶቹን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀን ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ አለበት፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ስለማስታወቂያ በጠቅላላው**

6. **ስለማስታወቂያ ይዘትና አቀራረብ**

1. ማንኛውም ማስታወቂያ፡-

ሀ) ማንኛውንም ሕግ ወይም መልካም ሥነ ምግባር የማይጻረር፣

ለ) አሳሳች ወይም ተገቢ ካልሆነ አገላለጽ ነፃ የሆነ፣

ሐ) የሕብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ እሴት የሚያከብርና የሸማቹን ሕጋዊ ጥቅም የማይጎዳ፣

መ) የሚተዋወቀውን ምርት ወይም አገልግሎት እውነተኛ ባህሪ፣ ጥቅም፣ ጥራትና ሌላ መሰል መረጃዎችን የሚገልጽ፣

ሠ) የሌሎችን ሰዎች ምርት ወይም አገልግሎት የማያንቋሽሽ፣

ረ) የአገርን ክብርና ጥቅም የሚጠብቅ፣ እና

ሰ) የሙያ ሥነ ምግባርን የሚያከብር፣

ይዘትና አቀራረብ ያለው መሆን አለበት፡፡

2. ማንኛውም በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ከሌሎች ፕሮግራሞች የተለየ መሆኑ በግልጽ እንዲታወቅ ሆኖ መቅረብ ያለበት ሲሆን በፕሮግራሞቹ ይዘት ላይም ተፅእኖ ማድረግ የለበትም፡፡
3. ማስታወቂያ በዜና መልክ መዘጋጀትና መሰራጨት የለበትም።
4. የማስታወቂያ ወኪል የአንድን ሰው ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሌላ መልእክት የሚያስተዋውቅ የንግድ ማስታወቂያ አዘጋጅቶ ባሰራጨ በሦስት ወራት ውስጥ የሌላ ሰውን ተመሳሳይ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሌላ መልእክት በተመሳሳይ የማስታወቂያ ተዋናይ ምስል ወይም ድምፅ አዘጋጅቶ ማሰራጨት የለበትም።
5. ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች እንዲሁም ለፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ውጤቶች መብት ጥበቃ የወጡ ሕግጋት በማስታወቂያ ሥራ ላይ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

7. <u>ሕግን ወይም መልካም ሥነ ምግባርን ስለሚፃረር ማስታወቂያ</u>

የሚከተሉት ማስታወቂያዎች ሕግን ወይም መልካም ሥነ ምግባርን የሚጻረር ይዘት ወይም አቀራረብ እንዳላቸው ሆነው ይቆጠራሉ፡-

1. ቋንቋን፣ ፆታን፣ ዘርን፣ ብሔርን፣ ብሔረሰብን፣ ሙያን፣ ሐይማኖትን፣ እምነትን፣ ፖለቲካዊ ወይም ማኅበራዊ አቋምን አስመልክቶ የሰው ልጅን ስብዕና፣ ነጻነት ወይም እኩልነት የሚጻረር ምስልን፣ አነጋገርን ወይም ንጽጽርን የያዘ ማስታወቂያ፤
2. የግለሰብን፣ የብሔርን፣ የብሔረሰብን ወይም የሕዝብን መልካም ሥነ ምግባር ወይም ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም የድርጅትን መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፍ ማስታወቂያ፤
3. ብሔራዊ ወይም የክልል ሰንደቅ ዓላማን፣ አርማን፣ ብሔራዊ መዝሙርን ወይም ገንዘብን የሚያንቋሽሽ ወይም የሚያዋርድ ማስታወቂያ፤
4. የአካል ጉዳተኛን፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደሙ ውስጥ ያለበትን ወይም በሌላ ህመም የተያዘ ሰውን ክብርና ሥነ ልቦና የሚነካ ማስታወቂያ፤
5. በሕብረተሰቡ መካከል አመጽ፣ የሀይል ተግባር፣ ሽብር፣ ግጭት ወይም የፍርሀት ስሜት እንዲፈጠር የሚያነሳሳ ማስታወቂያ፤
6. የሕብረተሰቡን አካላዊና አእምሯዊ ጤንነት ወይም ደህንነት ለጉዳት

የሚያጋልጥ ድርጊት እንዲፈጸም የሚያነሳሳ ማስታወቂያ፤

7. አግባብ ያለው የመንግስት አካል የሚወስነውን የድምፅ መጠን በመተላለፍ በማናቸውም አይነት የድምፅ ማጉያ መሳሪያ አማካኝነት አካባቢን በከፍተኛ ድምፅ በመበከል የሚሰራጭ ማስታወቂያ፤
8. ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ የጽሑፍ መልእክት፣ ምስል፣ ስዕላዊ መግለጫ፣ ፊልም ወይም መሰል አቀራረብን የያዘ ማስታወቂያ፤
9. የግለሰብን ስም፣ ምስል ወይም ፎቶግራፍ ግለሰቡ ሳይፈቅድ የሚጠቀም ወይም በሕግ ጥበቃ የሚደረግለትን የኪነጥበብ ወይም የፈጠራ ሥራ የሚመለከተው ሰው ሳይፈቅድ የሚጠቀም ማስታወቂያ፤
10. ለትራፊክ ደህንነት ወይም ለአካባቢ ጥበቃ ተጻራሪ የሆነ ማስታወቂያ፤
11. የመከላከያ ሰራዊት ወይም የፖሊስ የደንብ ልብስን፣ ምልክትን ወይም ሽልማትን በመልበስ ወይም በማድረግ የሚቀርብ የንግድ ማስታወቂያ፤
12. በሌላ ሕግ የተከለከለ ይዘት ወይም አቀራረብ የያዘ ወይም ማንኛውም ሕግ እንዲጣስ የሚያነሳሳ ማስታወቂያ፡፡

8. <u>ስለአሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ማስታወቂያ</u>

የሚከተሉት ማስታወቂያዎች አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ እንዳላቸው ሆነው ይቆጠራሉ፡-

1. የሚተዋወቀው ምርት የተመረተበት አገር ወይም ቦታ፣ ቀን፣ የምርቱን ባህሪ፣ በውስጡ የያዘውን ንጥረ ነገር፣ ክብደት፣ መጠን፣ ያለውን ጠቀሜታ ወይም ተቀባይነት በሐሰት የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤
2. ታክስና ሌላ ሕጋዊ ክፍያን ጨምሮ ምርቱ ወይም አገልግሎቱ የሚሸጥበትን ዋጋ በሚመለከት ወይም ለምርቱ ወይም ለአገልግሎቱ የቅጅ ወይም የፓተንት መብት፣ የጥራትና የደረጃ መሥፈርት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም እውቅና ካለው አካል ሽልማት መገኘቱን ወይም ሌላ መሰል መረጃን በሚመለከት በሐሰት የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤
3. አንድ ምርት ወይም አገልግሎት የሌለውን ጥቅም፣ ጥራት፣ መአዛ፣ ጣእም፣ ንጥረ ነገር፣ ጥንካሬ፣ እድሜ ወይም ብርካቴ እንዳለው አስመስሎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤

4. የአገልግሎት ጊዜው ለማለፍ የደረሰን ወይም ያለፈበትን ምርት የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤
5. የዱቄት ወተትን ወይም መሰል ምግብን ከስድስት ወር እድሜ በታች ለሆኑ ሕጻናት ከእናት ጡት ወተት የሚመረጥ ወይም የማይተናነስ እንደሆነ አድርጎ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤[54]
6. የሌላ ሰውን ምርት ወይም አገልግሎት እንደራስ አድርጎ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤
7. ተገቢ የሆነ የንግድ ውድድር መርህን በመተላለፍ የሚተዋወቀውን ምርት ወይም አገልግሎት የማይጠቀም ሰውን የሚያንቋሽሽ ማስታወቂያ፤
8. አንድን ምርት ወይም አገልግሎት ከሌላ ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በማወዳደር ለንጽጽር የቀረበውን ምርት ወይም አገልግሎት ወይም የተወዳዳሪውን ብቃት ወይም ዝና የሚያንቋሽሽ ወይም የውጭ አገር ምርት ተመራጭ እንዲሆን ለማድረግ ሲባል አገራዊ ምርትን ወይም አገልግሎትን የሚያንቋሽሽ ማስታወቂያ፤
9. ከውጭ ቋንቋ የተወሰደው ቃል ማስታወቂያው በተሰራጨበት የአገሪቱ ቋንቋ ፍቺ ከሌለው በቀር የአገሪቱን ቋንቋ ከውጭ አገር ቋንቋ ጋር በማቀላቀል የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤
10. በገበያ ውስጥ የሌለ ምርት ወይም አገልግሎት እንዳለ አስመስሎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤
11. አንድን ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት ከሌላ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት ጋር ሊያሳስት የሚችል አሻሚ የሆነ ማስታወቂያ፤
12. በትክክለኛ ዋጋው እየተሸጠ ያለን ምርት ወይም አገልግሎት በነጻ እየተሰጠ ወይም በቅናሽ እየተሸጠ እንደሆነ አድርጎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤
13. ለሸያጭ በቀረቡ እክሲዮኖቾች ያስገኛሉ የሚባለውን እርግጠኛ ያልሆነ የትርፍ ድርሻ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤
14. ምርት ወይም አገልግሎት ለሚገዛ ደንበኛ ሽልማት ወይም የዋስትና መብት እንደሚሰጥ ተገልጾ ሽልማቱ የማይሰጥበት ወይም ዋስትናው የማይከበርበት ማስታወቂያ፤

[54] በ25/39(2011) አ.1112 በአንቀፅ 70(2) ተሻረ፡፡

15. የምርምር ውጤትን ወይም ከሳይንሳዊ፣ ከቴክኒካዊ ወይም ከሌላ ሕትመት የተወሰደ መግለጫን ወይም ጥቅስን ከሚተዋወቀው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር ግንኙነት ሳይኖረው ግንኙነት እንዳለው አስመስሎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤
16. ሐሰተኛ ምስክርነትን የሚጠቀም ማስታወቂያ፤
17. በማስረጃ ሊረጋገጥ የማይችልን “የመጀመሪያው”፣ “ብቸኛው”፣ “ለመጀመሪያ ጊዜ”፣ “ከዚህ ቀደም ያልነበረ”፣ “ወደር የሌለው” የሚል ወይም መሰል የሆነ ማወዳደሪያን የያዘ ማስታወቂያ፤
18. መሰል አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ ያለው ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ፡፡

9. <u>የተለየ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለሚያስፈልገው ማስታወቂያ</u>

1. አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶችን ማሟላት የሚገባውን ማንኛውንም ምርት ወይም አገልግሎት ለማስተዋወቅ በቅድሚያ አግባብ ካለው አካል የተሰጠ የጥራት ወይም መሰል ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መኖር አለበት፡፡
2. የማስታወቂያ አስነጋሪው ለሚያቀርበው ምርት ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ማግኘት የሚገባው ከሆነ አግባብ ካለው አካል የምስክር ወረቀቱን ወይም ፈቃዱን ሳያገኝ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ማስተዋወቅ አይችልም፡፡

10. <u>አካለመጠን ያልደረሰ ልጅንስለሚመለከት ማስታወቂያ</u>

የሚከተሉትን ማስታወቂያዎች ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡-

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅን አመለካከት፣ ስሜት ወይም አስተሳሰብ ሊጎዳ የሚችል ማስታወቂያ፤
2. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በቤተሰቡ፣ በአሳዳሪው፣ በሞግዚቱ፣ በመምህሩ፣ በሕብረተሰቡ ወይም በአገሩ ላይ ፍቅር ወይም እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ ማስታወቂያ፤
3. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በማስታወቂያ የተነገረ ምርትን ወይም አገልግሎትን ቤተሰቡን፣ አሳዳሪውን፣ ሞግዚቱን ወይም ሌላ ሰውን እንዲያስገዛ በግልጽ የሚገፋፋ ማስታወቂያ፤
4. በማስታወቂያ የተነገረን ምርት ወይም አገልግሎት ትክክለኛ ያልሆነ ዋጋ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በመግለጽ ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በማናቸውም

ቤተሰብ ሊገዛ ይችላል የሚል እምነት በአካለመጠን ባልደረሰ ልጅ አእምሮ እንዲቀረጽ የሚያደርግ ማስታወቂያ፤

5. በማስታወቂያ የተነገረን ምርት ወይም አገልግሎት የገዛ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ካልገዛ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የተሻለ እንደሆነ በማስመሰል ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ያልገዛው የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርግ ማስታወቂያ፤
6. በማስታወቂያ ውስጥ የተለያየ ድምፅን፣ ፅሁፍንና ምስልን በማቀላቀል አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሕገ ወጥ ወይም ለመልካም ሥነ ምግባር ተፃራሪ የሆነ ተግባር እያከናወነ ወይም በአደገኛ ሁኔታ ወይም ቦታ ውስጥ ሆኖ የሚያሳይ ማስታወቂያ፤
7. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ያለ አሳዳሪውና ሞግዚቱ ፈቃድ የማስታወቂያ አቅራቢ ወይም ተዋናይ አድርጎ የሚጠቀም ማስታወቂያ፤ ወይም
8. መሰል ይዘት ወይም አቀራረብ ያለው ማናቸውንም ሌላ ማስታወቂያ፡፡

## 11.<u>ስለፀረ አረም ወይም ፀረ ተባይ ማስታወቂያ</u>

የፀረ አረም ወይም የፀረ ተባይ ማስታወቂያ፡-

1. አጠቃቀሙን የተመለከተና በአጠቃቀሙ ጊዜ መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ የሚገልፅ ግልጽና ትክክለኛ መረጃ መስጠት አለበት፤
2. ሙሉ በሙሉ መርዛማ እንዳልሆነ እና ለጤና ጎጂ እንዳልሆነ ተደርጎ መሠራጨትየለበትም።

## 12.<u>ሎተሪን ስለሚመለከት ማስታወቂያ</u>

1. ማንኛውም ሰው ሎተሪን የሚመለከት ማስታወቂያ ለማስተዋወቅ የሚችለው በሕግ ወይም አግባብ ባለው የመንግስት አካል የሎተሪን ሥራ ለማካሄድ የተሰጠ ፈቃድ ሲኖረው ነው፡፡
2. ማንኛውም የሎተሪ ማስታወቂያ፡-

   ሀ) እጣውን ያዘጋጀው ሰው ስምና ሕጋዊ ፈቃድ ያለው መሆኑን፤

   ለ) እጣው የሚያስገኘውን የገንዘብ መጠን ወይም የሽልማት አይነት፤ እና

   ሐ) እጣው የሚወጣበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፤

   መግለጽ አለበት፡፡

## 13.<u>ስለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ</u>

1. የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ የማንኛውንም ሰው የንግድ  ሥራ እንቅስቃሴ፣ ምርት፣ አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት የሚያስተዋውቅ መሆን የለበትም፡፡
2. በማስታወቂያ አሰራጭ ለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ የሚጠየቀው ክፍያ ለንግድ ማስታወቂያ ከሚጠየቀው ክፍያ መብለጥ የለበትም፡፡
3. ማንኛውም የማስታወቂያ አሠራጭ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያን ከንግድ ማስታወቂያ ቅድሚያ በመስጠት በማስታወቂያ አስነጋሪው ምርጫ መሰረት ማሠራጨት አለበት፡፡
4. የማስታወቂያ አሰራጩ ለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ ቅድሚያ በመስጠቱ ከማስታወቂያ ወኪል ወይም ከማስታወቂያ አስነጋሪ ጋር በገባው ውል መሰረት መሰራጨት የነበረበት ሌላ ማስታወቂያ ሳይሰራጭ ቢቀር ይህንኑ ለማስታወቂያ ወኪሉ ወይም ለማስታወቂያ አስነጋሪው አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡

14.**<u>የአፀፋ ማስታወቂያ</u>**

1. የማስታወቂያ አስነጋሪው፣ የማስታወቂያ ወኪሉ እና የማስታወቂያ አሰራጩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚጥስ ማስታወቂያ የተነሳ መብቱ የተነካበትንና ለጉዳት የተጋለጠውን ወገን ሕጋዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የአፀፋ ማስታወቂያ ማውጣት አለባቸው፡፡
2. የማስታወቂያ አስነጋሪው፣ የማስታወቂያ ወኪሉ እና የማስታወቂያ አሰራጩ ተቃራኒ ማስረጃ እስካላቀረቡ ድረስ የአፀፋ ማስታወቂያውን ለማውጣት የሚያስፈልገውን ወጪ በማይከፋፈል ኃላፊነት ይሸፍናሉ፡፡
3. የአፀፋው ማስታወቂያ ቀደምሲል የተሰራጨው ማስታወቂያ በተዘጋጀበትና በተሰራጨበት መንገድ፣ በቆየበት ጊዜ እና በተሰራጨበት አካባቢ በተመሳሳይ ሁኔታ መሠራጨት አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው ሌላ አካል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የአፀፋ ማስታወቂያው የተሰራጨበት ዘዴ፣ የቆየበት ጊዜ እና የተሰራጨበት አካባቢን በተመለከተ ለውጥ እንዲደረግ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስፖንሰርሺፕ</u>

15.**<u>በስፖንሰር ስለሚቀርብ ፕሮግራም</u>**

1. በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም ይዘት ወይም የጊዜ ሰሌዳ በስፖንሰሩ ተፅእኖ

ስር መውደቅ የለበትም፡፡ በተለይም በፕሮግራሙ ይዘት ውስጥ የስፖንሰሩ ምርት ወይም አገልግሎት እንዲሸጥ ወይም እንዲከራይ መቀስቀስ የለበትም፡፡

2. በስፖንሰር በሚቀርብ ፕሮግራም የስፖንሰር አድራጊው ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ ምርት እና መሠል ሁኔታዎች ወይም ለስፖንሰሩ የሚቀርብ ምስጋና በፕሮግራሙ መጀመሪያ፣ አካፋይ ወይም መጨረሻ ላይ ሊተዋወቅ ወይም ሊገለፅ ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 17(1) እና አንቀፅ 19 የተደነገገው ቢኖርም ተጓዳኝ፣ በፕሮግራም መልክ የሚሰራጭ ማስታወቂያን፣ የስፖንሰር አድራጊውን ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ የምርት እና መሰል መልእክቶችን እንዲሁም የምስጋና መግለጫን ጨምሮ ለማንኛውም ማስታወቂያ የሚመደበው ጊዜ ስፖንሰር ከተደረገው ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ10 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

3. በስፖንሰሩና በብሮድካስተሩ መካከል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ስፖንሰር በተደረገ ፕሮግራም ጣልቃ ሌላ የንግድ ማስታወቂያ መሰራጨት የለበትም፡፡ ስፖንሰር አድራጊዎች ከአንድ በላይ ሲሆኑ ሁሉም መፍቀድ አለባቸው።
4. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 25 እና አንቀፅ 26 መሰረት ማስታወቂያ እንዳይነገርለት የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ምርትን የሚያመርት ወይም የሚሸጥ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ማስታወቂያው እንዳይሰራጭ ለተከለከለበት የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ ስፖንሰር ሊሆን አይችልም፡፡
5. የፖለቲካ ድርጅቶች እና የሃይማኖት ተቋማት ስፖንሰር ሊሆኑ አይችሉም፡፡
6. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በማናቸውም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ ስፖንሰር ተደርጎ በሚሰራጭ ማስታወቂያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

16.<u>ስፖንሰር የማይደረግ ፕሮግራም</u>

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይቶችን የሚያሠራጩ ፕሮግራሞች፣ የዜና ፕሮግራሞች እና የወቅታዊ ጉዳይ ዘገባ ፕሮግራሞች ስፖንሰር መደረግ የለባቸውም።
2. የሕጻናት ፕሮግራም በንግድ ድርጅት አማካኝነት ስፖንሰር መደረግ የለበትም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የስፖርት ዜና፣ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና የቢዝነስ ዘገባዎች ከሌሎች ዜናዎች ተለይተው የሚቀርቡ ከሆነ ስፖንሰር ሊደረጉ ይችላሉ።

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>በተለያዩ የማሰራጫ መንገዶች ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>

17. <u>በብሮድካስት አገልግሎት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>

1. ማስታወቂያ ለማሰራጨት የተቋቋመ የብሮድካስት አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር በብሮድካስት አገልግሎት ተጓዳኝ፣ በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያን፣ የስፖንሰር አድራጊውን ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ ምርት እና መሰል መልእክቶችን እንዲሁም የምስጋና መግለጫን ጨምሮ ለማናቸውም ማስታወቂያ የሚመደበው ጊዜ፡-

   ሀ) ከእለቱ ፕሮግራም ወይም ከአንድ የተለየ ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ20 በመቶ

ለ) ከአንድ ሰዓት በታች የቆይታ ጊዜ ካለው ከአንድ የተለየ ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ15 በመቶ፤ ወይም

ሐ) በአንድ ሰዓት የስርጭት ጊዜ ከ12 ደቂቃ፤

መብለጥ የለበትም፡፡

2. ማንኛውም ተጓዳኝ ማስታወቂያ፡-

ሀ) በምስል ወይም በፎቶግራፍ የሚሰራጭ ሲሆን የማስታወቂያው የስፍራ ሽፋን የቴሌቪዥኑ መስኮት ወይም የስክሪኑ ፍሬም ከሚሸፍነው ጠቅላላ ስፍራ ከ15 በመቶ፤ ወይም

ለ) ተንቀሳቃሽ ተነባቢ መስመር ሆኖ የሚሰራጭ ሲሆን የማስታወቂያው ስፍራ ሽፋን የቴሌቪዥኑ መስኮት ወይም የስክሪኑ ፍሬም ከሚሸፍነው ጠቅላላ ስፍራ ከ7 በመቶ፤

መብለጥ የለበትም፡፡

3. የሚከተሉት ፕሮግራሞች በማስታወቂያ መቋረጥ የለባቸውም፡-

ሀ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይት፤

ለ) የሕፃናት ፕሮግራም፤

ሐ) የዜና ወይም የወቅታዊ ጉዳይ ዘገባ፤

መ) የቅጅ መብት ባለቤቱ ካልፈቀደ በስተቀር ሙዚቃ፣ ድራማ ወይም ዶክሜንተሪ ፊልም፤

ሠ) የስርጭት ጊዜው ከ20 ደቂቃ የማይበልጥ ማንኛውም ፕሮግራም፡፡

4. በአንድ ሰዓት የስርጭት ጊዜ ውስጥ የአንድን ምርት ወይም አገልግሎት ተመሳሳይ የንግድ ማስታወቂያ ከሁለት ጊዜ በላይ ማሰራጨት አይቻልም፡፡

5. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይት፣ በሕጻናት፣ በዜና ወይም በወቅታዊ ጉዳይ ዘገባ ፕሮግራም ውስጥ ተካታች ማስታወቂያ እንዲኖር ማድረግ አይቻልም፡፡

**18.<u>በፕሮግራም መልክ የሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>**

1. ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያን ማሰራጨት ይችላል፡፡

2. ማስታወቂያ ለማሰራጨት የተቋቋመ የብሮድካስት አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያ ከሌሎች ፕሮግራሞች የተለየ መሆኑ በግልፅ እንዲታወቅ

ለማድረግ የሚያስችል ርዕስ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡

19. <u>በማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ስለሚሠራጭ ማስታወቂያ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17(1) የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ተጓዳኝ፣ በፕሮግራም መልክ የሚሰራጭ ማስታወቂያን፣ የስፖንሰር አድራጊውን ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ ምርት እና መሰል መልእክቶችን እንዲሁም የምስጋና መግለጫን ጨምሮ ለማንኛውም ማስታወቂያ የሚመደበው ጊዜ፡-

1. ከእለቱ ፕሮግራም ወይም ከአንድ የተለየ ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ15 በመቶ፤ ወይም
2. በአንድ ሰዓት የስርጭት ጊዜ ከ9 ደቂቃ፤

መብለጥ የለበትም፡፡

20. <u>በጋዜጣና መጽሔት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>

ማስታወቂያ ለማሰራጨት ብቻ የተቋቋመ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ጋዜጣ ወይም መጽሔት ላይ የሚሰራጩ ማስታወቂያዎች፡-

1. ከእያንዳንዱ እትም ጠቅላላ የሕትመት ሽፋን ከ60% በመቶ የሚበልጠውን መያዝ የለባቸውም፤
2. ከሌሎች የሕትመቱ ውጤቶች የተለዩ መሆናቸውበግልፅ እንዲታወቅ "ማስታወቂያ" በሚል ርዕስ ሥር መቅረብ አለባቸው፡፡

21. <u>ስለውጭ ማስታወቂያ</u>

1. ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳያገኝና እንደ አግባብነቱ ባለቤቱ ወይም ባለይዞታው ሳይስማማ፡-
   ሀ) በማንኛውም ሕንጻ፣ ግድግዳ፣ አጥር፣ የአውቶብስ ፌርማታ፣ ምሰሶ፣ የቴሌኮም አገልግሎት መስጫ መሣሪያ ወይም ሌሎች መሰል ነገሮች ላይ፤
   ለ) በማንኛውም መንገድ፣ አውራጎዳና፣ የባቡር ሀዲድ ወይም የሕዝብ መጓጓዣ ላይ፤ ወይም
   ሐ) በማንኛውም የሕዝብ አገልግሎት በሚሰጥ ሥፍራ ላይ፤

   የውጭ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ መስቀል፣ መትከል ወይም በሌላ መንገድ ማስቀመጥ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ከመንገድ ምልክት ወይም አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክት ጋር በሚመሳሰል፣ እይታን በሚጋርድ፣ የትራፊክ እንቅስቃሴን በሚገታ ወይም

ደህንነቱን በሚቀንስ ወይም የአካባቢን ገጽታና ውበት በሚያበላሽ መልኩ መቀመጥ የለበትም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀመጥ የውጭ ማስታወቂያ በአገር ውስጥ ቋንቋ ወይም ፊደል የተጻፈ መሆን ወይም በውጭ ቋንቋ ወይም ፊደል ጭምር የተጻፈ ሲሆን የአገር ውስጥ ቋንቋው ወይም ፊደሉ ከውጭው ቋንቋ ወይም ፊደል አስቀድሞ ወይም ከላይ ሆኖ የተጻፈ መሆን አለበት፡፡

22. **<u>በስልክ አገልግሎት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>**

1. በስልክ አገልግሎት አማካኝነት ማስታወቂያ ለማሰራጨት የሚቻለው የቴሌኮም አገልግሎትን ከሚሰጠው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሲኖር ነው፡፡
2. የሕዝብ ማስታወቂያ ወይም የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪውን የሚመለከት ማስታወቂያ ካልሆነ በስተቀር የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚው ሳይፈቅድ ማንኛውም የንግድ ማስታወቂያ በስልክ አገልግሎት ተጠቃሚው የስልክ አገልግሎት መስጫ መሳሪያ ማሰራጨት የተከለከለ ነው።
3. የማስታወቂያ ወኪሉ፣ የማስታወቂያ አሰራጩ እና አስነጋሪው ለስልክ አገልግሎት ተጠቃሚው የሚያሰራጩት ማስታወቂያ ክፍያ የሚከፈልበት ከሆነ ለተጠቃሚው በግልፅ ማሳወቅ አለባቸው።

23. **<u>በፖስታ አገልግሎት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>**

1. በፖስታ አገልግሎት አማካኝነት ማስታወቂያ ለማሰራጨት የሚቻለው የፖስታ አገልግሎትን ከሚሰጠው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሲኖር ነው፡፡
2. የፖስታ አገልግሎት ሰጪው የሕዝብ ማስታወቂያን ወይም የፖስታ አገልግሎት ሰጪውን የሚመለከት ማስታወቂያን በፖስታ አገልግሎት ተጠቃሚ የፖስታ ሳጥን ማሰራጨት ይችላል፤ ሆኖም በፖስታ አገልግሎት ተጠቃሚ የፖስታ ሳጥን የንግድ ማስታወቂያን ለማሰራጨት የፖስታ አገልግሎት ተጠቃሚውን ፍላጐት ከግምት ውስጥ ማስገባትና አሰራር መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

24. **<u>በሲኒማ ወይም በፊልም ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>**

የሲኒማ ወይም የፊልም ትእይንትን በየእረፍት ሰዓቱ ወይም በየትእይንቱ ምዕራፍ ጣልቃ ካልሆነ በስተቀር በማስታወቂያ ማቋረጥ ክልክል ነው፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የተከለከሉና ገደብ የተደረገባቸው ማስታወቂያዎች</u>

## 25. የተከለከለ ማስታወቂያ

1. የሚከተሉትን ማስታወቂያዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማንኛውም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡-
   ሀ) አግባብ ባለው የመንግስት አካል በአደንዛዥ እፅነት የተመደበን ማንኛውንም እፅ የሚመለከት ማስታወቂያ፤
   ለ) ያለሐኪም ትእዛዝ የማይሰጥ ወይም በጥቅም ላይ የማይውል መድሀኒትን ወይም የሕክምና መገልገያን ተጠቃሚው በቀጥታ እንዲጠቀም የሚገፋፋ ማስታወቂያ፤
   ሐ) ናርኮቲክ መድሐኒትን ወይም ሳይኮቴራፒክ ንጥረ ነገርን የሚመለከት ማስታወቂያ፤
   መ) የጦር መሳሪያ ማስታወቂያ፤
   ሠ) የቁማር ማስታወቂያ፤
   ረ) የሕገ ወጥ ምርት ወይም አገልግሎት ማስታወቂያ፤
   ሰ) የአራጣ አበዳሪ ማስታወቂያ፤
   ሸ) የጥንቆላ ማስታወቂያ፤
   ቀ) የሲጋራ ወይም የሌሎች የትምባሆ ውጤቶች ማስታወቂያ፤
   በ) የፖለቲካ ግብ ያለው ማስታወቂያ፤ እና
   ተ) ሌሎች በሕግ የተከለከሉ ማስታወቂያዎች፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (በ) የተደነገገው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የምርጫ እጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት የሚያሰራጨውን የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅቱ የሚያሰራጨውን የአድራሻ ለውጥ፣ የስብሰባ ጥሪ እና መሰል ማስታወቂያዎችን የሚከለክል አይደለም።

## 26. ገደብ የተደረገበት ማስታወቂያ

1. የአልኮል መጠኑ ከ12 በመቶ በላይ የሆነ ማንኛውንም መጠጥ የሚመለከት ማስታወቂያ ከውጭ ማስታወቂያ እና እለታዊና ሳምንታዊ ካልሆነ ጋዜጣ እና መጽሔት በስተቀር በሌሎች የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶች አማካኝነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የአልኮል መጠኑ ከ12 በመቶ

በላይ የሆነ የማንኛውም መጠጥ ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን፣ በድምፅ ማጉያ፣ በድምፅ ካሴት ወይም በሌላ በምስልና በድምፅ በሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ሊሰራጭ አይችልም፡፡

3. ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ፡-

ሀ) የአልኮል መጠጡን መውሰድ ለጤና ተስማሚ እንደሆነ፣ ግላዊ ወይም ማኅበራዊ ስኬትን እንደሚያስከትል፣ የተሻለ ሥነ ልቦናዊ ወይም አካላዊ ብቃት እንደሚያስገኝ ወይም ፈዋሽ እንደሆነ የሚገልጽ ወይም በተደጋጋሚ ወይም ከልክ በላይ እንዲጠጣ የሚገፋፋ፤

ለ) ከአልኮል ሱስ መጠበቅን የሚያጣጥል ወይም የሚቃወም፤

ሐ) አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የማስታወቂያው ተዋናይ አድርጎ የሚጠቀም፤ ወይም

መ) ሌላ መሰል መልእክት የሚያስተላልፍ፤ መሆን የለበትም፡፡

4. የማንኛውም የአልኮል መጠጥ የውጭ ማስታወቂያ ከልጆች መዋያ ማዕከል፣ ከትምህርት ቤት፣ ከህክምና ወይም ታሪካዊ ተቋም፣ ከሲኒማ ቤት፣ ከቲያትር ቤት ወይም ከስታዲየም በመቶ ሜትር ራዲየስ ውስጥ እንዲቀመጥ መደረግ የለበትም፡፡

## ክፍል ሰባት

## የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል እና የማስታወቂያ አሰራጭ ግዴታዎች

### 27. መረጃን ስለማረጋገጥ

1. ማንኛውም የማስታወቂያ ወኪል ወይም አሰራጭ፡-

ሀ) በማስታወቂያ እንዲሰራጭ በማስታወቂያ አስነጋሪ የቀረበለትን መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ፤ እና

ለ) ማስታወቂያው በቀረበው መልኩ ቢሠራጭ ሕግን የመተላለፍ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ይህንኑ እንዲያስተካክል ለማስታወቂያ አስነጋሪው የማሳወቅ፤ ግዴታ አለበት፡፡

2. ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ በማስታወቂያው ውስጥ ያካተተውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በማስታወቂያ ወኪሉ ወይም አሰራጩ እንዲያቀርብ የሚጠየቀውን ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

3. ማስታወቂያ አስነጋሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) ወይም (2) መሠረት የተጠየቀውን ለማሟላት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ካልቻለ የማስታወቂያ ወኪሉ ወይም አሰራጩ ከማስታወቂያ አስነጋሪው ጋር የገባውን ውል በመሰረዝ ለደረሰበት ኪሳራ ካሳ እንዲከፈለው መጠየቅ ይችላል፡፡

28.ሪከርድ ስለመያዝና መረጃ ስለመስጠት

1. ማናኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል ወይም የማስታወቂያ አሰራጭ የአንድን የተሰራጨ ማስታወቂያ ቅጅ ሪከርድ ቢያንስ ለስድስት ወራት ይዞ ማቆየት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል ወይም የማስታወቂያ አሰራጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተያዘውን የማስታወቂያ ሪኮርድ ቅጅ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ከዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ምክንያት እንዲያቀርብ ሲጠየቅ በራሱ ወጪ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

29.ማስታወቂያን በፍትሃዊነት ስለማሰራጨት

ማንኛውም ማስታወቂያ የሚያሰራጭ የመገናኛ ብዙሃን ከማስታወቂያ አስነጋሪዎች እና ከማስታወቂያ ወኪሎች የሚቀርቡለትን ማስታወቂያዎች ያለአድልዎና በፍትሃዊነት ማሰራጨት አለበት።

30.የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል እና የማስታወቂያ አሰራጭ ሃላፊነት

ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የዚህ አዋጅ ድንጋጌን በመተላለፍ የተሰራጨ ማስታወቂያ በማስታወቂያ አስነጋሪው፣ በማስታወቂያ ወኪሉ እና በማስታወቂያ አሰራጩ ፈቃድ እንደተሰራጨ ተቆጥሮ እንደሃላፊነታቸው መጠን በአንድነት ወይም በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

31.የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ማስታወቂያ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት አስተዋፆ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤
2. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የማስታወቂያ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ

መስፈርት እና የሥነ ምግባር መመሪያ ያወጣል፤

3. የውጭ ማስታወቂያን ሳይጨምር የዚህን አዋጅ ድንጋጌ በመተላለፍ የተሰራጨን ማንኛውንም ማስታወቂያ ይመረምራል፣ ያግዳል፤ የአፀፋ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያዛል፤
4. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተሰራጨ ማስታወቂያ ጥፋት በፈጸመ ሰው ላይ የወንጀል ክስ ለመመስረት የሚረዳን መረጃ አግባብ ላለው የመንግስት አካል ያስተላልፋል፤
5. የውጭ ማስታወቂያዎችን በሚመለከት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መከበራቸውን በማረጋገጥ ረገድ ለሚመለከታቸው የክልል አካላት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
6. የማስታወቂያ ሙያ የሚያድግበትን ስልትና ዘርፉ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠርበትን ሁኔታ ይቀይሳል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

32.<u>የሸማቾች ማኅበር</u>

አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም የሸማቾች ማኅበር፡-

1. ይህን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ ከባለሥልጣኑና ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር ይተባበራል፤
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌ በመተላለፍ በተሰራጨ ማስታወቂያ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን አባላቱን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ የመመስረት መብት ይኖረዋል፡፡

33.<u>ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>

1. ከውጭ ማስታወቂያ በስተቀር የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተሰራጨ ማንኛውም ማስታወቂያ መብቱ የተጣሰ ሰው የማስታወቂያው ስርጭት እንዲታገድለት ወይም የአፀፋ ማስታወቂያ እንዲወጣለት ማስታወቂያው ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ሥልጣን ላለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብን የሚከለክል አይሆንም፡፡

34.<u>ቅጣት</u>

1. በሌላ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፡-

ሀ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 5(1) እና (2) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም

ሰው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 60(1) መሠረት ይቀጣል፤

ለ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 5(3)፣ አንቀጽ 5(5)፣ አንቀጽ 6(2)፣ አንቀጽ 6(3)፣ አንቀጽ 6(4)፣ አንቀጽ 10፣ አንቀጽ 11፣ አንቀጽ 12(2)፣ አንቀጽ 13፣ አንቀጽ 15(1)፣ አንቀጽ 15(2)፣ አንቀጽ 15(3)፣ አንቀጽ 16፣ አንቀጽ 17፣ አንቀጽ 18፣ አንቀጽ 19፣ አንቀጽ 20፣ አንቀጽ 21፣ አንቀጽ 22፣ አንቀጽ 23፣ አንቀጽ 24፣ አንቀጽ 26(3)፣ አንቀጽ 27፣ አንቀጽ 28 ወይም አንቀጽ 29 በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር 10,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

ሐ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 6(1)፣ አንቀጽ 7፣ አንቀጽ 8፣ አንቀጽ 9፣ አንቀጽ 12(1)፣ አንቀጽ 14፣ አንቀጽ 15(4)፣ አንቀጽ 15(5)፣ አንቀጽ 26(1)፣ አንቀጽ 26(2) ወይም አንቀጽ 26(4) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር 20,000 በማያንስና ከብር 150,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

መ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 25(1) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር 30,000 በማያንስና ከብር 250,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው የገንዘብ መቀጮ በተጨማሪ ጥፋተኛ የሆነው ሰው ከሕገ ወጥ ማስታወቂያ ሥራው ያገኘው ገቢ ይወረሳል፡፡

**35. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ሕግ</u>**

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**36. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።
3. ክልሎች የውጭ ማስታወቂያን በሚመለከት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

37.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 21 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

## <u>አዋጅ ቁጥር 813/2006 ዓ.ም</u>

## <u>ስለ ንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ የወጣ አዋጅ</u>

የንግድ ሥራ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት ተገቢውን አሠራር ተከትሎ መካሄድ ያለበት በመሆኑ፤

የንግዱን ህብረተሰብ ከፀረ-ውድድር አና ተገቢ ካልሆኑ የገበያ ተግባራት፣ እንዲሁም ሸማቹን ከሚያሳስቱ የገበያ ሁኔታዎች የሚከላከልና ለነፃ ገበያ ውድድር አመቺነት ያለው ሥርዓት ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የንግድ እንቅስቃሴዎች ማደግን ተከትሎ የሸማቾችን ጤንነትና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን መስፋፋት ለመግታት እንዲቻልና ደህንነታቸውንና ለጤና ተስማሚ መሆናቸውን በዘላቂነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ተጠቃሚዎች ላወጡት ዋጋ ተመጣጣኝ የሆኑ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ስርዓት ተፈፃሚነትን ለማረጋገጥ የአስፈፃሚነት በተለይም የመመርመር፣ የመክሰስ እና የዳኝነት ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታዉጇል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "የንግድ ዕቃዎች" ማለት ከማናቸውም ዓይነት ገንዘብና ገንዘብነት ካላቸው ሰነዶች በስተቀር ማናቸውም የሚገዙ ወይም የሚሸጡ ወይም የሚከራዩ ወይም በሌላ ሁኔታ በሰዎች መካከል የንግድ ሥራ የሚከናወንባቸው የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎች ናቸው፤
2. "አገልግሎት" ማለት ደመወዝ ወይም የቀን ሙያተኛ ክፍያ ያልሆነ ገቢ የሚያስገኝ ማንኛውም አገልግሎት የመስጠት ንግድ ሥራ ነው፤
3. "መሠረታዊ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት" ማለት በገበያ ላይ እጥረት በመፈጠሩ ምክንያት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ ሊያስከትል የሚችል ከሸማቾች የየዕለት ፍላጐት ጋር የተገናኘ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው፤
4. "ሸማች" ማለት ለማምረት ሥራ ወይም መልሶ ለመሸጥ ሳይሆን ዋጋዉን ራሱ ወይም ሌላ ሰዉ የሚከፍልለት ሆኖ ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ ፍጆታ የሚሆን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚገዛ የተፈጥሮ ሰው ነው፤
5. "ነጋዴ" ማለት የሙያ ሥራው አድርጎ ጥቅም ለማግኘት ሲል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሠራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የንግድ ሥራ ነው ተብሎ በህግ የሚወሰነውን ሥራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፤
6. "የንግድ ሥራ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) በተተረጎመው መሠረት ነጋዴ የሚሠራው ሥራ ነው፤

7. “የማምረት ሥራ” ማለት በኢንዱስትሪ የሚከናወን የመቀመም፣ የመለወጥ፣ የመገጣጠምና የማሰናዳት ሥራን ይጨምራል፤
8. “ተፈላጊ ግብዓት” ማለት ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለደንበኞቻቸው በማቅረብ ረገድ ለተወዳዳሪዎች በጣም አስፈላጊ የሆነና በቀላሉ ወይም እንደልብ ሊገኝ የማይችል መሠረተ ልማት ወይም ሀብት ነው፤
9. “ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ” ማለት ንግድን የሚመለከቱ ህግ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ማንኛዉም ድርጊት ነው፤
10. “የጅምላ ሻጭ” ማለት የንግድ ዕቃዎችን ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ሲሆን አምራች ወይም አስመጪ የንግድ ዕቃዎችን ለቸርቻሪ ወይም ለጅምላ ሻጭ ሲሸጥ በጅምላ ንግድ ውስጥ እንደተሳተፈ ይቆጠራል፤
11. “የችርቻሮ ሻጭ” ማለት የንግድ ዕቃዎችን በጅምላ ሻጭ ወይም ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ሲሆን ጅምላ ሻጭ ወይም አምራች ወይም አስመጪ የንግድ ዕቃዎችን ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ ሲሸጥ የችርቻሮ ንግድ ውስጥ እንደተሳተፈ ይቆጠራል፤
12. “ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
13. “ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ” ማለት ከማንኛውም የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሽያጭ የተገኘ ዉሳኔ ከሚሰጥበት ዓመት በፊት የነበረ የመጨረሻ አመት አጠቃላይ የሽያጭ ገቢ ሲሆን፤ የንግድ ድርጅቱ አዲስ ከሆነ እና የስራ ዘመኑ ከአንድ የበጀት አመት በታች ከሆነ በሰራባቸው ጊዜያት የተገኘው አጠቃላይ ገቢ ነው፤
14. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤
15. “ቢሮ” ማለት የክልል ወይም የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል ነው፤
16. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
17. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀዉ የሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>ዓላማዎች</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል

1. የንግዱን ህብረተሰብ ከፀረ-ውድድርና ተገቢ ካልሆኑ የገበያ ተግባራት እንዲሁም ሸማቹን ከሚያሳስቱ የገበያ ሁኔታዎች የሚከላከልና ለነፃ ገበያ ዉድድር አመቺነት ያለው ስርዓት የማስፈን፤
2. ሸማቾች ለደህንነታቸውና ለጤናቸው ተስማሚ የሆኑና ላወጡት ዋጋ ተመጣጣኝ የሆኑ የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸቱን ማረጋገጥ፤ እና
3. የኢኮኖሚ ልማትን ማፋጠን፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ በሚካሄድ ወይም ውጤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፅኖ ባለው ማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎት ግብይት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የሚኒስትሮች ምክር ቤት የዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የማይሆኑባቸውን ልማትን ለማሳደግ ይጠቅማሉ የሚባሉ የንግድ ስራዎችን በደንብ ለመወሰን ይችላል፡፡
3. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሌሎች ህጎች መሠረት የሚካሄዱ የቁጥጥር ሥራዎችን እና የሚወስዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን አያስቀሩም፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ፀረ-ውድድር የሆኑ የንግድ አሰራሮችን</u>
## <u>ስለመከላከልና ውህደትን ስለመቆጣጠር</u>

### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
### <u>ፀረ-ውድድር የሆኑ የንግድ አሰራሮችን ስለመከላከል</u>

5. <u>በበላይነት የተያዘ ገበያን አለአግባብ ስለመጠቀም</u>

1. ማንኛውም ነጋዴ በግሉ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በበላይነት የያዘውን ገበያ በግልፅም ሆነ በስውር አለአግባብ በመጠቀም የንግድ ሥራ ማካሄድ አይችልም።
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም የሚከተሉት በበላይነት የተያዘን ገበያ አለአግባብ የመጠቀም ድርጊት ተደርገው ይቆጠራሉ፡-

ሀ) ምርትን መገደብ፣ የንግድ ዕቃዎችን ማከማቸት ወይም የንግድ ዕቃዎች በመደበኛው የንግድ መሥመር እንዳይሸጡ ለማድረግ መደበቅ፣ ማገድ ወይም መያዝ፤

ለ) ከማምረቻ ዋጋ በታች በመሸጥ፣ የተወዳዳሪን ወጪ በማሳደግ ወይም ግብዓቶችን ወይም የስርጭት መስመሮችን ቀድሞ በመቆጣጠር ተወዳዳሪ ላይ ያነጣጠረ ጎጂ ድርጊት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መፈፀም፤

ሐ) በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ፍትሐዊ ያልሆነ የመሸጫ ዋጋ ወይም የመግዣ ዋጋ መወሰን፤

መ) ግልፅና ወቅታዊ የሆነ የገበያ አሠራርን በሚቃረን መልኩ ገበያን በበላይነት የያዘው ነጋዴ በልማድ የሚያደርገውን ወይም ሊያደርገው የሚችለውን እንደማይችለው ሆኖ ለመደራደር ፈቃደኛ አለመሆን፤

ሠ) አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሳይኖር፣ ገበያን በበላይነት በያዘ ነጋዴ ቁጥጥር ሥር ያለን ተፈላጊ ግብዓት ተወዳዳሪ ለሆነ ወይም ሊሆን ለሚችል ነጋዴ መከልከል፤

ረ) አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሳይኖር፣ በዕቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦትና ግዥ ላይ በደንበኞች መካከል በዋጋና በሌሎች ሁኔታዎች ልዩነት መፍጠር፤

ሰ) አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሳይኖር የአንድን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት፣ ሌላ ተወዳዳሪ የሆነን ወይም ያልሆነን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ከመቀበል ጋር እንዲገናኝ ማድረግ ወይም ሌላ ተወዳዳሪ የሆነውን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት በማከፋፈል ወይም በማምረት ላይ ገደብ መጣል፣ ወይም በገዥው ከሚፈለገው የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር ግንኙነት ከሌለው የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዢ ጋር እንዲገናኝ ማድረግ፤

ሸ) አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሳይኖር የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን አቅርቦት በተመለከተ የት ወይም ለማን ወይም በምን ሁኔታ ወይም መጠን ወይም በምን ያህል ዋጋ እንደገና መሸጥ ወይም ወደ ውጭ መላክ እንዳለበት ገደቦችን መጣል፤

ቀ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የሚዘረዘሩ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን መፈጸም፡፡

3. የሚከተሉትን ለማሳካት የሚፈጸሙ ለዚሀ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሠ) (ረ) (ሰ) እና (ሸ) ድንጋጌዎች አፈጻጸም ሲባል አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ተደርገው ይወሰዳሉ፡-
   ሀ) የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ጥራትና ደህንነት መጠበቅ
   ለ) ሌላዉ ተወዳዳሪ ከሰጠዉ ዋጋ ወይም ጥቅም ጋር መስተካከል
   ሐ) ብቁና ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት
   መ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የሚዘረዘሩ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች፡፡

6. <u>የበላይነትን ስለማረጋገጥ</u>
   1. ማንኛዉም ነጋዴ በግሉ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በአንድ የገበያ ክልል ዉስጥ ዋጋን ወይም ሌሎች የንግድ ድርድር ሁኔታዎችን መቆጣጠር ወይም ዉድድርን የማጥፋት ወይም በግልጽ የመገደብ የተረጋገጠ አቅም ያለዉ ሆኖ ከተገኘ ገበያዉን በበላይነት ይዟል ይባላል፡፡
   2. አንድ ገበያ በበላይነት መያዙን ለማረጋገጥ ነጋዴው በገበያው ውስጥ ያለው ድርሻ ወይም ሌሎች ወደ ገበያው እንዳይገቡ ለመከልከል ያለው አቅም ወይም አግባብነት ያላቸው ሌሎች መመዘኛዎች ወይም የመመዘኛዎቹ ጥምረት ግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው።
   3. በአንድ ገበያ ውስጥ የበላይነት አለ ለማለት የሚቻለው የተባለው ገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉ ወይም የሚተካኩ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን የያዘ ሲሆን ነው።
   4. የዚሁ ገበያ መልክዓ ምድራዊ ክልል የውድድር ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ አንድ ዓይነት የሆኑበት እና በአጐራባች ገበያዎች ከሚታዩት የውድድር ሁኔታዎች የሚለዩበት ነው።
   5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአኃዝ የሚገለጽ የገበያ የበላይነትን መጠን በደንብ ሊወስን ይችላል፡፡

7. <u>ፀረ-ዉድድር ስምምነቶች፣ በህብረት የሚያዙ አቋሞችና ውሳኔዎች</u>
   1. ወደጐን ግንኙነት ባላቸው ነጋዴዎች መካከል የተደረገ ስምምነት፣ በህብረት የተያዘ አቋም ወይም የተላለፈ ውሳኔ፡-

ሀ) የንግድ ውድድርን የሚያግድ ወይም በጉልህ ደረጃ የሚቀንስ ከሆነና ስምምነቱ፣ የተያዘው አቋም ወይም የተላለፈው ውሳኔ የሚያስገኘው የቴክኖሎጂ፣ የአሠራር ቅልጥፍና ወይም ሌላ ውድድርን የሚያጠናክር ጠቀሜታ ከሚያስክትለው ጎጂ ተፅዕኖ የሚያመዝን መሆኑን ማንኛውም ተሳታፊ ወገን ሊያስረዳ ካልቻለ፤ ወይም

ለ) በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የመግዣ ወይም የመሸጫ ዋጋ ወይም ማንኛውንም ሌላ የንግድ ገደብ መወሰን፣ ተመሳጥሮ መጫረትን ወይም ደንበኞችን፣ አቅራቢዎችን፣ ክልልን ወይም የምርትና የአገልግሎት ዓይነቶችን በኮታ በመመደብ የገበያ ድርሻ መከፋፈልን የሚመለከት ከሆነ፤

የተከለከለ ነው፡፡

2. ግንኙነታቸው ከላይ ወደታች በሆነ ነጋዴዎች መካከል የተደረገ ስምምነት፡-

ሀ) የንግድ ውድድርን የሚያግድ ወይም በጉልህ ደረጃ የሚቀንስ ከሆነና ስምምነቱ የሚያስገኘው የቴክኖሎጂ፣ የአሠራር ቅልጥፍና ወይም ሌላ ውድድርን የሚያጠና ክር ጠቀሜታ ከሚያስከትለው ጎጂ ተፅዕኖ የሚያመዝን መሆኑን ማንኛውም ተሳታፊ ወገን ሊያስረዳ ካልቻለ፤ ወይም

ለ) ዝቅተኛ የመልሶ መሸጫ ዋጋን የሚወስን ከሆነ፤

የተከለከለ ነው።

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) አፈጻጸም ሲባል፡-

ሀ) ስምምነት የሚለው ቃል በሕግ ተፈፃሚነት ቢኖረውም ባይኖረውም መግባባትን፣ በጽሑፍ ወይም በቃል የተፈፀመ ውልን እና የአሰራር ሥርዓትን ይጨምራል፤

ለ) በህብረት የተያዘ አቋም ማለት ስምምነት በማይመስል ሁኔታ በነጋዴዎች መካከል በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በየግል የሚፈፀምን ተግባር ለመተካት የሚፈጸም የትብብር ድርጊት ነው፤

ሐ) የጐንዮሽ ግንኙነት የሚባለው በአንድ ገበያ ውስጥ ባሉ ተወዳዳሪ ነጋዴዎች መካከል የሚኖር ግንኙነት ሲሆን፣ ከላይ ወደታች የሆነ ግንኙነት የሚባለው ደግሞ ነጋዴዎች ከደንበኞች ወይም ከአቅራቢዎች ወይም ከሁለቱም የሚኖራቸው ግንኙነት ነው።

## 8. ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር

1. ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ሥራ ሂደት ውስጥ ማንኛውም ሀቀኛ ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም አታላይነት ያለበት እና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ድርጊት መፈፀም አይችልም።
2. የሚከተሉት ድርጊቶች ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ውድድር ተግባራት ሆነው ይቆጠራሉ፡-

ሀ) በሌላው ነጋዴ ወይም በነጋዴው ተግባራት በተለይም ነጋዴው ከሚያቀርበው የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊት፤

ለ) የመረጃው ባለቤት ከሆነው ነጋዴ ፈቃድ ውጪ ከሀቀኛ የንግድ አሰራር ተፃራሪ በሆነ ሁኔታ የሌላውን መረጃ የማውጣት፣ የመያዝ ወይም የመጠቀም ማናቸውም ድርጊት፤

ሐ) የሌላውን ነጋዴ ወይም የነጋዴውን ተግባራት በተለይም ነጋዴው ከሚያቀርበው የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ታማኝነትን የሚያሳጣ ወይም ሊያሳጣ የሚችል ማናቸውም ሀሰት የሆነ ወይም ማረጋገጫ የሌለው አገላለጽ፤

መ) በንግድ ማስተዋወቅ ሥራ ሂደት የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሀሰት ወይም በተዛባ ሁኔታ ማነፃፀር፤

ሠ) ከንግድ ዕቃዎች ወይም ከአገልግሎቶች ዋጋ ወይም ባህሪ ወይም አመራረት ወይም ከማምረቻ ቦታ ወይም ይዘት ወይም ከአጠቃቀም ምቹነት ወይም ጥራት ጋር በተገናኘ ምንጩ ያልታወቀውን ጨምሮ ለሸማቾች ወይም ለተጠቃሚዎች ሀሰተኛ ወይም የተዛባ መረጃ ማሰራጨት፤

ረ) ሚስጥራዊ የሆኑ የሌላ ነጋዴ የንግድ መረጃዎችን በቀድሞ ወይም በሥራ ላይ ባሉ ሠራተኞቹ አማካኝነት ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር ወይም መረጃዎቹን በማግኘት የነጋዴውን ደንበኞች ለማስኮብለል ወይም ሌላ ተወዳዳሪነቱን ለሚቀንስ ዓላማ መጠቀም፤

ሰ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የሚዘረዘሩ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን መፈጸም፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ውህደትን ስለመቆጣጠር

9. **ክልከላ**

1. ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ውድድር ላይ ጉልህ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል ስምምነት ወይም ቅንብር ውስጥ መሳተፍ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም የዉህደት ስምምነት ወይም ቅንብር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም።
3. ለዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አፈጻጸም፡-

   ሀ) ግላዊ ተቋምነታቸውን ይዘው ይኖሩ የነበሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የንግድ ማህበራት ሲቀላቀሉ ወይም አንድ ዓላማ ያለው የንግድ ሥራ ለማከናወን ሁሉንም ወይም ከፊሉን ሀብታቸውን ሲያቀላቅሉ፤ ወይም

   ለ) በአንድ ሰው ወይም በብዙ ሰዎች በግዢ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሁኔታ የንግድ ማህበር አክስዮኖች፣ ሴኩሪቲዎች ወይም ንብረቶች የራስ ሲደረጉ ወይም የሌላ ሰው የንግድ መደብርን አመራር መቆጣጠር ሲቻል፤ የውህደት ድርጊት እንደተፈጸመ ይቆጠራል።

10. **የውህደት ማስታወቂያ**

1. ማንኛውም ነጋዴ በውህደት ስምምነት ወይም ቅንብር ለመሳተፍ ሲያቅድ የታቀደውን ውህደት በዝርዝር በመግለጽ ለባለሥልጣኑ የውህደት ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የውህደት ማስታወቂያ ሲቀርብለት የታቀደው ውህደት በንግድ ውድድር ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ ስለመኖሩ ያጣራል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የታቀደው ውህደት ሊያስክትል የሚችለውን ውጤት በማጣራት ሂደት

   ሀ) እንደአስፈላጊነቱ የውህደቱ ተሳታፊ ወገኖች ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነድ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያቀርቡ መጠየቀ፤ እና

   ለ) ውህደቱ ተፅዕኖ ሊያስክትልበት የሚችል ማንኛውም ነጋዴ ተቃውሞ ካለው ይህንኑ ተቃውሞ ማስታወቂያው በታተመ በ15 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ እንዲያቀርብ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ በሚታተም ማስታወቂያ ሊጋብዝ፤ ይችላል፡፡

**11.ውህደትን ስለመፍቀድ**

1. ባለሥልጣኑ የታቀደውን ውህደት ካጣራ በኋላ፡-
   - ሀ) ውህደቱ በንግድ ውድድር ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደማይኖረው ካመነበት ውህደቱን ይፈቅዳል፤
   - ለ) ውህደቱ በንግድ ውድድር ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ካመነበት ውህደቱን ይከለክላል፤ ወይም
   - ሐ) ውህደቱ በንግድ ውድድር ላይ ሊያስከትል የሚችለው የጎላ አሉታዊ ተፅኖ የተወሰኑ ተያያዥ ግዴታዎችን አክብሮ በመፈጸም ሊወገድ እንደሚችል ካመነበት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ተያያዥ ግዴታዎች በማከል ውህደቱን ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ቢኖርም ውህደቱ በንግድ ውድድር ላይ ከሚያስከትለው የጎላ አሉታዊ ተፅኖ ይልቅ ከቴክኖሎጂ፣ ከአሰራር ቅልጥፍና ወይም ከሌላ ተወዳዳሪነትን ከሚያጠናክር ጠቀሜታ አንፃር የሚያስገኘው ጥቅም የሚያመዝንና ይህም ጠቀሜታ ውህደቱ ከተከለከለ በሌላ መንገድ ሊገኝ የማይችል ሲሆን ባለሥልጣኑ ውህደቱን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**12.ውህደትን ስለመመዝገብ**

የሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት አንድን ውህደት በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ እንዲቀርብለት መጠየቅ አለበት፡፡

**13. የውህደት ፈቃድን ስለመሰረዝ**

1. ባለሥልጣኑ የውህደት ፈቃድን በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰርዝ ይችላል፡-
   - ሀ) የውህደት ፈቃዱ የተገኘው በቀረበ የተሳሳተ ወይም የተጭበረበረ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሲሆን፤ ወይም
   - ለ) ውህደቱ የተፈቀደው በቅድመ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ሲሆንና ቅድመ ሁኔታዎቹ ሳይከበሩ ሲቀሩ፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የውህደት ፈቃድን ሲሰርዝ የውህደቱ የንግድ ምዝገባም እንዲሰረዝ ለሚመለከተው መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ያሳውቀዋል።

## ክፍል ሦስት

## ስለሸማቾች ጥበቃ እና ስለንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስርጭት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የሸማቾች ጥበቃ

14. **የሸማች መብቶች**

ማንኛውም ሸማች የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. ስለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራትና አይነት በቂና ትክክለኛ መረጃ ወይም መግለጫ የማግኘት፤
2. ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን አማርጦ የመግዛት፤
3. የዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ጥራት ወይም አማራጮችን በማየቱ ወይም የዋጋ ድርድር በማድረጉ ምክንያት እንዲገዛ ያለመገደድ፤
4. በማንኛውም ነጋዴ በትህትናና በአክብሮት የመስተናገድ እንዲሁም በነጋዴዉ ከሚደርስበት የስድብ፤ የዛቻ፤ የማስፈራራት እና የስም ማጥፋት ተግባር የመጠበቅ፤ እና
5. የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በመግዛቱ ወይም በመጠቀሙ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት የንግድ ዕቃዎቹን ወይም አገልግሎቶቹን ከማቅረብ ጋር ተያይዞ በአምራችነት፣ በአስመጪነት፣ በጅምላ ፣በችርቻሮ ሻጭነት ወይም በሌላ ማንኛውም ሁኔታ በአቅርቦቱ የተሳተፉ ሰዎች በተናጠል ወይም በአንድነት ካሣ እንዲከፍሉት ወይም ከዚህ ጋር ተያያዥ መብቶችን የመጠየቅ::

15. **የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ ስለማመልከት**

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ዕቃዎቹንና የአገልግሎቶቹን የዋጋ ዝርዝር በንግድ ቤቱ በግልጽ በሚታይ ቦታ ማመልከት ወይም በንግድ ዕቃዎቹ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡
2. የዕቃዉ ወይም የአገልግሎቱ ዋጋ የታክስና ሌሎች ሕጋዊ ክፍያዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

16. **ስለንግድ ዕቃዎች መግለጫ**

1. ማንኛውም ነጋዴ በሚሸጣቸው የንግድ ዕቃዎች ላይ መግለጫ መለጠፍ ወይም በተለየ ወረቀት ላይ ጽፎ ለሸማቹ መስጠት አለበት፡፡

2. በንግድ ዕቃዎች ላይ የሚለጠፍ መግለጫ እንደአግባቡ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የሚያመለክት መሆን አለበት፡-

ሀ) የንግድ ዕቃውን ስም፤

ለ) የንግድ ዕቃው የተሰራበትን ወይም የመጣበትን አገር፤

ሐ) የንግድ ዕቃውን ጠቅላላና የተጣራ ክብደት፤ ብዛት፤

መ) የንግድ ዕቃውን ጥራት፤

ሠ) የንግድ ዕቃው ከምን እንደተመረተ የሚያሳይ ዝርዝር፤

ረ) የንግድ ዕቃውን የቴክኒክ ዝርዝሮች፣ የአሠራር ወይም የአጠቃቀም ዘዴ፤

ሰ) በንግድ ዕቃው አጠቃቀም ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች፤

ሸ) ነጋዴው ስለንግድ ዕቃው አገልግሎት ለገዢው የሚሰጠውን ዋስትና፤

ቀ) የአምራቹን፣ የአሻጊውን እና የአስመጪውን ስምና አድራሻ፤

በ) የንግድ ዕቃው አገልግሎት መስጠት የሚያበቃበትን ጊዜ፤

ተ) የንግድ ዕቃው የተመረተበትን ቀን፤

ቸ) በኢትዮጵያ ደረጃዎች የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን፤ እና

ኀ) የህብረተሰቡን ጥቅም ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ በሕዝብ ማስታወቂያ የሚያወጣቸውን ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

3. በንግድ ዕቃዎች ላይ የሚለጠፍ መግለጫ በቀላሉ የማይላቀቅ ሆኖ በራሱ በዕቃው ላይ ወይም በመያዣው ላይ መለጠፍ ወይም መታተም የሚገባው ሲሆን ቢያንስ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ መፃፍ አለበት፡፡

17. <u>ደረሰኞችን ስለመስጠትና ቀሪዎችን ስለመያዝ</u>

1. ማንኛውም ነጋዴ ለሸጠው ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሸማቹ ወዲያውኑ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ነጋዴው ለሸጣቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የሰጣቸውን የደረሰኝ ቀሪዎች ወይም መልሶ ለመሸጥ ለገዛቸው የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የተቀበላቸውን ደረሰኞች ለ10 ዓመታት ይዞ ማቆየት አለበት፡፡

18. <u>ራስን ስለመግለጽ</u>

1. ማንኛዉም ነጋዴ የንግድ ስሙን በግልጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ አለበት፡፡

2. ማንኛውም ነጋዴ ከሚሸጠው የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር በተያያዘ ሸማቹ በሚያቀርብለት ጥያቄ መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ ራሱን መግለፅና ሸማቹ የሚፈልገውን መረጃ እንዲወስድ መፍቀድ አለበት፡፡

19.<u>ስለንግድ ማስታወቂያ</u>

በማንኛውም መንገድ የሚገልጹ ስለንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚወጡ የንግድ ማስታወቂያዎች በማንኛውም ሁኔታ በተለይም የሚከተሉትን በተመለከተ ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መሆን የለባቸውም፡-

1. የዕቃውን ባህሪ፣ ውሁድ እና ብዛት፤
2. የዕቃውን ምንጭ፣ ክብደት፣ መጠን፣ የአመራረት ዘዴ፣ የማምረቻ ቀን፣ አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን እና ስለአጠቃቀሙ፤
3. የዕቃውን አምራች ወይም የአገልግሎቱን አቅራቢ፤
4. አገልግሎቱ የሚሰጥበትን ቦታ፣ መሠረታዊ ባህሪ፣ የአገልግሎቱን ጥቅም እና ስለአገልግሎቱ አጠቃቀም፤
5. የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ የግዢ ሁኔታ፣ ከግዢ በኋላ ስለሚሰጥ አገልግሎት፣ ዋስትና ዋጋና የክፍያ ሁኔታ፤
6. የጥራት ምልክቶችን፤
7. የንግድ ምልክትን እና አርማን፤ እና
8. ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን በመጠቀም የሚጠበቅ ውጤትን፡፡

20.<u>በንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ስለሚገኙ ጉድለቶች</u>

1. ማንኛውም ሸማች በገዛው የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ላይ ያገኛቸውን ጉድለቶችና ጉድለቶቹ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት ጉዳት ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው ቢሮ ማሳወቅ ይችላል፡፡
2. ለሸማቹ የበለጠ የሚጠቅሙ ዋስትናዎች ወይም የህግ ወይም የውል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ሸማቹ፡-
   ሀ) ጉድለት ያለበት የንግድ ዕቃን የሚመለከት ሲሆን የንግድ ዕቃው እንዲለወጥለት ወይም ዋጋው እንዲመለስለት፤ ወይም
   ለ) ጉድለት ያለበት አገልግሎት ሲሆን አገልግሎቱ በድጋሚ ያለክፍያ እንዲሰጠው ወይም የአገልግሎት ክፍያው እንዲመለስለት፣ ግዥው በተፈጸመ በ15 ቀናት ውስጥ ሻጩን መጠየቅ ይችላል፡፡

3. ሸማቹ ጉድለት ያለበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት በመጠቀሙ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ማንኛውም ጉዳት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ካሣ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡

21.<u>መብትን የሚያስቀሩ የውል ግዴታዎች</u>

ሸማቹ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን መብቶች የሚያስቀሩ በሸማችና በነጋዴ መካከል የሚደረጉ የውል ግዴታዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

22.<u>የተከለከሉ ድርጊቶች</u>

ለማንኛውም ነጋዴ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፦

1. የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስላላቸው ጥራት፣ መጠን፣ ብዛት፣ ተቀባይነት፣ ምንጭ፣ ባህሪ፣ ውሁድ ወይም ጥቅም የተሳሳተ መረጃ መስጠት፤
2. የንግድ ዕቃዎችን ሞዴል፣ አዲስ የተሠሩ፣ የተለወጡ፣ እንደገና እንደ አዲስ የተሠሩ ወይም ያገለገሉ ስለመሆናቸው ወይም በአምራቹ እንዲሰበሰቡ የተባሉ ስለመሆናቸው በትክክል አለመግለጽ፤
3. የሌላውን ነጋዴ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በአሳሳች ሁኔታ መግለጽ፤
4. የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን በማስታወቂያ እንደተነገረላቸው አለመሸጥ ወይም ማስታወቂያው የመጠን ውሱንነት መኖሩን ካልገለፀ በስተቀር ሸማቾች በሚፈልጉት መጠን ልክ አለመሸጥ፤
5. ስለዋጋ ቅናሽ ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ማስተላለፍ፤
6. አንድ ሸማች አንድን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት በመግዛቱ ወይም የገንዘብ መዋጮ በማድረጉ እና በሸማቹ አሻሻጭነት ከእሱ ቀጥሎ ሌሎች ሸማቾች የንግድ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን የሚገዙ ወይም የገንዘብ መዋጮ የሚያደርጉ ከሆነ ወይም በሽያጭ ስልቱ ውስጥ የሚገቡ ከሆነ በሸማቾቹ ቁጥር ልክ የገንዘብ ወይም የአይነት ጥቅም እንደሚያገኝ የሚገልጽ ፒራሚዳዊ የሽያጭ ስልት ተግባራዊ ማድረግ ወይም ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር፤
7. ከንግድ ዕቃ ወይም ከአገልግሎት ሽያጭ ጋር በተያያዘ የተገባ የዋስትና ግዴታን አለመወጣት፤
8. የንግድ ዕቃ የሚያስፈልገው ጥገና ወይም የሚተኩ ክፍሎቹ እንደሚያስፈልጉት አድርጎ ማቅረብ፤

9. ማንኛውም አገልግሎት የመስጠት ሥራን በንግድ ሥራው ከሚታወቀው ደረጃ በታች ወይም ባልተሟላ ሁኔታ መስጠት፤
10. ለሰው ጤናና ደህንነት አደገኛ የሆነ፣ ምንጩ ያልታወቀ፣ የጥራት ደረጃው የወረደ፣ የተመረዘ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈ ወይም ከባዕድ ነገሮች ጋር የተደባለቀ የንግድ ዕቃን ለሽያጭ ማቅረብ ወይም መሸጥ፤
11. በንግድ ዕቃ ወይም የአገልግሎት ግብይት ማንኛውንም የሚጭበረበር ወይም የማደናገር ተግባር መፈፀም፤
12. የሸማቹን መብት ለመጠበቅ ሲባል ካልሆነ በስተቀር የንግድ ዕቃን ወይም አገልግሎትን አልሸጥም ማለት፤
13. የደረጃዎች ማህተም መጠቀም የሚያስፈልጋቸው የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ያለደረጃ ማህተም ለሽያጭ ማቅረብ መሸጥ፤
14. የንግድ ዕቃን ወይም አገልግሎትን በንግድ ዕቃው ላይ ወይም በንግድ መደብሩ ውስጥ ከተለጠፈው ዋጋ አስበልጦ መሸጥ፤
15. የንግድ ዕቃዎች የተሰሩበትን አገር አሳስቶ መግለጽ፤
16. በሸማቾች መካከል ተገቢ ያልሆነ አድልዎ መፈጸም፤
17. አንድን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለመሸጥ ሸማቹ ያልፈለገውን ሌላ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት አብሮ እንዲገዛ ማስገደድ፤
18. ህገ ወጥ በሆነ ማንኛውም የመለኪያ መሳሪያ መጠቀም፤

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስርጭት

### 23. የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ስርጭት ስለመቆጣጠር

1. ሚኒስቴሩ እና ቢሮዎች የጤናና የደህንነት ደረጃዎችን ያላሟሉ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሽያጭንና ስርጭትን አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር በመሆን ያግዳሉ፡፡
2. ሚኒስቴሩ በአገር ውስጥ በሚመረቱ ወይም ከውጭ በሚመጡ የንግድ ዕቃዎች ላይ አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር በመሆን የጥራት ፍተሻ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ሚኒስቴሩ እና ቢሮዎች በነጋዴዎች የሚፈጸም የንግድ ዕቃዎች ክምችት ወይም የመደበቅ ተግባር ላይ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡
4. ሚኒስቴሩ ወይም ቢሮዎች የተበላሹና ለሰው ጤናና ደህንነት አደገኛ የሆኑ የንግድ ዕቃዎችን አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር በመመካከር እንዲወገዱ ያደርጋሉ፡፡

5. ሚኒስቴሩና ቢሮዎች በባለሥልጣኑ የሥልጣን ክልል ሥር ከሚወድቁት በስተቀር የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች የማስፈፀም ሥልጣን ይኖራቸዋል።

24.<u>የንግድ ዕቃዎችን ስለማከማቸት እና ስለመደበቅ</u>

1. በገበያ ላይ እጥረት ያለበት መሆኑ በሚኒስቴሩ በወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸ የንግድ ዕቃን፡-
   ሀ) ለማንኛውም ነጋዴ ከመደበኛ የግብይት አሠራር ዉጪ፤ ወይም
   ለ) ነጋዴ ላልሆነ ሰው ለግል ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚውል መጠን በላይ ማከማቸት ወይም መደበቅ ክልክል ነው፡፡
2. ማንኛውም የንግድ ዕቃ ከመደበኛ የግብይት አሰራር ውጪ ተከማችቷል ወይም ተደብቋል የሚባለው ግምቱ ከነጋዴው ካፒታል ሃያ አምስት በመቶ የማያንስ ሲሆንና የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡-
   ሀ) ከውጭ አገር የመጣ የንግድ ዕቃ ሲሆን አስመጪው ራሱ ለቀጣይ የምርት ሂደት በጥሬ ዕቃነት ወይም በግብዓትነት የሚጠቀምበት ካልሆነ በስተቀር የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተጠናቀቀለት በኋላ በሦስት ወራት ውስጥ ለሽያጭ ካልቀረበ፤
   ለ) በአገር ውስጥ የተመረተ የንግድ ዕቃ ሲሆን አምራቹ ራሱ ለቀጣይ የምርት ሂደት በጥሬ ዕቃነት ወይም በግብዓትነት የሚጠቀምበት ካልሆነ በስተቀር ከተመረተበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወራት ውስጥ ለሽያጭ ካልቀረበ፤ ወይም
   ሐ) በጅምላ ሻጭ ወይም በችርቻሮ ሻጭ የተገዛ የንግድ ዕቃ ሲሆን የጅምላ ሻጩ ወይም የችርቻሮ ሻጩ የንግድ ዕቃውን ከገዛበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለሽያጭ ካልቀረበ ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (የተመለከቱት መስፈርቶች ባይሟሉም በማናቸውም ማጓጓዣ ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጪ ሲጓጓዝ የተገኘ የንግድ እቃ እንደ ተከማቸ ወይም እንደ ተደበቀ ይቆጠራል።
4. ለማንኛውም ነጋዴ ላልሆነ ሰው በገበያ ላይ እጥረት ያለበት መሆኑ በሚኒስቴሩ በወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸ የንግድ ዕቃን ለግል ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚውል በላይ በሆነ መጠን ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጪ ማጓጓዝ ወይም እንዲጓጓዝ ማድረግ ክልክል ነው፡፡

5. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የአንድ የንግድ ዕቃ ተቀባይነት የሚኖረው የግል ወይም የቤተሰብ ፍጆታ መጠን እና የተፈቀደ የቆይታ ጊዜ በሚኒስቴሩ በሚወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ ይወሰናል፡፡
6. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በአርሶ አደር የሚያዝ የግብርና ምርት ክምችትን በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

25.<u>*መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ስለመወሰን*</u>

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ያደረገውን ጥናት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማስፈቀድ ዝርዝራቸውንና ዋጋዎቻቸውን በሕዝብ ማስታወቂያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ዋጋው በመንግሥት ተወስኖ በሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸን መሠረታዊ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ከተወሰነው ዋጋ በላይ መሸጥ ወይም ለመሸጥ መሞከር የተከለከለ ነው፡፡

26.<u>*ስለመሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች ስርጭት*</u>

ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ዝርዝራቸውና ዋጋዎቻቸው በሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጹት መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ስለሚሰራጩበት፣ ስለሚሸጡበትና ከቦታ ወደ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ለመወሰንና እንደ አስፈላጊነቱም ዕቃዎቹ ባለቁ ጊዜ እንዲተኩ ነጋዴውን ለማዘዝ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን፣ ስለፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳዷራዊ ፍርድ ቤት እና ስለክልሎች የሸማቾች ጥበቃ ዳኝነት አካላትና ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶች</u>

27.<u>*የባለሥልጣኑ መቋቋም*</u>

1. የንግድ ውድድር እና ጥበቃ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ ባለሥልጣን እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፤

3. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሰረት ይተዳደራል፡፡

## 28. የባለሥልጣኑ አደረጃጀት

ባለሥልጣኑ፡-

1. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንዳስፈላጊነቱ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35(1) መሠረት የሚሾሙ የዳኝነት ችሎት ዳኞች፣ እና
3. በዚህ አዋጅ መሠረት ምርመራ የሚያካሂዱና ክስ የሚመሠርቱ መርማሪዎች እና ዐቃቤ ሕጎች፤[55]
4. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

## 29. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## 30. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የገበያን ግልፅነት ለማሳደግ ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤
2. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አፈፃፀም በሕዝብ ዘንድ በሚገባ እንዲታወቁ ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤
3. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የዉህደት ድርጊት ማስታወቂያዎችን ይቀበላል ውሳኔ ይሰጣል፤
4. ከንግድ ውድድርና ከሸማቾች ጥበቃ ጋር በተገናኘ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፤
5. በመንግሥት ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከለከሉ የንግድ ዕቃዎችን እየተከታተለ ለፍጆታና ለሽያጭ እንዳይውሉ በየጊዜው ለሸማቾች ያሳውቃል፤
6. የሸማቾችን ግንዛቤ ለማዳበር የተለያዩ የትምህርትና የሥልጠና መድረኮችን ያደራጃል፣ ትምህርትና ሥልጠናም ይሰጣል፤

[55] በ22/62(2008) አ.943 አንቀፅ 22(6) የአቃቤ ህግነት ስልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የተላለፈ በመሆኑ በግልፅ ሳይነገር ተሻረ፡፡

7. ከጤናና ደህንነት መስፈርቶች ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጣጣሙ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ማስታወቂያዎችን ራሱ ሲደርስባቸው ወይም ከማንኛውም ሰው ጥቆማ ሲደርሰው ያግዳል፤ ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ማስታወቂያዎች ማስታወቂያዎቹ እንዲወጡለት ባደረገው ሰው ወጪ መጀመሪያ በተገለጹበት ዘዴ ማረሚያዎች እንዲወጡ ያስደርጋል፤
8. ነጋዴዎች በሸማቾች ላይ አግባብነት የጎደለው ተግባር እንዳይፈጽሙ ይከላከላል፤
9. የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ጉዳዮችን በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚዳኙ የዳኝነት ችሎቶችን ያደራጃል፤
10. ነጋዴዎች ከነጋዴዎች ጋር እንዲሁም በሸማቾች እና ነጋዴዎች መካከል የሚነሱትን ቅራኔዎች በእርቅ እና ድርድር እንዲፈቱ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
11. የተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ራሳቸውን በራሳቸው ከፀረ-ውድድር እና ተገቢ ካልሆኑ የንግድ ተግባራት እንዲቆጣጠሩ የሚያስችላቸውን አካሄድ እንዲከተሉ ድጋፍ ያደርጋል፤
12. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 መሠረት ለተቋቋመው ለፌደራል ንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት የጽሕፈትና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
13. የሸማቾች ጥበቃን በሚመለከት አግባብ ላላቸው የክልል አካላት አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፤
14. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የአገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ጋር ግንኙነትና ትብብር ይመሠርታል፤
15. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
16. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

31. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 እና አንቀፅ 32 የተደነገጉትን የባለሥ ልጣኑ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) የባለሥልጣኑን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎች መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል።

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራዎች ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡

## 32.<u>የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎቶች ስልጣንና ተግባር</u>

1. የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎቶች፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች የተከለከሉ ተግባራትን በፈጸሙ ነጋዴዎች ወይም ነጋዴ ባልሆኑ ሰዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት ለመወሰን፤

ለ) ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድርን በሚመለከት በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተጥሰዉ በተፈጸመ ድርጊት የተነሳ ጉዳት የደረሰባቸዉ ነጋዴዎች ለደረሰባቸው ጉዳት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲካሱ ለማድረግ፣ እና

ሐ) የሸማቾች ጥበቃን በሚመለከት በዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተጥሰው በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በተፈጸመ ግብይት የተነሳ ጉዳት የደረሰባቸው ሸማቾች ለደረሰባቸዉ ጉዳት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲካሱ ለማድረግ የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) መሠረት የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦

ሀ) ተገቢ አይደለም የተባለው ድርጊት እንዲቆም ማድረግ፤

ለ) የተጎጂውን የመወዳደር አቅም ወደነበረበት ቦታ ለመመለስ የሚያስችል ተገቢ እርምጃ መውሰድ፤ ወይም

ሐ/ የአጥፊው የንግድ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ማድረግ፡፡

## 33.ስለፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት

1. የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት (ከዚህ በኋላ "የፌደራል ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት" በመባል የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የፌደራል ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት፡-
   ሀ) ባለሥልጣኑ የውህደት ፈቃዶችን ለመከልከልና ለመሠረዝ እንዲሁም የንግድ ማስታወቂያዎችን ለማገድ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች፤ እና
   ለ) የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎቶች በሚሰጧቸው ውሳኔዎች፤
   ላይ የሚቀርቡለትን ይግባኞች የማየትና የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
3. የፌዴራል ይግባኝ ሰሚው አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔውን ማጽናት፣ ማሻሻል ወይም መሻር ወይም እንደ አግባቡ ባለሥልጣኑ ወይም የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት ጉዳዩን እንደገና መርምሮ እንዲወሰን ከአስፈላጊው መመሪያ ጋር ሊመልስለት ይችላል፡፡

## 34.የክልል የሸማቾች ጥበቃ ዳኝነት አካላት

እያንዳንዱ ክልል እንደአስፈላጊነቱ የሸማቾች ጥበቃ ዳኝነት አካል እና ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## 35.የዳኞች አሿሿም እና ነፃነት

1. እያንዳንዱ የባለስልጣኑ የዳኝነት ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ችሎት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢ እና ሁለት ሌሎች ዳኞች ይኖሩታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሾሙ ዳኞች ለሥራቸው ተፈላጊ የሆነ የሙያ ብቃት፣ የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰየሙ ዳኞች በዳኝነት ከሚያዩዋቸው ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ከማንኛውም ሰው ጣልቃ ገብነት ወይም አመራር ነፃ ይሆናሉ።

## ክፍል አምስት

## ምርመራ ስለማከናወንን፤ ክስ ስለማቅረብ እና ዳኝነት ስለማየት

## 36.ምርመራ ስለማከናወን[56]

1. ባለሥልጣኑ በራሱ መረጃ ወይም ማንኛውም ሰው በሰጠው መረጃ ላይ ተመሥርቶ
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 እና አንቀፅ 42 መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃዎችና አስተዳደራዊ ቅጣት ወይም በአንቀጽ 43(1) ወይም (7) መሠረት የወንጀል ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት በማናቸውም ቦታ ተፈጽሟል፤ ወይም
   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 (2)፤ (3)፤ (4)፤ (5) ወይም (6) መሠረት የወንጀል ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተፈጽሟል፤

   ብሎ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው ምርመራ ያካሂዳል።
2. ባለሥልጣኑ የምርመራ ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ስር ያሉ ሃይሎችን ማዘዝ ይችላል፤
3. በባለሥልጣኑ የምርመራ ኦፊሰር የሚጠየቅ የፍተሻ ወይም የመያዣ ትዕዛዝ አግባብ ባላቸው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በባስሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
4. የባለሥልጣኑ የምርመራ ኦፊሰር ምርመራ ሲያከናውን፡-
   ሀ) ወደ ተጠርጣሪው የንግድ ተቋም ወይም የንግድ ዕቃዎች ወደ ተከማቹበት ማንኛውም ሥፍራ በመግባት ወይም የንግድ ዕቃዎች የተጫኑበትን ተሽከርካሪ በማስቆም ፍተሻ ማድረግ፤
   ለ) ለምርመራው የሚያስፈልጉ የንግድ ዕቃዎችን ናሙና መውሰድ፤
   ሐ) በማንኛውም መንገድ የተያዙ መዝገቦችንና ሰነዶችን መመርመርና ቅጂዎቻቸውን መውሰድ፤
   መ) በሕገወጥ መንገድ የተከማቹ ወይም በመጓጓዝ ላይ ያሉ የንግድ ዕቃዎችን መያዝ ወይም የዕቃዎቹን ማከማቻ ወይም መያዣ ማሸግ፤

   ይችላል፡፡

---

[56] በ22/62(2008) አንቀፅ 22(7) መሰረት ለባለስልጣኑ የተሰጠው የመመርመር ስልጣን ለፌዴራል ፖሊስ ተላልፏል፡

5. ማንኛውም የባለሥልጣኑ የምርመራ ኦፊሰር የተሰጠውን የምርመራ ሥልጣን ማረጋገጫ ምርመራ ለሚካሄድበት የንግድ ተቋም፣ ማከማቻ ወይም ተሽከርካሪ ባለቤት ወይም ለወኪሉ ማሳየት አለበት፡፡
6. የንግድ ተቋማት ባለቤቶች፣ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚደረግ ምርመራ የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

**37.ክስ ስለማቅረብ**[57]

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 መሠረት በተከናወነ የምርመራ ውጤት ላይ ተመሥርቶ፡-
   ሀ) በባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድና አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲጣል፤ ወይም
   ለ) ሥልጣን ባለው የፌደራል ፍርድ ቤት የወንጀል ቅጣት እንዲጣል፣ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በባለሥልጣኑ ዓቃቤ ሕግ ይሆናል፡፡
2. ተገቢ ባልሆነ የንግድ ውድድር የተነሳ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ነጋዴ ካሳ እንዲከፈለው ለባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሠረት ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም ሸማች ግብይቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ሲሆን ለባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት ወይም ግብይቱ የተካሄደው በክልል ውስጥ ሲሆን ለክልሉ የሸማቾች ጥበቃ ዳኝነት አካል ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. በወንጀል ሕግ ክስን እና ቅጣትን ስለማቋረጥና ማስቀረት የተደነገጉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) መሠረት በሚቀርብ ክስ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**38.ዳኝነት ስለማየት**

1. የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎቶች፣ የፌደራል ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት፣ የክልል የሸማቾች ጥበቃ ዳኝነት አካላት እና የክልል ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ሲያዩ፡-
   ሀ) አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እና ሰነዶችን ማንኛውም ሰው እንዲያቀርብላቸው የማዘዝ፤
   ለ) ምስክሮች ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ የማዘዝ፤
   ሐ) ያስተላለፏቸውን ትዕዛዞች የማስፈጸም፤
   መ) ፖሊስን ወይም አግባብ ያለውን ሌላ አካል የማዘዝ፤ እና

---
[57] በ22/12(2008) አ.943 የአቃቤ ህግነት ስልጣን አንቀፅ 22(6) መሰረት ጠቅላይ አቃቤ ህግ ተላልፏል፡፡

ሠ) የንግድ ዕቃዎች እንዲታገዱ፣ እንዲያዙና እንዲሸጡ የማድረግ፤ ሥልጣን ይኖርበታል፡፡

2. የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት የአስተዳደር ቅጣት ወይም አስተዳደራዊ አርምጃ በሚወስንበት ጊዜ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፤

ሀ) የተፈፀመውን ጥፋት፣ ባህሪ፣ የቆይታውን ጊዜ፣ ክብደትና መጠን፤

ለ) በተፈፀመው ጥፋት ምክንያት የደረሰውን የጉዳት መጠን፤

ሐ) ጥፋቱ የተፈፀመበትን የገበያ ሁኔታ፤

መ) ከተፈፀመው ጥፋት አጥፊው ያገኘውን ጥቅም፤

ሠ) የአጥፊውን የኢኮኖሚ ደረጃ፤

ረ) በምርመራው ወቅት አጥፊው ከባለሥልጣኑ ጋር ያደረገውን ትብብር፤ እና

ሰ) የአጥፊውን የቀድሞ ባህሪና የጥፋት ሪከርዶች፡፡

39. <u>ይግባኝ</u>

1. ባለሥልጣኑ ውህደትን ለመከልከል ወይም የውህደት ፈቃድን ለመሰረዝ ወይም የንግድ ማስታወቂያን ለማገድ በሰጠው ውሳኔ ወይም በማንኛውም የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለፌደራሉ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. የፌዴራሉ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚቀርብለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33(3) መሠረት የተሰጠን ውሳኔ በሚመለከት የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

40. <u>የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ</u>

1. ማንኛውም መንግሥታዊ አካል ያልሆነ ሰው ለባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት ክስ ሲያቀርብ ወይም ለፌደራል ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

2. የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ታሪፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል፡፡

41. <u>የሥነ-ሥርዓት ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ዳኝነትን በተመለከተ እንደ አግባቡ የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 42.አስተዳደራዊ ቅጣቶች

1. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ነጋዴ የዓመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ5 እስከ 10 በመቶ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
2. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተላለፈ ማንኛውም ነጋዴ የዓመታዊ ሽያጭ ገቢውን 10 በመቶ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
3. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ነጋዴ የዓመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ5 አስከ 10 በመቶ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
4. የዚህን አዋጅ ከአንቀፅ 9 እስከ አንቀፅ 13 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መተላለፍ በውህደት ድርጊት የተሳተፈ ማንኛውም ነጋዴ የዓመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ5 አስከ 10 በመቶ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) በተዘረዘሩት ጥፋቶች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የማንኛውም ነጋዴ ያልሆነ ሰው ተሳትፎ መኖር ከተረጋገጠ ከብር 10,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተን ጥፋት በመፈጸም ተግባር የተሳተፈና ስለተፈጸመው ጥፋትና ስለተባባሪዎቹ ሚና በቂና በሌላ አኳኋን ሊገኝ የማይችል መረጃ የሰጠን ሰው ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ክስ እንዳይመሠረትበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 43.የወንጀል ቅጣቶች

1. ማንኛውም ነጋዴ የሆነ ወይም ነጋዴ ያልሆነ ሰው እንደ ቀደም ተከተሉ የባለሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት ወይም ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32(1) (ሀ) ወይም በአንቀጽ 33 (1) ያስተላለፈበትን አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39 (2) መሰረት በይግባኝ የማየት ስልጣኑ ያስተላለፈውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ሳያከብር የቀረ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

2. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 22 (6) ወይም (10) የተላለፈ ማንኛውም ነጋዴ የዓመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ7 እስከ 10 በመቶ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከ3 ዓመት እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
3. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 22 (6) እና (10) ሳይጨምር ከአንቀጹ ሌሎች ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱን የተላለፈ ማንኛውም ነጋዴ የዓመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ5 እስከ 10 በመቶ የገንዘብ ቅጣት እና ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
4. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 24 በመተላለፍ የንግድ እቃዎችን አከማችቶ ወይም ደብቆ ወይም በሕገወጥ መንገድ ሲያጓጉዝ የተገኘ ማንኛውም ነጋዴ ተከማችቶ ወይም ተደብቆ ወይም በሕገወጥ መንገድ ሲጓጓዝ የተያዘው የንግድ ዕቃ ተወርሶ የዓመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ5 እስከ 10 በመቶ የገንዘብ ቅጣት እና ከ1 አመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
5. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 24 በመተላለፍ የንግድ ዕቃዎችን በማከማቸት ወይም በመደበቀ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ በማጓጓዝ የተሳተፈ አሽከርካሪ ከብር 10,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ ተሽከርካሪው የንግድ ዕቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተሠራ ወይም የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመለት ከሆነ ወይም የተሽከርካሪው ባለቤት የሕገ ወጥ ማጓጓዝ ድርጊቱን እያወቀ እንዳይፈጸም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ የቀረ እንደሆነ ተሽከርካሪው ከንግድ ዕቃዎቹ ጋር ይወረሳል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ ንዑስ አንቀጽ (5) ከተጠቀሱት ውጪ ያሉትን የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጣን ደንብ መመሪያ ወይም የሕዝብ ማስታወቂያ የተላለፈ ነጋዴ የሆነ ወይም ነጋዴ ያልሆነ ሰው ከብር 5,000 እስከ ብር 50,000ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና በቀላል እስራት ይቀጣል::
7. የባለሥልጣኑን የምርመራ ሂደት የተቃወመ፣ ያሰናከለ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ተፅኖ ያደረሰ ጥፋተኛ ሆኖ በቀላል እስራት ይቀጣል፤
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተውን ወንጀል በሚመለከት ክስ የቀረበለት የፌደራል ፍርድ ቤት የባለ ሥልጣኑ የዳኝነት ችሎት አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም

የቅጣት ውሳኔ መከበር አለመከበሩን ከመመርመር በስተቀር የባለሥልጣኑን የዳኝነት ችሎት ውሳኔ ትክክለኛነት የመመርመር ሥልጣን አይኖረዉም፡፡

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (8) መሠረት የሚጣል የወንጀል ቅጣት የባለሥልጣኑን የዳኝነት ችሎት አስተዳደራዊ እርምጃና የአስተዳደራዊ ቅጣት ውሳኔ ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡

44.**በጀት**

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

45.**የሂሳብ መዛግብት**

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡
2. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተሩ በሚሰየሙ ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

46.**ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችንና የሕዝብ ማስታወቂያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

47.**የተሻሩ ሕጎች**

1. የንግድ አሰራርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 685/2002 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
2. ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

48.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. በንግድ አሰራር አዋጅ ቁጥር 329/1995 እና በንግድ አሰራርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 685/2002 መሠረት የወጡ መመሪያዎችና የሕዝብ ማስታወቂያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎችና የሕዝብ ማስታወቂያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።
2. በንግድ አሰራር አዋጅ ቁጥር 329/1995 እና በንግድ አሠራርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 685/2002 መሠረት በንግድ አሠራርና የሸማቾች

ጥበቃ ባለሥልጣን በመታየት ላይ የነበሩ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት በባለሥልጣኑ ይስተናገዳሉ፡፡

49.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## <u>አዋጅ ቁጥር 1147/2011</u>

## <u>በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ</u>

ዋስትናው የተጠበቀ ዘመናዊ የብድር ሥርዓት እንዲኖር እና ግለሰቦችና ተቋማት ተንቀሳቃሽ ንብረታቸውን በማስያዝ ሥራ ላይ የሚውል አዲስ ካፒታል ማግኘት እንዲችሉ፣ በሂደትም በየደረጃው ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት፣ ተጨማሪ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የፋይናንስ ተደራሽነትንና ተጠቃሚነትን ለማስፋፋት፣ በዋናነት በከተሞች ላይ ብቻ ውስን ሆኖ የቆየውን የባንክ አገልግሎትና ተደራሽነት ወደ ገጠሩ ማህበረሰብ ለማስፋፋትና ለማሳደግ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ፤

ተንቀሳቃሽ ንብረትን በዋስትና አስይዞ ብድር ማግኘት የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋትና የማስፈጸሚያ መንገዱንም ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

ለዋስትና በተያዘ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በተወዳዳሪ ባለመብቶች የሚነሳ የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን የሚያስችል አንድ ወጥና ሁሉን አቀፍ የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

## የፍትህ ሚኒስቴር

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ ቁጥር 1147/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. "የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ" ማለት ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተያያዘ ቢሆንም እንደተንቀሳቃሽ ንብረት የሚቆጠር ሀብት ነው፤
2. "የተገኘ የዋስትና መብት" ማለት በግዑዝ ሀብት ወይም አዕምሯዊ ንብረት ላይ ያልተከፈለ ቀሪ ዋጋን ለማስፈጸም ወይም መያዣ ሰጪው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዲያገኝ ለማድረግ የተፈፀመ ብድርን ለማስከፈል እንዲቻል በዚያው መጠን በንብረቱ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት ነው፤
3. "የንግድ ተቋም" ማለት በንግድ ሕግ የተመለከተው የንግድ መደብር ነው፤
4. "በሰነድ የተደገፈ ሴኩሪቲ" ማለት ሰነዱን በያዘው ሰው ስም ወይም ለአምጪው ተብሎ የታዘዘ አክሲዮን ወይም ቦንድ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፤
5. "የመያዣ መዝገብ" ማለት በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በስምምነት ወይም ከህግ ወይም ከፍርድ የመነጨ የዋስትና መብት መረጃን መቀበያ፣ ማስቀመጫ እና ለሕዝብ ተደራሽ ማድረጊያ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ነው፤
6. "የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት" ማለት የመያዣ ምዝገባ ሥርዓትን ለማስተዳደር የሚቋቋም ጽህፈት ቤት ነው፤
7. "ተወዳዳሪ ባለመብት" ማለት ገንዘብ ጠያቂ ወይም በዋስትና በተያዘ ንብረት ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ጋር ተወዳዳሪ የመብት ጥያቄ ያለው ሌላ ሰው ነው፤
8. "የፍጆታ ዕቃዎች" ማለት መያዣ ሰጪው በዋናነት ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ የቤት ውስጥ ፍጆታ የሚጠቀምባቸው ወይም ለመጠቀም ያዘጋጃቸው ዕቃዎች ናቸው፤
9. "የቁጥጥር ስምምነት"ማለት:-

ሀ) የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ዋስትናን በተመለከተ በሰነድ አውጪው፣ በመያዣ ሰጪው እና ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል የተደረገና አውጪው የመያዣ ሰጪው ተጨማሪ ፈቃድ ሳያስፈልገው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሚሰጠውን ትዕዛዝ በቀጥታ የሚፈጽምበት የጽሑፍ ስምምነት ነው፤ ወይም

ለ) ከተቀማጭ ሂሳብ ላይ ክፍያ የማግኘት መብትን ለማስፈጸም በፋይናንስ ተቋሙ፣ በመያዣ ሰጪው እና ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል የተደረገና የፋይናንስ ተቋሙ የመያዣ ሰጪው ተጨማሪ ፈቃድ ሳያስፈልገው በመያዣ ሰጪው ሂሳብ ውስጥ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሚሰጠውን ትዕዛዝ በቀጥታ የሚፈጽምበት የጽሑፍ ስምምነት ነው፤

10. "ግዑዝ ሀብት" ማለት ገንዘብ፣ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ፣ የሚተላለፍ ሰነድ እና በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎችን ጨምሮ ማንኛውም ዓይነት ዕቃ ነው፤

11. "ባለዕዳ" ማለት ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ገንዘብ የመክፈል ወይም ግዴታውን የመፈጸም ኃላፊነት ያለበት ሰው ሲሆን ለዚሁ ዋስ የሆነንም ይጨምራል፤

12. "የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ" ማለት የተሰብሳቢ ሂሳብን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሲሆን፣ ለሂሳቡ ክፍያ ዋስ የሆነን ወይም በሁለተኛ ደረጃ ዋስ የሆነ ሌላ ሰውን ይጨምራል፤

13. ‹‹ተቀማጭ ሂሳብ›› ማለት ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ ለመሰብሰብ ፈቃድ በተሰጠው የፋይናንስ ተቋም ውስጥ ያለ ሂሳብ ነው፤

14."መሣሪያ" ማለት ከንግድና ከፍጆታ ዕቃዎች ውጭ የሆነና መያዣ ሰጪው በዋናነት ለሥራው የሚጠቀምበት ወይም ሊጠቀምበት የያዘው ግዑዝነት ያለው ሀብት ነው፤

15. "ኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች" ማለት ኤሌክትሮኒካዊ በሆነ መንገድ የተመዘገቡ፣ የሚተላለፉ እና በሰነድ ያልተደገፉ አክሲዮኖችና ቦንዶች ናቸው፤

16."የግብርና ምርቶች" ማለት የበቀሉ ወይም በመብቀል ላይ ያሉ ወይም ወደፊት የሚበቅሉ ሰብሎች፣ ደንና የደን ውጤቶች፣ የቤት እንስሳት የሚወለዱትን ጨምሮ፣ የንብና የዶሮ ዕርባታ፣ ለግብርና ሥራ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብአቶች ወይም

በግብርና ሥራ የተመረቱ፣ ወይም በምርት ሂደት ያልተቀየሩ የሰብል ወይም የእንስሳት ምርቶችንና ሌሎች የግብርና ውጤቶችን ያጠቃልላል፤

17. “የፋይናንስ ኪራይ” ማለት አከራዩ አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን በተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በየተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ ዓይነት ነው፤
18. “ታሳቢ ሀብት” ማለት ገና ያልተፈጠረ ወይም የዋስትና ስምምነቱ በሚፈጸምበት ጊዜ መያዣ ሰጪው ገና የባለቤትነት መብት ያላገኘበት ተንቀሳቃሽ ንብረት ነው፤
19. “ታሳቢ ብድር” ማለት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከተበዳሪው ጋር ቀደም ሲል በመሰረተው የብድር ስምምነት መሠረት ለተበዳሪው ወደፊት የሚሰጠው ተጨማሪ ብድር ነው፡፡
20. “መያዣ ሰጪ” ማለት ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ግዴታ ማስፈፀሚያ ዋስትና ያስያዘ፣ በዋስትና ግዴታ የተያዘ ንብረትን ከነግዴታው የገዛ፣ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ያለው፣ በዱቤ ግዢ መሠረት የተከራየ ሰው ነው፤
21. “የዱቤ ግዢ” ማለት አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሠረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት፣ እያንዳንዱ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራይ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበትና ተከራይ የመጨረሻው ክፍያ እንዲፈጸመም በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያውኑ የሚያገኝበት የኪራይ ዓይነት ነው፤
22. “ግዑዝነት የሌለው ሀብት” ማለት ተሰብሳቢ ሂሳብን፣ ተቀማጭ ሂሳብን፣ የአእምሯዊ ንብረት መብትንና ከግዑዝ ንብረት ውጭ ያሉ ተመሳሳይ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ያካትታል፤
23. “አዕምሯዊ ንብረት” ማለት በአገሪቱ አእምሯዊ ንብረት ህጎች የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

24. "የንግድ ዕቃ" ማለት ጥሬ እና በከፊል የተቀነባበሩትን ጨምሮ መያዣ ሰጪው በመደበኛ የንግድ ሥራ ሒደት ለሽያጭ ወይም ለኪራይ የያዘዉ ግኡዝ ሃብት ነዉ፤
25. "ውህድ ወይም ምርት" ማለት አንድን ምርት ከሌላ ምርት ጋር በማዋሀድ ወይም በመቀላቀል የሚፈጠር አዲስ ይዘት ያለው ምርት ወይም ውህድ ነው፤
26."ገንዘብ" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚታተሙ ሕጋዊ መገበያያ የገንዘብ ኖቶች እና የሚቀረጹ ሳንቲሞች፣ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈጸም ክፍያ ተቀባይነት ያላቸውና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገለጹ የሌላ ሀገር ሕጋዊ የመገበያያ የገንዘብ ኖቶች እና ሳንቲሞች ናቸው፤
27."ተንቀሳቃሽ ንብረት" ማለት የንግድ ዕቃዎችን፣ የግብርና ምርቶችን፣ ግዑዝነት የሌላቸው ሀብቶችን፣ ግዑዝ ሀብቶችን፣ በሕግ ካልተከለከለ በስተቀር በመሬት ላይ የመጠቀም መብትን፣ በዱቤ ግዢ የሚገኝ መብት፣ በአደራ የተቀመጠ ንብረት ሠነድ፣ የአደራ መያዣ ደረሰኝ፣ የሸቀጦች ጭነት፣ ንግድን ለዋስትና ማስያዝ፣ ባለቤትነትን በማስጠበቅ የሚደረግ ሽያጭ፣ የተሸጠ ንብረትን መልሶ ለመግዛት መብት የሚሰጥ ሽያጭ፣ በምስክር ወረቀት የሚረጋገጡ ሴኩሪቲዎች ላይ የሚመሠረት የዋስትና መብት፣ እና በመጋዘን ደረሰኝ ላይ ያለ የዋስትና መብትን፣ የሞተር ተሽከርካሪን፣ ተሳቢን፣ የእርሻ መሣሪያን፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያን፣ የኢንዱስትሪ መሣሪያን ጨምሮ ሌሎች ከመሬት፣ ከቤት ወይም ከሕንጻ ውጭ ያሉ ንብረቶችን ያካትታል፤
28."የሚተላለፍ ሰነድ" ማለት በሰነዱ ላይ የተገለጸውን ንብረት የመረከብ መብት የሚሰጥና ሊተላለፍ የሚችል እንደ ማጓጓዣ ሰነድ፣ ቫውቸር ወይም በመጋዘን የተቀመጠ ዕቃ መቀበያ ደረሰኝ ነው፤
29. "የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ" ማለት የሐዋላ ወረቀት፣ የተስፋ ሰነድ እና ከቼክ በስተቀር ሌላ ለአምጪው ወይም በስሙ ወይም ለታዘዘለት ተብሎ የተዘጋጀ ሰነድን ያካትታል፤
30. "በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂ የሆነ" ማለት በዋስትና መያዣ ላይ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በሕግ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያገኘ ሰው ነው፤

31.“ማስታወቂያ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ወይም ፈቃድ በተሰጠው ሰው በመያዣ መመዝገቢያ ሥርዓት ውስጥ የሚካተት የመጀመሪያ ምዝገባ፣ የማስተካከያ ምዝገባ ወይም የስረዛ ምዝገባ ነው፤

32.“የአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ” ማለት በአከራዩ እጅ የሚገኝ አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ተከራዩ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ኪራይ በመክፈል ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲጠቀምበት የሚከራይበት የኪራይ ዓይነት ነው፤

33. “ቀደምት ሕግ” ማለት ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሥራ ላይ የነበረ ሕግ ነው፤

34.“ቀደምት የዋስትና መብት” ማለት ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በተፈጸመ የዋስትና ስምምነት የተሸፈነ መብት ነው፤

35.“ይዞታ” ማለት አንድ ሰው ወይም ተወካዩ አንድን ግዑዝ ንብረት በራሱ ወይም በሌላ ሰው ኃላፊነት ሥር እንዲሆን ማድረግ ነው፤

36. “ተያያዥ ገቢ” ማለት ከዋስትና መያዣው የሚገኝ ማንኛውም ገቢ ሲሆን፣ በሽያጭ፣ በማስተላለፍ፣ በመሰብሰብ፣ በማከራየት ወይም በፈቃድ የተገኘ ወይም የፍሬ ገቢ፣ የመድን ገቢ፣ በዋስትና ከተያዘው ንብረት ብልሽት፣ ጉዳት ወይም መጥፋት ጋር ተያይዞ የሚሰበሰብ ገቢንና በዚሁ ገቢ አማካይነት የተገኘ ተጨማሪ ገቢን ያካትታል፤

37.“ተሰብሳቢ ሂሳብ” ማለት ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ከሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ፣ ከተቀማጭ ሂሳብ እና ከዋስትና የሚገኝ የክፍያ መብትን ሳይጨምር ገንዘብ የመክፈል መብት ነው፤

38.“የታወቀ ገበያ” ማለት ዋጋ በይፋ የሚገለጽበት እና/ወይም በንግድ አሰራር ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንበት የተለመደና የታወቀ ገበያ ማለት ነው፤

39.“መዝጋቢ” ማለት ምዝገባው በሚጠይቀው መሥፈርት መሠረት መረጃዎችን በመያዣ መመዝገቢያ ሥርዓት ውስጥ የሚመዘግብ ወይም የሚያካትት ሰው ነው፤

40. “ሬጅስትራር” ማለት የመያዣ ምዝገባ ሥርዓቱን እንዲያስተዳድር እና እንዲቆጣጠር በመንግሥት የሚሾም ሰው ነው፤

41. “መረጃ” ማለት በመያዣ መመዝገቢያ ሥርዓት ውስጥ የተቀመጠ፣ የተጠበቀ፣ የተደራጀና ለሕዝብ ክፍት የሆነ የተመዘገበ መረጃ ነው፤
42. “ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ” ማለት የዋስትና መብት ያለው ወይም በህግ ወይም በፍርድ የገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፤
43. “የዋስትና ስምምነት” ማለት ተዋዋይ ወገኖች የዋስትና ስምምነት ብለው ባይሰይሙትም በመያዣ ሰጪውና በመያዣተቀባዩ መካከል የተፈረመ የዋስትና መብት የሚፈጥር ስምምነት ነው፤
44. “የዋስትና መብት” ማለት ተዋዋይ ወገኖች የዋስትና መብት ብለው ባይሰይሙትም በንብረቱ ዓይነት፣ በመያዣ ሰጪውና ተቀባዩ እና ዋስትና በተገባለት ግዴታ ላይ ሳይወሰን የክፍያ ወይም ሌላ ግዴታን ለማስፈጸም በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈጠር መብት ነው፤
45.“መለያ ቁጥር›› ማለት በሻሲ ወይም በሌላ የፋብሪካ ምርት አካል ላይ የሚገኝ መለያ ቁጥር ነው፤
46. “መለያ ቁጥር ያለው መያዣ” ማለት በአምራቹ በቋሚነት የተጻፈ ወይም የተለጠፈ መለያ ቁጥር ያለው ሞተር ተሽከርካሪ፣ ተሳቢ፣ የእርሻ መሣሪያ፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያ፣ የኢንዱስትሪ መሣሪያ እና ሌላ መለያ ቁጥር ያለው ዕቃ ነው፤
47. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
48.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ ለብድር ክፍያ ወይም ለሌላ ግዴታ አፈጻጸም በስምምነት በሚመሠረቱ በተንቀሳቃሽ ንብረት መብቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ይህ አዋጅ፡-

ሀ) በገበያ በሚሸጡ ሴኩሪቲዎች ላይ የሚመሠረት የዋስትና መብት ላይ፤

ለ) የባሕር ሕግ ተፈፃሚ የሆነበት መርከብና ለአገልግሎቱ በሚውሉ ተጓዳኞች ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት ላይ፤

ሐ) በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን በተመዘገበ አውሮፕላን ላይ የሚገኝ የተጠቃሚነት መብት ላይ፤

መ) በዚህ አዋጅ ካልተገለፀ በስተቀር ብድር እስኪመለስ ድረስ ገንዘብ ጠያቂው በሕግ እንዲይዘው በተፈቀደ ንብረት ላይ፤ እና

ሠ) አንድ ተያያዥ ገቢ ከዚህ አዋጅ የተፈፃሚነት ወሰን ውጭ ከሆነ፣ በገቢው ላይ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት ካላቸውና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን የሚሸፍኑና የሚፈቅዱ ከሆነ፤ ይህ አዋጅ በተያያዥ ገቢው የዋስትና መብት ላይ፤

ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3. ይህ አዋጅ በማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ሕግ መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ የሚፈጠር ዋስትናን አይከለክልም፡፡

## ክፍል ሁለት

## የዋስትና መብት አመሠራረት

4. **የዋስትና መብት በስምምነት የሚመሠረት ስለመሆኑና ይዘቱ**

   1. የዋስትና መብት የሚመሠረተው በስምምነት ሆኖ መያዣ ሰጪው ለዋስትና ባቀረበው ንብረት ላይ የባለቤትነት ወይም የማስያዝ መብት ሊኖረው ይገባል፡፡
   2. በዱቤ ግዢ ውል መሠረት በተገኘ የካፒታል ዕቃ ላይ ተከራይ የዋስትና መብት መፍጠር ይችላል፡፡ ሆኖም የመብቱ ከፍተኛ መጠን ከዕቃው ዋጋ ላይ ለአከራይ ሊከፈል የሚገባው ቀሪ ዕዳ ተቀንሶ በሚቀረው መጠን ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል፡፡
   3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የዋስትና መብት ስምምነት በታሳቢ ሀብት ላይ መመስረት ይቻላል፡፡
   4. የዋስትና መብት ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝን በመያዣነት ሊይዝ ይችላል፡፡ ሆኖም ተጓዳኙ ከተንቀሳቃሹ ወይም ከማይንቀሳቀሰው ንብረት ጋር በአካል መያያዙ መብቱን ቀሪ አያደርግም፡፡
   5. የዋስትና ስምምነት በጽሑፍ የተደገፈና በመያዣ ሰጪው ፊርማ የተረጋገጠ ሆኖ:-

      ሀ) የመያዣ ሰጪውንና የዋስትና ተቀባዩን ማንነት፤

      ለ) ዋስትና የተገባለትን ግዴታ፤ እና

      ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት መያዣውን፤

      መግለጽ ይኖርበታል፡፡

5. **ዋስትናቸው ሊጠበቅ የሚችል ግዴታዎች**

አንድ የዋስትና መብት የታወቀ ወይም ታሳቢ የሆነ፣ የተረጋገጠ ወይም ሊረጋገጥ የሚችል፣ በቅድመ ሁኔታ ወይም ያለ ቅድመ ሁኔታ፣ የተቆረጠ ወይም ተለዋዋጭ የሆነ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ግዴታዎችን ሊሸፍን ይችላል፡፡

6. **የመያዣው እና የዋስትናው ግዴታ መግለጫ**

1. መያዣው እና የዋስትናው ግዴታ በዋስትና ስምምነቱ ውስጥ በበቂ ሁኔታና በግልጽ ሊለዩ በሚያስችል መልኩ ሊገለጹ ይገባል፡፡
2. መግለጫው የዋስትና መያዣውን በዝርዝር፣ በምድብ፣ በዓይነት፣ ወይም በብዛት በመለየት ማስቀመጥ አለበት፡፡
3. ዋስትናው የተጠበቀ ግዴታ አሁን የተገባ ወይም ወደፊት የሚገባ ተብሎ፣ በአንድ ጠቅላላ ምድብ ወይም እያንዳንዱ ተለይቶ እና ዋስትና የተገባለትን ግዴታ ከፍተኛ መጠን በማመልከት መገለጽ ይኖርበታል፡፡

7. **በተያያዥ ገቢ ላይ ስለሚኖር መብት**

1. በአንድ ሀብት ላይ ያለ የዋስትና መብት በሀብቱ ላይ ተለይተው ሊታወቁ የሚችሉ ተያያዥ ገቢዎችን ያካትታል፡፡
2. ተያያዥ ገቢ በተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ከተደረገ ወይም ከሌላ ገንዘብ ጋር ከተቀላቀለ:-

ሀ) የተቀላቀለው ገንዘብ ተለይቶ መታወቁ ቢያከትምም የዋስትና መብቱ የተቀላቀለውን ተያያዥ ገቢ ይከተላል፤

ለ) በውህድ ንብረት ላይ ያለ የዋስትና መብት ንብረቶቹ ከመዋሀዳቸው በፊት በነበረው ተያያዥ ገቢ መጠን ላይ ይገደባል፤

ሐ) ከውህደት በኋላ በማንኛውም ጊዜ የተዋሀደው ገንዘብ ከውህደቱ በፊት ከተቀላቀለው ተያያዥ ገቢ ያነስ ከሆነ፣ በተዋሀደው ገንዝብ ላይ ያለ የዋስትና መብት ጥያቄው በቀረበበት ወቅት በሚኖረው መጠን ላይ የተገደበ ይሆናል፡፡

8. **ውህድ ወይም ምርት ውስጥ የተቀላቀሉ ግዑዝ ሃብቶች**

ግዑዝ ሀብት ከሌላ ተመሳሳይ ሀብት ወይም ምርት ጋር ቢዋሀድ እንኳን በሃብቱ ላይ የተመሠረተው የዋስትና መብት ወደ ውህድ ወይም ምርቱ ይተላለፋል፡፡

9. **የዋስትና መብት እንዳይመሠረት የሚገድቡ ስምምነቶች**

1. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት መመሥረትን የሚገድብ ስምምነት በባለመብቱና በባለዕዳው መካከል ቢኖርም ከዚህ በተቃራኒ በመያዣ ሰጪውና

ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል የተፈጠረ የዋስትና መብት ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም መያዣ ሰጪው በንዑስ አንቀጹ የተመለከተውን ውል በመጣሱ ምክንያት ካለበት ግዴታና ኃላፊነት ነጻ ሊሆን አይችልም፡፡ ሆኖም ሌላኛው ተዋዋይ ወገን:-

ሀ) ለተሰብሳቢ ሂሳቡ ወይም ለዋስትና ስምምነቱ መነሻ የሆነው ውል ተጥሷል በሚል ምክንያት ብቻ ውሉን መተው፣ ወይም

ለ) በውሉ አለመከበር ምክንያት በመያዣ ሰጪው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ማንኛውንም መብት ዋስትና ካለው ገንዘብ ጠያቂ ላይ ማንሳት፤

አይችልም፡፡

3. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው:-

ሀ) ከፋይናንስ አገልግሎት በስተቀር ከዕቃ ወይም ከአገልግሎት አቅርቦት ወይም ከኪራይ ውል፤

ለ) ከግንባታ ውል ወይም ከማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ወይም ከኪራይ ውል፤ እና

ሐ) ከአዕምሯዊ ንብረት ሽያጭ፣ ኪራይ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ውል፣

በሚመነጩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ብቻ ነው፡፡

4. መያዣ ሰጪው በተቀማጭ ሂሣብ ላይ የዋስትና መብት የመፍጠር መብቱን በማንኛውም ሁኔታ የሚገድብ ውል ከፋይናንስ ድርጅት ጋር ቢዋዋልም እንኳን በተቀማጭ ሂሳቡ ውስጥ ገቢ ከተደረገ ገንዘብ ላይ ክፍያ የማግኘት የዋስትና መብት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

10. <u>ክፍያን ወይም ሌላ ግዴታን ለማስፈጸም ዋስትና ወይም ደጋፊ ስለሚሆኑ ግላዊ ወይም የንብረት መብቶች</u>

1. ግዑዝነት በሌለው ሀብት ወይም በተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ዋስትናውን በአዲስ ስምምነት ማስተላለፍ ሳያስፈልግ ለክፍያ ወይም ለሌላ ግዴታ አፈጻጸም መጠቀም ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው መብት ሊተላለፍ የሚችለው በሌላ አዲስ ስምምነት ከሆነ መያዣ ሰጪው ይህን የተጠቃሚነት መብት ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

11. <u>በተላላፊ ሰነዶች የተሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች</u>

በተላላፊ ሰነድ ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሰነዱ በተካተተ ግዑዝ ሀብት ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

12.**<u>ከአዕምሯዊ ንብረት መብት ጋር ስለተያያዙ ግዑዝ ሀብቶች</u>**

በአዕምሯዊ ንብረት መነሻነት በተፈጠረ ግዑዝ ሀብት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት አዕምሯዊ ንብረቱን አያካትትም፤ በአዕምሯዊው ንብረት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብትም ግዑዝ ሀብቱን አይሸፍንም፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ስላለው ተፈፃሚነት</u>**

13.**<u>የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው መንገዶች</u>**

በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው:-

1. የዋስትና መብቱን አስመልክቶ በዋስትና መዝገብ ውስጥ ማስታወቂያው ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ከተመዘገበ፤
2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ገንዘብ፣ ተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች፣ ተላላፊ ሰነዶችና በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎች በአንቀጽ 56 መሠረት በይዞታው ሥር ካደረገ፤ ወይም
3. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ወደተቀማጭ ሂሳብ ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ወይም በኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ዋስትና ላይ የቁጥጥር ስምምነት ካለው፣

ነው፡፡

14.**<u>የተያያዥ ገቢ፣ የውሁድ ወይም የምርት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ስለሚኖረው ተፈፃሚነት</u>**

1. በአንድ ንብረት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት በንብረቱ ተያያዥ ገቢ ላይም በመያዣ ሰጪውና በዋስትና ተቀባዩ መካከል ሌላ ተጨማሪ ስምምነት ሳያስፈልግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ይህ የሚሆነው ተያያዥ ገቢው ገንዘብ፤ ተሰብሳቢ ሂሣብ፤ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ከሆነና ወደ ተቀማጭ ሂሣብ ገቢ ከተደረገ ገንዘብ ላይ ክፍያ የማግኘት መብት ካለ ነው፡፡
2. በአንድ ሀብት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተገለጹት ተያያዥ ገቢዎች በስተቀር

በሌሎች ገቢዎች ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት የሚፈጠረው የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው:-

ሀ) ገቢዎቹ ከተፈሩ በኋላ ለአሥር የሥራ ቀናት፣ እና

ለ) በገቢዎቹ ላይ ያለ የዋስትና መብት አሥሩ የሥራ ቀናት ከማለቃቸው በፊት አግባብ በሆነው የዋስትና ዓይነት ላይ ተፈፃሚ ከማድረጊያ መንገዶች በአንዱ አማካኝነት የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ፣

ነው፡፡

3. በግዑዝ ሀብቶች ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት በውህድ ወይም በምርት ላይ ያለተጨማሪ ሁኔታ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

15. <u>በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆኑ የዋስትና መንገዶች ለውጥ</u>

የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው መንገዶች ቢለወጡም በለውጡ ሂደት የጊዜ ክፍተት እስከሌለ ድረስ ተፈፃሚነቱ ይቀጥላል፡፡

16. <u>የዋስትና መብትን ስለማስተላለፍ</u>

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዋስትናው ላይ ያለውን የዋስትና መብት በሙሉ ወይም በከፊል ካስተላለፈ ይህንኑ የሚገልጽ የማስተካከያ ማስታወቂያ ማስመዝገብ ይችላል፡፡
2. የተላለፈ የዋስትና መብት የማስተካከያ ማስታወቂያ በመዝገብ ላይ ቢመዘገብም ባይመዘገብም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

17. <u>ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ላይ ክፍያ የመጠየቅ መብት</u>

ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ:-

1. የፋይናንስ ተቋሙን ተጠቃሚ የሚያደርግ የዋስትና መብት በመመሥረት፤
2. የቁጥጥር ስምምነት በመፈረም፤ወይም
3. የተቀማጭ ሂሳብን በይዞታ ሥር በማድረግ፤

ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ላይ ክፍያ ለማግኘት የሚያስችል የቁጥጥር መብት ይኖረዋል፡፡

18. <u>ተላላፊ ሰነድና በሰነዱ የሚሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች</u>

1. በተላላፊ ሰነድ ላይ ያለ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ መብቱ በሰነዱ በተሸፈነው ንብረት ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. የተላላፊ ሰነድ ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ይዞታ ሥር ከሆነ የዋስትና መብቱ በሰነዱ በተሸፈኑ ንብረቶችና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

19.**ኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች**

ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎችን መቆጣጠር የሚችለው:-

1. የሴኩሪቲዎቹን ይዞታ ለመመዝገብ ሲባል በአውጪው ወይም በወኪሉ በተዘጋጀ መዝገብ ላይ የዋስትና መብቱን መግለጫ በመፃፍ ወይም ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ ስም በመመዝገብ፣ ወይም
2. የቁጥጥር ስምምነት በመፈፀም፣

ነው፡፡

## ክፍል አራት

## የመያዣ መዝገብ

20.**የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት መቋቋም**

የተንቀሳቃሽ ንብረት ዋስትና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በደንብ ይቋቋማል፡፡

21.**የመያዣ መዝገብ መቋቋም**

የዋስትና መብትን እና በህግ ወይም በፍርድ የገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠውን በሚመለከት መረጃ ለመቀበል፣ ለማስቀመጥና ለሕዝብ ተደራሽ የማድረግ ዓላማ ያለው የተንቀሳቃሽ ንብረት የመያዣ መዝገብ ይቋቋማል፡፡

22.**መያዣ ሰጪው ለዋስትና ምዝገባ የሚሰጠው ፈቃድ**

1. በመያዣ መዝገብ ውስጥ የማሳወቂያ ምዝገባ የሚከናወነው ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ወይም በህጋዊ ወኪሉ ነው፡፡
2. መያዣ ሰጪው በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር የመጀመሪያ የዋስትና መብት ማስታወቂያ ምዝገባ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
3. መያዣ ሰጪው በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር በዋስትና ስምምነት ያልተሸፈነ መያዣን ለመጨመር የሚደረግ የማስታወቂያ ማሻሻያ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
4. ተጨማሪ መያዣ ሰጪ የሚሆነው ሰው በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር መያዣ ሰጪ ለመጨመር የሚደረግ የማስታወቂያ ማሻሻያ ተፈፃሚነት የለውም፡፡
5. በጽሑፍ የተደረገ የዋስትና ስምምነት መያዣ ሰጪው ማስታወቂያው እንዲመዘገብ እንደፈቀደ ይቆጠራል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የዋስትና ስምምነት ከቀረበ የመያዣ መዝገቡ መያዣ ሰጪው ምዝገባ እንዲደረግ ፈቃድ ስለመስጠቱ ማረጋገጫ አይጠይቅም፡፡

23.<u>ከአንድ በላይ በሆኑ የዋስትና ስምምነቶች ለተመሰረቱ የዋስትና መብቶች አንድ ማስታወቂያ በቂ ስለመሆኑ</u>

አንድ መያዣ ሰጪ ከአንድ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ጋር በተፈራረመው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ የዋስትና ስምምነት ላይ የተመሰረቱ የዋስትና መብቶችን በአንድ ማስታወቂያ መመዝገብ ይቻላል፡፡

24.<u>ለሕዝብ ተደራሽ ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም ሰው በመያዣ መዝገቡ ማስታወቂያ ማስገባት የሚችለው በመያዣ መዝገቡ የተጠቃሚነት መለያ ኮድ ካለው እና በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ከከፈለ ነው፡፡
2. የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ የሚቀርበው በተጠቃሚ መለያ ኮድ አማካኝነት እና በዚህ ክፍል መሠረት ማስታወቂያውን ለማቅረብ መብት ባለው ሰው አማካኝነት ብቻ ነው፡፡
3. ማንኛውም ሰው የመረጃ ፍለጋ ቅጽ በሚጠይቀው መሠረት ለመያዣ መዝገቡ የፍለጋ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. የመያዣ መዝገቡ የተጠየቀውን መረጃ የማይሰጥ ከሆነ የተከለከለበትን ምክንያት ለመዝጋቢው ወይም ለመረጃ ፈላጊው ወዲያውኑ መግለጽ አለበት፡፡

25. <u>የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የመረጃ ጥያቄን ውድቅ ስለማድረግ</u>

1. የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የመረጃ ፍለጋ መጠየቂያ ቅፅ በሚጠይቀው መሠረትና ቦታ ላይ መሞላት ያለበት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ መረጃ ካልገባ የመያዣ መዝገቡ የማስታወቂያ ምዝገባውን ወይም ፍለጋውን አይቀበልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተደነገገው ካልሆነ በስተቀር የመያዣ መዝገቡ የማስታወቂያ ምዝገባን ወይም የመረጃ ፍለጋ ጥያቄን ውድቅ ማድረግ አይችልም፡፡
3. የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የመረጃ ፍለጋ ጥያቄ ውድቅ የተደረገ እንደሆነ የመያዣ መዝገቡ ምክንያቱን ለአስመዝጋቢው ወይም ለመረጃ ፈላጊው ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

26.<u>የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ምርመራ እንዳያደርግ ስለመከልከሉ</u>

የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የፍለጋ ጥያቄ ወይም የማስታወቂያ ይዘትን መመርመር አይችልም፡፡

27.**ለመጀመሪያ ማስታወቂያ የሚያስፈልጉ መረጃዎች**

1. የመጀመሪያ ማስታወቂያ የሚከተሉትን አግባብነት ባላቸው ቦታዎች የተሞሉ መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል:-

   ሀ) በአንቀጽ 28 መሠረት የመያዣ ሰጪውን መለያ ቁጥር እና ሙሉ ስም፤

   ለ) በአንቀጽ 29 መሠረት ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ ወይም የተወካዩን መለያ፤

   ሐ) የመያዣ ሰጪውን እና ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ አድራሻ፤

   መ) በአንቀጽ 30 መሠረት መያዣውን የሚያብራራ መግለጫ፤

   ሠ) ምዝገባው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤ እና

   ረ) ለስታትስቲካዊ ዓላማ ብቻ እንዲሰበሰብ በመመሪያ የሚወሰን ማንኛውም ሌላ መረጃ፡፡

2. ከአንድ በላይ መያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በሚኖርበት ጊዜ መረጃዎች ለእያንዳንዱ መያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በተናጠል መሞላት ይኖርባቸዋል፡፡

28.**የመያዣ ሰጪው መለያ**

1. መያዣ ሰጪው የተፈጥሮ ሰው ከሆነ:-

   ሀ) መለያው በመመሪያ የሚወሰን ልዩ የመታወቂያ ቁጥር፤ እና

   ለ) ስሙ የኢትዮጵያ ዜግነት ላለው ሰው የፀና ኦፊሴላዊ መታወቂያ ሠነድ ላይ የሰፈረው ስም ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው የተፈጥሮ ሰው በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የፀና ፓስፖርት ላይ የተገለፀው ስም ይሆናል፡፡

2. መያዣ ሰጪው የሕግ ሰውነት ያለው ከሆነ:-

   ሀ) መለያው በመመሪያ የሚወሰን ልዩ የመታወቂያ ቁጥር፣ እና

   ለ) ስሙ በማቋቋሚያ ሰነድ ወይም ሕግ ላይ የሰፈረ ስያሜ ይሆናል፡፡

29. **ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መለያ**

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የተፈጥሮ ሰው በሚሆንበት ጊዜ መለያው በመመሪያ የሚወሰን የገንዘብ ጠያቂው ወይም የተወካዩ ሙሉ ስም ይሆናል፡፡

2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሕግ ሰውነት ያለው በሚሆንበት ጊዜ መለያው በመመሪያ የሚወሰን የገንዘብ ጠያቂው ወይም የተወካዩ ስም ይሆናል፡፡

30.**<u>የዋስትና መግለጫ</u>**

1. ለዋስትና የዋለ ወይም የሚውል ንብረት ማስታወቂያ ላይ በበቂ ሁኔታ እንዲለይ በሚያስችል መልኩ ተብራርቶ መገለጽ ይኖርበታል፡፡
2. መግለጫው የመያዣ ሰጪውን ተንቀሳቃሽ ንብረት በሙሉ፣ ወይም በአንድ በተወሰነ ምድብ ውስጥ ያለ ሁሉንም ተንቀሳቃሽ ንብረት የሚይዝ መሆኑን ከገለጸ፣ ወይም በብዛት ወይም በስሌት ቀመር ካስቀመጠ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መስፈርትን ያሟላ ይሆናል፤
3. በማስታወቂያው ላይ ያለው መግለጫ በዋስትና ስምምነቱ ካለው መግለጫ ጋር አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን የማስታወቂያው መግለጫ በዋስትና ስምምነቱ ከተገለጸው የንብረት ዓይነት የሚበልጥ ሆኖ ከተገኘ ማስታወቂያው በትርፍነት በገለጻቸው ንብረቶች ላይ የዋስትና መብቱ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
4. በተመዘገበ ማስታወቂያ ውስጥ አንድን ንብረት መጥቀስ መያዣ ሰጪው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዳለው ወይም ወደፊት እንደሚኖረው አያመላክትም፡፡
5. የንግድ ዕቃ ካልሆነ በስተቀር መለያ ቁጥር ያለው መያዣ መለያ ቁጥር፣ በዓይነቱና በአምራቹ ስም መገለጽ አለበት፡፡

31. **<u>የማስታወቂያ ምዝገባ ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ጊዜ</u>**

1. የመያዣ መዝገቡ ለመጀመሪያ ማስታወቂያ ልዩ የምዝገባ ቁጥር በመስጠት እና ይህንን ቁጥር መሠረት በማድረግ የተመዘገቡ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያዎችን መጀመሪያ ከተመዘገበው ማስታወቂያ ጋር ያያይዛል፡፡
2. የመጀመሪያ፣ የማሻሻያ እና የስረዛ ማስታወቂያ መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በመያዣ መዝገቡ ከተመዘገቡበት ቀን እና ሰዓት ጀምሮ ለህዝብ ክፍት ይሆናሉ፡፡
3. የመያዣ መዝገቡ በማስታወቂያው ውስጥ ያለውን መረጃ ማስታወቂያው በቀረበበት ቅደም ተከተል ወዲያውኑ ወደመዝገቡ ያስገባል፡፡
4. የመያዣ መዝገቡ ለመረጃ ፈላጊዎች ተደራሽ እንዲሆን በማስታወቂያው ውስጥ ያለው መረጃ ወደመዝገቡ የገባበትን ቀን እና ሰዓት ይመዘግባል፡፡

32. **<u>የማስታወቂያ ምዝገባ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

1. የመጀመሪያ ማስታወቂያ ተፈፃሚ ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ መዝጋቢው በማስታወቂያው ላይ ይህንኑ ለማመልከት በተዘጋጀው ቦታ ላይ የገለጸው ሆኖ ከአሥር ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

2. የመጀመሪያ ማስታወቂያ ምዝገባ የተፈፃሚነት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ ምዝገባው እንዲራዘም በሚጠይቅበት ቦታ ላይ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ የተጨማሪ ጊዜ በመመዝገብ ሊራዘም ይችላል፡፡
3. የመጀመሪያ ማስታወቂያ የተፈፃሚነት ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ መራዘም ይችላል፡፡
4. የጊዜ ማሻሻያ የዋስትናው መራዘም የሚጀምርበትን ቀን ካላስቀመጠ ዋስትናው የተሻሻለው ማስታወቂያ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ በማስታወቂያው ላይ ለተመለከተው ጊዜ ይራዘማል፡፡

33. <u>የተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ የመላክ ግዴታ</u>

1. አንድ ማስታወቂያ እንደተመዘገበ የመያዣ ምዝገባ ሥርዓቱ ወዲያውኑ ምዝገባው መፈፀሙን የሚገልጽ ሰነድ ለመዝጋቢው የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
2. ምዝገባው መፈፀሙን የሚገልጸው ሰነድ ምዝገባው የተፈፀመበትን ቀን ፣ ሰዓት፣ እና የምዝገባውን ቁጥር የሚያሳዩ መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መዝጋቢው የማስታወቂያውን ግልባጭ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ማስታወቂያውን በመያዣ ሰጪነት ለተመዘገበው ሰው መላክ ይኖርበታል፡፡

34.<u>የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ የመመዝገብ መብት</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በተመዘገበ የመጀመሪያ ማስታወቂያ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ተብሎ የተጠቀሰው ሰው ምዝገባውን አስመልክቶ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ መመዝገብ ይችላል፡፡
2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ማንነት የሚቀይር የማሻሻያ ማስታወቂያ ከተመዘገበ በኋላ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ መመዝገብ የሚችለው በማሻሻያ ምዝገባው ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ሆኖ የተጠቀሰው ሰው ብቻ ነው፡፡
3. በተመዘገበ የመጀመሪያ ወይም የማሻሻያ ማስታወቂያ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ተብሎ የተጠቀሰው ሰው ሳይፈቅድ የተመዘገበ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

35. <u>በማሻሻያ ወይም በስረዛ ማስታወቂያ ላይ መካተት ያለበት መረጃ</u>

1. አንድ የማሻሻያ ማስታወቂያ ለዚሁ ተብሎ በተለየ ቦታ ላይ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31(1) መሠረት በመያዣ መዝገቡ የተሰጠን ልዩ የምዝገባ ቁጥር፤ እና

ለ) የሚጨመረውን ወይም የሚለወጠውን መረጃ፤

መያዝ አለበት፡፡

2. የማሻሻያ ማስታወቂያው በተመዘገበ ማስታወቂያ ውስጥ ያለ መረጃ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆነውን ሊመለከት ይችላል፡፡
3. አንድ የስረዛ ማስታወቂያ ለመጀመሪያ ማስታወቂያው የተሰጠውን ልዩ የምዝገባ ቁጥር ለዚሁ በተለየ ቦታ ላይ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

36.<u>አስገዳጅ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ ምዝገባ</u>

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ:-

ሀ) የማሻሻያ ማስታወቂያው መያዣ ሰጪው ከፈቀደው በላይ መረጃ የያዘ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የተመዘገበው ማስታወቂያ የተወሰነ የዋስትና መያዣን የሚያሰርዝ ሆኖ ከተሻሻለ፣

የማሻሻያ ማስታወቂያ ማስመዝገብ አለበት፡፡

2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ:-

ሀ) መያዣ ሰጪው የመጀመሪያ ማስታወቂያ እንዲመዘገብ ካልፈቀደ፣

ለ) መያዣ ሰጪው የመጀመሪያው ምዝገባ እንዲፈጸም ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ የሰጠውን ፈቃድ ካነሳ እና የዋስትና ስምምነት ካልተፈረመ፣ ወይም

ሐ) ማስታወቂያው የሚመለከተው የዋስትና መብት ቀሪ እንደሆነ እና ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ለመያዣ ሰጪው ክፍያ የመፈፀም ተጨማሪ ግዴታ ከሌለበት፣

የስረዛ ማስታወቂያው መመዝገብ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና 2(ሀ) የተገለጸው ሁኔታ ሲኖር ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ግዴታውን ለመወጣት ክፍያ መጠየቅ ወይም መቀበል አይችልም፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተደነገጉት ሁኔታዎች አንዱ ከተሟላ መያዣ ሰጪው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ እንዲያስመዘግብ በጽሑፍ መጠየቅ የሚችል ሲሆን፣ ገንዘብ ጠያቂው ይህንን ለማድረግ ምንም ዓይነት ክፍያ ወይም ወጪ መጠየቅ ወይም መቀበል አይችልም፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከመያዣ ሰጪው በጽሐፍ በደረሰው ጥያቄ መሠረት በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ካልፈፀመ መያዣ ሰጪው የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያው በመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በኩል እንዲመዘገብ መጠየቅ ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የሚጠየቅን የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወዲያውኑ መዝግቦ ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ግልባጭ የሚደረግ ተገቢ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

37.<u>የመፈለጊያ መስፈርት</u>

ለሕዝብ ክፍት በሆነው የመያዣ መዝገብ ውስጥ ያለን መረጃ:-

1. የመያዣ ሰጪውን መለያ፣ ወይም
2. የመያዣን መለያ ቁጥር፣

በመጠቀም መፈለግ ይችላል፡፡

38.<u>ስለፍለጋ ውጤት</u>

1. በዚህ ክፍል የተገለጹትን መስፈርቶች ያሟላ የፍለጋ ጥያቄ ሲቀርብ የመያዣ ምዝገባ ሥርዓቱ ወዲያውኑ:-

   ሀ) ፍለጋው የተከናወነበትን ቀን እና ሰዓት፣

   ለ) እያንዳንዱ ከፍለጋው መሥፈርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰል መረጃ፣ ወይም

   ሐ) ከፍለጋው መሥፈርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰል መረጃ አለመገኘቱን፣

   የሚያሳይ ምላሽ ይሰጣል፡፡

2. ተቃራኒ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ በመያዣ መዝገቡ ለፍለጋ ጥያቄ የተሰጠ ማስረጃ ስለ ፍለጋው ይዘት ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

39.<u>ማስታወቂያ ውስጥ የገባ የአስፈላጊ መረጃ ስህተት</u>

1. የመያዣ ሰጪው መለያ ላይ የተፈጠረ ስህተት የማስታወቂያ ምዝገባው ተፈፃሚ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡
2. በአንድ የመያዣ ሰጪ መለያ ላይ የተፈጠረ ስህተት በሌሎች በትክክል የተገለጹ መያዣ ሰጪዎች ላይ ምዝገባው ተፈፃሚ እንዳይሆን አያደርግም፡፡
3. ከመያዣ ሰጪው መለያ በስተቀር በሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ላይ የተፈጠረ ስህተት አንድ ምክንያታዊ የሆነ መረጃ ፈላጊን በከባዱ የሚያሳስት እስካልሆነ ድረስ ምዝገባው ተፈፃሚ እንዳይሆን አያደርግም፡፡
4. ለስታቲስቲክስ ተብሎ በመመሪያ እንዲመዘገቡ በተጠየቁ መረጃዎች ላይ የተፈጠረ ስህተት የምዝገባውን ተፈፃሚነት አያስቀርም፡፡
5. በአንድ የዋስትና መግለጫ ላይ የተፈጠረ ስህተት ሌላ በበቂ ሁኔታ የተገለፀ መያዣ የማስታወቂያ ምዝገባ ተፈፃሚነትን አያስቀርም፡፡

6. የመለያ ቁጥር ያለው ዋስትናን መለያ ቁጥር መሳሳት ምዝገባውን በንብረቱ ገዢ እና ተከራይ ረገድ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

40.<u>ከምዝገባ በኋላ የመያዣ ሰጪው መለያ መለወጥ</u>

1. መያዣ ሰጪው መለያውን ከመቀየሩ ቢያንስ ከአሥር ቀናት በፊት ስለለውጡ ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
2. ከምዝገባ በኋላ የመያዣ ሰጪው መለያ ከተለወጠ፡ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ስለለውጡ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ እና የተመዘገበው ማስታወቂያ የተፈፃሚነት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የማሻሻያ ማስታወቂያውን ካስመዘገበ፣ ማስታወቂያው የሚመለከተው የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ያለው ተፈፃሚነት ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን ከለውጡ በፊት ከተወዳዳሪ መብት ጠያቂዎች የነበረው ቀደምትነትም የተጠበቀ ይሆናል፡፡
3. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ጊዜ ካበቃ በኋላ የማሻሻያ ማስታወቂያ ካስመዘገበ:-

   ሀ) ማስታወቂያ የተመዘገበበት ወይም የመያዣ ሰጪው መለያ ከተለወጠ በኋላ ነገር ግን ማሻሻያው ከመመዝገቡ በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የዋስትና መብት፣ የማሻሻያ ማስታወቂያው ከሚመለከተው የዋስትና መብት ቀደምትነት ይኖረዋል፤

   ለ) ከመያዣ ሰጪው መለያ ለውጥ በኋላ ነገር ግን ከማሻሻያ ማስታወቂያው ምዝገባ በፊት መያዣውን የገዛ፣ የተከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው የማሻሻያ ማስታወቂያ መብቱን ከሚመለከተው የዋስትና መብት ነፃ ሆኖ ያገኛል፡፡

41.<u>ከምዝገባ በኋላ ስለሚተላለፍ መያዣ</u>

የተመዘገበና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የዋስትና መያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መያዣው ለሌላ ሰው ከተሰጠ ወይም ከተላለፈ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ያለው የተፈፃሚነት መብት ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን፣ ከተፎካካሪ መብት ጠያቂዎች ያለው ቀደምትነትም የተጠበቀ ነው፡፡

42.<u>በመያዣ መዝገብ ውስጥ ስለተመዘገበው መረጃ ተአማኒነት</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 36(6) እንደተጠበቀ ሆኖ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ማንኛውም የተመዘገበ ማስታወቂያ ውስጥ ያለን መረጃ ማሻሻል ወይም መሰረዝ አይችልም፡፡
2. የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በመዝገቡ ውስጥ የሚገኝ መረጃን ጠብቆ የማቆየት እና መረጃው ሲጠፋ ወይም ሲጎዳ መልሶ የማደራጀት ግዴታ አለበት፡፡

43.**መረጃን ከመያዣ መዝገብ እና ከማህደር ስለማስወገድ**

1. የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ለሕዝብ ክፍት በሆነው የምዝገባ ማስታወቂያ ውስጥ ያለን መረጃ የማስታወቂያው ምዝገባ የተፈፃሚነት ጊዜ ሲያበቃ ማውጣት አለበት፡፡
2. የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ለሕዝብ ክፍት ከሆነው መዝገብ የተወገደ መረጃን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 መሠረት መልሶ ሊገኝ በሚያስችል መልኩ ለአሥር ዓመት ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

44.**የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የተጠያቂነት ወሰን**

የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በሌሎች ሕጎች ተጠያቂነት የሚኖረው:-

1. ለመረጃ ፈላጊው የተሰጠ ምላሽ ወይም ለመዝጋቢው ተሰጥቶ በተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ ውስጥ ስህተት በመፈፀም ወይም መረጃ ባለማካተት፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 (5) እና (6) መሠረት በዋስትና መዝገብ ውስጥ መረጃ ሲመዘገብ ስህተት በመፈፀም ወይም መረጃ ባለማስገባት ወይም ከመዝገቡ ውስጥ በስህተት መረጃ በማውጣት፤
3. የመያዣ መዝገቡ ለመዝጋቢው የተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ ባለመስጠቱ፤ ወይም
4. ለመዝጋቢው ወይም ለመረጃ ፈላጊው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ በመስጠት፣ ለደረሰ ኪሣራ ወይም ጉዳት ነው፡፡

**ክፍል አምስት**

**የቀዳሚነት መብት**

45.**ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የቀዳሚነት መብት**

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ይልቅ የቀዳሚነት መብት አለው፡፡
2. በኪሣራ ሕግ በተቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚነት በኪሣራ ወይም በሂሳብ ማጣራት ጊዜም ይቀጥላል፡፡

**46.በአንድ የመያዣ ሰጪ ስለተፈጠሩ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች**

1. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አንድ መያዣ ሰጪ በተመሳሳይ ዋስትና ላይ በፈጠራቸው የዋስትና መብቶች መካከል ያለው የቀዳሚነት መብት የሚወሰነው ዋስትና የተመሰረተበት ጊዜ ቅደም ተከተል ከግምት ሳይገባ በምዝገባቸው ቅደም ተከተል ነው፡፡
2. የዋስትና ውል ከመፈፀሙ ወይም በታሳቢ ሀብት ላይ መያዣ ሰጪው የማስያዝ መብት ወይም ስልጣን ከማግኘቱ በፊት የተመዘገበ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚወሰነው በምዝገባው ቅደም ተከተል መሠረት ነው፡፡

**47.በተለያዩ መያዣ ሰጪዎች ስለተፈጠሩ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች**

አንድ መያዣ ሰጪ መያዣውን ያገኘው በዚሁ መያዣ ላይ ቀደም ብሎ በሌላ ሰው የተመሰረተ የዋስትና መብት እንደተጠበቀና በሦስተኛ ወገኖች ላይም ተፈጻሚ ከሆነ፣ በመያዣው ላይ የተመሰረተው መብት ቀደም ብሎ በሌላው ሰው ከተመሰረተው የዋስትና መብት የበታች ነው፡፡

**48.የዋስትና መብት መኖሩን ማወቅ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ**

ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የዋስትና መብት መኖሩን ማወቁ በዚህ አዋጅ መሠረት ያለውን የቀዳሚነት መብት አያሳጣውም፡፡

**49.በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሆነ የዋሰትና መንገድ በሚለወጥበት ጊዜ ስለሚኖሩ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች**

በዚህ ክፍል ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የነበረ የዋስትና መብት የተመሠረተበት መንገድ ሲለወጥ የጊዜ ክፍተት እስከሌለው ድረስ የቀዳሚነት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

**50.ታሳቢ ብድር እና ታሳቢ መያዣ**

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ የተገቡ ግዴታዎችን ጨምሮ ሁሉንም ዋስትናቸው የተጠበቁ ግዴታዎችን ይሸፍናል፡፡
2. ከምዝገባው በፊት ወይም በኋላ በመያዣ ሰጪው የተገኘ ወይም የተፈጠረ ቢሆንም ቀዳሚ የዋስትና መብት በመያዣ መዝገቡ በማስታወቂያ ተለይተው የተመዘገቡ ዋስትናዎችን በሙሉ ይሸፍናል፡፡

**51.በተያያዥ ገቢ ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሆነ የተያያዥ ገቢ ዋስትና መብት ከተወዳዳሪ የዋስትና መብት ይልቅ የገቢው ምንጭ በሆነው ዋስትና ላይ በተመሠረተው የቀዳሚነት መብት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

52.<u>በውህድ ወይም በምርት ውስጥ የተቀላቀሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት</u>

1. የተቀላቀሉ ወይም የተዋሃዱ ዕቃዎች ከአንድ ለሚበልጥ የዋስትና መብት ከዋሉ ዕቃዎቹ ከመቀላቀላቸው በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነው የዋስትና መብት ዕቃዎቹ ከተቀላቀሉ በኋላ ከሚመሰረት የዋስትና መብት በፊት የቀዳሚነት መብት አለው፡፡
2. የተቀላቀሉ ወይም የተዋሃዱ ዕቃዎች ከአንድ ለሚበልጥ የዋስትና መብቶች ከዋሉና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆኑ የመብቶቹ ቀዳሚነትና ዋጋ ዕቃዎቹ በተዋሃዱበት ጊዜ ባለው መሠረት ይሆናል፡፡

53.<u>በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት</u>

1. የዋስትና መብት የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ በሆኑ ወይም ሊሆኑ በሚችሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ሊመሠረት ወይም ሊቀጥል ይችላል፡፡ ሆኖም መብቱ በመደበኛ የግንባታ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ የዋስትና መብት በሌሎች ህጎች ከተመሠረቱና ተፈፃሚ ከሆኑ ተወዳዳሪ መብቶች ይልቅ የቀዳሚነት መብት አለው፡፡

54.<u>መያዣውን የገዛ፣ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም እንዲጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው መብቶች</u>

1. የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ሆኖ እያለ መያዣው በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ ከተላለፈ፣ ከተከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከተሰጠ ገዢው ወይም መብቱ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም የተፈቀደለት በዚህ አንቀጽ እንደተደነገገው ካልሆነ በስተቀር የንብረቱ ባለመብት የሚሆነው በላዩ ላይ ያለው የዋስትና መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ነው፡፡

2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ንብረቱን ከዋስትና ነፃ ሆኖ እንዲተላለፍ የፈቀደ እንደሆነ መያዣው በግዢ ወይም በሌላ ሁኔታ የተላለፈለት ሰው መብቱን ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ ያገኛል፡፡
3. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲያከራይ ወይም የመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጥ ለመያዣ ሰጪው የፈቀደ እንደሆነ ተከራዩ ወይም የመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው መብት በዋስትናው መብት አይታወክም፡፡
4. በሻጩ መደበኛ የንግድ ሥራ ውስጥ ገዢው የሽያጭ ውሉን በተዋዋለበት ወቅት ንብረቱ ለመያዣ መዋሉንና ሻጩ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መብት የጣሰ መሆኑን ካላወቀ በገዢው የሚያገኛቸው መብቶች ከዋስትናው ነፃ ናቸው፡፡
5. በአከራዩ መደበኛ የንግድ ሥራ ውስጥ ተከራዩ የኪራይ ውሉን በተዋዋለበት ወቅት ንብረቱ ለመያዣ መዋሉንና ኪራዩ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መብት የጣሰ መሆኑን ካላወቀ በኪራዩ የሚያገኛቸው መብቶች ከዋስትናው ነፃ ናቸው፡፡
6. በፈቃድ ሰጪው መደበኛ የንግድ ሥራ ውስጥ ፈቃድ ተቀባዩ አዕምሯዊ ንብረትን ለመጠቀም የፈቃድ ውሉን በተዋዋለበት ወቅት አዕምሯዊ ንብረቱ ለዋስትና መዋሉንና ፈቃዱ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መብት የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ በፈቃዱ የሚያገኛቸው መብቶች ከዋስትናው ነፃ ናቸው፡፡
7. አንድን መያዣ የገዛ ወይም በሌላ መንገድ የተላለፈለት ሰው መብቶቹን ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ ካገኛቸው ቀጣዩ ገዢ ወይም መብቱ የሚተላለፍለት ሰው መብቶቹን የሚያገኘው ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ ነው፡፡
8. አንድ በዋስትና የተያዘ ግዑዝነት ያለው ወይም የሌለውን ሀብት ከዋስትና ነፃ የተከራየ ወይም ፈቃድ የተቀበለ ከሆነ የቀጣዩ ተከራይም ሆነ ፈቃድ ተቀባይ መብቶች በዋስትናው አይታወኩም፡፡

55.<u>በህግ ወይም በፍርድ የገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው መብቶች</u>

1. በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከመሆኑ አስቀድሞ በመያዣ መዝገብ ውስጥ ይህንኑ ካስመዘገበ መብቱ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
2. በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው ማስታወቂያ ከመመዝገቡ አስቀድሞ የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ ይኼው መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ የቀዳሚነት መብት:-

ሀ) በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው በመያዣ መዝገቡ ውስጥ ስለመመዝገቡ ማስታወቂያ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ፤ ወይም

ለ) መጠኑ አስቀድሞ የተወሰነ ወይም ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ተለይቶ በተቀመጠ ቀመር መሠረት በተወሰነ ገንዘብ ወይም የማይሻር ግዴታ በተገባለትና በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው ለመያዣ ሰጪው ማስታወቂያ ከመስጠቱ በፊት፤

በተሰጠ ብድር ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል፡፡

3. በመደበኛ የንግድ ሥራ ሂደት ለሚቀርቡ የአገልግሎት ወይም የአቅርቦት ክፍያን ወይም አፈጻጸምን ለማረጋገጥ ዕቃዎችን ለዋስትና በይዞታ ሥር ለማቆየት የሚያስችል የዋስትና መብት እስካለ ድረስ ይህ የይዞታ መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

56.<u>ከተገኘ የዋስትና መብት ጋር የሚወዳደር ሌላ የዋስትና መብት</u>

1. በፍጆታ ዕቃዎች፣ በመሣሪያዎች እና በአዕምሯዊ ንብረቶች ላይ የተገኘ የዋስትና መብት መያዣ ሰጪው ከመሠረተው ሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚኖረው:-

ሀ) የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ንብረቱን በይዞታው ሥር ካደረገ፤ ወይም

ለ) መያዣ ሰጪው ሀብቱን በይዞታው ሥር ባደረገ ወይም አዕምሯዊው ንብረት ላይ መብት ባገኘ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የተገኘ የዋስትና መብት ማስታወቂያ የተመዘገበ እንደሆነ፤

ነው፡፡

2. በንግድ ዕቃ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት መያዣ ሰጪው ከመሠረተው ሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚኖረው:-

ሀ) የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን በይዞታው ሥር ካደረገ፤ ወይም

ለ) መያዣ ሰጪው ሀብቱን በይዞታው ሥር ከማድረጉ ቀደም ብሎ የተገኘ የዋስትና መብት ማስታወቂያ የተመዘገበ ከሆነ፤ እና

ሐ) የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ሰው በተመሳሳይ ዓይነት መያዣ ላይ ማስታወቂያ ለመዘገበና ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ በመያዣው የዋስትና መብት እንዳለው ወይም ለማግኘት ማቀዱን ካስታወቀው፤ነው፡፡

57.<u>የተገኙ የዋስትና መብቶች ተወዳዳሪነት</u>

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተወዳዳሪ በሆኑ የተገኙ የዋስትና መብቶች መካከል ቀዳሚነት የሚወሰነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46 መሠረት ነው፡፡
2. ከሻጭ፣ ከአከራይ ወይም ከፈቃድ ሰጪ የተገኘ የዋስትና መብት ዋስትና ካለው ተወዳዳሪ ገንዘብ ጠያቂ መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

58.<u>በተያያዥ ገቢ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት</u>

1. በመዣሪያ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት ካለ በሀብቱ ተያያዥ ገቢ ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት ከተገኘ የዋስትና መብት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡
2. በአዕምሯዊ ንብረት ወይም በንግድ ዕቃ ላይ የተገኘ ቀዳሚ የዋስትና መብት ካለ በንብረቱ ተያያዥ ገቢ ላይም የቀዳሚነት መብቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ገቢው ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ፤ የንግድ ወረቀት ወይም ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ላይ ክፍያ የመጠየቅ መብት ከሆነ ቀዳሚነቱ አይሠራም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተመለከተው የቀዳሚነት መብት የሚፀናው የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ተያያዥ ገቢው ከመገኘቱ በፊት በመያዣ መዝገብ ውስጥ ማስታወቂያ ስለመመዝገቡ በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት ለተሰጣቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ያስታወቃቸው እደሆነ ነዉ፡፡

59.<u>ከውህድ ወይም ከምርት ጋር በተቀላቀሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ የተገኘ የዋስትና መብት</u>

ውህድን ወይም ምርትን በሚሸፍንና በግዑዝ ሀብት ላይ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ሆኖ የተገኘ የዋስትና መብት በተመሳሳይ መያዣ ሰጪ ከተመሠረተ ሌላ የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት አለው፡፡

60.<u>የቀዳሚነት መብትን ስለማሳለፍ</u>

1. ማንኛውም ሰው በማናቸውም ጊዜ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን የቀዳሚነት መብት ለማንኛውም ተወዳዳሪ የዋስትና ባለመብት ተጠቃሚውን ወገን ተዋዋይ ማድረግ ሳያስፈልግ የቅድሚያ መብቱን አሳልፎ መስጠት ይችላል፡፡

2. የቀዳሚነት መብትን ማሳለፍ መብቱን ካሳለፈው ሰው እና ከተጠቃሚው ውጭ የሌሎች ተወዳዳሪ ባለመብቶችን አያውክም፡፡

61.<u>የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች</u>

1. በዋስትና ከተመዘገበና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ካለው የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ የዋስትና መብት ይልቅ ሰነዱን በይዞታው ሥር ለዋስትና ያደረገ ባለመብት ቀዳሚነት አለው፡፡
2. በዋስትና የተያዘና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ሆኖ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድን ገዥው ወይም በህግ የተላለፈለት ሰው ከዋስትናው ነፃ በሆነ መንገድ ሊያገኝ የሚችለው:-

ሀ) ሰነዶቹን በንግድ ሕጉ መሠረት እንደያዘ የሚቆጠር ከሆነ፤ ወይም

ለ) ሰነዶቹን በይዞታው ሥር ካደረገ እና ሽያጩ ወይም ዝውውሩ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብት እንደሚጥስ ባለማወቅ ዋጋ ከከፈለ፤ነው፡፡

62.<u>በተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ከሚገባ ገንዘብ ክፍያን የመጠየቅ መብት</u>

1. ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ላይ ክፍያ የመጠየቅ የዋስትና መብት ያለውና ሂሳቡ በይዞታው ሥር የሚገኝ ባለመብት በሌላ ማንኛውም መንገድ ከሚገኝና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሚሆን የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት አለው፡፡
2. ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ከሚገባ ገንዘብ ክፍያ የመጠየቅ የዋስትና መብት ያለው የፋይናንስ ተቋም ከሆነ፣ የዋስትና መብት ያለው ሌላ ክፍያ ጠያቂ የሂሳቡ ባለይዞታ በመሆን በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ካደረገው ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ውጭ በሌላ ማንኛውም መንገድ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
3. በቁጥጥር ስምምነት አማካኝነት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ በሆነና ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ክፍያ የመጠየቅ መብት ላይ ያለ የዋስትና መብት:-

ሀ) ከፋይናንስ ተቋሙ የዋስትና መብት፤ ወይም

ለ) የሂሳቡ ባለይዞታ የሆነ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ካደረገው የዋስትና መብት፤

በስተቀር ከሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

4. ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ክፍያ የመጠየቅ መብት ያላቸውና በቁጥጥር ስምምነት አማካኝነት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆኑ ተወዳዳሪ የዋስትና

መብቶች መካከል ቀዳሚነት የሚወሰነው የቁጥጥር ስምምነት የተደረጉበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

5. ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ክፍያ የመጠየቅ የዋስትና መብት ካለው ሰው ይልቅ አንድ የፋይናንስ ተቋም የተበዳሪውን ዕዳ ለማቻቻል ያለው መብት ቀዳሚነት አለው፤ ሆኖም ይህ የቀዳሚነት መብት የሂሳቡ ባለይዞታ በመሆን የዋስትና መብቱን በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ያደረገ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን የዋስትና መብት አይጥስም፡፡
6. በመያዣ ሰጪው ፈቃድ ወይም አማካኝነት ከአንድ ተቀማጭ ሂሳብ ላይ ገንዘብ የተላለፈለት ሰው ይህ ዝውውር ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብትን የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ ገንዘቡን ከዋስትና ነፃ በሆነ መንገድ ያገኛል፡፡

63.<u>**ገንዘብ**</u>

በዋስትና መብት ከተያዘ ገንዘብ ላይ ዝውውር የተፈፀመለት ሰው ገንዘቡን ከዋስትና ነፃ በሆነ መንገድ ሊያገኝ የሚችለው ዝውውሩ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብትን የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ ብቻ ነው፡፡

64.<u>**ተላላፊ ሰነድ እና በሰነዱ የሚሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች**</u>

1. የሚተላለፍ ሰነድን በይዞታ ሥር በማድረግ ሰነዱ በሚሸፍነው ንብረት ላይ ተፈፃሚ የሆነ የዋስትና መብት በሌላ ማንኛውም መንገድ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው ተወዳዳሪ የዋስትና መብቱ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
2. በዋስትና የተያዘ ተላላፊ ሰነድ የተላለፈለት ሰው ሰነዱን ተቀብሎ በይዞታው ሥር ካደረገ፣ የንብረት ሽያጩ ወይም ዝውውሩ ሌላ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብትን እንደሚጎዳ ባለማወቅ ዋጋ ከፍሎበት ከሆነ፤ መብቱ በሰነዱ ወይም በሰነዱ በተሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ካለ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ነፃ ሆኖ ያገኛል፡፡

65.<u>**ሴኩሪቲዎች**</u>

1. በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎችን በይዞታው ሥር በማድረግ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ያደረገ የዋስትና መያዣ መብት፣ መያዣ ሰጪው በሴኩሪቲዎች ላይ ከፈጠረውና ማስታወቂያ ለማስመዝገብ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ካደረገው ሌላ ተፎካካሪ የዋስትና መብት ቀደምትነት ይኖረዋል፡፡

2. በአውጪው ወይም እርሱን በመወከል በኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ላይ ስለዋስትና መያዣ መብት በተዘጋጀ መዝገብ ላይ መግለጫ በመጻፍ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን ስም እንደባለመብት መመዝገብ በሴኩሪቲዎቹ ላይ በሌላ ማንኛውም መንገድ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ይልቅ በምዝገባው የተገኘው መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
3. የቁጥጥር ስምምነት በመፈራረም በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች የዋስትና መብት በእነዚሁ ሴኩሪቲዎች ላይ ማስታወቂያ በማስመዝገብ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
4. በቁጥጥር ስምምነቶች አማካኝነት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆኑ ተወዳዳሪ የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ላይ የዋስትና መብቶች መካከል ቀዳሚነት የሚወሰነው ስምምነቶቹ የተደረጉበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው፡፡
5. በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎችን በይዞታው ሥር ያደረገ ወይም የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ላይ መብት ያገኘና መብቱ የተላለፈለት ሰው ሽያጩ ወይም ዝውውሩ በዋስትና ውሉ መሠረት ዋስትና ያለው ሌላ ገንዘብ ጠያቂን መብት እንደሚጥስ ባለማወቅ ዋጋ ከፍሎበት ከሆነ መብቱን ከዋስትናው ነፃ ሆኖ ያገኛል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የተዋዋይ ወገኖች እና ሦስተኛ ወገን ተገዳጆች መብትና ግዴታ

### 66. መያዣውን በይዞታው ሥር ካደረገ ሰው የሚጠበቅ ግዴታ

አንድ የመያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በይዞታው ሥር የሚገኝ መያዣን ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መጠበቅ አለበት፡፡

### 67. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ግዴታ

የዋስትና መብት በሚቋረጥበት ጊዜ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ:-

1. በይዞታው ሥር ያለውን ዋስትና ለመያዣ ሰጪው ይመልስለታል፤
2. ያስመዘገበውን የዋስትና ማስታወቂያ በአንቀጽ 36 (2) (ሐ) መሠረት ይሰርዛል፤
3. በቁጥጥር ስምምነት መሠረት ስምምነቱን ያነሳል፡፡

### 68. መያዣውን የመጠቀም፣ ወጪው እንዲተካ የማድረግ እና የመቆጣጠር መብት

1. ዋስትናው በይዞታው ሥር የሆነ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ:-

ሀ) የመድን፣ የግብር እና ሌሎች ክፍያዎችን ጨምሮ ሀብቱን ለመጠበቅ ያወጣው ተገቢ የሆነ ወጪ እንዲተካለትና ወጪውም ዋስትናው በተጠበቀው ግዴታ ላይ እንዲታከል የማድረግ መብት አለው፣

ለ) መያዣውን በአግባቡ በመጠቀም፣ ከመያዣውም ይገኛል ተብሎ ስምምነት የተደረገበትን ገቢ ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ክፍያ ማዋል ይችላል፡፡

2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በመያዣ ሰጪው ወይም በሌላ ሰው ይዞታ ሥር ያለን መያዣ የመቆጣጠር መብት አለው፡፡

69.**<u>መረጃ የማግኘት መብት</u>**

1. መያዣ ሰጪው ዋስትና የተገባለትን ግዴታ ወይም መያዣውን በሚመለከት መረጃ እንዲሰጠው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መጠየቅ ይችላል፡፡
2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መረጃ እንዲሰጥ ጥያቄ በቀረበለት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለመያዣ ሰጪው ወይም መያዣ ሰጪው ለወከለው ሰው:-

ሀ) ዋስትና ተገብቶለት ነገር ግን ስላልተከፈለ ግዴታ የሂሳብ መግለጫ፤

ለ) ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በየትኛው ዋስትና ላይ የዋስትና መብት እንዳለው የሚያመለክት መግለጫ፤ ወይም

ሐ) ዋስትና ተገብቶለት ነገር ግን ስላልተከፈለ ግዴታ ሂሳብ የሚገልጽና የዋስትና መያዣ መብቱ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ዋስትና የሚያመለክት መግለጫ፣መስጠት አለበት፡፡

70.**<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ ስለሚደረግለት ጥበቃ</u>**

በዚህ አዋጅ በተቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት መመሥረት ለሂሳቡ መነሻ በሆነው ዋናው ውል የተካተቱ የክፍያ ሁኔታዎችን ጨምሮ የባለዕዳውን መብትና ግዴታ ከእርሱ ፈቃድ ውጭ አያውክም፡፡

71.**<u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብትንና ክፍያን ስለማሳወቅ</u>**

1. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት ተፈፃሚነት የሚኖረው ባለዕዳው በዋስትና የተያዘውን ተሰብሳቢ ሂሳብና ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን በሚገባ የለየ ማስታወቂያ ሲደርሰው ነው፡፡
2. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት ከማስታወቂያ በኋላ የሚፈጠር ተሰብሳቢ ሂሳብንም ሊያካትት ይችላል፡፡

3. የተሰበሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ ስለተመሰረተው የዋስትና መብት ማስታወቂያ እስከሚደርሰው ድረስ በዋናው ውል መሠረት የክፍያ ግዴታውን ይፈፅማል፡፡ ባለዕዳው ማስታወቂያው ከደረሰው በኋላ ከግዴታው ነፃ የሚሆነው ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ክፍያን በመፈፀም ወይም በማስታወቂያው ወይም በገንዘብ ጠያቂው በጽሑፍ ተቃራኒ ማሳወቂያ ከተሰጠው ብቻ ነው፡፡
4. የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ በተሰብሳቢ ሂሳቡ ላይ ስለተመሰረተና ከአንድ በላይ የሆነ የዋስትና መብት ማስታወቂያ ከመያዣ ሰጪው ከደረሰው መጀመሪያ በደረሰው ማስታወቂያ መሠረት ክፍያ በመፈፀም ከግዴታው ነፃ ይሆናል፡፡
5. የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ በተሰብሳቢው ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት ለመኖሩ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በቂ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ መሠረት እስከሚፈፅም ድረስ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ ስለዋስትና መብቱ ማስታወቂያ ቢደርሰውም እንኳን ለመያዣ ሰጪው ክፍያ በመፈፀም ግዴታውን መወጣት ይችላል፡፡

72.<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ መቃወሚያዎችና የማቻቻል መብት</u>

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳን በዋስትና የተያዘውን ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲከፍል ጥያቄ ሲያቀርብ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ በገንዘብ ጠያቂው ላይ በመቃወሚያነት:-
 ሀ) ለተሰብሳቢ ሂሳቡ መመስረት ምክንያት ከሆነው ውል የሚመነጩ መቃወሚያዎችንና የማቻቻል መብትን ወይም የዚሁ አካል ሌላ ግብይትን በመጥቀስ የዋስትና መብቱ እንዳልተመሰረተ፣
 ለ) ባለዕዳው ስለዋስትና መብቱ ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ ሊጠቀምበት የሚችለውን የማቻቻያ መብት፣ማንሳት ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ስምምነት ተጥሷል የሚል የመከላከያ ወይም መብት የማቻቻል ጥያቄ በማንሳት መያዣ ሰጪው በተሰብሳቢ ሂሳቡ ላይ ያለውን ዋስትና የመመስረት መብት በማንኛውም ሁኔታ ሊገድብበት አይችልም፡፡
3. የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱ መቃወሚያዎችንና የማቻቻል መብትን ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ላይ ላለማንሳት ከመያዣ ሰጪው ጋር በጽሑፍ ለመስማማት ይችላል፡፡ ሆኖም ዋስትና ከተሰጠው

ገንዘብ ጠያቂ የማጭበርበር ተግባር የሚመነጨ ወይም በራሱ ችሎታ ማጣት ላይ የተመሠረቱ መቃወሚያዎችን አያስቀርም፡፡

73.**ተሰብሳቢ ሂሳብ የተመሠረተበትን ዋና ውል ስለማሻሻል**

በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ስለተመሠረተ የዋስትና መብት ማስታወቂያ ከመሰጠቱ በፊት በመያዣ ሰጪውና በባለዕዳው መካከል የተፈረመ የዋናው ውል ማንኛውም ማሻሻያ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብትን የሚነካ ቢሆንም ተፈፃሚ ነው፤ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂም በተሻሻለው ውል መሠረት የሚመለከተውን መብት ያገኛል፡፡

74.**የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ የፈፀማቸውን ክፍያዎች ስለማስመለስ**

በመያዣ ሰጪው ወይም በውል የተሰብሳቢ ሂሳብን ሙሉ በሙሉ ያስተላላፈ ሰው የተሰብሳቢው ሂሳብ መነሻ የሆነውን ውል መፈፀም ባለመቻሉ ባለዕዳው ለመያዣ ሰጪው ወይም ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ የከፈለውን ገንዘብ የማስመለስ መብት አይሰጠውም፡፡

75.**ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመሰብሰብ ፈቃድ ከተሰጣቸው የፋይናንስ ተቋማት ተጻራሪ የሆነ መብት**

1. በተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ላይ ክፍያ የማግኘት የዋስትና መብት ሲመሰረት፣ ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመሰብሰብ ፈቃድ ያለው የፋይናንስ ተቋም ለዋስትና መብቱ መመሥረት ይሁንታውን ካልሰጠ በስተቀር መብቱና ግዴታው የተጠበቀ ሲሆን ለሦስተኛ ወገኖችም ስለሂሳቡ ማንኛውንም መረጃ እንዲሰጥ አይገደድም፡፡
2. በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ከተከፈተ የተቀማጭ ሂሳብ ላይ ተቋሙ ያለውን ማንኛውም የማቻቻል መብትና በተቀማጭ ሂሳቡ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ክፍያ የማግኘት የዋስትና መብቱን አያውክም፡፡

**ክፍል ሰባት**

**የዋስትና መብት ማስከበር**

76.**ከግዴታ አለመፈፀም በኋላ ስለሚኖሩ መብቶች**

1. ከግዴታ አለመፈጸም በኋላ በመያዣው ላይ ያለ መብትን መጠቀም ዋስትና የተገባለት ግዴታ የማስፈጸም መብት መጠቀምን አያስቀርም፤ ከግዴታ አለመፈጸም በኋላ ዋስትና የተገባለት ግዴታ የማስፈጸም መብትን መጠቀም በመያዣው ላይ ያለ መብት መጠቀምን አይከለክልም፡፡

2. መያዣ ሰጪው እና ዋስትና የተገባለት ግዴታን የመክፈል ወይም የመፈጸም ሃላፊነት ያለበት ሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ሥር ያሉትን መብቶች በራሱ መተው ወይም በስምምነት ማሻሻል አይችልም፡፡
3. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ ክፍል ሥር ያሉትን መብቶች በቅን ልቦና እና ተገቢ በሆነ የንግድ አሠራር መሠረት መጠቀም አለበት፡፡

77. <u>ባልተከበረ ግዴታ ላይ ዳኝነት ስለመጠየቅ</u>

1. ማንኛውም የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ባለመከበራቸው ምክንያት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብቱ በሌላ ሰው የተነካበት ከሆነ ዳኝነት እንዲሰጠው ለፍርድ ቤት ማመልከት የሚችል ሲሆን፣ ይህም በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት መዳኘትን ይጨምራል፡፡
2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በአንቀጽ 82/4/ ላይ የተደነገጉትን የፍትሐብሔር የጨረታ ሽያጭ አፈፃፀም ሥነ ሥርዓቶች በመተላለፍ በባለዕዳው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት አለበት፡፡

78.<u>በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ መብትን ስለማስከበር</u>

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ ያገኘውን የዋስትና መብት በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ማስከበር ይችላል፡፡
2. የአንድ ግዴታ አፈጻጸም በመያዣ ሰጪው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና ከተገባለት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በምርጫው:-
   ሀ) በተንቀሳቃሽ ንብረት የዋስትና መብት ማስከበር ድንጋጌዎች መሠረት በተንቀሳቃሽ ንብረቱ ላይ ያለውን የዋስትና መብት፤
   ለ) በማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና መብት የማስከበር ድንጋጌዎች መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረቱ ላይ ያለውን የዋስትና መብት፤ ወይም
   ሐ) በማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና መብት የማስከበር ድንጋጌዎች መሠረት በሁለቱም ዓይነት ንብረቶች ላይ ያገኘውን የዋስትና መብት፤

ማስከበር ይችላል፡፡

79.<u>መልሶ ስለመውሰድ መብት</u>

1. በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የመብት ማስከበር ሂደት መብቱ የተነካበት ማንኛውም ሰው ተገቢ የሆነ የማስከበር ወጪን ጨምሮ ዋስትና የተገባለት ግዴታን በመክፈል ወይም በመፈጸም መያዣውን መልሶ መውሰድ ይችላል፡፡

2. መያዣ ሰጪው ያለው መያዣውን መልሶ የመውሰድ መብት ሌላ ማንኛውም ሰው መያዣውን ለመውሰድ ካለው መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
3. መያዣውን መልሶ የመውሰድ መብትን መያዣው እስከሚሸጥ፣ ወይም እስከሚተላለፍ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ እስከሚወስደው ወይም ለዚሁ ዓላማ ውሉ እስከሚፈጸም ድረስ መጠቀም ይቻላል፡፡

80.**<u>ቀዳሚ ደረጃ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብቱን ለማስከበር ስለሚኖረው የመሪነት መብት</u>**

1. ሌላ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ወይም በህግ ወይም በፍርድ የገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው የዋስትና መብቱን ማስከበር ቢጀምርም ከነዚህ መብቶች የቀዳሚነት መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ዋስትናው ከመሸጡ፣ ከመተላለፉ ወይም በሌላኛው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከመወሰዱ ወይም ይኸው ገንዘብ ጠያቂ ለዚሁ ዓላማ ውሉን ከመፈጸሙ በፊት በማንኛውም ጊዜ የዋስትና መብት የማስከበር ሂደትን በበላይነት መምራት መጀመር ይችላል፡፡
2. ቀዳሚ ደረጃ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብት የማስከበር ሂደትን በበላይነት የመምራት መብት አንድ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አዋጅ በተደነገገ ማንኛውም መንገድ መብቱን ለማስከበር እንዲችል የተሰጠውን መብት ያካትታል፡፡

81.**<u>ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን በይዞታው ሥር ለማድረግ ስላለው መብት</u>**

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ:-
   ሀ) ያለፍርድ ቤት ማመልከቻ መያዣውን በይዞታው ሥር ማድረግ እንደሚችል መያዣ ሰጪው በዋስትና ስምምነቱ ከፈቀደ፤
   ለ) መያዣውን በይዞታው ሥር ለማድረግ በሚሞክርበት ጊዜ መያዣ ሰጪው ወይም መያዣውን በይዞታው ሥር ያደረገ ማንኛውም ሌላ ሰው ካልተቃወመ፤
   መያዣውን በይዞታው ሥር ማድረግ ይችላል፡፡
2. መያዣ ሰጪው ወይም መያዣውን በይዞታው ሥር ያደረገ ማንኛውም ሌላ ሰው መያዣውን ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የፖሊስ ኃይል ርክክቡን እንዲያስፈጽም የማዘዝ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው፡፡

3. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ሳይወስድ በመያዣ ሰጪው ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳለ አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ለማድረግ ወይም ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

**82.<u>ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ለማስተላለፍ ስላለው መብት</u>**

1. ግዴታ አለመፈጸምን ተከትሎ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ባለበት ሁኔታ ወይም ከንግድ አሠራር አንፃር ተገቢ የሆነ ዝግጅት ወይም ማሻሻያ በማድረግ ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከራየት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ለመስጠት ይችላል፡፡
2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው የሚሸጥበት፣ የሚተላለፍበት፣ የሚከራይበት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ የሚሰጥበትን መንገድ፣ ሁኔታ፣ ጊዜ፣ ቦታና ሌሎች ሁኔታዎች ማመቻቸት ይችላል፡፡ ይህም መያዣውን በተናጠል፣ በከፊል ወይም በጠቅላላ የመሸጥ፣ የማስተላለፍ፣ የማከራየት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ የመስጠት ምርጫን ይጨምራል፡፡
3. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የመያዣውን ባለቤትነት በሐራጅ ለገዛው ሰው ማስተላለፍ፣ ወይም በሁለተኛው ሐራጅ ገዢ ካልቀረበ በመጀመሪያው ሐራጅ በተወሰነው የመነሻ ዋጋ መያዣውን የመውሰድና ባለቤትነቱም እንዲተላለፍለት ማድረግ ይችላል፡፡
4. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ሐራጅን ከመረጠ የጨረታ ሂደቱ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከቁጥር 394-449 በተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው መሠረት መፈጸም አለበት፡፡
5. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈፀም መያዣን ማስተላለፍ መያዣ ሰጪውን በመወከል እንደተፈፀመ ይቆጠራል፡፡

**83.<u>መያዣን ለማስተላለፍ የሚሰጥ ማስታወቂያ</u>**

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን የማስተላለፍ ፍላጎት ካለው የአሥር የሥራ ቀናት ማስታወቂያ:-

ሀ) ለመያዣ ሰጪው እና ለባለዕዳው፤

ለ) በመያዣው ላይ መብት እንዳለው በጽሑፍ ላሳወቀው ማንኛውም ሰው፤

ሐ) የዋስትና መብት ማስታወቂያ ላስመዘገበ ማንኛውም ዋስትና ያለው ሌላ ገንዘብ ጠያቂ፤ እና

መ) ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን በይዞታው ሥር በሚያደርግበት ጊዜ መያዣው ቀደም ሲል በይዞታው ሥር ለነበረ ማንኛውም ዋስትና ያለው ሌላ ገንዘብ ጠያቂ፣

መስጠት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ ማስታወቂያ:-

ሀ) መያዣ ሰጪውን እና ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን፣

ለ) የመያዣውን መግለጫ፣

ሐ) ወለድና ተገቢ የሆነ የማስከበሪያ ወጪ ግምትን ጨምሮ ዋስትናው የተጠበቀ ግዴታን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን፣

መ) የታቀደው ማስተላለፍ ስለሚፈጸምበት ሁኔታ፣

ሠ) ከመቼ ቀን በኋላ መያዣው እንደሚሸጥ፣ እንደሚተላለፍ፣ እንደሚከራይ ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ እንደሚሰጥ ወይም በሐራጅ የሚሸጥበትን ጊዜና ቦታ፤

መግለፅና ማመልከት አለበት፡፡

3. ማስታወቂያው ይዘቱን በተገቢው ሁኔታ ይገልጻል ተብሎ በሚጠበቅ ቋንቋ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ለመያዣ ሰጪው የሚሰጠው ማስታወቂያ የዋስትና ስምምነቱ በተጻፈበት ቋንቋ ከሆነ በቂ ነው፡፡

4. የማስታወቂያው ይዘት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን መረጃ ካካተተ በንዑስ አንቀጹ ከተመለከተው ውጭ የሆነ መረጃ ቢይዝም ወይም ከባድ ስህተት የማያስከትሉ አነስተኛ ግድፈቶች ቢኖሩትም በቂ ይሆናል፡፡

5. ማስታወቂያ መስጠት የማያስፈልገው መያዣው:-

ሀ) ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ይዞታ ሥር ከሆነ በኋላ ያሉት አሥር የሥራ ቀናት ከማለቃቸው በፊት የሚበላሽ ከሆነ፤

ለ) ዋጋው በፍጥነት የሚወርድ ከሆነ፤

ሐ) በታወቀ ገበያ ላይ የሚሸጥ ዓይነት ከሆነ፤

ወይም

መ) ለእንክብካቤውና ለጥበቃው የሚያስፈልገው ወጪ ከዋጋው አንፃር እጅጉን የሚበልጥ ከሆነ፤

ነው፡፡

## 84.ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከመያዣው መተላለፍ የሚገኝ ተያያዥ ገቢን ለማከፋፈል ስላለው መብት

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 መሠረት በሚደረግ የመያዣ ማስተላለፍ ሂደት የሚገኝ ተያያዥ ገቢን፡-

   ሀ) መያዣውን መልሶ ለመውሰድ፣ ለመያዝ፣ ለማስተላለፍ ዝግጁ ለማድረግ፣ ለማሻሻል እና ለማስተላለፍ ለሚወጣ ተገቢ ወጪ፤

   ለ) መያዣውን ለማስተላለፉ መነሻ በሆነው የዋስትና መብት ላይ ያሉ ግዴታዎችን ለመወጣት፤እና

   ሐ) የገቢው ክፍፍል ከመጠናቀቁ በፊት የበታች የሆነ የዋስትና መብት ወይም ሌላ ዋስትና ያለው ሰው ድርሻው እንዲሰጠውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች እንዲፈጸሙ ጥያቄ ካቀረበ፤

   በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ቅደም ተከተል መሠረት ክፍያውን ይፈጽማል፡፡

2. የበታች የሆነ የዋስትና መብት ወይም ሌላ ዋስትና ያለው ሰው ስለጥቅሙ ወይም ስለዋስትና መብቱ ሌላ ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ከተጠየቀ ተገቢውን ማረጋገጫ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልተፈፀመ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) መሠረት የበታች የሆነ የዋስትና ባለመብቱ የሚያቀርብለትን ጥያቄ ለማክበር አይገደድም፡፡

3. በተወዳዳሪ ባለመብቶች መካከል የመብት ወይም የቀዳሚነት ክርክር ሲነሳ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የፍርድ ቤት ወይም ሌላ ሥልጣን ያለው አካል ትዕዛዝን የያዘ ባለመብት እስከሚመጣ ድረስ ተራፊውን ገንዘብ ወለድ በሚያስገኝ ዝግ ሂሳብ ውስጥ እስከ ስልሳ ቀናት ለማስቀመጥና ሂሳቡንም ይዞ ለማቆየት ይችላል፡፡

4. የዋስትና መብት በማስከበር የሚገኘው ገቢ ዋስትናው የተጠበቀ ግዴታን ለመወጣት ከዋለ በኋላ ላልተከፈለው ቀሪ ዕዳ ባለዕዳው ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

5. መያዣ ሰጪው ለተረፈው ገቢ ባለመብት ይሆናል፡፡

## 85.ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ሙሉ ወይም ከፊል የአፈጻጸም መያዣውን ስለመውሰድ

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ሙሉ ወይም ከፊል አፈጻጸም ሲባል አንድ ወይም ከአንድ በላይ የዋስትና መያዣዎችን ለመውሰድ የጽሑፍ ምክረ ሐሳብ መያዣዎቹ ከመተላለፋቸው በፊት ወይም በሚተላለፉበት ጊዜ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ምክረ ሐሳቡን:-
   ሀ) ለመያዣ ሰጪው፤
   ለ) ዋስትና የተገባለት ግዴታ ከፊል አፈጻጸምን በሚመለከት ብቻ ከሆነ ለባለዕዳው፤
   ሐ) ለመያዣ ሰጪው ከመላኩ ወይም መያዣ ሰጪው ምክረ ሐሳቡን ከመቀበሉ አሥር ቀናት አስቀድሞ በመያዣው ላይ ስላለው መብት በጽሑፍ ላሳወቀው ማንኛውም ሰው፤
   መ) ለመያዣ ሰጪው ከመላኩ ወይም መያዣ ሰጪው ምክረ ሐሳቡን የመቀበል መብቱን ከመተው ከአሥር ቀናት አስቀድሞ መያዣውን አስመልክቶ ማስታወቂያ ላስመዘገበ ሌላ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፤ እና
   ሠ) መያዣውን በይዞታው ሥር ባደረገ ጊዜ መያዣው ቀደም ሲል በይዞታው ሥር ለነበረ ሌላ ማንኛውም ዋስትና ያለዉ ገንዘብ ጠያቂ፤

   መላክ ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ ምክረ ሐሳብ:-
   ሀ) ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂንና የመያዣ ሰጪውን ማንነት፤
   ለ)ማስታወቂያው በተላከበት ቀን ያልተከፈለውን ዕዳ ከነወለዱና ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብቱን ለማስከበር ያወጣውን ወጪ እንዲሁም መያዣውን በመውሰድ ግዴታውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን መጠን፤
   ሐ) ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ለግዴታው አፈጻጸም መያዣውን የሚወስደው በሙሉ ወይም በከፊል መሆኑን፤
   መ) መያዣውን፤
   ሠ) ባለዕዳው ወይም መያዣ ሰጪው በአንቀጽ 79 መሠረት መያዣውን መልሶ ለመውሰድ ያለውን መብት፤ እና
   ረ) ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከመቼ ቀን በኋላ እንደሚወሰድ፤

   ለይቶና በዝርዝር መግለፅ አለበት፡፡
4. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን የሚወስደው:-
   ሀ) ዋስትናው ለተጠበቀ ግዴታ ሙሉ አፈጻጸም ከሆነ ማስታወቂያውን የመቀበል መብት ካለው ማንኛውም ሰው ማስታወቂያው በተላከለት አሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ተቃውሞ ካልቀረበለት፣ እና

ለ) ዋስትናው ለተጠበቀ ግዴታ ከፊል አፈጻጸም ከሆነ እያንዳንዱ ማስታወቂያው የተላከለት ሰው ማስታወቂያው በተላከ በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃደኛነቱን በጽሑፍ ካረጋገጠ ብቻ፤

ነው፡፡

86. <u>በመያዣው ላይ ስለሚገኝ መብት</u>

1. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፣ ገዢው ወይም የተላለፈለት ሰው ከሺያጩ ወይም ከአስተላላፊው ሌላ ቀዳሚ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌለ በስተቀር መያዣውን የማስያዝ መብት የሚያገኘው መያዣውን ከሸጠውና የበታች የሆነ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ነጻ በሆነ መንገድ ነው፡፡
2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ካከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከሰጠ፣ ተከራዩ ወይም ፈቃዱ የተሰጠው ሌላ ቀዳሚ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌለ በስተቀር ኪራዩ ወይም ፈቃዱ በሥራ ላይ ባለ ጊዜ የሚያስገኘውን ጥቅም ያገኛል፡፡
3. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ውጭ መያዣውን ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፣ ካከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከሰጠ ገዢው ወይም የተላለፈለት ሰው፣ ተከራዩ ወይም ባለፈቃዱ በመያዣው ላይ መብት ወይም ተጠቃሚነትን የሚያገኘው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች በመጣስ መያዣ ሰጪውን ወይም የሌላን ሰው መብት ጉልህ በሆነ አኳኋን መጉዳቱን ካላወቀ ነው፡፡

87. <u>ከተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነድ፣ በተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ከተደረገ ገንዘብ ወይም ከሴኩሪቲ ክፍያ ስለመሰብሰብ እና ስለመጠየቅ መብት</u>

1. ከግዴታ አለመወጣት በኋላ በተሰብሳቢ ሂሳብ፣ በተላላፊ የገንዘብ ሰነድ ወይም ሴኩሪቲ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከተሰብሳቢው ሂሳብ ባለዕዳ፣ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነዱ ተገዳጅ ወይም ከሴኩሪቲ አውጪው ክፍያ መሰብሰብ ይችላል፡፡
2. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከግዴታ አለመወጣት አስቀድሞ የመያዣ ሰጪውን ፈቃድ ካገኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ክፍያ የመሰብሰብ መብቱን መጠቀም ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ክፍያ የመሰብሰብ መብቱን የሚያስፈጽም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የክፍያ መያዣውን በሚደግፍ ወይም በሚያረጋግጥ ማንኛውም ግላዊ ወይም የንብረት መብት ላይም መብቱን ማስከበር ይችላል፡፡
4. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1)-(3) ባለው መሠረት ክፍያ የመሰብሰብ መብቱን ከአንቀጽ 70 እስከ 74 በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡
5. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ያለውን መብት በአንቀጽ 17 (2) መሠረት በቁጥጥር ስምምነት ተፈጻሚ ካደረገ ብቻ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተቀማጭ ገንዘብ የመቀበል መብት ካላቸው የፋይናንስ ተቋማት ክፍያ መሰብሰብ ይችላል፡፡

88.<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ መብት ሙሉ በሙሉ የተላለፈለት ሰው ስለሚሰበሰበው ክፍያ</u>

የተሰብሳቢ ሂሳብ መብት ሙሉ በሙሉ የተላለፈለት ሰው ክፍያውን አስተላላፊው ግዴታውን ከመወጣቱ በፊት ወይም በኋላ መሰብሰብ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

89. <u>ከቴምብር ቀረጥ ነፃ መሆን</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የዋስትና መብትን ለመመሥረት የሚደረግ ስምምነት ወይም ግብይት ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ነው፡፡

90. <u>ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በተጀመሩ ክርክሮች ላይ ተፈፃሚ አለመሆኑ</u>

1. ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተጀመረ የፍርድ ቤት ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክርክር ላይ የቀደምት ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
2. ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተጀመረ ቀደምት የዋስትና መብት አፈጻጸም በቀደምት ሕግ መሠረት ሊቀጥል ይችላል፡፡

91. <u>መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ</u>

1. በሌሎች ሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች መሠረት:-

   ሀ) የትራንስፖርት ሚኒስቴር በተሽከርካሪዎች፤

   ለ) የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች፤ እና

   ሐ) የንግድ ሚኒስቴር በንግድ ተቋማትና በዱቤ ግዥ ውል፤

በተንቀሳቃሽ ንብረት፣ የዋስትና መብት ምዝገባ ጋር በተገናኘ ያሏቸው መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ተላልፈዋል፡፡

2. ማንኛውም ሌላ መንግሥታዊ ተቋም በሌሎች ሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ድንጋጌዎች መሠረት የሌሎች ግዑዝ እና ግዑዝነት የሌላቸው ተንቀሳቃሽ ሀብቶች የዋስትና መብት ምዝገባ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ያለው መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ለመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ተላልፏል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዑዝ እና ግዑዝነት ለሌለው ሀብት የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት ኃላፊነት የተጣለባቸው ተቋማት ባለቤትነቱን ከማስተላለፋቸው በፊት መብቱ ከዋስትና ነፃ መሆኑን ከዋስትና መዝገብ ማጣራትና ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

92. <u>**ቀደምት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ስላለው ተፈፃሚነት**</u>

1. በቀደምት ሕግ መሠረት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ የነበረ የዋስትና መብት ከዚህ በታች ከተገለጹት አንደኛው በቅድሚያ እስከሚከሰት ድረስ በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ ሆኖ ይቀጥላል:-

   ሀ) በቀደምት ሕግ መሠረት በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ይህ አዋጅ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ባሉት አሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ማብቃት፤ ወይም

   ለ) ይህ አዋጅ ከፀና በኋላ ባሉት አሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ የዋስትና መብቱን በመያዣ መዝገቡ የተመዘገበ እንደሆነ ነው፡፡

2. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በመያዣ ሰጪው እና ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል ቀደምት የዋስትና መብት ለመመስረት በጽሑፍ የተደረገ ስምምነት መያዣ ሰጪው ይህ አዋጅ ከፀና በኋላ ማስታወቂያው እንዲመዘገብ ፈቃደኛነት ያለው መሆኑን ለማሳወቅ በቂ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቀደምት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ከማብቃቱ በፊት የዚህ አዋጅ በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በዚህ አዋጅ መሠረት ቀደምት የዋስትና መብቱ በቀደምት ሕግ መሠረት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቀደምት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ከማብቃቱ በፊት የዚህ አዋጅ በሦስተኛ ወገን ተፈፃሚነት

ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ቀደምት የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈጻሚ የሚሆነዉ በዚህ አዋጅ መሰረት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈጻሚ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ፡፡

93. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጐች</u>

1. በባንክ መያዣ ስለተያዘ ንብረት በወጣው አዋጅ ቁጥር 97/1990 ውስጥ በተንቀሳቃሽ ንብረት የመያዣ መብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ድንጋጌዎች በሙሉ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
2. ስለንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣ አዋጅ ቁጥር 98/1990 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
3. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

94. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

95. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ራሱን የቻለ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በደንብ እስኪቋቋም ድረስ፣ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤትን ለማደራጀት፣ የመያዣ መዝገብ ሥርዓትን ለመዘርጋት፣ ሥራ ለማስጀመር፣ እና ሬጅስትራሩን ለመሾም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

96. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን የ12 ወራት ማለቅ ወይም የመያዣ መዝገቡ ሥራ መጀመር ከሁለቱ በቀደመው በአንደኛው ቀን የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 1 ቀን 2011ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 1205/2012

## የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽንን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

ወረቀትን እና ኮምፒዩተርን ማዕከል ያደረጉ ሰነዶችንና ኢንፎርሜሽኖችን የሚጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በእኩል ሊያስተናግድ፣ እንደዚሁም ዜጎች፣ የግል ድርጅቶችና መንግሥታዊ ተቋሞች የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን እንዲጠቀሙ የሚያስችልና ይህን የሚያሳልጥ አስተማማኝ የህግ ማዕቀፍ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የኤሌክትሮኒክ ንግድን ጥቅም ላይ ማዋል የገበያ አማራጮቻችንን ስለሚያሰፋ፣ በዚህም ዜጎች በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ኢትዮጵያ የዲጂታል ዘመንን እንድትቀላቀል ስለሚያስችል፤

የኤሌክትሮኒክ የመንግስት አገልግሎትን ስራ ላይ ማዋል በየደረጃው ውጤታማ ተጠያቂና ሁሉን ያቀፈ መንግስታዊ ተቋሟችን በመገንባት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ጠቃሚ ስለሆነ፤

በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገምግሰት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ ቁጥር 1205/2012” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡

   1. "መልዕክት ተቀባይ" ማለት የመሐል አገናኞችን ሳይጨምር መልዕክቱን እንዲቀበል በአመንጪው የተወሰነ ሰው ነው፤
   2. “ዶሜን” በአንድ ምድብ የሚካተት የኔትወርክ አካል አድራሻ መለያ ስም ነው፤
   3. “የኮምፒዩተር ኮድ” ማለት አንድ የኮምፒዩተር ሥርዓት ተግባሩን እንዲያከናውን ወይም የታሰበውን ውጤት እንዲያስገኝ የሚያስችል በቃላት፤ በኮድ ወይም በዘዴ የሚገለፅ የመመሪያ ወይም የትዕዛዝ ስብስብ ነው፤

4. “ሶርስ ኮድ” ማለት በጽሁፍ የተቀመጠ በሰው ሊነበብ የሚችል ወደ ማሽን ተነባቢነት ያልተቀየረ የኮምፒዩተር ኮድ ወይም ፕሮግራም ማለት ነው፤
5. “ኦብጀክት ኮድ” ማለት ምንጩ ኮድን በግብዓትነት ለመውሰድ አቀናባሪ በመጠቀም ወደ ማሽን ተነባቢነት የተቀየረ የኮምፒዩተር ኮድ ማለት ነው፤
6. “አልጎሪዝም” ማለት ስልተ ቀመር ሲሆን ስልተ ቀመር ማለት አንድን ችግር ለመፍታት የምንከተለው ቅደም ተከተል ነው፤
7. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤
8. “ኮሙኒኬሽን" ማለት የውል አቀራረብና አቀባበልን ጨምሮ ሰዎች ከኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን ጋር በተያያዘ የሚወስኗቸው ወይም ለውሳኔ የሚመርጧቸው ትዕዛዞች፣ ማስጠንቀቂያዎች፣ ጥያቄዎች፣ ወይም መሰል መልዕክቶች ናቸው፤
9. “የኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ አገልግሎቶች” ማለት የኮሙኒኬሽን መስመሮችን ማቅረብ፣ ለኮሙኒኬሽን ሥርዓት የሚውሉ ግብዓቶችን ማንቀሳቀስ፣ የኮሙኒኬሽን ጭርዓቶችን ተደራሽ ማድረግ፣ ተገልጋይ በለያቸው የመዳረሻ ወይም የመተላለፊያ ነጥቦች መካከል ኢንፎርሜሽን ማስተላለፍ፣ ዳታ መተንተንና ማከማቸት ነው፤
10. “የዳታ መልዕክት” ማለት በኤሌክትሮኒክ፣ በማግኔታዊ፣ በኦፕቲካል ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ የመነጨ፣ የተሳላከ፣ የደረሰ ወይም የተከማቸ ኢንፎርሜሽን ነው፣
11. “ኤሌክትሮኒክ" ማለት ከቴክኖሎጂ አንጻር የኤሌክትሪክ፣ የማግኔታዊ፣ የኦፕቲካል ወይም ሌላ ተመሳሳይ አቅም ያለው የመጠቀሚያ መንገድ ነው፣
12. “የኤሌክትሮኒክ ንግድ” ማለት ኢንተርኔትን ወይም ሌሎች የመረጃ መረብን በመጠቀም የሚደረግ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ግብይት ወይም ልውውጥ ነው
13. "የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽ" ማለት በኢንተርኔት ወይም በሌላ የመረጃ መረብ አማካኝነት ሸቀጦችን በመሸጥ ወይምአገልግሎቶችን በማቅረብ የንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
14. "የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሽ” ማለት በኤሌክትሮኒክ ንግድ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በራሳቸው የንግድ ሥራ ለማካሄድ እንዲችሉ ቀጥታ ተደራሽ የሆኑ ድረገጾችን የሚያቀርብ፣ የሚያቀራርብ፣ ኢንፎርሜሽን የሚለቅና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት ነው፤
15. "ኤሌክትሮኒክ ሰነድ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ቅርጽ ያለ ሰነድ፣ መዝገብ፣ ኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን ወይም ትራንዛክሽን ነው፤

16."ኤሌክትሮኒክ መልዕክት" ማለት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት የመነጨ፣ የተላከ፣ የደረሰ ወይም የተከማቸ ኢንፎርሜሽን ነው፤

17."ኤሌክትሮኒክ መዝገብ" ማለት በኤሌክትሮኒክ መንገድ የመነጨ፣ የተከማቸ፣ የደረሰ ወይም የተሰራጨ የጽሑፍ ሰነድ ወይም መዝገብ ነው፤

18."ኤሌክትሮኒክ ፊርማ" ማለት ከኤሌክትሮኒክስ መልዕክት ጋር በተያያዘ ፈራሚውን ለመለየትና በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ውስጥ የተካተተው ኢንፎርሜሽን በፈራሚው የጸደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውል በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ውስጥ ያለ፣ በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ላይ የተለጠፈ ወይም ከኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ጋር ምክንያታዊ በሆነ አኳኋን የተቆራኘ በኤሌክትሮኒክ መልክ ያለ ኢንፎርሜሽን ነው፤

19."ኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን" ማለት ተንቀሳቃሽ ስልክንና ሌሎች መሰል መሣሪያዎችን ጨምሮ በኮምፒውተር በታገዘ የኢንፎርሜሽን መረብ ሥራን ማከናወን ሲሆን፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድንና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎትን ይጨምራል፤

20. "ዶት ኢቲ ዶሜይን ስም ቦታ" ማለት በአይ ኤስ ኦ 3166-1 ዓለምአቀፍ ደረጃዎች በተደረገው ምደባ መሠረት የኢንተርኔት ሥርዓት ከፍተኛ ደረጃ በሆነው የባለሁለት ፊደል ኮዶች መሠረት ለኢትዮጵያ ተለይቶ የተሰጠ የዶት ኢቲ የአገር መለያ ከፍተኛ ደረጃ ዶሜይን ነው፤

21.“ኢንፎርሜሽን” ማለት ጽሁፍን፣ መልዕክትን፣ ዳታን፣ ድምጽን፣ የዳታ ቋትን፣ ቪዲዮን፣ ምልክቶችን፣ ሶፍትዌርን፣ የኮምፒዩተር ፕሮግራሞችን፣ ኦብጀክት ኮድንና ሶርስ ኮድን ይጨምራል፤

22."የኢንፎርሜሽን ሥርዓት" ማለት ኢንፎርሜሽን የሚያመነጭ፣ የሚልክ፣የሚቀበል፣ የሚያከማች፣ ወይም በሌላ መንገድ የሚተነትን ሥርዓት ነው፤

23.“የመሐል አገናኝ" ማለት አንድን ሰው በመወከል የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን የሚልክ፣ የሚቀበል፣ የሚያከማች፣ ወይም ከኤሌክትሮኒክ መልዕክት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ሰው ነው፤

24."መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሽ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አማካኝነት ሸቀጦችን የሚሸጡ ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾችን በተለያየ ማዕቀፍ አደራጅቶ የሚይዝ ድርጅት ነው፤

25."ሚኒስቴር" ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

26."አመንጪ" ማለት በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት የኤሌክትሮኒክ መልዕክት የላከ ወይም እንዳግባቡ ከማከማቸቱ በፊት ያመነጨ ሲሆን፣ በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ዙሪያ ያሉ የመሐል አገናኞችን አይጨምርም፤

27."ምዝገባ" ማለት የዶሜይን ስም ምዝገባ አገልግሎት አቅራቢዎችንና የዶሚይን ስሞችን የሚመለከቱ ሌሎች ኢንፎርሜሽኖችን ለማከማቸትና መልሶ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ነው፤

28."የደህንነት ሥርዓት" ማለት

ሀ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ወይም የኤሌክትሮኒክ ፊርማ የአንድ የተወሰነ ሰው መሆኑን ማረጋገጥ፣ ወይም

ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች ሲሰራጩ ይዘታቸው ወይም ክምችታቸው ላይ የሚታዩ ግድፈቶችና ለውጦችን አልጎሪዝም እና ኮዶችን በመጠቀም፣ ቃላቶችን ወይም ቁጥሮችን በመለየት፣ የመመስጠሪያ ወይም ታወቁ ሂደቶችንና መሰል መሳሪያዎችን በመጠቀም የመልዕክቶችን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት ነው፡፡

29."ፈራሚ" ማለት የፊርማ መፍጠሪያ ዳታ የያዘ፣ እና በራሱ ወይም ሌላውን ሰው የሚሠራ ሰው ነው፤

30."ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

31.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>**የአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ፥

ሀ) ለሕዝብ አገልግሎት የመስጠት ሥልጣንና ተግባር ባላቸው የፌደራል እና የክልል መንግሥታት፣የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር ተቋማት ላይ እና፣ እንደዚሁም

ለ) በኤሌክትሮኒክ ንግድ፣ በኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎት፣ በኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች፣ በዶት ኢቲ የዶሜይን ስም አስተዳደር፣ እና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ፤ተፈጻሚ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ፦
   ሀ) ጋብቻና ፍቺን ጨምሮ ከግላዊ ሁኔታ ጋር ከተዛመዱ ጉዳዮች፤
   ለ) ከኑዛዜ መስጠት፣ ከኑዛዜ ፎርሞች፣ ኑዛዜን ከመሻር፣ እና ከውርስ አፈጻጸም ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች፤
   ሐ) ከፍርድ ቤት ትዕዛዞች፣ መጥሪያዎች፣ የብርበራና የመያዣ ትዕዛዞች እና ሌሎች መሰል ውሳኔዎች፤
   መ) የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከማስተለለፍ ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች፤ እና
   ሠ) ከህጋዊ የውክልና ጉዳዮች፤

   ጋር በተያያዘ ጽሁፍን ወይም የእጅ ፊርማን እንደ ግዴታ በሚወስዱ ማናቸውም ሕጎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

4. <u>የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አስገዳጅ አለመሆኑ</u>

ማንኛውም ሰው ፈቃደኝነቱን እስካልሰጠ ድረስ በማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴ ወይም ከመንግሥት ተቋማት ጋር ባለው ግንኙነት የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን እንዲጠቀም፣ እንዲያቀርብ ወይም እንዲቀበል አይገደድም።

5. <u>የተቆጣጣሪ ተቋሞች ኃላፊነትና ተግባር</u>

1. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ ይፈጽማል፤ያስፈጽማል፤ ለአዋጁ ተፈጻሚነት ሌሎች መንግሥታዊ እና የግል ተቋሞችን ያስተባብራል፣ ይመራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገጉ ተግባሮችን እና ኃላፊነቶችን ለመፈጸም ሚኒስቴሩ፡-
   ሀ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የብቃት ደረጃዎችን፣
   ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ኮሙኒኬሽንን፣
   ሐ) የመሐል አገናኞች የተጠያቂነት ገደብን፤
   መ) የሸማቾች መብት ጥበቃን
   ሠ) የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች፤
   ረ) የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብን፤
   ሰ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክት አመራር እና አጠባበቅ፤
   ሸ) ዳታን ወደ ኮምፒውተር የማስገባትና የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን የማረጋገጫ ዘዴዎችን፣ እንደዚሁም

ቀ) እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው በሚወሰኑ ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ፣ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

3. የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና ሌሎች ሕጎች መሠረት የዶት ኢቲ የዶሜይን ስም ቦታን የመምራትና የማስተዳደር ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል።

6. **የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ካውንስል መቋቋም**

1. በዚህ አዋጅ የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት ተቋቁሟል።
2. የምክር ቤቱ አባላት ሚኒስትሩን ጨምሮ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።
3. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማል፣ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት በውስጡ ያደራጃል፡፡
4. ካውንስሉ የኤሌክትሮኒክ ግብይት እና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶችን ጨምሮ በዲጂታል ኢኮኖሚ ዙሪያ መንግሥትን የማማከር ሚና አለው።
5. ካውንስሉ አግባብነት ካላቸው ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት የተውጣጡ የሥራ ቡድኖች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ሕጋዊ መስፈርቶች

7. **ሕጋዊ ውጤት**

1. ኢንፎርሜሽን በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ይዘት መቅረቡ ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው አያደርግም።
2. ኢንፎርሜሽን በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ውስጥ ተካቶ አለመቅረቡና ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ባደረገው በዚህ መልዕክት ውስጥ መጠቀሱ ኢንፎርሜሽኑ ለተላከለት ሰው ተደራሽ መሆን የሚችል ከሆነ ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው አያደርግም።

8. **ጽሁፍ**

ማንኛውም ኢንፎርሜሽን በጽሁፍ እንዲቀርብ በሕግ ግዴታ ከተጣለ ይህ ኢንፎርሜሽን በኤሌክትሮኒክ መልክ ከቀረበ ወይም ከተቀመጠ፣ ተደራሽ ከሆነ፣ እና በቀጣይ

ለማመሳከሪያነት መዋል የሚችል ከሆነ የኢንፎርሜሽኑን አቀራረብ አስመልክቶ የተጠየቀው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል።

9. ፊርማ

1. ማንኛውም ሰነድ ፊርማ እንዲያርፍበት በሕግ ግዴታ ከተጣለ እና የትኛው ፊርማ ተቀባይነት እንዳለው ሕጉ ካልገለጸ ፣ በኤሌክትሮኒክስ የቀረበው ፊርማ በሕግ የተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ የሚቆጠረው፦
   ሀ) የግለሰቡን ማንነት ለመለየት እና በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ውስጥ የተካተተው ኢንፎርሜሽን በግለሰቡ የጸደቀ መሆኑን የሚያመላክት ዘዴ ጥቅም ላይ ከዋለ፣ እና
   ለ) ዘዴው ስምምነትን ጨምሮ ያሉ ሌሎች ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ለመነጨበት ወይም ለተሰራጨበት ዓላማ አስተማማኝና ተስማሚ ሆኖ ከቀረበ ብቻ ነው፡፡
2. የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አስተማማኝ ነው የሚባለው፦
   ሀ) ጥቅም ላይ በዋለበት አግባብ፡፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ መፍጠሪያ ዘዴዎቹ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሳይሆን ከፈራሚው ጋር የተቆራኘ ከሆነ፤
   ለ) ፊርማው በሚፈረምበት ወቅት፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ መፍጠሪያ ዘዴዎቹ በሌላ በማንኛውም ሰው ሥር ሳይሆን በራሱ በፈራሚው ቁጥጥር ሥር የነበሩ፣ እና ከግዳጅና ካላስፈላጊ ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ የተፈረመ ከሆነ፤ እና
   ሐ) የኤሌክትሮኒክ ፊርማው ከተፈረመ በኋላ የተደረገ ማንኛውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል ከሆነ፤ ብቻ ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የአንድን ሰው የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ትክክለኛነት ወይም ትክክለኛ አለመሆን በማንኛውም ሕጋዊ መንገድ ማረጋገጥ ይቻላል፣
4. በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን ፊርማን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ተፈጻሚ ይሆናል።

10. ማህተም

ሕግ በሰነድ ላይ ማሕተም እንዲያርፍ ግዴታ ከጣለ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ቅርጽ ከቀረበና በኤሌክትሮኒክ ፊርማ መሠረት የዲጂታል ፊርማ ካረፈበት በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል።

**11. እማኝ**

ሕግ በሰነድ ላይ የእማኞች ፊርማ እንዲያርፍ ግዴታ ከጣለ፣ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ቅርጽ ከቀረበ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተቀመጠው መሥፈርት የሚያሟላ የምስክር የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ካረፈበት በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

**12. ዋና ቅጅ**

1. ሕግ ኢንፎርሜሽን በዋና ቅጅ እንዲቀርብ ወይም እንዲቀመጥ ግዴታ ከጣለ፦
   ሀ) ኢንፎርሜሽኑ የመጨረሻውን ቅርጽ ይዞ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ወይም በሌላ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመነጨበት ጊዜ አንስቶ ያለመቀየሩን የሚያሳይ አስተማማኝ ዋስትና ካለ፤ እና
   ለ) ኢንፎርሜሽኑ በማንኛውም በተፈለገ ጊዜ ጥቅም ላይ ከማዋል አኳያ ተደራሽና የሚነበብ ከሆነ፣

 የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ይህን ቅድመ-ሁኔታ እንዳሟላ ይቆጠራል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ያልተቀየረ መሆኑ የሚመዘነው፡-
   ሀ) ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን፣ ክምችትና ማሳየት ጋር በተያያዘ ከሚጨመሩ ወይም ከሚመነጩ ለውጦች ውጪ ኢንፎርሜሽኑ ምሉዕና ያልተለወጠ ሆኖ መቆየቱን በማገናዘብ፤
   ለ) ኢንፎርሜሽኑ የመነጨበት ዓላማን በመመልከት፤ እና
   ሐ) ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

**13. ተቀባይነት እና የማስረጃ ክብደት**

1. የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች በማንኛውም የሕግ ሂደቶች ተቀባይነት አላቸው፤ እንደ ማስረጃም ያገለግላሉ፡፡
2. የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የማስረጃ ክብደት ሲመዘን፦
   ሀ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የመነጨበት፣ የተከማቸበት ወይም የተሰራጨበት አግባብ አስተማማኝነት፤
   ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ይዘት ሳይቀየር የቆየበት መንገድ አስተማማኝነት፣፤
   ሐ) የመልዕክቱ አመንጪ ተለይቶ የታወቀበት መንገድ፤ እና

መ) ፍርድ ቤት አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያስቀምጣቸው ሌሎች እውነታዎች፤ ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡

14. **ማስቀመጥ**

1. በሕግ ሰነዶች፣ መልዕክቶች እና ኢንፎርሜሽን እንዲቀመጡ ግዴታ ከጣለ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ የሚቆጠረው፦
   - ሀ) በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ውስጥ የሚገኝ ኢንፎርሜሽን ተደራሽ እና በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል የሚችል ከሆነ፤
   - ለ) ኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በተቀረጸበት፣ በተላከበት፣ በደረሰበት ጊዜ በመነሻ የነበረውን ይዘት ጠብቆ ከቆየ ወይም የመልዕክቱ ይዘት ያልተለወጠ መሆኑን ማሳየት የሚቻል ከሆነ፤ እና
   - ሐ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ላኪና ተቀባይን፣ የተላከበትን ወይም የደረሰበትን ቀንና ሰዓትን ማወቅ የሚያስችል ከሆነ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) በተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች ዙሪያ ሶስተኛ ወገኖች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች እንደ በቂ ይቆጠራሉ፡፡
3. ሕግ ወረቀትን ማዕከል ያደረጉ ሰነዶችና መረጃዎች ለተወሰኑ ዓመታቶች እንዲቆዩ የጣለው ግዴታ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተጠቀሱ ሰነዶች፣ መዝገቦችና ኢንፎርሜሽን ላይ ተፈጻሚ ነው።
4. በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ሰነዶች፣ መልዕክቶች ወይም ኢንፎርሜሽን እንዲቀመጡ የተጣለው ግዴታ መልዕክቶችን ለመላክ ወይም ለመቀበል ሲባል ብቻ ጥቅም ላይ በዋሉ መልዕክቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

15. **ቅጅ እና አፃፃፍ**

1. በሕግ ሰነዶች ከአንድ በላይ በሆኑ ቅጂዎች መቀመጥ፣ መቅረብ፣ መላክ ወይም መስጠት አለባቸው በማለት ከደነገገ፤ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ከተቀመጠ፣ ከቀረበ፣ ከተላከ ወይም ከተሰጠ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡
2. በሕግ ሰነዶች በታዘዘው አፃፃፍ እንዲቀርቡ ከደነገገ፣ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት የሆነ ሰነድ በሕግ የተደነገገውን ቅድመ ሁኔታ አሟልቷል የሚባለው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ፦

ሀ) ከታዘዘው ቅርጽ ጋር ተመሳሳይ ወይም በአብዛኛው ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ፎርማት የተደረገ ከሆነ፣፤

ለ) በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል እንዲችል ተደራሽና ሊነበብ የሚችል፤ እና

ሐ) ሌላ ሰው ጋር ሊቀመጥ የሚችል ከሆነ ነው።

16. <u>ክፍያ እና ደረሰኝ</u>

1. ክፍያ እንዲፈፀም የሚጠይቅ ትራንዛክሽን ክፍያው በኤሌክትሮኒክ መንገድ ከተፈፀመና አግባብነት ያለው የመንግሥት ተቋም ያስቀመጣቸው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል። አግባብነት ያለው የመንግስት ተቋም የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፡፡
2. ሕግ የክፍያ ደረሰኝ እንዲሰጥ ግዴታ የሚጥል ከሆነ በሕግ የተቀመጠው ግዴታ እንደተሟላ የሚቆጠረው፦

   ሀ) ደረሰኙ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ቅርጽ የተዘጋጀ፣

   ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የወረቀት ደረሰኝ ይዘትን የሚያሟላ፤ እንደዚሁም

   ሐ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል እንዲችል ተደራሽና ሊነበብ የሚችል፤ ከሆነ ነው፡፡

17. <u>ስለውል አመሠራረት</u>

ከውል አመሠራረት ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒ ካልተስማሙ በስተቀር፣ የውል አቀራረብ፣ የውል አቀባበል፣ የውል አቀራረብ ቀሪ መሆን፣ የውል አቀባበል ቀሪ መሆን፣ ወይም ሌሎች የመረጃ ልውውጦች በሙሉ ወይም በከፊል በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊገለፁ ይችላል።

18. <u>ሕጎችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማተም</u>

ሕግ እንዲታተም ግዴታ ከተጣለ ሕጉ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ከታተመ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል።

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ኮሙኒኬሽን</u>

19. <u>የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ምንጭ</u>

1. ኤሌክትሮኒክ መልዕክት፦

   ሀ) በራሱ በአመንጪው፤

ለ) አመንጪውን እንዲወክል ሥልጣን በተሰጠው ሰው፤ ወይም

ሐ) አውቶማቲክ ሥርዓቱ ፕሮግራም በተደረገው መሠረት አለመሥራቱ ካልተረጋገጠ በስተቀር፤ መልዕክት በራሱ ጊዜ እንዲልክ ተደርጎ ፕሮግራም በተደረገ የአውቶማቲክ ሥርዓት አማካይነት የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በራሱ በአመንጪው ወይም በተወካዩ አማካይነት፤

የተላከ ከሆነ የአመንጪው ነው ተብሎ ይወሰዳል፡፡

2. የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ተቀባዩ መልእክቱ የተላከው ከአመንጪው ነው ብሎ ግምት የሚወስደው፦

ሀ) መልዕክቱ ከኢንፎርሜሽን አመንጪው የተላከ መሆኑን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ስምምነት የተደረሰበት አሠራር ጥቅም ላይ ከዋለ፤ ወይም

ለ) መልዕክቱ ከአመንጪው ወይም ከወኪሉ ጋር ያለው ግንኙነት፣ አመንጪው የሚልካቸው መልዕክቶች የእርሱ እንደሆኑ የሚያሳዩ ዘዴዎችን እንዲያገኝ የተመቻቸለት ሰው ከፈጸማቸው ተግባሮች የመጣ ከሆነ ነው።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው ቢኖርም፤ ከሌሎች ምክንያቶች ባሻገር፡-

ሀ) የመልዕክቱ ተቀባይ መልዕክቱ ከአመንጪው የተላከ እንዳልሆነ በጊዜ እንዲያውቅ መልዕክት ተቀባዩ እርምጃ ለመወሰድ የሚያስችል በቂ ጊዜ የተሰጠው ከሆነ፣ ወይም

ለ) መልዕክት ተቀባዩ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ወይም በአመንጪውና በእርሱ መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት የማረጋገጫ ዘዴ በመከተል፤ መልዕክቱ ከአመንጪው እንዳልሆነ ካወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት መንገድ ካለ፤ የኤሌክትሮኒክ መልእክቱ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡

4. መልዕክት ተቀባዩ መልዕክቱ የመጀመሪያው መልዕክት ቅጅ መሆኑን ካወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ ከሌለ በስተቀር፣ እያንዳንዱን የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን ራሱን የቻለ አዲስ መልዕክት አድርጎ መቁጠርና ለዚህም ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡

## 20. መልዕክት ስለመድረሱ የሚሰጥ ማረጋገጫ

1. መልዕክት አመንጪው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን ስለመቀበሉ ማረጋገጫ እንዲሰጠው ተቀባዩን ሊጠይቅ ይችላል። የመልዕክት አመንጪው ማረጋገጫ የሚሰጥበትን ፎርም ለይቶ ካልወሰነ መልዕክት ተቀባዩ፦

   ሀ) አውቶሜትድ በሆነ ወይም በሌላ መንገድ ምላሽ በመስጠት፤ ወይም

   ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን ስለመቀበሉ አመንጪው እንዲረዳ የሚያደርግ ማናቸውም ተግባርን በመፈጸም መልዕክቱ ስለመድረሱ ሊያረጋግጥ ይችላል።

2. የመረጃ አመንጪው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ከመልዕክት ተቀባዩ ማረጋገጫ ሲሰጠው እንደሆነ ገልጾ ከሆነ፤ ተቀባይ መልዕክቱ ስለመድረሱ የላከው ማረጋገጫ ለአመንጪው እስከሚደርሰው ድረስ መልዕክቱ እንዳልተላከ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

3. ማረጋገጫው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በተደረገው ስምምነት መሠረት ለአመንጪው ካልደረሰ፣ ወይም የጊዜ ገደብ ካልተቀመጠ፣ ወይም ጊዜን አስመልክቶ የተደረሰ ስምምነት ከሌለ ተገቢ ነው ተብሎ በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ ማረጋገጫው ካልደረሰ፣ አመንጪው፦

   ሀ) ከተቀባይ መልዕክቱን ስለመቀበሉ የሚያረጋግጥ መተማመኛ ያልደረሰው መሆኑን ሊያሳውቀው እና ይህን ማረጋገጫ በተወሰነ ቀነ ገደብ ውስጥ እንዲደርሰው ግዴታ ሊያስቀምጥ፤ እና

   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ አመንጪው ከመልዕክት ተቀባዩ ማረጋገጫ ያልደረሰው ከሆነ ለተቀባዩ ቀድሞ የላከለት የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ፈጽሞ አልተላከም ብሎ እንዲቆጥር ማስታወቂያ ሊሰጠውና፣ ያሉትን ሌሎች መብቶቹን ሊጠቀም ይችላል፡፡

4. አመንጪው ከተቀባይ መልዕክቱን ስለመቀበሉ የሚያረጋግጥ መተማመኛ ከተቀበለ የመልዕክቱ ተቀባይ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን እንደተቀበለ ተደርጎ ግምት ይወሰዳል፡፡

5. ማረጋገጫው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ሁለቱ ወገኖች የተስማሙበትን ወይም ደረጃውን በጠበቀ መመዘኛ ተለይተው የተቀመጡ ቴክኒካዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆኑን ከገለጸ እነዚህ የተቀመጡ መስፈርቶች እንደተሟሉ ይገመታል፡፡

21.**የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች የመላኪያ እና የመቀበያ ጊዜና ቦታ**

1. በመልዕክት አመንጪውና በተቀባዩ መካከል በሌላ መንገድ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ተልኳል የሚባለው መልዕክቱ ከመረጃ አመንጪው ወይም ከወኪሉ ውጪ በሆነ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ ሲገባ ነው፡፡
2. በመልዕክት አመንጪውና በተቀባዩ መካከል በሌላ መልክ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ከተቀባዩ ዘንድ ስለመድረሱ በሚከተለው አግባብ ይረጋገጣል፡-
   ሀ) የመልዕክት ተቀባዩ የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን ለመቀበል ሲል የለየው የመረጃ ሥርዓት ካለ መረጃው ደርሷል የሚባለው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በዚህ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ ሲገባ፣ ወይም ተቀባዩ መልዕክቱን ለመቀበል ባልለየው የመረጃ ሥርዓት በኩል የተቀበለ ከሆነ፣ ወይም
   ለ) ተቀባዩ መልዕክት የሚቀበልበትን የመረጃ ሥርዓት ለይቶ ካላስቀመጠ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ደርሶታል የሚባለው የተቀባዩ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ውስጥ ሲገባ ነው፡፡
3. በመልዕክት አመንጪውና በተቀባዩ መካከል በሌላ መልክ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ከአመንጭው የሥራ ቦታ ተልኳል ተብሎ የሚወሰደውና በተቀባይ የሥራ ቦታ ደርሷል የሚባለው፤ ከዚህ በታች ባለው አኳኋን ሲቀርብ ነው፡-
   ሀ) የመልዕክቱ አመንጪ ወይም ተቀባዩ ከአንድ በላይ የሥራ ቦታ ያለው ከሆነ በሁለቱ መካከል ከሚካሄደው ትራንዛክሽን ጋር የቀረበ ግንኙነት ያለው የሥራ ቦታ፤ ወይም ይህ ለግንኙነቱ መሠረት የሆነው ትራንዛክሽን ከሌለ ዋናው የሥራ ቦታ እንዳግባብነቱ የመልዕክቱ የመላኪያ ወይም የመቀበያ ቦታ ተደርጎ ይወሰዳል፤ወይም
   ለ) የመልዕክቱ አመንጪ ወይም ተቀባዩ የሥራ ቦታ የሌለው ከሆነ የመኖሪያ ቦታው እንደ ሥራ ቦታ ያገለግላል።

22.**የለውጥ ወይም የስህተት ውጤት**

1. የኤሌክትሮኒክ መልዕክት በሚተላለፍበት ወቅት ለውጥ ወይም ስህተት ተፈጽሟል የሚባለው የመልዕክት አመንጪው እና ተቀባዩ አንድን የደህንነት ሥርዓትን ጥቅም

ላይ ለማዋል የተስማሙ ከሆነና አንደኛው ወገን ይህን ሥርዓት ተከትሎ ካልፈጸመ ነው፡፡

2. ለውጥ ወይም ስህተት የፈጸመ አካል ለተቀየረው ወይም ለተሳሳተው የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ተጠያቂ ነው፡፡
3. የመልዕክት አመንጪ ወይም ተቀባይ ተጠያቂ የማይሆነው ስህተቱ በወኪሉ የተፈጸመ ከሆነና ወኪሉ ስህተቱ እንዲታረም ዕድል ያላመቻቸ ከሆነ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው መሠረት የተከሰተን ስህተት የተገነዘበ አካል፦
   ሀ) ስህተቱን ወይም ለውጡን ወዲያውኑ ሌላው ሰው እንዲያውቀው ማድረግ እና ለተቀበለው መልዕክት ተጠያዊ እንደማይሆን ማሳወቅ አለበት፤ እንደዚሁም
   ለ) ሌላው ወገን የሚሰጣቸውን ምክንያታዊ የሆኑ ትዕዛዞች ማክበርን ጨምሮ በተሳሳተው መልዕክት መሠረት ያገኘውን ጥቅም የመመለስ፣ የመደምሰስና ሌሎች ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባዋል።

## <u>ንዑስ ክፍል ሶስት</u>

## <u>የመሐል አገናኞች የተጠያቂነት ገደብ</u>

23. **<u>አስተላላፊ</u>**

1. የመሐል አገናኝ ኢንፎርሜሽን የማስተላለፍ አገልግሎቶች በሚሰጥበት ጊዜ ወይም ለቀጥታ መስመር ይፋዊ ግንኙነት ተደራሽነት በሚሰጥበት ጊዜ፦
   ሀ) የቀጥታ መስመር ግንኙነቱን የማይቆጣጠር፤
   ለ) ስርጭቱን የማያመነጭ፤
   ሐ) የስርጭቱን ተቀባይ የማይመርጥ፤ ወይም
   መ) በስርጭቱ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች የማይመርጥ ወይም የማይቀይር፣ ከሆነ ለተላለፈው መረጃ ተጠያቂ አይሆንም፡፡
2. ኢንፎርሜሽን የማስተላለፍ፣ የመላክ እና ተደራሽ የማድረግ ተግባር የአውቶማቲክን፣ የኮምፒውተር ሥርዓት የሂደት ደረጃዎችን እና ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ጊዜያዊ ክምችትን የሚያካትተው፦
   ሀ) ስርጭቱን በመረጃ ሥርዓት ውስጥ ለመልቀቅ ብቻ ከሆነ፣

ለ) ስርጭቱ መልዕክት ተቀባይ ነው ተብሎ ከሚገመተው ሰው ውጭ ለሌላ ሰው ተደራሽ እንዳይሆን ተደርጎ ከተለቀቀ፤ እና

ሐ) ለስርጭቱ ከሚያስፈልገው በላይ ለማይቆይ ጊዜ የሚከማች ከሆነ፣ ነው፡፡

24. <u>ይዞ ማቆየት</u>

የመሐል አገናኙ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ይዞ የሚያቆየው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን ለማግኘት ለጠየቁ ተቀባዮች መልዕክቱን ይበልጥ ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ ለማስተላለፍ ከሆነ፤ እንደዚሁም፦

1. የኤሌክትሮኒክ መዝገቡን ካልቀየረው፤
2. የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ተደራሽነት ሁኔታዎችን ካከበረ፣
3. የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ወቅታዊ ማድረግን በተመለከተ በኢንዱስትሪው ውስጥ በስፋት ዕውቅና ካገኙና ጥቅም ላይ ከዋሉ ደንቦች ጋር የሚስማማ ከሆነ፤
4. በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ዙሪያ መረጃ ከማግኘት ጋር በተያያዘ፣ በኢንዱስትሪው በስፋት ተቀባይነት ካገኘና ጥቅም ላይ ከዋለ ሕጋዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር የማይጣረስ ከሆነ፤ እና
5. የኤሌክትሮኒክ መረጃውን እንዲያስወግድ ወይም ተደራሽ እንዳይሆን ጥያቄ ሲቀርብለት ይህንኑ የሚፈጽም ከሆነ፤

የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን በአውቶማቲክ ፣ በኮምፒውተር ሥርዓቱ የሂደት ደረጃዎች እና ለአጭር ጊዜ በማከማቸቱ ተጠያቂ አይሆንም።

25. <u>ማስቀመጥ</u>

1. የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ክምችትን የሚያካትት አገልግሎት የሚያቀርብ የመሐል አገናኝ ከኢንፎርሜሽን ክምችት ጋር ተያይዞ ለሚነሳ ጉዳት፦

ሀ) ኢንፎርሜሽኑ ወይም ከኢንፎርሜሽኑ ጋር የተያያዘው ተግባር የሶስተኛ ወገን መብትን የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ፣

ለ) የተከማቸውን ኢንፎርሜሽን ሕገ-ወጥ ባህርይ ካወቀ በኋላ ወዲያውኑ ኢንፎርሜሽኑን የማውጣት ወይም እንዲህ ዓይነቱን ኢንፎርሜሽን ማግኘት እንዳይቻል የማድረግ እርምጃ ከወሰደ፣ ወይም

ሐ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሥረት ኢንፎርሜሽኑን እንዲያወርድ ማስታወቂያ ሲደርሰው ኢንፎርሜሽኑን ለማስወገድ ወይም ተደራሽ እንዳይሆን ለማድረግ በፍጥነት እርምጃ ከወሰደ፤

ተጠያቂ አይሆንም፡፡

2. ጥሰት የተፈጸመ መሆኑን በተመለከተ የሚሰጡ ማስታወቂያዎችን እንዲቀበልለት ተወካይ ካልሰየመ እና በሚሰጠው አገልግሎት በኩል በድረ-ገጹ ላይ ጭምር ለህዝብ ተደራሽ በሆኑ ስፍራዎች የተወካዩን ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ ካላሳወቀ በስተቀር፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገጉት የተጠያቂነት ገደቦች በአገልግሎት ሰጪው ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

3. የአገልግሎቱ ተቀባይ ከአገልግሎት አቅራቢው ጋር ሆኖ የሚሰራ ከሆነ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

26.<u>ኢንፎርሜሽን የማግኛ መሳሪያዎች</u>

የመሐል አገናኝ ተገልጋዮችን የሶስተኛ ወገኖችን መብት ወደሚጥሱ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች ወይም የጥሰት ተግባራትን ወደያዙ ድረ-ገጾች የሚያመላክት ወይም ከእነዚህ ድረ ገጾች ጋር የሚያገናኝ ከሆነ፡-

1. ኢንፎርሜሽኑ ወይም ከኢንፎርሜሽኑ ጋር የተያያዘው ተግባር የሶስተኛ ወገኖችን መብት የሚጥስ ስለመሆኑ ግንዛቤ ከሌለው፤
2. የተግባሩ እውነታዎች ወይም ከባቢያዊ ሁኔታዎች ላይ ግንዛቤ ከሌለው፤
3. የሶስተኛ ወገኖች መብትን አስመልክቶ የኢንፎርሜሽኑ ባህርይ ግልጽ ካልሆነ፣
4. ከተግባሩ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያለው የገንዘብ ጥቅም ካላገኘ፤ ወይም
5. የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የሶስተኛ ወገን መብቶችን የሚጥስ መሆኑ ከተገለጸለት በኋላ ከኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ጋር የተያያዙ ኢንፎርሜሽኖችን አግባብነት ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲወገዱ ወይም ተደራሽ እንዳይሆኑ ካደረገ፤

ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

27.<u>የይውረድ ማስታወቂያ ስለመስጠት</u>

1. ለሶስተኛ ወገኖች ተደራሽ ከተደረገ ኢንፎርሜሽን ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን ለመሐል አገናኙ፣ ለሚመለከተው አገልግሎት ሰጪ፣ ወይም ለሕጋዊ ወኪሉ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ቅሬታ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) ኢንፎርሜሽኑ እንዲወርድ ከመጠየቅ ባሻገር፡-
   - ሀ) የአቤቱታ አቅራቢውን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥርና የኢሜል አድራሻ፣
   - ለ) የአቤቱታ አቅራቢውን የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክ ፊርማ፤
   - ሐ) የተጣሱት መብቶች እና ድርጊቱ ሕገወጥ ስለመሆኑ ማብራሪያ፤
   - መ) ክርክሩን ለመፍታት መወሰድ ያለበትን የመፍትሔ እርምጃ፣ እና
   - ሠ) ያቀረበው ቅሬታና ኢንፎርሜሽን ትክክለኛ እና እውነተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫን ማካተት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠ ማስታወቂያ ሃሰት መሆኑ እየታወቀ የቀረበ ከሆነ ማስታወቂያ አቅራቢው በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
4. በሐሰት በቀረበ ማስታወቂያ መሠረት መረጃ የማውረድ ተግባር የፈጸመ የመሐል አገናኝ በኃላፊነት አይጠየቅም፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት

## የሸማቾች መብት ጥበቃ

### 28. የሚቀርቡ መረጃዎች

1. ሸቀጦችን እና አገልግሎቶችን በኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አማካኝነት የሚያቀርብ አቅራቢ፡-
   - ሀ) ሙሉ ስሙን፣ አድራሻውን፡ የስልክ ቁጥሩን፣ የድረ ገጽና የኢሜይል አድራሻውን፣
   - ለ) የዘርፍ ማህበር አባል ከሆነ አባል የሆነበትን የዘርፍ ማህበርና የማህበሩን አድራሻ፣
   - ሐ) አቅራቢው ተገዥ የሆነለትን  የሥነ- ምግባር ደንብና ሸማቹ የሥነ-ምግባር ደንቡን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማግኘት የሚችልበትን አግባብ፣
   - መ) ሕጋዊ የንግድ ተቋም ከሆነ የምዝገባ እና የፈቃድ  ቁጥሮችን፣ የምዝገባ ቦታና የንግድ ተቋሙን ኃላፊዎች ስም፣
   - ሠ) አቅራቢው ሕጋዊ ሰነዶችን የሚቀበልበትን አድራሻ፤

ረ) ሸማቹ ለቀረበለት የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲወስን ለማስቻል በአቅራቢው ስለቀረቡ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ዓበይት ባህሪያት የተሰጠ በቂ መግለጫ፤

ሠ) የትራንስፖርት ወጪዎችን፣ ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎችን ወይም ወጪዎችን ጨምሮ የሸቀጦቹን እና የአገልግሎቶቹን ሙሉ ዋጋ፤

ሸ) ግዥ ለተፈጸመበት ሸቀጥና አገልግሎት ክፍያ የሚፈጸምበት የአገር ውስጥ የባንክ አካውንት ዝርዝርን ጨምሮ የክፍያ መፈጸሚያ መንገድ፤

ቀ) ዋስትናዎችን ጨምሮ ማንኛቸውም ለትራንዛክሽኑ ተፈጻሚ የሚሆኑ ስምምነቶችና እነዚህ ስምምነቶች ሸማቾች በኤሌክትሮኒክ እንዴት ሊያገኙት፣ ሊያከማቹት እና ቅጅ ሊያዘጋጁለት እንደሚችሉ የሚገልጽ ማብራሪያ፤

በ) ሸቀጦቹ ለሸማች የሚላኩበት እና አገልግሎቶቹ ለሸማች የሚደርሱበት ጊዜን፤

ተ) ሸማቾች የግብይቱን ሙሉ መረጃ ማግኘት የሚችሉበት ጊዜ እና ሁኔታ፣

ቸ) የተሸጠ ዕቃን ስለመመለስ፣ ስለመለወጥ እና የተፈጸመን ክፍያ ተመላሽ ማድረግን በሚመለከት አቅራቢው የሚከተለው ፖሊሲ፤

ኀ) አቅራቢው ተገዥ የሆነለት አማራጭ የግጭት መፍቻ ደንብ እና ሸማቹ የዚህን ደንብ ዝርዝር ይዘት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማግኘት የሚችልበት አግባብ፣

ነ) ከክፍያና የሸማቹ ግላዊ መረጃ ጋር በተያያዘ አቅራቢው የሚከተለው የደህንነት ሥርዓቶች እና የሚስጥራዊነት ፖሊሲ፤ እና

ኘ) እንደ አስፈላጊነቱ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች አቅርቦት ቀጣይነት ባለው አኳኋን እንዲሆን ስምምነት ተደርጎ ከሆነ ስምምነቱ ጸንቶ የሚቆይበት አነስተኛው ጊዜ፤ የሚገልጽ ኢንፎርሜሽን ለሸማቹ ሸቀጦቹና አገልግሎቶቹ በሚቀርብበት ድረገጽ ላይ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

2. አቅራቢው ለሸማቾች፡-

ሀ) ሙሉ የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽኑን እንዲገመግሙ፤

ለ) ስህተቶችን እንዲያስተካክሉ፤ እና

ሐ) የግዥ ትዕዛዝ ከመስጠታቸው አስቀድመው ትራንዛክሽኑን ትተው እንዲወጡ፤ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

3. አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2)የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ካላሟላ ሸማቹ ሸቀጦቹን እና አገልግሎቶችን በተቀበለ 14 ቀናት ውስጥ ትራንዛክሽኑን ሊሰርዘው ይችላል።
4. ትራንዛክሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ከተሰረዘ፦
   ሀ) ሸማቹ ከአቅራቢው የመጣለትን ምርት ይመልሳል፤ ወይም እንዳግባብነቱ የቀረበለትን አገልግሎት መጠቀም ያቆማል፣
   ለ) አቅራቢው የተፈጸመውን ሙሉ ክፍያ ተመላሽ ያደርጋል፡፡
5. አቅራቢው ትራንዛክሽሽኑ ለተካሄደበት ጊዜና ለትራንዛክሽኑ የሚመጥን፣ ተቀባይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ደህንነቱ በሚገባ የተረጋገጠ የክፍያ ሥርዓት ይተገብራል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ በሸማቹ ላይ ጉዳት ቢደርስ አቅራቢው ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ነው፡፡

29.<u>ውል ማቋረጥ</u>

1. የሸቀጦቹን ባህርይ ታሳቢ በማድረግ ሸማቹ ያለ ምንም ምክንያት እና ቅጣት ዕቃውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ባሉ በሰባት (7) ቀናት ውስጥ ወይም አገልግሎቶቹን መቀበል ከጀመረበት በኋላ ባሉት ሰባት (7) ቀናት ውስጥ የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽኑን ሊሰርዘው ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ተፈጻሚ ሲሆን በሸማቹ ላይ ሊጣል የሚገባው ክፍያ ሸቀጡን ተመላሽ ለማድረግ የሚወጣ ቀጥተኛ ወጪ ብቻ ነው።
3. ሸማቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸውን መብት ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ለሸቀጦቹ ወይም ለአገልግሎቶቹ ክፍያ ፈጽሞ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው ወጪ ከሙሉ ክፍያው ላይ ተቀናሽ ተደርጎ የማስመለስ መብት አለው፤ ክፍያው ተመላሽ የሚደረግለት ውሉ ከተሰረዘ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ነው።

30.<u>ሸማች ለግዥ ባልጠየቃቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሚደረጉ ኮሙኒኬሽኖች</u>

1. ጥያቄ ባልቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የንግድ ኮሙኒኬሽኖችን ለሸማቾች የሚልክ ማንኛውም ሰው ሸማቹ ስሙ ከዚህ ሰው የመልዕክት ተቀባዮች ዝርዝር ውስጥ እንዲሰረዝ አማራጭ ሊያቀርብለት ይገባል።

2. ጥያቄ ባልቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የንግድ ኮሙኒኬሽኖችን ለሸማቾች የሚልክ ማንኛውም ሰው ሲጠይቀው የሸማቹን ግላዊ ኢንፎርሜሽን ያገኘበትን ምንጭ መስጠት አለበት።
3. ሸማቹ ጥያቄ ባላቀረበበት ጉዳይ ላይ ለቀረበለት የንግድ ኮሙኒኬሽኖች ምላሽ ካልሰጠ በሁለቱ መካከል ስምምነት እንደተፈፀመ ተደርጎ አይወሰድም።

31.<u>የውል አፈፃፀም</u>

1. ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒ ካልተስማሙ በስተቀር አቅራቢው ትዕዛዙን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ ባሉት በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ትዕዛዙን መፈፀም አለበት።
2. አቅራቢው ትዕዛዙን በ30 ቀናት ውስጥ ወይም በሌላ በተስማሙበት ጊዜ ውስጥ ካልፈፀመ ሸማቹ እነዚህ የውል መፈፀሚያ ጊዜዎች እንደተጠናቀቁ የሰባት ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱን ሊሰርዝ ይችላል።
3. አቅራቢው ለማቅረብ የተስማማባቸው ሸቀጦች ወይም አገልግሎቶች የማይገኙ ከመሆናቸው የተነሳ የስምምነት ግዴታዎቹን መፈፀም ካልቻለ ይህንኑ እውነታ ለሸማቹ ወዲያውኑ በማሳወቅ ሸማቹ የፈፀመውን ማንኛውንም ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ ተመላሽ ማድረግ አለበት።

32.<u>የውጭ አገራት ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

ተዋዋዮች ስምምነታቸው የሚገዛበትን የሕግ ሥርዓት አስመልክቶ የተስማሙባቸው ስምምነቶች የትኛውም ይሁኑ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከተው የሸማቾች ጥበቃ ድንጋጌዎች ገዥ ናቸው።

33.<u>ቀሪ የማይደረጉ መብቶች</u>

1. በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱትን መብቶች አጠቃቀም የሚያስቀር ማንኛውም የስምምነት ውል ዋጋ አይኖረውም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በሌላ በማንኛውም ሕግ ውስጥ ለሸማቾች የተሻለ መብት የሚሰጡ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

34.<u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

ሸማቹ በአቅራቢው በኩል የተፈፀሙ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚሜጻረሩ ድርጊቶችን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል።

## ንዑስ ክፍል አምስት

## የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች

35.ሰነድን በኤሌክትሮኒክ መቀበልና መስጠት

1. በሕግ መሠረት ሰነዶችን የሚቀበል፣ የሚያዘጋጅ፣ የሚያስቀምጥ፣ ፈቃድ የሚሠጥ፣ የክፍያ ሥርዓት የዘረጋ ማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም ሰነዶችን፣ ፈቃዶችን፣ ወይም የክፍያ ሥርዓቶችን በኤሌክትሮኒክ ቅርጽ ወይም መንገድ ሊቀበል፣ ሊያዘጋጅ እና ሊሰጥ ይችላል።
2. አንድ የመንግስት ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ተግባራት ሲያከናውን፦
   ሀ) የመዝገብ አያያዝ ሁኔታ፣ የሰነዶች ቅርጽ እና መልዕክቶች የሚሰራጩበትን አግባብ፤
   ለ) በኤሌክትሮኒክ ሰነድ ላይ ፊርማ የሚያርፍበትን ቦታ እና ጥቅም ላይ የሚውለውን የፊርማ ዓይነት፣
   ሐ) የኤሌክትሮኒክ ፊርማ የሚያርፍበትን አግባብና ዘዴ እና በሰርተፊኬት ሰጪ ባለሥልጣን ከተቀመጠው ሁኔታ ጋር የማይቃረኑ ተፈላጊ መስፈርቶች፤
   መ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶችን ትክክለኛነትና ዋና ቅጅ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና በአስተማማኝ ሁኔታ ተጠብቀው የሚቆዩበትን ሁኔታ ለመፈተሽ ጥቅም ላይ የሚውል ሥርዓት፤ እና
   ሠ) ከላይ ከተጠቀሱት ሰነዶች ጋር የተገናኘ ለኤሌክትሮኒክ መልዕክት እና የክፍያ ዘዴዎች ጠቃሚ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች አስፈላጊ ክፍሎችን፤ ለይቶ በዝርዝር ሊወስን ይችላል።
3. የመንግስት ተቋማት ለኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች እና ለኤሌክትሮኒክ ፊርማዎች አጠቃቀም የላቁ የደህንነት መስፈርቶችን መጠቀም አለባቸው።
4. የመንግስት ተቋማት ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን መስጠት መጀመር አለባቸው።

36.የፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ መቋቋም

1. የፌደራል የሕግ ጋዜጣ የሆነ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

   ሀ) ማንኛውም የፌደራል መንግሥት ሕግ የሚወጣው በፌደራሉ የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ ነው፤

   ለ) ማንኛውም የፌደራል እና የክልል ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚ፣ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም ሰው በፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ አለበት፤

   ሐ) የፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ የሚታተመው በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ነው፤ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል፡፡

3. ማንኛውም ህግ በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ይወጣል፡፡

37.<u>**የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ መቋቋም**</u>

1. የፌደራል የሕግ ጋዜጣ የሆነ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት  የሚወጣ የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎችተ መዝገብ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

   ሀ) ማንኛውም የፌደራል አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸው መመሪያዎች የሚወጡት በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ነው፤

   ለ) ማንኛውም የፌደራል እና የክልል ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚ፣ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ አለበት፣

   ሐ) የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ የሚታተመው በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ነው፤ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል።
3. መመሪያዎች በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ታትሞ የወጡበት ቀን ሕጉ የታተመበት ቀን እንደሆነ ይቆጠራል።
4. የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብን ቴክኒካዊ ጉዳዮች ያስተዳድራል።

5. በንዑስ አንቀጽ (4) የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ይችል ዘንድ፣ የፌደራሉ አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸውን መመሪያዎች፣ ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት የወረቀት እና የኤሌክትሮኒክ ቅጅዎች ለሚኒስቴሩ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፤ እነዚህ ቅጅዎች በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ መቅረብ አለባቸው።

## ክፍል ሶስት

## የዶሜን ስም ማኔጅመንት

38.**የዶሜን ስም ሬጂስትራር**

ባለሥልጣኑ የዶሜን ስም ሬጅስትራር በመሆን ያገለግላል፣ የዶሜን ስም ማኔጅመንት የሥራ ክፍል ይፈጥራል።

39.**የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ኃላፊነት**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦
   ሀ) የኢቲ ዶሜይን ስም ቦታን ያስተዳድራል፣ ይመራል፤
   ለ ለመዝጋቢ ተቋሞች ፈቃድ ይሰጣል ፤ይቆጣጠራል፤
   ሐ) ለመዝጋቢ ወኪሎች ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል፤
   መ) የኢቲ ዶሜይን ስም ቦታን በማስተዳደር ረገድ የተገኙ የተሻሉ ዓለማቀፋዊ ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ፥
   ሀ) አጠቃላይ የዶት ኢቲ ዶሜይን ስም ቦታ አስተዳደር እና ማኔጅመንትን፤
   ለ) ለዶሜይን ስም ምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና ሥነ-ሥርዓቶችን፤ እና
   ሐ) የምዝገባ ሰነዱ አያያዝና ተጠቃሚዎች ከሰነዱ መረጃ የሚያገኙበት አግባብ፤ በተመለከተ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የዶሜይን ስም ምዝገባ በሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ ይሠራል።
4. ባለሥልጣኑ ከዶሜይን ስም ቁጥጥር ጋር በተያያዘ፦
   ሀ) አስፈላጊ ናቸው ብሎ ባመናቸው ጉዳዮች ላይ ምርመራዎችን ሊያካሂድ ይችላል፣
   ለ) በአገር ውስጥና በሌሎች አካባቢዎች ከዶሜይን ስም ሥርዓት ጋር በተያያዘ በታዩ ለውጦች ዙሪያ ምርምሮችን ያካሂዳል፤

ሐ) የዶት ኢቲ ዶሜይን ስም የዜጎችን ፍላጎት በምን ያህል ደረጃ እንዳሟላ በቀጣይነት ያጠናል፣ ይገመግማል፤ እና

መ) በኢትዮጵያ የሚካሄድ የዶሜይን ስም ምዝገባን የሚመለከቱ መረጃዎችን ሊያሰራጭ ይችላል፡፡

5. ባለሥልጣኑ ይህ አዋጅ ፀድቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጠሩ የዶት ኢቲ ዶሜይን ስም ቦታን የመምራትና የማስተዳደር ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውንም ተቋም መብቶችና ጥቅሞችን ይጠብቃል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተጠቀሱት እና በዶት ኢቲ ዶሜይን ማኔጅመንትና አስተዳደር ላይ የራሳቸው መብቶችና ጥቅሞች ያሏቸው ተቋሞች፥

ሀ) በውክልና በያዟቸው ንዑስ ዶሜይኖች ላይ ለስድስት ወራት ያህል ጊዜ እንዲሠሩ፤ እና

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰው የስድስት ወር ጊዜ ካበቃ በኋላ በመዝጋቢነት እንዲመደቡ፣ ከሌሎች በተለየ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

40.<u>የዶሜይን ስሞችን ያለፈቃድ ማስተዳደር</u>

1. ፈቃድ ሳይሰጠው ሁለተኛ ደረጃ የዶሜይን ስምን ያስተዳደረ፣ የመራ ወይም ሥራ ላይ ያዋለ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ድርጊት በመፈፀሙ ምክንያት በሶስተኛ ወገን ጥቅም ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ወይም ተከሳሹ ድርጊቱን የተፈፀመው ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገን ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት አስቦ ከሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሰው ድርጊት የተፈፀመው በህግ ሰውነት በተሰጠው ተቋም በሆነ ጊዜ እንደ አግባብነቱ ከብር አንድ መቶ ሺህ (100,000 )ብር በማያንስ የገንዘብ ቅጣት የሚሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

41.<u>የአንቀሳቃሾች ግዴታዎች</u>

1. የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች፤ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች፣ እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ አንቀሳቃሾች እንደ ንግድ ተቋማት ዕውቅና ይሰጣቸዋል፤ የንግድ ተቋማት የሚገዙባቸው ሕጎችም በእነሱ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2. የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በእነርሱ ፕላትፎርም ላይ ሸቀጦች ወይም አገልግሎቶች ሊያቀርቡ ከሚፈልጉ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ማንነታቸውን፣ አድራሻና ተዛማጅ መረጃን፣ ፈቃዳቸውን እና ሌሎች መሠል መረጃዎች እንዲያቀርቡላቸው መጠየቅ አለባቸው፤ የእነዚህንም መረጃዎች ትክክለኛነት ማጣራት፣ መመዝገብ፣ መረጃዎቹን በየጊዜው ማስተካከልና ማረም አለባቸው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ በኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ላይ የተጣሉ ግዴታዎች በኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ አንቀሳቃሾች ላይ ተፈፃሚ ናቸው፡፡
4. አንቀሳቃሾች ለገበያ ከሚያቀርቧቸው ምርት እና አገልግሎት ውስጥ 50% የሚያህለው የአገር ውስጥ ምርት እና አገልግሎት መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
5. የፈጣን መልዕክት አገልግሎት ሰጪዎች በኤሌክትሮኒክ ግብይት ውስጥ ያላቸው ሚና እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

42.<u>አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገዶች</u>

1. የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አመቻቾች አለመግባባቶችን የመፍቻ አማራጭ መንገዶች መቀየስ አለባቸው፡፡
2. ባለሥልጣኑ የዶሜይን ስም ማኔጅመንትና አስተዳደርን አስመልክቶ አለመግባባቶችን የሚፈታበት አማራጭ መንገዶችን መቀየስ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች መፍትሔ ያላገኙ በዚህ አዋጅ፣ እና ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በተመሠረተ የግልግል የዳኝነት ሥርዓት ቀርቦ እልባት ያገኛል፡፡

43.<u>ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ</u>

1. በዚህ አዋጅ ወይም አግባብነት ባለው በሌላ ሕግ ከተፈቀደላቸው ሰዎች በስተቀር የኤሌክትሮኒክስ መልዕክቶችን፣ ሌሎች የጽሑፍ ሰነዶችን ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ማግኘት የሚችል ማንኛውም ሰው በዚህ አግባብ ያገኘውን ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት።
2. በዚህ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው የተጣሰ እንደሆነ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት የሚያሰቀጣ ይሆናል፡፡

**44.ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

**45.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚወጣ ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።
3. ባለሥልጣኑ ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚወጡ ደንቦች በሚመነጩ ጉዳዮች ላይ መመሪያ ማውጣት ይችላል።

**46.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በምክር ቤቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

<u>መ/ ኢንዱስትሪ ልማት</u>

## አዋጅ ቁጥር 886/2007

## የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ

የአገሪቱን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንና ልማትን ሊያፋጥኑ የሚችሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በተመረጡ አካባቢዎች በማቋቋም ውጤታማ የአገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ኢንዱስትሪዎችን ማሳደግና ተዛማጅ የስራ እድል መፍጠር በማስፈለጉ፤

የኤክስፖርት ልማት ማሳደግን፣ የአካባቢና የሰው ደኅንነት መጠበቅን እና በቁጠባ መሬት መጠቀምን እንዲሁም የከተሞች ዕድገት በዕቅድና በስርዓት የመምራትን አስፈላጊነት በመገንዘብ፤

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለማቋቋም፣ የአሰራር፣ የልማት፣ የአስተዳደር እና የቁጥጥር ስርዓትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመለከት የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት ያለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ በመረዳት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ኢንዱስትሪ ፓርክ" ማለት የኢንዱስትሪ እድገትን፣ ብክለት በአካባቢና በሰው ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ መቀነስንና የከተሞች ዕድገት በዕቅድና በስርዓት መምራት ዓበይት ዓላማዎችን የያዘ ሆኖ ዕቅድን መሰረት አድርጎ እንደ መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ውሃ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እና የመሳሰሉ አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች ተሟልተውለት እና ልዩ የማበረታቻ ዕቅድ ኖሮት፣ ሁሉን-አቀፍ፣ የተቀናጀ፣ ፈርጀ-ብዙ ወይም አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎች በተመጋጋቢነት ለማልማት የሚቋቋም፣ ድንበር የተበጀለት

በቦርድ የተሰየመ የተወሰነ ቦታ ሲሆን ልዩ የኢኮኖሚ ቀጠና፣ የቴክኖሎጂ ፓርክን፣ የኤክስፖርት ማቀነባበሪያ ቀጠናን፣ የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ቀጠናን፣ ነፃ የንግድ ቀጠናን እና ሌሎች ተመሳሳይ በኢንቨስትመንት ቦርድ የሚሰየሙትን ይጨምራል፤

2. "ሀብት" ማለት ማንኛውም ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ የመንግሥት፣ የመንግሥትና የግል ወይም የግል ንብረት መብትና ጥቅም ሆኖ የማይንቀሳቀስ፣ የሚንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት የሌለው ንብረት ነው፤
3. "መሬት" ማለት ለኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ዓላማ የተሰየመ ማንኛውም መሬት ነው፤
4. "የለማ መሬት" ማለት እንደ መንገድ ፣ ውኃ ፣ ማብራት ፣ ስልክ ፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት ፣ የአየር ብክለት መቀነሻ ስርዓት እና የመሣሰሉ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች የተሟሉለት መሬት ነው፤
5. "ሊዝ" ማለት በጊዜ በተገደበ ውል መሠረት የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት የመጠቀም መብት የሚገኝበት የመሬት ይዞታ ስሪት ነው፤
6. "ማልማት መጀመር" ማለት እንደአገባቡ፡-

ሀ) የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ሲሆን እንደ መንገድ፣ ውኃ፣ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ስልክ፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ እና የመሣሰሉ አስፈላጊ መሠረት ልማቶች እንዲሁም ሕንፃዎችን ግንባታ የመሠረት ሥራ መጀመር ነው፤

ለ) የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ሲሆን በኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ላይ ለመስራት ከተፈቀደው ግንባታ ወይም ሕንጻ ቢያንስ የመሠረት ሥራ መሥራትና የኮለን ግንባታ ለማከናወን የሚያስችሉ የኮለን ብረቶች የማቆም ስራ ማጠናቀቅ ነው፤

7. "ንዑስ ሊዝ" ማለት የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው በምደባ ወይም በሊዝ ወስዶ ካለማው የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ቆርሶ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ማስተላለፍ ነው፤
8. "ኢንቨስትመንት" ማለት የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በተሰጠው ፈቃድ እና በገባው ስምምነት መሰረት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ እንደአግባቡ አዲስ ወይም ነባር የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማልማት፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማስተዳደር፣ የኢንዱስትሪ

ፓርክ ድርጅት ለማቋቋም፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤

9. “ኮርፖሬሽን” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 326/2007 የተቋቋመው የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ኮርፖሬሽን ነው፤
10. “ኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ” ማለት በኢንቨስትመንት አዋጅ እና በኢንቨስትመንት ደንብ፣ በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ፈቃድ እና በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ስምምነት መሠረት የመንግሥት፣ የመንግሥትና የግል በቅንጅት ወይም የግል አልሚን እንዲሁም ኮርፖሬሽኑን ጨምሮ የኢንዱስትሪ ፓርክን ዲዛይን የሚያደርግ፣ የሚገነባ እና የሚያለማ ማንኛውም ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤
11. “ኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ” ማለት በኢንቨስትመንት አዋጅ እና በኢንቨስትመንት ደንብ መሠረት በተሰጠው በኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ፈቃድ እና በኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ስምምነት መሰረት ኢንዱስትሪ ፓርኩን የሚያስተዳድር፣ የሚንከባከብና የሚያስተዋውቅ ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ኮርፖሬሽኑን ይጨምራል፤
12. “ኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት” ማለት በኢንቨስትመንት አዋጅ እና በኢንቨስትመንት ደንብ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ፈቃድና በኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ስምምነት መሠረት በግል፣ በመንግስት ወይም በመንግሥትና በግል በቅንጅት የሚተዳደር በኢትዮጵያውያን ወይም በውጭ ሀገር ባለሀብቶች ወይም በቅንጅት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የለማ መሬትን በንዑስ ሊዝ ወስዶ ገንብቶ ወይም የተገነባ የፋብሪካ ሕንፃን ተከራይቶ ወይም ገዝቶ ምርት የሚያመርት ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛዉም ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤
13. “ኢንቨስትመንት አዋጅ” እና “ኢንቨስትመንት ደንብ” ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 (እንደተሻሻለው) እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 (እንደተሻሻለው) ነው፤
14. “ስምምነት” ማለት እንደአገባቡ፡-

ሀ) በኮሚሽኑ እና በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው መካከል የኢንዱስትሪ ፓርክን ዲዛይን ለማድረግ፣ ለመገንባት፣ ለማልማት እና በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ሌሎች አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚደረግ፣

ለ) በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ እና በኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው መካከል የኢንዱስትሪ ለማስተዳደር፣ ለመንከባከብ፣ ለማስተዋወቅ ወይም ሌሎች ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር ተያያዥነት ያላቸውንና የተመረጡ የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ የሚደረግ፣ ወይም

ሐ) የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው ከኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ጋር የሚያደርገው፤

ስምምነት ነው፤

15. “የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ” ማለት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ሆኖ ለመኖሪያ በተፈቀደ ቦታ እንዲኖር በኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀት የተሰጠዉ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

16. “መንግስት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ወይም የክልል መንግስት ነው፤

17. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47(1) ላይ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

18. “ቦርድ” እና “ኮሚሽን” ማለት በደንብ ቁጥር 313/2006 የተቋቋመዉ እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤

19. “አግባብ ያለው ባለስልጣን” ማለት የኢንዱስትሪ ፓርክን በሚመለከት በተወሰኑ ጉዳዮች ወይም መልክዓ-ምድራዊ ቦታዎች ላይ የቁጥጥር ሥልጣንና ኃላፊነት ያለው የፌደራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር መንግሥታዊ አካል ነው፤

20. “ፈቃድ” ማለት በኮሚሽኑ አማካይነት ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ወይም ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት የሚሰጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ነው፤

21.“የጉምሩክ ክልል” ማለት ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር አግባብነት ያላቸው በስራ ላይ ያሉ የሀገሪቱ የጉምሩክ ሕጎች ተግባራዊ የሚሆኑበት የኢትዮጵያ ግዛት ክልል ነው፤

22.“የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ቁጥጥር ክልል” ማለት የኢንዱስትሪ ፓርክ አካል የሆነ የጉምሩክ ቁጥጥር የሚደረግበት ነገር ግን ከጉምሩክ ክልል ውጪ እንደሆነ የሚቆጠር ቦታ ነው፤

23.“አግባብነት ያለው ሕግ” ማለት በዚህ አዋጅና በማስፈፀሚያ ደንብ ትርጓሜ መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተፈፃሚነት ያላቸው ሁሉም የሀገሪቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ናቸው፤

24.“ደንብ” ማለት ይህ አዋጅ ለማስፈፀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚያወጣው ደንብ ነው፤

25.“የሶስትዮሽ አሰራር” ማለት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር፣ እንደሁኔታው የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ የአስተደዳሪ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት አሠሪዎች እና የሠራተኛ ተወካይ የሠራተኛ ጉዳዮችን በጋራ ሆነው በውይይትና ምክክር መፍትሄ የሚያስቀምጡት አግባብ ነው፤

26.“መሠረታዊ አገልግሎት” ማለት ከኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ጋር በተያያዘ የውኃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ፣ የጋዝ እና ሌሎች በደንብ የሚወሰኑ አገልግሎቶች ናቸው፡

27.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

28.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ግዛት ወሰን ውስጥ ወጥነት ባለው መልኩ በፌዴራል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ እና በውስጣቸው በሚከናወኑ ተግባራት እና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት በፌዴራል የኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በሚያከናውኑ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4. **<u>የአዋጁ ዓላማዎች</u>**

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የኢንዱስትሪ ፓርኮች አሰያየም፣ ልማት እና አሰራር ስርዓት መዘርጋት፤
2. የሀገሪቱ የቴክኖሎጂና የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ዕድገት ላይ አስተዋፅኦ ማድረግ፤
3. የግሉን ኢንቨስትመንት ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪዎችና ተዛማጅ ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሳተፍ ማበረታታት፤
4. የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት ተወዳዳሪነት ማጐልበት፤
5. ሰፊ የሥራ ዕድሎች መፍጠርና ቀጣይ የኢኮኖሚ ልማት ማስገኘት።

## ክፍል ሁለት

## የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚና የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ

### 5. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ መብቶች

ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

1. የኢንዱስትሪ ፓርክን ዲዛይን የማድረግ፣ የማልማት ፣ የመገንባት፣ የመጠቀምና አገልግሎት የማቅረብ፤
2. የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክ መሬትን በንዑስ ሊዝ የማስተላለፍ፤
3. በደንብ በሚወሰነው መጠን መሰረት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለማምረቻ ለቢሮ፣ ለመኖሪያና ለመሣሰሉት አግልግሎቶች ራሱ የገነባቸውን የማይንቀሳቀሱ ሀብቶችን፣ ሕንፃዎችን ወይም ክፍሎችን ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የማከራየት ወይም የመሸጥ፤
4. የኢንዱስትሪ ፓርኩን መሬትን ለማልማት፣ ለማስተዳደርና ለማስተዋወቅ ንዑስ-ሊዝ ስምምነት የማድረግ፤
5. ያለማውን መሬት በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ስምምነት መሰረት ማስተዳደር መንከባከብ እና ማስተዋወቅ፤
6. በደንቡ መሠረት ኢትዮጵያዊያንና የውጭ ሀገር ዜጎች መቅጠር፤
7. ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ተለይተው በሚቀመጥ አሰራር መሠረት የብድር፣ የገንዘብ ዋስትናና ሌሎች የገንዘብ ምንጮችን ለማግኘት በፋይናንስ ገበያ ላይ የመሳተፍ፤

8. ከመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር በሚደረስ የኮሚሽን ስምምነት መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለተሰማሩ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች መሠረታዊ አገልግሎቶቹን የማቅረብ፣ ክፍያዎችንም የመሰብሰብ፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤
9. አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መሆንና ሌሎች ማበረታቻዎችን የማግኘት፡፡

6. **<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. በተሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፈቃድ እና በተገባው የኢንዱስትሪ ፓርክ ስምምነት መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ቋሚ ንብረት የመገንባት፣ መሠረተ ልማት የመዘርጋት፣ ለአንድ ማዕከል አገልግሎትና ለጉምሩክና ገቢዎች ባለሥልጣን መጠቀሚያ የሚውል ቢሮዎችና ቁሳቁሶች የመሟላት፤
2. በኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ዲዛይን ሥራ ላይ የአገር ውስጥ የሥልጠና ተቋማት የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
3. በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ስምምነት ሰነድ ውስጥ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማልማት የመጀመር፤
4. በስምምነቱ እና ፈቃዱ ላይ በሚቀመጠው መሰረት ተከፋፍሎ ለሚለማው ኢንዱስትሪ ፓርክ እንዲሁም ማንኛውም የፋይናንስ ግዴታዎች የካፒታልና የገንዘብ ብድር የጊዜ ሰንጠረዥ የአሰራር ሁኔታዎችን የማክበር፤
5. አስተማማኝ የገንዘብ ምንጫቸው የሚመለከት መረጃ የማቅረብ፤
6. ያልለማ የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬትን በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም፤
7. በዚህ አዋጅ፣ ደንብና አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በተሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩት ሌሎች ግዴታዎችን የማክበር፤
8. በደንብ በሚወሰነው መሠረት ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች አስፈላጊውን ሥልጠና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የውጭ ዜጎች ሠራተኞች ወይም ባለሙያዎች በኢትዮጵያዊያን እንዲተኩ ማድረግ።

7. **የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ መብቶች**

ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. የኢንዱስትሪ ፓርክን የለማ መሬትና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚውን ወክሎ በንዑስ ሊዝ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ማስተላለፍ፤ መሠረታዊ አገልግሎቶችንና ሌሎች አገልግሎቶችን በክፍያ የማቅረብ፤
2. በኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ስምምነት መሠረት የኢንዱስትሪ ፓርክን የማስተዳደር፣ የመንከብከብ እና የማስተዋወቅ፤
3. በደንቡ መሠረት ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ዜጎችን የመቅጠር፤
4. በዚህ አዋጅ፣ በደንቡ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተቀመጡትን መብቶች የመጠቀም፡፡

8. **የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ግዴታዎች**

ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

1. ይህን አዋጅ ፣ ደንቡን እና የገባውን የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳደር ስምምነትና የተሰጠውን ፈቃድ ሁኔታዎችን የማክበር፤
2. በተሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ፈቃድ መሰረት ኢንዱስትሪ ፓርክን ማስተዳደር፣ መንከባከብ፣ ማስተዋወቅ እና የኢንዱስትሪ ፓርኩ መሠረታዊ አገልግሎቶችና ሌሎች ንብረቶች በማንኛውም ጊዜ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነው የሚቆዩበትን ሁኔታ የመጠበቅ፤
3. ለአንድ ማዕከል አገልግሎትና ለጉምሩክ ሥራዎች የሚሆን የቢሮ ቦታና ሌሎች አቅርቦቶችን ዝግጁ ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ፤
4. ያልለማ የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬትን በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም፤
5. የአገር ውስጥ አምራች ድርጅቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር በማስተሳሰር የቴክኖሎጂ አቅም እንዲገነቡና ከዓለም አቀፍ ገበያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ፤
6. በዚህ አዋጅና ደንብ፣ አግባብነት ባላቸው ህጎች ወይም በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ማህበራዊና አካባቢያዊ ግዴታዎች እና ሌላ ማንኛውም ግዴታዎች የማክበር፤

7. በደንብ በሚወሰነው መሠረት ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች አስፈላጊውን ሥልጠና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የውጭ ዜጎች ሠራተኞች ወይም ባለሙያዎች በኢትዮጵያዊያን እንዲተኩ ማድረግ፡፡

## ክፍል ሶስት

## የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት እና ኢንቨስትመንት

### 9. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት መብቶች

ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የኢንቨስትመንት ሥራ ለመሥራት በቅድሚያ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ፈቃድ ማግኘት ይችላል፤ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ስለሚቀርብበት አሰራር እና መስፈርቶቹ እንዲሁም ውሳኔ ስለሚሰጥበት አሰራር በደንብ ላይ ይወሰናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) በተገለፀው መሰረት ፈቃድ ካገኘ በኋላ አግባብነት ባለው ሕግ የተገለፁትን የግብር፣ የጉምሩክ እና ሌሎች ማበረታቻዎችን ያገኛል፤
3. በደንቡ በሚገለፀው መሠረት የህዝብን ሠላም፣ ሞራል፤ ደህንነትና ጥበቃ እንዲሁም የሰውና የእንስሳት ጤንነትንና የዕፅዋትን ህይወት አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ በተሰጣቸው የኢንዱስትሪ ፓርክ ፈቃድ መሰረት የኢንቨስትመንት ሥራዎችን በነፃነት ይሠራል፤
4. የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬትን በንዑስ ሊዝ መሠረት የማግኘትና የመያዝ፣ የራሱን ሕንጻ የመሸጥ፣ ሌሎች የማይንቀሣቀሡ ሀብቶችን በኪራይ የመያዝ፤ በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሕጎች ላይ በተቀመጡት የጉምሩክ አሠራሮች መሠረት ዕቃዎች እና አገልግሎቶችን ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የማስገባት፣ በኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ቁጥጥር ክልል ውስጥ የመሸጥ መብት ይኖረዋል።

### 10. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ግዴታዎች

ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ፈቃድ እና ስምምነት ሰነድ ውስጥ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማልማት የመጀመር፤

2. በተሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ ፈቃድ መሠረት ኢንቨስትመንት ስራዎችን የማካሄድ፤
3. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ የትብብር ስልጠና እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኢንተርንሺፕ ስልጠና በኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቱ ውስጥ እንዲካሄድ የመፍቀድ፤
4. ይህንን አዋጅ፣ ደንብ፣ እና አግባብነት ያላቸው ሕጎችን እንዲሁም በነዚህ ሕጎች በተጠቀሱት መሠረት አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊና የአሰሪ ግዴታዎችን የማክበር፤
5. በደንብ በሚወሰነው መሠረት ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች አስፈላጊውን ሥልጠና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የውጭ ዜጎች ሠራተኞች ወይም ባለሙያዎች በኢትዮጵያዊያን እንዲተኩ ማድረግ።

11. <u>በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚና በኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ በሚፈፀሙ ጥሰቶች ላይ ቦርዱ ስለሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ከቦርዱ እውቅና ውጭ ይህንን አዋጅ፣ ደንቡንና ስምምነቱን በመተላለፍ የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬትን ለሶስተኛ ወገኖች ያስተላለፈ እንደሆነ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይሰዳል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው የለማ መሬትን በንዑስ ሊዝ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ቆርሶ የሚያስተላልፈውን አይመለከትም፡፡
3. ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም ቦርዱ የኢንዱስትሪ ፓርክን የመሬት ሊዝ ዓመታዊ የገበያ ዋጋን በየጊዜው ይመዘገባል።

12. <u>የንግድ ምዝገባና መስፈርቶች</u>

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ለመመስረት ወይም ለማስመዝገብ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ሰነዶች ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፤
   ሀ/ በድርጅቱ ኃላፊ ወይም በወኪል በትክክል የተሞላና የተፈረመ የማመልከቻ ቅፅ፤
   ለ) አግባብ ባለው ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፤

ሐ) ቅርንጫፍ ከሆነ ከመጣበት ሀገር እናት ድርጅት መመዝገቡንና ሕጋዊ ሰውነት ማግኘቱን የሚያረጋግጡ ሰነዶች፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ምዝገባ ያካሄደ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል።

3. በዚህ አዋጅ የተጠቀሱት የኢንዱስትሪ ፓርክ የንግድ ምዝገባና ተያያዥነት ያላቸው የአሰራር ማረጋገጫዎችና ፈቃዶች፣ ሪፖርት የማድረግ ግዴታዎች፣ ምርመራዎች፣ ኪሳራና ንብረት ማጣራትን የተመለከቱ የአተገባበርና የአሠራር ዝርዝር ሁኔታዎች በደንብ ይወስናሉ።

## ክፍል አራት

## ስለ ኢንዱስትሪ ፓርክ የስራ ፈቃድ እና ነዋሪነት የውጭ ዜጎችን ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስለማስገባት

### 13.ስለ ኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪነት ፈቃድ

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በከፍተኛ ማኔጅመንት፣ በተቆጣጣሪነት፣ በአሠልጣኝነት እና በሌሎች የቴክኒክ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ የውጭ ሀገር ዜጎችን መቅጠር ይችላል፡፡

2. የውጭ ሀገር ሠራተኞችንና በእነሱ ሥር የሚተዳደሩ ሰዎች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበትን ቪዛ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀትና የሥራ ፈቃዳቸውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስጠት በደንቡ በሚገለፀው አሰራር መሠረት የኢምግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በመተባበር በጋራ ይሰራሉ።

### 14.የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ወይም የውጭ ሀገር ዜጋ የተፈጥሮ ሰው ደንቡ ላይ የሚቀመጡትን መስፈርቶች ሲያሟላ የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ ሊሆን ይችላል፡፡

2. የኢንዱስትሪ ፓርክ የመኖሪያ ፈቃድ እና የሥራ ፈቃድ ተለይተው የሚሰጡበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል።

### 15.የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ መብቶች

የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት ምስክር ወረቀት ላይ ለተጠቀሰው ጊዜ ለመኖሪያ ተብሎ በተከለለው ቦታ የመኖር፤
2. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ክፍያዎች ነፃ የማስገባት፤
3. በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ አማካይነት የሚቀርቡ አቅርቦቶች በተመለከተ የተሻለ መግባባትና ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያበቁ የማኅበረሰብ ኮሚቴዎችን የማቋቋም፤
4. በደንቡ ውስጥ በተደነገገው መስፈርት መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለሚኖሩ ሌሎች ነዋሪዎች የግል መገልገያ ዕቃዎችን የማስተላለፍ፤
5. በደንቡ ውስጥ በተደነገገው መሠረት ሌሎች መብቶችን የመጠቀም፡፡

16.<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ ግዴታዎች</u>

የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን ካልተቀመጠ በስተቀር ለሚያስገባቸው ማናቸውም ዕቃዎች አግባብነት ያላቸው የጉምሩክ ቀረጥ፣ ታሪፍ፣ ግብር እና ሌሎች አግባብ ያላቸውን ክፍያዎችን የመክፈል፤
2. አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የገቢ ግብርን እና ሌሎች ግብሮችን የመክፈል፤
3. በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ ግዴታዎችን የማክበር፤

17.<u>በኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ ስለሚፈፀሙ ጥሰቶች እና በኮሚሽኑ ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

ይህን አዋጅ ወይም በደንቡ ውስጥ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመጣስ የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ የያዛቸውን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ እንደሆነ ኮሚሽኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡-

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀትን የመሰረዝ፤
2. በነዋሪነቱ ወቅት ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የወሰዳቸውን ወይም የተረከባቸውን ንብረቶች እንዲመልስ የማድረግ፤ እና

3. ለሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ እስከሚከራይ ድረስ ለ 30 ቀናት ያህል ለተባሉት ሀብቶች ኪራይ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም ለኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው እንዲከፍል የማድረግ።

18.**<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀትን ስለመሰረዝ</u>**

1. ኮሚሽኑ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪው በቅድሚያ የ90 ቀናት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እና በሕግ የተቀመጡ ሥነ-ሥርዓቶችን በተለይም የመሰማት መብቱን ከጠበቀለት በኋላ በሚከተሉት ምክንያቶች የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪነት የምስክር ወረቀትን ሊሰርዝ ይችላል፤

   ሀ) የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪው በዚህ አዋጅ፣ በደንቡ፣ በኢንዱስትሪ ፓርክ የአሠራር ደንቦችና ሥነ-ሥርአቶች፣ በኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከቱትን ግዴታዎች አጓድሎ ሲገኝ፤ ወይም

   ለ) የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪው የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማሳሳት ወይም የሀሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ እንደሆነ።

2. የኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪነት ምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ነዋሪ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያገኛቸውን ማናቸውንም መብቶች ያጣል፤ ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ እንደሁኔታው የወሰዳቸውን የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን እንዲመልስ ያስገድደዋል።

3. የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ወይም የሚለቅ ሰው የግል መገልገያዎቹን አግባብ ያለውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከፍሎ መሸጥ ይችላል፡፡

4. በደንቡ በተመለከተው መሠረት ኮሚሽኑ ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ሊወሰድ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ስለሚሰጡ ዋስትናዎች፣ ጥበቃዎችና እንክብካቤዎች</u>

19.**<u>እኩል እንክብካቤ የማግኘት መብት</u>**

በሌሎች አግባብ ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች ውስጥ ስለውጭ አገር ኢንቨስተሮች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ አገር ኢንቨስተሮች በግላቸው ወይም

ከኢትዮጵያዊያን ጋር በቅንጅት በመሆን በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚነት፣ በኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪነት ወይም በኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የሥራ መስክ መሳተፍ ይችላሉ፡፡

20.<u>የግል ንብረት ጥበቃ</u>

1. ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ተገቢ ካሳ በቅድሚያ ተከፍሎ ካልሆነ በስተቀር የኢንዱስትሪ ፓርክ ኢንቨስትመንትን ማስለቀቅ አይችልም።
2. ባለሀብቱ የውጭ ባለሀብት ከሆነ የካሳ ክፍያውም በውጭ ምንዛሪ በሚቀየርና በዓለም አቀፍ ገበያ በነፃ ሊተላለፍ በሚችል ገንዘብ መፈፀም አለበት፡፡
3. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከህግ አግባብ ውጭ ንብረቱን እንዲለቅ የተደረገ ማንኛውም ሰው ንብረቱን እንዲለቅ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ንብረቱ እስከተመለሰለት ጊዜ ድረስ ምክንያታዊ በሆነ ምጣኔ ከሚታሰብ ወለድ ጋር የተወሰደበት ሀብት ወይም ኢንቨስትመንት እንዲመለስለት ይደረጋል፡፡
4. ስለ ንብረት ግምት፣ ስለ ካሳ ክፍያ፣ ስለ ንብረት ማስለቀቅ እና ስለ ንብረት አመላለስ ዝርዝር አግባብ ባለው ሕግ የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

21.<u>ስለ የውጭ ምንዛሪ</u>

ማንኛውም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ይዞ የሚመጣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በአገሪቱ ሕጎች መሰረት፡-

1. ከውጭ ሀገር ባንኮች እና ከመረጧቸው የሀገር ውስጥ የገንዘብ ተቋማት ገንዘብ መበደር፣
2. የቦንድና ሌሎች ዋስትናዎችን በውጭ ሀገር የዋስትና ገበያ ላይ ማቅረብ፣
3. ከተፈቀደለት ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 26 ከንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሰ) የተመለከቱ ክፍያዎች በወቅቱ ባለው የምንዛሪ ተመን መሰረት በውጭ ምንዛሬ ከኢትዮጵያ ውጭ ማዛወር፣

ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## መሬት ስለመያዝና የአካባቢ ጥበቃ

### 22.የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት፣ ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀሱ ሀብቶች ስለመያዝ

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ በሊዝ ስሪት መሠረት የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት መያዝና በንዑስ ሊዝ መሠረት የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ማስተላለፍ ይችላል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት የተረከበው የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት በቦርዱ ሲፀድቅ ያስተዳድራል።
3. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ በንዑስ ሊዝ የሚያገኘው መሬት በኮሚሽኑ ሲፀድቅና የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲሰጠው በኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ውስጥ መያዝ ይችላል።
4. በገጠር ወይም በከተማ የመሬት ስርአትና አጠቃቀም እንዲሁም የጨረታ ስርአትን የሚመለከቱ ገደቦች በኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም።
5. ስለኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ቦታ ምዝገባ ስለሊዝ፣ ስለንዑስ ሊዝ፣ ስለቦታው ልማትና ግንባታ፣ ስለሕንፃ ደህንነትና መሠረታዊ አቅርቦቶች የተመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በደንብ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡
6. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ ኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ እና የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት መሬቱ ላይ ባዋለው ሀብት መጠን ብድር ለማግኘት የለማ መሬት፣ ሌሎች የማይንቀሳቀሱ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ማስያዝ ይችላል፡፡
7. ቦርዱ በጽሑፍ ካልፈቀደ እና ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ካልሆነ በቀር የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክ መሬትን የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም።

## 23.<u>ስለሕንፃ አሰራር</u>

የኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ልማትን፣ መሰረተ ልማትን፣ ሕንፃን፣ መዋቅርን፣ የአሰራር ደንቦችንና ደረጃዎችን በተመለከተ በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች የተደነገገው እንደጠበቀ ሆኖ አግባብነት ያለው የፕሮጀክት ዲዛይን፣ ፕላን፣ ግንባታ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ አስተዳደር፣ መሬት አስተዳደር እና ተያያዥነት ያለው የፕሮጀክት ክትትልና ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር ደንብ ይወጣል።

## 24.<u>ስለአካባቢ ጥበቃ ድንጋጌዎች</u>

1. የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ሕጎች በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
2. የአካባቢና የደን ሚኒስቴር የአካባቢ ጥበቃ ሥርዓቶችን፣ ደረጃዎችን፣ የአካባቢ መንከባከቢያ መንገዶችን እና በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳት መቀነሻ ዕቅዶችን በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ፣ ለማስፈጸም፣ ለመቆጣጠር፣ ለመጠበቅ እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ ቢሮ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያደራጃል፡፡
3. ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር የተያያዙ የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች ዝርዝር ሁኔታ በደንቡ ይወሰናል፡፡

## 25.<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየምና ማሻሻያ</u>

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ በቦርድ ይሰየማል።
2. ቦርዱ የኢንዱስትሪ ፓርክን ሲሰይም የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ያስገባል፦
   ሀ/ የቀረበዉ ፕሮጀክት አይነት፤
   ለ) ሊለማ የታሰበዉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ስፋትና መጠነ ዙሪያ፤
   ሐ) ከይገባኛል ጥያቄ ነጻ የተደረገ መሆኑ፣ ለግብአት እና ለመሠረተ ልማት ያለው ቅርበት፣ የሕዝብ ማዕከል ለመሆን ያለው አመቺነት፣ የፕሮጀክቱን ባሕሪ እና የጤናና የመዝናኛ ማዕከላት ያሉት መሆኑን፤ እና
   መ) ከማስተር ፕላን፣ ከመሬት አጠቃቀምና ከመሳሰሉት ጋር የሚጣጣም መሆኑን።
3. የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም ስርዓትና ዝርዝር መስፈርቶች በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
4. ማናቸውም የተሰየመ የኢንዱስትሪ ፓርክ ማሻሻያና ስረዛ በቦርዱ ይወሰናል፡፡

26.<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ አመራረጥ መስፈርት</u>

የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ አመራረጥ በደንብ ይወሰናል፡፡

27.<u>የአንድ ማዕከል አገልግሎት</u>

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ አግባብነት ባላቸው አካላት የሚሰጡት አገልግሎቶች በቅልጥፍናና በተሳለጠ ሁኔታ በአንድ ማዕከል ይሰጣሉ።
2. ኮሚሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ ሌሎች አግባብ ያላቸውን አካላት ያቀናጃል፤የየዕለት ተግባራቸውን ያስተባብራል።
3. አግባብ ያላቸው አካላት የሚመለከታቸውን የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሲሰጡ በሕግ የተደነገገውን የሥልጣንና ተግባር ወሰናቸውን ማክበር አለባቸው።
4. የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች በደንብ ይወስናሉ።

28.<u>ሠራተኛን የሚመለከቱ ጉዳዮች</u>

1. የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 (እንደተሻሻለ) በማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንዱስትሪ ፓርክን ልዩ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የሥራ ውል ድርድር ሊደረግ ይችላል።
3. የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር የሶስትዮሽ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ የሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከቱ የሥራ ደንቦችንና ሥርዓቶችን ያወጣል፤ ዝርዝሩም በደንብ ይወሰናል።
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ጋር በመተባበር የቴክኒክና የሙያ ስልጠና ያዘጋጃል።
5. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የክላስተር ሥርዓትን በመጠቀምና ሌሎች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የቴክኖሎጂ ሽግግርንና የክህሎት ልማት በአጠቃላይ፣ የሀገር ውስጥ አምራች ዘርፍ አቅም ግንባታ ሥራዎችን በተለየ ሁኔታ ያመቻቻል።

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ተቆጣጣሪ አካላት እና የቅሬታ አቀራረብ ስርአት</u>

**29.** **ተቆጣጣሪ አካላት**

1. ቦርዱ የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየምን አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳደርንና ቁጥጥርን በበላይነት ይመራል፡፡
2. ቦርዱ ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማናቸውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ እና የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ይወስናል።
3. ቦርዱ የመቆጣጠር ኃላፊነቱን የሚወጣበት ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት በደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡
4. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር [58]የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች የኤክስቴንሽን አግልግሎት፣ ቴክኖሎጂ፣ ግብአትና ግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል
5. ኮሚሽኑ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 (እንደተሻሻለ) ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ እና ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ፈቃድ ይሰጣል፤ ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ከኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ጋር ስምምነት ይፈርማል።
6. በዚህ አንቀፅ የተመለከቱት የቦርዱና የኮሚሽኑ ዝርዝር ተግባራት በደንብ ይወሰናሉ።

**30.** **ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት፣ ፈቃድ ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ**

1. ቦርዱ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው፤-
   ሀ) ፈቃዱን ለማግኘት የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች የጣሰ እንደሆነ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በደንቡ በተመለከተው የጊዜ ገደብ መሠረት ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤
   ለ) በዚህ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) በተገለፀው መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ የማስተካከያ እርምጃውን እስኪወስድ ድረስ በደንቡ ለተመለተከው የጊዜ ገደብ ፈቃዱ ይታገዳል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በተመለከተው የጊዜ ገደብ

[58] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ እና ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ቦርዱ ፈቃዱን ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) መክሰሩ ከታወጀ፤

ለ) ፈቃዱን ለማግኘት የሀሰት ወይም የተሳሳተ መረጃ ማቅረቡ ከተረጋገጠ፤

ሐ) በገባው ስምምነት መሰረት ያገኘውን መሬት ካላለማ ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ ማስተዳደር ስራን ካልጀመረ፤

መ) በገዛ ፈቃዱ ሥራውን ስለማቋረጡ አግባብ ላለው አካል በጽሁፍ ካሳወቀ፤

3. ፈቃዱ ከተሠረዘ በኋላ በባለፈቃዱ የተያዘው መሬትን ለአከራዩ ይመለሳል፡፡
4. የፈቃዱ መሠረዝ የተፈጸመውን የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚነት ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪነት ስምምነት እንዲቋረጥ ያደርጋል።
5. ኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ባለፈቃድ፦

ሀ) ፈቃዱን ለማግኘት የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች የጣሰ እንደሆነ ማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በደንቡ በተመለከተው የጊዜ ገደብ መሠረት ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተገለፀው መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ እርምጃውን እስኪወስድ ድረስ በደንቡ ለተመለከተው የጊዜ ገደብ ያግደዋል።

6. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በዚህ ንዑስ አንቀፅ (5) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ እና ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ኮሚሽኑ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፦

ሀ) መክሰሩ ከታወጀ፤

ለ) ፈቃዱን ለማግኘት የሀሰት ወይም የተሳሳተ መረጃ ማቅረቡ ከተረጋገጠ፤

ሐ) በገባው ንዑስ ሊዝ መሠረት ያገኘውን መሬት ካላለማ፤

መ/ በገዛ ፈቃዱ ሥራዉን እንዳቋረጠ አግባብ ላለው አካል በጽሁፍ ካሳወቀ፤

7. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የፈቃድ ስረዛ ባለፈቃዱ በዚህ ዓዋጅ መሰረት የተሰጡትን መብቶች እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

31.**ስለቅሬታ ማስተናገጃ**

1. ማንኛውም ኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ ኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ፣ ኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ወይም ኢንዱስትሪ ፓርክ ነዋሪ ሥልጣን ባለው አካል በተወሰደበት እርምጃ ላይ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ማቅረብ መብት ይኖረዋል።
2. ማንኛውም ጥያቄ ለኮሚሽኑ የሚቀርበው እርምጃው ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡
3. ኮሚሽኑ በቀረበው ቅሬታ ላይ አቤቱታው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔ በተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ቦርዱ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡
5. ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔዉ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይገባል፡፡
6. ስለቅሬታ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ ዝርዝር ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

32.**ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሰጡ ማበረታቻዎችን የሚመለከት እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

33.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. በዚህ አዋጅ ላይ የተመለከቱትን የአሰያየም መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ ማናቸውም ነባር ከኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ይቆጠራሉ፤ በዚህ አዋጅ መሠረትም ይተዳደራሉ።
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት፡-

ሀ) መንግሥት ከኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና፣ ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚና ከኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ጋር ያደረጋቸው ስምምነቶች፣

ለ) በመንግሥት ለኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና፣ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ወይም ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የተሰጡ ማበረታቻዎች

ፈፃሚነት ይቀጥላል።

3. የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ማልማትን ወይም ማስተዳደርን በተመለከተ ማንኛውም በሂደት ላይ ያለ ማመልከቻ ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው ደንብ መሠረት ወደ ኮሚሽኑ እንደቀረበ ይቆጠራል።

4. የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ኮርፖሬሽን ይህንን አዋጅ ተከትሎ እንደተቋቋመ ይቆጠራል።

**34.** **<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ፣ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**35.** **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ 1ቀን 2007 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 417/2009

## ስለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 አንቀጽ 32(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 417/2009 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

   1. "አዋጅ" ማለት የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 ነው፤
   2. "ኢንቨስትመንት አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 (እንደተሻሻለ) ነው፤
   3. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤
   4. "ኮሚሽን" ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤
   5. "ኮርፖሬሽን" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 326/2007 የተቋቋመው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ነው፤
   6. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን[59] ነው፤
   7. "የስሪት አገር የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ዕቃ ስለተመረተበት አገር ትክክለኛነት በተመረተበት አገር ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰነድ ነው፤
   8. "የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ" ማለት ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት፣ ሠራተኛ ወይም ነዋሪ ነው፤

[59] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 21(ሀ) መሰረት የጉምሩክ ኮሚሽን በሚል ይነበብ፡፡

9. “የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት” ማለት የጉምሩክ ሕግን ለማክበርና ለማስከበር በሚመለከታቸው ሰዎችና በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የጉምሩክ ሂደቶችን ያጠቃልላል፤
10. “የጉምሩክ ቁጥጥር” ማለት የጉምሩክ ሕግ መከበሩን ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የሚወሰድ ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ነው፤
11. “መሠረተ-ልማት” ማለት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ መብራት፣ ውሃ፣ የቴሌኮም (የድምጽ፣ የዳታ፣ የቪዲዮና ተዛማጅ አገልግሎቶች)፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ እና የአየር ብክለት መቀነሻ ሥርዓት ማሟላት እንዲሁም በፓርክ ውስጥ የሚከናወኑ የመንገድና ሌሎች አስፈላጊ ግንባታዎችን ያካትታል፤
12. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (6) የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዚህ ደንብ የተካተቱት ሌሎች ቃላት ወይም አገላለጾች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤
13. በማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸውድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. <u>የቦርዱ ዋና ዋና ተግባራት</u>

ቦርዱ አዋጁንና ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት፣ አስተዳደርና አመራር፣ ተቋማዊ ግንባታና ቁጥጥርን በበላይነት የመምራት፤
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ የመሰየም፣ የተሰየመ የኢንዱስሪ ፓርክን የማሻሻል እና የመሰረዝ፤
3. የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎችን የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን የመወሰን፣ አፈጻጸማቸውን የመከታተል፤
4. የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በተመለከተ በሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት የትብብርና የቅንጅት ዘላቂ ሥርዓት መዘርጋቱን የማረጋገጥ፤
5. በፓርኮች ውስጥ የእውቀትና የክህሎት ሽግግር መኖሩን ማረጋገጥ፤ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርኮች በመሳብ፣ በመመልመልና በመደገፍ ዘርፈ-ብዙና ቀጣይነት ያላቸው የግብዓት ትስስሮች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንዲፈጠሩ በዘርፉ አዲስ የምርት አቅም እንዲስፋፉ የሚረዱ ስትራቴጂዎችና ጥናቶችን የማጽደቅ፤

6. ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለማስተናገድ ደረጃውን የጠበቀ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት መዘርጋቱን የማረጋገጥ፡፡

4. <u>የኮሚሽኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

ኮሚሽኑ አዋጁንና ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚነት ሊሰማሩ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ባለሀብቶችን የመመልመል፤
2. በኢንዱስትሪ ፓርክ አምራችነት ሊሳተፉ የሚችሉ ብቃት ያላቸውን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ባለሀብቶችን በመመልመልና ስምምነቶችን በመፈጸም ፓርኮች ሙሉ በሙሉ በአምራች ድርጅቶች መያዛቸውን የማረጋገጥ፤
3. በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች በተሳለጠ ሁኔታ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤
4. ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ የእውቀት እና የክህሎት ሽግግር የሚያመጡ፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርክ በመሳብና በመደገፍ ዘርፈ-ብዙና ቀጣይነት ያላቸው የግብዓት ትስስሮች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንዲፈጠሩና በየዘርፉ አዲስ የምርት አቅም እንዲስፋፉ የሚረዱ ስትራቴጂዎችና ጥናቶችን ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር [60]ጋር በመመካከር ነድፎ በቦርዱ በማጸደቅ ተግባራዊ የማድረግ፤
5. ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች የሎጅስቲክስና የኤክስፖርት ድጋፍ የመስጠት፤
6. ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሆን መሬት መዘጋጀቱንና መሰየሙን የማረጋገጥ፤ የሊዝ፣ የንዑስ-ሊዝና የግንባታ ፈቃዶች በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት መሰጠታቸውን የማረጋገጥ፤ መሠረተ-ልማት በአግባቡ መቅረቡን፣ በዕቅዱ መሠረት መልማቱን እንዲሁም ለምርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ፤
7. የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ መከበራቸውን የማረጋገጥ፤
8. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች፣ አልሚዎች ወይም አስተዳዳሪዎች ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው እንደ አመቺነቱም በተደራጀ መልክ ከመንግሥት ጋር ቀጣይነት ያለው ምክክር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት

[60] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

9. የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎችን የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት በቦርዱ የማስወሰንና የማስፈጸም፤
10. ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ በሚመለከታቸው አካላት የሚያካሄድ የሠራተኞች ምልመላና ሥልጠና የማስተባበር፣ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች የማህበረሰብ ሬድዮ ስርጭትን ጨምሮ ሌሎች የተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎችን በመጠቀም በፋብሪካ ደረጃ ሠራተኞች ለሥራ ያላቸው ተነሳሽነት እንዲጨምር የማገዝ፤
11. ስለኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች የመሬት ልማትና የግንባታ አፈጻጸም፣ የፋብሪካና ሌሎች ሕንጻዎች አጠቃቀም፣ የምርትና የወጪ ንግድ አፈጻጸም፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ሠራተኞች የቅጥር ሁኔታ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አፈጻጸምና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን አጠናቅሮ የያዘና የተተነተነ ወቅታዊ ሪፖርት ለቦርዱና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት የማቅረብ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየምና የኢንቨስትመንት ፈቃድ

5. ስለኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም

1. ኮርፖሬሽኑ ወይም ሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማልማት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት አንድን የለማ ወይም ያልለማ ቦታ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተብሎ እንዲሰየምለት ለኮሚሽኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም ማመልከቻ የአዋጁን አንቀጽ 25 (2) ድንጋጌ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡
3. የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም ማመልከቻው በአዋጁ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዋናነት የሚከተሉት መኖራቸውን ማሳየት ይኖርበታል፤
   ሀ) ለዜጎች የሥራ ዕድል፤
   ለ) የዕውቀት፣ የክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር፤
   ሐ) ኤክስፖርትን የማሳደግ አቅም፤
   መ) የግብዓት አቅርቦትና ትስስር፤
   ሠ) አገራዊና ክልላዊ የመሠረተ-ልማት እድገት፤
   ረ) ለኢንዱስትሪ ፓርክ አስፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል አቅርቦት፡፡

4. በኢንዱስትሪ ፓርክነት የሚሰየመው አነስተኛ የመሬት መጠን እንደ ፕሮጀክቱ ሁኔታ እየታየ በቦርዱ ይወሰናል፡፡
5. በኢንዱስትሪ ፓርክ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለፋብሪካ፣ ለጋራ መጠቀሚያ፣ ለመኖሪያ እና ተያያዥ ሕንጻዎች እንዲሁም ለመሠረተ-ልማት የሚውለው መሬት ከጠቅላላ ይዞታው ከ50 በመቶ ማነስና ከ75 በመቶ መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም ቦርዱ ለእርሻም ይሁን ለግጦሽ ሊውል የማይችል መሬት ለአካባቢ ጥበቃ በሚረዳ መልኩ በኢንዱስትሪ ፓርክነት እንዲለማ ጥያቄ ከቀረበና ካመነበት ከዚህ በተለየ ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡
6. ኮሚሽኑ የአሰያየም ማመልከቻውን መርምሮ የውሳኔ ሀሳቡን በሰላሳ ቀናት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
7. ቦርዱ ከኮሚሽኑ በሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርክነት የተሰየመን መሬት መጠንና የሚተላለፍበትን የሊዝ ዋጋ በመወሰን ለተመረጠው አልሚ እንዲተላለፍ ይወስናል፡፡
8. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ለኮሚሽኑ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡-
   ሀ) የኢኮኖሚ አዋጭነት ጥናት፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፕላንና የሀይድሮሎጂ ጥናት ሰነድ፤
   ለ) የፋይናንስ አቅም የሚያሳይ ማስረጃ፤ እና
   ሐ) የአካባቢና የማሕበራዊ ተጽእኖ ግምገማ ሪፖርት ጋር በተያያዘ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን በሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ይሁንታ የተሰጠው መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ፡፡
9. ኮሚሽኑ የቦርዱን ውሳኔ በተወሰነ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

6. <u>ልዩ የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም</u>
   1. ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ አንድን የኢንዱስትሪ ፓርክ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የፋርማሲዩቲካል፣ የብረታ ብረት ወይም ሌላ የተለየ ባህርይ ያለው ልዩ የኢንዱስትሪ ፓርክ ብሎ ሊሰየም ይችላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድን ቦታ ከባለሥልጣኑ ጋር በመመካከር ዕቃዎች የሚራገፉበት፣ የሚስተናገዱበት፣ የሚመረቱበት ወይም የሚገጣጠሙበት እና ወደ ውጭ እንደገና የሚላኩበት ወይም ለኢንዱስትሪ ፓርክ በግብዓትነት እንዲቀርቡ የሚደረግበት እንደ ነፃ የንግድ ፓርክና የኤክስፖርት ማቀነባበሪያ ዞን አድርጎ ሊሰይም ይችላል፡፡
3. የልዩ ኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም ማመልከቻ በኮሚሽኑ ወይም በኮርፖሬሽኑ ወይም በሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ሊቀርብ ይችላል፡፡
4. የዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣የልዩ አሰያየም ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች በግልጽ ማሳየት ይኖርበታል፤
   ሀ) እንደዚህ ያለው ልዩ ስያሜ የክልሉን ወይም የአካባቢውን የተለየ የልማት ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ መሆኑን፤
   ለ) በፓርኩ ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች በእርስ በርስ ትስስር የተሻለ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያለውን ጠቀሜታ፤ እና
   ሐ) የተመረጠው አካባቢ ለግብዓት አቅርቦት ያለውን ምቹነት፡፡
5. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) መሠረት ልዩ ስያሜ ለሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ የተለየ ማበረታቻ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**7. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የኢንቨስትመንት ፈቃድ**

1. ማንኛውም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ለመሆን ለኮሚሽኑ በማመልከት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦
   ሀ) በመንግሥት ቅድሚያ በተሰጣቸው ልዩ የኢንቨስመንት መስኮች ለሚሰማሩ የኢንዱስትሪ ፓርክ አምራች ድርጅቶች የሚሆን የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማልማት የተስማማ፤
   ለ) ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ በቂ ካፒታል ያለው፤ እና
   ሐ) ሌሎች በኢንቨስትመንት ሕጉ ስለኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቀሱትን መስፈርቶች፡፡

3. ኮሚሽኑም አመልካቹ ያቀረበውን ጥያቄ መርምሮ መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኝ ከአመልካቹ ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአልሚው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
4. ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የተሰጠው ኢንቨስትመንት ፈቃድ ፓርኩ የሚያተኩርበትን የኢንቨስትመንት መስክ መግለጽ አለበት፡፡

8. <u>የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ለመሆን ለኮሚሽኑ በማመልከት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦
   ሀ) ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች መስጠቱን የሚያሳይ የሙያ እና የሥራ ልምድ ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ ማቅረብ፤
   ለ) ልምድ ያላቸው በቂ ባለሙያዎችና የፋይናንስ አቅም ያካተተ የአስተዳደር እና የፋይናንስ እቅድ፤ እና
   ሐ) ሌሎች በኢንቨስትመንት ሕጉ ስለኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቀሱትን መስፈርቶች፡፡
3. ኮሚሽኑም አመልካቹ ያቀረበውን ማመልከቻ በመመርመር መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
4. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ያለማውን ፓርክ ራሱ ለማስተዳደር ከፈለገ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሱት መስፈርቶች በሚሟላት እና ማመልከቻ በማቅረብ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪነት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

9. <u>የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የኢንቨስትመንት ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ለመሆን ለኮሚሽኑ በማመልከት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦
   ሀ) ዝርዝር የፕሮጀክት ሀሳብ፤

ለ) እንደ ፕሮጀክቱ ዓይነት የኤክስፖርት ወይም የገቢ ምርት የመተካት ዕቅድ፤

ሐ) የፋይናንስ ሁኔታ መግለጫ እና የአስር ዓመት ትንበያ፤

መ) ፕሮጀክቱን በተመለከተ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሪፖርት፤ እና

ሠ) ሌሎች በኢንቨስትመንት ሕጉ ስለኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቀሱትን መስፈርቶች፡፡

3. ኮሚሽኑም አመልካቹ ያቀረበውን ማመልከቻ በመመርመር መስፈርቱን የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፡

## ክፍል ሦስት

## መሬት መስተላለፍ እና ግንባታ

### 10.የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ እና ድርጅት የመሬት ሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት

1. ኮርፖሬሽኑ በተቋቋመበት ደንብ ቁጥር 326/2007 አንቀጽ (5) (2) መሠረት ራሱ የሚያለማውን ወይም ለሌሎች አልሚዎች የሚተላለፍን መሬት ከክልሎች በስምምነት እና በሳይት ፕላን ተረክቦ በመሬት ባንክነት ይይዛል፤ ስምምነቱም ኮርፖሬሽኑ ለራሱ ለማልማትም ሆነ ለሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ መሬት በሊዝ ለማስተላለፍ የሚያስችለው መሆን አለበት፡፡

2. ኮርፖሬሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከተረከበው መሬት ውስጥ የራሱን የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማልማት ከፈለገ የመሬት ሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው የክልል መንግሥት ተቋም ይሰጠዋል፡፡

3. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚነት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጠው ባለሀብት ከመሬት ባንክ መሬት በሊዝ ውል ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ይህንን ተከትሎ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው የሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት ከኮሚሽኑ ያገኛል፤ ሆኖም ኮርፖሬሽኑ መሬቱን በሊዝ የሚያስተላልፈው ኮሚሽኑ ይህንን መሬት ለአልሚው እንዲተላለፍ ቦርዱን በቅድሚያ አስፈቅዶ ይህንኑ የቦርዱን ውሳኔ ለኮርፖሬሽኑ ሲያሳውቀው ብቻ ይሆናል፡፡

4. በኮርፖሬሽኑ ወይም በሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ መሬት የተሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከኮርፖሬሽኑ ወይም ከዚሁ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ጋር የንዑስ-ሊዝ ውል ሲዋዋል፣ የንዑስ-ሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት ከኮሚሽኑ ይሰጠዋል፡፡

11.<u>በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት የሚካሄድ ግንባታ</u>

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ለኪራይ ወይም ለሽያጭ የፋብሪካ ሕንጻ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የተፈቀደ ሌላ ግንባታ ማከናወን ሲፈልግ የግንባታ ፈቃድ ከኮሚሽኑ ማግኘት ይኖርበታል፤ ኮሚሽኑ ይህንን ተግባር ሲፈጽም አግባብ ካለው ተቋም ሙያዊ እገዛ እንደአስፈላጊነቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የግንባታ ፈቃድ ሲጠይቅ የሚከተሉትን መስፈርቶች በግልጽ ማሳየት ይኖርበታል፤

   ሀ) ከተፈቀደው ቦታ ውስጥ ለፋብሪካና ተያያዥ ግንባታ የሚውለው ቦታ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 (5) ከተመለከተው ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤

   ለ) በቂና ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ የሆነ እንደ መኖሪያ ቤት፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ቦታ፣ ስፖርት ማዕከል፣ አረንጓዴ ቦታ፣ የሕክምና አገልግሎት መስጫ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ያካተተ መሆኑን፤ እና

   ሐ) በቂና ደረጃውን የጠበቀ የእሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ፣ እንደ ሲ.ሲ.ቲ.ቪ. ያሉ ለደሕንነት እና ለጉምሩክ ቁጥጥር አስፈላጊ የሆኑ ካሜራዎችና መፈተሻዎች፣ የዕቃ መጫኛና ማውረጃ ቦታ፣ የምድር ሚዛን፣ መጋዘንና ቢሮ፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታ፣ የመጸዳጃና የፋብሪካ ዝቃጭ ፍሳሽ የሚታከምበት ዘዴ ያለው መሆኑን፡፡
3. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የፕሮጀክት ግንባታ አፈጻጸም በተመለከተ ከኮሚሽኑ ጋር ስምምነት ይፈራረማል፡፡
4. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የፋብሪካና ተያያዥ ግንባታ አፈጻጸም የተመለከተ ስምምነት ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ከሚወክለው አስተዳዳሪ ጋር ይፈጽማል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተመለከቱትን ስምምነቶች ተከትሎ ኮሚሽኑ የግንባታ ፈቃድ እና ከግንባታ ጋር ተያያዥ የሆኑ ፈቃዶችን ይሰጣል፤ የግንባታ ወጪ ዝርዝር መርምሮ ያጸድቃል፡፡
6. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት በስምምነቱ መሠረት ባከናወነው ግንባታ ላይ ለውጥ ማድረግ ሲፈልግ ስምምነቱን ከፈጸመው አካል እንደ አግባብነቱ ኮሚሽኑን ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚውን ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

7. ኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ፕሮጀክት ወይም የድርጅቱ የፋብሪካና ተያያዥ ግንባታ አፈጻጸም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ኮሚሽኑ ይህንን ተግባር በራሱ ባለሙያዎች ወይም በኮርፖሬሽኑ ወይም በሌላ አማካሪ ድርጅት አማካኝነት ሊያከናውን ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪና ድርጅት የኢንቨስትመንት ተግባራቸውን ስለሚያከናውኑባቸው ሁኔታዎች

### 12. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ፓርኩን የሚያለማበት ሁኔታ

የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፡

1. ግንባታ በሚያከናውንበት ወቅት የሠራተኞች ደሕንነት መጠበቁን እንዲሁም ለሠራተኞቹ አገልግሎት መስጫ፣ የመመገቢያና የመጸዳጃ ቤቶች፣ የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጫና ሌሎች ለሠራተኞች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ፤
2. በዚህ ደንብ፣ በአልሚ ኢንቨስትመንት ፈቃድና ስምምነት መሠረት የሕንጻዎችን ግንባታ፣ የመሠረተ- ልማትና የአገልግሎት ዝርጋታ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በወቅቱ የማጠናቀቅ፤
3. ፓርኩ የሚያተኩርበትን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ያማከለ የምርት ጥራትና ሌሎች መመዘኛዎች መሟላታቸው የሚያረጋግጡ የምስክር ወረቀቶች የሚሰጡባቸው የአገልግሎት መስጫ ሕንጻ የማዘጋጀት፤
4. ስለፓርክ ልማት ያገኘውን ተሞክሮ ለኢትዮጵያውያን የማስተላለፍ፤
5. ስለሥራ አፈጻጸሙ በተለይ ስለኢንዱስትሪ ፓርኩ የመሬት ልማትና የግንባታ አፈጻጸም፣ የፋብሪካና ሌሎች ሕንጻዎች አጠቃቀም፣ በየሩብ ዓመቱ ዝርዝር ሪፖርት ለኮሚሽኑ የማቅረብኃላፊነት አለበት፡፡

### 13. የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ፓርኩን ስለሚያስተዳደርበት ሁኔታ

የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ፡-

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አግባብ ባላቸው ሕጎችና ከአስተዳዳሪ ስምምነት ጋር በተጣጣመ መልኩ የመፈጸም፣

2. የፓርክ አስተዳደሩ ምክንያታዊ በሆነ የንግድ አሰራር ላይ መመስረቱን የማረጋገጥ፣
3. በውል የተቀበላቸውን የኢንዱስትሪ ፓርክ አገልግሎቶች ያለ አድልዎ የመስጠት፤
4. ከኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች ማሕበር ጋር በመመካከር በተዘጋጀ ውስጠ ደንብ መሠረት በተለይ የሚከተሉትን ተግባራት፡-
   ሀ) የግንባታ ማሻሻያዎች አግባብነት ካላቸው ሕግጋት ጋር መጣጣማቸውን የማረጋገጥ፤
   ለ) በፓርኩ ውስጥ፣ በመግቢያ እና በመውጫ በሮች የሰዎችና የተሸከርካሪዎች እንቅስቃሴ የማሳለጥ፤
   ሐ) የጭነት ማራገፊያ ተርሚናል እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፤
   መ) በፓርኩ ውስጥ እና ዙሪያ ተገቢውን ፀጥታና ደህንነት የመጠበቅ፤
   ሠ) የእሳትና የድንገተኛ አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥርዓት በአግባቡ የመዘርጋት እና ዘወትር በተጠንቀቅ ላይ እንዲሆን የማድረግ፤
   ረ) የፈሳሽና የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድን ጨምሮ የጋራ ቦታዎች ጽዳት የመጠበቅ፤
   ሰ) የአረንጓዴ እና የጋራ ቦታዎች እንክብካቤና ልማት የማካሄድ፤
   ሸ) የመሠረተ-ልማት አውታሮች በአግባቡ መጠበቃቸውን፣ መጠገናቸውንና አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን የማረጋገጥ፡፡
5. የተወሰኑ አገልግሎቶች ከሦስተኛ ወገን በውል እንዲቀርቡ የማድረግ፣
6. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም የፀጥታና የሕግ ማስከበር አካላትን በተለይ የመንግሥት የፀጥታ ኃይል ትብብርን በመጠየቅ በፓርኩ ውስጥ ፀጥታ እና ደህንነት የማስከበር፣
7. በኢንዱስትሪ ፓርኩ ለተጠቃሚም ሆነ ለጉምሩክ ሕግ አፈፃፀም ምቹ የሆነና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራር የመዘርጋት፣
8. የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳደር ዕውቀትና ክህሎት ለኢትዮጵያውያን የማስተላለፍ፣
9. ስለሥራ አፈጻጸሙ በተለይ ስለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚና ድርጅት የመሬት ልማትና የግንባታ አፈጻጸም፣ የፋብሪካና ሌሎች ሕንጻዎች አጠቃቀም፣ በየሩብ ዓመቱ ዝርዝር ሪፖርት ለኮሚሽኑ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

14. **<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ሥራውን ስለሚያከናውንበት ሁኔታ</u>**

የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፤

1. የሠራተኛ የሥራ ሁኔታና ምርታማነት ትስስር ሥርዓት የመዘርጋት፤ በተለይም የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሽፋን፣ የሕጻናት ማቆያ፣ ካፊቴሪያዎችና እንደ አስፈላጊነቱ የመጓጓዣ አገልግሎቶች እንዲኖሩ የማድረግ፤
2. ዕውቀትና ክህሎት ለኢትዮጵያውያን እንዲተላለፍ የማድረግና በዚህ ረገድ ያከናወነውን ተግባር ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት በየዓመቱ ሪፖርት የማቅረብ፤
3. በሥራ ላይ ያሰማራቸውን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ሠራተኞች የተመለከተ መረጃ በየሩብ ዓመቱ ለኮሚሽኑ የመስጠት፤
4. የሥራ አፈጻጸሙን በተለይ የምርትና የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሪፖርት ለኮሚሽኑ በየወሩ የማቅረብ፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የአንድ ማዕከል አገልግሎትና ተያያዥ ጉዳዮች</u>

15. **<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ የአንድ ማዕከል አገልግሎት</u>**

1. ከኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰደ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት የሚከተሉትን የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያገኛል፡-
   ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዕድሳት፣ ማሻሻያ፣ ወይም ለውጥ ወይም ምትክ፣ ወይም ነባር የኢንቨስትመንት ሥራን ለማስፋፋት የሚሰጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፤

   ለ) የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ወይም ምትክ የንግድ የምስክር ወረቀት፤

   ሐ) የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ ዕድሳት ወይም ምትክ፤

   መ) የንግድ ማሕበር ስም ማሻሻያ ወይም ለውጥ፤

   ሠ) የንግድ ስም ምዝገባ፣ ምትክ የንግድ ስም፣ የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ማሻሻያ ወይም ስረዛ፤

   ረ) የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች ማሕበር ምዝገባና እድሳት፤

   ሰ) የውጭ ቀጥተኛ ካፒታል ምዝገባ፤

ሸ) ቪዛ የመስጠትና ዕድሳት፣ የመኖሪያ ፈቃድ የመስጠትና ዕድሳት፣

ቀ) የሥራ ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ መተካትና መሠረዝ፤

በ) የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ እና ያለ ውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ወደ አገር ውስጥ ዕቃ የማስገቢያ ፈቃድ፤

ተ) የገቢ ግብር ነጻ ማበረታቻ ፈቃድ፤

ቸ) በአንድ የኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከአንድ የቀረጥ ነፃ መብት ያለው ድርጅት ወደ ሌላ የቀረጥ ነፃ መብት ያለው ድርጅት የግንባታ ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች የማስተላለፍ ፈቃድ፤

ኀ) የመመስረቻ ጽሁፎች፣ የመተዳደሪያ ደንቦች ማሻሻያና ሌሎች ሰነዶች ማረጋጫ፤

ነ) ለኢንዱስትሪ ፓርክ ሠራተኞች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠት፣ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ውሳኔ፤

ኘ) ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማወራረድ፣ የቫውቸር እንዲሁም ሌሎች ከወጪ ንግድ ማበረታቻ ጋር ተያያዥ ፈቃዶችና አገልግሎቶች፤

አ) የግብር ማሳወቅ፣ የግብር ክፍያ፣ የግብር ተመላሽ ማወራረድ፣ የግብር ኦዲት እና ከግብር ጋር ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶች፤

ከ) ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር የተያያዙ ምዝገባዎች፤

ኸ) የስምሪት አገር ምስክር ወረቀት እና የተለየ የገበያ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ደጋፊ የምስክር ወረቀቶች፤

ወ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ማጽደቅ እና የምስክር ወረቀት፤

ዐ) አስፈላጊ ሲሆን፣ የብቃት ማረጋገጫ እና ሌሎች በግብይት ሥርዓት የሚጠየቁ የምስክር ወረቀቶች፤

ዘ) የባንክ፣ የመድህን፣ የመርከብ ማጓጓዣ፣ የሎጂስቲክስ እና ሌሎች ከፓርኩ ጋር አግባብነት ያላቸው አገልግሎቶች፤

ዠ) የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀት፤

የ) አሠሪና ሠራተኛ መዋጮዎችን ለግል ጡረታ ፈንድ የመሰብሰብ አገልግሎት፤

ደ) ከሥራው ጋር በተያያዘ የሠራተኛውን ደኅንነትና ጤንነት የተመለከተ ክትትል እና ድጋፍ፤

ጀ) ቅሬታዎችን ማስተናገድ እና ክርክሮችን መፍታት ወይም አግባብ ባለው አካል በተለይ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶች በመጠቀም እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

2. ሁሉም አግባብነት ያላቸው የመንግሥት ተቋማት ለኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መስጠት የሚገባቸውን አገልግሎቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ቅርንጫፍ ገብተው የመስጠት ወይም ኮሚሽኑን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማትን በመወከል አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

3. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ በፓርኩ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ውስጥ በመታቀፍ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌኮም (የድምጽ፣ የዳታ፣ የቪዲዮና ተዛማጅ አገልግሎቶች)፣ የፈሳሽ እና የደረቅ ቆሻሻ የማስወገድ እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን በቀጥታ ራሱ ወይም በሌላ አቅራቢ እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

4. የአንድ ማዕከል አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ያለበት መንግሥታዊ ተቋም የኢንዱስትሪ ፓርክን ባሕሪይ ከግምት ውስጥ ያስገባ ልዩ መዋቅርና ዝርዝር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

5. የአንድ ማዕከል አገልግሎትን የተቀናጀና ውጤታማ ለማድረግ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት በኮሚሽኑ አስተባባሪነት ስምምነት መፈራረም አለባቸው፡፡

## 16. <u>የቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ አገልግሎት ስለመስጠት</u>

1. ኮሚሽኑ ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ የውጭ አገር ዜጎች እና በእነርሱ ሥር ለሚተዳደሩ ቤተሰቦቻቸው ተገቢውን ቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኙ ሊጠይቅላቸው ይችላል፡፡

2. ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ የውጭ አገር ዜጋ ከሦስተኛ አገር ሆኖ የቪዛ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ወደ መኖሪያ አገሩ መመለስ ሳያስፈልገው ካለበት አገር የቪዛ ጥያቄ ሊያቀርብና ሊሰጠው ይችላል፡፡

3. ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት ባለቤት ወይም ባለአክስዮን የ5(አምስት) ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ በኮሚሽኑ በሚቀርብ ማረጋገጫ መነሻነት ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚሰራ የውጭ አገር ዜግነት ያለው አስተዳዳሪ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ምርት ገገር፣ ሠራተኛ፣ የሥራ ኃላፊ፣ የዋና መስሪያ ቤት ሥራ አስፈጻሚ፣ የቦርድ አባል ወይም ከፍተኛ ባለሙያ በኮሚሽኑ በሚቀርብ ማረጋገጫ መነሻነት የ3 (ሦስት) ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

17. <u>**የሥራ ፈቃድ ስለመስጠት**</u>

1. ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጠው አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ለሚቀጥረው የውጭ አገር ዜጋ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ በውጭ አገር ሠራተኛነት ተቀጥሮ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ሠራተኛ የትዳር አጋር በአገሪቱ ውስጥ አብሮ የሚኖር ከሆነ የሥራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

18. <u>**ስለዕውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር**</u>

1. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ የሠራተኞች ምልመላ፣ የክህሎት ልማትና ሽግግር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ማሳደግ እንዲሁም የግብዓት አቅርቦትና የገበያ ትስስር ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የክህሎትና እውቀት ሽግግር ወደ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች እንዲደረግ የሚያስችል የስልጠና መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ ስልጠናውም በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪና ድርጅት እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡
3. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ሽግግሩ እንዲፋጠን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤ በተለይ በመንግሥትና በኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች አጋርነት የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ቴክኖሎጂ ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ምርታማነትና የምርት ጥራት የማሳደግ እንዲሁም ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

4. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ኢንስቲትዩቶች እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንዲከፍቱ ያደርጋል ወይም ባለሙያዎች ይመድባል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የኢንዱስትሪ ፓርክን የተመለከተ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

### 19. የጉምሩክ ቁጥጥር

1. ማንኛውም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ይከናወናል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ ሙሉ በሙሉ ወይም ከፊል የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ቁጥጥር ክልል ይኖረዋል፡፡
3. ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ቁጥጥር የሚካሄደው በጉምሩክ ክልል መግቢያና መውጫ በሮች እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርኮች በሮች ላይ ይሆናል፡፡
4. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ቁጥጥር ክልል የተለያዩ ዕቃዎች ሲያስገባና ሲያስወጣ በተቃለለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ይስተናገዳል፡፡
5. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚያስተላልፈው ጭነት እስከ ኢንዱስትሪ ፓርክ ድረስ በሚጓጓዝበት ወቅት አይቆምም፤ አይፈተሽም፤ ነገር ግን ዕቃው በኮንቴነር የታሸገ እና የዕቃው ማጓጓዣ ሰነድም መድረሻ ጣቢያ የሆነው የኢንዱስትሪ ፓርክ ስም መገለጽ አለበት፡፡
6. በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኝ ምርቱን ሙሉ ለሙሉ ወደ ውጭ አገር የሚልክ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የምርት ግብዓቶችን ከውጭ አገር ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሲያስገባ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አይከፍልም፤ ሆኖም ድርጅቱ ምርቱን በከፊል አገር ውስጥ የሚሸጥ ከሆነ በልዩነቱ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ይከፍላል።
7. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ምርቱን በኢንዱስትሪ ፓርኩ ወይም በሌላ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለሚገኝና ምርቱን ወደ ውጪ ለሚልክ ድርጅት በግብዓትነት ሲያቀርብ ያለቀረጥና ታክስ መሸጥ ይችላል፡፡

8. በጉምሩክ ክልል ውስጥ ያለ ድርጅት በአገር ውስጥ የተመረተ ግብዓትን ምርቱን ወደ ውጭ አገር ለሚልክ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ሲያቀርብ ያለ ቀረጥና ታክስ መሸጥ ይችላል፤ ይህ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅትም ከጉምሩክ ክልል የገዛውን የምርት ግብዓት ተጠቅሞ የሚያመርተው ምርት ወደ ውጭ አገር የሚልክ ከሆነ በዚህ የምርት ግብዓት ላይ ታክስና ቀረጥ አይጠየቅም፡፡
9. ምርቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተስማማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከውጭ አገር ያለቀረጥና ታክስ ያስገባውን ጥሬ ዕቃ እስከ አንድ ዓመት ማቆየት ይችላል፤ ሆኖም ድርጅቱ ጥሬ ዕቃውን ከአንድ ዓመት በላይ ለማቆየት አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ ኮሚሽኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
10. ሙሉ ምርቱን ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተስማማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በማናቸውም ሁኔታ በጉምሩክ ክልል ውስጥ መሸጥ አይፈቀድለትም፤ ሆኖም በልዩ ሁኔታ በቦርዱ የተፈቀደለት ከሆነ ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከፍሎ በጉምሩክ ክልል መሸጥ ይችላል፡፡
11. ሙሉ ምርቱን ወደ ውጭ አገር እንዲልክ የሚጠበቅበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ያመረተው ምርት የኤክስፖርት ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም ምርቱ ወደ ውጭ ከተላከ በኋላ ጉድለት ኖሮት የተመለሰ ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበ፡-
    ሀ) በኮሚሽኑ ሲፈቀድ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በተዘጋጀ ልዩ ቦታ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ከአንድ ሳምንት ለማይበልጥ ተከታታይ ቀናት ልዩ የሽያጭ መርሀ-ግብር ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፍሎበት ሊሸጠው ወይም፣
    ለ) በአገሪቱ ውስጥ በሕግ አግባብ ለተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ ሊሰጠው ወይም፣
    ሐ) በሌላ መንገድ ሊያስወግደው ይችላል፡፡
12. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ተረፈ ምርቱን የተጨማሪ እሴት ታክስ ብቻ ከፍሎ በጉምሩክ ክልል ውስጥ መሸጥ ይችላል፤ ድርጅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሱን የሚከፍለው ግብይቱ በሚከናወንበት ጊዜ በሚኖረው ዋጋ ላይ ይሆናል፡፡
13. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት ከውጭ ያስመጣቸውን የተበላሹ ወይም እክል ያለባቸውን የካፒታል ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎች እና አክሰሰሪዎች ለባለሥልጣኑ የዋስትና ደብዳቤ በማቅረብ ወደ ውጭ ልኮ መተካት ወይም

ማስጠገን ይችላል፣ ይህንን በተመለከተ ከባለሥልጣኑ ምንም ክፍያ አይጠየቅም፡፡

14. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ሳይጠይቅ ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን ዕቃ ቀረጥና ታክስ የማይፈለግበት ከሆነ ከአገር መልሶ የሚወጣ ዕቃ ላይ የተጣለ ክፍያ ሳይፈጽም ባለሥልጣኑን በማስፈቀድ ማስወጣት ይችላል፡፡
15. የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት ወይም ጉዳት የደረሰበት የምርት ግብዓት ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ማረጋገጫ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ እንዲወገድ ማድረግ ይችላል፡፡

20. <u>**በጉምሩክ አሰራር ላይ የሚፈጸም ጥሰት**</u>

የጉምሩክንና ሌሎች ሕግጋትን የጣሰ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ቅሬታ እና ክርክር ስለሚፈታበት ሥርዓት

21.<u>**መርሆዎች**</u>

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚነሳ የአስተዳደር ቅሬታ፣ የፍትሐብሔር እና የንግድ ክርክር ቀልጣፋ፣ ሚዛናዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይፈታል፡፡
2. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የሚፈጠር ቅሬታና የወል ወይም የተናጠል የሥራ ክርክር ለአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች ቅድሚያ በመስጠት በሠራተኛና አሠሪ ሕግ መሠረት ይፈታል፡፡

22.<u>**አስተዳደራዊ እርምጃ**</u>

1. ፈቃዱን ለማግኘት የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች፣ ይህን ደንብ፣ መመሪያዎችን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕግጋት የጣሰው የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ከሆነ ቦርዱ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከሆነ ደግሞ ኮሚሽኑ ከስልሳ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡
2. ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ

እንደአግባብነቱ በቦርዱ ወይም በኮሚሽኑ ከስልሳ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ፈቃዱ ሊታገድ ይችላል፡፡

3. ፈቃዱ የታገደበት የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ማስተካከያ አድርጎ ወደ ሥራ ካልተመለሰ ቦርዱ የሦስተኛ ወገኖችን መብት ለማስጠበቅ ሲል አግባብ ባለው አካል ጊዜያዊ ባለአደራ እንዲሰየምና ቀጣይ እርምጃ እንዲወሰድ ሊወስን ይችላል፡፡

23.በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ በኮሚሽኑ በሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ለቦርዱ ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በኮሚሽኑ በተሰጠ ውሳኔ ወይም በተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅር በመሰኘት ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ በኮሚሽኑ ከተሰጠው ውሳኔ ወይም ከተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ግልባጭ ጋር በጽሁፍ መቅረብ አለበት፡፡
3. ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ እና የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ የሚመለከተው ወገን በጽሑፍ እንዲሰጠው ከጠየቀ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ሊሰጠው ይገባል፡፡

24.በቦርዱ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

1. በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍርድ ቤት በይግባኝ መውሰድ ይችላል፡፡
2. ቅሬታ አቅራቢው የቦርዱ ውሳኔ ግልባጭ በጽሑፍ እንዲሰጠው ከጠየቀ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ በቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሊሰጠው ይገባል፡፡

25.በሌሎች መንግሥታዊ አካላት ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ በሌሎች ማናቸውም መንግሥታዊ አካላት ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ውሳኔ ወይም በሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበን ቅሬታ በየኢንዱስትሪ ፓርኩ የአንድ ማዕከል አገልግሎ ውስጥ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው ቅሬታ ለኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ቀርቦ ከታየ በኋላ ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው

ባለጉዳዮች ጋር በመነጋገር በሰላሳ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ ሀሳብ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

26.**<u>ቅሬታን በእርቅ ስለመፍታት</u>**

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ቅሬታዎችን ኮሚሽኑ በአንድ ማዕከል አገልግሎት በእርቅ መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አገልግሎት የሚሰጠው ቅሬታ ውስጥ የገቡት ወገኖች የአስታራቂነት ጥያቄያቸውን ተስማምተው በጽሑፍ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት ሲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡
3. የአስታራቂነት ጥያቄ ለኮሚሽኑ በቀረበ ጊዜ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የቅሬታ አፈታት ባለሙያ እንደአስፈላጊነቱ ከባለጉዳዮቹ ጋር በመነጋገር እጅግ ቢዘገይ ቅሬታው በቀረበ ሰላሳ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ የመፍትሔ ሐሳብ በጽሁፍ ያቀርባል፡፡
4. በኮሚሽኑ የቀረበውን የመፍትሔ ሀሳብ እንደሚቀበሉት ቅሬታ ውስጥ የገቡት ወገኖች በጽሁፍ ያረጋገጡ እንደሆነ የቀረበው ሀሳብ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡
5. የእርቅ ሀሳቡ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ሁሉም ወገኖች የእርቅ ሀሳቡን እንደተቀበሉ በጽሑፍ ካላረጋገጡ እንዳልተቀበሉት ይቆጠራል፡፡
6. በእርቅ ሂደት የሚኖር ወጪ ተገልጋዮቹ ይሸፍናሉ፤ ይህንንም አስቀድመው ሊስማሙ ይገባል፡፡

27.**<u>በግልግል ዳኛ ስለመጨረስ</u>**

1. የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች ቅሬታቸውን በግልግል ዳኛ ለመጨረስ መስማማት ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ስምምነት በጽሑፍ መደረግ አለበት፤ ዝርዝሩ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል፡፡

28.**<u>የግልግል ዳኛ መሆን የሚችሉ ባለሙያዎች ዝርዝር</u>**

1. ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች የሚቀርበውን ጥቆማ መሠረት በማድረግ በግልግል ዳኝነት ለመስራት ተአማኒነትና የሙያ ብቃት ያላቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ዝርዝር ኮሚሽኑ በየሁለት ዓመቱ ወቅታዊ ያደርጋል፡፡

29. **የግልግል ዳኛ አመራረጥ**

1. ክርክራቸውን በግልግል ዳኛ ለመጨረስ የተሰማሙ ወገኖች በዚህ ደንብ አንቀጽ 28 ከተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በግልግል ዳኝነት መምረጥ ይችላሉ፡፡
2. የግልግል ዳኞች ስንት እንደሚሆኑ ወይም እንዴት እንደሚመረጡ ስምምነቱ ያላመላከተ እንደሆነ እያንዳንዱ ወገን አንድ የግልግለ ዳኛ ይመርጣል፡፡
3. ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር የግልግል ዳኞች ብዛት በጥንድ የሚቆጠሩ እንደሆነ ዳኞቹ ወደ ሥራው ከመግባታቸው በፊት አንድ ሌላ የግልግል ዳኛ ይመርጣሉ፡፡ ይኸውም የተመረጠው የግልግል ዳኛ ለግልግል ዳኝነቱ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ በግልግል ዳኞቹ መካከል ስምምነት የሌለ እንደሆነ ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ በሚያቀርበው ጥያቄ የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማህበር የግልግል ኢንስቲትዩት በዚህ ደንብ አንቀጽ 28 ከተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ይመርጣል፡፡
4. ብዛታቸው በጥንድ የማይቆጠሩ እንደሆነ የግልግል ዳኞቹ ከመካከላቸው ሰብሳቢ የሚሆነውን ይመርጣሉ፡፡ በግልግል ዳኞቹ መካከል ስምምነት የሌለ እንደሆነ ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ በሚያቀርበው ጥያቄ የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማህበር የግልግል ኢንስቲትዩት ከግልግል ዳኞቹ መካከል ለግልግል ዳኝነቱ ሰብሳቢ ይሾማል፡፡

30. **ተፈጻሚነት የሚኖረው ሕግ**

ቅሬታቸውን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የተስማሙ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች ጉዳያቸው የሚፈታበትን መሠረታዊና የሥነ-ሥርዓት ሕግ መምረጥ ይችላሉ፡፡

31. **የግልግል ዳኛ የአገልግሎት አበል**

ኮሚሽኑ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር በኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መካከል በሚደረግ የግልግል ዳኝነት የግልግል ዳኛ ሆነው የሚያገለግሉ ሰዎች የሚከፈላቸውን አበል ለመወሰን የሚረዳ የክፍያ ተመን ሰንጠረዥ ያዘጋጃል፤ የተመን ሰንጠረዡም በየሁለት ዓመቱ ወቅታዊ ያደረጋል፡፡

32. **ተዘዋዋሪ ችሎት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ስለሚያስችልበት ሁኔታ**

ኮሚሽኑ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጋር በመመካከር አግባብነት ያለው የፌደራል ፍርድ ቤት ተዘዋዋሪ ችሎት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚያስችልበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 33.የግል መገልገያ ዕቃዎች

1. በኢንዱስትሪ ፓርክ የተሰማራ የውጭ ባለሀብት ወይም ከውጭ አገር የተመለሰ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በሚሰራበት ጊዜ የግል መገልገያ ዕቃዎች እንደ የሳሎን/የመኝታ ቤት፣ የወጥ ቤት፣ የባኞ ቤት እና የስፖርት ዕቃዎች፣ ላፕ ቶፕ እና ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች፣ የሙዚቃ መሳሪያ፣ ካሜራ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ቲቪ፣ ሲዲ ማጫወቻ እና የመሳሰሉ ሌሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች ያለቀረጥና ታክስ ከውጭ አገር ማስገባት ይችላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
2. በኢንዱስትሪ ፓርክ የተሰማራ የውጭ ባለሀብት ወይም ከውጭ አገር የተመለሰ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ወደ አገር ውስጥ ያስገባቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች፡-

   ሀ) ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ያለቀረጥና ታክስ ማስተላለፍ ይችላል፤

   ለ) አስቀድሞ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል ለራሱ ከፓርክ ውጪ ሊወስደው ወይም ተመሳሳይ መብት ለሌለው ሰው ማስተላለፍ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መብቱን ማስተላለፍ የሚፈልግ ሰው ከማስተላለፉ በፊት ኮሚሽኑን ማስፈቀድ አለበት።

### 34.ከደመወዝ ገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን

ምርቱን ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተስማማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያ አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ የሚቀጥራቸው ባለሙያ የውጭ አገር ዜጎች ከደመወዝ ገቢ ግብር ነፃ ይሆናሉ፡፡

35.**የሦስትዮሽ አሰራር ኮሚቴ**

1. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ እንደሁኔታው የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት አሰሪዎች እና የሠራተኛ ተወካይ የሚገኙበት የሦስትዮሽ አሰራር ኮሚቴ ይቋቋማል።
2. የሦስትዮሽ አሰራር ኮሚቴው፡-
   ሀ) ቀጣይነት ያለው ምክክር በማድረግ የሠራተኛ መብትና ግዴታ መከበሩን ማረጋገጥ፣ ግጭት እንዳይከሰት አመቺ ሁኔታ የመፍጠር፤
   ለ) ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር የእውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር መደረጉን በማረጋገጥ ምርታማነት እንዲጨምር የማድረግ፤
   ሐ) ሌሎች የኢንዱስትሪ ሰላም ለማስፈን የሚረዱ ተግባራትን የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡
3. ኮሚሽኑም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተግባሩን በአግባቡ ስለማከናወኑ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ይቆጣጠራል፡፡

36.**ሕግ ስለማስከበርና የመረጃ ልውውጥ**

1. ኮሚሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ አግባብነት ያላቸው የፀጥታና የሕግ አስከባሪ አካላት ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ጋር በትብብርና በቅንጅት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት ወይም የሥራ ኃላፊ የፈቃድ መስፈርት መጣሱን ያወቀ ወይም ሌላ ምርመራ የጀመረ አግባብ ያለው አካል ጥሰቱን ወይም የጀመረውን ምርመራ በተመለከተ ኮሚሽኑን ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

37.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን በፊት የተሰየመን የኢንዱስትሪ ፓርክ በተመለከተ ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚዎች፤ አስተዳዳሪዎች እና ድርጅቶች ጋር የተፈጸሙ የመግባቢያ ስምምነቶችና የተሰጡ ውሳኔዎች ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

2. በዚህ ደንብ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ የተሻለ መብት የሚሰጡ ድንጋጌዎች ከዚህ ደንብ መውጣት በፊት በተሰየመ የኢንዱስትሪ ፓርክ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

38.<u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

1. ኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም፣ ፈቃድ፣ ግንባታ፣ አስተዳደር፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣ ቪዛና የመኖሪያ ፈቃድ፣ ጉምሩክ፣ የወጪ ንግድ፣ ቅሬታ አፈታት እና ሌሎች ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ከቅርብ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ረቂቅ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በቦርዱ ያጸድቃል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቦርዱ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ለመተግበር የሚያስችሉ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎች ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ማውጣት አለበት፤ ኮሚሽኑ በሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ መውጣቱን ይከታተላል፤ ያስተባብራል፡፡

39.<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ደንቦች፣ መመርያዎች እና አሰራሮች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

40.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 5 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ሠ/ ስለምርት ገበያ**

## አዋጅ ቁጥር 550/1999

## የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የሀገሪቱን ግብርና በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የአመሠራረት ሥርዓት ማሸጋገር ድህነት ለመቀነስ ወሳኝ መሣሪያ መሆኑ በመንግሥት ዋና ዋና ፖሊሲዎች የተገለጸ በመሆኑ፤

አነስተኛ የግብርና አምራቾች ወቅታዊ የገበያ መረጃ እንዲያገኙና ለምርታቸው የተሻለ ዋጋ መደራደር እንዲችሉ በማድረግ በገበያው ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ ተገቢ በመሆኑ፤

ለዚህም ቀልጣፋ፣ ሥርዓት ያለውና ወጥነት ያለው የግብርና ምርቶችን የገበያ ሥርዓት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም" ማለት የምርት ገበያው ወይም በባለሥልጣኑ እውቅና ያገኘ የአገር ውስጥ ባንክ ወይም ተመሳሳይ የፋይናንስ ተቋም ነው፤
   2. "የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም" ማለት አንድ ድርጅት በአገናኝነት ወይም በአቀራራቢነት የሚሠራበት ሥነ ሥርዓት፣ ድርጅቱ ለግብይቱ አፈጻጸም የገዢና የሻጭን ሚና በመውሰድ በተዋዋይ ወገኖች የሚሰጡትን ትዕዛዞች የሚያስታርቅበትና የገንዘብ ክፍያና ርክክብ የሚፈጸምበት አሠራር ነው፤
   3. "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 551/1999 የተቋቋመው የምርት ገበያ ባለሥልጣን ነው፤
   4. "ምርት" ማለት ከሌላ አንድ ዓይነት ምርት ጋር መለዋወጥ የሚችል ምርት ነው፤

5. “የምርት ገበያ” ማለት ወጥ ሆነው በተዘጋጁ ምርት ነክ ውሎች ግብይት የሚፈጸምበት የምርት ገበያ ነው፤
6. “ውል” ማለት ለምርት ገበያ ግብይት ሲባል አንድን ምርት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀና የምርቱን መጠን፣ ዋጋ፣ ደረጃ፣ መነሻ ቦታ፣ ተፈጻሚ የሚሆንበትንና የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበትን ቀን በዝርዝር የሚያካትት ስምምነት ነው፤[61]
7. “ዳታ” ማለት የኤሌክትሮኒክስ ዳታ ልውውጥን፣ የኤሌክትሮኒክስ መልዕክትን፣ ቴሌግራምን፣ ቴሌክስንና ቴሌኮፒን ጨምሮ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኦፕቲካል ወይም በተመሳሳይ ዘዴዎች የሚመነጭ፣ የሚላክ፣ የሚደርስ ወይም የሚከማች መረጃ ነው፤
8. “የኤሌክትሮኒክ ፊርማ” ማለት ከመረጃ መልዕክቶች ጋር በተያያዘ ፈራሚን ለመለየትና በመልዕክቱ የተካተተው መረጃ በፈራሚው የፀደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውል በመረጃ መልእክት ላይ የተለጠፈ ወይም ከመልዕክት ጋር የተያያዘ በኤሌክትሮኒክስ ፎርም ያለ መረጃ ነው፤
9. “የግብይት ፈጻሚ” ማለት ለሌሎች ወይም ለራሱ ሲል የምርት ግብይት ውሎችን በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ የተሰማራ በባለ ሥልጣኑ ዕውቅና ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፤
10. “ለወደፊት የሚፈጸም ውል” ማለት በተቆረጠ የወደፊት ቀን የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበት ምርትን ለመሸጥ ወይም ለመግዛት የሚደረግ የምርት ግብይት ውል ነው፤
11. “የመያዣ ገንዘብ” ማለት ግዢ ፈጻሚዎች በገበያ ላይ ለሚፈጽሙት አንድ ግብይት በመያዣነት ሊያስቀምጡት የሚገባ ገንዘብ ነው፤
12. “አባል” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 (1) የተመለከተውን የምርት ገበያ የአባልነት መመዘኛ የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ነው፤
13. ሚኒስቴር’ ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሚኒስቴር ነው፤[62]

---

[61] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

[62] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

14.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

15.“ወዲያውኑ የሚፈጸም ውል” ማለት ርክክብና ክፍያ ወዲያውኑ የሚፈጸምበት የምርት ግብይት ውል ነው፡፡

16.“ጥብቅ የማቆያ ሥፍራ” ማለት በምርት ገበያው ግብይት የሚካሄድበትን ምርት የያዙ የጭነት ተሽከርካሪዎች ጭነቱ ተሽከርካሪው ላይ እንዳለ ተሽጦ ወደገዥ እስከሚተላለፍበት ወይም በምርት ማከማቻ መጋዘን እስከሚራገፍበት ድረስ ባለው ጊዜ የሚቆሙበት የተከለለና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ነው፡፡[63]

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ምርት ገበያ

### 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ የምርት ገበያ /ከዚህ በኋላ “የምርተ ገበያ” እየተባለ የሚጠራ/ ሙሉ ባለቤትነቱ የመንግሥት የሆነና የሕግ ሰውነት ያለው የገበያ ተቋም ሆኖ ተቋቁሟል፡፡
2. የምርት ገበያው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 የተመለከቱትን የሚያሟሉ መቀመጫዎች ያሏቸው አባላት ይኖሩታል፤
3. የምርት ገበያው ባለቤትነት፣ አባልነትና የሥራ አመራሩ የተለያዩ ይሆናል፤
4. የምርት ገበያው በዚህ አዋጅ፣ በምርት ገበያ ባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 እና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች የሚተዳደር ይሆናል፡፡

### 4. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን[64]

የንግድ ሚኒስቴር የምርት ገበያው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

### 5. ዋና መሥሪ ቤት

የምርት ገበያው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን በሌሎች ቦታዎች ማቋቋም ይችላል፡፡

### 6. ዓላማዎች

የምርት ገበያው የተቋቋመበት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

[63] 23/7/8 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(3) አዲስ የገባ ነው፡፡

[64] በ25/8 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(4) መሰረት የንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

1. የገጢዎችን፣ የሻጮችንና የአገናኞችን ፍላጐት በማርካትና የኢትዮጵያ አነስተኛ አምራቾች የገበያ ተሳትፎን በማሳደግ ውጤታማ፣ ግልጽ አሠራርን የተከተለና በሥርዓት የሚመራ የግብይት ሥርዓት መፍጠር፤
2. የግገር ጥያቄ አቅርቦትና የግገር ጨረታ ውድድር ተቀናጅተው በግልፅ ጨረታ መድረክ በቃል በማስተጋባት ተጫራቾች ጨረታ በግላጭ በሚያካሂዱበት የመገበያያ መድረክ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ትዕዛዝን በሚያቀነባብር ሥርዓት ወይም ሁለቱም የሚካሄድበት የንግድ አሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፤
3. የምርት ግብይትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመያዝ፣ ለመከታተል፣ ለሕዝብ ለማሠራጨት የሚያግዝ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቢሮ አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ፤
4. ደረጃ ለወጣላቸው ምርቶች ግብይት መሠረት የሚሆኑ ወጥነት ያላቸው ውሎችን ማዘጋጀት፤
5. የምርት ደረጃ የምስክር ወረቀትንና ዋስትና ያለው የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝን መሠረት በማድረግ ግብይት ማካሄድ፤
6. ግዴታን ባለመወጣት የሚያጋጥሙ አደጋዎችን ለመቀነስ በምርት ገበያው የሚከናወኑ ግብይቶችን ክፍያና ርክክብ መፈጸም፤
7. ክርክሮች በሽምግልና ዳኝነት አማካይነት የሚታዩበትን ሥርዓት መዘርጋት፤
8. ወቅታዊ የገበያ መረጃዎችን ለሕዝቡ ማቅረብ፤
9. የምርት ገበያውንና የአባላቱን ህልውናና ጤናማ አሠራር የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ገበያውን በቅርብ መከታተል፣
10. የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደርን ተግባራዊ በማድረግ በአጠቃላይ የገበያ ሥርዓቱ ላይ አደጋ እንዳይከሰት መከላከል፡፡
11. ስትራተጂያዊ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የምርት ማከማቻ መጋዘኖችን እና ጥብቅ የማቆያ ሥፍራዎችን መገንባትና ማስተዳደር፤[65]
12. በምርት ገበያው ግብይት የሚደረግባቸው ምርቶች የሚጓጓዙበትን ሁኔታ በተመለከተ እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ካለው የመንግሥት አካል በሚሰጠው

[65] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(5) አዲስ የገባ ነው፡፡

ውክልና መሠረት አስገዳጅ መስፈርት ማውጣት፣ ተፈጻሚነቱን የማረጋገጥ እና ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ፡፡[66]

7. **ካፒታል** [67]

የምርት ገበያው የተፈቀደ ካፒታል 1 ቢሊዮን 250 ሚሊዮን (አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃምሣ ሚሊዮን) ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 725 ሚሊዮን (ሰባት መቶ ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

8. **ስለ አባልነት**

1. አባል ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፣

   ሀ) በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት በግብይት ፈጻሚነት ዕውቅና ያገኘ፣ እና

   ለ) ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ሲል በምርት ግብይት ሥራ የተሰማራ፣

   መሆን ይኖርበታል፡፡

2. የምርት ገበያው በሚደነግገው ሁኔታዎች መሠረት የምርት ገበያው በነጻ ሊተላለፉ የሚችሉ ቋሚ መቀመጫዎች ያሏቸው አባላት ይኖሩታል፡፡

3. በምርት ገበያው የተዘጋጁና በባለሥልጣኑ የፀደቁ የምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች ለአባልነት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን ይደነግጋሉ፣

4. በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች ስር የተመለከቱትን የአባልነት መመዘኛዎች ማንኛውም ሰው የአባል መቀመጫ ሊገዛ ይችላል፡፡

5. አባል መሆን በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ በተመለከቱት መብቶችና ጥቅሞች የመጠቀም መብት ይሰጣል፡፡

6. አባልነት ከሌሎች መብቶች በተጨማሪ በምርት ገበያው የመገበያየት መብት ይሰጣል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 (1) የተደነገገው ቢኖርም በምርት ገበያው የአባልነት መቀመጫ ሳይኖራቸው ያለአገናኝ በምርት ገበያው በራሳቸው መገበያየት የሚችሉ ምርት ሻጮች ወይም ገዥዎች የሚስተናገዱበት ዝርዝር ሁኔታ በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡[68]

9. **የምርት ገበያው፣ የአባላቱና የሦስተኛ ወገኖች ተጠያቂነት**

[66] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(5) አዲስ የገባ ነው፡፡

[67] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(6) ተሻሻለ፡፡

[68] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(7) አዲስ የገባ ነው፡፡

1. የምርት ገበያው ሹማምንቶቹ፣ ዳይሬክተሮቹና ሠራተኞቹ ለሚፈጽሙት ድርጊት ወይም ግድፈት ተጠያቂ ነው፡፡
2. የምርት ገበያው ከዚህ በታች ከተመለከቱት ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥሙ ጉድለቶች ተጠያቂ ነው፣
   ሀ) ከምርት ገበያው የግብይት ሥርዓት፣
   ለ) ከምርት ገበያው የመረጃ ሥርጭት ሥርዓት፣
   ሐ) በምርት ገበያው ከሚካሄዱ የማከማቻ መጋዘኖች፣ የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞችና የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞች ማስቀመጫ፣
   መ) በምርት ገበያው ከሚሰጡ የደረጃና የምርት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት፣
   ሠ) በምርት ገበያው ከሚከናወኑ የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም፣
3. የምርት ገበያው ከንብረቱ በላይ በዕዳ አይጠየቅም፡፡
4. አባላት የምርት ግብይት ውሎችን ሳይፈጽሙ ሲቀሩ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
5. አባላት በስማቸው ተወክሎ የሚሠራ ሰው ለሚፈጽመው ድርጊት፣ ግድፈት ወይም ጉድለት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
6. በምርት ገበያው የተመሰከረላቸው ወይም ከምርት ገበያው ጋር የሥራ ግንኙነት ኖሯቸው ማከማቻ መጋዘንን፣ የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞችንና የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞች የማስቀመጥ ሥራን የሚያካሂዱ የደረጃና የምስክርነት ማረጋገጫ የሚሰጡ፣ ክፍያን የሚያስፈጽሙ ወይም ሌሎች ሥራዎችን የሚያከናውኑ ሦስተኛ ወገኖች አግባብ ባላቸው ህጎችና ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

10.<u>**የምርት ገበያው አቋም**</u>

የምርት ገበያው፣

1. የዳሬክተሮች ቦርድ፣
2. አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ እና
3. አስፈላጊው ኃላፊዎችና ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

11.<u>**የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥንቅር**</u>

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ሰብሳቢውን ጨምሮ ስድስቱ በሚኒስቴሩ ይሰየማሉ፤ አምስቱ በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ መሰረት ከአባላት ወይም ከአባል ማህበራት ይመረጣሉ፡፡[69]
2. ዋናው ሥራ አስፈጻሚ ድምፅ የማይሰጥ የቦርድ አባል ይሆናል፡፡
3. የቦርድ ዳይሬክተር የሹመት ወይም የምርጫ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም የቦርድ ዳይሬክተሩ እንደገና መሾም ወይም መመረጥ ይችላል፡፡
4. የቦርድ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን ሳያቋረጡ እንዲያከናውኑ ለማድረግ ለሁሉም የዳይሬክተሮቹ የሥራ ዘመን በአንድ ጊዜ እንዲያበቃ አይደረግም፡፡
5. የቦርድ ዳይሬክተር ቦታ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ ሥራውን የለቀቀው ዳይሬክተር በተሾመበት ወይም በተመረጠበት ሁኔታ ሌላ ሰው እንዲመረጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጉዳዩን ሚኒስቴሩ ወይም የምርት ገበያው አባላት እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

12.<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር</u>

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የምርት ገበያውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሾማል፤
2. የምርት ገበያውን በበላይነት ይቆጣጠራል፤
3. ለዋናው ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት እንዲሁም ደሞዝና አበላቸውን ያፀድቃል፤
4. የምርት ገበያውን ኮርፖሬት ፕላንና ግብ፣ የምርት ግብይት አገልግሎት ክፍያ አደረጃጀት እና የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደር ስትራቴጅን ያጸድቃል፤
5. የተጣራ ትርፍ ለተወሰኑ ስራዎች ወይም ለኢንቨስትመንት እንዲውል መደረጉን ያጸድቃል፤
6. የምርት ገበያው ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለሚኒስቴሩ ሃሳብ ’ ያቀርባል፤
7. ምርት ገበያው የሂሣብ መዝገብ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፤
8. ለምርት ገበያው ኦዲተሮች የሂሣብ መግለጫ ያቀርባል፤
9. በየወቅቱ የፋይናንስና የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

[69] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(8) ተሻሻለ፡፡

10. በባለሥልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባልነትን፣ ንግድን፣ የክፍያና ርክክብ አፈጻጸምን፣ የምርት ገበያውን የግብይት ውሎችን የሚመለከቱ የምርት ገበያውን ደንቦችና መመዘኛዎች ያወጣል፣ ያሻሽላል፤
11. በባለሥልጣኑ በፀደቀው የምርት ገበያው የውስጥ ደንብ በተደነገገው መሠረት የምርት ገበያውን አዲስ አባል ይቀበላል፤ ከአባልነት ያግዳል ወይም ያሰናብታል፤
12. በምርት ገበያው የተዘረጋው የሽምግልና ዳኝነት ሥርዓት በአግባቡ መሰራቱን ያረጋግጣል፤
13. የቦርዱን ጸሐፊ ከምርት ገበያው ሠራተኞች መካከል መርጦ ይመድባል፤
14. የምርት ገበያውን በአግባቡ ለመምራት የሚረዱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡

13. <u>**የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት**</u>

1. የቦርዱ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን በተገቢው ጥንቃቄ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡
2. የቦርድ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን በአግባቡ ባለማከናወናቸው ምክንያት በምርት ገበያው ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት በነጠላና በአንድነት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም፣ ጉዳት ያደረሰው የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሣኔ ሲተላለፍ በድምጽ የተለየ የቦርድ ዳይሬክተር በኃላፊነት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

14. <u>**የዳይሬክተሮች ቦርድ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት**</u>

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ቢያንስ አራት የቦርድ ዳይሬክተሮች ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ሲጠይቁ ሊቀመንበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ይጠራል፡፡
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የስብሰባ አጀንዳ ለቦርድ ዳይሬክተሮች በቅድሚያ መድረስ ይኖርበታል፡፡
4. አብዛኞዎቹ የቦርድ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይኖራል፡፡
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡
6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ጉዳዮች የሚወሰኑት በሁለት ሦስተኛ የቦርድ ዳይሬክተሮች ድምጽ ይሆናል፤

ሀ) ክፍያዎች፣

ለ) የተጣራ ትርፍን እንደገና ኢንቨስት የማድረግ፣

ሐ) የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹመት፣

መ) የምርት ግብይት ደንቦችን ማፅደቅና ማሻሻል፣

7. የዳይሬክተሮች ቦርድ እያንዳንዱን ስብሰባ በተመለከተ በስብሰባ ላይ በተገኙ የቦርድ አባላት የተፈረመ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፤

8. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የዳይሬክትሮች ቦርድ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

15.<u>የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በመንግሥት የሚወከሉ የቦርድ ዳይሬክተሮችን ይሾማል፣ ያነሳል፤
2. ለቦርድ ዳይሬክትሮች የሚከፈለውን አበል ይወስናል፤
3. የውጭ ኦዲተሮችን አወዳድሮ አሸናፊውን ይመድባል፤
4. የምርት ገበያውን የተፈቀደ ካፒታል እንዲመደብ ያደርጋል፤
5. በኦዲተሮች የተመረመሩ የምርት ገበያውን የፋይናንስ ሪፖርቶች ያፀድቃል፤
6. ከምርት ገበያው የቀረበለትን የካፒታል ጥያቄን፣ የተጣራ ትርፍን እና እንደገና ኢንቨስት የማድረጊያ ፕላንን ያፀድቃል፤
7. የምርት ገበያውን አጠቃላይ ሥራ ይገመግማል፣ የግሉ ዘርፍ በባለቤትነት ስለሚሳተፍበት ሁኔታ ጥናቶች ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣
8. የምርት ገበያውን ዓመታዊና የረዥም ጊዜ የምርት ገበያውን የኮርፖሬት ግቦችን ከቦርዱ ጋር በመመካከር ይወሰናል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
9. ለቦርዱ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥትን የባለቤትነት መብቶች ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
10. የምርት ገበያውን አደረጃጀትና መዋቅር ያጸድቃል፡፡[70]

16.<u>የዋና ሥራ አስፈጻሚው ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋናው ሥራ አስፈጻሚ የምርት ገበያውን ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

[70] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(9) አዲስ የገባ ነው፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ሥራ አስፈጻሚ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
   ሀ) በዳይሬክተሮች ቦርድ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ኃላፊዎችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፤
   ለ) በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦችና አግባብ ባላቸው ሕጐች መሠረት የምርት ገበያውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ) የምርት ገበያው ከሦስተኛ ሰዎች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነት ሁሉ የምርት ገበያውን ይወክላል፣
   መ) የምርት ገበያውን የሂሣብ መዛግብት በአግባቡ ይይዛል፣
   ሠ) የምርት ገበያውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
   ረ) እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ማስኬጃ ገንዘቡን ለማሳደግ የአጭር ጊዜ የብድር ውሎች ይዋዋላል፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትን በዋስትና ያስይዛል፣
   ሰ) እንደአስፈላጊነቱ በምርት ገበያው ህልውና ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ቋሚ ንብረቶችን ቦርዱን በማስፈቀድ ይሸጣል፣
   ሸ) ለምርት ገበያው ሥራዎች ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለምርት ገበያው ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል፣
   ቀ) በቦርዱ በሚወሰነው መሠረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ያቀርባል፣
   በ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔን ይፈጽማል፣ እንዲፈጸም ያደርጋል፣
   ተ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

17.<u>**የዋና ሥራ አስፈጻሚው ኃላፊነት**</u>

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በምርት ገበያው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በሕግ መሠረት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

18.<u>**የሥራ አመራር**</u>

1. የምርት ገበያው ገለልተኛ በሆነ ባለሙያ የሚመራ የሥራ አመራር ይኖረዋል፡፡
2. በሚኒስቴሩ መፅደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምርት ገበያው የራሱ የሆነ የደሞዝ ስኬል ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የምርት ገበያው አሠራር

### 19. ስለአባላት የሥራ አመራር

1. የምርት ገበያው እያንዳንዱ አባል ተለይቶ የሚታወቅበትን መዝገብና አቋሙን የሚገልጽ ዳታ ቤዝ ይይዛል፡፡
2. አባላት በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች የተደነገጉ የአባልነት መመሪያዎችን እንዲያከብሩ ያደርጋል፡፡
3. የምርት ገበያው በአባላት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስናገዱበትን ሥርዓት ተግባራዊ ያደርጋል፣ ባለስልጣኑ በጠየቀ ጊዜ የሚቀርብ የቅሬታዎች መዝገብ ያደራጃል፡፡

### 20. ስለግብይትና የግብይት ሥርዓት

1. አባል ያልሆነ ወይም በአባል ተወካይነቱ ዕውቅና ያላገኘ ሰው በምርት ገበያው መገበያየት አይችልም፡፡
2. ስለምርቱ ጥራት ወይም ደረጃ ከምርት ገበያው የምርት የምስክር ወረቀት ሳያገኝ እንዲሁም ስለምርቱ መጠን፣ መነሻ ቦታ ሁኔታና የማከማቻ መጋዘኑ ወይም ጥብቅ ማቆያው የሚገኝበትን ቦታ የሚገልጽ የመጋዘን ማከማቻ ደረሰኝ ሳይኖረው ምርቱን በምርት ገበያው ለግብይት ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡[71]
3. የምርት ገበያው የግልፅ ጨረታ መድረክ በቃል በማስተጋባት ተጫራቾች በግላጭ ጨረታ የሚያካሂዱበት የመገበያያ መድረክ ወይም በርቀት የሚካሄድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የኤሌክትሮኒክስ ንግድን መሰረት ያደረገ የንግድ ሥርዓት ያካሂዳል፡፡
4. የምርት ገበያው ግብይትና የሚመለከቱ ውሎች የሚመዘገቡበትና ከአባላት ግብይት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚያቀላጥፍ ድጋፍ ሰጭ ቢሮ ይኖረዋል፡፡

### 21. የገበያ መረጃዎችን ስለማሠራጨት

1. የምርት ገበያው ለሕዝብ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ስለምርት ዋጋ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ይሰጣል፡፡
2. የምርት ገበያው የዋጋ መረጃዎች እንዳይሰራጩ ወይም ዘግይተው እንዲሰራጩ ማድረግ አይችልም፡፡

[71] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(10) ተሻሻለ፡፡

3. የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክ የዋጋ መረጃ ማሠራጫ ሥርዓት ያደራጃል፡፡

22.የምርት ግብይት ውሎች

1. የምርት ገበያው ከግብርና ምርቶች ጋር በተያያዘ ወዲያውኑ የሚፈጸም ወይም ርክብክባቸው ወደፊት የሚፈጸም ወይም ወደፊት በሚፈጸሙ ውሎች ላይ ተመስርቶ ይሰራል፡፡[72]
2. የምርት ገበያው የምርቱን ደረጃ፣ ምርቱ የሚቀርብበትን ቀንና ቦታ፣ እንዲሁም ሌሎች የውል ድንጋጌዎች ያካተተ ውል ያዘጋጃል፡፡
3. በምርት ገበያው ግብይት የሚደረግባቸው ርክክባቸው ወደፊት የሚፈጸም እና ወደ ፊት የሚፈጸሙ ውሎችን በተመለከተ ዝርዝሩባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያና በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡[73]
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የመንግሥት አካል መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ገበያው ከግብርና ምርቶች ውጭ ያሉ ውሎችን በማጥናት ሊያገበያይ ይችላል፡፡[74]

23.ደረጃ ስለማውጣትና ስለምስክርነት ማረጋገጫ

1. የምርት ገበያው በገበያው ለሚካሄድ ግብይት ዓላማ የፀደቁ ወይም ተቀባይነት ያገኙ ደረጃዎችን ያወጣል፣ ይጠብቃል፡፡
2. የምርት ገበያው ደረጃ የማውጣትና የማረጋገጥ ሥራ ያከናውናል ወይም ሌላ ሦስተኛ ሰው ይህንኑ ሥራ እንዲሠራ ይፈቅዳል፣ ለምርት ግብይት ዓላማ የምርት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
3. የኢትዮጵያ ደረጃዎችን አጽድቆ ለማውጣት በህግ ሥልጣን የተሰጠው አካል እንደተጠበቀ ሆኖ ምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡[75]
4. የምርት ደረጃን ለማረጋገጥ በምርት ገበያው ተቀባይነት ያገኘ ማንኛውም ሦስተኛ ወገን ወይም ተወካይ በምርት ገበያው ውስጥና ከምርት ገበያው ውጭ በምርት ግብይት ሥራ መሳተፍ አይችልም፡፡

24.ስለዕቃ ማከማቻና ደረሰኝ

---

[72] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(11) ተሻሻለ፡፡
[73] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(12) አዲስ የገባ ነው፡፡
[74] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(12) አዲስ የገባ ነው፡፡
[75] 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(13) ተሻሻለ፡፡

1. የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ደረሰኞች ሥርዐት አዋጅ ቁጥር 372/1995 አንቀጽ 26 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምርት ገበያው የግብርና ምርቶች የክብደት አለካክንና የምርቶች ዝርዝር አስተዳደርን ሥራ መሥራት፣ የዕቃዎች መጋዘንን ማካሄድና ለግብይቱ ዓላማዎች የምርት ገበያውን የዕቃዎች ማከማቻ ደረሰኞች መስጠት ይችላል፡፡
2. በዕቃ ማከማቻ መጋዘን ደረሰኞች ሥርዐት አዋጅ ቁጥር 372/1995 ለሚኒስቴሩ የተሰጠው የዕቃዎች ማከማቻ መጋዘኖችን የመቆጣጠር ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምርት ገበያው የግብርና ምርቶች የክብደት አለካከንና የምርቶች ዝርዝር አስተዳደርን ሥራ ለሚሠራ ሦስተኛ ሰው የምስክር ወረቀት መስጠት ወይም ለግብይቱ ዓላማዎች የምርት ገበያውን የዕቃዎች ማከማቻ ደረሰኞች መስጠት ይችላል፡፡
3. የምርት ገበያው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የምርት ገበያ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች ማስቀመጫ ይኖረዋል ወይም ሌላ ሦስተኛ ሰው ይህንኑ ሥራ እንዲሠራ ይፈቅዳል።
4. በምርት ገበያው ተቀባይነት ያገኘ የዕቃዎች መጋዘን የሚያካሂድ ሦስተኛ ሰው በምርት ገበያውም ሆነ ከምርት ገበያው ውጭ በምርት ግብይት መሳተፍ አይችልም፡፡

25.<u>ክፍያና ግዴታ መፈጸሚያ</u>

1. የምርት ገበያው በባለሥልጣኑ መመሪያዎች መሠረት ግብይቶችን የሥራ ግንኙነት ካለው ወይም ዕውቅና ካገኘ የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ወይም በሦስተኛ ወገን አማካይነት ክፍያንና ርክክብን ይፈጽማል፡፡
2. አባላት በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች መሠረት ከምርት ገበያው ጋር የሥራ ግንኙነትና ዕውቅና ካለው የምርት ገበያው የክፈያ መፈጸሚያ ተቋማት የባንክ ሂሣብ ይከፍታሉ፡፡
3. በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች መሠረት ክፍያንና ግዴታን ለማስፈጸም ዓላማ፣ አባላት የሥራ ግንኙነትና ዕውቅና ላለው የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት የገቢና የወጪ ትዕዛዞችን እንዲሰጥ የውክልና ሥልጣን የጽሁፍ ማስታወቂያ ለምርት ገበያው ይሰጣሉ፡፡

4. የምርት ገበያው የእያንዳንዱን አባል የግብይት አቋም በየግብይት ቀኑ ያስታርቃል፡፡
5. የምርት ገበያው በየግብይት ቀኑ ለእያንዳንዱ አባል የመገበያያ አቋምና ሁኔታ መግለጫ በጽሑፍና በኤሌክትሮኒክ ያወጣል።
6. የምርት ገበያው የአባላትን የመገበያያ አቋምና ሁኔታ መግለጫዎችን መሠረት በማድረግ ግዴታቸውን እንዲወጡ የሥራ ግንኙነት ላላቸው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት መመሪያ ይሰጣል፡፡
7. የምርት ገበያውና አባላቱ የሥራ ግንኙነት ላላቸው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ገንዘብ ከአንድ አባል ወደ ሌላ አባል ወይም ከምርት ገበያው የባንክ ሂሳብ ወደ ሌላ የባንክ ሂሣብ የኤሌክትሮኒክስ ትዕዛዝ ማስተላለፊያን በመጠቀም ቋሚ መመሪያዎች እንዲያስተላልፉ ይፈቅድላቸዋል፡፡
8. ፎርማዎች ሕጋዊ ውጤት እንዲኖራቸው በእጅ መፈረም እንዳለባቸው የሚያስገድድ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ ቢኖርም፣ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) አፈጻጸም በኤሌክትሮኒክስ ፎርማ ገንዘብ እንዲተላለፍ የተሰጠ ትዕዛዝ ተቀባይነት ይኖረዋል።
9. ማናቸውም የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም በምርት ገበያውም ሆነ ከምርት ገበያው ውጭ፡ በግብይት ሥራ መሰማራት አይችልም፡፡

26. <u>የገበያ ክትትል</u>

የምርት ገበያው በባለሥልጣኑ መመሪያ መሰረት የሚከተሉትን የገበያ መከታተያ ዘዴዎች ይጠቀማል፡፡

1. የአባላትን ዕዳ ለመከታተል የሚያስችል የገበያ ዕዳ መቆጣጠሪያ ሥርዓት፣
2. በምርት ገበያው ከተወሰኑት ጣሪያ በላይ ክፍት ቦታዎች እንዳይኖሩ ለማድረግ የሚያግዝ የክፍት ቦታዎች ጣሪያ ስርዓት፤
3. በውል መሠረት ለሚደረግ የዋጋ ለውጥ ጣሪያ የሚወሰን የዋጋ ሥርጭት ጣሪያ፤
4. ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው ሌሎች ተመሳሳይ ዘዴዎች፡፡

27. <u>የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደር</u>

የምርት ገበያው በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን የአደጋ መቆጣጠሪያ የአስተዳደር ሥርዓቶችን ይጠቀማል፣

1. የእያንዳንዱን አባል አቋምና ሁኔታ የሚያሳይ የአባላት የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብ፣
2. የምርት ገበያውን ዕዳዎች ለመሸፈን የሚያስችሉ የክፍያ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ፤
3. ለእያንዳንዱ ግገር በመያዣነት የሚያገለግል ተቀማጭ የመያዣ ገንዘብ፣
4. ከተቀማጭ ገንዘብ አንፃር የአባሉን አቋምና ሁኔታ የሚያሳይ የንግዱን የተጋላጭነት መጠን፣
5. በገበያ ቀናት በገበያው ውስጥ የሚፈጸሙ የቀን ተቀን የተጣሩ ግዴታዎች፣
6. በምርት አቅርቦት ረገድ ዲሲፕሊንን ለማስከበር የሚያግዝ ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል ቅጣት፤
7. ባለሥልጣኑ እንዲሟሉ የሚጠይቃቸው ሌሎች ሥርዓቶች፡፡

28. <u>ስለክርክር አፈታት</u>

1. የምርት ገበያው ከምርት ግብይት ጋር የተያያዙ ክርክሮች በሽምግልና ዳኝነት የሚፈቱበትን መመሪያና ሥርዓት በባለሥልጣኑ አጽድቆ ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በምርት ገበያው የሚወጣው የሽምግልና ዳኝነት መመሪያና ሥርዓት በተለይ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
   ሀ) የሽምግልና ዳኞችን ተፈላጊ ችሎታና የአመራረጥ ሥርዓት፤
   ለ) የሽምግልና ዳኝነቱ የሚመራበትን ሥርዓት፡
   ሐ) ከሽምግልና ዳኝነቱ ጋር የተያያዙ ወጭዎች ስለሚሸፈኑበት ሁኔታ፡፡
3. የምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚካሄደው የሽምግልና ዳኝነት የጽሕፈት ቤት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

29. <u>ስለ ዋስትና</u>

የምርት ገበያው የግል፣ የፋይናንስ፣ የግብይትና ሌሎች ከምርት ገበያው ጋር የተያያዙ መረጃዎች የሚጠበቁበትን ሥርዓት ያቋቁማል፣ ይጠብቃል፡፡

## 30. ባለቤትነትን እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ስለሚደረግ ግብይት[76]

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 (4) ስለምርት ተተካኪነት የተደነገገው ቢኖርም የምርት ገበያው የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርቱን ዱካ ያረጋገጠ የግብይት ሥርዓት ሊዘረጋ ይችላል፡፡
2. ባለቤትነትን እና የምርት ዱካን ባስጠበቀሁኔታ በሚደረግ ግብይት መካተት ያለባቸው ምርቶች ዝርዝር ሚኒስቴሩ በየጊዜው እየከለሰ ሊወስን ይችላል፡፡
3. በዚህ ሥርዓት ግብይት የሚፈጸምባቸው ምርቶች የመጋዘን ውስጥ የምርት አቀማመጥ፤ አስተዳደርና ርክክብም የምርቱንና የባለቤቱን ወይም አቅራቢውን ማንነት የሚያረጋግጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
4. በዚህ ሥርዓት ግብይት የሚደረግበትን ምርት እንደጫኑ በምርት ገበያው ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ ግብይት የሚካሔድባቸውን ተሽከርካሪዎችና ጭነቶች አቀባበል፤ ናሙና አወሳሰድ፤ ደረጃ አወሳሰን፤ የክብደት ምዘና፤ ግብይት፤ ርክክብና የአደጋ ቁጥጥር አሠራሮችን የተመለከቱ ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት በምርት ገበያው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 31. የምርት ገበያውን አሠራሮች ስለመለወጥ

ከሚከተሉት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የምርት ገበያውን አሠራሮች ለመለወጥ በቅድሚያ የባለሥልጣኑን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፣

1. የምርት ገበያው መመሪያዎችና የውስጥ ደንቦች፤
2. አባልነት፣
3. የአገልግሎት ክፍያዎች፤
4. የግብይት ሥርዓት፤
5. ለምርት ገበያው የተዘጋጁ ውሎች፤
6. የገበያ መረጃዎች ሥርጭት፤
7. የክፍያና የርክክብ አፈጻጸም፤
8. የክርክር አፈታት፣ እና
9. ዋስትና፡፡

[76] ይህ አንቀጽ 23/78 (2009) አ.1050 አንቀፅ 2(14) መሰረት የተጨመረ ሲሆን ነባሮቹ አንቀጾች ከ30 እስከ 33 የሚገኙት እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ 31፣ 32፣ 33 እና 34 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 32. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን[77]

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአንድን ምርት ግብይት በኢትዮጵያ የምርት ገበያ ብቻ እንዲፈጸም ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለመወሰንና እነዚህኑ ሁኔታዎች በማያከብሩት ላይ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ደንብ ማውጣት ይችላል።
3. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

### 33. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 34. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

---

[77] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በማሻሻያ አዋጅ 665/2002 አንቀጽ 2 መሰረት ንዑስ አንቀጽ 3 ሆኖ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተጨምሯል፡፡

## አዋጅ ቁጥር 551/1999

## የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ቀልጣፋና ዘመናዊ የግብርና ምርቶች ግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የምርት ግብይት ሥርዓቱ ፍትሐዊ፣ ግልጽና የተቀላጠፈ መሆኑን ለማረጋገጥና በገበያው የሚሳተፉትንም ሆነ በአጠቃላይ የኅብረተሰቡን ጥቅም ማስጠበቅ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህንንም ለማድረግ ያስችል ዘንድ የምርት ግብይት ሥርዓቱን የሚቆጣጠር የመንግሥት አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገመንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም" ማለት በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያገኘ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ወይም የአገር ውስጥ ባንክ ወይም ተመሳሳይ የፋይናንስ ተቋም ነው፣[78]
   2. "የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም" ማለት አንድ ድርጅት በአገናኝነት ወይም በአቀራራቢነት የሚሠራበት ሥነ ሥርዓት ሆነ፣ ድርጅቱ ለግብይቱ አፈጻጸም የገዢና የሻጭን ሚና በመውሰድ በተዋዋይ ወገኖች የሚሰጡትን ትዕዛዞች የሚያስታርቅበትና የገንዘብ ክፍያና ርክክብ የሚፈጸምበት አሠራር ነው፤
   3. "ምርት" ማለት ከሌላ አንድ ዓይነት ምርት ጋር መለዋወጥ የሚችል ምርት ነው፤
   4. "የምርት ገበያ" ማለት ወጥ ሆነው በተዘጋጁ ምርት ነክ ውሎች ግብይት የሚፈጸምበት የምርት ገበያ ነው፤

[78] በ14/17(2000) አ.566 አንቀጽ 2(1) ተሻሻለ፡፡

5. “ውል” ማለት ለምርት ገበያ ግብይት ሲባል አንድን ምርት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀና የምርቱን መጠን፣ ዋጋ፣ ደረጃ፣ ተፈጻሚ የሚሆንበትና የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበትን ቀን በዝርዝር የሚያካትት ስምምነት ነው፤
6. “አስቸኳይ ሁኔታ” ማለት የተለመዱትን የገበያ ተግባራት የሚከለክል ማናቸውም ከፍተኛ የሆነ የገበያ ቀውስ ነው፣
7. “የግብይት ፈጻሚ” ማለት ለሌሎች ወይም ለራሱ ሲል የምርት ግብይት ውሎችን በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ የተሠማራ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፤
8. “የውስጥ አዋቂ ንግድ” ማለት የተጣለበትን ከፍተኛ እምነት ወይም አደራ ወይም በእምነት ወይም በአመኔታ ላይ የተመሠረተን ሌላ ግንኙነት በማፍረስ ለሕዝብ ያልተገለጸ መረጃን በመጠቀም የምርት ግብይት ውልን መግዛት ወይም መሸጥ ነው፤
9. “አሳሳች ድርጊት” ማለት የምርትን ዋጋ ወይም መጠን በተመለከተ የገበያ ተሳታፊዎችን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ማናቸውም ድርጊት ነው፤
10. “የመያዣ ገንዘብ” ማለት ግዢ ፈጻሚዎች በገበያ ላይ ለሚፈጽሙት አንድ ግብይት በመያዣነት ሊያስቀምጡት የሚገባ ገንዘብ ነው፤
11. “አባል” ማለት ለምርት ገበያ የሚጠይቀውን የአባልነት መመዘኛ የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ነው፤
12. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

## ክፍል ሁለት

## የምርት ገበያ ባለሥልጣን

### 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ “ባለሥልጣን” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የባለ ሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ይኖሩታል፡፡

5. **ዓላማዎች**

የባለሥልጣኑ አጠቃላይ ዓላማ ውጤታማ የሆነ ዘመናዊ የመገበያያ ሥርዓት መገንባቱን ማረጋገጥ፣ የምርት ገበያው አስተማማኝ፣ ግልፅና የተረጋጋ አሠራር እንዲኖረው መቆጣጠር፣ እንዲሁም የሻጮችን፣ የገዢዎችን፣ የአገናኞችንና በአጠቃላይ የሕብረተሰቡን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ ሆኖ ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

1. በኃላፊነት የሚከናወኑ የፈጠራ ሥራዎችን ማበረታታት፣ ሁሉም የገበያ ተሳታፊዎች የገበያ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ወይም በገበያዎችና በገበያ ተሳታፊዎች መካከል የሚደረጉ ተገቢ ውድድሮችን ማዳበር፤
2. ዋጋን በተመለከተ አሳሳች ድርጊትን ወይም ሌላ የገበያውን ህልውና የሚያናጋ ድርጊትን መግታትና መከላከል፣
3. ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ የግብይቶችን የፋይናንስ አቋም የመጠበቅና አጠቃላይ የገበያ ሥርዓቱን የሚያናጉ አደጋዎች እንዳይከሰቱ መከላከል፤
4. የገበያ ተሳታፊዎችን ከመታለልና ተገቢ ካልሆኑ ሌሎች ድርጊቶች እንዲሁም የደንበኞች ንብረት አለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል መጠበቅ፡፡

6. **የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. ለክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ዕውቅና የመስጠት ወይም የመንሳት፤
2. ለግብይት ፈጻሚዎች ዕውቅና የመስጠት ወይም የመንሳት፤
3. የምርት ገበያን፤ የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማትንና የግብይት ፈጻሚዎችን ቁጥጥር በተመለከተ መመሪያዎቸችን የማውጣት እንዲሁም ይህንኑ በተመለከተ የምርመራ፣ የማፅደቅና ትክክለኛነቱን የማረጋገጥ ሥልጣኑን ተግባራዊ የማድረግ፤
4. ከምርት ገበያ ሥራ ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት አማካሪዎችን፣ የአማካሪ ድርጅቶችን፣ የሕግ ባለሙያዎችን፣ የሂሣብ አዋቂ ባለሙያዎችን አሠራር የመቆጣጠር፤

5. የምርት ግብይት ውሎችን ዝርዝር ይዘት፣ ሽያጭና ግዢ መርሆዎች በሚመለከት መመሪያ የማውጣት፤
6. የምርት ግብይት ውሎች ክፍያንና ርክክብ አፈጻጸምን የመቆጣጠር፤
7. ከምርት ግብይት ጋር በተያያዘ የውስጥ አዋቂ ንግድን፣ ማታለልንና ተገቢ ያልሆነ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን የመውሰድ፤
8. ከፌዴራል ዋና ኦዲተር ጋር በመተባበር የምርት ግብይትን በተመለከት የገለልተኛ የኦዲት አሰራር መርሆዎችን የመወሰን፤[79]
9. በዚህ አዋጅ መሠረት በእጁ የገቡትን ወይም የቀረቡለትን የሂሣብ መግለጫዎች፣ ሪፖርቶችና ሌሎች ሰነዶች የመመርመር፣ ከምርት ገበያው፣ ከክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት፣ ከግብይት ፈጻሚዎች፣ ከውስጥና ከውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት እንዲቀርብለት የመጠየቅ፤
10. ከምርት ገበያና ከገበያ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ የሚፈፀሙ የህግ መጣስ ድርጊቶችን የመመርመርና እርምጃ የመውሰድ፤
11. የምርት ገበያውን ሠራተኞች በሚመለከት ስለሚደረግ ቁጥጥር እንዲሁም ከመብትና ግዴታቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ደንቦችንና መርሆዎችን በተመለከተ መመሪያ የማውጣት፤
12. የምርት ገበያን የክርክር አፈታት መመሪያና ሥርዓት ያጸድቃል፤
13. የምርት ገበያ ቁጥጥርን እንዲሁም የግብይት ፈጻሚዎችን፣ የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማትን፣ የግብይት ፈጻሚዎች ማህበርን ዕውቅናንና ቁጥጥርን በተመለከተ በባለሥልጣኑ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ክፍያዎች የማስከፈል፤
14. ከምርት ገበያ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በተመለከተ ለሕዝብ የሚሰጠውን ትምህርት የማሳደግ፤
15. አግባብ ካላቸው የመንግሥትና የግል አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት የመፍጠርና የመተባበር፤

7. <u>የመዳኘት ሥልጣንና ጉዳዮችን ስለመምራት</u>

1. ባለሥልጣኑ በሥልጣን ክልሉ ውስጥ የሚወድቁ ጉዳዮችን በሚዳኝበት ጊዜ፤
   ሀ) ማንኛውንም ሰው የመጥራትና በጥሪው መሠረት እንዲገኝ የማድረግ፤ ቃለ መሐላ በማስፈጸም ምርመራ የማካሄድ፣

[79] ይህ ንዑስ አንቀፅ ለ20/81(2006) አ.847 ዓላማ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

ለ) ማናቸውም ሰነድ እንዲፈለግና እንዲቀርብ የመጠየቅ፣

ሐ) በቃለ መሐላ የተረጋገጠ ማስረጃ የመቀበል፣

መ) የሕዝብ ወይም የመንግሥት ሰነድ ወይም ኮፒውን ከማናቸውም መሥሪያ ቤት እንዲቀርብለት የመጠየቅ፣ እና

ሠ) አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣

ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

2. ከምርት ገበያ ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ወንጀል ሲያጋጥመው ጉዳዩን ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

3. ምርመራ እንዲካሄድ ካደረገ በኋላ ማናቸውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን ጥሶ ከተገኘ ወይም ሊጥስ የሚችል መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የተባለው ሰው ድርጊቱን ከመፈጸም እንዲገታ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

8. <u>ስለባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለስልጣኑ፣

1. የምርት ገበያ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፣
2. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣ እና
3. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

9. <u>የቦርድ አባላት</u>

1. ቦርዱ የሚከተሉትን ይይዛል፣

ሀ) አንድ ሊቀመንበር፤

ለ) ከግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር[80] የሚመደብ አንድ አባል፤

ሐ) ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[81] የሚመደብ አንድ አባል፣

መ) ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር[82] የሚመደብ አንድ አባል፣ እና

ሠ) ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚመደብ አንድ አባል፡፡

2. የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ በአባልነት ይሳተፋል፡፡

---

[80] በ25/82011) አ.1097 አንቀፅ 9(6) መሰረት የግብርና ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[81] በ25/82011) አ.1097 አንቀፅ 9(6) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

[82] በ25/82011) አ.1097 አንቀፅ 9(6) መሰረት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

3. የቦርዱ ሊቀመንበርና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከቱት አባላት በመንግሥት ይሾማሉ፡፡
4. የባለሥልጣኑ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ካልፈቀደ በቀር ማንኛውም የቦርድ አባል ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ሥራውን ከለቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ በግብይት ሥራ ላይ ከተሰማራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የሥራ ቅጥር መቀበል ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ በማናቸውም ሥራ መሰማራት አይችልም፡፡

10.<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ለባለሥልጣኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፡፡
2. ቦርዱ በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ ፖሊሲ የመቅረጽና የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት የመምራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

11.<u>ስለቦርዱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት</u>

1. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ከባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ ለቦርዱ የሚቀርብ ማናቸውም ጉዳይ ቦርዱ በአብላጫ ድምፅ ይወስናል፣ ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ስብሰባውን የመራው የቦርድ አባል ሁለተኛ ወይም ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
2. በባለሥልጣኑ መመሪያዎች በተመለከቱት መሠረት ቦርዱ በሳምንት አንድ ጊዜ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ሲጠይቅ ይሰበሰባል፤ የስብሰባ ምልዐተ ጉባዔን ጨምሮ በቦርዱ ስብሰባ ስለሚከናወኑ ሥራዎች በልምድ ተቀባይነት ያገኙ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንቦችን ያከብራሉ፡፡
3. የቦርዱ ሊቀመንበር በማናቸውም ምክንያት በቦርዱ ስብሰባ መገኘት ያልቻለ እንደሆነ፣ በሰብሳቢው የተወከለ ሌላ ማንኛውም የቦርድ አባል ስብሰባውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

12.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የባለሥልጣኑ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ በተለይም

ሀ) የግብይት ተሳታፊዎችና የክፍያ አፈጻጸም ክትትል፣

ለ) የገበያ ክትትል፣

ሐ) የሕግ አፈጻጸም ክትትል፣

መ) የኢኮኖሚ ትንተና ፤ ሥራዎችን በበላይነት የመከታተል ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በመንግሥት በሚጸድቀው መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤[83]

ለ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ያስፈጽማል፤

ሐ) በጸደቀው የባለሥልጣኑ በጀት መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

መ) ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ሠ) የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

13. <u>የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባር በውክልና ስለመስጠት</u>

1. በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (3)፣ (5)፣ (11) እና (12) ከተመለከቱት በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት፣

ሀ) በባለሥልጣኑ ለተቋቋመ ማናቸውም ኮሚቴ፣ ወይም

ለ) ለምርት ገበያ፣

በውክልና መስጠት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠ ውክልና የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት ጐን ለጐን ተግባራዊ ማድረግን አይከለክልም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ስር የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት አለበት፡፡

14. <u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

[83] በ14/17(2000) (566) አንቀጽ 2(2) ተሻሻለ፡፡

15.የሂሣብ መዛግብት

1. ባለሥልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክላቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ለግብይት ፈጻሚዎች ዕውቅና ስለመስጠት

16.እውቅና የማግኘት አስፈላጊነት

1. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ እውቅና ካላገኘ በቀር፣ በምርት ገበያ ወይም በምርት ገበያ ላይ ደንበኞች ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ማናቸውንም የምርት ግብይት ውል በግብይት ፈጻሚነት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ፣ ትዕዛዞችን ለማፈላለግ ወይም ለመቀበል አይችልም።
2. በግብይት ፈጻሚነት እውቅና ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ማመልከቻው በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት በተዘጋጀው ቅጽና የአቀራረብ ሥርዓት መሠረት ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን መረጃዎችና ፍሬ ነገሮች አካቶ መቅረብ ይኖርበታል። ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተገቢ የመሰለውን የእውቅናና የእውቅና ዕድሳት ክፍያዎች ይወስናል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

17. እውቅና ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

ማንኛውም ለእውቅና የሚያመለክት ሰው፣

1. የተሰማራበትን የንግድ ሥራ ለማከናወን አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ፈቃድ ያለው፣
2. በባለሥልጣኑ መመሪያዎች የተወሰነውን አነስተኛውን የካፒታል መጠን የሚያሟላ፣
3. በባለሥልጣኑ መመሪያዎች የተመለከተውን አነስተኛውን የትምህርት ወይም የንግድ ብቃት መመዘኛዎችን የሚያሟላ፣
4. የሚሳተፍበትን የንግድ ዘርፍ የሚመለከቱ መረጃዎች ማቅረብ የሚችል፣
5. የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሥራ አስኪያጆች ስሞችንና አድራሻዎቻቸውን እንዲሁም የሽርክና ድርጅት ከሆነ የኃላፊዎቹንና የሽሪኮቹን ስሞች፣ ኃላፊነቱ

የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የአክሲዮን ማኅበር ከሆነ የኃላፊዎቹን፣ የዳይሬክተሮቹንና የባለአክስዮኖቹን ስሞች መግለጽ፣

6. በሚገባ የተደራጀ የንግድና የአደጋ ቁጥጥር አመራር ሥርዓት ያለው፣ እና
7. በባለስልጣኑ መመሪያዎች መሰረት የሚወሰኑ ሌሎች መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

18.**ሪፖርት ስለማቅረብና መረጃ ስለመስጠት**

እውቅና የተሰጠው የግብይት ፈጻሚ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 የተመለከቱትንና በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ ሌሎች ከሥራው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በተመለከተ በየጊዜው ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

19.**የግብይት ፈጻሚዎችን ዕውቅና ስለማንሳት**

1. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና የባለሥልጣኑን መመሪያዎች በግብይት ፈጻሚው መጣሱን በማሳየት ከ180 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ዕውቅናውን የማገድ ወይም የመሰረዝ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የእገዳ ወይም የሥረዛ ውሳኔ የሚሰጠው ለግብይት ፈጻሚው ማስታወቂያ ደርሶት እንዲሰማ ከተደረገ በኋላ ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ የተወሰነበት ሰው ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካላቀረበ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በተሰጠ የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከቀረበና ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ባስሥልጣኑ የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔውን ካላነሳ የግብይት ፈጻሚው በምርት ግብይት ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

**ክፍል አራት**

**ለግብይት ፈጻሚዎች ማህበር ዕውቅና ስለመስጠት**

20.**እውቅና**

የአባላትን ታማኝነት፣ ሙያዊ ብቃትና የችሎታ ደረጃ ለመጠበቅ ሲባል የግብይት ፈጻሚዎች ማህበር በባለሥልጣኑ ዘንድ በመመዝገብ በግብይት ፈጻሚዎች ማህበርነት ዕውቅና ሊያገኝ ይችላል፡፡

21.<u>የምዝገባ መግለጫ</u>

በባለሥልጣኑ ለመመዝገብ የሚፈልግ ማናቸውም የግብይት ፈጻሚዎች ማህበር በባለሥልጣኑ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት የምዝገባ መግለጫው እንዲመረመርና እንዲፀድቅ ከዚህ በታች ከተመለከቱት መረጃዎችና ሰነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል፣

1. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመተዳደሪያ ደንቡንና የመመሥረቻ ጽሑፉን ኮፒዎች ማሻሻያ ካለ ከነማሻሻያው፣ ከውስጥ ደንቦቹና ከነዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች፤
2. ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ወይም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ፣ ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚጠይቃቸው ስለማኅበሩ፣ ስለአባላቱ፣ ስለስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንቡና ስለሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች መረጃ፤
3. የሥልጠና ደረጃዎችና የብቃት ችሎታ ፈተና መመዘኛ፣
4. ከዚህ በታች የተመለከቱትን ለማስከበር የተዘረጉ የኦዲትና የማስፈጸሚያ ፕሮግራም፤

    ሀ) አባላቱ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ አነስተኛ ካፒታልና የተለያዩ ሂሣቦች አያያዝና ፋይናንስን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች፣ እና

    ለ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በአባላቱና ከነርሱ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሌሎች ሰዎች የንግድ ሥራዎች አካሄድ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ አነስተኛ ደረጃዎች፡፡

22.<u>ስለሪፖርት</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ የግብይት ፈጻሚዎች በባለሥልጣኑ ሲጠየቁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 የተመለከቱትንና ሌሎች መረጃዎች ለባለሥልጣኑ በቀጣይነት ሪፖርት ማድረግና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

23.<u>ዕውቅናን ስለመከልከል፣ ስለማገድና ስለመንፈግ</u>

ባለሥልጣኑ በማስታወቂያ ጠርቶ የመስማት ዕድል ከሰጠ በኋላ፤ የግብይት ፈጻሚዎች ማኅበር ደንቦች ከባለሥልጣኑ መመሪያዎች ጋር የማይጣጣሙ ሆነው ከተገኙ ማኅበሩን የዕውቅና ምዝገባ ለመከልከል፣ ለማገድ ወይም ለማንሳት ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ለክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ዕውቅና ስለመስጠት

### 24. ስለ አሰራሩ

1. በምርት ገበያ በየቀኑ ከሚካሄድ የምርት ግብይት ውሎች ግዢዎችና ሽያጮች መጠን ጋር የሚስማማ የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ አሰራር እንዲሁም ከምርት ግብይቱ ጋር በተያያዘ የገንዘቦች መተላለፊያ ዘዴዎች ይኖሩታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ዕውቅና ሳያገኝ በግብይት ክፍያና ርክክብ ማስፈጸም ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም፡፡

### 25.ዕውቅና ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

በክፍያ መፈጸሚያ ተቋምነት ዕውቅና ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚያቀርበው ማመልከቻ በባለሥልጣኑ መመሪያ የተመለከቱትን መረጃዎች መያዝና በተለይም አመልካቹ፣ የሚከተሉትን ማሳየት ይኖርበታል፤

1. የተሟላ የፋይናንስ፣ የሥራ እንቅስቃሴና የሥራ አመራርና ሀብቶች ያሉት መሆኑን፣
2. ኃላፊነቱን በሚወጣበት ጊዜ የሚያጋጥሙትን ችግሮች አግባብነት ያላቸውን ዘዴዎችንና ሥርዓቶችን በመጠቀም የመቋቋም ችሎታ ያለው መሆኑን፤
3. በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በመሆን ክፍያን በተፈለገው ጊዜ በተሟላ ሁኔታ የማጠናቀቅ ችሎታ ያለው መሆኑን፣
4. የሚፈጽማቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ከእያንዳንዱ ግብይት ጋር በተያያዘ ስለገንዘብ ፍሰት የተሟላ መረጃ የመያዝ ችሎታ ያለው መሆኑን፣
5. ከሌሎች የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ጋር ባለው ግንኙነት ስለማናቸውም የተፈቀዱ ማቻቻያዎች የተመለከቱትን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች የማክበር ችሎታ ያለው መሆኑን፣
6. የገንዘብን ወይም የፈንድን ደኅንነት ለመጠበቅና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ደረጃዎችና ሥርዓቶች ያሉት መሆን፤
7. ግዴታ አለመወጣትን በተመለከተ ውጤታማ፣ ፍትሐዊና ጤናማ አስተዳደር እንዲኖር የሚያግዙ ደንቦችና ሥርዓቶች ያሉት መሆኑን፤

8. የምርት ገበያንና የክርክር አፈታት ደንቦች ተግባራዊነትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከታተልና ለማስፈጸም የሚያግዙ የተሟሉ የአሠራር ዘዴዎችና ሀብቶች ያሉት መሆኑን፤
9. ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ግብአቶችና የአሠራር ሥርዓቶች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውንና የተሟላ አቅምና ዋስትና ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ቁጥጥር የሚደረግበትና የሚያጋጥሙ አደጋዎች የሚተነተኑበት ፕሮግራም ያለው መሆኑን፣ እና
10. በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ አሠራሮች ለአደጋ ሲጋለጡ ተመልሰው የሚቋቋሙበት ቀልጣፋና ፈጣን የአሠራር ሥርዓቶችና ፕላኖች ያሉት መሆኑን፤ ማሳየት አለበት፡፡

26. <u>የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማትን ዕውቅና ስለማገድና ስለማንሳት</u>

1. ባለሥልጣኑ አንድን የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም አሠራር ደረጃዎችና ሥርዓቶች ከባለሥልጣኑ መመሪያ ጋር እንደማይጣጣም በማሳየት ዕውቅናውን የመሰረዝ ወይም 180 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የተሰጠውን ዕውቅና የማገድ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡
2. የእገዳና የመሠረዝ እርምጃ የሚወሰደው ለተቋሙ ኃላፊዎች በማስታወቂያ እንዲያውቁት ተደርጐ ለባለጉዳዩ የመሰማት ዕድል ከተሰጠው በኋላ ይሆናል፡
3. የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔ የተሳለፈበት ሰው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ካላቀረበ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለተከለከሉ ግብይቶች እና ስለቅጣት</u>

27. <u>ሕገ ወጥ ግብይት</u>

1. ማንኛውም ሰው ከግብይት ውል ጋር በተያያዘ፣
   ሀ) ካታለለ ወይም
   ለ) ካጭበረበረ፣

ድርጅት ከሆነ ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 1000,000[84] በማይበልጥ፣ ግለሰብ ከሆነ ከብር 10,000 በማያንስና ከብር 200,000 ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው፣

ሀ) ከግብይት ውል ጋር በተያያዘ አሳሳች ድርጊት ከፈጸመ፣

ለ) የዕቃ ዋጋን እንደተፈለገ ለመወሰን ይቻል ዘንድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ምርትን ወይም የምርት ግብይት ውሎችን ለመያዝ ወይም ለማከማቸት ቢሞከር፣

ሐ) በመካሄድ ላይ ላለ ንግድ የሌለውን ገፅታ በመስጠት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ምርት ወይም የምርት ግብይት ውሎች ከገዛ ወይም ከሸጠ ወይም የገበያን ሁኔታ ወይም የማናቸውም የምርት ግብይት ውሎችን ዋጋ በተመለከተ አሳሳች መረጃ ከሰጠ፣

መ) የግብይቱ አፈጻጸም በባለቤትነት ላይ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ እየታወቀ ወይም ይኸው ታውቆ ወደ አፈጻጸም እንዲገባ ካደረገ፣ የምርት ግብይት ውሎች እንዲገዙ ወይም እንዲሸጡ ትዕዛዝ ከሰጠ፣

ሠ) በምርት ገበያ ውስጥና ውጪ የሚከሰቱ የዋጋ ውጣ ውረዶች ለመጠቀም በማሰብ ስለገበያ ሁኔታ እውነት ያልሆነ፣ አሳሳች መግለጫ ወይም መረጃ ካሰራጨ ወይም ሌላ ሰው እንዲያሰራጭ ካደረገ፣ ወይም

ረ) ለሌላ ወገን አሳሳች መግለጫ በመስጠትና ውሉ አትራፊ እንደሆነ አስመስሎ በማቅረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የምርት ግብይት ውል እንዲያደርግ ከገፋፋ፣ ድርጅት ከሆነ ከብር 50,000 በማያንስና ከብር አንድ ሚሊዮን በማይበልጥ፣ ግለሰብ ከሆነ ከብር 10,000 በማያንስና ከብር 200,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ ለሚወስነው ጊዜ ዕውቅናው ይታገዳል ወይም ጸግም ዕውቅና ይከለከላል።

[84] በ14/17(2000) አ. 566 አንቀጽ 2(3) ተሻሻለ፡፡

28.**ውስጥ አዋቂ ነጋዴ**

1. ማንኛውም የባለሥልጣኑ ቦርድ አባል ወይም ሠራተኛ ወይም ተወካይ ይህ አዋጅ በሚመለከተው የምርት ገበያ ውስጥም ሆነ ውጭ ወይም በማናቸውም ተመሳሳይ ንግድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከተሳተፈ ከብር 20,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡
2. በሠራተኛነቱ ወይም ባለው የሥራ ቦታ በምርት ግብይት ውሎች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ወይም ተፅዕኖ የማድረግ አዝማሚያ ያለው በሕዝብ ያልታወቀ መረጃን ማግኘት የሚችል ማንኛውም የባለሥልጣኑ የቦርድ አባል ወይም ሠራተኛ ወይም ተወካይ ሆነ ብሎ በምርት ገበያ ውስጥም ሆነ ውጭ በሚደረግ ግብይት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲሳተፍ ለማስቻል ያገኘውን መረጃ ለሌላ ሰው ካቀበለ ከብር 20 ሺ በማያንስና ከብር 100 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተውን መረጃ ከማንኛውም የባለሥልጣኑ የቦርድ አባል ወይም ሠራተኛ ወይም ተወካይ የተቀበለ ወይም የወሰደና መረጃውን በምርት ገበያ ውስጥ ወይም ከምርት ገበያ ውጭ ለሚካሄድ ግብይት የተጠቀመ ማንኛውም ሰው ከብር 20ሺ በማያንስና ከብር 100ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

29. **የባለሥልጣኑን መመሪያ ስለመጣስ**

የማናቸውም የምርት ገበያ ወይም የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ወይም የግብይት ፈጻሚዎች ማኅበር ሰራተኛ፣ የአስተዳደር ቦርድ አባል ወይም አባል የሆነ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የወጡትን መመሪያዎች በራሱ ፈቃድ ሆነ ብሎ በመጣስ፤

1. ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ወይም በሌላ ሰው ስም በምርት ግብይት ውል ከተገበያየ፤
2. በሠራተኛነቱ ወይም በአባልነቱ ከሥራው ጋር በተያያዘ ያገኘውን ለሕዝብ ያልተገለጸ መረጃ ከሥራው አፈጻጸም ጋር በማይጣጣም ሁኔታ ለማናቸውም ዓላማ እንዲታወቅ ካደረገ፤

3. መረጃው የዚህን አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌን በመጣስ ከምርት ገበያ ወይም ከክፍያ ፈጻሚዎች ማኅበር ሠራተኛ፣ የአስተዳደር ቦርድ አባል ወይም አባል የተገኘ መሆኑን እያወቀ ይህንኑ መረጃ መሠረት በማድረግ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ወይም በሌላ ሰው ስም በምርት ግበይት ውል ከተገበያየ፣ ከብር 20,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ

### 30.ስለዋስትና መቋቋምና አጠቃቀም

1. የምርት ገበያ የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ ያቋቁማል፡፡

   ፈንዱም፤

   ሀ) ለክፍያና ርክክብ ማስፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ ወጪዎችና ጥበቃ ማቻቻያ ወይም መደጎሚያ፤

   ለ) በምርት ገበያ የውስጥ ደንቦች መሠረት ከተከናወነ የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም ለሚያጋጥሙ ጉድለቶች በጊዜያዊ ማሟያነት ለመጠቀሚያ፤

   ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ ለምርት ገበያ የኢንሹራንስ አረቦን ክፍያ ለመፈጸም፤ እና

   መ) በባለሥልጣኑ ለሚወሰን ሌሎች የባለሥልጣኑ አግባብ ያላቸው ተግባራትና ኃላፊነቶች ማስፈፀሚያ ሊውል ይችላል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ የምርት ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርት ገበያን የክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድን የሚያስተዳድር የሥራ አመራር ንዑስ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

### 31.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ባለሥልጣኑ፤

1. ስለክፍያና ርክክብ ፈንድ መዋጮ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ፤
2. ስለክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር፤
3. ስለገንዘብ አወጣጥና ስለመልሶ ክፍያ፤
4. ስለ ሽፋንና ከሽፋን ውጭ ስለመሆን፤
5. ስለ አገልግሎት መጠቀሚያ ክፍያዎች፤ እና

6. ግዴታን ባለመፈጸም ስለሚጣሉ ቅጣቶችና የዲሲፕሊን እርምጃዎች፤ መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል ስምንት

## የአስቸኳይ ሁኔታ ስልጣን

### 32.የባለሥልጣኑ ሥልጣን

ባለሥልጣኑ አስቸኳይ ሁኔታ ተከስቷል ብሎ ሲያምን የምርት ግብይት ሥርዓቱን ለመጠበቅ ወይም ለማስተካከል በተለይ የሚከተሉትን እርምጃዎች የምርት ገበያው እንዲወስድ መመሪያ መስጠት ይችላል፣

1. ማናቸውም የግብይት ውልን የመሰረዝ፣
2. በማናቸውም የግብይት ውል ላይ ጊዜያዊ እገዳ የመጣል፣
3. በማናቸውም የግብይት ውል ላይ ጊዜያዊ የአስቸኳይ የመያዣ መጠን የመወሰን፣ እና
4. የባለሥልጣኑ ውሳኔ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በቅን ልቦና በተገኘ የገበያ አቋም ላይ የሚደረገውን ገደብ የመወሰን፡፡

### 33.አቤቱታ

ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ ለአቤት ባዩና ለባለሥልጣኑ ማስታወቂያ እንዲደርሳቸውና እንዲሰሙ ካደረገ በኋላ የባለሥልጣኑ ውሳኔ በዘፈቀደ የተሰጠ፣ በማስረጃ ያልተደገፈ ወይም ሕግን ያልተከተለ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር የባለሥልጣኑን ውሳኔ ማገድ አይችልም፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 34.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

35.<u>ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

36.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 178/2002

## የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ[85]

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998[86] አንቀጽ 5 እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 31(2) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 178/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**[87]

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል" ማለት ለሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ መገበያያነት እንዲሆን አግባብነት ባለው የክልል አካል የተከለከለ ሥፍራ ነው፤
   2. "አገልግሎት ሰጪ" ማለት በማንኛውም የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት ያልተሰማራ ሆኖ በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ አገልግሎት የተሠማራ ሰው ነው፤
   3. "የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ" ማለት ከመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላት በአቅራቢ ተገዝቶ ወይም በአምራች ወይም በኅብረት ሥራ ማህበር በቀጥታ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚቀርብ ለኤክስፖርት ያልተዘጋጀ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ነው፤
   4. "አቅራቢ" ማለት ማንኛውም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

---

[85] በደንቡ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "ሚኒስቴር" ወይም "አግባብ ያለው የክልል አካል" በሚል የተገለጸው በ20/32(2006) ደ.307 አንቀፅ 2(7) መሰረት "አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት" በሚል ተተክቷል።
[86] እንግሊዘኛው "አዋጅ ቀጥር 178/1998" የሚል ሲሆን ትክክለኛው የእንግሊዘኛው ትርጓሜ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ተስተካክሎ ተፃፈ፡፡
[87] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ፣ 9 እና 12 በ20/32 (2006) ደ. 307 አንቀጽ 2(1) እና (2) ተሻሻሉ፡፡

5. “ላኪ” ማለት ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ወይም ከራሱ ማሳ ያመረተውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለውጭ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው፤
6. “አምራች” ማለት አነስተኛ አምራች ገበሬዎች፣ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራትን እና የእርሻ ድርጅቶችን ጨምሮ ማንኛውንም ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የሚያመርት ሰው ነው፤
7. “አሳሳች ድርጊት” ማለት የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ዋጋን፣ መጠንን፣ ደረጃን ወይም ዓይነትን በተመለከተ የገበያ ተሳታፊዎችንና መንግሥትን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ማንኛውም ድርጊት ነው፤
8. “ማዘጋጀት” ማለት የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርትን አበጥሮና ከባዕድ ነገር አፅድቶ ለገበያ ለማቅረብ ማሰናዳት ነው፤
9. “አግባብ ያለው የክልል አካል” ማለት ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፡፡
10. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬድዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡
11. “የምርት ዘመን” ማለት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ ኅዳር 1 ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት 30 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው፤
12. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
13. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
14. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡
15. “አቀናባሪ” ማለት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄን ኢንዱስትሪ ተጠቅሞ በመፈተግ፣ በመቁላት ወይም ጣህና፣ ሐለዋ ወይም የምግብ ዘይት በማምረት ወይም ሌሎች መሰል የኢንዱስትሪ ምርት በማምረት ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤[88]

[88] ንዑስ አንቀጽ 15 እና 16 በ20/32 (2006) ደ. 307 አንቀጽ 2(3) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

16.“አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት” ማለት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ ወይም ለማቀናበር ወይም ለመሰል ተግባራት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት በሕገ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

## ክፍል ሁለት

## የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት

### 3. የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት

1. በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በአምራቾችና በአቅራቢዎች ወይም በአምራቾችና በአቀናባሪዎች መካከል ብቻ የሚከናወን ይሆናል[89]፡፡
2. አግባብነት ያለው የክልል አካል በግብይት ጉዳይ በሕግ ሥልጣን ከተሠጣቸው ሌሎች የክልሉ አካላት ጋር በመመካከር በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አምራች አካባቢ የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ የግብይት ማዕከላትን ብዛትና ሥርጭት ይወስናል፡፡
3. አግባብነት ያለው የክልል አካል የመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላትን ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡-
   ሀ) ለሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ አምራቾችና አቅራቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ፤
   ለ) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለማስወጣት ያላቸው አመቺነት፤
   ሐ) በባሕሪያቸው ተመሳሳይ ለሆኑ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን ለመገበያየት ያላቸውን አመቺነት፤
   መ) ለሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ ግብይት አገልግሎት ለመስጠት ያላቸው አመቺነት፣ እና
   ሠ) ከትምህርት ቤቶች እና ከጤና ፣ ከእምነትና ከሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በበቂ ርቀት ላይ መገኘታቸውን፡፡
4. የመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከልን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ቦታው በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ጥራት ላይ ተፅዕኖ

[89] 20/32 (2006) ደ. 307 አንቀጽ 2(4) ተሻሻለ፡፡

ከሚያሳድሩ የአካባቢው ሁኔታዎች ነጻ እንዲሆን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

5. የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት አደረጃጀትና አሠራር ክልሎች በሚያወጡት ህግ ይወሰናል፡፡

4. **<u>በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት</u>**

1. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በአምራቾች ወይም በአቅራቢዎች እና በላኪዎች ወይም በአቀናባሪዎች መካከል ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ስርዓት መሠረት የሚከናወን ይሆናል[90]፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፡-
   ሀ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከፍተኛ ጥራት ላለውና የተሻለ ገቢ ለሚያስገኝ የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ልዩ የማስተናገጃ ሥርዓት ሊያመቻች ይችላል፡፡
   ለ) ህገ ወጥ ድርጊት ተፈፅሞበት የተገኘና አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት የተያዘ ወይም አንድ ላኪ ወደ ውጭ ሲልክ የተረፈና ከአንድ ኮንቴኔር በታች የሆነ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቀርቦ ሊሸጥ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አቅራቢ ወይም ላኪ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት መሳተፍ የሚችለው በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

5. **<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት</u>**

[90] በ20/32 (2006) አ. 307 አንቀጽ 2(5) ተሻሻለ፡፡

ማንኛውም የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አቅራቢ፣ ላኪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ለንግድ ፈቃድ ከማመልከቱ በፊት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

6. **<u>የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>**

የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፡-

1. አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማከማቻ መጋዘን፣ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ከረጢት እና ሌሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ፤
2. በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያሉት መሆኑ፤[91]
3. ባሕሪያቸው የተለያዩ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ዓይነቶችን እንደ ባህሪያቸው ለማዘጋጀት የሚያስችል አሠራር የዘረጋ መሆኑ፤
4. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፤
5. ከሰሊጥ ወይም ከነጭ ቦሎቄ ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሠማራ መሆኑ፤ እና
6. ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለማቅረብ የገዛውን፣ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያቀረበውንና በመጋዘን የቀረውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ክምችት በዓይነትና በመጠን ለይቶ ቢያንስ በየወሩ መጨረሻ ላይ አግባብ ያለው የሴክተር መስሪያ ቤት የሚያሳውቅበት የመረጃ ፍሰት ስርዓት የዘረጋ መሆኑ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

7. **<u>የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>**

የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፡-

[91] በአንቀፅ 6(2)፣ 7(2) እና 8(4) "የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን" ይል የነበረው በ20/32(2006) ደ.307 አንቀፅ 2(6) "በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል" በሚል ተተክቷል።

1. የአቅርቦት ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ለውጭ ገበያ አዘጋጅቶ ለመላክ የሚገለገልበት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው አግባብ ያለው ሴክተር መስሪያ ቤት ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ የሰሊጥ ማከማቻ መጋዘን፣ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማዘጋጃ ወይም ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ፤
2. በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለው መሆኑ፤
3. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አካባቢ፣ በአካባቢው በሚገኝ ማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆኑ፣
4. ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የገዛውን፣ ወደ ውጭ የላከውንና በመጋዘን የቀረውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ክምችት በዓይነትና በመጠን ለይቶ ቢያንስ በየወሩ መጨረሻ ላይ አግባብ ላለው ሴክተር መስሪያ ቤት የሚያሳውቅበት የመረጃ ፍሰት ስርዓት የዘረጋ መሆኑ፤
5. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመሰጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፤ እና
6. ከሰሊጥ ወይም ከነጭ ቦሎቄ ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሠማራ መሆኑ፤ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

8. <u>ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማዘጋጀት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

ለሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማዘጋጀት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፡-

1. አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት ያወጣውን የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም ከሦስተኛ ወገን በኪራይ ያገኘው የማከማቻ መጋዘንና የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማዘጋጃ ወይም ማበጠሪያና ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ መሣሪያዎች ያለው መሆኑ፤
2. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፤

3. ከሰሊጥ ወይም ከነጭ ቦሎቄ ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሠማራ መሆኑ፤
4. በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለው መሆኑ
5. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አካባቢ፣ በአካባቢው በሚገኝ ማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆኑ፣ እና
6. የተለያየ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን ለመለየት የሚያስችለው አሠራር ያለው መሆኑ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

9. <u>የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

ለሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፡-

1. አግባብ ያለው ሴክተር መስሪያ ቤት ያወጣውን የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆኑ፤
2. የተለያዩ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን ለመለየት የሚያስችለው አሠራር ያለው መሆኑ፤ እና
3. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል ፡፡

10. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማመልከቻውን አግባብነት ላለው ሴክተር መስሪያ ቤት ወይም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ላኪነትን የሚመለከት ሲሆን ለአግባብነት ላለው ሴክተር መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

2. ማመልከቻው የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ ደንብ የተደነገጉት መስፈርቶች መሟላታቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችንና ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡
3. አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት አመልካቹ የብቃት ማረጋገጫው የማይገባው መሆኑን በወሰነ ጊዜ የክልከላውን ምክንያት በውሳኔው ላይ በዝርዝር ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡
4. አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሣኔው በተሰጠው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ አግባብነት ላለው ሴክተር መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ የሕግ አተረጓጎምን በሚመለከት በሚኒስትሩ ወይም በበላይ ኃላፊው ውሳኔ ቅር ከተሰኘም ውሣኔው በተሰጠው በ20 የሥራ ቀናት ውስጥ እንዳአግባብነቱ ለፌዴራል ወይም ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

11.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድና መሠረዝ</u>

1. በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን መስፈርቶች አጓድሎ ሲገኝ፣ ወይም

   ለ) የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ፤

   አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት ጉድለቶቹን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያስተካክል በማስገንዘብ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል፡፡
2. በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው፤

   ሀ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ፤ ወይም

   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤

   የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ አግባብነት ባለው ሴክተር መስሪያ ቤት ሊሠረዝ ይችላል፡፡

3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሠረዘበት ሰው ውሣኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 20 ቀናት ውስጥ እንዳግባቡ አግባብነት ላለው ሴክተር መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. የሕግ አተረጓጎምን በሚመለከት በሚኒስትሩ ወይም በበላይ ኃላፊው ውሳኔ ቅር ከተሰኘም ውሣኔው በተሰጠው በ60 ቀናት ውስጥ እንደአግባብነቱ ለፌዴራሉ ወይም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

12.<u>የእግድ ወይም የመሠረዝ ውጤት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዕገዳው ወይም በመሰረዙ ላይ የቀረበው ይግባኝ በመታየት ላይ እያለ ቢሆንም በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ግብይት ሥራ ላይ ሊሠማራ አይችልም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዚህ ደንብ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ መገልገያዎቹን፣ መሣሪያዎቹንና ዕቃዎቹን የፀና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>በሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ወይም አገልግሎት ሰጪነት ተግባር የተሠማራ ሰው ግዴታዎች</u>

13.<u>የግብይት ተሳታፊዎች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ግብይት ሥራ የተሠማራ ሰው፡-

1. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትን በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላትና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላይ ብቻ የማካሄድ፣
2. አግባብ ያለው አካል ለሥራው አፈጻጸም የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈጸም፣
3. ሰሊጡን ወይም ነጭ ቦሎቄውን ከማስጫኑ በፊት አሽከርካሪውን እና ተሽከርካሪውን በዚህ ደንብና ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት መሠማራታቸውን የማረጋገጥ፣

4. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማዘጋጃና ማከማቻ ድርጅቱና መሣሪያዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣
5. ለግብይት ካዘጋጀው ሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የማቅረብ፣
6. ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ከአምራች አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ወደ ወደብ ሲያጓጉዝ በሚመለከተው አስፈጻሚ አካል በፕሎምፕ ማሳሸግና የተሰጠውን መሸኛ የመያዝ፣
7. የየእለቱን የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግዥና ሽያጭ መጠን፣ ደረጃና ዋጋ ዝርዝር መዝግቦ የመያዝና በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሲጠየቅ የማሳየት፣ እንዲሁም ድርጅቱን በአካል በመገኘት ለመጎብኘት ወይም ክምችቱን ለማወቅ ሲፈለግ የመተባበር፣
8. የአገሪቱን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ተቀባይነት የሚቀንስ ማናቸውንም ድርጊት ከመፈጸም የመቆጠብ፣

ግዴታዎች አሉበት፡፡

14. <u>**የአቅራቢ ግዴታዎች**</u>

ማንኛውም አቅራቢ፡-

1. ለመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላት የተገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በወቅቱ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ በማቅረብ የመሸጥ፣
2. ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያቀርበው አቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ፣
3. የአንድን አካባቢ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ከሌላ አካባቢ ሰሊጥ ጋር ሳያደባልቅ የመሸጥ፣

ግዴታ አለበት፡፡

15. <u>**የላኪ ግዴታዎች**[92]</u>

ማንኛውም ላኪ፡-

[92] በ20/32 (2006) ደ. 307 አንቀጽ 2(9) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (5) የነበረው ንዑስ አንቀጽ (7) ሆኖ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) አዲስ ተጨምረዋል፡፡

1. ወደ ውጭ አገር የሚልከውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም በአገሪቱ የጥራት ደረጃ ያልወጣለት ከሆነ በገዥው መሥፈርት መሠረት የማዘጋጀት ወይም የማቀነባበር፣[93]
2. የሚያደርገውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ሽያጭ ስምምነትና ትክክለኛ ዋጋ ውል ከፈፀመ 24 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስመዝገብ እንዲሁም ለሚኒስቴሩና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካሎች በ15 ቀናት ውስጥ የማሳወቅ፣
3. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተገዛውን የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አንድ የምርት ዘመን ባለቀ ሁለት ወር ውስጥ አጠናቆ ወደ ውጭ የመላክ፣
4. አሳማኝ ምክንያት በመኖሩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተፈቅዶ ካልተራዘመ በስተቀር ከገዢ ጋር የገባውን ውል በውሉ ጊዜ ውስጥ የመፈጸም፣
5. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመግዛት፣
6. ተረፈ ምርትን ወይም ብጣሪን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ አቅርቦ የመሸጥ፣
7. ወደ ውጭ ሲልክ የተረፈና ከአንድ ኮንቴኔር በታች የሆነ ካልሆነ በስተቀር ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያለማቅረብ፣

ግዴታዎች አሉበት፡፡

**16.<u>የአቀናባሪ ግዴታዎች</u>**[94]

ማንኛውም አቀናባሪ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1. ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዛውን ምርት ፈትጎ ወይም ቆልቶ ወይም ጣህና፣ ሐለዋ፣ የምግብ ዘይት ወይም መሰል ኢንዱስትሪያዊ ምርት አቀናብሮ ለገበያ የማቅረብ፤
2. ተረፈ ምርትን ወይም ብጣሪን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ አቅርቦ የመሸጥ፤
3. ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አዘጋጅቶ ብቻ ለገበያ ያለማቅረብ፤
4. ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ዳግም ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያለማቅረብ፤

---

[93] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በ20/32 (2006) ደ. 307 አንቀጽ 2(8) ተሻሻለ፡፡

[94] በ20/32 (2006) ደ. 307 አንቀጽ 2(10) ተሻሻለ፡፡

5. ስለሚያቀናብረው ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ሲጠየቅ ማንኛውንም መረጃ የማቅረብና ናሙና የመስጠት፡፡

17.**የአገልግሎት ሰጪዎች ግዴታዎች**

ማንኛውም የአገልግሎት ሰጪ፣

1. አግባብ ያለው አካል ለአገልግሎቱ አሰጣጥ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈፀም፣
2. የአገሪቱን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ተቀባይነት የሚቀንስ ማናቸውንም ድርጊት ከመፈፀም የመቆጠብ፣
3. ለግብይት ካዘጋጀው ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የማቅረብ፣
4. ወደ ውጭ አገር የሚላክን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም በአገሪቱ የጥራት ደረጃ ያልወጣለት በሆነ ጊዜ በገዥው መሥፈርት መሰረት የማዘጋጀት፣[95]

ግዴታዎች አሉበት፡፡

18.**የአምራች ግዴታዎች**

1. ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላት ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመሸጥ ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በግሉ ወይም አባል በሆነበት የኅብረት ሥራ ማህበር አማካኝነት በቀጥታ ወደ ውጭ የመላክ መብት ይኖረዋል፡፡

## **ክፍል አምስት**

## **የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ጥራትና ግብይት ቁጥጥር**

19.**የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ጥራት ቁጥጥር**

1. በአቅራቢ ወይም በአምራች ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጓጓዝ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ሲጫን አግባብነት ባለው የክልል አካል በተመደበ የግብይትና ጥራት

---

[95] በ20/32 (2006) አ. 307 አንቀጽ 2(11) ተሻሻለ፡፡

ተቆጣጣሪ በጥራትና በዓይነቱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ከተደረገ በኋላ ታሽጎ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ይሸኛል፡፡

2. ሰሊጡ ወይም ነጭ ቦሎቄው ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ሲደርስ በወካይ ናሙና መሠረት አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎለት በደረጃ ይመደባል፡፡
3. ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ መሟላቱ በሚኒስቴሩ ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት እንዲያገኝ ከተደረገ በኋላ ታሽጎ ወደ ወደብ ይሸኛል፡፡

20.<u>የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪዎች ስለመመደብ</u>

1. እንደ አግባቡ ሚኒስቴሩና አግባብነት ያላቸው የክልል አካላት የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪዎችን ይመድባሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚመደብ የሰሊጥ ተቆጣጣሪ ስለሰሊጥ ወይም ስለነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት በቂ ዕውቀት ያለውና በመልካም ሥነ-ምግባሩ የተመሠከረለት መሆን ይኖርበታል፡፡

21.<u>የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 20 መሠረት የተመደበ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችንና ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ፤

   ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የሚካሄደውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት፣

   ለ) በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አምራች ባለሀብቶች የሚካሄደውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አመራረትና አዘገጃጀት፣

   ሐ) በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አቅራቢዎች፣ ላኪዎችና አዘጋጆች የሚከናወነውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ዝግጅት፣

   መ) በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አቅራቢዎች፣ ላኪዎች፣ አዘጋጆችና አጓጓዦች የሚደረገውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማጓጓዝ፣

   የመቆጣጠር ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡
2. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ኃላፊነቱን ለመወጣት፡-

ሀ) ወደ ማንኛውም የሰሊጥ ወይ የነጭ ቦሎቄ መጋዘን ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት ለመግባትና አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች ለመመልከትና ኮፒ ለመውሰድ እና የፎቶግራፍ መረጃና የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ናሙና ለመውሰድ፣

ለ) ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪን በማስቆም ለመፈተሽና አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች እንዲቀርቡለት ለመጠየቅ፣ እና

ሐ) በአቅራቢ ወይም በአምራች ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጓጓዝ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርት ሲጫን በጥራትና በዓይነቱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ማድረግ ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማውጣት ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ደረሰኝ ሰጥቶ የመያዝ ወይም የሰሊጡን ወይም የነጭ ቦለቄውን ናሙና ወስዶ ሰሊጡ ወይም ነጭ ቦሎቄው የተከማቸበትን መጋዘን የማሸግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

4. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦለቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ስለተወሰደው እርምጃ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ሪፖርት ማድረግና በዚህ ደንብ አንቀጽ 23 መሠረት መወሰድ ስላለባቸው ተከታታይ እርምጃዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልሉ አካል የሚሰጠውን መመሪያ መፈጸም አለበት፡፡

22.<u>ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም</u>

1. ማንኛውም ሰው በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አዘገጃጀት፣ ክምችት፣ ማጓጓዝ ወይም ግብይት ሂደት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገ ወጥ ድርጊት መፈጸሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ወይም ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል በጽሑፍ መጠቆም ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ያስያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (4)(ለ) መሠረት የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል፡፡

23. <u>ስለተያዘ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የተያዘበት ወይም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ መጋዘኑ የታሸገበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልሉ አካል ተቃውሞውን ከአንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ውሳኔ፡-
   ሀ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚሽር ከሆነ ወዲያውኑ የተያዘው ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም ሰሊጡ የተከማቸበት መጋዘን እሽግ እንዲነሳ ይደረጋል፣ ወይም
   ለ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያጸና ከሆነ የሰሊጡን ወይም የነጭ ቦሎቄውን ናሙና በማስቀረት የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ለአቅራቢዎች ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለላኪዎች ወይም ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ከሆነ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላኪዎች እንዲሸጥ ተደርጎ ገንዘቡ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) የተመለከተውን ውሳኔ የሚቃወም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደአግባብነቱ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት፡-
   ሀ) የሚኒስቴሩን ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል የሰጠውን ውሳኔ ከሻረው ሰሊጡን ወይም ነጭ ቦሎቄውን ለመሸጥ የወጣውን ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሽያጩ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፣ ወይም

ለ) ውሳኔውን ካጸናው ወይም ባለሰሊጡ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ ለጠቋሚ የሚከፈል አበል ካለ በሚኒስቴሩ መመሪያ መሠረት ተሰልቶ ከተቀነሰ በኋላ የሽያጩን ገንዘብ እንደአግባቡ ለፌዴራሉ ወይም ለክልሉ መንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 24.የተከለከሉ ተግባራት

የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

1. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በተሰማራ ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ካወጣው የቴክኒክ አሠራር ውጭ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ማዘጋጀት፤
2. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በተሰማራ ማንኛውም ሰው ወይም በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አምራች ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ውጭ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ መሸጥም ሆነ መግዛት፤
3. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን በማንኛውም አቅራቢ ከአንድ ምርት ዘመን በላይ ወይም በማንኛውም ላኪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3) ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ማከማቸት፤
4. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በተሠማራ ማንኛውም ሰው የሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን እንዲያከማች ከተፈቀደለት መጋዘን ውጭ ማከማቸት፤
5. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማጓጓዝ ሥራ በተሠማራ ማንኛውም ሰው ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ንጽህና በጎደለው ሁኔታ ወይም ህጋዊ ፈቃድ ለሌለው ሰው ማጓጓዝ፤
6. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በተሰማራ ወይም ከሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ሥራ በተሰማራ ማንኛውም ሰው አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሆነ ብሎ አሳሳች ድርጊት መፈጸም፡፡

### 25.የመተባበር ግዴታ

1. ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2. የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለመያዝ በሚደረገው እንቅስቃሴ ፖሊስ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

26. <u>ቅጣት</u>

በዚህ ደንብ የተደነገጉትን የሚጥስ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

27. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

28. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ማንኛውም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አቅራቢ፣ ላኪ ወይም አገልግሎት ሰጭ ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ከአግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስኪያገኝ ድረስ ባለው የጸና የንግድ ፈቃድ ሥራውን ማካሄድ ይችላል፡፡

29. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች</u>

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

30. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

1. ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት መካሄድ የሚጀምርበት ቀን በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 14 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## ደንብ ቁጥር 377/2008

## የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 (በአዋጅ ቁጥር 665/2002 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 31(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 377/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጉም**

   በዚህ ደንብ ዉስጥ፦

   1. "የጥራጥሬ ምርቶች" ማለት ከነጭ ቦሎቄ ውጭ ያሉ የተለያዩ የቦሎቄ ዝርያዎች፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር፣ ምስር፣ ባቄላ፣ ሽምብራ፣ አተር፣ ጓያ፣ ግብጦ እና የመሳሰሉት ናቸው፤
   2. "የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል" ማለት ለጥራጥሬ ምርቶች መገበያያነት እንዲሆን አግባብነት ባለዉ የክልል አካል የተከለለ ስፍራ ነው፤
   3. "አገልግሎት ሰጪ" ማለት የጥራጥሬ ምርትን በማዘጋጀት፣ በማከማቸት ወይም በማጓጓዝ አገልግሎት ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤
   4. "የአቅርቦት ጥራጥሬ ምርት" ማለት በአቅራቢ፣ በአምራች ወይም በህብረት ስራ ማህበር አማካኝነት ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ተገዝቶ በቀጥታ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚቀርብ ለኤክስፖርት ያልተዘጋጀ የጥራጥሬ ምርት ነው፤
   5. "አቅራቢ" ማለት ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያቀርብ ማንኛዉም ሰው ነው፤
   6. "ሸማቾች" ማለት የጥራጥሬ ምርቶችን በመግዛት ለፍጆታ የሚጠቀሙ ሲሆኑ በከፍተኛ መጠን በመግዛት ለፍጆታ የሚያውሉ የግል ድርጅቶችን፣ የሸማቾች

ህብረት ሥራ ማህበራትን፣ የመከላከያ ተቋማትን፣ የትምህርት ተቋማትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማትን ያካትታል፤

7. "ላኪ" ማለት ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ለውጭ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ወይም በራሱ ማሳ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት ለዉጭ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ አነስተኛ አምራች፣ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር ወይም የእርሻ ድርጅት ነው፤
8. "ጅምላ ነጋዴ" ማለት በአምራች አካባቢዎች ከሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የጥራጥሬ ምርቶችን በመግዛት አምራች ባልሆኑ አካባቢዎች ላሉ የእህል ቸርቻሪ ነጋዴዎች የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤
9. "ቸርቻሪ ነጋዴ" ማለት የጥራጥሬ ምርትን ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል ገዝቶ በቀጥታ ለሸማቾች በመሸጥ ንግድ የተሰማራ ሰው ነው፤
10. "አምራች" ማለት አነስተኛ አምራች ገበሬዎች፣ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራትን፣ የእርሻ ድርጅቶችን፣ በኮንትራት የሚያስመርቱትን ጨምሮ ማንኛውም የጥራጥሬ ሰብሎችን የሚያመርት ሰው ነው፤
11. "የግብይት ተዋናይ" ማለት የጥራጥሬ ምርቶች ሸማች፣ ሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበር፤ ቸርቻሪ ነጋዴ፣ ጅምላ ነጋዴ፣ አቅራቢ፣ አቀናባሪ፣ ላኪ እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነው፤
12. "አቀናባሪ" ማለት የማቀናበሪያ ኢንዱስትሪ ተጠቅሞ እሴት የተጨመረባቸውን የጥራጥሬ ምርቶች የኢንዱስትሪ ምርት በማምረት ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤
13. "አሳሳች ድርጊት" ማለት የጥራጥሬ ምርቶች ዋጋን፣ መጠንን፣ ጥራትን ወይም ዓይነትና ዝርያን እንዲሁም የነዚህን ማንኛውንም መረጃ በተመለከተ የግብይት ተዋንያንና የሚመለከታቸው አካላትን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ወይም የሃገሪቱን የጥራጥሬ ምርቶች ተቀባይነት የሚቀንስ ተግባር ነው፤
14. "ማዘጋጀት" ማለት የጥራጥሬ ምርቶችን አበጥሮና ከባዕድ ነገር አፅድቶ ለገበያ ለማቅረብ ማሰናዳት ነው፤
15. "አግባብነት ያለው የክልል አካል" ማለት ንግድን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፡፡

16. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬድዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
17. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድ ሚኒስቴር[96] ወይም ሚኒስትር ነው፤
18. “አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት” ማለት የጥራጥሬ ምርቶችን ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ ወይም ለማቀናበር ወይም ለመሰል ተግባራት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤
19. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
20. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በጥራጥሬ ሰብሎች አምራቾች እና የግብይት ተዋንያን ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት</u>

4. <u>የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት</u>
   1. በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የአቅርቦት ጥራጥሬ ምርት ግብይት ሻጭ በሆነ አምራች እና ገዢ በሆነ ሸማች ወይም ጅምላ ነጋዴ ወይም አቀናባሪ ወይም ቸርቻሪ ነጋዴ ወይም አቅራቢ መካከል ብቻ የሚከናወን ይሆናል።
   2. አግባብነት ያለው የክልል አካል በጥራጥሬ ምርት ግብይት ጉዳይ በሕግ ሥልጣን ከተሠጣቸው ከሌሎች አካላት ጋር በመመካከር በጥራጥሬ ምርቶች አምራች አካባቢ የሚከለሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ብዛትና ሥርጭት ይወስናል።
   3. አግባብነት ያለው የክልል አካል የመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ማዕከላትን ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

      ሀ) ለጥራጥሬ ምርቶች አምራቾችና አቅራቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ፤

[96] በ25/82011) አ.1097 አንቀፅ 9(6) መሰረተ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ይነበብ፡፡

ለ) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለማስወጣት ያላቸውን አመቺነት፤

ሐ) የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት አገልግሎት ለመስጠት ያላቸውን አመቺነት፤

መ) በትምህርት ቤቶች፣ በጤና፣ በእምነት ተቋማት እና በሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ተፅዕኖ በማይፈጥር ርቀት ላይ መገኘታቸውን፡፡

4. የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከልን ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው አካል የግብይት ቦታው በጥራጥሬ ምርቶች ጥራት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ የአካባቢው ሁኔታዎች ነፃ እንዲሆን ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መስራት አለበት፡፡

5. የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት አደረጃጀት፣ አሠራር እና አስተዳደር ክልሎች በሚያወጡት ህግ ይወሰናል፡፡

5. **<u>በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት</u>**

1. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ሻጭ በሆኑ አምራቾች ወይም አቅራቢዎች እና ገዥ በሆኑ ላኪዎች፣ አቀናባሪዎች፣ ጅምላ ነጋዴዎች፣ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት መካከል በገበያው ሥርዓት መሠረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፦

ሀ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከፍተኛ ጥራት ላለውና የተሻለ ገቢ ለሚያስገኝ የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርት ልዩ የማስተናገጃ ሥርዓት ሊያመቻች ይችላል፤

ለ) ህገ ወጥ ድርጊት ተፈፅሞበት በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተያዘ የጥራጥሬ ምርት ወይም አንድ ላኪ ወደ ውጭ ሲልክ የተረፈና ከአንድ ባለ 20 እግር ኮንቴይነር በታች የሆነ የጥራጥሬ ምርት በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቀርቦ ሊሸጥ ይችላል፤

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

**<u>ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ስለግብይት ተዋንያን ግዴታዎች</u>**

6. **<u>ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>**

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ ያለባቸውን ግብይት ተዋንያን ዝርዝር እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ አግባብ ያለው ሴክተር መስሪያ ቤት በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

7. <u>በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የተሠማራ ሰው ግዴታዎች</u>

ማንኛውም በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ሥራ ላይ የተሠማራ ሰው፦

1. የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 እና 5 መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የማካሄድ፤
2. አግባብ ያለው አካል ለሥራው አፈጻጸም የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈፀም፤
3. ለግብይት ካዘጋጃቸው የጥራጥሬ ምርቶች ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና በነፃ የማቅረብ፤
4. የየዕለቱን የጥራጥሬ ምርቶች ግዥና ሽያጭ መጠን፣ ደረጃና የዋጋ ዝርዝር እና ለግብይት ሥርዓቱ ጠቃሚ የሆኑ ማንኛቸውንም መረጃዎች መዝግቦ የመያዝና በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሲጠየቅ የማሳየት፣ እንዲሁም ድርጅቱን በአካል በመገኘት ለመጎብኘት ወይም ክምችቱን ለማወቅ ሲፈለግ የመተባበር፤
5. አሳሳች የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እና ሕገወጥ ዝውውር ከመፈፀም የመቆጠብ።

8. <u>የአቅራቢ ግዴታዎች</u>

ማንኛዉም አቅራቢ፦

1. ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርት በምርት ዘመኑ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ በማቅረብ የመሸጥ፣
2. ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያቀርበው የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ፣
3. የአንድን አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ጋር ሳያደባልቅ የመሸጥ፣
4. ለጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻነት ብቻ በተፈቀደ መጋዘን ውስጥ የማከማቸት፣
5. የጥራጥሬ ምርቶችን የጥራት ደረጃውን በጠበቀ ከረጢት ውስጥ የማከማቸት እና ጥራቱን በማይቀንስ ወይም በማያበላሽ ሁኔታ የማጓጓዝ፣

   ግዴታዎች አሉበት፡፡

9. <u>**የላኪ ግዴታዎች**</u>

ማንኛውም ላኪ ፦

1. ወደ ውጭ አገር የሚልካቸውን የጥራጥሬ ምርቶች በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም በአገሪቱ የጥራት ደረጃ ያልወጣለት ከሆነ በገዥው የጥራት ደረጃ መሠረት የማዘጋጀት፣
2. የሚያደርገውን የጥራጥሬ ምርቶች ሽያጭ ስምምነትና ትክክለኛ ዋጋ ውል ከፈፀመ 24 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በኢትየጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስመዝገብ እንዲሁም ለሚኒስቴሩና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በ15 ቀናት ውስጥ የማሳወቅ፣
3. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርት አንድ የምርት ዘመን ባለቀ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ወደ ውጭ የመላክ፣
4. አሳማኝ ምክንያት በመኖሩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተፈቅዶ ካልተራዘመ በስተቀር ከገዢ ጋር የገባውን ውል በውሉ ጊዜ ውስጥ የመፈፀም፣
5. የጥራጥሬ ምርቶችን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመግዛት፣
6. ወደ ውጭ ሲልክ የተረፈና ከአንድ ባለ 20 እግር ኮንቴይነር በታች የሆነ ካልሆነ በስተቀር ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን የጥራጥሬ ምርት በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያለማቅረብ፣

ግዴታዎች አሉበት፡፡

10. <u>**የጅምላ ነጋዴ ግዴታዎች**</u>

ማንኛውም ጅምላ ነጋዴ፤-

1. የጥራጥሬ ምርቶችን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመግዛት፣
2. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛዉን የጥራጥሬ ምርት በምርት ዘመኑ ለቸርቻሪ ነጋዴዎች ወይም ለሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የመሸጥ፣
3. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛዉን የጥራጥሬ ምርት ከሌላ አካባቢ የጥራጥሬ ምርት እና ባዕድ ነገሮች ጋር ሳያደባልቅ የመሸጥ፣
4. ለጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻነት በተፈቀደ መጋዘን ብቻ የጥራጥሬ ምርቶች የማከማቸት፣

5. የጥራጥሬ ምርቶችን የጥራት ደረጃውን በጠበቀ ከረጢት የማከማቸት እና ጥራቱን በማይቀንስ ወይም በማያበላሽ ሁኔታ የማጓጓዝ፣

ግዴታዎች አሉበት።

11. **<u>የአገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ፦

1. አግባብ ያለው ሴክተር መስሪያ ቤት ለአገልግሎቱ አሰጣጥ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈፀም፣
2. የተከለከሉ ተግባራትንና አሳሳች የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እና ዝውውርን ከመፈፀም የመቆጠብ፣
3. ከሚያዘጋጀውና ከሚያጓጉዘው የጥራጥሬ ምርት ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና በነፃ የማቅረብ፣
4. ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የጥራጥሬ ምርቶችን በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም በአገሪቱ የጥራት ደረጃ ያልወጣላቸው ከሆነ በገዥው ጥራት ደረጃ መሠረት የማዘጋጀት፣
5. የጥራጥሬ ምርቶችን ምርት ከአምራች አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ወደ ወደብ ሲያጓጉዝ በሚመለከተው አስፈጻሚ አካል በፕሎምፕ የማሳሸግና የተሰጠውን መሸኛ የመያዝ፣
6. የጥራጥሬ ምርቶችን ከማስጫኑ በፊት አሽከርካሪው እና ተሽከርካሪውን በዚህ ደንብና ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት መሠማራታቸውን የማረጋገጥ፣
7. የጥራጥሬ ምርቶች ማዘጋጃና ማከማቻ ድርጅቱ እና የመገልገያ መሳርያዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በሚመለከታቸው አካላት የተሰጠ ማረጋገጫ የመያዝ፣

ግዴታዎች አሉበት፡፡

12. **<u>የአምራች ግዴታዎች</u>**

1. ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት በመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርት ግብይት ማዕከላት ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመሸጥ ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት በግሉ ወይም አባል በሆነበት የህብረት ሥራ ማኅበር በኩል በቀጥታ ወደ ውጭ መላክ ወይም በማቀነባበር ለገበያ ማቅረብ ይችላል።

## ክፍል አራት

## የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ቁጥጥር

### 13. የጥራጥሬ ምርቶች ደረጃ አሰጣጥና ስለማጓጓዝ

1. በአቅራቢ ወይም በአምራች ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጓጓዝ የጥራጥሬ ምርት ሲጫን አግባብነት ባለው የክልል አካል በተመደበ የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በጥራትና በዓይነቱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ከተደረገ በኋላ ታሽጎ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ መሸኘት አለበት፡፡
2. የጥራጥሬ ምርት ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ሲደርስ በወካይ ናሙና መሠረት አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎለት በደረጃ መመደብ አለበት፡፡
3. ለኤክስፖርት የተዘጋጀ የጥራጥሬ ምርት ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ስለማሟላቱ በሚኒስቴሩ ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት እንዲያገኝ ከተደረገ በኋላ ታሽጎ ወደ ወደብ መሸኘት አለበት፡፡

### 14. የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተቆጣጣሪዎችን ስለመመደብ

እንደ አግባቡ ሚኒስቴሩና አግባብ ያላቸው የክልል አካላት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተቆጣጣሪዎችን ይመድባሉ፡፡

### 15. የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 መሠረት የተመደበ ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችና ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
2. በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የሚካሄደው የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት፣ አከመቻቸት፣ አዘገጃጀት እና አጓጓዝ በዚህ ደንብና በመመሪያ በተደነገገው አሠራርና ደረጃ መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራል፤
3. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ ሕገወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን የጥራጥሬ ምርት

ደረሰኝ ሰጥቶ ይይዛል ወይም ናሙና በነፃ ወስዶ የጥራጥሬ ምርቱ የተከማቸበትን መጋዘን ያሽጋል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ስለተወሰደው እርምጃ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ሪፖርት ያደርጋል፤
5. በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 መሠረት መወሰድ ስላለባቸው ተከታታይ እርምጃዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካል የሚሰጠውን ትእዛዝ በመከታተል ይፈፅማል፡፡

16. <u>ህገ ወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም</u>

1. ማንኛውም ሰው በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት፣ አዘገጃጀት፣ ክምችት ወይም ማጓጓዝ ሂደት ላይ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ደንቡን ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገ ወጥ ድርጊት መፈፀሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ወይም ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል መጠቆም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን የጥራጥሬ ምርት ያስያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 17(4)(ለ) መሠረት የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል፡፡

17. <u>ስለተያዙ የጥራጥሬ ምርቶች እና ስለታሸጉ ማከማቻ መጋዘኖች</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 15(3) መሠረት የጥራጥሬ ምርት የተያዘበት ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻ መጋዘኑ የታሸገበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልሉ አካል ተቃውሞውን ከአንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡ የሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ውሳኔ፡-

   ሀ/ የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚሽር ከሆነ ወዲያውኑ የተያዘው የጥራጥሬ ምርቱ ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም የተከማቸበት መጋዘን እሽግ እንዲነሳ ይደረጋል፤ ወይም

   ለ/ የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያፀና ከሆነ የጥራጥሬ ምርቱን ናሙና በማስቀረት የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርት ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት

ለአቅራቢዎች ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለላኪዎች ወይም ለኤክስፖርት የተዘጋጀ የጥራጥሬ ምርት ከሆነ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለላኪዎች እንዲሸጥ ተደርጎ ገንዘቡ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ለ) የተመለከተውን ውሳኔ የሚቃወም የጥራጥሬ ምርቱ ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል የሰጠውን ውሳኔ ፡-

   ሀ/ ከሻረው የጥራጥሬ ምርቱን ለመሸጥ የወጣው ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሽያጩ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፣ ወይም

   ለ/ ካፀናው እና የጥራጥሬ ምርቱ ባለንብረት በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ካላቀረበ ከጥራጥሬ ምርቱ ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ አስተዳደራዊ ወጪዎች ተቀንሰው 40 መቶኛ ለጠቋሚው ወይም ያለጥቆማ የተያዘ ከሆነ ለያዘው የመንግሥት ፀጥታ ተቋም ይከፈላል፤ ቀሪው 60 መቶኛ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የተከለከሉ ድርጊቶች

የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈፀም የተከለከለ ነው፦

1. የብቃት ማረጋገጫና የፀና የንግድ ፍቃድ ሳይኖረው የጥራጥሬ ምርቶችን መነገድ፤
2. በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት ካወጣው የቴክኒክ አሠራር ውጭ የጥራጥሬ ምርቶችን ማዘጋጀት፤
3. በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ውጭ የጥራጥሬ ምርቶችን መሸጥም ሆነ መግዛት፤

4. የጥራጥሬ ምርቶችን በማንኛውም አቅራቢ ወይም ጅምላ ነጋዴ ወይም ላኪ ከአንድ የምርት ዘመን በላይ ወይም በማንኛውም ላኪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 9(3) ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በላይ ማከማቸት፤
5. በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቶችን እንዲያከማች ከተፈቀደለት መጋዘን ውጭ ማከማቸት፤
6. በጥራጥሬ ምርቶች የማጓጓዝ ስራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቶችን ንፅህና በጎደለው ሁኔታ ወይም ሕጋዊ የማጓጓዣ ፈቃድ በሌለው ተሽከርካሪ ማጓጓዝ፤
7. በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሰማራ ወይም ከጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ያለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሆነ ብሎ አሳሳች ድርጊት መፈፀም፤
8. ይህንን ደንብ እና ደንቡን ተከትሎ የሚወጡ መመሪያዎችን ያለማክበር፤
9. የሀገሪቱን የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚያጎድፍ ማንኛውንም ድርጊት መፈፀም፤
10. በገባው ውል መሰረት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ያለመፈፀም፤
11. በተቆጣጣሪ ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት የሚጠየቀውን መረጃ ያለመስጠት ወይም የተጭበረበረና የተዛባ መረጃ መስጠት፡፡

19. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

በዚህ የቅጣት ድንጋጌ ውስጥ ያልተካተቱ ጥፋቶች አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የሚያስቀጡ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. የጥራጥሬ ምርቶች ግዢ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ውጭ የፈፀመ ማንኛውንም አቅራቢ፣ ጅምላ ነጋዴ፣ ቸርቻሪ ነጋዴ፣ ላኪ ወይም አቀናባሪ የጥራጥሬ ምርቱን ከመውረስ በተጨማሪ ብር 10,000 መቀጮ ይቀጣል፤
2. የጥራጥሬ ምርቶችን ከተፈቀደላቸው የማከማቻ ቦታ ውጭ ያከማቸ ወይም ከተፈቀደ የማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ውጭ ሲያዘጋጅ የተገኘ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቱን ከመውረስ በተጨማሪ ብር 7,000 መቀጮ ይቀጣል፤

3. የጥራጥሬ ምርቶች ጅምላ ንግድ ፍቃድ እና የማዘዋወሪያ ፍቃድ ሳይኖረው የጥራጥሬ ምርቶችን ከአንድ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ ሲያጓጉዝ የተገኘ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቱን ከመውረስ በተጨማሪ ብር 7,000 መቀጮ ይከፍላል፤
4. የጥራጥሬ ምርቶችን ፈቃድ የሌለው ሶስተኛ ወገን ወይም የውጭ ዜጋ ወደ ውጭ አገር መላክ እንዲችል በላኪነት ፈቃዱ ሽፋን የሰጠ ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቸ ማንኛውም ላኪ ከጥራጥሬ ምርቱ መወረስ በተጨማሪ የመላኪያ ፍቃዱ ተሰርዞ ብር 10,000 መቀጮ ይቀጣል፤
5. የመላክ ፈቃድ ሳይኖረው የጥራጥሬ ምርቶችን በመላክ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከጥራጥሬ ምርቱ መወረስ በተጨማሪ ብር 5,000 መቀጮ ይቀጣል፤
6. የጥራጥሬ ምርቶችን የጥራት ደረጃ በሚጎዳና በሚያበላሽ ሁኔታ ያከማቸ ወይም ያጓጓዘ ማንኛውም ሰው ብር 5,000 መቀጮ ይቀጣል፤
7. የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ ማንኛውንም አሳሳች ድርጊት የፈፀመ ሰው የጥራጥሬ ምርቱ ከመወረሱ በተጨማሪ ብር 5,000 መቀጮ ይቀጣል፤
8. የዚህን ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ደንቡን ለማስፈፀም የሚወጣን መመሪያ የጣሰ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቱ ከመወረሱ በተጨማሪ ብር 5,000 መቀጮ ይቀጣል፡፡

20. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ሕገ-ወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን የጥራጥሬ ምርት ለመያዝ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ፖሊስ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

21. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

22. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ማንኛውም የጥራጥሬ ምርቶች አቅራቢ፣ ጅምላ ነጋዴ፣ ላኪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ከሚኒስቴሩ ወይም

አግባብነት ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስኪያገኝ ድረስ ባለው የፀና የንግድ ፈቃድ ሥራውን ማካሄድ ይችላል፡፡

23. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች</u>

የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ወይም የተለምዶ አሰራር በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

24. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

1. ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም እያንዳንዱ የጥራጥሬ ምርት ግብይት በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት መካሄድ የሚጀምርበት ቀን በሚኒስቴሩ ይወሰናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ክፍል ሃያ

## ኢንቨስትመንት፣ አምሮአዊ ንብረት እና ጥራትና ደረጃዎች

### ሀ/ ኢንቨስትመንት

## አዋጅ ቁጥር 1180/2012

## የኢንቨስትመንት አዋጅ

አምራች እና አስቻይ የኢንቨስትመንት መስኮችን ጨምሮ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ በማበረታታት እና በማስፋፋት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን፣ የእድገቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ማጠናከር እና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የአገራዊ ኢኮኖሚውን ዓለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነት የሚያፋጥን፣ የወጪ ንግድን የሚያስፋፋ፣ ሰፊ እና ጥራት ያለው የሥራ ዕድል የሚፈጥር፣ እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች መካከል ዘላቂ እና ተመጋጋቢ ትስስርን የሚያሳልጥ የኢኮኖሚ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት መጠን እና የተሳትፎ መስክ በማስፋት የዕውቀት፣ የክህሎት፣ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ስርጸትን ማፋጠን ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፤

በውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል ትስስርን ማስፋት፣ የኢንቨስትመንት ክልላዊ ስርጭትን ማሻሻል፣ እንዲሁም የውጭ ካፒታል በመጠቀም የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ተወዳዳሪነት ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

ኢንቨስትመንቶች በአገራዊ የኢንቨስትመንት ዓላማዎች የተመለከቱ ግቦችን ማሳካታቸውን እንዲሁም በሕግ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፤

የኢንቨስትመንት ፍሰት፣ መስፋፋት፣ እና ቆይታን ማሳደግ እንዲቻል ኢንቨስትመንት የሚመራበትን ሥርዓት ይበልጥ ግልጽ፣ ተገማች፣ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ሕግ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፦

1. "ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅትን ለማቋቋም፣ ወይም ነባር ድርጅትን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ለመግዛት፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤
2. "ድርጅት" ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤
3. "ካፒታል" ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሰነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንጻ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ የንብረት መብት፣ የአእምሯዊ ንብረት መብት ወይም ሌላ የሚዳሰስ ወይም የማይዳሰስ የንግድ ሀብት ነው፤
4. "ባለሀብት" ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው፤
5. "የአገር ውስጥ ባለሀብት" ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ፤
   - ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ፤
   - ለ) ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊ ዜጋ የተያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፤
   - ሐ) መንግሥት፤
   - መ) የመንግሥት የልማት ድርጅት፤
   - ሠ) አግባብነት ባለው ሕግ የተቋቋመ የህብረት ሥራ ማህበር፤
   - ረ) አግባብነት ባለው ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ባጸደቀችው ዓለምአቀፍ ስምምነት መሠረት እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት፤
   - ሰ) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ-አንቀጽ 5 ፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ረ) በተመለከቱት በማናቸውም መካከል በጋራ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፤

ሸ) ይህ አዋጅ ሲወጣ በሥራ ላይ የነበረ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ብቻ ሆኖ ከዚህ በፊት ታውጀው ከጊዜ በኋላ በተሻሩ ሕጎች መሠረት የአገር ውስጥ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው እና አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያለ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት፣ ወይም

ቀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (5) ፊደል ተራ (ሸ) የተገለጸ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ብቻ ሆኖ በዚሁ ንዑስ-አንቀጽ የተመለከተ የውጭ አገር ዜጋ ተወላጅ ነው፤

6. “የውጭ ባለሀብት” ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ሥራ ላይ ያዋለ፤

ሀ) የውጭ አገር ዜጋ፤

ለ) የውጭ አገር ዜጋ በባለቤትነት የተሳተፈበት ድርጅት፤

ሐ) በማንኛውም ባለሀብት ውጭ አገር የተቋቋመ ድርጅት፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (6) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) በተመለከቱት ማናቸውም ባለሀብቶች መካከል በጋራ የተቋቋመ ድርጅት፤ ወይም፤

ሠ) እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ ውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ነው፤

7. “የመንግሥት የልማት ድርጅት” ማለት ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ነው፤

8. “ማስፋፋት” ወይም “ማሻሻል” ማለት ሊደረስበት የሚችል የነባር ድርጅትን የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅም ቢያንስ ሀምሳ በመቶ በመጠን በማሳደግ ወይም የነባር ድርጅትን አዲስ የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መስመር በመጨመር ምርትን ወይም አገልግሎትን ቢያንስ መቶ በመቶ በዓይነት ማሳደግ ወይም በሁለቱም ማሳደግን ያጠቃልላል፤

9. “የቴክኖሎጂ ሽግግር” ማለት ምርትን ለማምረት ወይም የአመራረት ሂደትን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ለማሻሻል ወይም አገልግሎትን ለመስጠት የሚረዳ ሥርዓት ያለው ዕውቀት ማስተላለፍ ሲሆን የሥራ አመራር እና የቴክኒክ ዕውቀት እንዲሁም የግብይት ሁኔታ ቴክኖሎጂንም ይጨምራል፤ ሆኖም ዕቃዎችን ብቻ ለመሸጥ ወይም ለማከራየት የሚደረግን ግንኙነት አይሸፍንም፤

10.“ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳይኖረው የሚያደርገው ትብብር” ማለት መቶ በመቶ ከወጪ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር የሚያደርገው የውል ግንኙነት ሆኖ የውጭ ድርጅቱ ለአገር ውስጥ ባለሀብቱ በሙሉ ወይም በከፊል የሚሰጠው የሚከተሉት ትብብሮችን ይጨምራል፤

ሀ) አስተማማኝ የውጭ ገበያ ግኝት፤

ለ) ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን የማምረት ዘዴ፤

ሐ) የውጪ ንግድ ሥራ አመራር ዕውቀት፤

መ) በውጭ ገበያ የመሸጥ ስልት፤

ሠ) ለውጪ ምርት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች እና ግብዓቶች አቅርቦት ስልት፤

11.“መንግሥት” ማለት የፌደራሉ መንግሥት ወይም የክልል መስተዳድር ነው፤

12.“ክልል” ወይም “የክልል መስተዳድር” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ- መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

13.“ቦርድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤

14.“ኮሚሽን” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤

15.“ጉባዔ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 መሠረት የተቋቋመ የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳደሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ ነው፤

16.“አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት” ማለት ኮሚሽኑ፣ ከኮሚሽኑ በውክልና ሥልጣን የተሰጠው የፌደራል መንግሥት አካል፣ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ኢንቨስትመንት ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል መስተዳድር አካል ነው፤

17.“የኢንዱስትሪ ፓርክ” የሚለው ሐረግ በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 አንቀጽ 2/1/ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል ፤

18.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ይጨምራል።

2.

3. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በማዕድን እና በነዳጅ ፍለጋ፣ ምርመራ እና የማምረት ሥራዎች ላይ ከሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች በስተቀር በሁሉም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. **<u>የሥልጣን ክልል</u>**

1. የሚከተሉት ኢንቨስትመንቶች አስተዳደር በኮሚሽኑ የሥልጣን ክልል ሥር ይወድቃሉ፡-

   ሀ) ሙሉ በሙሉ በውጭ ባለሀብት የተያዘ ኢንቨስትመንት፤

   ለ)በአገር ውስጥ እና በውጭ ባለሀብቶች በጋራ የተያዘ ኢንቨስትመንት፤

   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ-አንቀጽ (5) ከፊደል ተራ (ረ) እስከ (ቀ) በተደነገገው መሠረት እንደ የአገር ውስጥ ባለሀብት በተቆጠረ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ባልሆነ የውጭ አገር ዜጋ የሚካሄድ ኢንቨስትመንት፤ እና

   መ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚሰጥበት የኢንቨስትመንት መስክ አግባብ ካለው የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣት ባለበት የአገር ውስጥ ባለሀብት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ወይም ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት አገልግሎት፣ እና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሥራዎች ላይ ለሚሰማራ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማሻሻል፣ የመለወጥ፣ የመተካት፣ የመሰረዝ እና የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ፈቃድ የመስጠት ሥራን እንደ ቀደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ኮሚሽኑን በመወከል ያከናውናሉ።

3. የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን፡-

   ሀ) በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት የሰጧቸውን አገልግሎቶች የሚመለከት ሪፖርት በየሦስት ወር ለኮሚሽኑ ያቀርባሉ፤

   ለ) የየዘርፎቹን እምቅ አቅም ለመለየት የሚያስፈልጉ ጥናቶችን የማካሄድ፣ ዘርፍ-ተኮር የኢንቨስትመንት ልማት ስትራቴጂዎችን የመቅረጽ እና

የኢንቨስትመንት እድሎችን የማስተዋወቅ ሥራዎችን ከኮሚሽኑ ጋር በመቀናጀት ያከናውናሉ።

4. የክልሎች አግባብ ያላቸው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) እና (2) ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉ ኢንቨስትመንቶችን የማስተዳደር ሥልጣን ይኖራቸዋል።

## ክፍል ሁለት

## የኢንቨስትመንት ዓላማዎች

5. **የኢንቨስትመንት ዓላማዎች**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንቨስትመንት ዓላማ ፈጣን፣ አካታች እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት እንዲኖር በማድረግ የኢትዮጵያን ህዝቦች የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ይጨምራል፦

1. በልዩ የአምራች እና አስቻይ የልማት ዘርፎች ኢንቨስትመንትን በማሳደግ ብሔራዊ የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትን ማጠናከር፤
2. ለኢትዮጵያውያን ሰፊ እና ጥራት ያለው የሥራ ዕድል መፍጠር እና ለአገሪቱ ዕድገት የሚያስፈልገውን የዕውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ማሳለጥ፤
3. ውጭ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በመጠን፣ በዓይነት እና በጥራት እንዲጨምሩ በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፤
4. ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን ማዳን፤
5. በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት የግል ሴክተሩን ሚና ማሳደግ፤
6. የአገሪቱን የተፈጥሮ፣ የባህል እና ሌሎች ሀብቶች ጥቅም ላይ ማዋል እና ማልማት፤
7. በተለያዩ ዘርፎች እንዲሁም በውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር የተቀናጀ ኢኮኖሚ መፍጠር፤
8. የማህበራዊ እና የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን የሚከተሉ እና አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያላቸው ኢንቨስትመንቶችን ማበረታታት።

## ክፍል ሦስት

## የኢንቨስትመንት መስኮች፣ የድርጅት ዓይነቶች እና የካፒታል መጠን

### 6. የኢንቨስትመንት መስኮች

1. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለሀብት ለሕግ፣ ለሞራል፣ ለማህበረሰብ ጤና ወይም ደህንነት ተጻራሪ ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የኢንቨስትመንት መስክ መሰማራት ይችላል።
2. ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ፣ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ፣ እና ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ዝርዝር በደንብ ይወሰናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) መሠረት ከሚከለሉ በስተቀር ሁሉም የኢንቨስትመንት መስኮች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ይሆናሉ።
4. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት የሚወሰኑ የኢንቨስትመንት መስኮችን ዝርዝር ሊያሻሽል ይችላል።

### 7. ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት

እንደ አግባብነቱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታ እና አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም በመንግሥት እና የግል ዘርፍ አጋርነት የሚቋቋሙ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ተቋም፤ ማንኛውም የግል ባለሀብት ከመንግሥት ጋር በቅንጅት በኢንቨስትመንት መስክ ለመሰማራት የሚያቀርበውን የፕሮጀክት ሀሳብ ይቀበላል፣ ተገቢነት ባለው ሕግ የተመለከቱ የአፈጻጸም ሂደቶችን በመከተልም አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በቅንጅት ተሳታፊ የሚሆነው የልማት ድርጅት እንዲሰየም ወይም የፕሮጀክት ኩባንያ እንዲቋቋም ያደርጋል።

### 8. ኢንቨስትመንት የሚካሄድባቸው ድርጅቶች ዓይነት

1. ኢንቨስትመንት ከሚከተሉት ድርጅቶች በአንደኛው ሊካሄድ ይችላል፡-

    ሀ) በግለሰብ፤

    ለ) ኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ውጭ አገር በተቋቋመ ድርጅት፤

    ሐ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተቋቋመ የመንግሥት የልማት ድርጅት፤

    መ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተቋቋመ የህብረት ሥራ ማህበር።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ በተመለከቱት የድርጅት ዓይነቶች የሚካሄድ ማንኛውም ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ መሠረት መመዝገብ አለበት።
3. ማንኛውም ውጭ አገር ተቋቁሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገበ ድርጅት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እና ድርጅቶችን በሚመለከቱ ሌሎች ሕጎች ይገዛል።

9. <u>ከውጭ ባለሀብት የሚጠየቅ ዝቅተኛ የካፒታል መጠን</u>

1. ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በዚህ አዋጅ መሠረት በኢንቨስትመንት መስክ ለመሰማራት ለአንድ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ከ 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ያላነሰ ካፒታል መመደብ አለበት።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት በኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማራ የውጭ ባለሀብት የሚጠየቀው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን 150,000(አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ይሆናል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በአርክቴክቸር ወይም በኢንጂነሪንግ ሥራዎች ወይም በተዛማጅ የቴክኒክ ማማከር አገልግሎት፣ በቴክኒክ ምርመራ እና ትንተና ወይም በአሳታሚነት ሥራ የሚሰማራ የውጭ ባለሀብት የሚጠየቀው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን፦

   ሀ) በተናጠል ሲሆን 100,000 (አንድ መቶ ሺ) አሜሪካን ዶላር፣

   ለ) ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ሲሆን 50ሺ (ሀምሳ ሺ) አሜሪካን ዶላር ይሆናል።
4. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ዝቅተኛ የመነሻ ካፒታል የመመደብ ግዴታ በሚከተሉት ባለሀብቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

   ሀ) ከነባር ኢንቨስትመንቱ የሚያገኘውን ትርፍ ወይም የትርፍ ድርሻ በማንኛውም ለውጭ ባለሀብት በተፈቀደ መስክ መልሶ ሥራ ላይ የሚያውል የውጭ ባለሀብት፤

   ለ) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወደ አክስዮን ማኅበር ሲለወጥ ለአክስዮን ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚመረጡ ግለሰቦች፤ እና

   ሐ) የውጭ ባለሀብት ሙሉ ድርጅትን ወይንም በድርጅቱ ያለውን አክሲዮን በሙሉም ሆነ በከፊል የሚገዛ የውጭ ባለሀብት።

5. ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን የኢንቨስትመንት ካፒታል በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በማስመዝገብ የምስክር ወረቀት መያዝ ይኖርበታል። አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ለባለሀብቱ የሚሰጠውን የምስክር ወረቀት ቅጂ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይልካል።

## ክፍል አራት

## የኢንቨስትመንት ፈቃድ

### 10.የኢንቨስትመንት ፈቃድ አስፈላጊነት እና አሰጣጥ

1. የሚከተሉት ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል፦

   ሀ) የውጭ ባለሀብቶች፣

   ለ)በቅንጅት በኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች፣

   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ-አንቀጽ (5) ፊደል ተራ (ረ)፣ (ሰ)፣ (ሸ) እና (ቀ) የተመለከቱ እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት በመቆጠር በኢንቨስትመንት የሚሰማሩ ባለሀብቶች፣

   መ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚሰጥበት የኢንቨስትመንት መስክ የሚሰማሩ እና የማበረታቻው ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ እና

   ሰ) የማስፋፊያ ወይም የማሻሻያ ኢንቨስትመንት ማካሄድ የሚፈልግ ባለሀብት ሆኖ ኢንቨስትመንቱ ማበረታቻ በሚሰጥበት መስክ ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ እና ባለሀብቱ በማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ከመረጠ።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሐ) ድንጋጌ ቢኖርም እንደ የአገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ዜጋ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በማይሰጠው፣ ወይም ማበረታቻ የሚሰጠው ቢሆንም ማበረታቻ የማግኘት መብቱን በመተው ያለኢንቨስትመንት ፈቃድ ኢንቨስትመንት ላይ ሊሰማራ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ ነባር ድርጅት ገዝቶ ባለበት ሁኔታ ለማካሄድ ወይም የነባር ድርጅትን አክስዮን ለመግዛት የሚፈልግ የውጭ ባለሀብት ጥያቄውን ለኮሚሽኑ በማቅረብ በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል። ኮሚሽኑ የተጠየቀውን ፈቃድ ያለበቂ ምክያት ሊከለክል ወይም ሊያዘገይ አይችልም።

4. ማንኛውም ባለሀብት በማናቸውም ጊዜ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን በአንድ ላይ ሊይዝ አይችልም።

11. <u>የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት</u>

1. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ባለሀብቱ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለገበያ ማቅረብ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ በየአመቱ መታደስ አለበት። የንግድ ሥራ ፈቃድ ከወጣ በኋላ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መታደስ አይኖርበትም፡፡
2. የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ አመት ጊዜ ባለቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።
3. ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ትግበራ ሳይጀምር ሁለት ዓመት ካለፈው ወይም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ትግበራውን ለማጠናቀቅ አግባብ ካለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ጋር ከሚስማማበት ጊዜ በሁለት ዓመት ከዘገየ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ ይሰረዛል።
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) ድንጋጌ ቢኖርም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ባለሀብቱ የፕሮጀክት ትግበራውን ሊጀምር ወይም ሊያጠናቅቅ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካመነበት ፈቃዱ ይታደሳል።

12. <u>በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ማስተላለፍ</u>

የንግድ ሥራ ፈቃድ ከማውጣቱ በፊት በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ለሌላ ባለሀብት ማስተላለፍ የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት ጥያቄውን አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል። አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የተጠየቀውን ፈቃድ ያለበቂ ምክንያት ሊከለክል ወይም ሊያዘገይ አይችልም። ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም የሚስፈልጉ ዝርዝር ሁኔታዎች ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

13. <u>የኢንቨስትመንት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት፦

   ሀ) አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠይቀውን መረጃ ወይም የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት በትክክል እና በወቅቱ ካላቀረበ፣ ወይም ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የተሳሳተ ሪፖርት ካቀረበ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ወይም የፈቃድ እድሳትን ያገኘው በማታለል ወይም የሐሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፤

ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ከተሰጠበት ዓላማ ውጭ ከተገለገለበት፤

መ) ያለበቂ ምክንያት በአዋጁ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ላይ በተመለከተው መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ካላሳደሰ፤

ሠ) የፕሮጀክት ትግበራ ጀምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ (3) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ካላጠናቀቀ እና ፕሮጀክቱን ሊያጠናቅቅ እንደማይችልም ከታመነ፤ ወይም

ረ) ይህን አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ድንጋጌዎችን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ከተላለፈ፤ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ ይታገዳል።

2. የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የታገደበት ባለሀብት ለዕገዳው ምክንያት የሆነውን ጉዳይ እንዲያስተካክል የአንድ ዓመት ጊዜ ይሰጠዋል።

3. ማንኛውም ባለሀብት፡-

ሀ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ (3) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የኢንቨስትመንት ትግበራ ካልጀመረ፤

ለ) ለኢንቨስትመንት ፈቃዱ እገዳ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካላስተካከለ፤

ሐ) የኢንቨስትመንት ሥራውን በፈቃዱ ከተወ፤ ወይም

መ) ተፈጻሚነት ባለው ሕግ መሠረት የተሰጡትን ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው ዓላማ ውጭ ካዋለ ወይም ከሕግ ውጭ ለሌላ ሰው ካስተላለፈ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ ይሰረዛል።

4. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወስደውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመሰረዝ እርምጃ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ያሳውቃል። የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘበት ባለሀብት ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ሲያገኝ የነበረው ጥቅም ወዲያውኑ ይቋረጥበታል።

5. ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሀብት የወሰዳቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች በሙሉ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና አግባብነት ላላቸው ሌሎች አካላት ይመልሳል።
6. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ፈቃዱን ከሰጠው አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ውጭ በሌላ ማንኛውም አካል ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ አይችልም።
7. የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰረዘበት የውጭ ባለሀብት ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጨምሮ ከሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ በፊት አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት አይችልም።
8. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወሰኑ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀሩም።

14.<u>ሪፖርት የማድረግ እና የመተባበር ግዴታ</u>

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም ባለሀብት፦

1. ስለኢንቨስትመንቱ አፈጻጸም ሂደት በየሦስት ወሩ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፤
2. አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ሲጠየቅ ስለሚያካሂደው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት።

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት እና ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር የሚደረጉ የትብብር ስምምነቶች ምዝገባ</u>

15.<u>የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ የሚዋዋለውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በኮሚሽኑ ማስመዝገብ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት ያልተመዘገበ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በኮሚሽኑ ዘንድ ሕጋዊ እውቅና አይኖረውም።
3. ኮሚሽኑ የመዘገበውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ለሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት አስፈጻሚ አካላት እና በግልባጭ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል።

16.**ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳያደርግ የሚያደርገው የትብብር ስምምነት**

1. ማንኛውም የአገር ውስጥ ባለሀብት ከወጪ ንግድ ጋር በተያያዘ የካፒታል መዋጮ ከማያደርግ የውጭ ድርጅት ጋር የሚፈጽመውን የትብብር ስምምነት በኮሚሽኑ ማስመዝገብ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት ያልተመዘገበ የትብብር ስምምነት በኮሚሽኑ ዘንድ ሕጋዊ እውቅና አይኖረውም።
3. ኮሚሽኑ የመዘገበውን የትብብር ስምምነት ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት እና በግልባጭ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል።

**ክፍል ስድስት**

**የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣ ዋስትና እና ጥበቃ፣ እና ማሳለጥ**

17.**የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች**

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለማግኘት ብቁ የሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሁም የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ዓይነት እና መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናሉ።

18.**የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን**

1. በፍትሐብሔር ሕግ ከአንቀጽ 390 እስከ አንቀጽ 393 የተደነገገው ቢኖርም የውጭ ባለሀብት ወይም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ ዜጋ ለኢንቨስትመንት ሥራው የሚያስፈልግ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን ይችላል። ለዚህ ድንጋጌ ዓላማ “የማይንቀሳቀስ ንብረት” መሬትን አይጨምርም።
2. በፍትሐብሔር ሕግ ከአንቀጽ 390 እስከ አንቀጽ 393 የተደነገገው ቢኖርም ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት ባለቤት የሆነ የውጭ ባለሀብት ወይም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ ዜጋ የአንድ መኖሪያ ቤት ባለቤት እንዲሆን ሊፈቀድለት ይችላል። ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ሁኔታዎች በደንብ ይወሰናሉ።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው መብት ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶችንም ይጨምራል።

19.<u>የኢንቨስትመንት ዋስትና እና ጥበቃ</u>

1. መንግሥት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ማንኛውንም ኢንቨስትመንት ለሕዝብ ጥቅም፣ በሕግ አግባብ፣ እና ያለመድልዎ ሊወስድ ይችላል።
2. ማንኛውም ኢንቨስትመንት በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት የሚወሰድ ከሆነ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ መከፈል አለበት።

20.<u>ገንዘብ ወደ ውጭ አገር ማዛወር</u>

1. ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ከሚያካሂደው ኢንቨስትመንት የሚያገኛቸውን የሚከተሉትን ክፍያዎች እና ገቢዎች በወቅቱ ተመን አግባብነት ያለው የአገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት መሠረት በውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ ውጭ ማዛወር ይችላል፦
   ሀ) ከኢንቨስትመንቱ ያገኘውን ትርፍ እና የትርፍ ድርሻ፤
   ለ) ከውጭ አገር ላገኘው ብድር ዋና ገንዘብ እና ወለድ ክፍያ፤
   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 መሠረት ካስመዘገበው የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ጋር የተያያዘ ክፍያ፤
   መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት ካስመዘገበው የትብብር ስምምነት ጋር የተያያዘ ክፍያ፤
   ሠ) ለሌላ ባለሀብት አክሲዮን በማስተላለፍ ወይም ድርጅቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማንኛውም ሌላ ባለሀብት በማዛወር ያገኘው ገንዘብ፤
   ረ) ድርጅት ሲሸጥ፣ ካፒታል ሲቀንስ ወይም ፈርሶ ሂሳቡ ሲጣራ የሚገኝ ገቢ፤ እና
   ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ-አንቀጽ (2) መሠረት የሚፈጸም የካሣ ክፍያ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም በቅንጅት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት ተሳታፊ የሆነ የአገር ውስጥ ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ የሚያገኘውን ገንዘብ ወደ ውጭ ማዛወር አይፈቀድለትም።
3. በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ቋሚ ነዋሪነታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆነ የውጭ አገር ዜጎች የሚያገኙትን ደመወዝ አግባብነት ያለው የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በወቅቱ ተመን በውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ አገር መላክ ይችላሉ።

21.<u>የውጭ ብድር እና የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልገውን ብድር ከውጭ አገር አበዳሪዎች ተፈጻሚነት ባለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ሊወስድ ይችላል።
2. ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ለኢንቨስትመንቱ ዓላማ የሚውል የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ተፈጻሚነት ባለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ባንኮች ከፍቶ ማንቀሳቀስ ይችላል።

22.<u>የውጭ ዜጎች ቅጥር እና የሥራ ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ እና ተገቢ ሙያ ያላቸውን በከፍተኛ ማኔጅመንት፣ በተቆጣጣሪነት፣ በአሰልጣኝነት እና በሌሎች የቴክኒክ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ የውጭ አገር ዜጎችን መቅጠር ይችላል። ሆኖም የውጭ ዜጎችን መቅጠር የሚችለው ዘርፉ በሚፈልገው ደረጃ ተመሳሳይ ሙያ ወይም ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ ነው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፤ ማንኛውም ባለሀብት ዋና ሥራ አስፈጻሚን፣ ዋና የኦፕሬሽን ኃላፊን እና ዋና የፋይናንስ ኃላፊን ጨምሮ ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልጉ የውጭ ዜግነት ያላቸው ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላትን እንደ አስፈላጊነቱ መቅጠር ይችላል። የከፍተኛ ማኔጅመንት አባላት የሥራ ፈቃድ ሌሎች የውጭ ዜግነት ያላቸው ሠራተኞችን የሚመለከቱ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላት ሳያስፈልግ ይታደሳል።
3. የማንኛውም ባለሀብት ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት ተቀጥሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሰራ የውጭ ዜጋ የትዳር አጋር የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት የውጭ ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት ለኢትዮጵያውያን አስፈላጊው ስልጠና እንዲዘጋጅ እና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ ሠራተኞችን እንዲተኩ የማድረግ ግዴታ አለበት።
5. ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው በአንድ የሥራ መደብ ለማገልገል እስከ ሦስት አመት ሲሆን እንደ አግባብነቱ ባለሀብቱ በቅድሚያ ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሌሉ መሆኑን ማረጋገጡን፣ እንዲሁም ተተኪ ኢትዮጵያውያንን በማሰልጠን ረገድ የወሰደውን ተጨባጭ እርምጃ መሠረት በማድረግ በየአመቱ ይታደሳል።

6. የውጭ አገር ዜጋ ለተቀጠረበት ሥራ አስፈላጊ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ኮሚሽኑ የሥራ ፈቃዱ እንዳይታደስ ወይም እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል።
7. ኮሚሽኑ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚመለከት የአሠራር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ተፈጻሚም ያደርጋል፦

   ሀ) የውጭ አገር ዜጋ ለሚቀጠርበት የሥራ መደብ የሚኖረውን አስፈላጊነት እና ሙያዊ ተገቢነት፤

   ለ) የፈቃድ ዕድሳት ለማከናወን እንዲሟላ የሚጠበቀው የኢትዮጵያውያን ተተኪዎች ስልጠና አፈጻጸም፤

   ሐ) በአገር ውስጥ ገበያ ተፈላጊ ችሎታ ያለው ተተኪ የሰው ሀይል መኖር አለመኖሩ የሚረጋገጥበት አግባብ፤ እና

   መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (7) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ወይም በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት፣ ዕድሳት የሚከለከልበት ወይም ፈቃዱ የሚሰረዝበት ሥርዓት፡፡
8. ኮሚሽኑ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ባለሀብቶች ለተተኪ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የስልጠና መርሐግብር በማዘጋጀት የዕውቀት እና የክህሎት ሽግግር እንዲኖር የማድረግ ግዴታቸውን ለመከታተል የሚያስችል የክትትል መመሪያ በማዘጋጀት ይተገብራል።

23. <u>የቪዛ አገልግሎት</u>

1. ኮሚሽኑ ወይም የውክልና ሥልጣን የተሰጠው የኢንቨስትመንት አካል ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ የውጭ አገር ዜጎች እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ቤተሰቦች (የትዳር አጋር፣ ልጆች እና ወላጆች) ተገቢ ቪዛ እንዲያገኙ ሊያመቻች ይችላል።
2. ለኢንቨስትመንት ጉዳዮች ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ከትውልድ ወይም መኖሪያ አገሩ ውጭ የቪዛ ጥያቄ ለሚያቀርብ የውጭ አገር ዜጋ ከኮሚሽኑ ሊሰጥ በሚችል የድጋፍ ደብዳቤ መሠረት ባለበት ሦስተኛ አገር ውስጥ ቪዛ ሊሰጠው ይችላል።

3. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት ባለቤት ወይም ባለድርሻ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት የአምስት ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ሊሰጠው ይችላል።
4. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከናወን ኢንቨስትመንት የሚያካሂድ ድርጅት ውስጥ የሚሰራ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የቦርድ አባል እና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ፣ እንዲሁም የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ሆልዲንግ ኩባንያ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት የሦስት ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ሊሰጠው ይችላል።
5. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት በብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ማናቸውም የውጭ አገር ዜጋ በአንድ ጊዜ የሚኖረው ከፍተኛ የቆይታ ጊዜ ከዘጠና (90) ቀናት ሊበልጥ አይችልም።
6. ለዚህ አንቀጽ ተገቢ አፈጻጸም ኮሚሽኑ ከኢሚግሬሽን፣ ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ እና ሌላ አግባብነት ካለው የመንግሥት አካል ጋር በመተባበር ይሰራል።

24.<u>የአንድ ማዕከል አገልግሎት</u>

1. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጣቸው ባለሀብቶች የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣል፣ አግባብነት ያላቸው ሌሎች አካላትን ያስተባብራል፣ የየዕለት ተግባራቸውን ያቀናጃል።
2. የክልል የኢንቨስትመንት አካላት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጧቸው ባለሀብቶች አግባብነት ባላቸው የፌደራል እና የክልል ሕጎች መሠረት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>የአቤቱታ ሥርዓት እና የኢንቨስትመንት አለመግባባት አፈታት</u>

25.<u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር የተያያዘ ቅሬታ ካለው አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።
2. ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በተሰጠ የመጨረሻ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ በባለሀብት የሚቀርብ አቤቱታ ቀልጣፋ፣ ሚዛናዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይፈታል።

3. በዚህ የአዋጁ ክፍል የተደነገገው የአቤቱታ ሥርዓት በኢንቨስትመንት ላይ ለመሰማራት የቀረበ ጥያቄ ላይ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን በመቃወም ለሚቀርብ አቤቱታም ተፈጻሚ ይሆናል።

26.<u>የኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት በኮሚሽኑ የሚተላለፍ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔን በመቃወም ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።
2. የኮሚሽኑ ውሳኔ የጽሑፍ ቅጂ ውሳኔው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በሰባት (7) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።
3. በኮሚሽኑ በተሰጠ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ባለሀብቱ ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።
4. ቦርዱ በቀረበለት አቤቱታ ላይ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በዘጠና (90) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
5. የቦርዱ ውሳኔ ጽሑፍ ቅጂ ውሳኔው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በሰባት (7) የሥራ ቀናት ውስጥ በቦርዱ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።

27.<u>በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚሰጥ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል የተላለፈን በኢንቨስትመንቱ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያደርስ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔን የተመለከተ አቤቱታ ለኮሚሽኑ የማቅረብ መብት አለው።
2. የማናቸውም የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የጽሑፍ ቅጂ በሰባት (7) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።
3. በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል በተሰጠ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ባለሀብቱ ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።
4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ አቤቱታ መፍትሔ እንዲያገኝ አቤቱታ ከቀረበበት የመንግሥት አካል ጋር በመነጋገር አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ የመፍትሔ ሀሳብ በጽሑፍ ያቀርባል።

5. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) መሠረት ያቀረበው የመፍትሔ ሀሳብ የጽሑፍ ቅጂ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሰባት (7) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።
6. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) መሠረት ያቀረበውን የመፍትሔ ሀሳብ በመቃወም፣ ወይም የተሰጠው የመፍትሔ ሀሳብ አቤቱታ በቀረበበት የመንግሥት አካል ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ ባለሀብቱ ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (6) መሠረት ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ በኮሚሽኑ የቀረበው የመፍትሔ ሀሳብ ለባለሀብቱ በተገለጸ ወይም የመፍትሔ ሀሳቡ አቤቱታ በቀረበበት የመንግሥት አካል ተቀባይነት አለማግኘቱን ባለሀብቱ ባወቀ በሰላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።
8. ቦርዱ በቀረበለት አቤቱታ ላይ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በዘጠና (90) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
9. የቦርዱ ውሳኔ የሚመለከተው ማንኛውም የፌደራል መንግሥት አካል ውሳኔውን የማክበር እና በውሳኔው መሠረት የመፈጸም ግዴታ አለበት።

28.<u>የኢንቨስትመንት አለመግባባት አፈታት</u>

1. በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ፍትሕ የማግኘት መብትን ሳይቃረን፤ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ በባለሀብት እና በመንግሥት መካከል የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባት በውይይት ወይም በድርድር ይፈታል።
2. የፌደራል መንግሥት የውጭ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የሚነሱ የኢንቨስትመንት አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት እንዲፈቱ ሊስማማ ይችላል።
3. የውጭ ባለሀብት የኢንቨስትመንት አለመግባባትን በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ወይም ለግልግል ዳኝነት ለማቅረብ ከመረጠ ምርጫው የመጨረሻ እና ሌላኛውን ከመጠቀም የሚያግድ ይሆናል።

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት</u>

29.<u>የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት</u>

የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

1. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ፤

2. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤
3. የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ፤ እና
4. በክልል ሕጎች የሚወሰኑ የክልል ኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት።

30.<u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

31.<u>የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር</u>

1. ቦርዱ፦
   ሀ) በዚህ አዋጅ፣ አዋጁን መሠረት አድርገው በሚወጡ ደንቦች፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አሰያየም፣ አስተዳደር እና ቁጥጥርን ለመግዛት በወጡ ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባሮች ይፈጽማል፤
   ለ) የዚህን አዋጅ አፈጻጸም እና የኮሚሽኑን ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፤
   ሐ) በኢንቨስትመንት ጉዳዮች ላይ የፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፤
   መ) እንደ አስፈላጊነቱ ይህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች እንዲሻሻሉ ሀሳብ ያቀርባል ፣
   ሠ) ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ የመመሪያዎቹን ተፈጻሚነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
   ረ) ኮሚሽኑ ወይም ሌሎች የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት በሚሰጡት የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኙ ባለሀብቶች በዚህ አዋጅ በተመለከተው የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በሚያቀርቡት አቤቱታ ላይ ይወስናል፤
   ሰ) ለባለሀብቶች የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ዓይነት እና መጠን፣ እንደዚሁም በማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች የሚለዩበትን መመዘኛ በተመለከተ አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል በጥናት ላይ የተመረኮዘ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
   ሸ) ከሚመለከታቸው የመንግሥት እና የግል ዘርፍ አካላት ጋር ተገቢውን ምክክር በማድረግ ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚካሄዱ፣ ወይም ለአገር ውስጥ ባለሀብት የተከለሉ፣ ወይም ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሀብት የቅንጅት

ኢንቨስትመንት የተከለለ የኢንቨስትመንት መስኮች ለውጭ ባለሀብት ክፍት እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ክፍት የሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከውጭ ባለሀብት ተሳትፎ እንዲከለሉ ይወስናል።

2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (8) ፊደል ተራ (ሸ) መሠረት የሚያሳልፋቸው ማናቸውም ውሳኔዎች ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ውሳኔዎቹ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በህትመት ወይም በሌላ መንገድ ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል።

32.<u>የቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ የሚከተሉት አስራ ሦስት አባላት ይኖሩታል፡-
   ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ...........................ሰብሳቢ፤
   ለ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም የመንግሥት ኃላፊ.......ምክትል ሰብሳቢ፤
   ሐ) ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከአገልግሎት፣ ከፋይናንስ፣ ከገቢዎች፣ ከግብርና፣ ከኃይል፣ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ዘርፎች አስተዳደር ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ ወይም ተዛማጅ የሥራ ኃላፊነት ያላቸው ስምንት የመንግሥት ኃላፊዎች......... አባላት፤
   መ) በግሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚሰየሙ ሁለት ተወካዮች...............አባል፤ እና
   ሠ) የኮሚሽኑ ኮሚሽነር....................አባል እና ጸሀፊ፡፡
2. አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት ለቦርዱ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
3. የግል ኢንቨስትመንት ዘርፍን በመወከል ለቦርዱ አባልነት የሚሰየሙ አባላት፡-
   ሀ) በቦርዱ ውሳኔዎች ድምጽ አይሰጡም፤
   ለ) ለሁለት አመት የሚያገለግሉ ሆኖ ለተጨማሪ ሁለት አመት ሊሰየሙ ይችላሉ፤
   ሐ) ኃላፊነታቸውም ሆነ በቦርዱ ውይይቶች የሚያደርጉት ተሳትፎ በማናቸውም መልኩ ከሚገለጽ የግል ጥቅም ግጭት ነጻ በሆነ መልኩ መወጣት ይኖርባቸዋል፤ የግል ጥቅምን የሚነካ ወይም ማናቸውም የጥቅም ግጭት የሚያስነሳ ጉዳይ ካለ ራሳቸውን ከተሳትፎ ማቀብ ይኖርባቸዋል።
4. ቦርዱ አጠቃላይ አሠራሩ የሚመራበት፣ ስብሰባዎቹ የሚካሄዱበት፣ የሚያያቸው ጉዳዮች የሚቀርቡበት እና ውሳኔዎች የሚሰጡበትን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

5. ኮሚሽኑ የቦርዱ ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል። የቦርዱ ጽህፈት ቤት የራሱን የሰው ሀይል ያደራጃል።

## 33.የቦርዱ ስብሰባዎች

1. ቦርዱ በየሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቦርዱ አባላት በማንኛውም ስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም የተሰጠ ድምጽ ዕኩል የሆነ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው የውሳኔ ሀሳብ ያልፋል።

## 34.የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴ

ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ኃላፊነታቸውን ይወስናል፣ አባላቱን እና ሰብሳቢዎቻቸውን ይሰይማል።

## 35.የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት፤ ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

## 36.ዋና መስሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ ቅርንጫፍ ወይም ተጠሪ ጽህፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

## 37.ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር፣ ኢንቨስትመንትን መሳብ እና ማቆየት፣ እና ግልጽ እና ቀልጣፋ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ነው።

## 38.የኮሚሽኑ ሥልጣን እና ተግባር

ኮሚሽኑ፡-

1. በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ መሠረት አድርገው በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደር እና ቁጥጥርን ለመግዛት በወጡ ሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

2. የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን በተመለከተ በማዕከልነት በማገልገል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ይመራል፣ ያበረታታል፣ ያስተባብራል፣ ያስፋፋል፤
3. ምቹ እና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ የሚወሰዱ የፖሊሲ እና የአፈጻጸም ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. ኢንቨስትመንት የማስተዋወቅ ሥራዎችን ይመራል፣ በኢንቨስትመንት ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉ ተፈላጊ ባለሀብቶችን ዝርዝር ያደራጃል፣ እንዲሁም የተመረጡ ባለሀብቶችን ለመሳብ የሚያስችሉ ሥራዎችን ያከናውናል፤
5. አገሪቱ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ መሆኗን የሚያሳዩ የአዲስ ገጽታ ማቋቋም እና ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፣ በየዘርፉ ተነጻጻሪ የውድድር አቅሞችን እና የንግድ ሥራ ስኬትን የሚያመላክቱ መረጃዎችን የያዙ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለይቶ ያደራጃል፣ የዘርፍ ፕሮፋይሎችን እና ሌሎች የማስተዋወቂያ ጽሑፎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ዓውደ-ርዕዮችን፣ እና ሴሚናሮችን በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ያካሂዳል፣ በተዘጋጁ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ላይ ይሳተፋል፣ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤
6. ተጨባጭ የኢንቨስትመንት እድል መግለጫዎችን በማዘጋጀት ያስተዋውቃል፣ ሲጠየቅም በቅንጅት ለሚደረግ ኢንቨስትመንት ተሳታፊዎችን የማገናኘት አገልግሎት ይሰጣል፤
7. በአገራዊ የኢንቨስትመንት እድሎችን የማስተዋወቅ እንቅስቃሴ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማስተዋወቅ አንዱ እና ወሳኙ ሥራው አድርጎ ይንቀሳቀሳል፤
8. በመንግሥት ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኖሩ ምቹ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ከማስተዋወቅ፣ ባለሀብቶችን ከመሳብ እና ከመመልመል ጋር በተያያዘ በማዕከልነት የሀብት ብክነትን የሚቀንስ ሥርዓት በማደራጀት የተቀናጀ፣ ተደራሽ እና ትክክለኛ መረጃ ለባለሀብቶች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያቀርባል፤
9. የውጭ ኢንቨስትመንቶች ሊመጡ ከሚችሉባቸው አገሮች ጋር አገሪቱ የምታደርጋቸውን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ እና ጥበቃ ስምምነቶች ተፈጻሚነት ባለው የዓለምአቀፍ ስምምነቶች መዋዋያ እና ማጽደቂያ ሕግ ሥርዓት መሠረት ይደራደራል፣ ይፈርማል፤

10.በኮሚሽኑ፣ በባለሀብቶች እና በሌሎች መንግሥታዊ አካላት መካከል ወቅታዊ እና ትክክለኛ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል የመረጃ መለዋወጫ ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፤

11.ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በባለሀብቶች፣ በመንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች፣ በክልል መስተዳድሮች እና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤

12.ማንኛቸውንም ኢንቨስትመንት-ነክ መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

13.በተሰጠው የሥልጣን ክልል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ እንዲሁም የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን ካፒታል ይመዘግባል፤

14.ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶችን ይመዘግባል፤

15.የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳያደርግ ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር የሚያደርገውን የትብብር ስምምነት ይመዘግባል፤

16.የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ደረጃ እና አፈጻጸም ይከታተላል፣ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውን፣ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን እንዲሁም ብሔራዊ የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤

17.የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣል፣ ያስተባብራል፤

18.የድህረ-ኢንቨስትመንት የድጋፍ እና ክትትል ሥራን ለዚህ ዓላማ ከተቋቋሙ አካላት ጋር በቅንጅት ያከናውናል፤

19.የክልል አግባብ ያላቸው ኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶችን ለማጠናከር የሚረዱ የምክር እና የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የጋራ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤

20.ባለሀብቶች በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ይዘት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤

21.ከባለሀብቶች እና ማህበሮቻቸው ጋር መደበኛ እና በሥርዓት የተዋቀረ የመንግሥት እና የግል ዘርፍ ምክክሮችን ያካሂዳል፣ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

22.የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድን መመሪያዎች እና ውሳኔዎች ይፈጽማል፤ በሚመለከታቸው ሌሎች አካላት መተግበራቸውንም ይከታተላል፤

23.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

24.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

25.በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ከሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድር አካላት ጋር በቅንጅት ያከናውናል።

39.<u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፦

1. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ኮሚሽነር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች፤ እና
2. ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል።

40.<u>የኮሚሽነር ሥልጣን እና ተግባር</u>

ኮሚሽነሩ፦

1. የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣን እና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
3. የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌደራል የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
4. ከተለያዩ የልማት አጋራት እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚፈጸሙ የተቋማዊ አቅም ግንባታ ትብብር ሁኔታዎችን ይወስናል፤
5. በተሰጠው ሥልጣን ማዕቀፍ ይህን አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤
6. የኮሚሽኑን የሥራ መርሐግብር እና በጀት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ መርሐግብር መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤
8. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤
9. የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያቀርባል፤

10. ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣን እና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል።

41. <u>የምክትል ኮሚሽነር ሥልጣን እና ተግባር</u>

1. ምክትል ኮሚሽነሩ፡-

ሀ) የኮሚሽኑን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፤

ለ) በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል፤

ሐ) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል፤

መ) ከኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

2. ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል።

42. <u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

43. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ-ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራሉ።

44. <u>የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ መቋቋም</u>

የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት አስተዳደርን በተመለከተ በትብብር እና በቅንጅት የሚሰሩበት ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

45. <u>የጉባዔው ሥልጣን እና ተግባር</u>

ጉባዔው፡-

1. የተቃለለ እና የተቀናጀ የኢንቨስትመንት አሠራር ለማስፈን በአገራዊ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ጉዳዮች በፌደራል መንግሥት እና በክልል መስተዳድሮች መካከል የሚኖረውን ሁሉን-አቀፍ የጎንዮሽ ግንኙነት እና ቅንጅት በበላይነት ይመራል፤
2. በኢንቨስትመንት አስተዳደር የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች በሚኖራቸው ሥልጣን እና ኃላፊነት ዙሪያ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል ወይም

የመፍትሔ ሀሳብ ይሰጣል፣ ውሳኔዎች ወይም የመፍትሔ ሀሳቦችም አግባብነት ላለው ተቋም እንዲተላለፉ በማድረግ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

3. የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮችን በሚያገናኙ የሥራ ሂደቶች የኢንቨስትመንት አገልግሎት አፈጻጸምን ለመገምገም የሚያስችል የክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፣ የኢንቨስትመንት አገልግሎት አፈጻጸም እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን መከላከያ እና ማስተካከያ ሥርዓት ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን መሠረት በማድረግ ባለሀብቶች የመሬት አቅርቦትን ጨምሮ ከክልል የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት የሚያገኙትን የቅድመ-ኢንቨስትመንት እና ድህረ-ኢንቨስትመንት አገልግሎት አሰጣጥን በማስመልከት በሚነሱ መሠረታዊ ቅሬታዎች ወይም ጉልህ አለመግባባቶች ላይ ውሳኔ ወይም የመፍትሔ ሀሳብ ይሰጣል።

46. <u>የጉባዔው አባላት</u>

ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖሩበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ.............................................ሰብሳቢ፤
2. የሁሉም ክልሎች ርዕሰ-መስተዳድሮች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች............አባል፤
3. ኮሚሽነሩ፣ የሁሉም ክልሎች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ኃላፊዎች............................................አባል፤ እና
4. እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ አባላት።

47. <u>የጉባዔው ስብሰባዎች</u>

1. ጉባዔው በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም አስቸኳይ ጉዳይ ሲኖር በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የጉባዔው አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።
3. ጉባዔው በጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውይይት በማካሄድ ውሳኔ ያሳልፋል ወይም የመፍትሔ ሀሳቦችን ያጸድቃል።
4. ማናቸውም የፌደራል መንግሥት ወይም የክልል መስተዳድር አካል የጉባዔውን ውሳኔዎች ወይም የመፍትሔ ሀሳቦች ይፈጽማል።

48.**የጉባዔው ጽህፈት ቤት**

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የጉባዔው ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።

49.**የጉባዔው ተቋማዊ አሠራር**

ጉባዔው አጠቃላይ አሠራሩ የሚመራበት፣ ስብሰባዎቹ የሚካሄዱበት፣ የሚያያቸው ጉዳዮች የሚቀርቡበት እና ውሳኔዎች ወይም የመፍትሔ ሀሳቦች የሚሰጡበትን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

50.**ከክልል የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት ጋር የሚኖር ቅንጅት**

1. ወጥ የሆነ፣ የተቀናጀ እና የተቀላጠፈ ብሔራዊ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓትን ለመመሥረት ኮሚሽኑ በክልል ሕጎች ከሚመሠረቱ የኢንቨስትመንት አስተዳደር እና ባለድርሻ አካላት ጋር በጥብቅ ትብብር ይሰራል።
2. ለዚህ ዓላማ አፈጻጸም ኮሚሽኑ ከክልሎች ጋር የሚኖረውን ሁሉን-አቀፍ የአሠራር ግንኙነት የሚመራ መመሪያ አግባብ ካላቸው የክልል የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ ያዘጋጃል።
3. ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለማስተዋወቅ፣ የአስተዳደር ሥራዎችን ለማቀናጀት እና በሂደቱም የክልሎችን ተሳትፎ ለማጠናከር፣ እንዲሁም ከኮሚሽኑ የኢንቨስመንት ፈቃድ ያገኙ ባለሀብቶች በክልል የሚያገኙትን የቅድመ እና የድህረ-ኢንቨስትመንት አገልግሎት የተሳለጠ ለማድረግ እና የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለማቃለል እንዲቻል በኮሚሽኑ ተቋማዊ መዋቅር ውስጥ ቋሚ የክልል ኢንቨስትመንት አስተዳደር ዴስኮች ይቋቋማሉ።

51.**የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦትን በተመለከተ የሚፈጸሙ አሠራሮች**

1. ክልሎች አግባብነት ባላቸው የፌደራል የመሬት አስተዳደር ሕጎች የተሰጣቸውን ሥልጣን መሠረት በማድረግ ለማምረቻ ዘርፍ፣ ለእርሻ እና ሌሎች የኢንቨስትመንት መስኮች የሚውሉ የመሬት አቅርቦት ጥያቄዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ያስተናግዳሉ፣ ለዚህ የሚሆን ግልጽ እና ተገማች ሥርዓትም ሊዘረጉ ይችላሉ።
2. ክልሎች ለኢንቨስትመንት ሥራ የሚውል መሬትን አስቀድሞ በመለየት፣ በመመደብ እና በአንድ ተጠሪ ክልላዊ አካል ሥር በማደራጀት መረጃዎቹን አግባብነት ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ያስተላልፋሉ።

3. በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚከናወን ኢንቨስትመንት የተሰጠ ፈቃድን መሠረት በማድረግ ለክልል አካል የሚቀርቡ የመሬት አቅርቦት ጥያቄዎች በተሳለጠ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ኮሚሽኑ ከክልል መስተዳድሮች እና አግባብ ካላቸው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት የማስተባበር እና የክትትል ሥራዎችን ያከናውናል።
4. የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠው ባለሀብት ለኢንቨስትመንት ሥራ የሚውል መሬት አቅርቦት ጥያቄ የቀረበለት የክልል መስተዳድር አካል ለማምረቻ ዘርፍ የሚውለውን መሬት በስልሳ (60) ቀናት ውስጥ፤ ለሌሎች ዘርፎች የሚውል መሬትን አስመልክቶ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ደግሞ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ የሚያስችል ልዩ አሠራር ክልሎች ሊዘረጉ ይችላሉ።

52.<u>የኢንቨስትመንት-ነክ መረጃዎችን ማቅረብ</u>

1. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን እና ተግባር በአግባቡ መወጣት እንዲችል አግባብነት ያላቸው የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድር አካላት ለተለያዩ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውሉ መሬቶችን፣ የመሬት አጠቃቀም ፕሮፋይል እና ሌሎች አስፈላጊ፣ የተሟሉ እና ወቅታዊ ኢንቨስትመንት-ነክ መረጃዎችን ለኮሚሽኑ ማስተላለፍ አለባቸው።
2. እያንዳንዱ አግባብ ያለው የክልል ኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ስለክልሉ የሀብት ክምችት እና የኢንቨስትመንት ዕድል የተጠናቀረ መረጃ፣ እንዲሁም ስለክልሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተዘጋጁ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለኮሚሽኑ ያስተላልፋል።

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

53.<u>የኢንዱስትሪ ፓርኮች</u>

በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የተመለከቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የኢንቨስትመንት ሕጎች ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

54. <u>ሌሎች ሕጎችን የማክበር እና ዘላቂ የማህበራዊ እና የአካባቢ ጉዳዮች ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ተግባሩን የአገሪቱን ሕጎች በማክበር ያከናውናል።

2. ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ሲያደርግ የአካባቢ ጥበቃ ደረጃዎች እና የማህበራዊ አካታችነት ዓላማዎችን ጨምሮ ለዘላቂ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ እሴቶች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ አለበት።

### 55. <u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል።
2. ቦርዱ፣ ኮሚሽኑ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን፣ እና የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ይህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጣ ደንብን ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ።

### 56. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1. የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 (እንደተሻሻለ) እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድን እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 313/2006 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 313/2006 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ለተቋቋመው ኮሚሽን ተላልፈዋል።
3. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### 57. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 የተደነገገው ቢኖርም ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈቀዱ ኢንቨስትመንቶችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 (እንደተሻሻለ) እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት የተሰጡ መብቶች እና ጥቅሞች ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

### 58. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 473/2012 ዓ.ም

## የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር1097/2011 አንቀጽ 5 እና 34 መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 473/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፤በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር" ወይም ሚኒስትር ማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስተር ነው፤
2. "ኢንስቲትዩት" ማለት የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት ነው፤
3. “ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ማለትሀገራዊ፣ቀጠናዊና ዓለምአቀፋዊ የሰላም፣ የፀጥታና ደህንነት፣ የውቅረ-መንግሥት፣ የሀገረ መንግሥት፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ህገ መንግስታዊነት፣ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሀሳባዊ፤ ህጋዊና ተቋማዊ የፖሊሲና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ያካትታል፤
4. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

3. **መቋቋም**

1. የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋዉማል፡፡
2. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **የኢንስቲትዩቱ ዓላማ**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የሀገሪቱን የሰላም የደህንነትና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት በማድረግ የምርምር ስራዎችን፣ ጥናቶችን፣ ትንተናዎችን፣ ሴሚናሮችን፣

አውደጥናቶችን፣ የውይይትና የገለፃ መድረኮችን በማከናወን አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማፈላለግ ምክረ ሀሳብ የማቅረብ፣

2. የሀገር ውስጥ፣ አካባቢያዊ፣ ቀጠናዊና ዓለምአቀፋዊ የሰላም፣ የፀጥታና የደህንነት ኩነቶች፣ ክስተቶች፣ ስጋቶችና አዝማሚያዎች ላይ የምርምርና የጥናት ተግባራትን በማከናወን የልህቀት ማዕከል ሆኖ የማገልገል፤
3. የውቅረ-መንግስት፣የሀገረ-መንግስት፣የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና ሕግ መንግስታዊነት, ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሀሳባዊ፤ ህጋዊና ተቋማዊ መሰረት ጥናቶችን ፣ትንተናዎችን፣ሴሚሜናሮችን ፣ዐውደ ጥናቶችን፣ የውይይት እና የገለፃ መድረኮችን በማከናወን አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማፈላለግ ምክረ ሃሳብ የማቅረብ፤
4. ሰላምና መረጋጋት ይበልጥ እንዲጐለብት የሚረዱ የግንዛቤና የክህሎት ማስፋፊያ ስልጠናዎችን የማካሄድ፡፡

6. **<u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ዓበይት የሆኑ ሀገራዊ፣ ክፍለ ዓለማዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የመተንተንና የምርምር
2. ሀገራዊ የሰላም፣ ደህንነትና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም አፈፃፀም ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ አማራጭ የአፈፃፀም ሥልቶች ላይ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፣ፀ፤
3. በሰላምና ደህንነት ፣ ሀገራዊ መግባባት፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የውጭ ግንኙነት ዙሪያ በጥናትና መረጃ የተደገፈ የማማከር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
4. የሰላምና ደህንነት፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የውጭ ግንኙነት በሚመለከቱ ጉዳዮች አጫጭር ሥልጠናዎችን እንዲሁም ሴሚሜናሮች፣ ዐውደ ጥናቶች፣ ሲምፖዚየሞች፣ ጉባዔዎች እና ሌሎች የዕውቀት፣ የልምድ ልውውጥና የክርክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤
5. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ዓለምአቀፍና ሀገር በቀል መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትብብር ግንኙነት ይመሰርታል፣ የጋራ መድረኮችን ያዘጋጃል፣
6. የጥናት እና የምርምር ውጤቶችን ያሳትማል፣ያሰራጫል፤

7. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
8. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. **<u>አደረጃጀት</u>**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል

1. በመንግሥት የሚሜሾም ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
2. አስፈላጊው ሠራተኞች፤ይኖሩታል፡፡

8. **<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባር</u>**

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውሳላል፣

   ለ) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞችና ተመራማሪዎች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጐች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

   ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ መርሀ ግብሮች አዘጋጅቶ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

   መ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለመንግሥት ቀርቦ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውሳላል፤

   ሠ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት የሥራ መርሀ ግብርና በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ረ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በማደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፣

   ሰ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች ያዘጋጃል፡፡
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣን እና ተግባራቱ በከፊል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

9. **<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባራት</u>**

1. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

   ሀ) የኢንስቲትዩቱን ሥልጣን እና ተግባራትአፈፃፀም በሚመለከት ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፣

ለ) በተመደቡበት የሥራ መስኮች የሚከናወኑ ተግባራትንና ፕሮጀክቶችን ሥራ ይቆጣጠራሉ፤

ሐ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ መመሪያዎችን እና ውሳኔዎችን አፈፃፀም ይከታተላሉ፣ ያስፈጽማሉ፤

መ) በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር የኢንስቲትዩቱን ሥራ ይመራል፣ያስተባብራል፡፡

10.**<u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል፡፡

11.**<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡
3. ኢንስቲትዩቱ የውስጥ ኦዲተር ይኖረዋል፡፡

12.**<u>የተሻሩና ቲፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>**

1. የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ በጥናት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 347/2007 ደንብ ተሽሯል፡፡
2. ይህን ደንብ የሚቃረኑ ሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

13.**<u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 347/2007 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ጥናት ኢንስቲትዩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡፡

14.**<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 20 ቀን 2012 ዓ.ም**

**አብይ አሕመድ(ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 270/2005[97]

## ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 39 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

   1. "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
   3. "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 269/2005 እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ነው፤[98]
   4. "ቦርድ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 269/2005 አንቀጽ 6(1) የተመለከተው የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤[99]
   5. "የካፒታል ዕቃ" ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ወይም ዕቃዎች እና አክሰሰሪዎቻቸው ሲሆኑ፤ ለእነዚሁ አገልግሎት የሚውሉ የወርክ ሾፕ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን ይጨምራል፤

---

[97] በ26/78(2012) ደ.474 አንቀፅ 20(1) እና 21 መሰረት የዚህ ደንብ የኢንቨስትመንት (የሥራ) መስኮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ ደንብ የተሻሩ ሲሆን የኢንቨስትመንት ማበረታቻን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሌላ ሕግ እስኪሻሩ ድረስ እንደጸኑ ይቆያሉ።

[98] በ20/63 (2006) ደ. 313 መሠረት ይህ ደንብ የተሻረ እና ኤጀንሲው ፈርሶ በ"የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን" የተተካ ሲሆን በደንቡ ውስጥ "ኤጀንሲ" የሚለው "ኮሚሽን" በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

[99] በ20/63 (2006) ደ. 313 ቦርዱ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

6. “የግንባታ ዕቃ” ማለት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ግንባታ የሚያገለግሉ መሠረታዊ ግብዓቶችን ያጠቃልላል፤
7. “የጉምሩክ ቀረጥ” ማለት በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጣሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችንም ይጨምራል፤
8. “የገቢ ግብር” ማለት የፌዴራሉ መንግሥት ወይም የክልል መንግሥታት ወይም የሁለቱ የጋራ ገቢ የሆነ በትርፍ ላይ የሚጣል ታክስ ነዉ፡፡
9. “ነባር ድርጅት” ማለት የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ፈቃድ ኖሮት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ድርጅት ነው።[100]

3. <u>ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች</u>
   1. የሚከተሉት የሥራ መስኮች ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው ባለሀብቶች ብቻ የሚካሄዱ ይሆናሉ፤
      ሀ) ባንክ፣ የኢንሹራንስ እና አነስተኛ የብድርና የቁጠባ ተቋም ሥራዎች፤
      ለ) ዕቃዎችን የማሸግ፣ የማስተላለፍ እና የመርከብ ውክልና አገልግሎቶች፤
      ሐ) የብሮድካስቲንግ አገልግሎት፤
      መ) የመገናኛ ብዙኀን ሥራዎች፤
      ሠ) የጥብቅና እና የሕግ ማማከር አገልግሎት፤
      ረ) አገር በቀል ባህላዊ መድኃኒቶችን ማዘጋጀት፤
      ሰ) የማስታወቂያ፣ የፕሮሞሽን እና የትርጉም ሥራዎች፤
      ሸ) እስከ 50 መንገደኞች የመጫን አቅም ባለው አውሮፕላን የሚሰጥ የአገር ውስጥ የመንገደኞች የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፡፡
   2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም አንድ የንግድ ማኅበር ኢትዮጵያዊ ዜግነት አለው የሚባለው የማኅበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት የተያዘ እንደሆነ ነው፡፡

4. <u>ለውጭ ባለሀብቶች ስለተፈቀዱ የሥራ መስኮች</u>
   1. ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 1.3.3፣ 1.4.2፣ 1.7፣ 1.11.3፣ 1.11.4፣ 5.3፣ 6.2፣ 8.2፣ 9.2፣ 9.3 እና 12 ከተመለከቱት በስተቀር በሠንጠረዡ በተመለከቱት ሌሎች የሥራ መስኮች የውጭ ባለሀብት ኢንቨስት ማድረግ ይፈቀድለታል፡፡

[100] በ20/62 (2006) ደ. 312 አንቀፅ 2(1) መሠረት አዲስ የገባ ነዉ፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጁ አንቀጽ 6(1) እና (2) እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ 3(1) ከተመለከቱት በስተቀር የዉጭ ባለሀብቶች በሠንጠረዡ ከተዘረዘሩት ውጭ በሌሎች የሥራ መስኮች እንዲሳተፉ ቦርዱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት በኢንቨስትመንት ሥራ የተሠማራ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ለሥራው የሚያስፈልገው የግል የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለቤት ሊሆን ይችላል፡፡

<u>**ክፍል ሁለት**</u>

<u>**የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች**</u>

<u>**ንዑስ ክፍል አንድ**</u>

<u>**የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ**</u>

5. <u>**ለአዲስ ድርጅት ስለሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ**</u>
   1. አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡
   2. አዲስ ድርጅት ለማቋቋም፡-
      ሀ) በጋምቤላ ሕዝቦች ክልል፤
      ለ) በቤንሻንጉል/ጉሙዝ ክልል፤
      ሐ) በአፋር ክልል (ከአዋሽ ወንዝ እስከ 15 ኪሎ ሜትር ግራና ቀኝ ካሉ አካባቢዎች በስተቀር)፤
      መ) በሱማሌ ክልል፤
      ሠ) በኦሮሚያ ክልል በጉጂና ቦረና ዞኖች፤ ወይም
      ረ) በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን፣ በሰገን (ደራሼ፣ አማሮ፣ ኮንሶና ቡርጂ) አካባቢ ሕዝቦች ዞን፣ በቤንች ማጂ ዞን፣ በሸካ ዞን፣ በዳውሮ ዞን፣ በከፋ ዞን ወይም በኮንታና በባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች፤ ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት በሠንጠረዡ በተመለከተው መሠረት የሚያገኘው የገቢ ግብር ማበረታቻ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ የ30 በመቶ የገቢ ግብር ቅናሽ ይደረግለታል፡፡

6. **<u>ለነባር ድርጅት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ስለሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ</u>**

በአዋጁ አንቀጽ 2(8) መሠረት ነባር ድርጅቱን ያስፋፋ ወይም ያሻሻለ ባለሀብት ከማስፋፊያው ወይም ከማሻሻያው በሚያገኘው ተጨማሪ ገቢ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል።

7. **<u>ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት ስለሚሰጥ ተጨማሪ የገቢ ግብር ማበረታቻ</u>** [101]

1. ማንኛውም ባለሀብት ቢያንስ 60 በመቶ የሚሆነውን ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ወይም በአገልግሎት ግብዓት የሚያቀርብ ከሆነ በሠንጠረዡ ከተፈቀደለት በተጨማሪ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ ይሆናል፡፡
2. በኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ባለሀብት ካቋቋመው የማምረቻ ፋብሪካ 80 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን ምርት ወደ ውጭ የሚልክ ከሆነ ወይም ምርቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሃብት በምርት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ከሚያገኘው ማበረታቻ በተጨማሪ ኢንቨስትመንቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ወይም በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሚገኝ የኢንዱስትሪ ቀጠና ውስጥ ከሆነ ለ2 ዓመት ወይም በሌላ አካባቢ በሚገኝ የኢንዱስትሪ ቀጠና ውስጥ ከሆነ ለ4 ዓመት የገቢ ግብር ማበረታቻ ያገኛል።
3. አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከመንግስት ጋር ስምምነት በመድረስ የተቋቋመ ወይም የሚቋቋም የግል ኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና ውስጥ የተሠማራ ወይም የሚሠማራ ባለሀብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ካሟላ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ የተመለከተውን ማበረታቻ ያገኛል፡፡

[101] የዚህ አንቀጽ ነባሩ ድንጋጌ በ20/62 (2006) ደ. 312 አንቀጽ 2(3) መሰረት ንዑስ አንቀጽ (1) ሆኖ፣ ንዑስ አንቀጾች (2) እና (3) አዲስ የገቡ ናቸዉ፡፡

8. **መረጃ ስለማቅረብ** [102]

ማንኛውም ባለሀብት በዚህ ደንብ አንቀጽ 5፣ 6 እና 7 ለተመለከቱት የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆነው አስፈላጊውን መረጃ አግባብ ላለው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

9. **ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ**

1. ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው ባለሀብቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይሆናል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ባለሀብቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን ጊዜ ለሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ያሳውቃል።

10. **በገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን ገቢን ስለማሳወቅ**

የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ባለሀብት ከገቢ ግብር ነፃ በሆነበት ዘመን የሚያገኘውን ገቢ አግባብ ላለው የገቢ ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

11. **ኪሣራን ስለማስተሳለፍ**

1. ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ በተሰጠበት ዘመን ውስጥ ኪሣራ ያጋጠመው ማንኛውም ባለሀብት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመኑ ከተጠናቀቀ በኋላ የዚሁ ዘመን ግማሽ ለሚሆን ጊዜ ኪሣራው ይተላለፍለታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ኪሳራን የማስተላለፍ ዘመን ሲሰላ ግማሽ ዓመት ያጋጠመ እንደሆነ እንደሙሉ የገቢ ግብር ዘመን ይቆጠራል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም በገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን ኪሣራ የደረሰበት ማንኛውም ባለሀብት የደረሰበትን ኪሣራ ከአምስት የገቢ ግብር ዘመን በላይ ማስተላለፍ አይችልም።

[102] ነባሩ አንቀፅ 8 በ20/62 (2006) ደ. 312 አንቀፅ 2(4) ተሰርዞ ከአንቀጽ 9 እስከ 18 ያሉት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 8 እስከ 17 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ

12.የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ስለመሆን

1. ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 7፣ 11፣ 14 እና 15 የተመለከቱን ሳይጨምር በሠንጠረዡ ከተዘረዘሩት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሠማራ ማንኛም ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል።
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም ባለሃብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የሚፈልጋቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ለሚመለከተው የኢንቨስትመንት አካል በቅድሚያ በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡
3. የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሃብት ከአገር ውስጥ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የካፒታል ወይዎ የግንባታ ዕቃዎችን ሲገዛ ዕቃዎቹን ለማምረት በግብዓትነት በዋሉት ጥሬ ዕቃዎች ወይም አካሎች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ዋጋቸው ከካፒታል ዕታዎች ጠቅላላ ዋጋ 15 በመቶ የማይበልጡ መለዋወጫዎችን ፕሮጀክቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-[103]
   ሀ) በማምረቻ ኢንዱስትሪ ወይም በግብርና የሥራ መስክ የተሠማራና ቢያንስ 200,000 የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር ካፒታል ኢንቨስት ያደረገና ቢያንስ ለ50 ኢትዮጵያውያን ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ ማንኛውም ባለሀብት ለነባር ድርጅቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች በማናቸውም ጊዜ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፤

[103] ይህ ንዑስ አንቀፅ በ20/62 (2006) ደ. 312 አንቀፅ 2(5) መሰረት አዲስ የገባ ነዉ፡፡

ለ) በሌላ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ በሚፈቀድበት የሥራ መስክ የተሠማራና ቢያንስ 200,000 የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር ካፒታል ኢንቨስት ያደረገና ቢያንስ ለ50 ኢትዮጵያውያን ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ ማንኛውም ባለሀብት የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ፈቃድ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 5 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለነባር ድርጅቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

13.<u>የተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መሆን</u>

ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡበት ሁኔታ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ዓይነትና ባህሪ መሠረት በማድረግ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወስን ይሆናል፡፡

14.<u>ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃን ስለማስተላለፍ</u>

1. ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ማናቸውም የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃ ወይም ተሽከርካሪ ተመሳሳይ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ላለው ሰዉ ሊተላለፍ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉ ቢኖርም አስቀድሞ ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥ ተከፍሎ የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃው ወይም ተሽከርካሪው የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰዉ ሊተላለፍ ይችላል፡፡
3. ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ ያስገባውን የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃ ወይም ተሽከርካሪ መልሶ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ ይችላል፡፡
4. የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ባለሀብት አግባብ ባለው የጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

15.<u>ስለተሻረና ተፈጻሚነት ስለማይኖረው ሕግ</u>

1. ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

16.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 የተደነገገው ቢኖርም ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) እና ደንቡን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች መሠረት የተፈቀዱ ማበረታቻዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል።
2. ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) እና ደንቡን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለተፈቀዱ ማበረታቻዎች ብቁ ሆኖ በመብቱ ያልተጠቀመ ባለሀብት በዚህ ደንብ መሠረት በሚፈቀዱ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ለመሆን ከመረጠ ይህንኑ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት በማስታወቅ የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ይችላል፡፡

17.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 20 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**የፍትህ ሚኒስቴር**

**ሠንጠረዥ**

**የኢንቨስመንት መስኮች እና የገቢ ግብር ማበረታቻዎች**

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | **የማምረቻ ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.1 **የምግብ ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.1.1 ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>1.1.2 ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>1.1.3 ፍራፍሬ እና/ወይም አትክልት ማቀነባበር<br>1.1.4 የምግብ ዘይት ማምረት<br>1.1.5 ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶችን ማምረት<br>1.1.6 ስታርች እና የስታርች ውጤቶችን ማምረት<br>1.1.7 ዱቄትን ማምረት ሳይጨምር ጥራጥሬ፣ የቅባት እህል ወይም ሌላ እህል ማቀነባበር<br>1.1.8 ሌሎች ምግቦችን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.9 ስኳር ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የመሆን | የመሆን |
| | 1.1.10 ቸኮሌት፣ ከረሜላ፣ብስኩት ወይም ሌሎች ጣፋጭ ምግቦችን (አይስክሬም እና ኬክን ሳይጨምር) ማምረት | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.11 ማካሮኒ፣ ፓስታ እና/ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.12 የሕጻናት ምግብና ወተት፣ ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ፣ እርሾ፣ ሆምጣጤ፣ማዮኔዝ፣ሰው ሰራሽ ማር፣አዮዲን የተጨመረበት ጨው፣ ወይም መሰል ምግቦችን ማምረት<br>1.1.13 የእንሰሳት መኖ ማቀነባበር | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.2 **የመጠጥ ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.2.1 የአልኮል መጠጥ ማምረት | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.2.2 የወይን ጠጅ ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.2.3 ቢራ እና/ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.2.4 ለስላሳ መጠጥ፣ የማዕድን ወይም | ለ1 ዓመት ከገቢ | ለ2 ዓመት ከገቢ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የታሸጉ ሌሎች ውኃዎችን ማምረት | ግብር ነፃ የመሆን | ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3 **የጨርቃጨርቅና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.3.1 የጥጥ፣ የሱፍ፣ የሐር እና የመሳሰሉ የጨርቃጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀትና መፍተል | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3.2 ጨርቃጨርቅ መሸመን፣ ማጠናቀቅና ማተም | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3.3 ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትና ሌሎች የጨርቃጨርቅ ውጤቶችን በማንጣት፣ በማቅለም፣ በማኮማተር፣ በማፍካት፣ በማጠንከር፣ ወርድንና ቁመትን በመጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3.4 ሌሎች የጨርቃጨርቅ ማጠናቀቅ ሥራዎች | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3.5 ሹራብ ወይም ፎጣ ማምረት<br>1.3.6 ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃጨርቆችን ማምረት<br>1.3.7 ምንጣፍ ማምረት | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 1.3.8 የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳትን ጨምሮ) ማምረት<br>1.3.9 የጨርቃጨርቅ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.4 **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.4.1 ባለቀለት ደረጃ ቆዳና ሌጦ ማልፋት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.4.2 ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 1.4.3 የቆዳ ውጤቶችን (ሻንጣ፣ቦርሳ፣የቆዳ ኳስ እና የመሳሰሉትን) ማምረት<br>1.4.4 የቆዳ ጫማ ማምረት<br>1.4.5 የቆዳ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.5 **የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ**<br>የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት መሰንጠቅን፣ጣውላ ማምረትን እና ቀድመው የተዘጋጁ የእንጨት ውጤቶችን መገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆ | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.6 **የወረቀት እና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 1.6.1 ፐልፕ ማምረት<br>1.6.2 ወረቀት ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.6.3 የወረቀት ማሸጊያዎችን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.6.4 ሌሎች የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.7 የማተሚያ ኢንዱስትሪ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 1.8 **የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.8.1 መሠረታዊ ኬሚካሎችን (ኢታኖልን ጨምሮ) ማምረት<br>1.8.2 ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሮጅን ውህዶችን ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.8.3 የፕላስቲክ እና/ወይም የሰው ሠራሽ ጎማ ጥሬ ዕቃዎችን ማምረት<br>1.8.4 ፀረ-ተባይ፣ ፀረ-አረም ወይም ፀረ-ሻጋታ ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 1.8.5 የግድግዳ ቀለም፣ ቫርኒሽ ወይም መሰል መለሰኛዎችን፤ የማተሚያ፣ የመጻፊያ ወይም የሥዕል ቀለም ወይም ማጣበቂያ ማምረት<br>1.8.6 ሳሙናና ዲተርጀንት፣ ማፅጃና መወልወያ፣ ሽቶ እና መሰል መዋቢያዎችን ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.8.7 ሰው ሠራሽ ጭረቶችን ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.8.8 ሌሎች የኬሚካል ውጤቶችን (ባሩድ፣ ፈንጂ፣ የፎቶግራፍ ፊልም እና የመሳሰሉትን) ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.9 **የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ዝግጅት ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.9.1 ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረትና ማዘጋጀት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.9.2 መድኃኒት ማምረት ወይም ማዘጋጀት | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.10 **የጎማና የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.10.1 የጎማ ውጤቶችን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.10.2 ለሕንጻ ግንባታ፣ ለተሽከሪካሪ | ለ4 ዓመት ከገቢ | ለ5 ዓመት ከገቢ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ወይም ለሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶች ግብዓት የሚሆኑ፣ ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ ማስተላለፊያነት እንዲሁም ለፍሳሽ ማስወገጃ የሚያገለግሉ የፕላስቲክ ቧንቧዎችን ወይም ቱቦዎችን እና መገጣጠሚያዎችን ማምረት | ግብር ነፃ የመሆን | ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.10.3 ፌስታልን ሳይጨምር ሌሎች የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11 **ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.11.1 መስተዋት እና/ ወይም የመስታወት ውጤቶችን ማምረት<br>1.11.2 የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11.3 ሲሚንቶ ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11.4 የሸክላና የሲሚንቶ ውጤቶችን ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 1.11.5 ዕብነ በረድ እና የኖራ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርፅ ማውጣት እና ማጠናቀቅ (ከካባ ድንጋዮቹን ማውጣት ሳይጨምር) | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11.6 ኖራ፣ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ | የገቢ ግብር | ለ2 ዓመት ከገቢ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መለሰኛዎችን ማምረት | ማበረታቻ አያገኝም | ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11.7 የወፍጮ ድንጋይ፣ የብርጭቆ ወረቀት ወይም የድምጽ መገደብያ ወይም የሙቀት መከላከያ ምርቶችን ማምረት | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆ |
| | 1.12 **የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ (ማዕድኑን ማውጣትን ሳይጨምር)** | | |
| | 1.12.1 መሠረታዊ ብረትና የአረብ ብረት ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.12.2 መሠረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.12.3 ከብረት እና ከአረብ ብረት ፈሳሽ የተለያዩ ቅርፆችን ማውጣት | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.13 **የማምረቻ መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን ማምረትን የማይጨምር የብረታብረት ዕቃዎች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.13.1 የማዋቀሪያ ብረት ውጤቶችን፣ የብረት በርሜሎችን፣ ገንዳዎችን እና ኮንቴይነሮችን ወይም የእንፋሎት ማመንጫዎችን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.13.2 የቤት ክዳን ቆርቆሮንና ምስማርን ሳይጨምር ሌሎች የብረታ ብረት | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ውጤቶችን (የእጅ መሣሪያ፣ ቁሳቁስ እና የመሳሰሉትን) ማምረት | የመሆን | የመሆን |
| | 1.14 **የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.14.1 የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.14.2 ኮምፒዩተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.14.3 የመገናኛ መሣሪያዎችን ማምረት | | |
| | 1.14.4 የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስ (ቴሌቪዥን፣ዲ.ቪ.ዲ፣ ሬድዮ እና የመሳሰሉ) ዕቃዎችን ማምረት | | |
| | 1.14.5 የመለኪያ፣ የመፈተሻ፣ የመቃኛ፣ የመቆጣጠሪያ ዕቃዎችን ወይም ሰዓት ማምረት | | |
| | 1.14.6 የሕክምና መሣሪያዎችን (ኢራዲዬሽን፣ ኤሌክትሮ-ሜዲካል ወይም ኤሌክትሮ-ቴራፔቲክ) ማምረት | | |
| | 1.14.7 የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ዕቃዎችን ማምረት<br>1.14.8 መግነጢሳዊ እና የዕይታ ሚዲያዎችን ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.15 **የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ** | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 1.15.1 የኤሌክትሪክ ሞተር፣ ጀነሬተር፣ ትራንስፎርመር ወይም የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ወይም መቆጣጠሪያ ዕቃዎችን ማምረት | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.15.2 የኤሌክትሪክ ኃይል ማከማቻ ወይም ባትሪ ማምረት<br>1.15.3 የኤሌክትሪክ ኃይል ሽቦዎችን ወይም ገመዶችን (የፋይበር ኦፕቲክስን ጨምሮ) እና ተያያዥ ዕቃዎችን ማምረት<br>1.15.4 የኤሌክትሪክ ብርሃን መስጫ ዕቃዎችን ማምረት<br>1.15.5 የቤት ውስጥ መገልገያ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት፣<br>1.15.6 ሌሎች የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.16 **የማምረቻ/አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.16.1 ሁለገብ መሣሪያዎችን (ሞተር፣ ዕቃ ማንሻ፣ ፓምፕ እና የመሳሰሉትን) ማምረት<br>1.16.2 ለተለዩ ዓላማዎች (ለግብርና ሥራ፣ ለምግብ ማቀነባበሪያ፣ ለመጠጥ፣ ለጨርቃ ጨርቅና ማዕድን ለማምረት የሚሆኑና ለመሳሰሉት ሥራዎች) የሚውሉ መሣሪያዎችን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ማምረት | | |
| | 1.17 **የመኪና፣ የተጎታች እና ከፊል ተጎታች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.17.1 መኪና ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.17.2 የመኪና አካላትን፣ ተጎታችን እና/ወይም ከፊል ተጎታችን ማምረት፣<br>1.17.3 የመኪና መለዋወጫዎችን እና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.17.4 የባቡር ሞተሮችን እና ጋሪዎችን ማምረት | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.17.5 ሌሎች የትራንስፖርት ዕቃዎችን ጀልባ፣ ብስክሌት፣ ሞተር ብስክሌት እና የመሳሰሉትን ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.18 የቢሮና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን (ከሴራሚክ የሚሠሩትን ሳይጨምር) ማምረት<br>1.19 ሌሎች ዕቃዎችን (የጌጣጌጥና ተዛማጅ ዕቃዎች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ የስፖርት ዕቃዎች፣ መጫወቻዎችና አሻንጉሊቶች | ለ1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | እና የመሳሰሉትን) ማምረት | | |
| | 1.20 ከግብርና ጋር የተቀናጀ የማምረቻ ኢንዱስትሪ | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.21 የኢንዱስትሪ ልማት ቀጣና[104] (አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከመንግስት ጋር ስምምነት በመድረስ የተቋቋመን የግል ኢንዱስትሪ ቀጣናን ጨምሮ) | ለ10 ዓመት ከገቢ ግብር ነጻ የመሆን | ለ15 ዓመት ከገቢ ግብር ነጻ የመሆን |
| 2 | **ግብርና** | | |
| | 2.1 **የእርሻ ልማት** | | |
| | 2.1.1 **የዓመታዊ ሰብሎች ልማት** | | |
| | 2.1.1.1 የብርዕ፣ የአገዳ፣ የጥራጥሬ እና/ወይም የቅባት እህሎች እና ሩዝ ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.1.1.2 አትክልት እና/ወይም ዕፀ-ጣዕም ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.1.1.3 የጭረት ሰብሎችን ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.1.1.4 ሌሎች ዓመታዊ | ለ2 ዓመት ከገቢ | ለ3 ዓመት ከገቢ |

[104] በ20/62(2006) ደ. 312 አንቀጽ 2(2) መሠረት አዲስ የተጨመረ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሰብሎችን (ለእንስሳት መኖነት፣ ለመድኃኒትነት፣ ለሽቶ፣ ለቅመምነት እና ለመሳሰሉት የሚሆኑ ምርቶችን) ማምረት | ግብር ነፃ የመሆን | ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.1.1.5 የተረጋገጠ ምርጥ ዘር ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.1.2 **የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች ልማት** | | |
| | 2.1.2.1 የአበባ ልማት<br>2.1.2.2 የመካከለኛ ጊዜ ፍራፍሬዎች (ስትሮ ቤሪ፣ ብሉ ቤሪ እና የመሳሰሉት) ልማት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.1.2.3 የመካከለኛ ጊዜ የቅመማ ቅመም፣ የመዓዛ እና/ወይም የመድኃኒት ተክል (ሄል፣ ኮረሪማ፣ ቊንዶ በርበሬ እና የመሳሰሉት) ልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.1.3 **የቋሚ ተክሎች ልማት** | | |
| | 2.1.3.1 የረጅም ጊዜ ፍራፍሬዎች (ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ፓፓያ፣ወይን፣ ፓሽን ፍሩት እና | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የመሳሰሉት) ልማት<br>2.1.3.2 የአንቂ ተክሎች (ቡና፣ ሻይ እና የመሳሰሉት) ልማት | | |
| | 2.1.3.3 የሌሎች ቋሚ ተክሎች (የጎማ ዛፍ፣ጃትሮፋ፣ ፓልም፣ እና የመሳሰሉ ተክሎች) ልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.2 **የእንስሳት ሀብት ልማት** | | |
| | 2.2.1 የቤት እንስሳት እና ተዋጽኦ (ወተት፣ እንቁላል፣ የሱፍ ፀጉር እና የመሳሰሉት) ልማት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.2.2 የዱር እንስሳት እና ተዋጽኦ (ወተት፣ እንቁላል እና የመሳሰሉት) ልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.2.3 ንብ ማነብ/ማር ማምረት | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.2.4 ሐር ማምረት<br>2.2.5 በሰው ሠራሽ ኩሬ ዓሣ ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.3 የተጣመረ ግብርና (የእርሻ እና እንስሳት) ልማት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 2.4 የደን ልማት | ለ8 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ | ለ9 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የመሆን | የመሆን |
| 3 | የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት (ICT) መስኮች | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 4 | የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና ማሠራጨት | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 5 | **ሆቴልና ቱሪዝም** | | |
| | 5.1 የኮከብ ደረጃ ያለው ሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ሞቴል፣ ሎጅ እና ሬስቶራንት<br>5.2 ደረጃ 1 የማስጎብኘት አገልግሎት<br>5.3 ከደረጃ 1 በታች የሆነ የማስጎብኘት አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 6 | **የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት** | | |
| | 6.1 የደረጃ 1 ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት (የውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ለማዕድን ፍለጋ የሚደረግ ቁፋሮን ጨምሮ)<br>6.2 ከደረጃ 1 በታች የሆነ የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት (የውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ለማዕድን ፍለጋ የሚደረግ ቁፋሮን ጨምሮ) | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 7 | የሕንፃ ግንባታ (ሪል እስቴት) | የገቢ ግብር ማበረታቻ | የገቢ ግብር ማበረታቻ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አያገኝም | አያገኝም |
| 8 | **ትምህርትና ሥልጠና** | | |
| | 8.1 የራስን ሕንፃ በመገንባት የሚሰጥ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት<br>8.2 የራስን ሕንፃ በመገንባት የሚሰጥ የዋዕለ ሕጻናት፣ የአንደኛ ደረጃና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት<br>8.3 የቴክኒክና የሙያ ሥልጠና (ስፖርትን ጨምሮ) አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 9 | **የጤና አገልግሎት** | | |
| | 9.1 የራስን ሕንፃ በመገንባት የሚሰጥ የሆስፒታል አገልግሎት<br>9.2 የራስን ሕንፃ በመገንባት የሚሰጥ የምርመራ ማዕከል አገልግሎት<br>9.3 የራስን ሕንፃ በመገንባት የሚሰጥ የክሊኒክ አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 10 | **የአርኪቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች፣ የቴክኒክ ምርመራና ትንተና** | | |
| | 10.1 የአርኪቴክቸርና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች እና ተዛማጅ የቴክኒክ ማማከር አገልግሎት<br>10.2 የቴክኒክ ምርመራና ትንተና | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኙም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኙም |
| 11 | የአሳታሚነት ሥራ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 12 | ተሽከርካሪን የማይጨምር የካፒታል ዕቃዎች | የገቢ ግብር | የገቢ ግብር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ኪራይ | ማበረታቻ አያገኝም | ማበረታቻ አያገኝም |
| 13 | **<u>የገቢ ንግድ</u>**<br>ቡታ ጋዝ ወይም ቢትመን ማስመጣት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 14 | **<u>የወጪ ንግድ</u>**<br>ጥሬ ቡና፣ ጫት፣ የቅባት እህል፣ ጥራጥሬ፣ የከበሩ ማዕድናት እና ቆዳና ሌጦ ከገበያ በመግዛት፤ የተፈጥሮ ደን ውጤቶች እና ኢንቨስተሩ ራሱ ካረባቸው በስተቀር በግ፣ ፍየል፣ ግመል፣ የቀንድና የጋማ ከብት በቁም መላክን ሳይጨምር | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 15 | **<u>የጅምላ ንግድ</u>**<br>ነዳጅና የነዳጅ ምርቶችን ማቅረብ እና የራስን ምርት በጅምላ መሸጥ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |

## ደንብ ቁጥር 162/2001

## ስለመስኖ ልማት ኢንቨስትመንት ማበረታቻ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 አንቀጽ 9 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ ደንብ "የመስኖ ልማት ኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 162/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፤

   1. "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994[105] ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተደነገጉት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
   3. "የመስኖ ልማት" ማለት ከ50 ሄክታር በላይ የሆነ የመስኖ ልማት፤
   4. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በመስኖ ልማት ዘርፍ እና ከመስኖ ልማት ጋር ተደራራቢ በሆኑ ውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ በሚደረግ ኢንቨስትመንት ላይ ብቻ ነው፡፡

4. **የመስኖ ልማት ኢንቨስትመንት ማበረታቻ ዓላማ**

   በመስኖ ልማት ዘርፍ ለተሠማሩ ባለሃብቶች በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥ ማበረታቻ ዓላማ የሀገሪቱን ሰፊ ለመስኖ ልማት ሊውል የሚችል መሬትና ውሃን ጥቅም ላይ በማዋል የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠን በሚደረገው ጥረት የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ ነው፡፡

5. **ስለፈቃድ አስፈላጊነት**

   በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጥ የመስኖ ልማት ማበረታቻ ብቁ ለመሆን በአዋጁ መሠረት አግባብ ባለው አካል የተሠጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሁም በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 እና በኢትዮጵያ የውሃ

[105] በ18/63 (2004) አ. 769 ተተክቷል፡፡

ሃብት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 115/1997 መሠረት የተሰጠ በውሃ የመጠቀም ፈቃድ መኖር የግድ ይሆናል፡፡

6. **የመስኖ ልማት ማበረታቻዎች**

ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻና ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/1995[106] መሠረት የሚሰጡ ሌሎች ማበረታቻዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥ የመስኖ ልማት ማበረታቻ፡-

1. ከውሃ ዋጋ ክፍያ ነፃ ማድረግን፣
2. ጥናትና ዲዛይናቸው የተጠናቀቀ ፕሮጀክቶችን ዝግጁ ማድረግን፣ እና
3. የግድብ፣ የዋና ዋና ቦይና የመጋቢ መንገድ ግንባታዎችን የመሳሰሉ የመስኖ ልማት ዋና ስትራክቸሮችን በመንግሥት ወጪ ለቀጣይ ልማት ዝግጁ ማድረግን ያካትታል፡፡

7. **ከውሃ ዋጋ ክፍያ ነፃ ስለማድረግ**

1. በመስኖ ልማት ወይም ከመስኖ ልማት ጋር ተደራቢ በሆኑ ውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታ ዘርፍ ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት ለኢንቨስትመንት ያወጣው ወጪ በትክክል ተሰልቶ ወጪው እስኪመለስ ድረስ ከውሃ ዋጋ ክፍያ ነፃ የመሆን መብት ይሰጠዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ ማበረታቻ መቆጠር የሚጀምረው ባለሀብቱ እንደአግባቡ በውሃ ሀብት መጠቀም ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

8. **ጥናትና ዲዛይን የተጠናቀቀላቸውን ፕሮጀክቶች ዝግጁ ስለማድረግ**

በመስኖ ልማት ዘርፍ የሚሠማራ ባለሀብት በመንግሥት ወጪ ጥናትና ዲዛይን የተጠናቀቀላቸውን ፕሮጀክቶች በነፃ ወስዶ መጠቀም ይችላል፡፡

9. **የመስኖ ልማት ዋና ስትራክቸሮችን ዝግጁ ስለማድረግ**

መንግሥት በመደበኛ የልማት ፕሮግራሙ ባለማቸው የግድብ፣ የዋና ዋና ቦይና የመጋቢ መንገድ ግንባታዎችን የመሳሰሉ የመስኖ ልማት የሚገባ ባለሀብት በመንግሥት ለተጠቀሱት ስትራክቸሮች ግንባታ የወጣውን ወጪን መተካት አይጠበቅበትም፡፡

---

[106] በ19/4 (2005) ደ. 270 ተተክቷል፡፡

10.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

የውሃ ሀብት ሚኒስቴር[107] ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

[107] በ25/82011) አ.1097 አንቀፅ 33(3) መሰረት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በሚል ይነበብ፡፡

## ለ/ አምሮአዊ ንብረት

### አዋጅ ቁጥር 123/1987

### የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ

የአገር ውስጥ የፈጠራና መሰል ስራዎችን በማበረታታት ብሄራዊ የቴክኖሎጂ አቅምን ለመገንባት አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

ብሄራዊ ዕድገት ለማስገኘት የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ የውጭ ቴክኖሎጂን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ተስማሚ ሁኔታን መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለሕዝቡ ጥቅም ሲባል ሀገሪቱ የሰመረ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ግስጋሴ እንድትቀዳጅ በሁሉም አቅጣጫ የታቀደውን ፍላጎት የማሟላት ተግባር የበለጠ ሊሳካ የሚችለው ተገቢው ህጋዊ መሠረት ሲኖር በመሆኑ፣

በህገ መንግሥት ጉባኤ የመሸጋገሪያ ውሳኔ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ምዕራፍ አንድ

### አጠቃላይ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ፣**

   ይህ አዋጅ "የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ፣**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ እንዲሰጠው ካላስፈለገ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "ፍርድ ቤት" ማለት የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡
   2. "ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ" ማለት የመስመሮች ወይም የቀለሞች ቅንጅት ወይም ከመስመሮችና ከቀለሞች ጋር የተያያዘ ወይም ያልተያያዘ ባለሶስት ገፅታ ቅርፅ ሲሆን ቅንጅቱ ወይም ቅርጹ ለኢንዱስትሪ ወይም ለዕደ ጥበብ ውጤት ልዩ መልክ የሚሰጥና በኢንዱስትሪ ወይም በዕደጥበብ ለሚመረት ምርት እንደንድፍ የሚያገለግል ነው፡፡
   3. "ፈጠራ" ማለት በቴክኖሎጂ መስክ ለአንድ የተወሰነ ችግር ተግባራዊ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የአንድ የፈጠራ ሠራተኛ ሀሳብ ነው፡፡

4. “ኮሚሽን” ማለት የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን፡፡[108]
5. “ፓተንት” ማለት የፈጠራ ሥራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን የፈጠራ ስራው ከአንድ ምርት ወይም ከምርት ሂደት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡
6. “ባለ ፓተንት” ማለት የፓተንት ወይም የአስገቢ ፓተንት ባለቤት ነው፡፡
7. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው፡፡
8. “የግልጋሎት ሞዴል ሠርተፍኬት” ማለት ለተግባራዊ አገልግሎት ብቃት ላለው አነስተኛ ፈጠራ የሚሰጥ ሰርተፍኬት ነው፡፡
9. “ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ በሥራ ላይ ማዋል” ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የተሟላ ተቋም ፓተንት የተሰጠውን ዕቃ በፋብሪካ ማምረት ወይም የአሠራር ሂደቱን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ፓተንት

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

3. **ፓተንት የሚሰጣቸው የፈጠራ ስራዎች**
   1. አንድ የፈጠራ ስራ አዲስነት፣ ፈጠራዊ ብቃትና፣ ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት ካለው ፓተንት ሊሰጠው ይችላል፡፡
   2. አንድ ፈጠራ አዲስ የሚሆነው በቀደምት ጥበብ ያልተሸፈነ ሲሆን ነው፡፡ ቀደምት ጥበብ ፈጠራውን በሚመለከት ማመልከቻ ከገባበት ወይም እንደአግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት በየትኛውም የዓለም ክፍል በተጨባጭ በሚታይ ሕትመት ወይም በቃል ወይም ጥቅም ላይ በመዋል ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ለሕዝብ የተገለፀን ነገር ይይዛል፡፡
   3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ቢኖርም ማመልከቻው ከገባበት ወይም እንደአግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት ባሉት አስራ ሁለት ወራት ውስጥ በአመልካቹ ወይም ከአመልካቹ በፊት በነበረ ባለመብት ድርጊት ወይም ሶስተኛ ወገን በሚፈፀመው ጥፋት የፈጠራው ለሕዝብ መገለጽ የአዲስነት ባሕርዩን አያሳጣውም፡፡

[108] በ9/40 (1995) አ. 320 አንቀፅ 17 (1) መሠረት ለኮሚሽኑ የተሰጠዉ ስልጣን አእምሮዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት በመተላለፉ “ኮሚሽን” የሚለዉ “ጽህፈት ቤት” በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

4. አንድ ፈጠራ ፈጠራዊ ብቃት አለው የሚባለው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ ከተገለጸውና ከማመልከቻው ጋር አግባብነት ካለው ቀደምት ጥበብ ጋር ሲታይ በመስኩ ተራ እውቀት ላለው ሰው ግልጽ ያልሆነ እንደሆነ ነው፡፡
5. አንድ ፈጠራ ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት እንዳለው የሚቆጠረው ፈጠራው በዕደጥበብ፣ በግብርና በዓሣ ሀብት ልማትና በማህበራዊ አገልግሎቶችና በሌላ ማናቸውም መስክ ሊሰራ ወይም ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ነው፡፡

4. **<u>የፓተንት ጥበቃ የማይደረግላቸው የፈጠራ ሥራዎች፣</u>**

1. የሚከተሉት በፓተንት ጥበቃ አይደረግላቸውም፤

ሀ) የሕዝብን ሰላም ወይም ሥነ-ምግባር የሚፃረሩ ፈጠራዎች፣

ለ) የዕፅዋት ወይም የእንስሳት አይነቶች ወይም የዕፅዋት ወይም የእንስሳት ውጤቶችን ለማስገኘት በስነ ህይወት ዘርፍ የሚከናወኑ ሥራዎች፣

ሐ) ጨዋታዎችን ለማካሄድ ወይም የንግድና የኢንዱስትሪ ስራዎችን ለማከናወን የተዘጋጁ ስልቶች፣ ደንቦችና ዘዴዎች እንዲሁም የኮምፒዩተር ፕሮግራሞች፣

መ) ግኝቶች፣ ሳይንሳዊ ቲዮሪዎችና የቀመራ ዘዴዎች፣

ሠ) ሰውን ወይንም እንስሳትን በቀዶ ጥገና ወይም በቴራፒ ህክምና ዘዴዎች ለማከም እንዲሁም የሰዎችን ወይም የእንስሳትን በሽታ ለመመርመር የሚረዱ ዘዴዎች፣

ረ) በኮፒራይት ጥበቃ የማይደረግላቸው፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ (ሠ) ድንጋጌ ሰውን ወይም እንስሳትን በቀዶ ጥገና ወይም በቴራፒ ህክምና ዘዴዎች ለማከም እንዲሁም የሰዎችን ወይም የእንስሳትን በሽታ ለመመርመር የሚረዱ ዘዴዎችን በጥቅም ላይ ለማዋል በሚያገለግሉ ውጤቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5. **<u>የውጭ ዜጎች መብቶች</u>**

በእንካ ለእንካ መርሆ ወይም እንደ አግባቡ ኢትዮጵያ በምትገባው ማናቸውም ስምምነት ላይ በመመሥረት የውጭ ዜጎች ኢትዮጵያውያን ያሏቸው መብቶችና ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡፡

6. <u>**የፓተንት ማመልከቻዎችን ወይም ፓተንቶችን ማስተላለፍ**</u>

ማንኛውም ፓተንት ወይም የፓተንት ማመልከቻ በሕግ መሠረት በሽያጭ ወይም በውርስ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በዚህ አኳኋን የሚደረገው መተላለፍ በደንቡ የተገለጸው ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ በኮሚሽኑ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፓተንት መብትና የፈጠራ ሠራተኛ ስያሜ

7. <u>**የፓተንት መብት**</u>
    1. የፓተንት መብት የሚሰጠው ለፈጠራ ሠራተኛ ነው፡፡
    2. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ አንድ የፈጠራ ሥራ ካከናወኑ የጋራ የፓተንት መብት ይኖራቸዋል፡፡
    3. ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር በአግልግሎት ወይም በቅጥር ውል አማካኝነት በተከናወነ የፈጠራ ስራ ላይ የፓተንት መብቱ የሚሰጠው የፈጠራ ሥራው በውል አማካኝነት እንዲከናወንለት ላደረገው ሰው ወይም ለቀጣሪው ይሆናል፡፡
    4. ከቅጥር ወይም ከአገልግሎት ውል ጋር ግንኙነት በሌለው መንገድና የቀጣሪውን ወይም የአሰሪውን ሀብት፣ መረጃ፣ ማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ፣ ማቴሪያል ወይም መሳሪያ ሳይጠቀም ለሚያከናውነው የፈጠራ ሥራ ባለቤት ተቀጣሪው ወይም በውሉ መሠረት ሥራውን የሠራው ሰው ይሆናል፡፡
    5. የፈጠራ ሠራተኛውን የግል አስተዋፅኦና የቀጣሪውን ሀብት፣ መረጃ የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ፣ ማቴሪያል ወይም መሳሪያ በማስተባበር በተቀጣሪው ወይም በውሉ መሰረት ሥራውን በሚሰራው ሰው የተከናወኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ስር ሊካተቱ የማይችሉ የፈጠራ ስራዎች ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር እኩል ድርሻን መሰረት በማድረግ የሁለቱም የጋራ ንብረቶች ይሆናሉ፡፡

8. <u>**በፈጠራ ሠራተኛነት መሰየም**</u>

የፈጠራ ሰራተኛው ለኮሚሽኑ በሚያቀርበው ልዩ መግለጫ በፈጠራ ሰራተኛነት እንዳይሰየም በጽሁፍ ካልጠየቀ በስተቀር በማመልከቻው ወይም በፓተንቱ ላይ ስሙ መስፈር አለበት፡፡ እንደዚሁ አይነቱን መግለጫ ለመስጠት በማቀድ ለማንኛውም ሰው በፈጠራ ሠራተኛው የተገባ ቃል ወይም የተደረገ ስምምነት ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

## ክፍል ሶስት

## የፓተንት ማመልከቻና የማመልከቻ ምርመራ

### 9. ማመልከቻ

1. በአንቀጽ 7 መሠረት ለፈጠራው ፓተንት የማግኘት መብት ያለው ሰው የተመደበውን ክፍያ በመፈጸም ኮሚሽኑ ለፈጠራው ፓተንት እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡
2. ማመልከቻው አንድን የፈጠራ ሥራ ብቻ የሚመለከት ሆኖ በጽሁፍ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ፈጠራዎች በአንድ አጠቃላይ ፅንሰ ሀሳብ የተካተቱ ሆነው ሲገኙ በአንድ ማመልከቻ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡
3. ማመልከቻው የፓተንት ይሰጠኝ ጥያቄ እና የፈጠራውን መግለጫ፣ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ የመብት ወሰን፣ የፈጠራውን አጭር ይዘት እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥዕሎችን መያዝ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሰረት የሚቀርብ፤
   ሀ) ጥያቄ ፓተንት እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻን፣ የአመልካቹን፣ የፈጠራ ሠራተኛውና ወኪል ካለው የወኪሉን ስምና ሌሎች የሚፈለጉ መረጃዎችን እንዲሁም የፈጠራውን አርዕስት መያዝ አለበት፡፡ አመልካቹ የፈጠራ ሠራተኛ ባልሆነ ጊዜ ፓተንት ለማግኘት ያለውን መብት የሚያስረዳ መግለጫ በማመልከቻው ውስጥ መስጠት ይኖርበታል፡፡
   ለ) መግለጫ በሙያው የሰለጠነ ሰው በመግለጫው መሠረት ፈጠራውን ስራ ላይ ለማዋል እንዲችል የሚያበቃውን ያህል ግልፅና ሙሉ መሆን አለበት፡፡ መግለጫው በተለይም ፈጠራውን ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉትን በአመልካቹ ከሚታወቁት ዘዴዎች ቢያንስ አንደኛውን ማመልከት ይኖርበታል፡፡ መግለጫው የመብት ወሰኑን ለመተርጎም ሊያገለግል ይችላል፡፡
   ሐ) የመብት ወሰን ጥበቃ የሚፈለግበትን ነገር ግልፅና አጠር ባለ ሁኔታ መወሰን አለበት፡፡ የመብት ወሰኑ በመግለጫው ሙሉ በሙሉ መደገፍ ይኖርበታል፡፡
   መ) የፈጠራ አጭር መግለጫ ለቴክኒካዊ መረጃ ዓላማ ብቻ እንጂ የጥበቃ ወሰኑን ለመተርጎም አያገለግልም፡፡

5. ፈጠራውን ለመረዳት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥዕሎች እንዲቀርቡ ይጠየቃል፡፡ ሥዕሎቹም የመብት ወሰንን ለመተርጎም ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡
6. ማንኛውም አመልካች ፓተንት ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማመልከቻውን መተው ይችላል፡፡
7. ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ ድርጅት የሌለው አመልካች ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ ወኪል መሰየም ይኖርበታል፡፡
8. ማመልከቻው በወኪል አማካይነት በሚቀርብበት ጊዜ የውክልናው ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

10.<u>ተዛማጅ የውጭ ፓተንት ማመልከቻን የሚመለከት መረጃ</u>

1. ማመልከቻ ከቀረበበት ፈጠራ ወይም ከዚያ ጋር ለተዛመደ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ፈጠራ በውጪ አገር ማመልከቻዎች የቀረቡ እንደሆነ በኮሚሽኑ ጥያቄ መሰረት አመልካቹ የውጪውን ማመልከቻ ቀንና ቁጥር መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት የቀረቡ የውጪ ማመልከቻዎች ሲኖሩ ኮሚሽኑ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል፤
   ሀ) አመልካቹ የተቀበለው የውጪ ማመልከቻን የሚመለከት ፍለጋ እና ምርመራ ውጤት ቅጅ፣
   ለ) በውጪው የፓተንት ማመልከቻ መሠረት የተሰጠ ፓተንት ቅጅ፣
   ሐ) የውጪ ማመልከቻውን ውድቅ ለማድረግ ወይም ፓተንት ላለመስጠት የተደረገ የማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ቅጅ፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ በተመለከተው የውጪ ማመልከቻ መሰረት የተሰጠን ፓተንት የሰረዘ ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ቅጅ ኮሚሽኑ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት አመልካቹ ማቅረብ አለበት፡፡

11.<u>የመጀመሪያ ተመዝጋቢነት መርህና የቀዳሚነት መብት</u>

1. አንድ ዓይነት ፈጠራ ራሳቸውን ችለው የሠሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ለፈጠራው ፓተንት እንዲሰጣቸው ሲያመለክቱ ፓተንት የማግኘት መብት የሚሰጠው ማመልከቻውን በመጀመሪያ ላገባው አመልካች ይሆናል፡፡

2. በእንካ ለእንካ መርሆ ወይም እንዳግባቡ ኢትዮጵያ በምትገባው ማናቸውም ስምምነት መሠረት አንድ የውጭ አገር አመልካች በውጭ አገር ፓተንት እንዲሰጠው ከጠየቀበት ቀን አንስቶ ባሉት አስራ ሁለት ወራት ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመሳሳዩ የፈጠራ ስራ ማመልከቻ ሲያቀርብና የቀዳሚነት መብት ሲጠይቅ የቀዳሚውን ማመልከቻ ቅጂ ከተመዘገበበት ጽ/ቤት ትክክለኛነቱን የሚገልጽ ማረጋገጫ እና ሌሎች የሚጠየቁ ሰነዶችንና መረጃዎችን በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካመጣ በውጭ ሀገር ማመልከቻው የተመዘገበበት ቀን የምዝገባ ቀን ተብሎ ይወሰዳል፡፡

12.<u>የምዝገባ ቀን</u>

1. ኮሚሽኑ ማመልከቻው፣

   ሀ) ፓተንት እንዲሰጥ መፈለጉን የሚያሳይ ግልፅ ወይም አንድምታዊ ጥቆማ፣

   ለ) የአመልካቹን ማንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥቆማ፣

   ሐ) በጥቅሉ ሲታይ የፈጠራ መግለጫ የሚመስል ክፍል፣ የያዘ መሆኑን ሲያረጋግጥ ማመልከቻውን የተቀበለበትን ጊዜ የምዝገባ ቀን ብሎ ይሰጣል፡፡

2. ኮሚሽኑ ማመልከቻውን በተቀበለበት ጊዜ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከቱት ተሟልተው ካልተገኙ አመልካቹ አስፈላጊውን ማሻሻያ እንዲያደርግ ይጠራዋል፡፡ ማሻሻያውን የተቀበለበትን ቀን የምዝገባ ቀን ብሎ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም ግን ማሻሻያው ሳይደረግ ቢቀር ማመልከቻው ከመጀመሪያው እንዳልቀረበ ይቆጠራል፡፡

3. በማመልከቻው መግለጫ ያልታቀፉ ሥዕሎችን ማመልከቻው የሚያመለክት ሲሆን ኮሚሽኑ አመልካቹ የጎደሉትን ሥዕሎች እንዲያመጣ ይጠራዋል፡፡ አመልካቹ በጥሪው መሠት የጎደሉትን ሥዕሎች ሲያመጣ እነዚሁ ሥዕሎች የቀረቡበትን ቀን ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ብሎ ይሰጣል፡፡ የጎደሉት ሥዕሎች ያልቀረቡ እንደሆነ ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ብሎ የሚሰጠው ማመልከቻ የቀረበበትን ቀን ሲሆን የጎደሉ ሥዕሎችን በሚመለከት የሚደረገው ነገር ሀሉ እንደሌለ ይቆጠራል፡፡

13. <u>ስለ ማመልከቻ ምርመራ</u>

1. ኮሚሽኑ የማመልከቻ ፎርማሊቲ ምርመራ ያከናውናል፡፡

2. የማመልከቻው የፎርማሊቲ ምርመራ ሲደረግ በዚህ አዋጅና በደንቡ ውስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ካላሟላ ኮሚሽኑ አመልካቹ ማመልከቻውን

እንዲያሻሽል ይጠራዋል፡፡ አመልካቹ እንደተጠየቀው በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ለማሻሻል ካልቻለ ማመልከቻውን መልሶ እንደወሰደ ይቆጠራል፡፡

3. ኮሚሽኑ ከፎርማሊቲ ምርመራ በኋላ ማመልከቻው ተቀባይነት አለው ብሎ ሲወስን የፈጠራ ሥራውን ሥረ-ነገር ምርመራ ያከናውናል ወይንም እንዲከናወን ያደርጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ፓተንት ስለመስጠት፣ የፓተንት ይዘት፣ ፓተንት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜና፣ ስለአመታዊ ክፍያ፣

### 14. ፓተንት ስለመስጠት

1. በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብ የሚጠየቁ መመዘኛዎችን ለሚያሟላ አመልካች ፓተንት ይሰጣል፡፡
2. ኮሚሽኑ ፓተንት በሰጠ ጊዜ፣
   ሀ) ፓተንት ስለመሰጠቱ በኦፊሴላዊ ጋዜጣ ያሳውቃል፣
   ለ) ፓተንት ስለመሰጠቱ ሠርተፊኬት እና የፓተንቱን ቅጅ ለአመልካቹ ይሰጣል፣
   ሐ) ፓተንቱን ይመዘግባል እንዲሁም፣
   መ) የፓተንቱን ቅጅ የተወሰነውን ክፍያ ለሚፈፅም ማንኛውም ሰው ይሰጣል፡፡
3. አመልካቹ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ኮሚሽኑ ፓተንት በተሰጠው የመጀመሪያ ማመልከቻ ላይ ከተገለጠው ውጪ የሆነ ነገር ካላስከተለ የጥበቃ ወሰኑን ለመገደብ በፓተንት ሰነዱ ወይም ስዕሎች ላይ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 15. የፓተንት ይዘት

ፓተንቱ ባለፓተንቱ በፈጠራው ላይ ያለውን ብቸኛ መብት የሚያረጋግጥ እና ሌሎች በደንቡ ውስጥ የተደነገጉ ዝርዝር ነጥቦችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

### 16. የፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

የፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጥበቃ ለማግኘት የቀረበው ማመልከቻ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ለአሥራ አምስት ዓመታት ይሆናል፡፡ ሆኖም ፈጠራው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገባ ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲቀርብ የፓተንት መብቱ ለተጨማሪ አምስት አመታት ሊራዘም ይችላል፡፡

## 17. <u>አመታዊ ክፍያ</u>

1. ፓተንቱን ወይም የፓተንት ማመልከቻውን ባለበት አኳኋን ለማቆየት እንዲቻል ፓተንት እንዲሰጥ የቀረበው ማመልከቻ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ከአንድ ዓመት በኋላ ለያንዳንዱ አመት ለኮሚሽኑ አመታዊ ክፍያ በቅድሚያ መከፈል አለበት፡፡ ዓመታዊውን ክፍያ ከተወነው ጊዜ ዘግይቶ ከተጨማሪ ክፍያ ጋር ለመክፈል የስድስት ወር የችሮታ ጊዜ ይኖራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ላይ በተደነገገው መሠረት አመታዊ ክፍያው ካልተከፈለ፣ አመልካቹ ማመልከቻውን መልሶ እንደወሰደው ወይም የፓተንት መብቱን እንደተወው ይቆጠራል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የአስገቢ ፓተንት</u>

## 18. <u>የአስገቢ ፓተንት መሰጠት</u>

በውጭ አገር ፓተንት ለተሰጠው እና የጥበቃ ጊዜው ላላለፈበት እንዲሁም በኢትዮጵያ ፓተንት ላልተሰጠው የፈጠራ ስራ መግለጫ ለሰጠና ሙሉ ኃላፊነት ለሚወስድ ማንኛውም ሰው የአስገቢ ፓተንት ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 19. <u>የአስገቢ ፓተንት መመዘኛዎችና ሁኔታዎች</u>

1. ለአስገቢ ፓተንት የሚጠየቁ መመዘኛዎች፣ ሁኔታዎችና ፎርማሊቲዎች ለፈጠራ ፓተንት ከሚጠየቁት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የአስገቢ ፓተንት አመልካች የውጭውን ፓተንት ቁጥር ቀንና ምንጭ ወይም ዝርዝሩን የማያውቅ ሲሆን ተፈላጊው መረጃ ሊገኝ የሚችልበትን ምንጭ መጠቆም አለበት፡፡

## 20. <u>የአስገቢ ፓተንት መሠረዝ</u>

1. በአንቀጽ 11/2/ የተመለከተው የአንድ ዓመት ጊዜ ከማለቁ በፊት የውጪው ፓተንት ባለቤት ማመልከቻ ካቀረበ ወይም ያሰገቢ ፓተንት ባለቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት ፈጠራው ስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ወይም አመታዊውን ክፍያ መፈፀም ካልቻለ የአስገቢ ፓተንቱ ዋጋ ቢስ ወይም ህጋዊ ውጤት የሌለው እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
2. የሚመለከተው ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የአስገቢ ፓተንቱ መሠረዝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 መሠረት በፍ/ቤት ይወሰናል፡፡

21.**<u>የአስገቢ ፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣</u>**

የአስገቢ ፓተንቱ ከተሰጠ ከሶስት አመት በኋላ በየአመቱ ባለቤቱ ፈጠራው ሥራ ላይ መዋሉን እና ተገቢው ዓመታዊ ክፍያ መከፈሉን የማረጋገጥ ግዴታው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአስገቢ ፓተንቱ ፀንቶ የሚቆየው እስከ አስር ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

**<u>መብቶችና ግዴታዎች</u>**

22.**<u>የባለ ፓተንቱ መብቶች</u>**

1. ባለፓተንቱ ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ ለመፈብረክ ወይም በሱ ለመገልገል ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ለመጠቀም መብት ይኖረዋል፡፡ ሶስተኛ ወገኖች ከባለፓተንቱ ፈቃድ ካላገኙ በቀር ፓተንት በተሰጠበት ፈጠራ ለመጠቀም አይችሉም፡፡
2. ባለፓተንቱ በኢትዮጵያ ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ ውጤት ወደ አገር ውስጥ የማስገባት የሞኖፖሊ መብት አይኖረውም፡፡

23.**<u>መብቶችን ስለማግኘት</u>**

የባለፓተንቱ መብት የሚገኘውና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ፓተንት ሲሰጥ ይሆናል፡፡

24.**<u>ባለፓተንቱ መብቱ ሲነካበት የሚወስደው እርምጃ</u>**

በአንቀጽ 25፣ 26፣ 29 እስከ 33 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፓተንቱ ሊኖሩት ከሚችሉ ሌሎች መብቶች ወይም ሊወስድ ከሚችላቸው መፍትሄዎች ወይም እርምጃዎች በተጨማሪ በአንቀጽ 22/1/ ላይ የተገለጹትን ማናቸውም ድርጊቶች ያለእርሱ ፈቃድ ፓተንቱን የሚጻረር ወይም መብቱን ሊነኩ የሚችሉ ድርጊቶችን በሚፈጽም ማናቸውም ሰው ላይ በፍ/ቤት ክስ የመመሥረት መብት አለው፡፡

25.**<u>የባለፓተንቱ መብት ገደቦች</u>**

1. የባለፓተንቱ መብት በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤
   ሀ) ንግድ ነክ ባልሆኑ ተግባሮች፣
   ለ) ፓተንት የተሰጠበት ፈጠራ ለሳይንሳዊ ምርምርና ሙከራዎች ዓላማ አገለግሎት ብቻ የሚውል ከሆነ፣
   ሐ) በባለፓተንቱ ወይም በሱ ፈቃድ ኢትዮጵያ ውስጥ በገበያ ላይ ከዋሉ ፓተንት ከተሰጣቸው ሸቀጦች ጋር በተያያዘ መልክ የሚከናወኑ ድርጊቶች ወይም፣

መ) ለአጭር ጊዜ ወይም በድንገት ወደ ኢትዮጵያ የአየር፣ የምድር ወይም የውሀዎች[109] ክልል በሚገቡ የሌሎች አገሮች የአየር የየብስና የባሕር መጓጓዣዎች ላይ ፓተንት የተሰጣቸውን ዕቃዎች መገልገል፡፡

2. የሕዝብን ጥቅም በተለይም የብሄራዊ ደህንነት፣ የምግብና፣ የጤና ወይም የሌሎች ብሄራዊ ኢኮኖሚ ዋና ዘርፎችን የልማት ፍላጎት ለመጠበቅ ኮሚሽኑ ያለባለፓተንቱ ፈቃድ የመንግሥት ድርጅት ወይም ኮሚሽኑ የሚሰይመው ሶስተኛ ወገን ለባለፓተንቱ ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ፈጠራውን እንዲጠቀም ሊወስን ይችላል፡፡ ክፍያውን በሚመለከት ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባልበት ይችላል፡፡

## 26. ቀደምት ተጠቃሚዎች

1. ማመልከቻ ከተመዘገበበት ወይም እንደአግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት ባለው ጊዜ ጥበቃ እንዲደረግ በሚጠይቀው ማመልከቻ የተጠቀሰውንና ፓተንት የተሰጠበትን ፈጠራ በቅን ልቦና ይገለገልበት የነበረ ማንም ሰው ፓተንት ቢኖርም በፈጠራው መጠቀሙን ለመቀጠል ግላዊ መብት ይኖረዋል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው የቀደምት ተጠቃሚዎች መብት ሊተላለፍ የሚችለው አገልግሎቱ ከሚሰጥበት ወይም አገልግሎት ላይ ለማዋል ዝግጅት ከተደረገበት ድርጅት ወይም ንግድ ወይም ከድርጅቱ ወይም ከንግዱ አካል ጋር ብቻ ነው፡፡

## 27. የባለፓተንቱ ግዴታዎች

1. ባለፓተንቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጠራውን ስራ ላይ የማዋል ወይም በርሱ ፈቃድ ሌሎች ሰዎች ፈጠራውን ስራ ላይ እንዲያውሉ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
2. ባለፓተንቱ ፈጠራውን ባለው ሁኔታ በቂና ተገቢ ነው ተብሎ በሚታመን መጠን ሥራ ላይ ማዋል አለበት፡፡

## 28. ተፈጻሚነት

ከዚህ በላይ የተደነገጉት እንደየአግባቡ በአስገቢ ፓተንቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

[109] አገሪቱ የውሃዎች ክልል ስለሌላት በአሁኑ ጊዜ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ክፍል ሰባት

## የግዴታ ፈቃድ

### 29.የግዴታ ፈቃድ ማመልከቻ

1. ቀደም ብሎ ፓተንት የተሰጠበትን ፈጠራ ካልተጠቀመ በስተቀር የራሱን ፈጠራ በሚገባ ተግባራዊ ሊያደርግ ያልቻለ ባለፓተንት ቀደም ባለው ፈጠራ ለመጠቀም የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. በኋለኛው ፈጠራ ካልተጠቀመ በስተቀር የራሱን ፈጠራ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ ያልቻለ ባለፓተንት በኋለኛው ፈጠራ ለመጠቀም የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡
3. ባለፓተንቱ ያለበቂ ምክንያት ፈጠራውን በኢትዮጵያ ውስጥ በአጥጋቢ ሁኔታ ተግባራዊ ሳያደርግ ፓተንቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሶስት ዓመት ወይም የፓተንቱ ማመልከቻ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አራት ዓመት ከሁለቱ ዘግይቶ የሚፈፀመው ካለፈ በኋላ ፈጠራውን በሥራ ላይ ለማዋል ችሎታ ያለው ማንኛውም ሰው የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡

### 30. የግዴታ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ኮሚሽኑ ጥያቄው ብቁ ሆኖ ሲያገኘው የግዴታ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. የግዴታ ፈቃድ መስጠት የፓተንት ባለቤቱ በፈጠራው እንዳይጠቀም፣ የፈቃድ ውል እንዳይገባ ወይም ሌሎች የግዴታ ፈቃዶች እንዳይሰጡ አይከለክልም፣
3. ኮሚሽኑ የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት የሚያደርገው ውሳኔ ተመዝግቦ በኦፊሴላዊ ጋዜጣ ይገለፃል፡፡

### 31.ከአመልካቹ የሚፈለገው ማስረጃ

ፓተንት በተሰጠበት ፈጠራ ለመጠቀም የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው ከባለፓተንቱ ጋር ተገቢ ሁኔታዎችን የያዘ በፈጠራው ለመጠቀም የፈቃድ ውል ለመግባት ያዳገተው ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

### 32.የፈቃድ ተቀባይ መብቶች ወሰን

1. ፓተንት በተሰጠው ፈጠራ ላይ የግዴታ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በፈጠራው ላይ ብቸኛ መብት የለውም፣ ሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲጠቀምበት ለመፍቀድም መብት አይኖረውም፡፡

2. ፈቃድ በተሰጠበት ውሳኔ ላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት ፓተንት የተሰጠበትን ፈጠራ ኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ ለማዋል መብት ይኖረዋል፡፡ ውሳኔው በሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥም ፓተንት የተሰጠበትን ፈጠራ ተግባራዊ ማድረግ መጀመር ይኖርበታል፡፡

33.<u>የመጠቀሚያ ክፍያ</u>

1. የግዴታ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለባለፓተንቱ ተገቢ የመጠቀሚያ ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡ የመጠቀሚያው ክፍያ መጠን በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ይወሰናል፡፡
2. ሁለቱም ወገኖች በክፍያው መጠን ሳይስማሙ ሲቀር ኮሚሽኑ መጠኑን ይወስናል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>የፓተንት መቋረጥ፣ መተው እና መሠረዝ</u>

34.<u>የፓተንት መቋረጥ</u>

አንድ ፓተንት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አንዱ ሁኔታ ሲኖር ይቋረጣል፣

1. ባለፓተንቱ ፓተንቱን የተወ መሆኑን በፅሁፍ ለኮሚሽኑ ሲያሳውቅ ወይም፣
2. የመብት ማቆያ ክፍያው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተፈፀመ ሲሆን፣

35.<u>የፓተንት መተው</u>

1. የፓተንት መተው አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ የፓተንት መብት ጥያቄዎች ላይ የተወሰነ ሊሆን ይችላል፣
2. የፓተንት መተው በኮሚሽኑ ወዲያውኑ ተመዝግቦ ታትሞ ይወጣል፣
3. ፓተንቱ በውል ተላልፎ ከሆነ የፓተንቱ መተው ውጤት የሚኖረው የተመዘገበው የውል ተቀባይ ፓተንቱን ስለመተው የተስማማ መሆኑን ከገለጸ ብቻ ይሆናል፡፡

36.<u>የፓተንት መሰረዝ</u>

1. የሚመለከተው ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤቱ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ከተረጋገጠ በሙሉ ወይም በከፊል ፓተንቱን ይሰርዛል፡፡
   ሀ) ፓተንት የተጠየቀበት ነገር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ፓተንት ሊሰጥበት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣
   ለ) ፈጠራው በሚበቃ መጠን ግልጽና ሙሉ በሆነ መልክ ባለመገለጹ በመስኩ ለሰለጠነ ሰው በተግባር ለመተርጎም የማያስችል ሲሆን፣

2. በከፊል ወይም በሙሉ የተሰረዘ ፓተንት ዋጋ ቢስ ሆኖ የሚቆጠረው ፓተንቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

37.**<u>ተፈጻሚነት</u>**

ከአንቀጽ 34-36 የተጠቀሱት አንቀጾች ለአስገቢ ፓተንቶች መቋረጥ፣ መተው ወይም መሰረዝ እንደ የአግባብነታቸው ያገለግላሉ፡፡

**<u>ምዕራፍ ሶስት</u>**

**<u>የግልጋሎት ሞዴሎች ሰርተፍኬት</u>**

38.**<u>የአነስተኛ ፈጠራ ጥበቃ</u>**

1. አዲስነትና ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት ያለው አነስተኛ ፈጠራ ለአመንጪው የጥበቃ መብት ያስገኛል፡፡
2. የጥበቃ መብቱ ኮሚሽኑ በሚሰጠው የግልጋሎት ሞዴል ሰርተፊኬት ይረጋገጣል፡፡
3. ሰርተፊኬት መሰጠቱ በአነስተኛ ፈጠራው ለመጠቀም እና ሶስተኛ ወገኖች ያለ ሠርተፊኬት ያገኙ ፈቃድ በአነስተኛ ፈጠራው እንዳይጠቀሙ ለመከላከል የሚያስችል ብቸኛ መብት ያጎናጽፋል፡፡

39.**<u>የአዲስነት አለመኖር</u>**

1. አነስተኛ ፈጠራው ማመልከቻው በተመዘገበበት ቀን በኢትዮጵያ ውስጥ በታተሙ ጽሁፎች ላይ ቀደም ሲል የተገለጸ፣ ወይም ለሕዝብ የቀረበ ወይም በይፋ ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ እንደአዲስ አይቆጠርም፡፡
2. በአመልካቹ ሥራ ላይ ተመስርቶ ማመልከቻው ከመመዝገቡ ከስድስት ወራት አስቀድሞ መገለጹና ጥቅም ላይ መዋሉ ግን አዲስነቱን አያስቀረውም፡፡

40.**<u>በግልጋሎት ሞዴል ሰርተፍኬት ጥበቃ የማይደረግላቸው</u>**

የሚከተሉት በግልጋሎት ሞዴል ሰርተፍኬት ጥበቃ አይደረግላቸውም፣

1. ፓተንት የተሰጠበት ወይም የሕዝብ ንብረት የሆነን ነገር የቀድሞ ይዘት፣ ጠባይ ወይም ተግባር ቀይሮ በአጠቃቀሙ ወይም በታለሙለት ተግባሮች ላይ መሻሻልን የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር በቅርጽ፣ በመጠን ወይም በማቴሪያል መልክ የሚደረጉ ለውጦች፣
2. የታወቁ ንጥረ ነገሮችን ጥንቅር ተመሳሳይ ተግባር ባላቸው ሌሎች የታወቁ ንጥረ ነገሮች የመተካትና ይህም በሚገኘው ጥቅም ወይም አሠራር ላይ ምንም አይነት መሻሻል የማያስገኝ ሲሆን፣

3. ለሕዝብ ሰላምና ስነምግባር ተጻራሪ የሆኑ አነስተኛ ፈጠራዎች፡፡

41.<u>ምርመራ</u>

ኮሚሽኑ በማመልከቻው ላይ የፎርማሊቲ ምርመራ በማድረግ የግልጋሎት ሞዴል ሰርተፍኬት እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ይወስናል፡፡

42.<u>የግልጋሎት ሞዴል ሠርተፍኬትተ ስለመስጠት</u>

ኮሚሽኑ የግልጋሎት ሞዴል ሰርተፍኬት ለመስጠት ሲወስን ለአመልካቹ የግልጋሎት ሞዴል ሠርተፍኬት ይሰጣል፡፡

43.<u>የፓተንት ማመልከቻ እና የግልጋሎት ሞዴል ማመልከቻን ስለማለዋወጥ</u>

1. የፓተንት አመልካቹ ፓተንት ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ከመወሰኑ በፊት ባለው ማናቸውም ጊዜ የሚጠየቀውን ክፍያ በመፈጸም ማመልከቻውን ወደ ግልጋሎት ሞዴል ሠርተፍኬት ማመልከቻ ሊቀይር ይችላል፡፡ ማመልከቻው የመጀመሪያው ማመልከቻ የምዝገባ ቀን ይሰጠዋል፡፡
2. የግልጋሎት ሞዴል ሠርተፍኬት አመልካቹ የግልጋሎት ሞዴል ሠርተፍኬት ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ከመወሰኑ በፊት ባለው ማናቸውም ጊዜ የሚጠየቀውን ክፍያ በመፈጸም ማመልከቻውን ወደ ፓተንት ማመልከቻ ሊቀይር ይችላል፡፡ ማመልከቻው የመጀመሪያው ማመልከቻ የምዝገባ ቀን ይሰጠዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የሚደረገው የማመልከቻ ለውጥ ከአንድ ጊዜ በላይ አይሆንም፡፡

44.<u>የግልጋሎት ሞዴል ሰርተፍኬት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

1. የግልጋሎት ሞዴል ሰርተፍኬት የሚሰጠው ለአምስት አመት ሲሆን አነስተኛ ፈጠራው በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲቀርብ ሰርተፍኬቱ ለተጨማሪ አምስት አመታት ሊታደስ ይችላል፡፡
2. ሠርተፍኬቱን ለማሳደስ የሚቀርበው ማመልከቻ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈጸም የጥበቃ ዘመኑ ከማብቃቱ ከዘጠና ቀናት በፊት ለኮሚሽኑ ይቀርባል፡፡

45.<u>ተፈጻሚነት</u>

የዚህ አዋጅ የምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች እንደየአግባቡ በግልጋሎት ሞዴል ሰርተፍኬቶች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## ኢንዱስትሪያዊ ንድፎች

### 46.የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃ

1. አዲስነትና ተግባራዊ ተፈጻሚነት ያለው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በዚህ አዋጅ መሠረት ጥበቃ ይደረግለታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት አንድ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ፣
   ሀ) አዲስ ነው የሚባለው የንድፉ ዋና ዋና ባሕሪያት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ እና ከምዝገባ ቀን ወይም እንዳግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተገለጸ ሲሆን ነው፡፡ በንድፎቹ መካከል ያሉ የተለዩ ገጽታዎች ልዩነት በጥቃቅን ዝርዝሮች ከሆነ ተመሳሳይ ናቸው ተብለው ይወሰዳሉ፡፡
   ለ) ተግባራዊ ተፈጻሚነት አለው የሚባለው ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ምርቶችን በተደጋጋሚ ለማውጣት በሞዴልነት ለማገልገል የሚችል ሲሆን ነው፡፡
3. ለሕዝብ ሰላም ወይም ሥነምግባር ተጻራሪ የሆነ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አይመዘገብም፡፡
4. ቴክኒካዊ ውጤቶችን ለማግኘት ብቻ ለሚውሉ ማናቸውም ነገሮች በዚህ አዋጅ ለኢንዱስትሪያዊ ንድፎች የሚሰጠው ጥበቃ አይሰጥም፡፡

### 47.ማመልከቻ

1. አንድን ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ለማስመዝገብ ማመልከቻ የሚቀርበው ኮሚሽኑ ይሆናል፡፡
2. ማመልከቻው የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃ ይሰጠኝ ጥያቄ፣ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ያቀፈ ምርት ናሙና ወይም የንድፉን ስዕላዊ አምሳያና ንድፉ ሊያገለግል የታቀደውን የምርት ዓይነት መያዝ ይኖርበታል፡፡
3. ማመልከቻው በአንድ ምርት ውስጥ የሚካተት አንድን ንድፍ ወይም ተመሳሳይነት ባላቸው በአንድነት በሚሸጡ ወይም በጥቅም ላይ በሚውሉ ምርቶች ላይ የሚገቡ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ንድፎችን ይይዛል፡፡
4. ከማመልከቻው ጋር የተመደበው ክፍያ ይከፍላል፡፡

**48.<u>ምርመራና ምዝገባ</u>**

1. ኮሚሽኑ ማመልከቻው የዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/2/ እና አንቀጽ 47 እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣው ደንብ የሚዘረዘሩ መመዘኛዎችን ማሟላቱን ይመረምራል፡፡
2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱም፣
   ሀ) የንድፍ ሥራው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መሆኑን፣
   ለ) የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ቀዳሚነት፣
   ሐ) የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ሠራተኛ ማንነትና ባለቤቱ በኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ላይ ያለውን ብቸኛ መብት መያዝ አለበት፡፡

**49.<u>በምዝገባው የሚገኙ መብቶች</u>**

የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ሠርተፍኬት ባለቤት በንድፉ ለመሥራት፣ ወይም ለመገልገል ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን ለመጠቀም ብቸኛ መብት ይኖረዋል፡፡

**50.<u>የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መብት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

1. ለኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚሰጠው ጥበቃ ፀንቶ የሚቆየው የምዝገባ ማመልከቻው ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ለአምስት ዓመታት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መብት ለተጨማሪ ሁለት አምስት አመታት ሊራዘም ይችላል፡፡
2. የጥበቃ ጊዜው እንዲራዘም የሚጠይቀው ማመልከቻ አስፈላጊው ክፍያ ተፈፅሞ ለኮሚሽኑ የሚቀርበው የጥበቃ ዘመኑ ከማብቃቱ ከዘጠና ቀናት በፊት ይሆናል፡፡

**51.<u>ተፈጻሚነት</u>**

የዚህ አዋጅ ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች እንደየአግባቡ ለኢንዱስትሪያዊ ንድፎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

52.**የጊዜ መራዘም**

ኮሚሽኑ በፅሁፍ ሲጠየቅና በሁኔታው ሲያምን በዚህ አዋጅና በደንቡ መሠረት ለሚፈጸሙ ማናቸውም ድርጊቶች ወይም ለሚወሰዱ ርምጃዎች የተመለከተው የጊዜ ገደብ የሚመለከታቸውን ሶስተኛ ወገኖች በማሳወቅና ተገቢውን መመሪያ በመስጠት እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል፡፡ የጊዜ ማራዘሚያው ውሳኔም ተግባሩን ለማከናወን ወይም ርምጃውን ለመውሰድ የሚጠየቀው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ሊሰጥ ይችላል፡፡

53.**ደንብ ስለማውጣት**

1. ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ሊወጡ ይችላሉ፡፡
2. ደንቡ በተለይም ፓተንትና የግልጋሎት ሞዴል ሠርተፍኬት እንዲሰጥ፣ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ እንዲመዘገብ ከሚቀርቡ ማመልከቻዎች እንዲሁም ከሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን ይወስናል፡፡

54.**በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1. በዚህ አዋጅ አግባብ ባላቸው ድንጋጌዎች የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ይግባኝ የሚቀርበው ቅር የተሰኘው ወገን ውሳኔው ከደረሰው ጊዜ አንስቶ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

55.**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 2 ቀን 1987 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 12/1989

## የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራ እና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 በአንቀጽ 53(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራ እና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/1989" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

   1. "ኮሚሽን" ማለት የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ነው፤[110]
   2. "መርማሪ" ማለት ለፓተንት፣ ለግልጋሎት ሞዴል ሰርተፊኬት ወይም ለኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ሰርተፊኬት የሚቀርብን ማመልከቻ እንዲመረምር በኮሚሽኑ የተሰየመ ባለሙያ ነው፤
   3. "ባለ ፓተንት" ማለት የፓተንት ወይም የአስገቢ ፓተንት ባለቤት ነው፤
   4. "አዋጅ" ማለት የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ነው።

3. **ክፍያዎች**

   በአዋጁ አንቀጽ 53(2) መሰረት የሚፈጸሙ ክፍያዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተዘረዘረው መሠረት ይሆናል፡፡

4. **ቅጾች**

   1. በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱት ቅጾች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ II ላይ የተመለከቱት ናቸው፡፡

[110] በ9/40(1995) አ. 320 አንቀፅ 17 (1) መሠረት ለኮሚሽኑ ተሰጠዉ ስልጣን ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት በመተላለፉ ከዚህ በኃላ "ኮሚሽን" ተብሎ የተገለፀው "ጽህፈት ቤት" በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

2. ኮሚሽኑ የታተሙ ቅጾችን ቅጅዎች ያለ ክፍያ ያቀርባል፡፡

5. <u>ሰነዶች ስለሚቀርቡበት ቋንቋና ትርጉም</u>

1. ማናቸውም ማመልከቻ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅረብ አለበት፡፡
2. በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ የማመልከቻ አካል የሆነ ወይም ሌላ ሰነድ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ያልተዘጋጀ ከሆነ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ ከዋናው ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት።

6. <u>ስለስም፣ አድራሻ፣ ዜግነትና የመኖሪያቦታ ጥቆማ</u>

1. ከኢትየጵያዊያን በስተቀር የአንድ ተፈጥሮአዊ ሰው ስም የቤተሰብን ስም በማስቀደም በቤተሰብና በመጀመሪያ ስም መገለፅ ያለበት ሲሆን ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካሎች ደግሞ ሙሉ ሕጋዊ መጠሪያ ስማቸው መመልከት ይኖርበታል፡፡
2. ማናቸውም አድራሻ አመልካቹ የሚገኝበትን የተሟላ አድራሻ በተለይም የፖስታ ሳጥን የቴሌግራፍ፣ የቴሌክስ፣ የስልክ ወይም የፋክስ ቁጥር ሊያመለከት ይገባል፡፡
3. ዜግነት አንድ ሰው ዜጋ በሆነበት አገር ስም መገለጽ አለበት፡፡ የህግ ሰዉነት ያለዉ ድርጅት ከሆነ የተቋቋመበትን ሀገር ስም የሚገልጽ ሆኖ ዋናው መሥሪያ ቤት የተመዘገበበትን ዝርዝር መግለጫ የያዘ መሆን ይኖርበል።
4. የመኖሪያ ቦታ አንድ ሰው የሚኖርበትን ሀገር ስም ጭምር የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡

7. <u>በሽርካዎች፣ በኩባንያዎችና በማሕበራት ስለሚደረግ ፊርማ</u>

1. ማናቸውም ሰነድ በሽርካው ወይም በኩባንያው ወይም በማሕበር ስም የሚፈረመው ሥልጣን በተሰጣቸው ሰዎች ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚፈረም ሰነድ ላይ የሽርካዉ፣ የኩባንያው ወይም የማሕበሩ ማሕተም ሊያርፍበት ይገባል፡፡

8. <u>ስለውክልና</u>

የውክልና ሠነድ ከማመልከቻው ጋር ወይም ከምዝገባው ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ውክልናው በአዋጁ አንቀጽ 9(7) እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ 48 በተደነገገው መሠረት ካልተፈጸመ ማመልከቻውን ከማስመዝገብ ውጭ በወኪሉ በየደረጃው የተከናወኑ ተግባራት እንዳልተፈጸሙ ይቆጠራሉ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ፓተንት

## ክፍል አንድ

## ስለማመልከቻ እና የፓተንት አሰጣጥ ስርዓት

9. **ስለፓተንት ምደባ**

ከፓተንት አሰጣጥና ሕትመት ጋር ለተዛመዱ ጉዳዮች እንዲሁም የፍለጋ ፋይሎችን ለማኖር ኮሚሽኑ እ.ኤ.አ ማርች 24/1971 ዓ.ም በስትራስበርግ ስምምነት የፀደቀውንና በተከታታይ ሕትመቶች የተሻሻለውን ዓለምአቀፍ የፓተንት ምደባ ስርዓት ይጠቀማል፡፡

10. **የፓተንት ይሰጠኝ ጥያቄ**

1. የፓተንት ይሰጠኝ ጥያቄ በቅፅ 1 ተሞልቶ እና በእያንዳንዱ አመልካች ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. ጥያቄው የእያንዳንዱን አመልካች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነትና መኖሪያ ማመልከት ይኖርበታል፡፡
3. አመልካቹ የፈጠራ ሠራተኛው ሲሆን ጥያቄው ይህንኑ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሆኖም አመልካቹ የፈጠራ ሰራተኛ ካልሆነ ጥያቄው የእያንዳንዱን የፈጠራ ሰራተኛ ስም እና አድራሻ እንዲሁም አመልካቹ በፓተንቱ ላይ ያለውን መብት የሚያስረዳ መግለጫ መያዝ ይኖርበታል።
4. አመልካቹ በወኪል ከተወከለ ጥያቄው ይህንኑ ማመልከትና የወኪሉን ስምና አድራሻ መግለፅ ይኖርበታል።
5. የፈጠራው ርዕስ አጠር ያለና ቢቻል ከሁለት እስከ ሰባት ባልበለጡ ቃላት ሊገለጽ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡

11. **ስለ መግለጫ**

1. መግለጫው በቅድሚያ በመጠይቁ ላይ እንደተመለከተው የፈጠራውን ርዕስ የሚገልጽ ሆኖ፤

   ሀ) ከፈጠራው ጋር ግንኙነት ያለውን የቴክኒክ መስክ የሚያመለክት፣

   ለ) በአመልካቹ እስከታወቀ ድረስ ፈጠራውን ለመረዳት፣ ለመፈለግ፣ እና ለመመርመር ጠቃሚ የሆኑ መነሻ ጥበቦችን በይበልጥም እነኝህኑ ጥበቦች የሚያመለክቱ ሰነዶችን የሚጠቁም፤

ሐ) ፈጠራው ያሚላል ተብሎ የታለመውን ተግባር የሚገልጽ፤

መ) በሙያው የሰለጠነ ሰው ፈጠራውን ተግባራዊ ሊያደርገው በሚችልበት አኳኋን በበቂና በተሟላ ሁኔታ የሚያብራራ እና ጠቃሚ ውጤት ካለው ከመነሻ ጥበቡ ጋር በማነፃፀር የሚገልጽ፣

ሠ) ከቀደምት ጥበብ ጋር ሲወዳደር ፈጠራው የሚኖረውን በጎ ጎን ወይም ውጤታማነት የሚገልጽ፣

ረ) ሥዕሎች ካሉ በሥዕሎቹ ውስጥ ያሉ ቁጥሮችን በአጭሩ የሚዘረዝር፣

ሰ) ፈጠራውን በሥራ ላይ ለማዋል በአመልካቹ ከተተለሙ መንገዶች ቢያንስ አንዱን የሚገልጽና እንደ አስፈላጊነቱ ምሳሌዎችን በመጠቀም እና ስዕሎች ካሉ ከሥዕሎች ጋር በማገናዘብ የሚያቀርብ፣

ሸ) ከፈጠራው መግለጫ ወይም ባህርይ ግልፅ ሊሆን ካልቻለ ፈጠራው በኢንዱስትሪ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን እና ፈጠራው የሚሰራበትንና ግልጋሎት ላይ የሚውልበትን መንገድ ወይም አገልግሎት መስጠት ብቻ ከሆነም አገልግሎት ላይ የሚውልበትን መንገድ በግልጽ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል፡፡

2. በፈጠራው ባህሪ ምክንያት ፈጠራውን በተለየ መንገድ ወይም ቅደም ተከተል መግለጹ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳትና በአጭሩ ለማቅረብ የሚያመች ሆኖ ካልተገኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ በተመለከተው መንገድ እና ቅደም ተከተል መግለጫው መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. የፈጠራው መግለጫ የኬሚካል ወይም የሂሳብ ፎርሙላዎችን እንጅ የንግድ ማስታወቂያዎችን ሊይዝ አይችልም።

4. መግለጫው ፈጠራውን የበለጠ ለማብራራት የሚረዱ ነገሮችን ብቻ መያዝ የሚችል ሆኖ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያላገኘ አዲስ ቃል ወይም ሙያ ነክ ቃልን የያዘ እንደሆነ ቃሉ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

12.<u>ስለመብት ወሰን ጥያቄ</u>

1. የመብት ወሰን ጥያቄ ጥበቃ እንዲደረግለት የሚፈለግን ጉዳይ በፈጠራው ቴክኒካዊ ገፅታዎች አማካኝነት ግልጽ በሆነና አጠር ባለ መንገድ የሚገልጽና አንድን ምርት ወይም የምርት ሒደት የሚመለከት ይሆናል፡፡

2. የመብት ወሰን ጥያቄዎች ብዛት የፈጠራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት አግባብነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ ብዙ የመብት ወሰን ጥያቄዎች በሚኖሩበት ጊዜ ተከታታይ የአረብኛ ቁጥር ይሰጣቸዋል፡፡
3. በመብት ወሰን ጥያቄ ላይ የሚገለጽ የቴክኒክ ቃል በመግለጫው ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡ የመብት ወሰን ጥያቄዎች የኬሚካል ወይም የሂሳብ ፎርሙላዎችን እንጂ ሥዕሎችን አይዙም፡፡
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመብት ወሰን ጥያቄ፣
   ሀ) ፈጠራውን ለመግለጽ አስፈላጊና በጣምራ የቀደምት ጥበብ አካል የሆኑትን የፈጠራውን ቴክኒካዊ ባህርያት የሚያመለክት መግለጫ፣
   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) (ሀ) ከተመለከቱት ባህርያት ጋር በመጣመር ጥበቃ ሊደረግለት የተፈለገውን ቴክኒካዊ ባህርይ በአጭሩ የሚገልጽ “የሚገለጸው” “የሚለየው” “ማሻሻያው የሚያካትተው” በሚሉ ሐረጎች የሚጀምር የመለያ ባህርይ ክፍል ሊይዝ ይገባል፡፡
5. የግድ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር የመብት ወሰን ጥያቄ የፈጠራውን ቴክኒካዊ ባህርያት አስመልክቶ መግለጫዎችን ወይም ስዕሎችን መሠረት ያደረጉ በተለይም “በመግለጫው………. ክፍል እንደተገለጸው”፣ ወይም “በስዕሉ ………ላይ እንደተመለከተው” በሚሉ ተጠቃሾች ላይ አይወሰኑም።
6. ማመልከቻው ሥዕሎችን ያካተተ እንደሆነ በመብት ወሰን ጥያቄ ውስጥ የተገለጹት ቴክኒካዊ ባህርያት ጠቋሚ ምልክቶችን ቢያስከትሉና ምልክቶቹም በጥቅም ላይ በዋሉ ጊዜ በቅንፍ ውስጥ ቢቀመጡ ይመረጣል፡፡ ጠቋሚ ምልክቶቹ የመብት ወሰን ጥያቄውን በፍጥነት ለመገንዘብ የሚያገለግሉ ካልሆኑ መካተት የለባቸውም፡፡
7. ከማመልከቻው የምዝገባ ቀን በኋላ የቀረበ በቀድሞ ማመልከቻ ውስጥ ከሚገኙት የመብት ወሰን ጥያቄዎች ጋር ያልተዛመደ የመብት ወሰን ጥያቄ በአመልካቹ ምርጫ እንደተሻሻለ ወይም እንደ አዲስ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡
8. በቀድሞ ማመልከቻ ላይ ሰፍሮ የነበረ ማናቸውም የመብት ወሰን ጥያቄ የተሰረዘ እንደሆነ የቀድሞውን የመብት ጥያቄ የመለያ ቁጥሩን በመጥቀስ “ተሠርዟል” የሚል ቃል ይደረግበታል፡፡

13. <u>ሥዕሎች</u>

1. ለፓተንት የቀረበ ማመልከቻ አካል የሆኑ ሥዕሎች የሚቀርቡበት ወረቀት ጥቅም ላይ የሚውለው ክፍል ስፋት ከ26.2 ሣ.ሜ በ17 ሣ.ሜ መብለጥ የለበትም፡፡ በእነኝህ ወረቀቶች በጥቅም ላይ በሚውለው ወይም በዋለው ቦታ ዙሪያ ከፈፍ ሊኖር አይገባም፡፡ የአነስተኛ ህዳጎች መጠን፣

   ከላይ 2 ነጥብ 5 ሣ.ሜ

   ከግራ ጎን 2 ነጥብ 5 ሣ.ሜ

   ከቀኝ ጎን 1 ነጥብ 5 ሣ.ሜ

   ከታች 1 ነጥብ ዜሮ ሣ.ሜ ይሆናል።

2. ሥዕሎች፣

   ሀ) አጥጋቢ የሆነ ቅጅ ለማውጣት እንዲቻል ቀለም አልባ በሆኑ በበቂ መጠን ደማቅና ጥቁር እንዲሁም ወጥ ስፋትና ግልፅነት ባላቸው መስመሮችና ጭረቶች ሊሰሩ ይገባል፤

   ለ) የአንድ ሥዕል ክፍል እይታ የመሪ መስመሮችንና የአመልካች ምልክቶችን ተነባቢነት በማይከለክል አኳኋን ተጋዳሚና ተደጋጋሚ መስመሮችን በመጠቀም መታየት ይኖርበታል፤

   ሐ) የሥዕሎች ስኬልና የግራፊክ አሰፋፈራቸው የግልጽነት ደረጃ ወደ ሁለት ሶስተኛ በተቀነሰ የፎቶ ግራፍ ቅጅአቸው ሁሉንም ዝርዝር ያለምንም ችግር በቀላሉ ለመለየት የሚረዳ መሆን አለበት፤ በተለየ ምክንያት ስኬሉ በሥዕሉ ላይ ተሰጥቶ ከሆነ በግራፍ መልክ መቀመጥ ይኖርበታል፤

   መ) በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ቁጥሮች፣ ፊደላት እና ጠቋሚ ምልክቶች ቀላልና ግልጽ መሆን ያለባቸው ሲሆን ቅንፎች፣ ክቦች እና የጥቅስ ምልክቶች ከቁጥሮች እና ከፊደላት ጋር በተያያዘ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋል አይኖርባቸውም፤

   ሠ) ለሥዕሉ ጥራት ሲባል የመጠን ልዩነት ማድረግ አስፈላጊ እስካልሆነ ድረስ የአንድ ሥዕል አካሎች መጠን እርስ በእርሳቸው ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፤

ረ) የቁጥሮችና የፊደላት ከፍታ ከዜሮ ነጥብ 32 ሣ.ሜ ማነስ የሌለበት ሲሆን ሥዕሎችን ለማመልከት የላቲን እና የተለመደም ሆኖ ሲገኝ የግሪክ ፊደላትን መጠቀም ይቻላል፤

ሰ) አንድ የሥዕል ወረቀት ብዙ ምስሎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወረቀቶች ላይ የተሣሉ ሥዕሎች አንድ ሙሉ ሥዕልን የሚመሠርቱ ከሆነ እነኝሁ ሥዕሎች የስእሉን ማናቸውም አካል ሳይደብቁ ሊቀናጁ በሚችሉበት መንገድ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ የተለያዩት ሥዕሎች በግልጽ አንዱ ከሌላው የሚለዩ ሆነው ቦታ ሳይባክን ሊቀናጁ የሚችሉ መሆን አለባቸው፤ ለየገፁ ከተሰጠው ቁጥር ጋር ሳይገናዘቡ ለተለያዩ ሥዕሎች ተከታታይነት ያለው የአረብ ቁጥር መሰጠት ይኖርበታል፤

ሸ) በመግለጫ ወይም በመብት ወሰን ጥያቄዎች ላይ ያልተገለጹ ጠቋሚ ምልክቶች በስዕሎች ላይ ወይም በሥዕሎች ላይ ያልተገለጹ ጠቋሚ ምልክቶች በመግለጫው ወይም በመብት ወስን ጥያቄዎች ላይ መታየት የለባቸውም፡፡ አንድ ዓይነት ገጽታዎች በጠቋሚ ምልክቶች ከተገለጹ ይህ ሁኔታ በማመልከቻው ውስጥ ያለምንም ለውጥ ስራ ላይ መዋል ይኖርበታል፤

ቀ) ስዕሎችን ለመረዳት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ማብራሪያ ጽሑፍ ተያይዞ መቅረብ የለበትም፡፡ እንደ "ዉሀ" "እንፋሎት" "ክፍት ነው" "ዝግ ነው" "በክፍል ሀሀ" ያለ ቃል ወይም ቃላት እንዲሁም በብሎክ ስኬማቲክ ወይም በፍሎውሺት ዲያግራም ውስጥ አጭርና ገላጭ ቃላት መካተት አይኖርባቸውም፤

በ) ስዕሎች ያረፉባቸው ገጾች በዚህ ደንብ አንቀጽ 16(7) በተደነገገው መሠረት ቁጥር ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

3. የፍሎው ሺት እና ዲያግራሞች ሥዕሎች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

14. <u>የፈጠራ አጭር ይዘት</u>

1. የፈጠራው አጭር ይዘት በአንድ የተወሰነ ጥበብ ዘርፍ ቀልጣፋ ፍለጋ ለማድረግ የሚያገለግል መሳሪያ በመሆን መዘጋጀት ያለበት ሆኖ ተጠቃሚው ሙሉ ማመልከቻውን ለመመልከት አስፈላጊ መሆኑን እና አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችለው ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡

2. የፈጠራው አጭር ይዘት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

ሀ) ከፈጠራው ጋር የሚዛመደውን የቴክኒክ መስክ የሚጠቁም እና ቴክኒካዊ ችግሩን፣ ፈጠራው ለችግሩ የሚሰጠውን ዋና መፍትሄ እና የፈጠራውን ዋና ጥቅም ወይም ጥቅሞች በግልጽ ለመረዳት እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ በመግለጫው በሙብት ወሰን ጥያቄውና በስዕሎች የተካተቱ የፈጠራው ገህድነት ማጠቃለያ፤

ለ) እንደአግባቡ በማመልከቻው ውስጥ ከተካተቱ የኬሚካል ፎርሙላዎች መካከል በተሻለ ሁኔታ ፈጠራውን የሚገልጽ የኬሚካል ፎርሙላ።

3. የፈጠራው ገህድነት በሚፈቅደው መጠን የፈጠራው አጭር ይዘት አጠር ያለ ሆኖ በፈጠራው ይገኛል ተብሎ ስለሚጠበቅ በጎ ጎን ወይም ዋጋ ወይም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ስለሚባልበት ሁኔታ መግለጫ መያዝ የለበትም።

4. በፈጠራው አጭር ይዘት የተገለፀና በማመልከቻው ውስጥ ባሉ ስዕሎች የተመለከተ እያንዳንዱ አብይ ቴክኒካዊ ባህርይ በቅንፍ ውስጥ የተቀመጡ ጠቋሚ ምልክቶችን ማስከተል አለበት፡፡

5. የፈጠራው አጭር ይዘት በአመልካቹ ከቀረቡት ሥዕሎች መካከል በይበልጥ ገላጭ ከሆነው ሥዕል ጋር አብሮ መሆን አለበት፡፡

15.<u>መለኪያዎች፣ ቃላቶች እና ምልክቶች</u>

1. የክብደት እና የርዝመት መለኪያዎች በሜትሪክ ሲስተም መገለጽ አለባቸው።
2. የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴንትግሬድ መገለጽ አለበት።
3. እፍጋት በሜትሪክ አሀድ መገለፅ ይኖርበታል።
4. ሙቀት፣ ኃይል፣ ብርሀን፣ ድምፅ እና መግነጢሳዊነት እንዲሁም የሂሳብ ፎርሙላዎችን እና የኤሌክትሪክ አሀዶችን ለማመልከት በጥቅም ላይ ያሉ አጠቃላይ ደንቦችን መከተል ያስፈልጋል። ለኬሚካል ፎርሙላዎች በአጠቃላይ አገልግሎት ላይ የዋሉ ምልክቶችን የአቶም ክብደቶችን እና የሞሎኪዊል ፎርሙላዎችን መገልገል ያስፈልጋል፡፡
5. በአንድ የጥበብ መስክ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙት የቴክኒክ ቃላትና ምልክቶች ብቻ በጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡
6. በማመልከቻ ውስጥ የቃላትና ምልክቶች አጠቃቀም መዛባት የለበትም፡፡

16.**የቅጅዎች ብዛትና የአቀራረብ መልክ**

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ 20(7) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማመልከቻዎችና ማናቸውም ተያይዘው የሚቀርቡ ማብራሪያዎች ወይም ሠነዶች በሦስት ቅጅ መቅረብ አለባቸው፡፡ ነገር ግን ኮሚሽኑ አመልካቹን ተጨማሪ ቅጂዎች እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡
2. ሁሉም የማመልከቻው ክፍሎች በፎቶግራፍ፣ በኤሌክትሮ ስታቲክ ሂደት፣ በፎቶ ኦፍ ሴትና በማይክሮ ፊልም በቀጥታ ሊባዙ በሚችሉበት መልክ መቅረብ አለባቸው፡፡
3. በማመልከቻው ውስጥ ያለ የእያንዳንዱ ወረቀት አንዱ ገጽ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡
4. ሁሉም የማመልከቻው ክፍሎች ተጣጣፊ፣ ጠንካራ፣ ነጭ፣ ለስላሣ፣ የማያንፀባርቅ እና ረጅም እድሜ በሚቆይ ወረቀት ላይ ሠፍረው መቅረብ አለባቸው፡፡
5. የወረቀቶች መጠን ኤ4 (29 ነጥብ 7 ሣ.ሜ × 21 ሣ.ሜ) መሆን አለበት።
6. የዚህ ደንብ አንቀጽ 13(1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የወረቀቶቹ አነስተኛ ህዳጎች እንደሚከተለው መሆን አለባቸው፡፡
   ሀ) ከመጀመሪያው ገፅ በስተቀር የሌሎቹ ገፆች በሙሉ የላይኛው ህዳግ 20 ሚ.ሜ፤
   ለ) የመጀመሪያው ገፅ የላይኛው ህዳግ 30 ሚ.ሜ፤
   ሐ) ወረቀቱ በሚጠረዝበት በኩል ያለው የጎን ህዳግ 25 ሚ.ሜ፤
   መ) ሌላኛው የጎን ህዳግ 20 ሚ.ሜ፤
   ሠ) የታችኛው ህዳግ 20 ሚ.ሜ፤
7. ሀ) የዓረባዊ ቁጥሮች በሁሉም ወረቀቶች አናት መሀከሉ ላይ በተከታታይ መፃፍ አለባቸው፡፡
   ለ) ለወረቀቶች ተከታታይ ቁጥር ሲስጥ የማመልከቻው ክፍሎች ጥያቄ፣ መግለጫ፣ የመብት ወሰን፣ አጭር መግለጫ እና ሥዕል በተራ ሊቀመጡ ይገባል፡፡
   ሐ) ለወረቀቶቹ ተከታታይነት ያለው ቁጥር አሰጣጥ ሶስት የተለያዩ የቁጥር አሰጣጥ ተራዎችን በመጠቀም ሆኖ የመጀመሪያው ተራ ለጥያቄው ብቻ የሚያገለግልና ከጥያቄው የመጀመሪያው ገፅ የሚጀምር ነው፡፡ ሁለተኛው ተራ ከመግለጫው የመጀመሪያ ገፅ የሚጀምርና የጥበቃ ወሰንን አካትቶ እስከ

አጭር ይዘቱ የመጨረሻ ገፅ የሚቀጥል ነው። ሦስተኛው ተራ ሥዕሎችን ለያዙ ገፆች ብቻ የሚያገለግልና ከስዕሎች የመጀመሪያ ገፅ የሚጀምር ነው፡፡

8. የማመልከቻው ጽሑፍ መተየብ ያለበት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግራፊክ ምልክቶች የኬሚካል ወይም የሂሣብ ፎርሙላዎች እና የተወሰኑ ካራክተሮች በእጅ ሊፃፉ ወይም ሊሣሉ ይችላሉ፡፡
9. ሥዕሎች ሲሣሉ ያለ ቀለም ዘላቂነት ባለው ጥቁር በበቂ መጠን ወፈር እና ደመቅ ባሉ አንድ ወጥ ስፋት እና በግልጽ በተቀመጡ መስመሮችና ጭረቶች መሆን አለበት፡፡

17.<u>የፈጠራ አሀዳዊነት</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 9(2) ከሚከተሉት ሦስት አማራጮች በተለይ፣
   ሀ) ለአንድ ምርት ከሚቀርብ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በተጨማሪ በተለይ የተጠቀሰውን ምርት ለማምረት የሚረዳ የምርት ሂደት ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ እንዲሁም የተጠቀሰውን ምርት የመጠቀም ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ማካተትን፤ ወይም
   ለ) ለአንድ የምርት ሂደት ከሚቀርብ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በተጨማሪ ሂደቱን ተግባራዊ ለማድረግ በተለይ ለተዘጋጀ መሣሪያ ወይም ዘዴ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ማካተትን፤ ወይም
   ሐ) ለአንድ ምርት ከሚቀርብ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በተጨማሪ በተለይ የተጠቀሰውን ምርት ለማምረት የሚረዳ የምርት ሂደት ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ እና ሂደቱን ተግባራዊ ለማድረግ ለማከናወን በተለይ ለተዘጋጀ መሣሪያ ወይም ዘዴ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ማካተትን የሚፈቅድ ሆኖ ሊተረጎም ይገባል፡፡
2. የአዋጁ አንቀጽ 9(2) እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ በአንድ መደብ የሚፈረጁ ሆኖም በቀጥታ በአንድ አጠቃላይ የመብት ወሰን የማይካተቱ ሁለት ወይም ከዛ በላይ ራሳቸውን የቻሉ የመብት ወሰን ጥያቄዎችን ማቅረብ ይፈቀዳል፡፡
3. የአዋጁ አንቀጽ 9(2) እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ራሱን በቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ ስር የተመለከቱት የተለያዩ የፈጠራውን መስኮች

የሚመለከቱ ተገቢ ቁጥር ያላቸው ጥገኛ የመብት ወሰን ጥያቄዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

4. በአዋጁ አንቀጽ 9(2) መሠረት የፈጠራ አሀዳዊነት መመዘኛ ለማያሟላ ማመልከቻ ፓተንት መስጠት ለፓተንቱ መሰረዝ ምክንያት አይሆንም፡፡

18. **ማመልከቻን ስለማሻሻልና መከፋፈል**

1. ማሻሻያው በመጀመሪያው ማመልከቻ ከተገለፀው የሆነ ነገር የማያስከትል ከሆነ አመልካቹ ፓተንት እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ማመልከቻውን ማሻሻል ይችላል፡፡
2. እያንዳንዱ ክፋይ ማመልከቻ በመጀመሪያው ማመልከቻ ላይ ከተገለጸው ውጪ የሆነ ነገር የማያስከትል ከሆነ ፓተንት እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ አመልካቹ ማመልከቻውን ወደ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ማመልከቻዎች ሊከፋፍል ይችላል።
3. እያንዳንዱ ክፋይ ማመልከቻ የመጀመሪያው ማመልከቻ የምዝገባ ቀንና እንደአግባቡ የመጀመሪያው ማመልከቻ የቀዳሚነት ቀን ይኖረዋል፡፡
4. አንድ ክፋይ ማመልከቻ የመጀመሪያውን ማመልከቻ የሚጠቅስ ክፍል መያዝ አለበት።
5. አመልካቹ ክፋይ ማመልከቻው የመጀመሪያው ማመልከቻ ማናቸውም የቀዳሚነት ጥያቄ ተጠቃሚ እንዲሆን ከፈለገ ክፋይ ማመልከቻው ይህንኑ የሚያመለክት ጥያቄ መያዝ አለበት፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የመጀመሪያው ማመልከቻ የቀዳሚነት መግለጫ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 20 መሠረት የቀረቡ ሠነዶች ለክፋይ ማመልከቻው የሚያገለግሉ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡
6. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቀድመው የገቡ ማመልከቻዎች ቀዳሚነት ለመጀመሪያው ማመልከቻ የተጠየቀ እንደሆነ ክፋይ ማመልከቻው ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው አግባብ ካለው /ካላቸው የቀዳሚነት ጥያቄ/ ጥያቄዎች ነው።

19. **አስቀድሞ ለህዝብ የተገለፀ ፈጠራ እንደቀደምት ጥበብ ስለማይቆጠርበት ሁኔታ**

በአዋጁ አንቀጽ 3(3) መሠረት ቀደም ሲል የተከናወነ ፈጠራውን ገሀድ የማድረግ ተግባር እንደቀደምት ጥበብ እንዳይቆጠር ፍላጎት ያለው አመልካች ይህንኑ በማመልከቻው ላይ መግለጽ እና ከማመልከቻው ጋር ወይም ማመልከቻው በገባ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ የገሀድነቱን ሙሉ መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡ ለገሀድነት የበቃው በኢግዚቢሽን ላይ ከሆነ አመልካቹ ከላይ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ

የኢግዚቢሽኑ ኃላፊ በሆነው አካል የተዘጋጀና የተፈረመ የኢግዚቢሽኑን ልዩ ባህርይ የሚገልጽና በእርግጥም ፈጠራው በኢግዚቢሽኑ መቅረቡን የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት ማቅረብ አለበት።

20. **<u>ቀዳሚነትን ስለማሳወቅና ስለቀዳሚ ማመልከቻ ትርጉም</u>**

1. በአዋጁ አንቀጽ 11(2) የተገለጸው መግለጫ የሚከተሉትን ማመልከት አለበት፤
   ሀ) የቀዳሚውን ማመልከቻ ቀን፤
   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀዳሚውን ማመልከቻ ቁጥር፤
   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ ማመልከቻው የተመደበበትን የዓለም አቀፍ ፓተንት ምደባ መለያ፤
   መ) ቀዳሚ ማመልከቻው ቀርቦበት የነበረው ሀገር ወይም ቀዳሚ ማመልከቻው አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ማመልከቻ ከሆነ በማመልከቻው የተመለከቱትን ሀገሮች፤
   ሠ) ቀዳሚ ማመልከቻው አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ከሆነ ማመልከቻው የቀረበበት ጽሕፈት ቤት፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 11(2) መሠረት የተገለጸው መግለጫ በሚቀርብበት ወቅት የቀዳሚ ማመልከቻው ቁጥር የማይታወቅ ከሆነ መግለጫውን የያዘው ማመልከቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ ባሉ ሶስት ወራት ውስጥ ቁጥሩ መገለጽ አለበት፡፡
3. ቀዳሚ ማመልከቻው የዓለም አቀፍ የፓተንት ምደባ መለያ ያልተሰጠው ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለጸው መግለጫ በቀረበበት ጊዜም መለያው ያልተሰጠው ከሆነ አመልካቹ በመግለጫው ላይ ይህንኑ መግለጽና መለያው እንደተሰጠ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. አመልካቹ ፓተንት ከመስጠቱ አስቀድሞ በማንኛውም ጊዜ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) የተገለጸውን መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ይችላል፡፡
5. በአዋጁ አንቀጽ 11(2) የተገለጸው የቀዳሚ ማመልከቻ የተረጋገጠ ቅጅ ማቅረቢያ ጊዜ ኮሚሽኑ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ወራት ይሆናል፡፡ ቅጅው ለሌላ ማመልከቻ የተሰጠ ከሆነ አመልካቹ ይህንኑ በማመልከት ምላሽ መስጠት ይችላል፡፡

6. ቀዳሚ ማመልከቻው የቀረበው ከእንግሊዝኛ ወይም ከአማርኛ በተለየ ቋንቋ ሲሆን አመልካቹ የቀዳሚ ማመልከቻውን የእንግሊዝኛ ወይም የአማርኛ ትርጉም በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) የተገለፀው ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
7. ኮሚሽኑ የተለየ ጥያቄ ካላቀረበ በስተቀር የቀዳሚነት ማመልከቻውና ማናቸውም የዚሁ ትርጉም በአንድ ቅጅ ብቻ ይቀርባል፡፡

21.<u>የዉጪ አገር አመልካች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 10(2) እና በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረቡ ሰነዶች የሚያገለግሉት የፓተንት ማመልከቻ የቀረበበትን ፈጠራ አዲስነት እና ፈጠራዊ ብቃት ግምገማ ለማገዝ ብቻ ይሆናል፡፡
2. የውጭ አገር አመልካች በዚህ አንቀጽ መሠረት ባቀረባቸው ሰነዶች ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. በኢትዮጵያ ውስጥ የመኖሪያ ቦታ ወይም የንግድ ጽሕፈት ቤት በሌለው የውጭ ዜጋ፤ ኢንተርፕራይዝ ወይም ሌላ የውጪ ድርጅት ለፓተንት ማመልከቻ ሲቀርብና ኮሚሽኑ ጥርጣሬ ሲያድርበት አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፣
   ሀ) የአመልካቹን ዜግነት የሚመለከት ሰርተፊኬት፤
   ለ) የውጭ ኢንተርፕራይዙን ወይም ሌላ የውጭ ድርጅቱን ዋና ጽሕፈት ቤት መቀመጫ የሚመለከት ሠርተፊኬት፤
   ሐ) የአንድ የውጭ ዜጋ፣ የውጭ ኢንተርፕራይዝ ወይም የሌላ የውጭ ሀገር ድርጅት ለዜጎቿ ተፈጻሚ በሚሆንበት መልክ የኢትዮጵያ ዜጎች ወይም ድርጅቶች በሀገሪቱ ፓተንት የማግኘት መብት እንዳላቸው እውቅና የምትሰጥ መሆኑን ማረጋገጫ፡፡

22.<u>ተዛማጅ የዉጪ ማመልከቻ፣ ፓተንት እና ሌሎች የጥበቃ አይነቶችን አስመልክቶ መረጃ ስለማቅረቢያ ጊዜ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት የተጠየቀ መረጃን የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ወር ማነስ ወይም ከስድስት ወር መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም በአመልካቹ አሳማኝ ጥያቄ ኮሚሽኑ የጊዜ ገደቡን ሊያራዝም ይችላል፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት የተጠየቁትን ሰነዶች አመልካቹ ሊያገኛቸው እንዳልቻለ መልስ ከሰጠ ኮሚሽኑ የማመልከቻውን ምርመራ ሂደት ሰነዶቹ እስከሚቀርቡበት ጊዜ ድረስ ሊያግደው ይችላል፡፡

23. ማመልከቻን ስለመተው

1. አንድ ማመልከቻ አመልካቹ በፈረመበትና ለኮሚሽኑ በቀረበ የጽሁፍ መግለጫ ይተዋል፡፡
2. ማመልከቻው ቢተውም የማመልከቻ ክፍያው ተመላሽ አይሆንም ፡፡

24. ማመልከቻ ላይ ምልክት ስለማድረግ

1. ማመልከቻው እንደደረሰ ኮሚሽኑ ማመልከቻው በሚያቅፈው እያንዳንዱ ሰነድ ላይ ማመልከቻው የደረሰበትን እርግጠኛ ቀንና ኢት የሚሉ ፊደሎች እዝባር፣ ፓ የሚል ፊደል እዝባር፣ የመጀመሪያው ወረቀት የደረሰበት ዓመት የመጨረሻ ሁለት ቁጥሮች እዝባርና ማመልከቻዎች ሲደርሱ የሚሰጡ ተከታታይነት ያላቸው አምስት ቁጥሮች የያዘ የማመልከቻ ቁጥር ማስፈር አለበት፡፡ እርማቶቹ ወይም ዘግይተው የገቡ ሰነዶች በሌላ ቀን ሲደርሱ ኮሚሽኑ የደረሰበትን እርግጠኛ ቀን አግባብ ባለው ቦታ የፓተንት ጥያቄ በቀረበበት ሰነድ (ቅጽ ቁጥር 01) ላይ ያሰፍራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት ለማመልከቻ የተሰጠ ቁጥር ማመልከቻውን አስመልክቶ በሚደረግ የደብዳቤ ልውውጥ ላይ መጠቀስ አለበት፡፡

25. የምዝገባ ቀን መስጠትና ማሳወቅ

1. ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ለመሰጠት ማመልከቻው የአዋጁን አንቀጽ 12(1) መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆኑን ይመረምራል፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 12(2) መሠረት የሚቀርብ ማናቸውም ማሻሻያ የማቅረብ ጥሪ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን ተፈላጊውን ማሻሻያ መግለጽና ማሻሻያው ጥሪው ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከተመደበው ክፍያ ጋር እንዲቀርብ መጠየቅ አለበት፡፡
3. ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ከሰጠ በኋላ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በአዋጁ አንቀጽ 12(2) መሠረት ማመልከቻው እንዳልቀረበ የተቆጠረ እንደሆነ ኮሚሽኑ ለአመልካቹ ምክንያቶችን በመዘርዘር በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል 2

## ስለማመልከቻ ምርመራ

26.**መርማሪ ከመሆን ስለመገለል**

አንድ መርማሪ በራሱ ፍላጎት፣ ወይም በአመልካቹ ወይም በሌላ ማናቸውም ጉዳዩ በሚመለከተው ወገን በሚቀርብ ጥያቄ ከምርመራ ሥራው የሚገለለው፣

1. ከአመልካቹ ወይም ከፓተንት ወኪሉ ጋር የቅርብ ዝምድና ያለው ሆኖ ሲገኝ፣
2. በፓተንት ማመልከቻው ላይ ጥቅም ያለው ሲሆን፣
3. ከአመልካቹ ወይም ከፓተንት ወኪሉ ጋር ያለው ማንኛውም ሌላ አይነት ግንኙነት አድሎአዊ ያልሆነ የማመልከቻ ምርመራ ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል ሆኖ ሲገኝ ይሆናል፡፡

27.**የፎርማሊቲ ምርመራ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 9(3) ና 4(ሀ) እና ይህንኑ በተመለከተ በደንቡ ከተገለጹት መሟላት ከሚገባቸው ሁኔታዎች በተጨማሪ የአዋጁ አንቀጽ 5፣ 8፣ 9(7) እና (8) እንዲሁም 10 ለአዋጁ ዓላማ ፎርማሊቲን አስመልክቶ መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 13(2) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው ያልተገኙ እንደሆነ ኮሚሽኑ አመልካቹን በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ማሻሻያ ከተመደበው ክፍያ ጋር እንዲያቀርብ በጽሁፍ ይጠራዋል፡፡
3. አመልካቹ የተጓደለውን ለማሟላት በተደረገው ጥሪ መሰረት ምላሽ ያላቀረበ ሲሆን ወይም አመልካቹ ማሻሻያ ያቀረበ ቢሆንም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጹት ሁኔታዎች ያልተሟሉ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ሲያምን ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ለአመልካቹ ምክንያቱን ገልጾ በጽሁፍ ያሳውቃል።
4. የማመልከቻው ውድቅ መሆን የምዝገባውን ቀን ተቀባይነት አያሳጣውም፡፡

28.**የስረ-ነገር ምርመራ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 13(3) መሠረት ኮሚሽኑ በሚሰይማቸው ልምድ ባላቸው የቴክኒክና የህግ ኤክስፐርቶች አማካኝነት የሥረ-ነገር ምርመራ ይከናወናል፡፡
2. የፍለጋና የምርመራ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ኮሚሽኑ ማመልከቻውን አግባብ ካላቸው ሰነዶች ጋር በማያያዝ በአዋጁ አንቀጽ 13(3) መሠረት የሚከናወነውን

የምርመራ ተግባር በተመለከተ ከኮሚሽኑ ጋር ስምምነት ላደረገ የምርመራ ባለሥልጣን መላክና የፍለጋና የምርመራ ዘገባ እንዲላክለት መጠየቅ ይችላል፡፡

3. አንድ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 3፣ 4፣ 7፣ 9(2)፣ (4)(ለ) (ሐ) እና (5) እና አግባብነት ባላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆኑን ይመረመራል፡፡
4. ኮሚሽኑ የፍለጋና ምርመራ ሪፖርት ውጤትን ግምት ውስጥ በማስገባት በአዋጁ እና በዚህ ደንብ የተገፁት መመዘኛዎች ያልተሟሉ መሆናቸውን ሲያምን አመልካቹን በመጥራት (አስፈላጊ ከሆነ ጥሪው ተደጋጋሚ ሊሆን ይችላል) ማመልከቻውን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አሻሽሎ ወይም ከፋፍሎ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ይጠይቀዋል፡፡ የጊዜ ገደቡ ለአመልካቹ ጥሪ ከሚደረግበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ወር ያላነሰ ወይም ከስድስት ወር ያልበለጠ ይሆናል፡፡ ጥሪውም የሚከናወነው በቅጽ 2 መሠረት ነው፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 መሠረት የሚደረግ ማናቸውም ማሻሻያ ከተወሰነለት ክፍያ ጋር መከናወን አለበት፡፡
6. አመልካቹ በጥሪው መሠረት ተገቢውን ሳያደርግ ሲቀር ወይም አመልካቹ ያቀረበው ማንኛውም አስተያየት፣ ማሻሻያ ወይም ክፍፍል የምርመራና ፍለጋ ሪፖርቱን ውጤት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲታይ በአዋጁና በዚህ ደንብ የተዘረዘሩ ሁኔታዎችን የማያሟላ መሆኑ ሲታመን ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል፡፡ ይህንኑም ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል 3

## ፓተንት ስለመስጠትና ስለፓተንት ይዘት

### 29. ፓተንት የመስጠት ወይም የመከልከል ውሳኔ

1. ተመሳሳይ የምዝገባ ቀን ወይም እንደ አግባቡ ተመሳሳይ የቀዳሚነት ቀን ያላቸው አንድን ፈጠራ የሚመለከቱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማመልከቻዎች በአንድ አመልካች ሲቀርቡ ኮሚሽኑ በዚሁ ምክንያት ከአንድ በላይ ለሆኑ ማመልከቻዎች ፓተንት አልሰጥም ብሎ መከልከል ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ የፍለጋና ምርመራ ሪፖርት ውጤትን ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ደንብ አንቀጽ 28 የተጠቀሰውን መሠረት በማድረግ የአዋጁ አንቀጽ 13(3) ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያምን ፓተንት ይሰጣል፡፡

3. ኮሚሽኑ ፓተንት ለመስጠት ወይም ለመከልከል የሰጠውን ውሳኔ ለውሳኔው መሠረት ከሆነው የፍለጋና ምርመራ ሪፖርት ቅጅ ጋር በማያያዝ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡ በተጨማሪም ውሳኔው የፓተንት መሰጠትን የሚከለክል ሲሆን ዝርዝር ምክንያቶቹ መገለጽ አለባቸው፡፡ ውሳኔው ፓተንት ለመስጠት ሲሆን አመልካቹ ውሳኔውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ የፓተንትና የህትመት ክፍያ እንዲፈጽም ይጠይቃል፡፡

30.<u>ፓተንት ስለመስጠት</u>

1. የፓተንትና የህትመት ክፍያ ፓተንት ለመስጠት መወሰኑ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ የተከፈለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 14(1) እና በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት ኮሚሽኑ ፓተንት ይሰጣል፡፡
2. ኮሚሽኑ ለእያንዳንዱ ለሚሰጠው ፓተንት እንደ አሰጣጡ ቅደም ተከተል የፓተንት የህትመት ቁጥር ይሰጣል፡፡
3. ፓተንቱ፣
   ሀ) በቅጽ ቁጥር 3 መሠረት የሚሰጥና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ከተገለጸው መረጃ በተጨማሪ የፓተንቱን ህትመት ቀን፣ በቀደምት ጥበብ የተመለከቱ ሰነዶች ዋቢዎች፣ የፈጠራው መግለጫ፣ የመብት ወሰንና ካሉም ስዕሎችን ያካትታል፤
   ለ) እንደተሰጠ የሚገመተው ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 14(2)(ሀ) ስለፓተንቱ መሰጠት ጠቅሶ በህትመት ባወጣበት ቀን ነው፡፡

31.<u>ፓተንት ስለመሰጠቱ ጠቅሶ ስለማተም</u>

ፓተንት ስለመሰጠቱ ተጠቅሶ የሚወጣ ህትመት፤

1. የፓተንቱን ቁጥር፣
2. የፓተንት ባለቤቱን ስምና አድራሻ፣
3. በፓተንቱ ውስጥ ስሙ እንዳይጠቀስ ካልጠየቀ በስተቀር የፈጠራ ሰራተኛውን ስምና አድራሻ፤
4. በኖረ ጊዜ የወኪሉን ስምና አድራሻ፤
5. የማመልከቻውን የምዝገባ ቀንና ቁጥር፤

6. ቀዳሚነት ከተጠየቀና ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ ቀዳሚነቱን የሚመለከት መግለጫ፣ የቀዳሚነት ቀንና ቀዳሚው ማመልከቻ የገባበትን ሀገር ወይም ሀገሮች ስም፣
7. ፓተንት የተሰጠበትን ትክክለኛ ቀን፣
8. የፈጠራውን ርዕስ፣
9. የፈጠራውን አጭር ይዘት፣
10. በኖረ ጊዜ ከስዕሎቹ መካከል በይበልጥ ገላጭ የሆነውን እንዲሁም፤
11. የዓለም አቀፍ ፓተንት ምደባ ምልክትን ማካተት አለበት፡፡

32. <u>የፓተንት ሰርተፊኬት ስለመስጠት</u>

የፓተንት መሰጠት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በቅጽ ቁጥር 5 ላይ መዘጋጀት፣ በኮሚሽኑ መፈረምና

1. የፓተንቱን ቁጥር፣
2. የፓተንት ባለቤቱን ስምና አድራሻ፣
3. የምዝገባውን ቀንና እንደአግባቡ የማመልከቻውን የቀዳሚነት ቀን፣
4. ፓተንት የተሰጠበትን ትክክለኛ ቀን እና፤
5. የፈጠራውን ርዕስ ማካተት አለበት፡፡

33. <u>ስለፓተንት መብት መራዘም</u>

በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የፓተንት መብት ጥበቃ ዘመን የማራዘም ጥያቄ በጽሁፍ ለኮሚሽኑ መቅረብና ፈጠራው በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ የዋለበትን ዝርዝር ሁኔታ ከሚገልጽ በፓተንት ባለቤቱ የተፈረመበት መግለጫ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## <u>ክፍል 4</u>

## <u>ፈቃድ በተሰጠው ሰው በፓተንት የሚጠበቅን ፈጠራ ጥቅም ላይ ስለማዋል</u>

34. <u>በፓተንት የሚጠበቅን ፈጠራ በመንግሥት ወይም በመንግሥት ሥልጣን በተሰጣቸው ሦስተኛ ወገኖች ጥቅም ላይ ስለማዋል</u>

1. ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 25(2) መሠረት ውሳኔ ከመስጠቱ አስቀድሞ ለባለፓተንቱ፣ ለግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚዎች እና ለማንኛውም ተሳትፎው ጠቃሚ ይሆናል ብሎ ለሚገምተው ወገን ጉዳያቸው ከሚሰማበት ቀን በፊት ቢያንስ ሀያ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡፡ ባለፓተንቱ

ፓተንቱን በፈቃድ ለወሰዱ ወገኖች በሙሉ የጉዳዩን መሰማት አስመልክቶ የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት ያለበት ሲሆን እነሱም በጉዳዩ የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡

2. ኮሚሽኑ ጉዳዩን ካየ በኋላ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸውን ነጥቦች እና ፈጠራው በአዋጁ አንቀጽ 25(2) መሠረት አገልግሎት ላይ እንዲውል ከወሰነ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ በጽሑፍ መግለጽ አለበት፡፡
3. ኮሚሽኑ ውሳኔውን መመዝገብ፣ ማሳተም እንዲሁም ባለፓተንቱ እና ሌሎች በጉዳዩ የገቡ ወገኖች በጽሑፍ እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፡፡
4. ኮሚሽኑ የመጠቀሚያ ክፍያን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ከተጠየቀበት የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር የፍርድ ቤቱን የመጨረሻውን የይግባኝ ውሳኔ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ኮሚሽኑም ውሳኔውን ይመዘግባል፣ በሕትመት ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

35.<u>የግዴታ ፈቃድ ጥያቄ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 29 መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ የግዴታ ፈቃድ ጥያቄ በቅፅ ቁጥር 6 ተሞልቶ ከተመደበው ክፍያ ጋር እና

1. ፈጠራው በሌላ ፓተንት በተሰጠው ፈጠራ ላይ ጥገኛ መሆኑንና ይህንኑ ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ ካልተጠቀመ ፈጠራውን ለመጠቀም እንደሚያስቸግር ከሚገልጽ ማስረጃ፤
2. ባለፓተንቱ ከግዴታ ፈቃድ ጠያቂው የፈቃድ ውል ጥያቄ የደረሰው መሆኑንና የግዴታ ፈቃድ ጠያቂው ፈቃዱን በተገቢው ሁኔታና ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ያልቻለ መሆኑን ከሚገልጽ ማስረጃ፤
3. የግዴታ ፈቃድ ጠያቂው ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ በስራ ላይ ለማዋል የተለመውን የስራ እቅድ ፈጠራውን በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ለማዋል ብቃት እንዳለው ከሚገልጽ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

36.<u>የግዴታ ፈቃድ ጥያቄን ስለመቀበል ወይም አለመቀበል</u>

1. ኮሚሽኑ የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉ ሦስት ወራት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 29 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 35 የተገለጹት ሁኔታዎች ጠቅለል ባለ አኳኋን መሟላታቸውና አለመሟላታቸውን ይመረምራል፡፡

2. ኮሚሽኑ በምርመራው ወቅት፤
   ሀ) መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ያልተሟሉ ሆኖ ሲያገኝ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ላቀረበው ግለሰብ ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል፤
   ለ) መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ተሟልተው ሲያገኝ ወዲያውኑ ለባለፓተንቱ፣ ለግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚዎች እና በአዋጁ አንቀጽ 25(2) መሠረት ፓተንት የተሰጠበትን ፈጠራ ጥቅም ላይ ላዋሉ ሰዎች የጥያቄውን ቅጅ መላክና ጥሪው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ያላቸውን አስተያየት ለኮሚሽኑ በጽሑፍ እንዲያቀርቡ መጋበዝ አለበት፡፡
3. ባለፓተንቱ ወዲያውኑ ለሁሉም ፈቃድ ተቀባዮች ስለጥያቄው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ፈቃድ ተቀባዮቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ጥሪ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ ያላቸውን አስተያየት በጽሑፍ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡
4. ኮሚሽኑ ለግዴታ ፈቃድ ጠያቂው ወዲያውኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት የቀረቡትን አስተያየቶች ያሳውቃል፡፡
5. ኮሚሽኑ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን በመወሰን የግዴታ ፈቃድ የጠየቀውን ግለሰብ፣ ባለፓተንቱን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት አስተያየታቸውን ያቀረቡ ግለሰቦች ይጠራል ይህንኑም ጉዳዩ የሚሰማበት ቀን ከመድረሱ ከአንድ ወር በፊት በጽሑፍ ያሳውቃል ፡፡

37. <u>የግዴታ ፈቃድ የመስጠት ወይም የመከልከል ውሣኔ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 36(5) መሠረት ጉዳዩ ከተሰማ በኋላ ኮሚሽኑ የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት የሚያበቁት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ፈቃዱን ይሰጣል፣ ካልሆነ ግን ይከለክላል፡፡
2. የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል የተሰጠው ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ለውሳኔው መሰረት የሆኑትን ምክንያቶች መያዝ ይኖርበታል ውሳኔው የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት ሲሆን፣
   ሀ) ፈቃድ የተሰጠበትን ጊዜ ገደብ፤
   ለ) ፈቃዱ በአዋጁ አንቀጽ 22(1) ከተገለጹት ተግባራት የትኞቹን እንደሚሸፍን፤

ሐ) የግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚው ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጀመርበትን የጊዜ ገደብ፣ እንዲሁም

መ) የመጠቀሚያ ክፍያ አፈፃፀም ሁኔታዎችን መዘርዘር አለበት፡፡

3. ኮሚሽኑ የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል የደረሰበትን ውሳኔ በመመዝገብ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ የውሳኔውን ቅጅ የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው ለጠየቀው ሰው፤ ለባለፓተንቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 36(2) እና (3) መሠረት አስተያየታቸውን ላቀረቡ ሰዎች ይልካል፡፡

38.<u>ስለፓተንት መሰረዝ</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 36(1) ድንጋጌ ተፈፃሚነት በተወሰኑ የጥበቃ ወሰን ጥያቄዎች ላይ ብቻ ወይም በተወሰኑ የጥበቃ ወሰን ጥያቄ አካሎች ላይ ሲሆን እነኘህ የጥበቃ ወሰን ጥያቄዎች ወይም የጥበቃ ወሰን አካሎች ይሰረዛሉ፡፡

2. ባለፓተንቱ የፓተንት መሰረዝን አስመልክቶ በፍርድ ቤት ስለተጀመረ ጉዳይ ለማንኛውም ፈቃድ ተቀባይ በፅሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ የፓተንት ስረዛን ጥያቄ ያቀረበው ወገን በአዋጁ አንቀጽ 30 መሠረት ለተሰጠ የግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚዎች በጽሑፍ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን ለፓተንቱ መሰረዝ የቀረበው ምክንያት ባለፓተንቱ ወይም የእርሱ ወራሽ የፈጠራው ሠራተኛ ወይም የሱ ሕጋዊ ወራሽ አይደለም በሚል ከሆነ በፓተንቱ ላይ መብት አለው ለሚባል ወገን በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

<u>ምዕራፍ 3</u>

<u>ስለግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት</u>

39.<u>ከፓተንት ጋር ስለተዛመዱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት</u>

1. የአዋጁ አንቀፅ 3(1)፣ (3) እና (4) በግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

2. የአዋጁ አንቀጽ 16 በግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀቶች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

3. አንድ ጉዳይ የአዋጁን አንቀፅ 45 ከአንቀፅ 36 ጋር በማጣመር በሚታይበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በሚከተሉት ምክንያቶች የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትን ይሰርዛል፤

ሀ) የአዋጁ አንቀፅ 39 እና 45 ድንጋጌዎች ከአንቀፅ 3(5) ጋር በመጣመር ሲታዩ ጥበቃ እንዲደረግለት የቀረበው ፈጠራ ለግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ብቁ ሳይሆን፤

ለ) የፈጠራው መግለጫና የመብት ወሰን ጥያቄዎች አንቀፅ 45፣ አንቀጽ 9(4) (ለ) እና (ሐ) እና ከዚሁ ጋር በሚዛመዱ ደንቦች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች የማያሟሉ ሲሆን፤

ሐ) ፈጠራውን ለመረዳት አስፈላጊ የሆነ ማንኛውም ሥዕል ሳይቀርብ ሲቀር፤

መ) የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀቱ ባለቤት የፈጠራ ሠራተኛው ወይም የሱ ሕጋዊ ወራሽ ሳይሆን፤

ሠ) በአዋጁ አንቀፅ 40 መሠረት ጥበቃ እንዲደረግለት የቀረበው ፈጠራ ለጥበቃ ብቁ ያልነበረ ሲሆን፡፡

4. ከዚህ በታች የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ ምዕራፍ ሁለት በተዘረዘሩት አንቀጾች የተገለፁት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፤

ሀ) በደንቡ አንቀፅ 24 ላይ የተገለጸው ፊደል “ፓ” “ግልሞ” ሆኖ እንዲነበብ፤

ለ) የዚህ ደንብ አንቀፅ 28 ተፈፃሚነት አይኖረውም፣ እንዲሁም

ሐ) በደንቡ አንቀጽ 38 የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ 36(1)፣ የአዋጁን አንቀጽ 45 እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የሚጠቅስ ሆኖ ይነበባል ።

5. በአዋጁ አንቀጽ 43 መሠረት የሚቀርብ የፓተንትና የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን የማለዋወጥ ጥያቄ በአመልካቹ ተፈርሞ ከተመደበው ክፍያ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት። ጥያቄው በቀረበ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ኮሚሽኑ ውሳኔውን በጽሑፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ እና ጥያቄውን ካልተቀበለ ምክንያቱን መግለጽ አለበት፡፡

## ምዕራፍ 4

## ስለ ኢንዱስትሪያዊ ንድፎች

### 40. ከፓተንት ጋር ስለተዛመዱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት

የዚህ ደንብ አንቀጽ 20፣ 23 እና 24 እንደአግባብነቱ በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፣ ለዚሁ ሲባል በዚሁ ደንብ አንቀጽ 24(1) የተገለጸው ፊደል “ፓ” “ኢን” ተብሎ ይነበባል።

41. **ኢንዱስትሪያዊ ንድፍን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ**

1. ኢንዱስትሪያዊ ንድፍን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በቅጽ ቁጥር 7 ተሞልቶ በእያንዳንዱ አመልካች መፈረም አለበት።
2. ማመልከቻው የእያንዳንዱን አመልካች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነትና መኖሪያ መያዝ ይኖርበታል።
3. አመልካቹ ኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ያመነጨው ሰው ከሆነ ጥያቄው ይህንኑ የሚያመለክት መግለጫ መያዝ አለበት። አመልካቹ ሌላ ሰው ከሆነ ጥያቄው የእያንዳንዱን የፈጠራ ሠራተኛ ስምና አድራሻ ማመልከትና አመልካቹ ኢንዱስትሪያዊ ንድፉን በስሙ ለማስመዝገብ ባለመብት መሆኑን የሚገልጽ ማረጋገጫ መያዝ ይኖርበታል፡፡
4. አመልካቹ በወኪል የተወከለ ከሆነ ጥያቄው ይህንኑ ማመልከትና የወኪሉን ስምና አድራሻ መያዝ ይኖርበታል።

42. **ስለመግለጫዎችና ስለናሙናዎች ብዛትና መጠን**

1. የሚከተሉት ከማመልከቻው ጋር መያያዝ አለባቸው
   ሀ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ባለ ሁለት ገጽታ ከሆነ አራት ግራፊክ መግለጫዎች ወይም አራት ሥዕሎች፣ ወይም ንድፎች፣ ወይም
   ለ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ባለሦስት ገጽታ ከሆነ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ እያንዳንዱ የተለያዩ ጎኖች አራት ግራፊክ መግለጫዎች ወይም አራት ሥእሎች ወይም ንድፎች፣ እና
   ሐ) የሕትመት መጠኑ በኮሚሽኑ ተገቢ ነው ተብሎ የሚወሰን የማተሚያ ቅርጽ ወይም የማተሚያ ቅርጾች ፡፡
2. የናሙና መጠን ከ20 ሴ.ሜ × 20 ሴ.ሜ × 20 ሴ.ሜ መብለጥ የለበትም ፡፡ ማንኛውም የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የግራፊክ መግለጫ፣ ሥዕል ወይም ንድፍ ከ10 ሴ.ሜ × 20 ሴ.ሜ መብለጥ የለበትም፡፡ መግለጫዎቹ፣ ሥእሎቹ ወይም ንድፎቹ የኤ4 መጠን ባላቸው ጠንካራና ረጅም እድሜ በሚቆዩ አራት ወረቀቶች ላይ መለጠፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ሥዕሎችና ንድፎች በጥቁር ቀለም መሠራት አለባቸው።

## 43.<u>የምዝገባ ቀን ስለመስጠት፣ ስለማሳወቅ እና ምርመራ</u>

1. ኮሚሽኑ ማመልከቻውን በተቀበለበት ጊዜ ማመልከቻው ያመልካቹን ማንነት ለማረጋገጥ የሚረዳ ጥቆማ እና ተፈላጊውን ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ያካተተውን እቃ ግራፊክ መግለጫ የያዘ ሲሆን ማመልከቻውን የተቀበለበትን ቀን የምዝገባ ቀን አድርጎ ይወስደዋል። የአዋጁ አንቀጽ 12(2) እንደአግባቡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
2. በአዋጁ አንቀጽ 12(2) እና 51 እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማናቸውም የማሻሻያ ጥሪ በጽሑፍ ሆኖ ጥያቄው የሚፈለገውን ማሻሻያ ወይም ማሻሻያዎች ምንነት ይዞ ከተመደበው ክፍያ ጋር በሁለት ወር ውስጥ እንዲቀርብ የሚጠይቅ መሆን አለበት።
3. ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ከሰጠ በኋላ ይህንኑ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ማመልከቻው በአዋጁ አንቀጽ 12(2) እና አንቀጽ 51 እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከመጀመሪያ እንዳልቀረበ ከተቆጠረ ኮሚሽኑ ምክንያቶቹን በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።
4. ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 48(1) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 41 እና 42 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች አለመሟላታቸውን ሲያረጋግጥ አመልካቹ ተፈላጊውን ማሻሻያ ከተመደበው ክፍያ ጋር ከጥሪው ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ እንዲያቀርብ በጽሑፍ ይጠራዋል። አመልካቹ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጉድለቱን ሳያርም ሲቀር ወይም እርማቱ ቢቀርብም ኮሚሽኑ የተጠየቁት ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚል እምነት ሲኖረው ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ምክንያቶቹን በመዘርዘር በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።
5. የማመልከቻው ውድቅ መሆን የምዝገባውን ቀን ተቀባይነት አያሳጣውም፡፡

## 44.<u>ማመልከቻን ስለመቀበል ወይም ስላለመቀበል ውሣኔ</u>

ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መወሰኑን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል። ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ለመቀበል ከወሰነ ውሳኔውን ካሳወቀበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ውስጥ አመልካቹ የምዘገባና የሕትመት ክፍያ እንዲፈጸም መጠየቅ ይኖርበታል ።

## 45.ስለኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ፣ ሕትመትና ምስክርወረቀት መስጠት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 44 በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምዝገባና ሕትመት ክፍያ ከተፈጸመ ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 48(2) እና በዚህ አንቀጽ መሠረት የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ይመዘግባል፡፡
2. ኮሚሽኑ ለሚመዘግበው ለእያንዳንዱ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በምዝገባ ቅደም ተከተል መሠረት ቁጥር ይሰጣል፡፡
3. የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን መግለጫ፣ እና
   ሀ) የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ቁጥር፣
   ለ) የተመዘገበውን ባለቤት ስምና አድራሻ፣
   ሐ) ወኪል ካለ የወኪሉን ስምና አድራሻ፣
   መ) በምዝገባው ላይ ስሙ እንዳይጠቀስ ካልጠየቀ በስተቀር ኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ያመነጨው ሰው ስምና አድራሻ፣
   ሠ) የቀዳሚነት ጥያቄ ከቀረበና ጥያቄውም ተቀባይነት ካገኘ የቀዳሚ ቀኑንና የመጀመሪያው ማመልከቻ የተመዘገበበት ሀገር/ሀገሮች ወይም የመጀመሪያው ማመልከቻ ምዝገባ እንዲሸፍን የተጠየቀ/ቁ ሀገር/ሀገሮች፣
   ረ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት መያዝ ይኖርበታል።
4. በአዋጁ አንቀጽ 14(2) (ሀ) እና አንቀጽ 51 የሚከናወን የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ሕትመት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተዘረዘሩትን መያዝ ይኖርበታል።
5. የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት በቅጽ ቁጥር 8 ተሞልቶ ይሰጣል፡፡

## 46.ስለምዝገባ እድሳት

1. በአዋጁ አንቀጽ 50(2) መሠረት የሚፈጸም የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ እድሳት በተመዘገበው ባለቤት ወይም በወኪሉ አማካይነት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሊከናወን ይችላል፡፡ የዚህ ደንብ አንቀጽ 33 እንደ አግባቡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

2. እድሳቱ ተገቢውን የእድሳቱን ክፍያ በመፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 50(2) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ወይም ከተጨማሪ ክፍያ ጋር በአዋጁ አንቀጽ 17(1) እና በአንቀጽ 52 በተፈቀደው የችሮታ ጊዜ ሊፈጸም ይችላል፡፡
3. የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ እድሳት በመዝገቡ ላይ መስፈርና መታተም አለበት፣
4. ኮሚሽኑ ለተመዘገበው ባለቤት
   ሀ) የአንዱስትሪያዊ ንድፍ የምዝገባ ቁጥር ፣
   ለ) የእድሳት ቀንና የጥበቃ ዘመኑ የሚያበቃበትን ቀን፣
   ሐ) የተመዘገበውን ባለቤት ስምና አድራሻ፣ እና
   መ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የተመዘገቡትን የምርት ዓይነቶች ጥቆማ የያዘ የእድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ 5

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 47.ስለባለቤትነት ለውጥ

1. ማንኛውም የፓተንት፣ የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ወይም የእንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ለዚሁ የቀረበ ማመልከቻ ባለቤትነት ለውጥ በጽሑፍ መሆን ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም በጉዳዩ ላይ ፍላጎት ያለው ወገን ለኮሚሽኑ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ለውጡ መመዝገብና ከማመልከቻ ባለቤትነት ለውጥ በስተቀር በኮሚሽኑ መታተም አለበት። የሚደረገው ለውጥ ከመመዝገቡ በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት አይኖረውም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ የመብት ባለቤትነት ለውጥ ወይም ለዚሁ የቀረበ ማመልከቻ ባለቤትነት ለውጥ ጥያቄ በቅጽ ቁጥር 9 ተሞልቶ የተመደበው ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት፣
3. የባለቤትነት ለውጥ ሕትመት፣
   ሀ) አግባብነት ያለውን የጥበቃ ዓይነት፣
   ለ) የምዝገባ ቀን፣ በኖረ ጊዜ ቀዳሚ ቀንና የምዝገባ ወይም መብት የተሰጠበትን ቀን፣
   ሐ) ባለቤቱንና አዲሱን ባለቤት፣ እና

መ) የባለቤትነት ለውጥ፣ ባህሪን፣ መግለፅ ይኖርበታል፡፡

48.ስለወኪል መሰየምና የግንኙነት አድራሻ

የወኪል ስያሜ በአመልካቹ ወይም ከአንድ በላይ አመልካቾች ካሉ በእያንዳንዱ አመልካች በተፈረመ ህጋዊ የውክልና ሰነድ መሆን አለበት፡፡ ከአዋጁ ወይም ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወኪል ከሰየመው ሰው/ሰዎች ጋር የሚደረግ ግንኙነት በወኪሉ አድራሻ ይሆናል።

49.ስለማይቆጠሩ ቀናት

ማንኛውንም ተግባር ለማከናወን ወይም ሁኔታዎችን ለመፈጸም የተሰጠው የመጨረሻ ቀን የሚውለው የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት ለሥራ ለሕዝብ ክፍት በማይሆንበት ቀን ከሆነ ተግባሩን ወይም ሁኔታውን የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ክፍት በሚሆንበት በቀጣዩ ቀን መፈጸም ሕጋዊነት ይኖረዋል።

50.ስለመዝገቦችና ኦፊሴላዊ ጋዜጣ

1. ኮሚሽኑ ለፓተንት፣ ለግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና ለኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የተለያዩ መዝገቦች ይኖሩታል፡፡ በአዋጁና በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱት ምዝገባዎች በሙሉ በነዚሁ መዝገቦች ላይ ይፈጸማሉ፡፡
2. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የተገለጹ ሕትመቶችን ኮሚሽኑ በኦፊሴላዊ ጋዜጣ ላይ ያወጣል።

51.መዝገቦችን ስለማየት፣ ከመዝገቦቹ የተመረጡ ክፍሎች እና የሰነዶች ቅጂዎችን ስለመጠየቅ

1. ማንኛውም ሰው የተወሰነውን ክፍያ በመፈጸም መዝገቦችን ማየትና ከመዝገቦቹም ላይ ቅጂዎችን መውሰድ ይችላል፡፡
2. ከመዝገቦች ላይ የሚወሰዱ የተመረጡ ክፍሎችን፣ የተረጋገጡ ቅጂዎች ወይም የሰነዶችን ቅጂዎች የማግኘት ጥያቄ በጽሁፍ ሆኖ ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት፡፡

52.ስለግድፈቶች እርማት

1. ኮሚሽኑ በቀረበለት ማመልከቻ ወይም ሰነድ ወይም በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት በተፈጸሙ ምዝገባዎች ላይ ያለን ማንኛውንም የትርጉም ግድፈት የአጻጻፍ ግድፈት ወይም ስህተት ሊያርም ይችላል፡፡

2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚያከናውነው የግድፈቶች እርማት በጽሑፍ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ወይም በራሱ አነሳሽነት ሊፈጸም ይችላል፡፡ ኮሚሽኑ ከጉዳዩ ጋር አግባብ ላላቸው ሰዎች እርማቶችን በጽሑፍ ማሳወቅ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማተም አለበት፡፡

53. <u>ስለጉዳይ ማሰማት</u>

1. ኮሚሽኑ በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ የተሰጠውን ሥልጣን የማንኛውንም ሰው ጥቅም በሚነካ ጉዳይ ላይ ከመጠቀሙና ከመወሰኑ አስቀድሞ ለሚመለከተው ሰው ጉዳዩን ለማሰማት ዕድል እንዳለው በመግለጽ ጉዳዩን የማሰማት ጥያቄ ማቅረብ የሚችልበት ከአንድ ወር ያላነሰ የጊዜ ገደብ ሰጥቶ በጽሑፍ ያሳውቃል።
2. ጉዳይን የማሰማት ጥያቄ የሚቀርበው በጽሑፍ ይሆናል፡፡
3. ኮሚሽኑ ጥያቄው ሲደርሰው ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀንና ሰዓት ለአመልካቹና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር አግባብ ላላቸው ሰዎች ቢያንስ ሁለት ሳምንት አስቀድሞ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

54. <u>በፖስታ መልዕክት የሚደረግ ግንኙነት</u>

1. ማንኛውም በፖስታ አማካኝነት ለኮሚሽኑ የሚላክ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ ወይም ሌላ ሰነድ ለኮሚሽኑ እንደተሰጠ ወይም እንደቀረበ የሚቆጠረው በተለመደው የፖስታ ሥርጭት ሂደት መሰረት ለኮሚሽኑ ሲደርስ ነው። መልዕክቱ ለመላኩ ማረጋገጫ ማስታወቂያውን፣ ማመልከቻውን ወይም ሌላ ሰነድ የያዘውን ደብዳቤ በትክክለኛው አድራሻና በአደራ መላኩን ማረጋገጥ ብቻ በቂ ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የምዝገባ ቀን መስጠትን አስመልክቶ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

55. <u>ቅፆች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር በአባሪነት የተያያዙት ቅጾች ለተዘጋጁባቸው የተለያዩ ጉዳዮች መዋል ያለባቸው ሆኖ ኮሚሽኑ በሚሰጠው መመሪያ ለሌሎች ጉዳዮች እንዲውሉ ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡

**56.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 27 ቀን 1989 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 410/1996

## የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ለማድረግ የወጣ አዋጅ

የሥነፅሁፍ፣ የኪነጥበብ እና ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎች የአንድን ሀገር ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ልማትን በማፋጠን ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው የሚበረታቱበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሥነፅሁፍ፣ የኪነጥበብና ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ በሚከናወኑ ስራዎች ላይ ተዛማጅ መብቶችን በሕግ እውቅና መስጠትና ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**[111]

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "የኦዲዮ ቪዥዋል ሥራ" ማለት ለዚሁ ተግባር በተሰራ መሳሪያ በመጠቀም በቀላሉ ሊታይ የሚችል፣ ተከታታይነትና ተዛማጅነት ያለውን በድምፅ የታጀበ ወይም ያልታጀበ የእንቅስቃሴ ስሜትን የሚፈጥሩ ምስሎችን የያዘ ማንኛውም ሥራ ሲሆን ሲኒማቶግራፊንና ሌሎች ፊልሞችን ይጨምራል፡፡
   2. "የሥራ አመንጪ" ማለት የአንድን የአእምሮ ውጤት የሆነን ሥራ የፈጠረ ማንኛውም ግለሰብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፣

      ሀ) ሥራው የኮምፒውተር ፕሮግራም ከሆነ የኮምፒውተር ፕሮግራሙን የፈጠረው ግለሰብ፣

      ለ) ሥራው ፎቶግራፍ ከሆነ ለጥንቅሩ ኃላፊ የሆነውን ግለሰብ፣
   3. "ብሮድካስቲንግ" ማለት ድምፅን ወይም ምስልንና ድምፅን ሽቦ አልባ በሆነ መንገድ ለሕዝብ ማሰራጨት ነው፤

[111] ከንዑስ አንቀፅ 31 እስከ 35 በ21/20 (2007) ኢ. 872 አንቀፅ 2(2) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

4. “የብሮድካስቲንግ ድርጅት” ማለት ሬድዮ፣ ቴሌቭዥን እና የኬብል ቴሌቭዥን ጣቢያ ወይም ሳተላይት ነው፣
5. “ስብስብ ሥራ” ማለት በአንድ የተፈጥሮ ሰው አነሳሽነትና መሪነት ከሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች የተፈጠረ እና በሥራው ላይ አስተዋፅኦ ያላቸው ግለሰቦች ሳይጠቀሱ በመሪው ስም ብቻ እንደሚታወቅ ግንዛቤ ተወስዶ የተሰራ ሥራ ነው፣
6. “ለህዝብ ማሰራጨት” ማለት የአንድ ሥራ ክወና፣ የድምፅ ሪከርድ ወይም ብሮድካስት ምስል፣ ድምፅ ወይም ሁለቱን በሽቦ ወይም ያለሽቦ ማሰራጨት ሲሆን ምስሉ ወይም ድምፅ በመደበኛው የቤተሰብ ዙሪያ እና የቤተሰቡ የቅርብ ወዳጆች ከሚገኙበት ቦታ ውጪ በሆነ ወይም ስርጭቱ ከሚተላለፍበት በጣም ራቅ ያለ ቦታ ላይ በሚገኝ ሰው ሊሰማ ወይም ሊታይ የሚችል ሆኖ ምስሉ ወይም ድምጹ በአንድ አይነት ቦታና ጊዜ ወይም በተለያዩ ቦታዎች እና ወይም ጊዜያት ሊሰማ ወይም ሊታይ መቻሉ ግምት ውስጥ ሳይገባ ምስሉ ወይም ድምጹ ያለ ስርጭቱ ሊሰማ ወይም ሊታይ የማይችል ሲሆን ነዉ፤
7. “የኮምፒዩተር ፕሮግራም” ማለት በመሳሪያ ተነባቢ የሚሆን አንድ ኮምፒዩተር ተግባሩን እንዲያከናውን ወይም የታለመለትን ውጤት እንዲያመጣ የሚያስችል የቃላት፣ የኮዶች፣ የዘዴዎች፣ ወይም በሌላ አኳኋን የሚገኝ የመመሪያዎች ስብስብ ነው፣
8. “የቅጅ መብት” ማለት ከአንድ ስራ የሚመነጭ የኤኮኖሚ መብት ሲሆን አግባብነት ባለው ጊዜ የሞራል መብቶችን ይጨምራል፣
9. “ፍርድ ቤት” ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፤
10. “ዳታ ቤዝ” ማለት በኮምፒዩተር አማካኝነት ለመፈለግ እንዲቻል ስርአት ባለው አኳኋን የተደራጀ የመረጃ፣ መጣጥፍ፣ ቁጥር ወይም ዲያግራም ስብስብ ነው፣
11. “መቅረፅ ወይም ግዝፈት እንዲያገኝ ማድረግ” ማለት አንድ ሥራ፣ ምስል፣ ድምፅ ወይም የአንደኛቸው አምሳያ ምትክ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ መሣሪያ አማካኝነት እንዲታይ፣ እንዲባዛ፣ ወይም እንዲሰራጭ ማድረግ ነው።
12. “በቅጥር የተከናወነ ሥራ” ማለት በቅጥር ወይም በአገልግሎት ውል መሰረት ተከፋይ በሆነ የሥራ አመንጪ የተፈጠረ ሥራ ነው፣

13.“የሙዚቃ ሥራ” ማለት ሙዚቃ ሲሆን ከሙዚቃው ጋር ሊከወኑ፣ ሊነገሩ ወይም ሊዘመሩ የተዘጋጁ ማናቸውም ቃላትን ወይም ድርጊትን አይጨምርም፤

14.“ተዛማጅ መብት” ማለት ከዋኝ፣ የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰር፣ የብሮድካስቲንግ ድርጅት በሥራው ላይ ያለው መብት ነው፤

15.“ፅህፈት ቤት” ማለት በአዋጅ ቁጥር 320/1995 ዓ.ም የተቋቋመው የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ፅህፈት ቤት ነው፣

16.“የቅጅ መብት ባለቤት” ማለት ኢኮኖሚያዊ መብቱ ለሥራ አመንጪው በሆነ ጊዜ የሥራ አመንጪው፣ ኢኮኖሚያዊ መብቱ ከመጀመሪያው ሥራ አመንጪው ውጪ ላለ ግለስብ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሰጥ ግለሰቡ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወይም የኢኮኖሚ የባለቤትነት መብቱ ለአንድ ግለሰብ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ተላልፎ ከሆነ መብቱ የተላለፈለት ግለሰብ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፣

17.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነዉ፡፡

18.“የፎቶግራፍ ሥራ” ማለት አንድ ምስል ለማውጣት ወይም ምስልን በማናቸውም ዘዴ ለማውጣት እንዲቻል ብርሃን እና ወይም ሌላ ጨረርን በማናቸውም የመቀበያ አካል ላይ መቅረፅ ሲሆን ፊልምን አይጨምርም።

19.“ከዋኝ” ማለት ተዋናይ፣ ዘፋኝ፣ ዘማሪ፣ ሙዚቀኛ ተወዛዋዥ እና ሌላ ማናቸውም የሚተውን፣ የሚያወጣ፣ የሚጫወት፣ የሚዘፍን፣ የሚያዝናና ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የስነ-ፅሁፍና የኪነጥበብ ሥራን የሚከውን ግለሰብ ነው፤

20.“ፕሮዲውሰር” ማለት የኦዲዮቪዡዋል ሥራ ለመስራት ሃሳብ ያመነጨና ሥራውን በኃላፊነት የሚያሰራ ሰው ነው፤

21.“የድምፅ ሪኮርዲንግ ፕሮዲውሰር” ማለት የድምፅ ሪኮርዲንግ ሥራ ለመስራት ሃሳብ ያመነጨና ሥራውን በሀላፊነት የሚያሰራ ሰው ነው፤

22.“የታተመ ሥራ” ማለት የአንድን ሥራ ወይም የድምፅ ሪኮርዲንግ ተጨባጭነት ያላቸው ቅጂዎች በሽያጭ፣ በኪራይ፣ ለህዝብ ውሰት፣ እንዲሁም የቅጅዎችን ባለቤትነት ወይም ይዞታ ለማስተላለፍ እንደሁኔታው በሥራው አመንጪ ወይም በቅጂ ባለመብቱ ወይም በድምፅ ራኮርዲንግ ፕሮዲውሰር ፈቃድ በበቂ መጠን ለህዝብ የቀረበ ሥራ ነው፤

23. "ለሕዝብ የሚደረግ ውሰት" ማለት በአንድ ሥራ ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ ኦሪጂናል ወይም ቅጂው ላይ ያለን የይዞታ መብት በጊዜያዊነት ያለ ትርፍ ሕዝባዊ አገልግሎት በሚሰጡ ቤተመፃህፍት፣ ቤተመዛግብት፣ ወይም ተመሳሳይ ተቋማት ለሕዝብ ማስተላለፍ ነው፤

24. "ለሕዝብ የቀረበ ክወና" ማለት

ሀ) በግንባር ወይም በማናቸውንም የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም በመነባነብ፣ በጭውውት፣ በውዝዋዜ፣ በትወና፣ አንድን ሥራ ለህዝብ መከወን፣

ለ) የኦዶዩቪዥዋል ሥራን በተመለከተ ምስል በተከታታይ እንዲታይ፣

ሐ) የድምፅ ሪከርዲንግን በተመለከተ ድምፅ ለህዝብ እንዲሰማ ማድረግ ነው፣

25. "ማባዛት" ማለት አንድን ሥራ ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የኤሌክትሮኒክ ማከማቻን ጨምሮ በማንኛውም አኳኋን ወይም መልክ ሥራውን ወይም የድምፅ ሪከርዱን በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቅጅዎች ማራባት ነው፤

26. "ትክክለኛ ቅጅ" ማለት ፎቶኮፒን በመሳሰሉ ከማተም ውጪ ባሉ መንገዶች የአንድን ሥራ ኦሪጅናል ወይም ቅጂ መጠኑ ይነስም ይደግም በትክክል መገልበጥ ነው፤

27. "ኪራይ" ማለት ለትርፍ ሲባል አንድ የኦዲዮቪዥዋል ሥራ ወይም የኮምፒዩተር ፕሮግራም ወይም የድምፅ ሪከርዲንግ ወይም ግዝፈት ያለው ክወና ይዞታ በጊዜያዊነት ማስተላለፍ ነው፤

28. "የድምፅ ሪከርዲንግን" ማለት የክወና ድምፅ ወይም ሌላ ድምፅ ወይም አምሳያ ምትክ ግዝፈት ያገኘበት ዘዴን ወይም ድምፁ የተቀረፀበትን አካል ግምት ውስጥ ሳይገባ ክዋኔ ወይም ድምፅ ወይም አምሳያው ግዙፍነት እንዲያገኝ ማድረግ ሲሆን የኦዲዩቪዥዋል ሥራን፣ የድምፅ ትራክን የመሳሰሉ የድምፅና ምስል ግዝፈትን አይጨምርም፣

29. "የጋራ የባለቤትነት ሥራ" ማለት ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የሥራ አመንጪዎች አስተዋፅኦ ያበረከቱበት የፈጠራ ሥራ ሲሆን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) መሰረት የስብስብ ሥራ ያልሆነ ሥራ ነው፣

30. "ሥራ" ማለት የሥነ ፅሁፍ፣ ኪነጥበብ እና ሳይንሳዊ መስኮች ውጤት ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ) መፅሐፍ፣ ቡክሌት፣ በመፅሄት ወይም በጋዜጣ ላይ የሚገኝ መጣጥፍ፣ የኮምፒውተር ፕሮግራም፤

ለ) ንግግር፣ ሌክቸር፣ ለአንድ ለተወሰነ ክፍል የሚደረግ መልእክት አዘል ንግግር፣ የሃይማኖት ስብከት፣ እና በቃል የቀረበ ሥራ፤

ሐ) ድራማ፣ ድራማዊ የሙዚቃ ሥራ፣ በእንቅስቃሴ ብቻ የሚቀርብ ድራማ (ፓንቶማይምስ) የመድረክ ውዝዋዜ እና ሌላ ለመድረክ ተብሎ የሚሰራ ሥራ፤

መ) የሙዚቃ ሥራ፤

ሠ) የኦዲዮቪዥዋል ሥራ፤

ረ) የኪነ ህንፃ ሥራ፤

ሰ) የስዕል፣ የቅብ፣ የሀውልት፣ የቅርፃ ቅርፅ፣ የህትመት፣ የፊደል ቅርፅ ጥልፍ እና ሌላ የስነጥበብ ሥራ፤

ሸ) የፎቶግራፍ ስራ፤

ቀ) ስዕላዊ መግለጫ፣ ካርታ፣ ፕላን፣ ንድፍ እና ባለ ሶስት ገፅታ ከጂኦግራፊ፣ ቶፖግራፊ፣ ኪነ ህንፃ ወይም ሳይንስ ጋር የተያያዘ ሥራ፤

በ) የዕደ-ጥበብ ስራዎች[112]

31.“ሮያሊቲ” ማለት ከንግድ ስራ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ለሚውል በዚህ አዋጅ መሠረት ጥበቃ ለሚያገኝ ስራ በተጠቃሚው አማካኝነት ለባለመብቱ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ነው፤

32.“የጋራ አስተዳደር ማህበር” ማለት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ባለቤቶች መብቶቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር የሚያቋቁሙት ማህበር ነው፤

33.“የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር” ማለት ሮያሊቲ የሚከፈልበትን ስራ እና የተጠቃሚዎችን ማንነት መሠረት በማድረግ የሚሰበሰብን የሮያሊቲ መጠን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው፡፡

34.“ባለቤት የሌለው ስራ” ማለት ባለቤት የሌለው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ስራ ነው፤

35.“ለህዝብ ለመቅረብ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ስራዎች” ማለት ከሽያጭ ወይም ከኪራይ ውጪ በቀጥታ ለህዝብ በይፋ ለመከወን ወይም ለመታየት ወደ አገር

[112] በ21/20 (2007) አ.872 አንቀፅ 2(1) አዲስ የገባ ነው፡፡

ውስጥ የሚገቡ እና የእንካ ለእንካ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ የጋራ አስተዳደር ማህበራት የማይተዳደሩ ስራዎች ናቸው፡፡

3. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

1. በዚህ አዋጅ የሚደረገው የህግ ጥበቃ፤
   ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባለው ወይም ቋሚ መኖሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የሥራ አመንጪ ሥራ፣
   ለ) የስራ አመንጪው ዜግነት ወይም ቋሚ መኖሪያ ግምት ውስጥ ሳይገባ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በታተመ ወይም በውጭ ሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ በታተመና በ30 ቀናት ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ በታተመ ሥራ፣
   ሐ) የፕሮዲውሰሩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም ቋሚ መኖሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የኦዲዮቪዥዋል ስራ እና፤
   መ) በኢትዮጵያ ውስጥ የተገነባ የኪነ ህንፃ ሥራ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በቆመ ህንፃ ወይም ሌላ ስትራክቸር ውስጥ የተካተተ የኪነጥበብ ሥራ፣

   ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ኮንቬንሽኖች መሰረት ጥበቃ ባገኙ ስራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
3. የከዋኞች ጥበቃን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፤
   ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባለው ከዋኝ፣
   ለ) በውጭ ዜጎች፣
      i. በኢትዮጵያ ውስጥ የተከወነ፤
      ii. በዚህ አዋጅ ጥበቃ ባገኘ የድምፅ ሪከርዲንግ ውስጥ የተካተተ ወይም፣
      iii. በድምፅ ሪከርዲንግ ውስጥ ግዙፍነት የሌለው ቢሆንም በዚህ አዋጅ ጥበቃ ባገኘ ብሮድካስት ውስጥ የተካተተ ክውና፣

      ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
4. የድምፅ ሪከርዲንግ ጥበቃን በተመለከተ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣
   ሀ) በኢትዮጵያውያን ፕሮዲውሰሮች የተዘጋጀ የድምፅ ሪከርዲንግ፣
   ለ) ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ግዝፈት ባገኘ የድምፅ ሪከርዲንግ፣
   ሐ) ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በታተመ የድምፅ ሪከርዲንግ፣

ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

5. የብሮድካስት ጥበቃን በተመለከተ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣
   ሀ) ዋና መሥሪያ ቤቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የብሮድካስቲንግ ድርጅት ብሮድካስት፣
   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ አሰራጭ የሚያስተላልፈው ብሮድካስት፣ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
6. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ኮንቬንሽኖችና ስምምነቶች መሰረት ጥበቃ ባገኙ ከዋኞች፣ የድምፅ ሪኮርድ ፕሮዲውሰሮች እና የብሮድካስቲንግ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
7. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ላይ ሥራው የታቀፈበትን ቁሳዊ ነገር የባለቤትነት መብት አያጠቃልልም፡፡

4. ***<u>የመጀመሪያ ስራን መሰረት ያደረገ ስራ</u>***

1. የሚከተሉት እንደ ሥራ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፣
   ሀ) ትርጉም፣ የማመሳሰል ስራ፣ ቅንብር እና ሌላ የስራውን አይነት የሚቀይር ወይም የሚያሻሽል ሥራ፣
   ለ) በይዘት፣ በቅንብር ወይም በአመራረጥ የተነሳ ኦሪጅናል የሆነና በሚነበብ መሳሪያ ወይም በሌላ መልክ ያለ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ የቅኔ ስብስብ ወይም ዳታቤዝን የመሳሰለ የስብስብ ሥራ፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ጥበቃ የመጀመሪያ ስራን መሰረት ያደረገ ሥራ ለመስራት ጥቅም ላይ ለዋለ ወይም በዚሁ ሥራ ውስጥ ለተካተተ የቀድሞ ሥራ ላይ ያለን ጥበቃ አያስቀረውም፤

5. ***<u>ጥበቃ የማይደረግላቸዉ ስራዎች</u>***

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 2፤ 3 እና 4 የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ጥበቃ አይደረግላቸውም፣

ሀ) ማንኛውም ሀሳብ፣ የአሰራር ሂደት፣ ሲስተም፣ የአሰራር ዘዴ፣ ፅንሰ ሀሳብ፣ ቀመር፣ ለአጠቃላይ ሥራ የሚያገለግል የቁጥር ሰንጠረዥና ቅፅ፣ መርህ፣ በአንድ ሥራ ውስጥ የተብራራ፣ የተገለፀ፣ የተተነተነ ወይም የተነገረ ሆነም አልሆነ ግኝት ወይም ዳታ፣

ለ) የህግ ባህሪ ያላቸው ማናቸውም ይፋ የሆኑ የህግ እና የአስተዳደር ሰነዶችና ይፋ የሆነ ትርጓሜያቸው፣

## ክፍል ሁለት

## ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች፣ የብቸኝነት መብት አይነትና የተፈፃሚነት ወሰን

6. **ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች**[113]

   1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ የሥራው አላማና የጥራት ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ፣

      ሥራዉ፤

      ሀ) ወጥ (ኦርጅናል) ከሆነ፣

      ለ) ከተቀረፀ ወይም ግዙፍነት ካገኘ፣

      ሥራውን በማውጣት ምክንያት ብቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ ያገኛል።

   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ለሥራ አመንጪ የተሰጠው ጥበቃ በዚህ አዋጅ የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲውሰር፣ ብሮድካስተር ወይም ከዋኝ በሚያገኙት መብት ቀሪ አይሆንም።

7. **ኢኮኖሚያዊ መብቶች**

   1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 እስከ 19 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ ወይም የአንድ ሥራ ባለቤት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፤

      ሀ) ሥራን የማባዛት፣

      ለ) ሥራን የመተርጎም፣

      ሐ) ሥራን የማመሳሰል፣ የማቀናበር ወይም ወደ ሌላ አይነት የመቀየር፣

      መ) በሽያጭ ወይም በኪራይ አርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን የማከፋፈል፣

      ሠ) ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ከውጭ ሀገር የማስገባት፤

      ረ) ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ለህዝብ የማሳየት፣

      ሰ) ሥራን በይፋ የመከወን፣

      ሸ) ሥራን ብሮድካስት የማድረግ፤

---

[113] የዚህ አንቀጽ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (2) በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(3) የተሰረዘ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ (3) ንዑስ አንቀጽ (2) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

ቀ) ሥራን በሌላ መንገድ የማሰራጨት፤

2. የኮምፒውተር ፕሮግራሙ የኪራይ ወይም የህዝብ ውሰት መሰረታዊ አካል ካልሆነ በቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) (መ) ላይ የተደነገገው በኮምፒውተር ፕሮግራም ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፣

3. የአንድ ወጥ የስነ ጥበብ ስራ ወይም የአንድ ደራሲ ወይም የዜማ ደራሲ ኦርጅናል ፅሁፍ በሥራው አመንጪ ከተላለፈ በኋላ ከሚደረገው ድጋሚ ሽያጭ ዋጋ ላይ የሥራ አመንጪው ወይም ወራሹ የተወሰነ ድርሻ የማግኘት መብት ይኖረዋል። የክፍያው መጠንና የተፈፃሚነት ሁኔታ በዚህ አዋጅ ስር በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

8. <u>የሞራል መብት</u>

1. የሥራ አመንጪው የኤኮኖሚ መብት ባለቤት ቢሆንም ባይሆንም የሚከተሉት የሞራል መብቶች አሉት፡፡

ሀ) ወቅታዊ ሁኔታን በብሮድካስት አማካኝነት ለመዘገብ ባጋጣሚ ወይም በድንገት ከተካተተ ሥራ ውጪ የሥራ አመንጪነቱ እንዲታወቅ የመጠየቅ፤

ለ) ሳይታወቅ የመቆየት ወይም የብዕር ስም የመጠቀም፤እና

ሐ) ክብሩንና መልካም ስሙን የሚያጎድፍ የሥራ መዛባት፣ መቆራረጥ ወይም በሌላ መልክ መቀየርን የመቃወም፣

መ) ሥራን የማሳተም፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩት መብቶች በህግ መሠረት ለወራሾች ወይም ለስጦታ ተቀባዮች ካልሆነ በቀር የሥራ አመንጪው በህይወት እያለ ወደ ሶስተኛ ሰው ሊተላለፉ አይችሉም፤

3. ሥራ አመንጪው፣ ወራሽና ስጦታ ተቀባይ

ሀ) ያነሳውን መብትና የመብት መነሳቱ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ በፅሁፍ በማመልከት፣

ለ) በሥራው ላይ የሚደረግ ማሻሻል የሚኖረውን ባህሪና የለውጥ መጠን በመግለፅ፣

በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩትን መብቶች ሊተው ይችላል።

4. የሞራል መብቶች የሥራ አመንጪው ከሞተ በኋላ ኢኮኖሚያዊ መብቶች ፀንተው ለሚቆዩበት ጊዜ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

9. <u>ለግል አገልግሎት ሰራን ስለማባዛት</u>
   1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7(1)(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ የታተመ ሥራን አንድ ቅጅ ለግል ጥቅም ፍጆታ ለማዋል ማባዛትን አይከለክልም፤
   2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም፤
      ሀ) በህንፃ ወይም በኮንስትራክሽን መልክ የሚገኝ የኪነ ህንፃ ሥራን፤
      ለ) በኖታ መልክ የሚገኝ የሙዚቃ ስራን ወይም በአመንጪው የተፈረመ ኦሪጅናል ወይም ቅጅ የስነ ጥበብ ሥራን፤
      ሐ) በሙሉ ወይም በአመዛኙ በዲጂታል መልክ የተቀመጠ ዳታ ቤዝን፣
      መ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 ከተደነገገው ውጪ የኮምፒዩተር ፕሮግራምን ወይም፤
      ሠ) የሥራ አመንጪው ህጋዊ ጥቅም ወይም የተለመደ አጠቃቀም ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ የሚጎዳ ሥራን፤
      ማባዛት አይቻልም።
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተቀመጠው ልዩ ሁኔታ መሰረት አንድ ቅጅ ለግል ጥቅም ፍጆታ ለማዋል ማባዛት የሚፈቀደው የሚያባዛው ግለሰብ በቅድሚያ የስራው ኦርጅናል ቅጅ ባለቤት ከሆነ ነው፡፡[114]

10. <u>ጥቅስ</u>
   1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 (1) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከአንድ ከታተመ ሥራ ጥቅስ እንዳይጠቀስ የቅጅ መብት ባለቤቱ ሊከለከል አይችልም፤
   2. ጥቅሱ ከተገቢ አሰራርና አላማው ከሚጠይቀው በላይ መሆን የለበትም፣
   3. ጥቅሱ የተወሰደው የሥራው አመንጪውን ስም ከያዘ ሥራ ሲሆን የጥቅሱን ምንጭና የሥራውን አመንጪ ስም መጥቀስ አለበት፡፡

11. <u>ለማስተማር ስራ ስለሚደረግ ማባዛት</u>
   1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 (1) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ ከተገቢ አሰራርና አላማው ከሚጠይቀው በላይ እስካልሆነ ለማስተማሪያነት ወይም

[114] በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(4) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

ለማብራሪያ የሚውል የታተመ ሥራ ወይም የድምፅ ሪኮርዲንግ እንዳይባዛ ሊከለክል አይችልም፣

2. በዚህ አንቀፅ መሰረት የተደረገ ቅጂ እስከተቻለ ድረስ በማንኛውም ጊዜ የተባዛውን ሥራ ወይም የድምፅ ሪኮርዲንግ ምንጭና የአመንጪው ስም መጥቀስ አለበት፡፡

12. **በቤተመፃህፍት፤ በቤተመዛግብት፤ ወይም መሰል ተቋማት ስለሚደረግ ማባዛት**

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 (1) (ሀ) ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ ለትርፍ ባልቆመ ቤተመፃህፍት፣ ቤተመዛግብት ወይም መሰል ተቋማት የሚደረግ የማባዛት ተግባርን ሊከለክል አይችልም፣

2. አንድ ቤተመፃህፍት፣ ቤተመዛግብት ወይም መሰል ተቋም በግለሰብ ጥያቄ የታተመን መጣጥፍ፣ አጭር ሥራ ወይም ከአንድ ሥራ ላይ የተወሰደ ቅንጫቢ ሥራን ማባዛት የሚችለው፣

   ሀ) ቅጂው ለትምህርት፣ ለጥናት፣ ለስኮላርሺፕ ወይም ለምርምር እንደሚውል በቤተመፃህፍት፣ በቤተመዛግብት ወይም መሰል ተቋም ሲረጋገጥ፣

   ለ) ሥራው ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚባዛ ከሆነ፣ የሚደጋገም ከሆነም በተያዩና ተዛማጅነት በሌላቸው ሁኔታዎች የሚፈፀም ከሆነ፤

   ሐ) ሥራው እንዲባዛ ፈቃድ የሚሰጥ አስተዳደራዊ አካል የሌለ ከሆነ ብቻ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) የተመለከተው የቅጅ ሥራ የሚከናወነው፤

   ሀ) የአንድ ሥራን ቅጅ ለመጠበቅ ወይም ለመተካት አስፈላጊ ሲሆን ወይም በሌላ ተመሳሳይ ቤተመፃህፍት ወይም ቤተመዛግብት ቋሚ ስብስብ ውስጥ የነበረ፣ የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችል ሲሆን፣

   ለ) በደህና ሁኔታ ያለን ቅጅ ለማግኘት የማይቻል ሲሆን፣

   ሐ) የማባዛቱ ተግባር አንድ ጊዜ ብቻ የተፈፀመ ሲሆን፣ የሚደጋገም በሆነ ጊዜም በተለያዩና በማይዛመዱ ሁኔታዎች ሲሆን፣ ብቻ ይሆናል፡፡

13. **ለህዝብ መረጃ አገልግሎት አላማ ማባዛት፤ ብሮድካስት ማድረግና ማሰራጨት**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 (1) (ሀ) ፤ (ሸ) እና (ቀ) የተደነገገው ቢኖርም እስከተቻለ ድረስ የሥራውን ምንጭና የሥራ አመንጪውን ስም መጥቀስ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጅ መብት ባለቤቱ፣

1. የማባዛት፣ ብሮድካስት የማድረግ ወይም ለህዝብ የማሰራጨት መብቱ የሥራው አመንጪ ወይም የቅጅ ባለመብቱ መሆኑን በቅጅው ላይ በግልፅ የተጠቀሰ ነገር ከሌለ በወቅታዊ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ጉዳዮች ላይ በጋዜጣ፣ በመፅሄት የወጡ ወይም ተመሳሳይ ባህሪ ኖሯቸው ብሮድካስት የተደረጉ መጣጥፎችን በሌላ ጋዜጣ ወይም መፅሄት ማባዛትን፣ በብሮድካስቲንግ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ማድረስን፤
2. ወቅታዊ ሁኔታን ለመዘገብ ሲባል በአንድ በታየ ወይም በተሰማ ጉዳይ ላይ የተዘጋጀ በአጭሩ የተወሰደ ሥራን ማባዛት ወይም ብሮድካስት ማድረግን ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ማድረስን፣
3. የፖለቲካ ንግግርን፣ ሌክቸርን፣ ስብከትን ወይም ተመሳሳይ ባህርይ ያለው ሌላ ሥራን ወይም በፍርድ ሂደት ላይ የተደረገ ንግግርን ወቅታዊ መረጃ ለህዝብ ለመስጠት በጋዜጣ ወይም በመፅሄት ማባዛት፣ ብሮድካስት ማድረግን ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ማቅረብን፣ ሊከለክል አይችልም።

14.<u>የኮምፒዩተር ፕሮግራም ስለማባዛትና ስለማሻሻል</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 (1) (እና (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብቱ ባለቤት የኮምፒዩተር ፕሮግራምን ነጠላ ቅጅ ማድረግን ወይም ማሻሻልን ሊክለክል አይችልም፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተውን የኮምፒዩተር ፕሮግራም ማሻሻል ወይም ማባዛት የሚቻለው፣
   ሀ) የኮምፒዩተር ፕሮግራሙ ለታሰበለት አላማና አገልግሎት እንዲውል በኮምፒዩተር ለመጠቀም፣
   ለ) የወደፊት አጠቃቀምን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ በኮምፒዩተር ፕሮግራሙ የመጠቀም መብት ያለው ሰው መጠባበቂያ ቅጅ ሲፈልግ ወይም፤
   ሐ) የኮምፒዩተር ፕሮግራም የተሰራበትን አላማና ያለውን አቅም መሠረት በማድረግ ከኮምፒዩተር ጋር ተጣጥሞ እንዲሰራ የፕሮግራሙን አጠቃቀም ማሻሻል የግድ ሲሆን፣ ነው።

15.**ለግል አገልግሎት አላማ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት**

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 7 (1) (ሠ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለቤቱ የአንድ ሥራ ቅጅን ለግል አገልግሎት ከውጪ አገር ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን መከልከል አይችልም።

16.**በግልና ያለ ዋጋ የሚደረግ ክውና**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 (1) (ሰ) የተደነገገው ቢኖርም የቅጅ መብት ባለመብቱ በቤተሰብ ወይም በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ ዋጋ የሚደረግ ሥራን የመከወን ተግባር መከልከል አይችልም።

17.**የግዴታ ፈቃድ ስለመስጠት**

1. የቅጅ መብት ባለቤቱ ወይም ወራሽ ወይም ስጦታ ተቀባይ ተቃውሞ ቢያቀርብም ፅህፈት ቤቱ ለህዝቡ ጥቅም ሲል አንድ የታተመ ሥራ እንዲባዛ፤ እንዲተረጎም ወይም ብሮድካስት እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታና ፎርም በተለይም ለቅጅ መብት ባለቤቱ የሚሰጠው ተገቢ የሆነ ካሳ በደንብ ይወሰናል፣
3. ፅህፈት ቤቱ በዚህ አንቀፅ በተመለከተው ሥራ ላይ ለውጥ እንዲደረግ ሊፈቅድ አይችልም፤፡

18.**ስራን ለህዝብ እይታ ስለማቅረብ**

ያለ ስራ አመንጪዉ ወይም የቅጂ መብት ባለቤቱ ፈቃድ የአንድ ስራን ኦሪጂናል ወይም ቅጂ ለህዝብ ማቅረብ የሚቻለው እይታው ከፊልም ስላይድ ከቴሌቪዥን ምስል ወይም በሌላ ማናቸውም ስክሪን ወይም ከሌላ ማናቸውም መሳሪያ ወይም ሂደት ውጪ በሆነ መንገድ ሲቀርብ እና ስራው የታተመ ሲሆን ወይም የኦሪጂናል ሥራው ወይም ቅጂው በስራ አመንጪዉ ወይም በወራሹ የተሸጠ ወይም ለሶስተኛ ሰው የተሰጠ ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የተላለፈ ሲሆን ነው።

19.**ቅጂን ስለማሰራጨት**

አንድ የታተመ ሥራ ቅጅ ለህዝብ የተሸጠ ሲሆን ቅጅው ያለፈቃድ ወይም ክፍያ በሽያጭ መልክ እንደገና ሊሰራጭ ይችላል፡፡

20.**የኢኮኖሚ መብቶች ፀንተዉ የሚቆዩበት ጊዜ**

1. የኢኮኖሚ መብቶች የስራ አመንጪው በህይወት በሚቆይበት ዘመንና ከሞተ በኋላ ለወራሾቹ እስከ 50 ዓመት ጸንተው የሚቆዩ ሲሆን የጥበቃ ጊዜው መቆጠር

የሚጀምረው የስራ አመንጪው ከሞተበት ቀን ቀጥሎ ካለው እ.አ.አ ጥር 1 ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡[115]

2. በጋራ የሥራ አመንጪዎች የተሠራ ሥራን በሚመለከት ጉዳይ የ50 ዓመት ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የሥራ አመንጪው ከሞተበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣
3. የሥራው አመንጪው ከሞተ በኋላ የታተመ ሥራ የ50 ዓመት የጥበቃ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ሥራው ከታተመበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፣
4. አንድ ከኦዲዮቪዥዋል ሥራ ውጪ የሆነ ስብስብ ሥራ ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ሥራው ከተሰራበት ወይም መጀመሪያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመሪያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመት ይሆናል፣
5. ሥራው የአመንጪውን ስም ካልያዘ ወይም በብዕር ስም የታተመ ከሆነ የሥራ አመንጪው ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ሥራው ከተሰራበት ወይም መጀመሪያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመሪያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለ50 ዓመታት ይሆናል፣
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) ከተመለከተው ጊዜ በፊት የሥራው አመንጪ ማንነት ከታወቀ ወይም የማያጠራጥር ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) እንደ ሁኔታው ተፈፃሚ ይሆናል፣
7. በፎቶግራፍ ስራ ላይ ያሉ ኢኮኖሚያዊ መብቶች ፀንተው የሚቆዩት ሥራው ከተሰራበት ጊዜ ጀምሮ ለሃያ አምስት ዓመት ይሆናል፣
8. በኦዲዮቪዥዋል ሥራ ላይ ያለ ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ሥራው ከተሰራበት ወይም ለህዝብ ከተሰራጨበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመት ይሆናል፣

## ክፍል ሶስት

## የመብት ባለቤትና የህግ ግምቶች

### 21.ስለመጀመሪያ ኢኮኖሚ መብት ባለቤትነት

1. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) እስከ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ሥራ አመንጪ የኢኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤት ይሆናል፣

[115] በ21/20 872/2007 አንቀፅ 2(5) ተሻሻለ፡፡

2. አንድ ሥራ በበርካታ የሥራ አመንጪዎች የተሰራ ሲሆን የኢኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤቶች የጋራ ሥራ አመንጪዎች ይሆናሉ፤
3. አንድ ሥራ የስብስብ ሥራ ሲሆን ሥራው እንዲሰራ ያመነጨውና የአመራር አቅጣጫ የሰጠው ሰው የኢኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤት ይሆናል፤
4. አንድ ሥራ በተቀጠረ ወይም የአገልግሎት ክፍያ በተከፈለው ሰው የተሰራ ሲሆን ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር የኢኮኖሚያዊ መብቶች የመጀመሪያ ባለቤት ቀጣሪው ወይም ስራውን እንዲሰራ ያደረገው ሰው ይሆናል፣
5. ሥራው የኦዲዮቪዥዋል ሥራ ከሆነ፣
   ሀ) ፕሮዲውሰሩ የኢኮኖሚያዊ መብቶቹ ባለቤት ይሆናል፡፡ ሆኖም እስክሪፕት ፀሀፊው፣ ዳይሬክተሩ፣ የካሜራ ባለሙያው፣ የዜማ ደራሲው፣ ሌሎች የሥራ አመንጪው በሥራው ላይ የሥራ አመንጪነት መብትና ከፕሮዲውሰሩ ጋር በሚያደርጉት ውል መሠረት ክፍያ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል፣
   ለ) በኦዲዮቪዥዋል ሥራ የተካተተና በነጠላ ጥቅም ላይ የሚውል የስክሪን ፅሁፍ፣ የሙዚቃ ሥራ እንዲሁም ሌላ ሥራ አመንጪ ራሱን ችሎ በቅጅ መብቱ የመገልገል መብት ይኖረዋል።
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) የተደነገገው ቢኖርም የኦዲዮቪዥዋል ሥራ ክፍል የሆኑትን ወይም ተሻሽለው የተካተቱትን አስቀድመው የነበሩ ሥራዎችን የሰሩ የሥራ አመንጪዎች ከአስተዋፅኦቸው ወይም አስቀድሞ ከነበረው ሥራ የሚመነጩ ኢኮኖሚያዊ መብቶች ከኦዲዮቪዥዋል ሥራው ከሚመነጩ መብቶች ተለይተው እንደ ቅደም ተከተላቸው ባደረጉት አስተዋፅኦ ወይም ቀዳሚ ሥራቸው ላይ ኢኮኖሚያዊ መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል፡፡

22. <u>የስራ አመንጪነት ግምትና ዉክልና</u>

1. ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ሥራው በስሙ የታተመ ሰው የሥራው አመንጪ ተደርጎ ይቆጠራል፤
2. የሥራ አመንጪው የብዕር ስም የሚጠቀም ቢሆንም ስለማንነቱ የሚያስጠረጥር ሁኔታ ከሌለ በቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ግምት የሚያስገኘውን ጥቅም መጠየቅ ይችላል፣
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስሙ በሥራ ላይ የተጠቀሰው አሳታሚ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር የሥራ

አመንጪውን እንደወከለ ተቆጥሮ የሥራ አመንጪውን የኢኮኖሚያዊ እና የሞራል መብቶች ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይህ ግምት የሥራ አመንጪው ማንነቱን ሲያሳውቅ ተፈፃሚነት አይኖረውም

## ክፍል አራት

## ኢኮኖሚያዊ መብት ስለማስተላለፍና ፈቃድ ስለመስጠት

23.መብት ስለማስተላለፍና ፈቃድ ስለመስጠት

1. የቅጅ መብት ባለመብቱ ኢኮኖሚያዊ መብቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማስተላለፍ ወይም በፈቃድ መስጠት ይችላል፣
2. ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ መብት በሥራ አመንጪው ወይም በቅጅ መብት ባለቤቱ የሚተላለፈው ወይም ፈቃድ የሚሰጠው በፅሁፍ ይሆናል፣
3. ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊ መብት ማስተላለፍ ወይም በፈቃድ መስጠት በግልፅ ያልተመለከተን መብት መተላለፍን ወይም መፍቀድን እንደጨመረ አይቆጠርም።

24.መብት የማስተላለፍ ወይም የፈቃድ ወሰን

1. ኢኮኖሚያዊ መብትን የማስተላለፍ ወይም በፍቃድ የመስጠት ወሰን በስምምነት የተመለከተውን መብት በመገልገል ወይም በመጠቀም የተገደበ ይሆናል፣
2. የቅጅ መብት ባለቤቱ ወይም ኢኮኖሚያዊ መብቱ የተላለፈለት ወይም በፈቃድ የተሰጠው ሰው መብት ሥራው የታቀፈበትን ቁሳዊ ነገር የባለቤትነት መብትን አያጠቃልልም፣
3. በአንድ በተወሰነ የኢኮኖሚ መብት መተላለፍ ወይም መፈቀድ ላይ የተደረሰው ስምምነት የመብት መተላለፉ ወይም ፈቃዱ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ ሳይወስን ሲቀር የመብት መተላለፉ ወይም ፈቃዱ እንደቅደም ተከተሉ ከ10 ወይም ከ5 ዓመት በኋላ ይሆናል፤
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተመለከተው ስምምነት መብቱ ሥራ ላይ የሚውልበት መንገድ ወይም ዘዴ በግልፅ ሳያመለክት ከቀረ መብቱ የተላለፈለት ወይም ፈቃድ ተቀባዩ ተዋዋይ ወገኖች በጋራ ያላቸውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ዘዴዎችና መንገዶች በመጠቀም መብቱን ሥራ ላይ ሊያውል ይችላል፡፡

25.በኢኮኖሚያዊ መብቶች ስላለመጠቀም

1. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የኢኮኖሚያዊ መብት የተላለፈለት ወይም የብቸኝነት ፈቃድ ያገኘ ሰው በመብቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በበቂ ካልተጠቀመበት እና በዚህም ምክንያት የሥራ አመንጪው ህጋዊ ጥቅም የተጎዳ ሲሆን የሥራ አመንጪው የመብቱን መተላለፍ ወይም ፈቃዱን ሊሽር ይችላል፣
2. የተላለፈው ወይም የተፈቀደው መብት ሙሉበሙሉ ወይም በበቂ ሁኔታ ሥራ ላይ ያልዋለው በዋነኛነት የሥራ አመንጪው መፍትሄ ሊሰጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ተከስተው ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ስምምነት የመሻር መብት ተፈፃሚ አይሆንም፣
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው የስምምነት መሻር መብቱ ከተላለፈበት ወይም ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ወይም ሥራው ከዚህ ቀን በኋላ መብቱ ለተላለፈለት ወይም ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 3 ዓመታት ውስጥ ተፈፃሚ አይሆንም፣
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው የመሻር መብት በቅድሚያ ሊነሳ አይችልም።

## ክፍል አምስት

## ስለከዋኝ፣ ድምጽ ሪኮርዲንግ ፕሮዲዉሰርና ብሮድካስቲንግ ድርጅት መብት ጥበቃ

### 26. የከዋኝን ፈቃድ የሚጠይቁ ድርጊቶች

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ከዋኝ የሚከተሉትን ለማድረግ ወይም ሌሎች እንዲፈፅሙት ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፣
   ሀ) ብሮድካስቲንጉ ወይም ሌሎች ለህዝብ የሚሰራጩ ነገሮች፣
      i. ከዋኙ እንዲሰራ በፈቀደው መሠረት ግዙፍነት እንዲያገኝ ካልተደረገ ወይም፣
      ii. ክዋኔውን በመጀመሪያ ብሮድካስት ያደረገው ድርጅት በፈቀደው መሠረት እንደገና ብሮድካስት ካልተደረገ በቀር ክዋኔውን ብሮድካስት የማድረግ ወይም በሌላ መገናኛ መሳሪያ ለህዝብ የማሰራጨት፣
   ለ) ግዙፍነት የሌለውን ክዋኔ ግዙፍነት እንዲኖረው የማድረግ፣

ሐ) በማንኛውም መልክ ወይም አኳኋን ግዙፍነት እንዲኖረው የተደረገን ክዋኔ ማባዛት፣

መ) በቅድሚያ ግዙፍነት ያገኘን ክዋኔ ወይም ቅጅውን በሽያጭ ወይም በሌላ የባለቤትነት ማስተላለፊያ ዘዴ የማቅረብ፣

ሠ) ኦሪጅናል ክዋኔውን ወይም ቅጅውን ለኪራይ ወይም ለሕዝብ ውሰት የማቅረብ፣

ረ) ግዙፍነት ያገኘ ክዋኔን በሽቦ ወይም በሽቦ አልባ መንገድ የህብረተሰቡ አባላት በተናጠል በመረጡት ቦታ ወይም በመረጡት ሰዓት እንዲደርሳቸው የማድረግ፣

2. ከዋኙ ክዋኔው በቪዥዋል ወይም ኦዶዮቪዥዋል መልክ እንዲካተት ከፈቀደ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ተፈፃሚነት የለውም፣

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የአንድ ትዕይነት ወይም ሥራ ወይም ኦዶዮቪዥዋል ሰነድ ዋነኛ ጉዳይ የሆነ ክስተት ደጋፊ የሆነ ክዋኔን ማባዛትና ለሕዝብ ማቅረብን ከዋኙ መከልከል አይችልም፣

4. ከዋኙ ከኤኮኖሚያዊ መብቱ ውጪ ወይም ይህንኑ መብት ካስተላለፈም በኋላ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፣

ሀ) የክዋኔው አጠቃቀም የከዋኙን ማንነት መጥቀስ የማያስችል ካልሆነ በቀር ክዋኔው በቀጥታ ሲተላለፍ ወይም በድምፅ ሪኮርዲንግ ሲቀረፅ ማንነቱ እንዲታወቅ የማድረግ፣

ለ) በሥራው ላይ የሚደረግ ማንኛውንም መዛባት፣ መቆራረጥ ወይም ሌላ ማሻሻያ ስሙንና ክብሩን የሚጎዳ ከሆነ የመቃወም፣

ሐ) የዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንዳግባቡ በዚህ አንቀፅ በተመለከተው የከዋኝ መብት ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

5. በዚህ ክፍል የተመለከቱት መብቶች ክዋኔው በድምፅ ሪከርዲንግ ግዙፍነት ካገኘበት ወይም ግዙፍነት በሌለ ጊዜ ክዋኔው ከተፈፀመበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ለ50 ዓመት ፀንቶ ይቆያል፡፡

27.<u>የድምፅ ሪኮርድ ፕሮዲዉሰር ብቸኛ መብቶች</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 28 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የድምፅ ሪኮርድ ፕሮዲውሰር የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሶስተኛ ወገን እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፣

ሀ) በማንኛውም አኳኋን ወይም መልክ የድምፅ ሪኮርዱን የማባዛት፣

ለ) የድምፅ ሪኮርዱን ቅጅዎች ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት፣

ሐ) በሽያጭና መሰል የባለቤትነት ማስተላለፊያ መንገድ በፕሮዲውሰሩ ፈቃድ ለስርጭት ያልቀረበ የድምፅ ሪኮርዲንግ ኦሪጅናል ወይም ቅጂውን ለሕዝብ የማሰራጨት፣

መ) ለኪራይ ወይም ለውሰት የቀረበ ቅጂ ላይ ያለ ባለቤትነት ከግምት ሳይገባ የድምፅ ሪከርድ ቅጅ ለሕዝብ በኪራይ ወይም በውሰት የማቅረብ፣

ሠ) የድምፅ ሪኮርዲንግን በሽቦ ወይም በሽቦ አልባ መንገድ የሕብረተሰቡ አባላት በተናጠል በመረጡት ቦታ ወይም ሰዓት እንዲደርሳቸው የማድረግ፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው መብት የታተመ የድምፅ ሪኮርዲንግ ሲሆን ከታተመበት ዓመት የመጨረሻ ቀን ወይም የድምፅ ሪኮርዲንጉ ያልታተመ ሲሆን ግዙፍነት ካገኘበት ዓመት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ለ50 ዓመት ፀንቶ ይቆያል፡፡

28.<u>የድምፅ ፕሮዲውሰር ግዴታዎች</u>

1. ማናቸውም የድምፅ ሪኮርዲንግ ወይም የኦዲዮቪዥዋል ሥራ ፕሮዲውሰር በሪከርዲንግ ሌብሉ ወይም በመያዣው ላይ የሚከተሉትን መጥቀስ አለበት፣

ሀ) የሥራውን ወይም የሥራዎቹን ርዕስ፣

ለ) የሥራ አመንጪውንና የዋነኛ ከዋኞቹን ስም፣

ሐ) የፕሮዲውሰሩ ስም ወይም መለያ ምልክት፣ እንዲሁም፣

መ) በዚህ አዋጅ መሠረት ፕሮዲውሰሩ ያገኘው መብት የተጠበቀ ስለመሆኑ፣

2. ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ዓላማ አንድ የሙዚቃ ቡድን ወይም ኦርኬስትራ በስሙ እና መሪ በኖረ ጊዜ በመሪው ስም ይጠራል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው በሪከርዲንግ ሌብሉ ወይም በመያዣው ላይ የተጻፈ ጽሁፍ የድምጽ ሪከርዲንግ ወይም ኦዲዮ-ቪዥዋል ስራ

ፕሮዲውሰር መብት በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ፍሬ ነገርን የሚያስረዳ መነሻ ማስረጃ ይሆናል፡፡[116]

29.ስለ መብት ጥበቃ ማስታወቂያ

1. የኦዲዮቪዥዋል ወይም የድምጽ ሪኮርዲንግ ቅጂ ለንግድ ዓላማ እንዲውል ሲዘጋጅ ሌብል ወይም መያዣው ፕሮዲውሰሩ የመብት ጥበቃ ያለው መሆኑን በበቂ ሊያሳውቅ በሚችል አኳኋን የተቀመጠና፤
   ሀ) የ (p) ን ምልክት እና
   ለ) ሪኮርዱ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመበትን ዓመት የያዘ ማስታወቂያ ይታተምበታል፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ማስታወቂያ የፕሮዲውሰሩን መብት በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ፍሬ ነገርን የሚያስረዳ መነሻ ማስረጃ ይሆናል፡፡

30.የብሮድከስቲንግ ድርጅትን ፈቃድ የሚጠይቁ ድርጊቶች [117]

1. ማንኛውም የብሮድካስቲንግ ድርጅት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም እንዲፈፀሙ ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፣
   ሀ) ብሮድካስቱን እንደገና ብሮድካስት የማድረግ፣
   ለ) ብሮድካስቱ ግዙፍነት እንዲያገኝ የማድረግ፣
   ሐ) ግዙፍነት ያገኘውን ብሮድካስቱን የማባዛት
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው መብት ብሮድካስት ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ለሃያ ዓመት ፀንቶ ይቆያል፡፡

31. የመብት ገደቦች

1. በዚህ አዋጅ ከአንቀፅ 26 እስከ 31 ያሉት መብቶች ከሚከተሉት ድርጊቶች ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የላቸውም፤
   ሀ) ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ከአንድ ሥራ ላይ በአጭሩ የተወሰዱ መጣጥፎችን ለወቅታዊ ሁኔታ ዘገባ የመጠቀም፣
   ለ) ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ የማባዛት፣

116 በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(6) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

117 የዚህ አዋጁ ነባሩ አንቀፅ 30 በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(7) ተሰርዞ ነባሮቹ አንቀጽ 31 እና 32 እንደ ቅደም ተከተላቸው አንቀጽ 30 እና 31 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

ሐ) ለማስተማሪያነት ወይም ማብራሪያ ለመስጠት የታተሙ ክንዋኔዎች ወይም የድምፅ ሪኮርዲንግን ሳይጨምር ፊት ለፊት ለማስተማር ዓላማ የማባዛት ብቻ፣

መ) በክፍል ሁለት በተጠቀሰው መሠረት አንድን ሥራ ያለ አመንጪው ወይም ሌላ የቅጅ መብት ባለቤቱ ፈቃድ መጠቀም በሚቻልባቸው ሁኔታዎች፣

## ክፍል ስድስት[118]

## የጋራ አስተዳደር ማህበር

### 32.የጋራ አስተዳደር ማህበር አመሰራረት

1. በዚህ አዋጅ ጥበቃ የሚያገኙ ስራዎች ባለመብቶች መብቶቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር የሚያስችላቸውን የጋራ መብት አስተዳደር ማህበር ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡
2. የጋራ አስተዳደር ማህበር በጽሕፈት ቤቱ በሚሰጥ እውቅና የሚመሠረት ይሆናል፡፡
3. የጋራ አስተዳደር ማህበር የሚመሠረተው ትርፍ የማግኘት ላልሆነ ዓላማ ይሆናል፡፡
4. የጋራ አስተዳደር ማህበር አደረጃጀት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 33.የጋራ አስተዳደር ማህበርን ለመመስረት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1. ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ የጋራ አስተዳደር ማህበር ምስረታ ዕውቅና ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ በጽሁፍ መቅረብ ይኖርበታል፦

   ሀ) የአባላት የፈጠራ ስራ ዓይነት መግለጫ፤

   ለ) የውስጥ አሰራር ደንብ፤

   ሐ) የመመስረቻ ጽሁፍ፤ እና

   መ) በስሩ የተቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት እና የማህበራቱ አባላት ዝርዝር።
2. የጋራ አስተዳደር ማህበሩ በሥሩ የሚያቋቁማቸው የዘርፍ ማህበራት ቁጥር ከሶስት ማነስ የለበትም፡፡

[118] በዚህ ክፍል (ከአንቀፅ 32 እስከ 39) በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(8) መሰረት አዲስ የገባ ነዉ፡፡

## 34.የጋራ አስተዳደር ማህበሩ ስልጣንና ተግባር

የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ ጥበቃ የሚደረግላቸው እንዲሁም የውጭ አገር ጥበቃ ያላቸውን ስራዎች ከሚጠቀሙ ሰዎች ሮያሊቲ የመሰብሰብ እና መብት ላላቸው አባላት የማከፋፈል፤
2. የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ረቂቅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በማዘጋጀት ለጽህፈት ቤቱ የማቅረብ፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ የማድረግ፤
3. የሮያሊቲ  አሰባሰብንና አከፋፈልን አስመልክቶ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ለጽሕፈት ቤቱ የማቅረብ፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ የማድረግ፤
4. ለአባላት ከሚከፈል የሮያሊቲ ክፍያ በህግ መሠረት ግብር ተቀናሽ በማድረግ አግባብ ላለው ገቢ ሰብሳቢ አካል ገቢ የማድረግ፤
5. ለህዝብ ለመቅረብ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ስራዎችን ለማቅረብ ከሌሎች አገራት ለሚገቡ የባንድ ወይም የክወና ቡድኖች እንዲሁም ለስነ ጥበብ ስራዎች ዓውደ ርዕይ አቅራቢዎች በተመጣጣኝ ክፍያ ፈቃድ የመስጠት፤
6. ባለቤት የሌላቸው ስራዎችን ሮያሊቲ በመሰብሰብ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ የማደረግ፤
7. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፤
8. በማንኛውም ጊዜ በጽሕፈት ቤቱ ሲጠየቅ የሥራ ሪፖርት የማቅረብ፤
9. ለተመሠረተበት ዓላማ አስፈላጊ የሆኑ በጽሕፈት ቤቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

## 35.በጀት

1. የጋራ አስተዳደር ማህበር በጀት ከሚከተሉት ምንጮች በሚገኝ ገቢ የሚሸፈን ይሆናል፦

   ሀ) በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚሰበሰብ የሮያሊቲ ክፍያ ከሚደረግ ተቀናሽ፣

   ለ) ከአባልነት መዋጮ፣

   ሐ) ከሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) መሠረት የሚደረገው ዓመታዊ ተቀናሽ መጠን ከሚሰበሰበው አጠቃላይ ሮያሊቲ ከሰላሳ በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የሮያሊቲ ተቀናሽ መጠን ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በየዓመቱ ለጽህፈት ቤቱ ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

## 36.የሂሳብ መዛግብት

1. የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን መያዝ አለበት፡፡
2. የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውጪ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡
3. የጋራ አስተዳደር ማህበር ኦዲት የተደረገውን ያለፈውን ዓመት የሂሳብ ሪፖርት እና የቀጣዩን ዓመት በጀት ለጽሕፈት ቤቱ ያቀርባል።
4. የጋራ አስተዳደር ማህበር የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ በጀት ዓመት መሰረት ይሆናል፡፡
5. ጽሕፈት ቤቱ በማናቸውም ጊዜ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የፋይናንስ ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊጠይቅ እንዲሁም የሂሳብ መዛግብቱን ሊመረምር ይችላል፡፡

## 37.እውቅና ስለመሰረዝ

ጽሕፈት ቤቱ በሚከተሉት ምክንያቶች የማንኛውንም የጋራ አስተዳደር ማህበር እውቅናን ሊሰርዝ ይችላል፦

1. በዚህ አዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች ተጻራሪ የሆኑ ተግባራትን ፈጽሞ ሲገኝ፤
2. በአባላት አብላጫ ድምጽ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ እንዲፈርስ የተወሰነ ሲሆን፤ ወይም
3. ሥልጣን ባለው የዳኝነት አካል የጋራ አስተዳደር ማህበሩ እውቅና እንዲሰረዝ ውሳኔ የተላለፈበት ሲሆን ነው።

## 38.ሮያሊቲ የመክፈል ግዴታ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ጥበቃ የሚያገኝ ማንኛውንም ስራ ለንግድ ዓላማ ጥቅም ላይ የሚያውል ማንኛውም ሰው የሮያሊቲ ክፍያን ለሚመለከተው የጋራ አስተዳደር ማህበር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል።
2. የሮያሊቲ ክፍያ የሚፈጸምባቸው ስራዎች ምድብ እና ክፍያ ሊፈጽሙ የሚገባቸው ተጠቃሚዎች ዝርዝር የጋራ አስተዳደር ማህበራት በሚያቀርቡት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተመሥርቶ በጽሕፈት ቤቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡

39.<u>ባለቤት ከሌላቸው ሥራዎች የሚሰበሰብ ሮያሊቲ</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ የሥራውን ዓይነት ግምት ውስጥ በማስገባት ባለቤት ከሌላቸው ሥራዎች የሚሰበሰብ የሮያሊቲ ክፍያን ሊሰበስብ የሚገባውን የጋራ አስተዳደር ማህበር በመለየት ያሳውቃል፡፡
2. ባለቤት ከሌለው ስራ የሚሰበሰብ የሮያሊቲ ክፍያ መጠን በተመሳሳይ ወቅት ለተመሳሳይ ሥራ በጋራ አስተዳደር ማህበሩ ከሚሰበሰብ የሮያሊቲ መጠን ጋር እኩል ይሆናል፡፡
3. ባለቤት ከሌላቸው ሥራዎች የሚሰበሰብ ሮያሊቲ በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ልማት ዘርፍ ለሚከናወኑ ተግባራት የሚውል ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት[119]

## ስለመብቶች ተፈፃሚነት

40.<u>በጊዜያዊነት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. ፍርድ ቤት፣
   ሀ) በቅጂ ምክንያት የሚፈጠርን የመብት ገሰሳ መከላከል በተለይም የጉምሩክ ክሊራንስን ጨርሰው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ጨምሮ እቃዎች ወደ ንግድ ውስጥ እንዳይገቡ ለማድረግ፣
   ለ) ተፈፀመ የተባለን የመብት ገሰሳ የሚያስረዳ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ለመጠበቅ፤ ፈጣንና ውጤታማ የጊዜያዊ እርምጃ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ አግባብ ሆኖ ሲገኝ በተለይም መዘግየቱ በባለመብቱ ላይ ሊተካ የማይችል ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ከሆነ ወይም ማስረጃ እንደሚጠፋ በግልፅ የሚታይ አደጋ ካለ ሌላው ወገን ሳይሰማ ጊዜያዊ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፣
3. ተከሳሹ መብት ከመጣስ እንዲታቀብ በቀረበ ክስ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ከሳሹ የመብት ገሰሳን ለማስቆም ጊዜያዊ የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም፡-

---

[119] ነባሩ ክፍል ስድስት በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(9) መሰረት ክፍል ሰባት ሆኖ በዚሁ ክፍል ከአንቀጽ 33 እስከ 36 ያሉት ነባር ድንጋጌዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 40 እስከ 43 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

ሀ) በእግድ ትእዛዝ ጥያቄው ላይ ለመወሰን አደጋ ላይ የወደቀው ጥቅም በካሳ ሊሸፈን የማይችል መሆኑን፣ አደጋው የማይቀር መሆኑን፣ የክሱን ጥንካሬና ውሳኔ መስጠት በእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት መመርመር አለበት፣

ለ) የእግድ ትእዛዙን ሊሰጥና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እግዱ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ተከሳሹ የሚያስፈልገውን ገንዘብና ዋስትና ወይም ሌሎች ጉዳዮች ሊያመለክት ይችላል፣

ሐ) ከፍ ሲል በተመለከተው መመዘኛ ተከራካሪዎች ሲመዘኑ በእኩል ደረጃ በሆኑ ጊዜ ጊዜያዊ እግድ ከመስጠቱ በፊት አንፃራዊ ጥንካሬያቸው ላይ ጥልቅ ምርመራ ማድረግ ይችላል፣

4. በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኘን መብት የሚጥስ ተግባር በተፈፀመ ጊዜ ብርበራና ዕቃ መያዝን የሚመለከቱ የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግና የወንጀል ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፣

5. ፍርድ ቤቱ አመልካች የመብት ባለቤት መሆኑን እና መብቱ መጣሱን ወይም ሊቀር የማይችል የመብት መጣስ አደጋ መኖሩን፣ በበቂ ደረጃ ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ እንዲያቀርብ እና ተከሳሹን ከጉዳት ለመጠበቅ አመልካቹ መያዣ ወይም ተመጣጣኝ ዋስትና እንዲያቀርብ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፤

6. ሌላው ወገን ሳይሰማ ጊዜያዊ እርማጃ በተወሰደ ጊዜ በእርምጃው የተጎዳ ወገን እርምጃው ተፈፃሚ እንደሆነ ወዲያውኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡ እርምጃው ከተገለፀ በኋላ ተከሳሹ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ የተወሰደውን እርምጃ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም ለመለወጥ የሚያስችል ውሳኔ ለመስጠት የመስማት መብት ጨምሮ በቂ ጊዜ በመስጠት ጉዳዩ እንደገና መታየት አለበት፤

7. ጊዜያዊ እርምጃው የተሻረ ወይም አመልካቹ በፈፀመው ወይም ሳይፈፅመው በቀረ ድርጊት ምክንያት እርምጃው ሳይፈፅም የቀረ ከሆነ ወይም ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ የተጣሰ ወይም የመጣስ አደጋ ያጋጠመው መብት የሌለ መሆኑ ከታወቀ በተከሳሹ ጠያቂነት ለደረሰበት ጉዳት በቂ ካሳ እንዲከፈለው ፍርድ ቤቱ ማዘዝ አለበት፡፡

41.<u>የፍትሐብሄር መፍትሔዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ የሚነሱ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን አስመልክቶ የዳኝነት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የመብቱ ባለቤት ያወጣውን ወጪ ጨምሮ ለደረሰበት ቁሳዊ

ወይም ሞራላዊ ጉዳት በቂ ካሳ እንዲከፈለው የማዘዝ፣ ጊዜያዊ እግድ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ በታች የተመለከተውን ጨምሮ ማንኛውንም ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ትእዛዝ መስጠት አለበት፣

ሀ) በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኘ መብት እንዳይጣስ የመከላከል ወይም የመብት መጣስ እንዲቆም ጊዜያዊ እግድ የመስጠት፤

ለ) ቅጅን የመስራት ወይም ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ድርጊት የባለቤቱ ፈቃድ የሚያስፈልገው ሲሆን ያለ ባለቤቱ ፈቃድ የተሰራ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ሥራን እንዲወረስ የማዘዝ፣

ሐ) ከቅጂዎች ጋር የተያያዙ ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች ወይም የንግድ ሥራ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወረቀቶችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና እሽጎች እንዲያዙ ትእዛዝ የመስጠት፣

2. የቅጅ መብት ወይም የተዛማጅ መብት ባለቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተመለከተው ካሳ በምትክ ወይም በአማራጭ ከመብት መጣሱ አላግባብ የተገኘ ብልፅግና እንዲተካለት ሲጠይቅ ይችላል፣ መብት ጣሹ በባለቤቱ ፈቃድ ቢሰጠው ኖሮ ፈቃዱን በመጠቀሙ ምክንያት ይከፍለው የነበረውን ያህል አላግባብ እንደበለፀገ ይቆጠራል፣

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ቢኖርም የመብቱ ባለቤት በመብት ጣሹ የተገኘ የተጣራ ትርፍ ብቻ እንዲከፈለው ሊጠይቅ ይችላል። በዚህ ጊዜ መብት ጣሹ ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለመወሰን ሂሳብ የሚሰራ ሲሆን ትርፉ በሌሎች የገበያ ሁኔታዎች ምክንያት የተገኘ መሆኑን የማስረዳት ሀላፊነት የመብት ጣሹ ይሆናል፣

4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ለደረሰ ቁሳዊ ጉዳት የሚከፈል ካሳ መጠን የመብት ባለቤቱ የደረሰበትን የገንዘብ ጉዳት እና በመብቱ መጣስ ምክንያት የተገኘ ትርፍን ግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰናል፡፡ ለሞራል ጉዳት የሚከፈል ካሳ ከብር 100,000 (አንድ መቶሺ ብር) የማያንስ ሆኖ የደረሰውን ጉዳት መሠረት በማድረግ ይወሰናል፤

5. የመብት መጣስ ድርጊት የፈፀመው ሰው ድርጊቱን ያላወቀ ከሆነ ወይም ሊያውቅ የሚያስችለው በቂ ምክንያት የሌው ከሆነ ፍርድ ቤቱ ካሳው ከድርጊቱ በተገኘ ትርፍ ላይ ብቻ እንዲወሰን ሊያደርግ ይችላል፤

6. መብት የጣሱ ቅጂዎችና ጥቅሎች መኖራቸው የታወቀ ከሆነ ባለቤቱ በተቃራኒው ካልጠየቀ በቀር ፍርድ ቤቱ ቅጂዎቹ በባለቤቱ መብት ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ከንግድ እንቅስቃሴው ውጭ እንዲሆኑ ወይም እንዲወገዱ ወይም በሌላ ተገቢ አኳኋን እንዲጣሉ ለማዘዝ ይችላል። ይህ ድንጋጌ ቅጂዎቹንና ጥቅሉን በቅን ልቦና በያዘ ሶስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

## 42.የድንበር ላይ እርምጃዎች

1. የኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን የቅጅ ወይም ተዛማጅ መብት ባለቤት በሚያቀርበው ማመልከቻ መሰረት አመልካቹ መብቱን የጣሱ ናቸው ተብሎ ያመነባቸውን ዕቃዎች ወይም በራሱ አነሳሽነት የመብት ጥሰት ያስከትላሉ ብሎ ያመነባቸውን ዕቃዎች በቁጥጥሩ ስር መያዝ ይኖርበታል፡፡[120]
2. የጉምሩክ ባለሥልጣኑ ዕቃውን ለመያዝ የወሰደውን እርምጃ በተመለከተ ለአመልካቹ ወይም ለዕቃው ባለቤት ወዲያውኑ ያሳውቃል፤
3. አመልካቹ ዕቃው ስለመያዙ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ ተገቢውን ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻለ ዕቃውን ለመያዝ የተወሰደው እርማጃ ይነሳል፤
4. ዕቃ እንዲያዝ የቀረበው ማመልከቻ ህጋዊ መሠረት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ዕቃው በመያዙ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት አመልካቹ ተጠያቂ ይሆናል፤
5. በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት የጉምሩክ ባለሥልጣን መብት የጣሰን ዕቃ መውረስ ይችላል፤

## 43.የወንጀል ቅጣት[121]

1. በወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያሰቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኙ መብቶችን ሆነ ብሎ የጣሰ ማንኛውም ሰው ከ5 ዓመት በማያንስ እና ከ10 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፤
2. በወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኙ መብቶችን ከፍ ባለ ቸልተኝነት የጣሰ ማንኛውም ሰው ከ1 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፤

[120] በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(10) ተሻሻለ፡፡
[121] የዚህ አንቀፅ ንዑሰ አንቀፆች (4) እና (5) በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(11) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸዉ፡፡

3. አግባብነት ባለው ጊዜ ቅጣቱ ወንጀሉን ለመፈፀም ያገለገሉ እቃዎች ወይም መሳሪያዎች እና መብት የጣሱ ዕቃዎችን መያዝ፣ መውረስ እና ማውደምን ይጨምራል።
4. ጥበቃ ያገኙ መብቶችን ሆነ ብሎ የጣሰ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተደነገገው የእስራት ቅጣት በተጨማሪ ከብር 25,000 በማያንስ እና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጫ ይቀጣል፡፡
5. ጥበቃ ያገኙ መብቶችን በከፍተኛ ቸልተኝነት የጣሰ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተደነገገው የእስራት ቅጣት በተጨማሪ ከብር 5,000 በማያንስ እና ከብር 25,000 በማይበልጥ መቀጫ ይቀጣል፡፡

## ክፍል ስምንት[122]

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 44.የዳኝነት ስልጣን

1. ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሃላፊነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን የሚኖረው ጽሕፈት ቤቱ የሚያቋቁመው የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል ይሆናል፡፡
2. የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናሉ ውሳኔ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ተዛብቷል በሚል ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ60 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል እስኪቋቋም ድረስ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታዩ ይሆናል፡፡

### 45.በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ ስለሚፈጸም ቅጣት

በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ህግ አንቀጽ 34 በተመለከተው መሠረት በዚህ አዋጅ ጥበቃ ባገኙት ቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥሰት ወንጀል ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 90 መሠረት ይቀጣል፡፡

---

[122] ነባሩ ክፍል ሰባት በ21/20 (2007) አ. 872 አንቀፅ 2(12) መሰረት ክፍል ስምንት ሆኖ በዚሁ ክፍል አዲስ አንቀፅ 40፣ 45 እና 46 የገቡ ሲሆን፣ ነባሮቹ ከአንቀጽ 37 እስከ አንቀጽ 40 እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 47 እስከ አንቀጽ 50 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

46.**<u>ውሳኔዎችን ለሕዝብ ስለማወቅ</u>**

ጽሕፈት ቤቱ በቅጅና ተዛማጅ መብት ጥሰት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ማንኛውንም ጉዳይ ሰፊ ሥርጭት ባለው የብዙሃን መገናኛ ዘዴ እንዲሰራጭ ያደርጋል፡፡

47.**<u>ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች ጥበቃ ስላላቸው ሥራዎች</u>**

1. ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት በነበሩና የጥበቃ ጊዜያቸው ፀንተው በሚገኙ ሥራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
2. ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት በተደረጉ ሥራን የሚመለከቱ ውሎች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

48.**<u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ሕግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

49.**<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም ፅህፈት ቤቱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

50.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ግዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 17 ቀን 1996 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 305/2006

## የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የሚያስገኙ ሥራዎች ለመመዝገብ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 39(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የሚያስገኙ ሥራዎች ምዝገባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 305/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "አዋጅ" ማለት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/1996 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
   3. "ጽሕፈት ቤት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 320/1995 የተቋቋመው የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ነው፤
   4. በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **ስለምዝገባ**

   1. የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎች ባለቤት ወይም መብቱ የተላለፈለት ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ለጽሕፈት ቤቱ በማመልከት መብቱን ማስመዝገብ ይችላል፡፡
   2. ጽሕፈት ቤቱ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎችን በዚህ ደንብ መሠረት የመመዝገብና የናሙና ስራዎችን ጠብቆ የማቆየት ኃላፊነት ይኖረዋል።

4. **የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎች ምድብ**

   የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎች በሚከተሉት ምድብ መሠረት ሊመዘገቡ ይችላሉ፦

   1. የፅሁፍ ወይም የቃል ሥራ፤
   2. የመድረክ፣ የሙዚቃና የኦዲዮቪዥዋልና የመሳሰሉት የኪነ-ጥበብ ሥራዎች፤
   3. የፎቶግራፍ፣ የሥዕል፣ የግራፊክስና የኪነ-ሕንፃን የመሳሰሉ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች፤

4. የኮምፒውተር ፕሮግራሞች፣
5. የድምፅ ሪከርድ፣
6. ብሮድካስት፡፡

5. <u>**የምዝገባ መመዘኛዎች**</u>

**ቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ማንኛውም ሥራ ሊመዘገብ የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 6 ላይ የተመለከቱትን መመዘኛዎች ሲያሟላ ይሆናል፡፡**

6. <u>**ስለምዝገባ ማመልከቻ ይዘት**</u>

1. የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ለማስመዝገብ ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ ማንኛውም ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡
   ሀ) የአመልካቹ ሙሉ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፣
   ለ) አመልካቹ በሥራው ላይ ያለው የጥቅም ዓይነት፣
   ሐ) የሥራው ምደባና መግለጫ፣
   መ) የሥራው ርዕስ
   ሠ) ስራዉ የተዘጋጀበት ቋንቋ፣
   ረ) የሥራው አመንጪ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፣
   ሰ) የሥራው አመንጪ በሕይወት የሌለ እንደሆነ የሞተበት ቀን፣
   ሸ) ሥራው የታተመ መሆን አለመሆኑ፣
   ቀ) ሥራው የታተመ ከሆነ መጀመሪያ የታተመበት ዓመት፣ የታተመበት አገር እና የአሳታሚው ስም፣ አድራሻና ዜግነት፣
   በ) ሥራው በተከታታይ የታተመ ከሆነ የታተመባቸው ዓመታት፣ የታተመባቸው አገሮች እና የአሳታሚዎቹ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፣
   ተ) ጽሕፈት ቤቱ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሥራው ናሙና እና ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-
   ሀ) የአመልካቹ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ፣
   ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ሕጋዊ ሰውነት ማግኘቱን የሚያሳይ ሰነድ፣
   ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ የውክልና ማስረጃ፣
   መ) አመልካቹ የሥራው አመንጪ ካልሆነ ባለመብትነት ያገኘበት ሰነድ፣

ሠ) በዚህ ደንብ መሠረት የተፈጸመ የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፤

ረ) ጽሕፈት ቤቱ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ሰነዶች

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከማመልከቻ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ ካልሆነ የአማርኛ ወይም የእንግሊዘኛ ትርጉሙ አብሮ መቅረብ ይኖርበታል።

7. **<u>የምዝገባ ማመልከቻ አቀራረብ</u>**

   1. ማንኛውም የቅጅና ተዛማጅ መብት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል።
   2. ማመልከቻውና ተያያዥ ሰነዶች በጽሕፈት ቤቱ የፖስታ ወይም የድረ ገጽ አድራሻ ሊላኩ ይችላሉ፡፡
   3. ማመልከቻው በፖስታ ቤት በኩል የሚላክ ሲሆን የጽሕፈት ቤቱን ትክክለኛ ስምና አድራሻ መግለጽ ይኖርበታል።
   4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አመልካቹ ወይም ወኪሉ በግንባር እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

8. **<u>አንድ ማመልከቻ ለአንድ ስራ ብቻ ስለመሆኑ</u>**

   1. ማንኛውም በዚህ ደንብ መሠረት ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ አንድ ማመልከቻ አንድ ቅጅን ወይም ተዛማጅ መብትን የሚያስገኝ ሥራን ብቻ ለማስመዝገብ መቅረብ ይኖርበታል።
   2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም እንደ ኢንሳይክሎፒዲያ ያሉ በተከታታይ ክፍሎች የታተሙ ሥራዎች አንድ ማመልከቻ ብቻ በማቅረብ ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

9. **<u>የፎርማሊቲ ምርመራ</u>**

   1. ጽሕፈት ቤቱ የቀረበለትን ማመልከቻ ተቀብሎ በአዋጁና በዚህ ደንብ የተቀመጡት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የፎርማሊቲ ምርመራ ያካሂዳል።
   2. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለፎርማሊቲ ምርመራ የቀረበለት ማመልከቻ ጉድለት ያለበት ሆኖ ካገኘው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እርማት እንዲደረግ ለአመልካቹ ወይም ለወኪሉ በጽሁፍ ያሳውቃል።

3. አመልካቹ ወይም ወኪሉ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን እርማት ወይም ማስተካከያ ካላደረገ ማመልከቻው እንደተተወ ይቆጠራል።

10.<u>የአመልካች ቃለ መሃላ</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ በሚቀርብለት የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ምዝገባ ማመልከቻ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ የሥረ-ነገር ምርመራ አያደርግም፤ ሆኖም አመልካቹ ባለቤት ስለመሆኑ በቃለ መሃላ እንዲያረጋርገጥ ይደረጋል፡፡
2. አመልካቹ የሰጠው ቃለ መሃላ ትክክለኛ ሆኖ ባይገኝ ለፈጸመው የማጭበርበር ተግባር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

11.<u>የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

ማመልከቻው የፎርማሊቲ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ሲሆን ጽሕፈት ቤቱ ቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራውን በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

12.<u>የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት ይዘትና የህግ ዉጤት</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ የሚሰጠው የቅጂ እና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፦
   ሀ) የምዝገባ ቁጥር፤
   ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6(1) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተመለከቱትን ዝርዝሮች፤
   ሐ) የማመልከቻውን ቀን፤
   መ) የምዝገባውን ቀንና ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤
   የሚይዝ ይሆናል፡፡
2. ጽሕፈት ቤቱ የሚሰጠው የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቀዳሚ የባለቤትነት ማስረጃ በመሆን ያገለግላል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ በዚህ ደንብ መሠረት አለመመዝገቡ በአዋጁ መሠረት የሚደረግ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃን አያስቀርም፡፡

13.<u>የምዝገባ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ስለእድሳት</u>

1. የቅጂና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ይሆናል፡፡

2. ባለመብቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደተጠናቀቀ ቀጥሎ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡
3. ባለመብቱ በአዋጁ የተደነገገው የመብት ጥበቃ ጊዜ ጸንቶ የሚቆይበት ዓመት እስኪያበቃ ድረስ በየአምስት ዓመቱ በተከታታይ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመብቱ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈጸም የዕድሳት ጥያቄ ለጽሕፈት ቤቱ ካላመለከተ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

14.<u>ስለመብት መተላለፍ ምዝገባ</u>

1. የተመዘገበ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ መብት ለሌላ ሰው ሲተላለፍ መብቱ የተላለፈለት ሰው መብቱ መተላለፉን የሚገልጹ አግባብ ያላቸው ማስረጃዎችን በማያያዝ ለጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብና ማስመዝገብ ይችላል፡፡
2. መብቱ የተላለፈለት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር የአገልግሎት ክፍያ መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ የመብቱን መተላለፍ መዝግቦ መብቱ በተላለፈለት ሰው ስም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

15.<u>የተመዘገቡ ስራዎች መረጃ ስለመመልከት</u>

1. ፍርድ ቤቶች፣ የፖሊስና የዐቃቤ ሕግ ተቋማት እና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት ጽሕፈት ቤቱን በጽሁፍ በመጠየቅ የተመዘገቡ የቅጅና ተዛማጅ መብት ሥራዎችን በሚመለከት በጽሕፈት ቤቱ የተያዙ መረጃዎችን ያለክፍያ ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ በማቅረብና አግባብ ያለውን ክፍያ በመፈጸም የተመዘገቡ የቅጅና ተዛማጅ መብት ሥራዎችን በሚመለከት በጽሕፈት ቤቱ የተያዙ መረጃዎችን ሊመለከት ይችላል፡፡

16.<u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

ጽሕፈት ቤቱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚፈጸመው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

17.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 19 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**የአገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ አይነት | የክፍያዉ መጠን በብር | |
|---|---|---|---|
| | | ለግለሰብ | ለድርጅት |
| 1 | ለምዝገባ ጥያቄ ማመልከቻ | 250 | 315 |
| 2 | ለምዝገባ ማመልከቻ እርማት | 250 | 315 |
| 3 | የምዝገባ እድሳት | 250 | 315 |
| 4 | የመብት መተላለፍ ምዝገባ | 300 | 375 |
| 5 | የተመዘገቡ ስራዎችን መረጃ ለመመልከት | 100 | 125 |

## አዋጅ ቁጥር 501/1998

## የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ

ዕቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስም እና ዝና ለመጠበቅ፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መካከል መሳከርን ለማስወገድ የንግድ ምልክት ጥበቃ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የንግድ ምልክቶች በነፃ ገበያ ሥርዓት ውስጥ የሸማቾችን ምርጫ በመምራት እና ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው የታወቀ በመሆኑ፤

ለንግድ ምልክቶች ጥበቃ ማድረግ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ መዳበር በተለይም ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ልማት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው በመታመኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. “የወል የንግድ ምልክት” ማለት በባለቤትነት የያዘውን ማህበር አባላት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያገለግል የንግድ ምልክት ነው።
   2. “ፍርድ ቤት” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 የተመለከተው ፍርድ ቤት ነው።
   3. “ቀዳሚ የንግድ ምልክት” ማለት በንግድ ምልክት መዝገብ የተያዘ የንግድ ምልክት ወይም የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን በፊት የምዝገባ ማመልከቻ ቀን ያለው የንግድ ምልክት ነው።
   4. “የውጭ አገር ሰው” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገበ የንግድ ሥራ የሌለው ሰው ነው።

5. "የጉምሩክ ወደብ" እና "የጉምሩክ ጣቢያ" የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989[123] የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡
6. "ዓለም ዓቀፍ ምደባ" ማለት በኒስ ዲፕሎማቲክ ኮንፈረንስ እ.ኤ.አ ጁን 15 ቀን 1957 በተመሠረተው እና በስቶክሆልም እ.ኤ.አ በ1967፣ በጄኔቫ እ.ኤ.አ በ1977 እንዲሁም 1979 በተሻሻለው ለንግድ ምልክት ምዝገባ እንዲያገለግል በወጣው የኒስ የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ምደባ ስምምነት መሠረት የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ምደባ ነው።
7. "የፈቃድ ውል" ማለት የንግድ ምልክት ባለቤት ማንኛውም ሌላ ሰው የንግድ ምልክቱ ለተመዘገበባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በሙሉ ወይም በከፊል በንግድ ምልክቱ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት በስምምነት ነው።
8. "ጽሕት ቤት" ማለት የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት ነው።
9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡
10. "የቀዳሚነት ቀን" ማለት ለቀዳሚ ባለመብትነት መነሻ የሚሆነው ቀዳሚ የምዝገባ ማመልከቻ የገባበት ቀን ነው።
11. "ደንብ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 መሠረት የሚወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ነው።
12. "የንግድ ምልክት" ማለት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው። ምልክቱ ቃላቶችን፣ ዲዛይኖችን፣ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀለሞችን ወይም የዕቃዎችን ወይም የመያዣዎቻቸውን ቅርፅ ወይም የእነዚህኑ ቅንጅት ሊይዝ ይችላል፡፡
13. "የቤተዘመድ ስም" ማለት የአንድ ቤተሰብ አባላት በተናጠል ከሚሰጣቸው ስም በተለይ በወል የሚጠቀሙበት የመለያ ስም ሲሆን የቤተሰብ ስም ወይም የመጨረሻ ስም በመባልም ይታወቃል፡፡

[123] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ለአቻ ትርጉም 20/82 (2006) አ.859ን ተመልከት፡፡

3. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

በእንካ ለእንካ መርሆ ወይም ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት ዓለም አቀፍ ውል ላይ በመመስረት የውጭ አገር ሰዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ኢትዮጵያውያን ያሏቸው መብቶችና ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የንግድ ምልክት ላይ ባለመብትነት ስለማግኘት እና ምዝገባ</u>**

4. **<u>መብቶችን ስለማግኘት</u>**

የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት የሚገኘውና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረው የንግድ ምልክት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሲሰጥ ይሆናል።

5. **<u>ለምዝገባ ብቁ የሆኑ የንግድ ምልክቶች</u>**

   1. ማንኛውም የንግድ ምልክት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በግልፅ ለመለየት የሚያስችል ከሆነ ሊመዘገብ ይችላል፡፡
   2. የንግድ ምልክት በጥቁርና ነጭ ወይም በከለር ቀለም ሊመዘገብ ይችላል። በጥቁርና ነጭ ቀለም የተመዘገበ የንግድ ምልክት በማናቸውም የቀለሞች ቅንጅት ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን የንግድ ምልክቱ የተመዘገበው በከለር ቀለም ከሆነ ጥበቃ የሚደረግለት በተመዘገበው የከለር ቀለም ቅንጅት ብቻ ይሆናል።
   3. አንድ ሊመዘገብ የሚችል የንግድ ምልክት የምልክቱን ልዩ ባህርይ የሚቀንስ ወይም የሌላ ሰውን መብት የሚጥስ እስካልሆነ ድረስ ጥበቃ ሊደረግላቸው የማይችሉ ክፍሎችን ሊይዝ ይችላል።

6. **<u>ለምዝገባ ብቁ ስለማይሆኑ የንግድ ምልክቶች</u>**

   1. የሚከተሉት በንግድ ምልክትነት አይመዘገቡም፤

      ሀ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ድንጋጌዎችን የማያሟላ የንግድ ምልክት፣

      ለ) ድምፅ ወይም ሽታን የያዘ የንግድ ምልክት፣

      ሐ) የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች ለመለየት የማያስችል የንግድ ምልክት፣

      መ) የሕዝብን ሰላም ወይም ሥነ ምግባር የሚፃረር የንግድ ምልክት፣

      ሠ) የዕቃዎችን ወይም የአገልግሎቶችን ዓይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ ጠቀሜታ፣ ዋጋ፣ ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ የመነጩበትን ቦታ፣ የተመረቱበትን ወይም

የሚቀርቡበትን ጊዜ ወይም ሌሎች የዕቃዎቹን ወይም የአገልግሎቶቹን ባህርይ ብቻ የሚያንፀባርቁ ምልክቶችን ወይም መለያዎችን ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት፣

ሪ) ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ምልክት የሚመለከታቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በሚመለከት ወይም በኢኮኖሚያዊ ወይም የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተለመዱና በጋራ መግባቢያ ቋንቋነት የሚያገለግሉ ምልክቶችን ወይም መለያዎችን ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት፣

ሰ) ከዕቃው ተፈጥሯዊ ሁኔታ የመነጨ ወይም የአንድን ዕቃ ቴክኒካዊ ውጤት ለማግኘት አስፈላጊ የሆነን ወይም ዕቃው ላይ ከፍተኛ ዋጋ የሚጨምርን ቅርፅ ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት፣

ሸ) ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የመነጩበትን ቦታ ወይም የዕቃዎችን ዓይነትና ባህርይ በተመለከተ ሕዝቡን ወይም የንግዱን ማሕበረሰብ ሊያሳስት የሚችል የንግድ ምልክት፣

ቀ) አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር ከማንኛውም ሀገር መንግሥት፣ ከበይነ መንግሥታዊ ድርጅት ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ከተቋቋመ ሌላ ድርጅት ወታደራዊ ምልክት፣ ሰንደቅ ዓላማ ወይም ሌላ አርማ፣ ስም፣ የምህፃረ ቃል ወይም የስም አህፅሮት ወይም በእነዚሁ ከተዘጋጀ ኦፊሴላዊ ምልክት ወይም የክብር አርማ ጋር አንድ አይነት የሆነ ወይም ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት፣

በ) የአመልካቹን የቤተዘመድ ስም ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት፣

ተ) ያለግለሰቡ ፈቃድ የአንድን በህይወት ያለ ግለሰብ ሙሉ ስም የያዘ የንግድ ምልክት፣

2. የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ በቀረበበት ቀን የንግድ ምልክቱ በጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገባ የሚታወቅ መሆኑ ከተረጋገጠ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1(ሠ)፣ (ረ) እና (በ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

7. <u>በሦስተኛ ወገን መብት ምክንያት መመዝገብ የማይችሉ የንግድ ምልክቶች</u>

አንድ የንግድ ምልክት በሚከተሉት የሦስተኛ ወገኖች የቅድሚያ መብቶች ምክንያት ሊመዘገብ አይችልም።

1. ከአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ የሌላ ሰው ቀዳሚ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት የሆነ ወይም መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው፤
2. የንግድ ምልክቱ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ የሌላ ሰው ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት በሚገባ ከሚታወቅ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ግልጋሎት ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ፤
3. የንግድ ምልክቱ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ያልሆኑ የሌላ ሰው ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ከሆነ ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን የያዘ ከሆነና አጠቃቀሙ በዕቃዎቹ ወይም በአገልግሎቶቹ መካከል ግንኙነት እንዳለ በማስመሰል በተመዘገበው የንግድ ምልክት ባለቤት ጥቅም ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ከሆነ፤
4. በባለቤቱ በፅሁፍ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚደረግለትን የሌላ ሰው የሥነ-ጽሑፍ ወይም ኪነ-ጥበባዊ መብት ወይም የሌላ ሰውን የፎቶግራፍ ወይም የዲዛይን መብት የያዘ ነው ተብሎ ሲታመን፡፡

## ክፍል ሦስት

## የንግድ ምልክት የምዝገባ ሥርዓት

### 8. የምዝገባ ማመልከቻ

1. የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ የማመልከቻ ቅፅ ተሞልቶ በደንብ ከተወሰነው ክፍያ ጋር ለጽሕፈት ቤቱ ይቀርባል፤
2. አንድ የምዝገባ ማመልከቻ የሚይዘው አንድ የንግድ ምልክት ብቻ ይሆናል፤
3. አመልካቹ በደንቡ የተወሰነውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት የሚከተሉትን ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

   ሀ) የንግድ ምልክቱን ናሙና ሦስት ቅጅዎች፤

   ለ) የዓለም አቀፍ ምደባን መሠረት በማድረግ የንግድ ምልክቱ የሚያገለግልባቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር እና የምደባ ክፍል ቁጥራቸውን፤

ሐ) የምዝገባ ማመልከቻው በወኪል አማካይነት ሲቀርብ ይህንኑ የሚገልጽ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ፤

መ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተውን ክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ወይም ቅጅውን፤

ሠ) በደንቡ የተወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

4. የውጭ አገር ሰው የሆነ አመልካች ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ ወኪል መሰየም ይኖርበታል።

9. <u>ማመልከቻን ስለመተው</u>

በምዝገባ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ወቅት አመልካቹ ጥያቄውን መተው ይችላል።

10. <u>የቀዳሚነት መብት</u>

1. ማንኛውም አመልካች በውጪ አገር የንግድ ምልክቱ እንዲመዘገብ ካመለከተበት ቀን አንስቶ ባሉት 6 ወራት ውስጥ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክቱ ለተመሳሳይ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች እንዲውል ማመልከቻ ሲያቀርብና የቀዳሚነት መብት ሲጠይቅ በተመዘገበበት ጽሕፈት ቤት ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የቀዳሚውን ማመልከቻ ቅጅ እና ሌሎች የሚጠየቁ ሰነዶችንና መረጃ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ካቀረበ ማመልከቻው በውጪ ሀገር የተመዘገበበት ቀን የምዝገባ ቀን ተብሎ ይወሰዳል፤

2. ለጽህፈት ቤቱ የቀረበው መግለጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና በደንቡ የተወሰነውን መስፈርት የማያሟላ ከሆነ የተባለው መግለጫ እንዳልቀረበ ይቆጠራል።

11. <u>ስለማመልከቻ ምርመራ</u>

ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልቻ ሲቀርብለት፣

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 እና በደንቡ መሠረት የፎርማሊቲ ምርመራ ያደርጋል፤

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 እና 7 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የሥረ-ነገር ምርመራ ያደርጋል፤

3. ማመልከቻው በዚህ አዋጅ እና በደንቡ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የማያሟላ በመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ማመልከቻውን ውድቅ

በማድረግ በደንቡ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለፅ በጽሑፍ ያሳውቃል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን አለመቀበሉን ከመወሰኑ በፊት አመልካቹ አስተያየቱን በጽሑፍ የሚሰጥበት ወይም ስህተቱን የሚያርምበት በቂ ጊዜ ይሰጣል።

12.<u>የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ስለማውጣት</u>

የንግድ ምልክት ማመልከቻው ተቀባይነት ሲያገኝ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱን ምዝገባ በተመለከተ በአአምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በሬድዮና በቴሌቭዥን ተቃውሞ ካለ እንዲቀርብ በአመልካቹ ወጭ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ያወጣል።

13.<u>ስለተቃውሞ</u>

1. ማንኛውም የንግድ ምልክት ምዝገባን የሚቃወም ሰው የሚቃወምበትን ምክንያት በዝርዝር በመጥቀስ በደንቡ በተወሰነው የጊዜ ገደብና የተቃውሞ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት ማስረጃዎቹን በማያያዝና በደንቡ የተወሰነውን ክፍያ በመፈፀም ለጽህፈት ቤቱ በፅሁፍ ተቃውሞውን ማቅረብ ይችላል፤
2. ጽህፈት ቤቱ የተቃውሞውን ማመልከቻና ማስረጃዎች ለንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ በደንቡ በተወሰነው ጊዜና ሥርዓት መሠረት እንዲደርሰው ያደርጋል፤
3. የንግድ ምልክቱ እንዲመዘገብለት ጥያቄ ያቀረበው አመልካችም በማመልከቻው መሠረት ያደረጋቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር በመግለጽና በደንቡ በተወሰነው ጊዜና ሥርዓት መሠረት ለተቃውሞው የመከላከያ መልስ ለጽሕፈት ቤቱ ማቅረብ ይችላል። መከላከያ መልስ ካላቀረበ ማመልከቻውን እንደተወው ይቆጠራል፤
4. ጽሕፈት ቤቱ አመልካቹ የሰጠውን መልስ ለተቃውሞ አቅራቢው በደንቡ በተወሰነው ጊዜና ሥርዓት መሠረት እንዲደርሰው በማድረግ የጉዳዩን ፍሬ ነገር ከመረመረ በኋላ ስለንግድ ምልክቱ ምዝገባ ውሳኔ ይሰጣል፤
5. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት የሰጠውን ውሳኔ ቅጅ በደንቡ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለአመልካቹና ለተቃውሞ አቅራቢው መስጠት አለበት፤

## 14.በእንጥልጥል ላይ ስላሉ ማመልከቻዎች

1. ማመልከቻው ከታተመበት ቀን ጀምሮ እስከ ምዝገባው እለት ባለው ጊዜ ውስጥ አመልካቹ የንግድ ምልክቱ ተመዝግቦለት ቢሆን ኖሮ ሊኖረው የሚችለው መብትና ጥቅም ይኖረዋል። ሆኖም የምዝገባ ማመልከቻው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በኋላ በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት በተመሰረተ ክስ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ የንግድ ምልክቱ ብቁ ሆኖ ሊመዘገብ አይችልም ነበር በማለት ተከሳሹ ካስረዳ እንደበቂ መከላከያ ይቆጠራል።
2. የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ከመፈፀሙ ቀን በፊት የመብት መጣሱን ጉዳይ የሚመለከተው የክስ ሂደት ሊጀመር አይችልም።

## 15.ስለምዝገባና የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ጽሕፈት ቤቱ የቀረበለት የምዝገባ ማመልከቻ፣

1. በዚህ አዋጅና በደንቡ የተጠቀሱት ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ፤ እና
2. በምዝገባ ማመልከቻው ላይ ተቃውሞ ያልቀረበ ወይም ተቃውሞ ቀርቦ ተቃውሞው ውድቅ የተደረገ ከሆነ፤

የንግድ ምልክቱን መዝግቦ በደንቡ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጣል።

## 16.ምዝገባን ስለማሳወቅ

ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ መፈፀሙን የሚገልፅ ማስታወቂያ በአእምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሬድዮ ወይም በቴሌቭዥን ወይም በዌብሳይት በአመልካቹ ወጭ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## 17.ይግባኝ የማቅረብ መብት

1. ጽሕፈት ቤቱ ስለንግድ ምልክት ምዝገባ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቅሬታ ጽሕፈት ቤቱ ውሳኔውን ለባለጉዳዩ ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤቱ መቅረብ አለበት።

## ክፍል አራት

## የወል የንግድ ምልክቶች እና ታዋቂ የሆኑ የንግድ ምልክቶች

### 18.የወል የንግድ ምልክቶች ምዝገባ

1. ለወል የንግድ ምልክት ምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ የንግድ ምልክቱ የወል የንግድ ምልክት መሆኑን መግለፅና የወል የንግድ ምልክቱን አጠቃቀም ከሚወሰን መተዳደሪያ ደንብ ቅጅ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤
2. በዚህ አዋጅ ስለንግድ ምልክት ምዝገባ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ለወል የንግድ ምልክት ምዝገባም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የመተዳደሪያ ደንብ፣ የማህበሩን ስም፣ ዋና መሥሪያ ቤት፣ አላማዎቸንና ወኪሎችን መጥቀስ ይኖርበታል። በተጨማሪ በንግድ ምልክቱ የመጠቀም መብት ያላቸውን ሰዎች፣ የአጠቃቀሙን ሁኔታና የመብት መጣስ ሁኔታ ሲያጋጥም የሚመለከታቸው ሰዎች የሚኖራቸውን መብትና ግዴታ መግለፅ ይኖርበታል፤
4. የተመዘገበው የወል የንግድ ምልክት ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ባቀረበው መተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ለውጥ ለጽሕፈት ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል።

### 19.የወል የንግድ ምልክትን ለማስመዝገብ ስለሚችሉ ሰዎች

የሠራተኛ ማህበራት፣ ወይም ፌዴሬሽኖች የአባላቶቻቸውን መብት ለማስጠበቅ የወል የንግድ ምልክቶችን ሊያስመዘግቡ ይችላሉ፡፡

### 20.የወል የንግድ ምልክቶች ምዝገባን ስለመሰረዝ

1. የወል የንግድ ምልክት ምዝገባ በሚከተሉት ምክንያቶች ይሰረዛል፣
   ሀ) በባለቤትነት የተመዘገበው በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲፈርስ፤
   ለ) ተመዝጋቢው ባለቤት የዚህን አዋጅ መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፤
   ሐ) ተመዝጋቢው ባለቤት ራሱ ወይም እያወቀ ሌሎች ሰዎች መተዳደሪያ ደንቡ ከሚፈቅደው ውጭ በንግድ ምልክቱ ሲጠቀሙ፤
   መ) መተዳደሪያ ደንቡ ለሕዝብ ሰላም ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ሲይዝ፤

2. የወል የንግድ ምልክት ከተሰረዘ ሰባት አመት ከማለፉ በፊት በአዲስ ምዝገባ አማካኝነት ለተመሳሳይ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች በባለቤትነት ሊያዝ ወይም በሌላ መልክ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

21. <u>**መተዳደሪያ ደንብን ለሕዝብ እይታ ክፍት ስለማድረግ**</u>

የወል የንግድ ምልክት አጠቃቀምን የሚገዛው መተዳደሪያ ደንብ ለሕዝብ እይታ ክፍት ይሆናል።

22. <u>**መተዳደሪያ ደንብን ስለማሻሻል**</u>

1. የተመዘገበን የወል የንግድ ምልክት አጠቃቀም በሚገዛ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ተፈፃሚ የሚሆነው ማሻሻያው ለጽሕፈት ቤቱ ቀርቦ ሲመዘገብ ነው፤
2. ጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተሻሻለውን የመተዳደሪያ ደንብ ከመመዝገቡ በፊት ተቃውሞንና አስተያየትን ለመጋበዝ ታትሞ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል።

23. <u>**ታዋቂ የንግድ ምልክቶች**</u>

1. ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት ዓለም አቀፍ ስምምነት እንደ ታዋቂ የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚደረግለት የንግድ ምልክት በዚህ አዋጅ መሠረት ጥበቃ የሚደረግለት በኢትዮጵያ ውስጥ የታወቀ ሲሆንና የምልክቱ ባለቤት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ስራ ወይም መልካም ዝና ቢኖረውም ባይኖረውም፣
   ሀ) የስምምነቱ አባል የሆነ አገር ዜጋ ሲሆን፣ ወይም
   ለ) የስምምነቱ አባል በሆነ አገር ውስጥ ቋሚ መኖሪያ ወይም የንግድ ተቋም ሲኖረው ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አንድ የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ መሆኑንና አለመሆኑን የሚወስነው አግባብነት ያለው የህብረተሰብ ክፍል ስለንግድ ምልክቱ ያለውን ዕውቀት እንዲሁም የንግድ ምልክቱን የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት ምክንያት የተገኘን ዕውቀት ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ፀንቶ ስለሚቆይበት ዘመንና ስለዕድሳት

### 24.የንግድ ምልክት ምዝገባ ፀንቶ የማቆይበት ዘመን

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 35 እስከ 37 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ምልክት ምዝገባ ፀንቶ የሚቆየው የምዝገባው ማመልከቻ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለሰባት ዓመታት ይሆናል።

### 25.የንግድ ምልክት ምዝገባ ዕድሳት

1. የንግድ ምልክት ምዝገባ በምልክቱ ባለቤት ጥያቄ በየሰባት ዓመቱ ለሌላ ተከታይ ሰባት ዓመት ሊታደስ ይችላል። የንግድ ምልክቱ ባለቤት ከማመልከቻው ጋር በደንቡ የተወሰነውን የዕድሳት ክፍያ ስለመፈፀሙ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤
2. በዕድሳት ወቅት በምልክቱ ስር ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የተወሰኑትን ለመቀነስ የሚቻል ከመሆኑ በስተቀር በንግድ ምልክቱ ላይ ለውጥ ማድረግም ሆነ የተጨማሪ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር ማካተት አይቻልም፤
3. የንግድ ምልክት ምዝገባን ማሳደስ የሚቻለው ምዝገባው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ነው። ሆኖም የሦስት ወራት ጊዜው ካለፈ በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ከመደበኛው የዕድሳት ክፍያ በተጨማሪ በደንቡ የተወሰነውን ቅጣት በመክፈል ምዝገባውን ማሳደስ ይቻላል፤
4. ጽህፈት ቤቱ እድሳቱን በመዝገብ በማስፈር ይህንን የሚመለከት ማስታወቂያ በአእምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሬድዮ ወይም በቴሌቭዥን ወይም በዌብሳይት በንግድ ምልክቱ ባለቤት ወጪ እንዲወጣ ያደርጋል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተገለጸው የጊዜ ገደብ ያልታደሰ የንግድ ምልክት እንደተተወ ወይም እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤
6. የንግድ ምልክት ምዝገባ በዚህ አንቀፅ መሠረት ሳይታደስ ሲቀር ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱን ከመዝገብ ይሰርዛል፤

7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (5) እና (6) ድንጋጌዎች ማንኛውንም ሰው የቀድሞ ባለቤቱንም ጨምሮ የተተወን ወይም የተሰረዘን የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ ከመጠየቅ አያግዱትም።

## ክፍል ስድስት

## መመዝገብ ስለሚያስገኘው መብትና የፈቃድ ውሎች

### 26.ምዝገባ ስለሚያስገኘው መብት

1. የንግድ ምልክት ባለቤት የንግድ ምልክቱን ከተመዘገበበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር አያይዞ የመጠቀም ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የመፍቀድ መብት ይኖረዋል፤
2. የንግድ ምልክት ምዝገባ የንግድ ምልክቱ ባለቤት ሌሎች ሰዎች፤
   ሀ) የንግድ ምልክቱን ወይም ሕዝብን ሊያሳስት የሚችል ማንኛውንም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ የንግድ ምልክቱ ከተመዘገበባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ወይም ሕዝብን ሊያሳስት በሚችል አኳኋን ከሌሎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ እንዳይጠቀሙ፤
   ለ) የንግድ ምልክቱን ወይም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ ያለበቂ ምክንያቶች ጥቅሙን ሲጎዳ በሚችል አኳኋን እንዳይጠቀሙ፤ እና
   ሐ) ሌሎች መሰል ድርጊቶች እንዳይፈጽሙ፤
   
   ለማገድ የሚያስችል መብት ያስገኝለታል።
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌዎች ዓላማ አንድ አይነት መለያ ለአንድ ዓይነት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ሲውል የመሳከር ሁኔታ እንዳለ ይገመታል፤
4. ታዋቂ የንግድ ምልክትን በሕገ ወጥ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋልን አስመልክቶ በታዋቂ የንግድ ምልክቱ ባለቤት የሚቀርብ ማናቸውንም ክስ በተመለከተ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) ድንጋጌዎች እንዳግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

### 27.በምዝገባ የተገኘ መብት ገደቦች

1. የንግድ ምልክት ምዝገባ ምልክቱን ይዞ በህጋዊ መንገድ በማናቸውም አገር ውስጥ የተሸጠ ዕቃን በሚመለከት ምንም ዓይነት ለውጥ እስካልተደረገበት ድረስ ሦስተኛ ወገኖች ዕቃውን በሚሸጡበት ጊዜ በንግድ ምልክቱ እንዳይጠቀሙ የመከልከል መብት ለባለቤቱ አያሰጠውም፤

2. የንግድ ምልክቱ መመዝገብ ለተመዘገበው የምልክቱ ባለቤት ሦስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና ስማቸውን፣ አድራሻቸውን፣ የማስመሰያ ስሞችን፣ የአካባቢ ስምን ወይም የራሳቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዓይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ መድረሻ ቦታ፣ ዋጋ፣ መነሻ ቦታ፣ የምርት ወይም አቅርቦት ጊዜ ለማመልከት ቢጠቀሙ አጠቃቀሙ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ለማሳወቅና ለመረጃ ዓላማ ብቻ የተወሰነና ሕዝቡን ስለዕቃዎቹ ወይም ስለአገልግሎቶቹ ምንጭ የማያሳስት እስከሆነ ድረስ ምልክቱን ከመጠቀም ለማገድ የሚያስችል መብት አያስገኝለትም፡፡

28. **መብት ስለማስተላለፍ**

1. በተመዘገበ የንግድ ምልክት ወይም በንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ላይ ያለን መብት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማስተላለፊ ወይም በፈቃድ መስጠት ይቻላል፤
2. በተመዘገበ የንግድ ምልክት ወይም ለምዝገባ በቀረበ ማመልከቻ ላይ ያለ መብትን ለማስተላለፍ የሚቀርብ ጥያቄ ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ መቅረብ አለበት። ማመልከቻው መብትን ለማስተላለፍ ከተደረገው ስምምነት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤
3. በጋራ ባለቤትነት በተያዘ የንግድ ምልክት ላይ ያለ ድርሻ ያለ ባለመብቶቹ የጋራ ፈቃድ አይተላለፍም፤
4. በንግድ ምልክት ላይ ያለ መብት ጥቅም ላይ ከሚውልበት የንግድ ሥራ ጋር አብሮ ወይም ተነጠሎ ሊተላለፍ ይችላል። ሆኖም የንግድ ሥራው በተላለፈ ጊዜ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የንግድ ምልክቱ መብት አብሮ ይተላለፋል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ ከሚውልበት የንግድ ሥራ ተነጥሎ መተላለፉ ሕዝቡን ሊያሳስት ይችላል ብሎ ሲገምት የንግድ ምልክቱን የማስተላለፍ ጥያቄን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፤
6. ጽሕፈት ቤቱ መብትን የማስተላለፍ ጥያቄን ተቀባይነት ከመረመረና በደንቡ የተወሰነው ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ የመብቱን መተላለፍ ይመዘግባል፤ የመብት መተላለፉ በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## 29.ፍቃድ ውሎች

1. የተመዘገበ ወይም ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ምልክት ባለቤት ማንኛውም ሌላ ሰው በፈቃድ ውል መሠረት በምልክቱ እንዲጠቀም ሊፈቅድ ይችላል፤
2. በተመዘገበ የንግድ ምልክት ወይም ለምዝገባ በቀረበ ማመልከቻ ላይ የሚደረግ ማናቸውም የፈቃድ ውል እንዲሁም በፈቃድ ውል ድንጋጌዎች ላይ የሚደረግ ማሻሻያና የውል መቋረጥ ማስታወቂያ ለጽሕፈት ቤቱ መቅረብ አለበት፡፡ ጽህፈት ቤቱም ውሉ በመዝገብ እንዲገባ በማድረግና ዝርዝር ጉዳዮችን በምስጢር በመያዝ ይህንኑ የሚመለከት ማስታወቂያ በአእምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ የፈቃድ ውል በመዝገብ ከመግባቱ በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት አይኖረውም፡፡
3. የተመዘገበ የወል የንግድ ምልክት ወይም ማመልከቻ በፈቃድ ውል አማካይነት አይተላለፍም፡፡

## 30.ፈራሽ የሆኑ የፈቃድ ውሎች

በተመዘገበ የንግድ ምልክት ወይም ለምዝገባ በቀረበ ማመልከቻ ላይ የሚደረግ ማናቸውም የፈቃድ ውል የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጥራት በሚመለከት የንግድ ምልክቱ ባለቤት ተገቢ የሆነ ቁጥጥር ያለው ስለመሆኑ የሚያመለክት ድንጋጌ ከሌለው ፈራሽ ይሆናል፡፡

## 31.ዋጋ የማይኖራቸው የፈቃድ ውል ድንጋጌዎች

1. በምዝገባ ከተገኘው መብት ያልመነጩ ወይም መብቱን ለመጠበቅ አስፈላጊ ያልሆኑ ግዴታዎችን በፈቃድ ተቀባዩ ላይ የሚጥሉ የፈቃድ ውሉ ድንጋጌዎች ፈራሽ ይሆናሉ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ቀጥሎ የተዘረዘሩት እንደ ገደብ አይቆጠሩም፤
   ሀ) የንግድ ምልክቱን ወሰን፣ የቦታ ክልል፣ የመገልገያ ዘመን ወይም ምልክቱ ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ጥራት የሚመለከቱ ገደቦች፤
   ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት በንግድ ምልክቱ ባለቤት የሚደረግ ተገቢ ቁጥጥር፤
   ሐ) የንግድ ምልክቱን ምዝገባ ዋጋ ሊያሳጣ ከሚችል ድርጊት እንዲቆጠብ በፈቃድ ተቀባዩ ላይ የሚጣል ግዴታ፡፡

**32.ተጨማሪ ፈቃድ የመስጠት መብት**

1. በፈቃድ ውሉ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፣ ፈቃድ መስጠቱ የተመዘገበው የንግድ ምልክት ባለቤት ለሦስተኛ ወገኖች ተጨማሪ ፈቃድ ከመስጠት ወይም ራሱ በንግድ ምልክቱ ከመጠቀም አያግደውም፤
2. ለፍቃድ ተቀባዩ የብቸኛ ተጠቃሚነት ፈቃድ በተሰጠ ጊዜ፣ የንግድ ምልክቱ ባለቤት ከሌለ ሦስተኛ ወገን ጋር ሌላ የፈቃድ ውል ማድረግ ወይም ተቃራኒ ድንጋጌ በውሉ ከሌለ በስተቀር በምልክቱ መጠቀም አይችልም።

**33.የፈቃድ ተቀባዩ መብት**

በፈቃድ ውል ላይ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፣ ፈቃድ ተቀባዩ የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ፀንቶ በሚቆይበት እና በሚታደስበት ጊዜ የንግድ ምልክቱ ከተመዘገበባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የንግድ ምልክቱን የመጠቀም መብት ይኖረዋል።

## ክፍል ሰባት
## በተመዘገበ ንግድ ምልክት ላይ ያለን መብት
## ስለመተው፣ ስለ መብት መሰረዝ እና ፈራሽ መሆን

**34.መብትን ስለመተው**

1. አንድ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ባለቤት የንግድ ምልክቱ ምዝገባ በሙሉ ወይም የንግድ ምልክቱ የተመዘገበባቸውን የተወሰኑ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በሚመለከት የባለቤትነት መብቱን ለመተው ከፈለገ የንግድ ምልክት ምዝገባው እንዲሰረዝ ለጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፤
2. የተመዘገበ የንግድ ምልክት በፈቃድ ውል የተሰጠ ሲሆን መብትን የመተው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው ፈቃድ ተቀባዩ በጉዳዩ የተስማማ ስለመሆኑ መግለጫ ሲቀርብ ብቻ ነው፤
3. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበውን ማመልከቻ እንደተቀበለ ስለመብቱ መተው በአአምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ያሳውቃል። የመብት መተው የሚፀናው ምዝገባውን የመሰረዙ ውሳኔ በመዝገብ ከሰፈረ በኋላ ይሆናል።

35.**<u>ጥቅም ላይ ያልዋሉ የንግድ ምልክቶችን ስለመሰረዝ</u>**

1. ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም ሰው የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ አልዋለም ማለት ምዝገባው እንዲሰረዝ ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ ሊያመለክት ይችላል፤
2. አንድ የንግድ ምልክት ጥቅም ላይ አልዋለም የሚባለው የሰረዛ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን በፊት ቢያንስ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት የተመዘገበው የምልክቱ ባለቤት ወይም ፈቃድ ተቀባዩ የንግድ ምልክቱን ለተመዘገበባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ያለበቂ ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ላይ ያላዋለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፤
3. ጽሕፈት ቤቱ ምዝገባውን የሚሰርዘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሱት ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ነው። የንግድ ምልክቱ ባለቤት ምልክቱ አገልግሎት ላይ ያልዋለው ከተመዘገቡት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካከል በተወሰኑት ላይ ብቻ መሆኑን ሲያረጋግጥ ጽህፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱን በከፊል ይሰርዛል፤
4. ባለቤቱ ወይም ፈቃድ ተቀባዩ የንግድ ምልክቱን ያልተጠቀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ምዝገባው አይሰረዝም፡፡
5. አንድን የንግድ ምልክት የተመዘገበበትን የመለየት ባህርይ በማይቀይር ሁኔታ በተለየ መልኩ መጠቀም የንግድ ምልክቱን ለመሰረዝ ምክንያት አይሆንም።

36.**<u>የንግድ ምልክት ምዝገባን ፈራሽ ስለማድረግ</u>**

1. ማንኛውም የሚመለከተው ሰው በጽሑፍ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በጽሕፈት ቤቱ ተነሳሽነት የንግድ ምልክት ምዘገባ በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ከመሠረቱ ያላሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ ፈራሽ ሊደረግ ይችላል፤
2. ጽህፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባን ፈራሽ ከማድረጉ በፊት ፈራሽ እንዲሆን የሚያደርጉትን ምክንያቶች ለባለቤቱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤
3. ምዝገባው ፈራሽ የተደረገው የንግድ ምልክቱ ከተመዘገበባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካከል ከፊሎቹን በሚመለከት የሆነ እንደሆነ የምዝገባው ፈራሽነት ተፈፃሚ የሚሆነው እነዚህኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚመለከት ብቻ ይሆናል።

37.<u>የምዝገባ ፈራሽ መሆን ውጤት</u>

1. የንግድ ምልክት ምዝገባ ፈራሽ መሆኑን የሚገልፀው ውሳኔ ተፈፃሚነት የሚኖረው ከምዝገባው ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡ ጽሕፈት ቤቱ ምዝገባው ፈራሽ ስለመሆኑ በአእምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በማውጣት ያሳውቃል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የንግድ ምልክቱ በፈቃድ ውል የተሰጠ ሲሆንና ፈቃድ ሰጪው ከፈቃድ ውሉ ጥቅም ያገኘበት ከሆነ የምዝገባው ፈራሽ መሆን ባለፈቃዱ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ለመጠየቅ አያስችለውም፤

38.<u>የጊዜ መራዘም</u>

ጽሕፈት ቤቱ በጽሑፍ ሲጠየቅና በሁኔታው ሲያምን በዚህ አዋጅና በደንቡ መሠረት ለሚፈጸሙ ድርጊቶች የተመለከተው የጊዜ ገደብ የሚመለከታቸውን ወገኖች በማሳወቅና ተገቢውን መመሪያ በመስጠት በመስጠት እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል። የጊዜ ማራዘሚያው ውሳኔ ድርጊቱ የሚፈፀምበት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላም ሊሰጥ ይችላል።

<u>**ክፍል ስምንት**</u>

<u>**ስለመብቶች ተፈፃሚነት**</u>

39.<u>በጊዜያዊነት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. ስልጣኑ የተሰጠው ፍርድ ቤት
   ሀ) የመብት ገሰሳን ለመከላከል በተለይም ገቢ ወይም ወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ ስርዓት አጠናቀው ወደ ንግዱ እንዳይገቡ ለማድረግ፤ ወይም
   ለ) ተፈፀመ የተባለውን የመብት ገሰሳ የሚያስረዳ አግባብነት ያለው ማስረጃ ለመጠበቅ፤

   ፈጣንና ውጤታማ የግዜያዊ እርምጃ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው በተለይም የእርምጃው መዘግየት በከሳሹ ላይ ሊካስ የማይችል ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ከሆነ ወይም ማስረጃ እንደሚጠፋ በግልፅ የሚታይ አደጋ ካለ ተከሳሹ ሳይጠራ ጊዜያዊ እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ይኖረዋል፤

3. ተከሳሹ መብት ከመጣስ እንዲታቀብ በቀረበ ክስ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ከሳሹ የመብት ገሰሳን ለማስቆም ጊዜያዊ የእግዱ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል፤
4. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዐስ አንቀፅ (3) መሰረት በቀረበለት የእግዱ ትዕዛዝ ጥያቄ ላይ ሲወስን፣
   ሀ) አደጋ ላይ የወደቀው ጥቅም ካሳ ሊሸፈን የማይችል መሆኑን፣ አደጋው የማይቀር መሆኑን፣ የክሱን ጥንካሬና ውሳኔ መስጠት በእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ላይ የሚያስከተለውን ጉዳት መመርመር አለበት፤
   ለ) እግዱ የሚቀይበትን ጊዜ እና እንደአስፈላጊነት ከሳሹ የሚያስይዘውን ገንዘብ ወይም የሚያቀርበውን ሌላ ዋስትና ሊያመለከት ይችላል፣
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ተራ ፊደል (ሀ) በተመለከተው መመዘኛ ተከራካሪዎች ሲመዘኑ በእኩል ደረጃ በሆኑ ጊዜ ጊዜያዊ እግድ ከመስጠቱ በፊት በአንፃራዊ ጥንካሬያቸው ላይ ጥልቅ ምርመራ ማድረግ ይችላል፣
5. በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኘን መብት የሚጥስ ተግባር በተፈፀመ ጊዜ ፍተሻና ዕቃ መያዝን የሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓትና የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፣
6. ተከሳሹ ሳይጠራ ጊዜያዊ እርምጃዎች በተወሰዱ ጊዜ እርምጃዎቹ ተፈፃሚ እንደሆኑ ወዲያውኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡ እርምጃው ከተገለፀ በኋላ ተከሳሹ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ የተወሰደውን እርምጃ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም ለመለወጥ የሚያስችል ውሳኔ ለመስጠት የተከሳሹን የመደመጥ መብት ጨምሮ በቂ ጊዜ በመስጠት ጉዳዩ እንደገና መታየት አለበት፣
7. ጊዜያዊ እርምጃው አመልካቹ በፈፀመው ወይም ሳይፈፅመው በቀረ ድርጊት ምክንያት ወይም ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ የተጣሰ ወይም የመጣስ አደጋ ያጋጠመው መብት የሌለ መሆኑ በመታወቁ የተሻረ ከሆነ በተከሳሹ ጠያቂነት ለደረሰበት ጉዳት በቂ ካሳ በከሳሹ እንዲከፈለው ያዛል።

40.<u>የፍትሐብሔር መፍትሄዎች</u>

1. የንግድ ምልክት መብት መጣስን በሚመለከት ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት፣
   ሀ) ተከሳሹ የመብት መጣሱን ድርጊት እንዲያቆም፣ እና

ለ) በመብቱ መጣስ ምክንያት በከሳሹ ላይ ደረሰውን ጉዳት እንዲክስ፣ ሊወስን ይችላል።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1)(ለ) መሠረት ሊወሰን የሚችለው ካሳ መጠን ተከሳሹ በንግድ ምልክቱ በመጠቀም ካገኘው የተጣራ ትርፍና በንግድ ምልክቱ እንዲጠቀም ተፈቅዶለት ቢሆን ኖሮ ሊጠየቅ ይችል ከነበረው የሮያሊቲ ክፍያ መካከል የሚበልጠውን የሚያህል እና ከሳሹ ከክሱ ጋር ተያይዞ ያወጣውን ወጭ የሚሸፍን መሆን አለበት፣

3. ተከሳሹ የንግድ ምልክቱን በመጠቀም ከሸጣቸው እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ያገኘው ትርፍ በከፊል በሌሎች የገበያ ሁኔታዎች ምክንያት የተገኘ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በስተቀር ትርፉ በሙሉ በንግድ ምልክቱ ከመጠቀም የተገኘ እንደሆነ ይቆጠራል።

41.<u>የወንጀል ቅጣት</u>

1. የወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኘ መብትን ሆነ ብሎ የጣሰ ማንኛውም ሰው ከ5 ዓመት በማያንስ እና ከ10 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፣

2. የወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ጥበቃ ያገኘ መብትን በኃላ ቸልተኝነት የጣሰ ማንኛውም ሰው ከ1 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፣

3. አግባብነት ባለው ጊዜ ቅጣቱ ወንጀሉን ለመፈፀም ያገለገሉ ቁሳቁሶች ወይም መሳሪያዎች እና መብት የተጣሰባቸው ዕቃዎችን መያዝ፣ መውረስ እና ማስወገድን ይጨምራል።

42.<u>በጉምሩክ ወደቦች እና ጣቢያዎች ላይ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. የጉምሩክ ባለሥልጣን የመብቱ ባለቤት የንግድ ምልክት ምዝገባ የምስክር ወረቀትና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች አያይዞ በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት በቂ ዋስትና እንዲቀርብለት በማድረግ አመልካቹ መብቴ የተጣሰባቸው ናቸው ብሎ ያመለከታቸውን ዕቃዎች ይዞ በቁጥጥሩ ሥር ሊያቆይ ይችላል፣

2. የጉምሩክ ባለስልጣን ዕቃውን ለመያዝ የወሰደውን እርምጃ በተመለከተ ለአመልካቹ እና ለዕቃው ባለቤት ወዲያውኑ ያሳውቃል፣

3. አመልካቹ ዕቃው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በአሥር የስራ ቀናት ውስጥ የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ካላቀረበ የጉምሩክ ባለሥልጣን የያዘውን ዋስትና ገቢ በማድረግ ዕቃውን ይለቃል።

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 43.የንግድ ምልክት መጽሔት

በዚህ አዋጅ ለሕዝብ መገለጽ ያለባቸውን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤቱ በአእምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ማውጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ምልክቶችን ለማስተዋወቅ የሚረዳ የንግድ ምልክት መጽሔት ማውጣት ይችላል፡፡

### 44.የንግድ ምልክት ወኪሎች ምዝገባ

1. የንግድ ምልክት ወኪሎች በጽ/ቤቱ መመዝገብ አለባቸው፣
2. የንግድ ምልክት ወኪሎቹ የአመዘጋገብ ሁኔታ በደንቡ ይወሰናል፣

### 45.መረጃ ስለመጠየቅና ስለማግኘት

1. ማንኛውም ሰው በደንቡ የተመለከተውን ክፍያ በመፈፀም የንግድ ምልክት ፍለጋና ማጣሪያ ተደርጎ የንግድ ምልክት ሪፖርት እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፣
2. ጽህፈት ቤቱ በደንቡ የተመለከተውን ክፍያ የፈፀመ ማንኛውም ሰው መዛግብቱን እንዲመረምር መፍቀድና የመረጃዎች ቅጅ እንዲሰጠው ማድረግ አለበት፡፡

### 46.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቀመጡ የንግድ ምልክቶች ይህ አዋጅ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣
2. ጽህፈት ቤቱ የንግድ ምልክቶቹን በመመርመር በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲመዘገቡ ይወሰናል፣
3. ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በክርክር ላይ ያሉ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ አንቀፅ 49 ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ይታያሉ።

### 47.ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

48.<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎችና አሠራሮች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

49.<u>ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት</u>

በዚህ አዋጅና በደንቡ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችና ተዛማጅ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይሆናሉ።

50.<u>አዋጁ የማፀናበት ግዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 273/2005

## ስለንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 47 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 273/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "ጽሕፈት ቤት" ማለት የኢትየጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ነው፤
   4. "ወኪል" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በጽሕፈት ቤቱ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ወኪል ነው፤
   5. "የምዝገባ ባለቤት" ማለት የንግድ ምልክት በጽሕፈት ቤቱ ዘንድ ያስመዘገበ ሰው ነው፤
   6. "የንግድ ምልክትን በጥቅም ላይ ማዋል" ማለት የንግድ ምልክቱን በዕቃዎቹ ወይም በዕቃዎቹ በማሸጊያ ወይም መለያ ምልክት ላይ መለጠፍ፣ የንግድ ምልክቱ ከዕቃዎቹ ጋር በቅርበት ሆኖ እንዲታይ ማድረግ፣ የንግድ ምልክቱን በዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ማስታወቂያ ወይም የማስተዋወቂያ ማቴሪያሎች ላይ መጠቀም ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በንግድ ምልክቱና በዕቃዎቹ ወይም በአገልግሎቶቹ መካከል ግንኙነት መፍጠር ነው፤
   7. "ማሳተም" ማለት በአዕምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ ሀገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ማሳተም ወይም በጽሕፈት ቤቱ ድረገጽ ላይ መጫን ነው፤

8. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ከጽሕፈት ቤቱ ጋር ስለሚደረጉ ግንኙነቶች

### 3. በጽሑፍ ስለመገናኘት

1. ከጽሕፈት ቤቱ ጋር የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡
2. በጽሕፈት ቤቱ የሚወሰድ ማንኛውም እርምጃ በጽሑፍ በተያዙ የጽሕፈት ቤቱ መዝገቦች ላይ ብቻ መመሥረት ይኖርበታል። በቃል የተደረጉ መግባባቶች፣ መተማመኛዎችና ግንኙነቶች በጽሕፈት ቤቱ ላይ አስገዳጅነት አይኖራቸውም፡፡

### 4. ሰነዶች የሚቀርቡበት ቋንቋ

1. ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ የንግድ ምልክት ምዝገባ ወይም ማንኛውንም በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ የተመለከተ ማመልከቻ አካል የሆነ ማንኛውም ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል።
2. ማንኛውም በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ያልተዘጋጀ ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ተተርጉምና ከዋናው ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።
3. ጽሕፈት ቤቱ ትክክለኛ ትርጉም መስሎ ያልታየውን ማንኛውንም ትርጉም ላለመቀበልና ተስተካክሎ እንዲቀርብ ሰነዱን ለአመልካቹ ሊመልስለት ይችላል፡፡
4. ጽሕፈት ቤቱ ከአማርኛ ወይም ከላቲን በተለየ ፊደል የተጻፈ ቃል ያካተተ ሰነድ ሲቀርብለት የቃሉ ገላጭ ሃሳብ ወይም ትርጉም እንዲቀርብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ገላጭ ሃሳቡ ወይም ትርጉሙ ቃሉ ከምን ቋንቋ እንደተገኘ መግለጽና በአመልካቹ ወይም በአመልካቹ ወኪል መፈረም አለበት፡፡

### 5. ግንኙነት የሚደረግበት አድራሻና ጉዳዩን ለይቶ ስለመግለጽ

1. ከጽሕፈት ቤቱ ጋር የሚደረግ ማንኛውም የጽሑፍ ግንኙነት የጽሕፈት ቤቱን ትክክለኛ ስምና አድራሻ መግለጽ ይኖርበታል።
2. የጽሑፍ ግንኙነቱ እንደአግባቡ የንግድ ምልክቱን፣ የአመልካችን ስምና አድራሻ፣ ማመልከቻው ገቢ የሆነበትን ቀን፣ የማመልከቻውን ወይም ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ የተሰጠውን ቁጥር፣ የምዝገባ ባለቤቱን፣ የምዝገባውን ቁጥር እና የምዝገባውን ቀን የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል።

3. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገውን የማያሟላ ሰነድ ለላኪው ሊመልስለት ይችላል፡፡
4. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4(3) ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተመላሽ የተደረገ ሰነድ፡-
   ሀ) ከተመለሰበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ተስተካክሎ በድጋሚ ከቀረበ መጀመሪያ በቀረበበት ቀን ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፤ ወይም
   ለ) ከ30 ቀናት በላይ ዘግይቶ ተስተካክሎ በድጋሜ ከቀረበ በድጋሜ በቀረበበት ቀን ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።

6. <u>ሰነዶችን ስለመረከብና መለያ ቁጥር ስለመስጠት</u>
   1. ጽሕፈት ቤቱ በተረከባቸው ሰነዶች ላይ ሰነዶቹ ገቢ የሆኑበትን ቀንና ሰዓት የያዘ ማህተም ማድረግና ሰነዶቹን ስለመቀበሉ ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡
   2. ጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ጉዳይ ባወጣው መመሪያ መሠረት በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ አማካኝነት ሰነድ የተቀበለ እንደሆነ በኤሌክትሮኒክ መሣሪያው ላይ የተመዘገበው ቀንና ሰዓት ጽሕፈት ቤቱ ሰነዱን የተቀበለበት ቀንና ሰዓት ተደርጎ ይወሰዳል።
   3. ጽሕፈት ቤቱ ለተረከበው ማመልከቻ የመለያ ቁጥር መስጠትና የማመልከቻው አካል በሆነው እያንዳንዱ ሰነድ ላይ የመለያ ቁጥሩን ማስፈር አለበት፡፡
   4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ለማመልከቻ የተሰጠ መለያ ቁጥር ማመልከቻውን አስመልክቶ በቀጣይ በሚደረጉ የጽሑፍ ግንኙነቶች ሁሉ የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

7. <u>በፖስታ ቤት ሰነዶችን ስለመላክ</u>
   1. በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ የሚገባው ሰነድ ጊዜው ከማለፉ ከአምስት ቀናት አስቀድሞ በአስቸኳይና በተመዘገበ ፖስታ ለጽሕፈት ቤቱ የተላከ ከሆነ ለጽሕፈት ቤቱ የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ የደረሰው ቢሆንም እንኳ በወቅቱ እንደቀረበ ይቆጠራል።
   2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የንግድ ምልክትን ለማስመዝገብና የንግድ ምልክት ምዝገባን ለማሳደስ በሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

8. **ተመላሽ ስለማይደረጉ ሰነዶች**

1. በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም ጽሕፈት ቤቱ ባወጣው መመሪያ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ የተደረገ ሰነድ ተመላሽ አይደረግም፤ ሆኖም ጽሕፈት ቤቱ በጽሑፍ ጥያቄ ከቀረበለት ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል የሰነዱን ኮፒ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ዋናውን ሰነድ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ ያደረገ ሰው ፎቶ ኮፒውን በማስቀረት ዋናውን ሰነድ መውሰድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

9. **የማመልከቻ አቀራረብ**

የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 8 ከተመለከቱት በተጨማሪ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

1. አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጅ እና ፈራሚው ድርጅቱን ወክሎ ለመፈረም የሚያስችል ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ፤
2. ማመልከቻው በወኪል አማካይነት የቀረበ ከሆነ የውኪሉ የምዝገባ የምስክር ወረቀትና በአግባቡ የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ፤
3. የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ ከሆነ ወይም ሥዕላዊ ነገሮች ካሉት የእነዚሁ አጠር ያለ የጽሑፍ መግለጫ፤
4. ምልክቱ ከአማርኛ ወይም ከላቲን ፊደል ወይም ከአማርኛ፣ ከአረብኛ ወይም ከላቲን ቁጥር የተለየ የሌላ ቋንቋ ፊደል ወይም ቁጥር የያዘ እንደሆነ አቻ የአማርኛ ወይም የላቲን ፊደል እና አቻ የአረብኛ ቁጥር የያዘ መግለጫ፤
5. አመልካቹ የቀለም ቅንጅትን እንደ ንግድ ምልክት ወይም የንግድ ምልክቱ መለያ ባህሪ አድርጎ የሚወስደዉ ከሆነ ባለቀለሙን የንግድ ምልክት ሦስት ኮፒዎች እና በምልክቱ ውስጥ እያንዳንዱ ቀለም የሚገኝበትን ቦታ ጭምር የሚገልጽና አመልካቹ የንግድ ምልክቱ የቀለም ቅንጅት ወይም መለያ ባህሪው ነው የሚልበትን ምክንያት የያዘ መግለጫ፤

10.**<u>የወል የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ፤</u>**

የወል የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ፤ በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ስለንግድ ምልክቱ አጠቃቀም ከሚደነግግ መተዳደሪያ ደንብ ሁለት ቅጅዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

11.**<u>የንግድ ምልክት ስዕላዊ መግለጫ</u>**

1. የንግድ ምልከት ስዕላዊ መግለጫ ከአመልካቹ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ የዋለውን ወይም ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰበዉን የንግድ ምልክት በትክክል የሚወክል መሆን ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 መሠረት የቀዳሚነት መብት ለመጠየቅ የሚቀርብ ማመልከቻ የሆነ እንደሆነ የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ አመልካቹ በሚገኝበት ሀገር በተገቢው ሁኔታ ተመዝግቦ በተሰጠው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ላይ የተቀመጠውን የንግድ ምልክት በትክክል የሚወክል መሆን ይኖርበታል።

12.**<u>በማመልከቻ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ</u>**

1. አመልካች ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 25(1) መሠረት ምዝገባውን ስለመቀበሉ ማስታወቂያ ከመላኩ እና የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ከማሳተሙ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማመልከቻውን ለማሻሻል ጽሕፈት ቤቱን በጽሁፍ መጠየቅ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ የማሻሻያ ጥያቄ፦
   ሀ) ዋናው ማመልከቻ ገቢ በተደረገበት ጊዜ በነበረው በንግድ ምልክቱ ባህሪ ወይም በንግድ ምልክቱ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ፤ ወይም
   ለ) ዋናው ማመልከቻ ገቢ በሆነበት ጊዜ ከተካተቱት የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ዝርዝር ውስጥ ሌላ ተጨማሪ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማካተት ከሆነ፤

   ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) በተመለከተው መሠረት ጽሕፈት ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን የማሻሻያ ጥያቄዉ ተቀባይነት እንደሌለው ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

13.<u>የቀዳሚነትነት መብት</u>

በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን ቀደም ሲል በውጭ ሀገር የቀረበ ማመልከቻ ገቢ የተደረገበት ቀን ለጽሕፈት ቤቱ የቀረበ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ገቢ እንደተደረገበት ቀን ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው፡-

1. የቀድሞው ማመልከቻ የኢንዱስትሪያዊ ንብረት ጥበቃ የፓሪስ ኮንቬንሽን ተዋዋይ ወገን በሆነ ሀገር ወይም የፓሪስ ኮንቬንሽን ከሚሰጠው የቀዳሚነት መብት ጋር ተመሳሳይ ውጤት ያለው መብት ለአመልካች በሚሰጥ ሀገር ማመልከቻው በተገቢው ሁኔታ ገቢ የሆነ እንደሆነ፤ እና
2. አመልካቹ የንግድ ምልክት ምዝገባው ማመልከቻ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ የቀድሞውን ማመልከቻ የተረጋገጠ ኮፒ ወይም የቀድሞው ማመልከቻ ገቢ በሆነበት ሀገር የተሰጠ የቅድሚያ መብት የምስክር ወረቀት ለጽሕፈት ቤቱ ያቀረበ እንደሆነ፤

ነው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ማመልከቻን ስለመመርመር</u>

14.<u>ስለፎርማሊቲ ምርመራ</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ ሲቀርብለት በአዋጁ አንቀጽ 8 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የፎርማሊቲ ምርመራ ያካሂዳል።
2. ማመልከቻው በአዋጁ አንቀጽ 8 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 የተመለከቱትን መመዘኛዎች የማያሟላ ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ አመልካቹ ሊያሟላ የሚገባውን መመዘኛዎች አሟልቶ ማስታወቂያው ከተላከበት ቀን ጀምሮ ከ90 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ እንዲያደርግ በጽሑፍ ያስታዉቀዋል፡፡
3. አመልካቹ በጽሕፈት ቤቱ እንዲያቀርብ የተጠየቀውን እርማቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ካላደረገ፣ ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርገዋል። አመልካቹ የከፈለው የገንዘብ ክፍያ ካለም ተመላሽ አይደረግለትም፡፡
4. ማመልከቻው በአዋጁ አንቀጽ 8 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን ለምርመራ ስለመቀበሉ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።

15.<u>በመታየት ላይ ያሉ ማመልከቻዎች ዝርዝር</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 መሠረት የፎርማሊቲ ምርመራ አሟልተው በመታየት ላይ ያሉ ማመልከቻዎችን ዝርዝር አዘጋጅቶ ይይዛል፡፡
2. ዝርዝሩ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

   ሀ) የእያንዳንዱን አመልካች ስምና አድራሻ፣

   ለ) ማመልከቻ የቀረበበት የእያንዳንዱ የንግድ ምልክት መግለጫ ወይም ቅጂ፣

   ሐ) እያንዳንዱ ማመልከቻ የሚሸፍናቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችና የምደባ ቁጥራቸውን፣

   መ) እያንዳንዱ ማመልከቻ ገቢ የሆነበትን ቀንና ሰዓት፣ እና

   ሠ) ጽሕፈት ቤቱ ለእያንዳንዱ ማመልከቻ የሰጠውን ቁጥር፡፡

16.<u>የሥረ- ነገር ምርመራ</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ፡-

   ሀ) ማመልከቻ የቀረበለት የንግድ ምልክት በአዋጁ አንቀጽ 5 መሠረት ለምዝገባ ብቁ መሆኑን፣ ወይም

   ለ) ምዝገባው በአዋጁ አንቀጽ 6 ወይም አንቀጽ 7 መሠረት መከልከል ያለበት መሆኑን፣

   ለመወሰን በቀረበለት የንግድ ምዝገባ ማመልከቻ ላይ የሥረ-ነገር ምርመራ ያከናውናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በማመልከቻ ላይ የሥረ-ነገር ምርመራ የሚያከናውነው፡-

   ሀ) ለዚሁ ተግባር በጽሕፈት ቤቱ የወጣውን መመሪያ በመከተል ማመልከቻ የቀረበለትን ምልክት በመገምገም፣ እና

   ለ) የተመዘገቡ ምልክቶች እና በመታየት ላይ ያሉ ማመልከቻዎችን በተመለከተ በጽሕፈት ቤቱ መዛግብት የሠፈሩ መረጃዎችን በመፈተሽ፣

   ይሆናል፡፡

3. ማንኛውም ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በመፈጸም የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ከማቅረቡ በፊት ቀደም ሲል ተመሳሳይ የንግድ ምልክት አለመመዝገቡን ለማረጋገጥ ፍተሻ እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላል፡፡

17. **ተመሳሳይ የንግድ ምልክቶችን ለማስመዝገብ ስለሚቀርቡ ማመልከቻዎች**

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ማመልከቻዎች የሚመሳሰሉ የንግድ ምልክቶችን ለአንድ ዓይነት ወይም ለተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለማስመዝገብ በአንድ ቀን ለጽሕፈት ቤቱ ከቀረቡና የቀደምትነት መብት ለማንኛውም ተፈፃሚ የማይሆን ከሆነ፡-

1. ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀድሞ ጥቅም ላይ የዋለውን የንግድ ምልክት ለአዋጁ አንቀጽ 7 ዓላማ እንደቀዳሚ የንግድ ምልክት ሊቆጥረው ይችላል፤ ወይም
2. ከቀረቡት የንግድ ምልክቶች መካከል አንዱም በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ በጊዜ ቅደም ተከተል መጀመሪያ ማመልከቻ የቀረበለት የንግድ ምልክት ለአዋጁ አንቀጽ 7 ዓላማ ቀዳሚ ምልክት እንደሆነ ይቆጠራል።

18. **በጽሕፈት ቤቱ ስለሚወስድ እርምጃ**

ጽሕፈት ቤቱ ባደረገው የሥረ-ነገር ምርመራ፡-

1. አመልካቹ በአዋጁ አንቀጽ 5 መሠረት የተወሰኑ ተጨማሪ መሥፈርቶችን ማሟላት የሚገባው ሆኖ ካገኘዉ፤ ወይም
2. የንግድ ምልክቱ ምዝገባ በአዋጁ አንቀጽ 6 ወይም አንቀጽ 7 መሠረት ሊከለከል የሚገባው ሆኖ ካገኘው፤

ይህንኑ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

19. **ለጽሕፈት ቤቱ እርምጃ መልስ ስለመስጠት**

1. አመልካቹ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 18 መሠረት ለተሰጠው ማስታወቂያ ማስታወቂያው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ መልሱን ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል።
2. አመልካቹ በሚሰጠዉ መልስ፡-
   ሀ) የተጠየቀውን ተጨማሪ መሥፈርት ለማሟላት ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶች ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤ ወይም
   ለ) በዚህ ደንብ ማመልከቻ ማሻሻልን አስመልክቶ የተቀመጠው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሱትን እርምጃዎች ለመውሰድ በማመልከቻው ላይ ማሻሻያ ለማድረግ መጠየቅ፤

ይችላል፡፡

3. ጽሕፈት ቤቱ የአመልካቹ መልስ እንደደረሰው ማመልከቻዉን እንደገና ይመረምራል።

## 20.የመልስ መስጫ ጊዜን ስለማራዘም

1. አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 የተደነገገው የጊዜ ገደብ በበቂ ምክንያት እንዲራዘምለት የጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት በጽሑፍ ሲጠይቅ እና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘዉ ሰንጠረዥ የተመለከተዉን ክፍያ ሲፈጽም ሊራዘምለት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የጊዜ ገደቡ ሊራዘም የሚችለው የመልስ መስጫ የጊዜ ገደብ ከሚያበቃበት ጊዜ ጀምሮ ለተከታታይ 90 ቀናት ይሆናል፤ ሆኖም ከሁለት ጊዜ በላይ ሊራዘም አይችልም።
3. ጽሕፈት ቤቱ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄው የተፈቀደ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 21.ማመልከቻን ውድቅ ስለማድረግ

1. አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 መሠረት የሰጠው መልስ እንደቀረበ ማመልከቻው እንደገና ተመርምሮ በተገኘው ውጤት አመልካቹ የተጠየቁትን ተጨማሪ መሥፈርቶች ሙሉ በሙሉ አለማሟላቱ ወይም ለምዝገባዉ እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶችን ለማስወገድ አለመቻሉ የተረጋገጠ እንደሆነ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠ ውሳኔ ለአመልካቹ በጽሑፍ መድረስና የምዝገባ ማመልከቻዉ ዉድቅ የተደረገባቸዉን ምክንያቶች መግለጽ አለበት፡፡
3. የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ የተደረገበት አመልካች የጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ በደረሰው 60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 22.ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገ በሃላ በአመልካቹ ስለሚወስድ እርምጃ

አመልካቹ የይግባኝ ጊዜው ከማለፉ በፊት ሳይሟሉ የቀሩ መስፈርቶችን ለማሟላት ወይም ለምዝገባዉ እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶችን ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ወይም እነዚህን እርምጃዎች ለመዉሰድ ማመልከቻውን ማሻሻል ይችላል፡፡

**23.<u>የተተወ ማመልከቻ</u>**

1. ጽሕፈት ቤቱ በሚከተሉት ምክንያቶች አንድን ማመልከቻ እንደተተወ ይቆጥረዋል፤
   ሀ) ማመልከቻው እየታየ ባለበት ወቅት በማንኛውም ጊዜ አመልካቹ ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ በማሳወቅ ማመልከቻውን የተወ እንደሆነ፤
   ለ) አመልካቹ ለጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ መልስ መስጠት የነበረበት ጊዜ ወይም የተራዘመዉ የመልስ መስጫ ጊዜ ሳይበቃ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ ወይም ሳይሟሉ የቀሩትን መስፈርቶች ለማሟላት ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶች ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ያልወሰደ ወይም እነዚሁኑ እርምጃዎች ለመዉሰድ ማመልከቻዉን ያላሻሻለ እንደሆነ፤
   ሐ) በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የነበረበት ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ፤ ወይም
   መ) ይግባኝ አቅርቦ ይግባኙ ውድቅ የሆነበት እንደሆነ።
2. ማመልከቻው የተተወ እንደሆነ ጽሕፈት ቤቱ በመዝገቡ ላይ "የተተወ" የሚል ምልክት በማድረግ በተተዉ መዝገቦች ፋይል ዉስጥ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

**24.<u>መርማሪ ከመሆን ስለመነሳት</u>**

ማንኛውም ለንግድ ምልክት ምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ እንዲመረምር በጽሕፈት ቤቱ የተመደበ ሰዉ፡-

1. ከአመልካቹ ወይም ከወኪሉ ጋር የቅርብ ዝምድና ያለው ሆኖ ሲገኝ፤
2. በንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው ላይ ጥቅም ያለው ሲሆን፤ ወይም
3. ከአመልካቹ ወይም ከወኪሉ ጋር ያለው ማንኛውም ሌላ ዓይነት ግንኙነት ከአድሎ ነጻ የሆነ ምርመራ እንዳያካሂድ ተጽኖ ሊያሳድር የሚችል ሆኖ ሲገኝ፤ በራሱ አነሳሽነት ወይም በአመልካቹ ወይም በሌላ ጉዳዩ በሚመለከተው ወገን በሚቀርብ ጥያቄ ከምርመራ ኃላፊነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## የንግድ ምልክት ምዝገባን ስለመቃወም

### 25.የንግድ ምልክት ለምዝገባ ብቁ መሆንን ስለማሳወቅ

ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ የቀረበለት የንግድ ምልክት፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ወይም አንቀጽ 19(3) መሠረት የተደረገ ምርመራን ወይም ድጋሚ ምርመራን፤ ወይም
2. ሳይሟሉ የቀሩ መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ለማሟላት ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶችን ለማስወገድ አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ 22 መሠረት የወሰዳቸውን እርምጃዎች፤

ተከትሎ ለምዝገባ ብቁ ሆኖ ካገኘው የንግድ ምልክቱን ለተቃውሞ ጥሪ ሕትመት ማዘጋጀትና ማመልከቻው ለምዝገባና ለተቃውሞ ጥሪ ተቀባይነት እንዳለው ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

### 26.የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ስለማውጣት

1. ጽሕፈት ቤቱ፡-

   ሀ) የአመልካቹን ስምና አድራሻ፤

   ለ) የንግድ ምልክቱን ሥዕላዊ መግለጫ፤

   ሐ) ማመልከቻው የሚሸፍናቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና የምደባ ቁጥራቸዉን፤

   መ) እንደአግባቡ ማመልከቻው ገቢ የሆነበትን ቀን ወይም የቀዳሚነት መብት ቀን

   ሠ) የማመልከቻውን ቁጥር፤

   ረ) የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ፤ እና

   ሰ) አመልካቹ ወኪል ካለው ስምና አድራሻውን፤

   በማካተት የንግድ ምልክቱን ምዝገባ የሚቃወም ቢኖር እንዲቀርብ በአዋጁ አንቀጽ 12 መሠረት በአመልካቹ ወጪ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ያሳትማል።

2. አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ 25 የተመለከተው ማስታወቂያ በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያውን ማሳተሚያ ካልከፈለ ማመልከቻውን እንደተወው ተቆጥሮ የዚህ ደንብ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

27.<u>የንግድ ምልክት ምዝገባን ስለመቃወም</u>

1. ለምዝገባ የቀረበውን የንግድ ምልክት ለመቃወም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የተቃውሞ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የተቃውሞ ማመልከቻው ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

   ሀ) ተቃውሞው የተመሠረተባቸውን ምክንያቶች የሚደገፉ ማስረጃዎች፤

   ለ) በዚህ ደንብ የተወሰነው ክፍያ መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

   ሐ) ተቃውሞው የቀረበው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጅ እና ፈራሚው ሰው ድርጅቱን ወክሎ ለመፈረም የሚያስችል ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

   መ) ማመልከቻው በወኪል አማካይነት የቀረበ ከሆነ የወኪሉ የምዝገባ የምስክር ወረቀትና በአግባቡ የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ፡፡

28.<u>ተቃውሞ ማቅረቢያ ጊዜ</u>

1. የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ የሚቀርብ የተቃውሞ ማመልከቻ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ከታተመበት ቀን ጀምሮ በ60 በቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
2. ጽሕፈት ቤቱ ተቃዋሚው ወገን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ጊዜ ከማለቁ በፊት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በመፈፀም በጽሁፍ ከጠየቀ የተቃውሞ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜውን ለተጨማሪ 60 ቀናት ሊያራዝምለት ይችላል፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተፈቀደ የመቃወሚያ ጊዜ መራዘምን የንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ እንዲያዉቀዉ ማድረግ አለበት፡፡

29.<u>በተቃውሞ ማመልከቻ ላይ ዉሳኔ ስለመስጠት</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ የተቃዉሞ ማመልከቻ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የማመልከቻዉንና የተያያዙ ሰነዶችን ቅጂ ለንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ እንዲደርሰዉ ማድረግ አለበት፡፡

2. ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ ለቀረበው ተቃዉሞ በአዋጁ አንቀጽ 13(3) መሠረት መልስ ሊሰጥ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ያሳውቀዋል። ይህም የግዜ ገደብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተቃውሞ ማመልከቻው እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ90 ቀናት ያነሰ ሊሆን አይችልም።
3. የንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልሱን ካላቀረበ ማመልከቻውን እንደተወዉ ተቀጥሮ የዚህ ደንብ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡
4. ጽሕፈት ቤቱ ለመቃወሚያው የተሰጠው መልስ በቀረበ በ90 ቀናት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 13(4) መሠረት በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ላይ ከሁለት ባንዱ ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ጥያቄ በዚህ ደንብ አንቀጽ 30 መሠረት ያልቀረበ እንደሆነ ውሳኔው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

30.<u>ይግባኝ ስለማቅረብ</u>

የንግድ ምልክት ምዝገባን በመቃወም የቀረበ ማመልከቻን በተመለከተ በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 17(2) መሠረት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የምዝገባ ሥነ ሥርዓት

31.<u>የንግድ ምልክትን ስለመመዝገብ</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ በንግድ ምልክት ምዝገባው ላይ የቀረበ ወይም ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ተቃውሞ ከሌለ የንግድ ምልክቱ ለምዝገባ ብቁ መሆኑን በመግለጽ አመልካቹ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ እንዲፈጽም ያሳውቀዋል።
2. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለአመልካቹ በሚልከው ማስታወቂያ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 5(3) ድንጋጌ መሠረት ጥበቃ ሊደረግላቸው በማይችሉ የንግድ ምልክቱ ይዘቶች ላይ አመልካቹ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት እንዳይጠይቅ ለምዝገባው እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

3. አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ማስታወቂያ በደረሰው 90 ቀናት ውስጥ፡-

   ሀ) አግባብ ያለውን ክፍያ፤ እና

   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተቀመጠ ቅደመ ሁኔታን የተቀበለ መሆኑን ከገለጸ፤

   ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱን ይመዘግባል።

4. አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አግባብ ያለውን ክፍያ ካልፈጸመ ወይም የተጣለውን ቅድመ ሁኔታ መቀበሉን ካልገለጸ ማመልከቻውን እንደተወው ተቆጥሮ የዚህ ደንብ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

32.<u>የምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 31 መሠረት የንግድ ምልክትን እንደመዘገበ ለአመልካቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

   ሀ) የንግድ ምልክቱን ቅጅ፤

   ለ) የምዝገባውን ቀንና ቁጥር፤

   ሐ) የባለቤቱን ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤

   መ) እንደአግባቡ ማመልከቻው ገቢ የሆነበትን ቀን ወይም የቀዳሚነት መብትን ቀን፤

   ሠ) ምዝገባው የሚሸፍናቸዉን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና የምደባ ቁጥራቸውን፤

   ረ) ምዝገባዉ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤

   ሰ) አመልካቹ ወኪል ካለው ስምና አድራሻውን፤ እና

   ሸ) የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ፡፡

33.<u>ምዝገባን ስለማሳወቅ</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 32 (2) መሠረት በምዝገባው የምስክር ወረቀት ከተዘረዘሩት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መረጃዎች የያዘና የንግድ

ምልክቱ የተመዘገበ ስለመሆኑ የሚገልጽ የምዝገባ ማስታወቂያ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት እንዲወጣ ያደርጋል።

2. በጽሕፈት ቤቱ የተመዘገበው የንግድ ምልክት ባለቤት ይህን ® ምልክት ከንግድ ምልክቱ ጋር በቅርበት ተያይዞ እንዲታይ በማድረግ የንግድ ምልክቱን መመዝገብ ማስተዋዋቅ ይችላል፡፡

**34.<u>ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>**

1. የንግድ ምልክት ምዝገባ የምሰክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት የምዝገባ ባለቤት ምትክ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ጽህፈት ቤቱ ስለጠፋው የምስክር ወረቀት በአመልካቹ ወጪ ማስታወቂያ በማሳተም ወይም የተበላሸው የምስክር ወረቀት እንዲመለስ በማድረግ እና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

**35.<u>የንግድ ምልክቶች መዝገብ</u>**

1. ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቶች መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፡፡
2. ጽሕፈት ቤቱ፡-

   ሀ) የሚመዘግባቸውን የንግድ ምልክቶች፤

   ለ) የሚያድሳቸውን፣ የሚያሻሽላቸውን፣ የሚሰርዛቸውንና ፈራሽ የሚያደርጋቸውን የንግድ ምልክት ምዝገባዎች፤ እና

   ሐ) የንግድ ምልክት ባለቤትነት ማስተላለፍንና የፈቃድ ውሎችን፤

   የሚመለከቱ መረጃዎችን በንግድ ምልክቶች መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት በንግድ ምልክቶች መዝገብ ውስጥ ከሚያሰፍራቸው ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች በስተቀር የተመዘገበ የንግድ ምልክትን በተመለከተ በመዝገቡ ውስጥ የሚሠፍሩ መረጃዎች በምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ላይ ከሠፈሩት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው።

**36.<u>የንግድ ምልክቶች ምደባ ሥርዓት</u>**

ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቶችን የሚመዘግበው ምልክቶችን ለመመዝገብ ዓላማ ተፈጻሚነት የሚኖረውን ዓለም አቀፍ የዕቃዎች እና አገልግሎቶች አመዳደብ ሥርዓት በመከተል ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የንግድ ምልክት ምዝገባ እድሳት እና ማሻሻል

### 37.የእድሳት ማመልከቻ አቀራረብ

የንግድ ምልክት ምዝገባ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና ተገቢው የማመልከቻ ክፍያ መፈጸሙን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ በአዋጁ አንቀጽ 25(3) በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ ለጽሕፈት ቤቱ መቅረብ አለበት፡፡

### 38.የእድሳት ጥያቄን ስለመቀበል ወይም ውድቅ ስለማድረግ

1. ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ እድሳት ማመልከቻን መርምሮ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ አስከፍሎ ምዝገባውን በማደስ ለምዝገባ ባለቤቱ የእድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።
2. ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ ዕድሳት ጥያቄው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ሆኖ ሲያገኘው የእድሳት ማመልከቻውን ያልተቀበለው መሆኑንና ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ ውሳኔውን ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።
3. ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱን ምዝገባ ካደሰ በኋላ በምስክር ወረቀቱ ላይ የተገለጹትን መረጃዎች በማካተት የንግድ ምልክቱ የታደሰ ስለመሆኑ ማስታወቂያ ያሳትማል።

### 39.ስለምዝገባ ቀሪ መሆን

1. የንግድ ምልክት ምዝገባ ባለቤት፡-
   ሀ) በወቅቱ የእድሳት ጥያቄ ማመልከቻ ያላቀረበ ወይም ተገቢውን ክፍያ ያልፈጸመ እንደሆነ፣ ወይም
   ለ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ 38(2) የተመለከተው ማስታወቂያ በደረሰው 90 ቀናት ውስጥ በማስታወቂያው የተገለጹትን የእድሳት ጥያቄውን ለመቀበል መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፣ ወይም
   ሐ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ 38(2) የተመለከተው ማስታወቂያ በደረሰው 60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የጽሕፈት ቤቱን ውሳኔ ያላሻረ እንደሆነ፣

   የንግድ ምልክት ምዝገባው ቀሪ እንደሆነ ይቆጠራል።

2. የንግድ ምልክት ምዝገባ ባለቤቱ፡-
   ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ያልቻለበትን አሳማኝ ምክንያት ጊዜው ከማለፉ በፊት በማቅረብ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው በጽሑፍ ካመለከተ፤ እና
   ለ) ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰነውን ክፍያ ከፈጸመ፤
   
   በዚህ ደንብ አንቀጽ 38(2) የተገለጹትን የእድሳት ጥያቄውን ለመቀበል መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ለማሟላት እንዲችል ጽሕፈት ቤቱ ተጨማሪ የ90 ቀናት ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

40. <u>ምዝገባን ስለማሻሻል</u>

1. የንግድ ምልክት ምዝገባ በሚከተሉት ምክንያቶች እንዲሻሻል ሊፈቀድ ይችላል።
   ሀ) በምዝገባው ላይ የተፈጸመ ስህተትን ለማረም፤
   ለ) ምዝገባው ከሚሸፍናቸው እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር ውስጥ የተወሰኑትን እቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና የምደባ ቁጥራቸውን ለመሠረዝ፤
   ሐ) የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫን ለመመዝገብ፤ ወይም
   መ) በምዝገባው ላይ ሌሎች መሠረታዊ ያልሆኑ ለውጦችን ለማድረግ፡፡
2. የንግድ ምልክት ምዝገባን ለማሻሻል የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽሕፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት፡-
   ሀ) በጽሕፈት ቤቱ ምክንያት የተፈጠረን ስህተት ለማሳረም የቀረበ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ክፍያ መፈጸሙን ከሚያሳይ ማስረጃ፤
   ለ) የንግድ ምልክቱን ማሻሻል የሚመለከት ሲሆን ከተሻሻለው የንግድ ምልክት ስዕላዊ መግለጫ ሦስት ኮፒ፤ እና
   ሐ) ከምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ዋና ቅጅ፤
   
   ጋር ተያይዞ ለጽሕፈት ቤቱ መቅረብ አለበት፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን መርምሮ የማሻሻያውን ተገቢነት ሲያረጋግጥ የተደረጉትን ለውጦች በንግድ ምልክቶች መዝገብ ውስጥ በማስፈር ለምዝገባ ባለቤቱ በማሻሻያው ላይ የተመሠረተ አዲስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤ ሆኖም ማሻሻያው በምዝገባው ላይ የተፈጸመ ስህተትን ለማረም

የተደረገ ከሆነ ምዝገባው መጀመሪያ በተፈጸመበት ጊዜ ተስተካክሎ እንደተፈጸመ ምዝገባ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል።

4. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተዉ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ላይ ከሠፈሩት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መረጃዎች የያዘና የንግድ ምልክት ምዝገባው የተሻሻለ ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስታወቂያ አሳትሞ ያወጣል።

41.<u>የወል የንግድ ምልክት አጠቃቀም የሚመራበትን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 22(1) መሠረት ለምዝገባ የቀረበ የወል የንግድ ምልክት አጠቃቀም የሚመራበት መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያን መመርመርና ለሕዝብ ሰላም ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎችን ያልያዘ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. በማሻሻያዉ ላይ ተቃዉሞና አሰተያየት ለመጋበዝ በአዎጁ አንቀጽ 22(2) መሠረት የሚወጣው ሕትመት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

   ሀ) የወል የንግድ ምልክቱን ባለቤት ስም፣

   ለ) የወል የንግድ ምልከቱን፣

   ሐ) ምልክቱ የሚሸፍናቸዉን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣

   መ) የምዝገባውን ቁጥርና ቀን፣

   ሠ) የተሸሻለዉን የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ፣ እና

   ረ) ተቃዉሞ ወይም አስተያየቱ መቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ፣ ሆኖም የጊዜ ገደቡ ከሕትመቱ ቀን ጀምሮ ከ60 ቀናት ያነሰ ሊሆን አይችልም።
3. ጽሕፈት ቤቱ፡-

   ሀ) ማሻሻያው ለሕዝብ ሰላም ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆነ ድንጋጌ አለመያዙን፣ እና

   ለ) ምዝገባውን ሊያስከለክል የሚችል ተቃውሞ ወይም አስተያየት ያልቀረበ መሆኑን፣

   ሲያረጋግጥ የተሻሻለውን መተዳደሪያ ደንብ መዝግቦ የምዝገባ ማስታወቂያ እንዲታተም ያደርጋል፣
4. ጽሕፈት ቤቱ የተሻሻለውን መተዳደሪያ ደንብ የምዝገባ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ውሳኔውን ከነምክንያቶቹ ለምዝገባው ባለቤት ማሳወቅ አለበት፡፡

5. በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የምዝገባ ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## መብትን ስለመተዉ እና ምዝገባን ስለመሰረዝና ፈራሽ ስለማድረግ

### 42. መብት ስለመተው

1. በተመዘገበ የንግድ ምልክት ላይ ያለ መብትን በመተው ምዝገባውን ለማሠረዝ በአዋጁ አንቀጽ 34(1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በጽሕፈት ቤቱ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡
2. የንግድ ምልክቱ በፈቃድ ውል ለሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ተሰጥቶ ከሆነና ይኸው በንግድ ምልክቶች መዝገብ ተመዝግቦ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 34(2) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው መስማማቱን በመግለጽ ከሰጠው መግለጫ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

### 43. ምዝገባን ስለመሰረዝ ወይም ፈራሽ ስለማድረግ

1. የንግድ ምልክት ምዝገባን በአዋጁ አንቀጽ 35 ወይም አንቀጽ 36 መሠረት ለማሰረዝ ወይም ፈራሽ ለማስደረግ በሚመለከተው ሰው የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽሕፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከደጋፊ ማስረጃዎችና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰነው ክፍያ መፈጸሙን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
2. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻና ደጋፊ ማስረጃዎች ለምዝገባ ባለቤቱ እንዲደርሰው በማድረግ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ እንዲሰጥበት ያሳውቀዋል፤ ሆኖም የሚሰጠዉ የጊዜ ገደብ ማስታወቂያ ከደረሰዉ ቀን ጀምሮ ከ60 ቀናት ማነስ የለበትም፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት የንግድ ምልክት ምዝገባ ፈራሽ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት መኖሩን ሲረዳ የምዝገባ ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ምላሽ እንዲሰጥበት በፅሁፍ ያሳዉቃል፤
4. የምዝገባ ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረተ በተወሰነዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ መልሱን ካላቀረበ ምዝገባዉን ለመሠረዝ ወይም

ፈራሽ ለማድረግ ያስችላሉ ተብለዉ የተጠቀሱትን ምክንያቶች እንደተቀበላቸዉ ተቆጥሮ ጽሕፈት ቤቱ ምዝገባዉን የመሠረዝ ወይም ፈራሽ የማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5. የምዝገባ ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልሱን ካቀረበ ጽሕፈት ቤቱ የተነሱትን የክርክር ጭብጦችና የቀረቡለትን ማስረጃዎች በሚገባ መርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ወይም (5) መሠረት በጽሕፈት ቤቱ የተሰጠ ውሳኔ ቅጅ ለምዝገባ ባለቤቱና እንደ አግባቡ ምዝገባው እንዲሠረዝ ወይም ፈራሽ እንዲሆን ላመለከተው ሰው እንዲደርሳቸዉ ይደረጋል፡፡
7. የምዝገባዉ ባለቤት፡-

   ሀ) ጽሕፈት ቤቱ ምዝገባ እንዲሰረዝ ወይም ፈራሽ እንዲሆን የሰጠዉ ዉሳኔ በደረሰዉ 60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ካላቀረበ፤ ወይም

   ለ) ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔዉን ካልሻረለት፤

   የምዝገባዉ መሰረዝ ወይም ፈራሽ መሆን በንግድ ምልክቶች መዝገብ እንዲሰፍርና በማስታወቂያ ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል፤

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለባለቤትነት መተላለፍ እና ስለፍቃድ ውል

### 44. የባለቤትነት መተላለፍን እና የፍቃድ ውልን ስለመመዝገብ

1. የተመዘገበ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መተላለፍን ወይም የፍቃድ ውልን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽህፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት ከባለቤትነት ማስተላለፊያ ስምምነት ሰነዱ ወይም ከፍቃዱ ውሉ ቅጅና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ የተወሰነውን ክፍያ መፈፀሙን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
2. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ማመልከቻ ተሟልቶ ሲቀርብለት ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች በንግድ ምልክቶች መዝገብ ላይ ማስፈርና የምዝገባ ማስታወቂያ ማሳተም አለበት፤-

ሀ) ባለቤትነት የተላለፈለትን ወይም የፈቃድ ውል የተሰጠውን ሰው ሙሉ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤

ለ) የባለቤትነት መተላለፉ ወይም የፈቃድ ውሉ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝርና ምደባቸውን፤

ሐ) ባለቤትነት በተላለፈበት ስምምነት ወይም በፈቃድ ውሉ መሠረት የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልበትን ጂኦግራፊያዊ ክልል፤ እና

መ) የባለቤትነት መተላለፉ ወይም የፈቃድ ውሉ የተመዘገበበትን ቀን።

3. የባለቤትነት መተላለፉ ወይም የፈቃድ ውሉ የሚመለከተው በንግድ ምልክቱ ምዝገባ ከተሸፈኑት እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ውስጥ የተወሰኑትን ብቻ ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ የነዚህኑ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር የያዘ አዲስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ባለቤትነቱ ለተላለፈለት ሰው ወይም ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ለባለፈቃዱ ይሰጣል፡፡

45.<u>የፈቃድ ውል መሰረዝን ስለመመዝገብ</u>

1. የተመዘገበ የንግድ ምልክት የፈቃድ ውል መሠረዝን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽሕፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የፈቃድ ውሉን ከሰረዘው ሰነድ ቅጅና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰነው ክፍያ መፈጸሙን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

2. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ማመልከቻ ተሟልቶ ሲቀርብለት የፈቃድ ውሉ ስለመሰረዙ በንግድ ምልክቶች መዝገብ ላይ ማስፈርና የምዝገባውን መሰረዝ የሚመለከት ማስታወቂያ ማሳተም አለበት፡፡

<u>ክፍል አሥር</u>

<u>ስለመከፋፈል፣ ስለማዋሃድ እና ተከታታይነት ስላላቸው የንግድ ምልክቶች</u>

46.<u>ማመልከቻን ስለመከፋፈል</u>

1. ማንኛውም አመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባው ከመከናወኑ በፊት በማናቸውም ጊዜ ማመልከቻው በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ የተለያዩ ማመልከቻዎች እንዲከፋፈል በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡

2. አመልካቹ እያንዳንዱ የተከፋፈለው ማመልከቻ የሚሸፍናቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡

3. የክፍፍሉ ውጤት የሆነው እያንዳንዱ ማመልከቻ የመጀመሪያውን ማመልከቻ ቀን እንደያዘ ሆኖ እንደተለያየ ማመልከቻ ይስተናገዳል፡፡
4. ማመልከቻ ለመከፋፈል ጥያቄ የቀረበው ማመልከቻው ከታተመ በኋላ ከሆነ በመጀመሪያው ማመልከቻ ላይ የቀረበው ተቃውሞ የክፍፍሉ ውጤት በሆነው በእያንዳንዱ ማመልከቻ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

47.<u>የተለያዩ ማመልከቻዎችን ስለማዋሃድ</u>

1. የተለያዩ ማመልከቻዎችን ያቀረበ አመልካች ጽሕፈት ቤቱ ማናቸውንም ማመልከቻ የማሳተም ዝግጅቱን ከማጠናቀቁ በፊት በማንኛውም ጊዜ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከቻዎቹ እንዲዋሃዱ ማመልከት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የማዋሃድ ጥያቄ የቀረበባቸው ማመልከቻዎች፡-
   ሀ) አንድ ዓይነት የንግድ ምልክትን የሚመለከቱ ከሆነ፤
   ለ) አንድ ዓይነት የማመልከቻ ቀን ካላቸው፤ እና
   ሐ) የውህደት ጥያቄው በቀረበበት ወቅት በአንድ ሰው ስም ተይዘው የሚገኙ ከሆነ፤

   ጽሕፈት ቤቱ ጥያቄውን ተቀብሎ ወደ አንድ ማመልከቻነት ያዋህዳቸዋል፡፡

48.<u>የተለያዩ ምዝገባዎችን ስለማዋሃድ</u>

1. የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የንግድ ምልክት ምዝገባዎች ባለቤት የሆነ ሰው ምዝገባዎቹ ወደ አንድ ምዝገባ እንዲዋሃዱ በጽሕፈት ቤቱ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡
2. ምዝገባዉ አንድ አይነት የንግድ ምልክትን የሚመለከት ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ የተለያዩትን ምዝገባዎች ወደ አንድ ምዝገባ ያዋህዳል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚዋሃዱት ምዝገባዎች አንዱ የብቸኝነት መብትን ያለመጠየቅ መግለጫ የያዘ ከሆነ ይኸው ገደብ በተዋሃደው ምዝገባም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. የተዋሃዱት ምዝገባዎች የተለያየ የምዝገባ ቀናት ከኖራቸው ከምዝገባ ቀኖቹ ውስጥ የቅርብ ጊዜ የሆነው የተዋሃደው ምዝገባ ቀን ይሆናል፡፡

## 49.ተከታታይነት ስላላቸው የንግድ ምልክቶች ምዝገባ

1. ተከታታይነት ያላቸው የንግድ ምልክቶች ባለቤት የሆነ ሰው የንግድ ምልክቶቹ በአንድ ምዝገባ ውስጥ ተከታታይ ሆነው እንዲመዘገቡለት በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡
2. ተከታታይ የተባለው የእያንዳንዱ የንግድ ምልክት ስዕላዊ መግለጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚቀርበው ማመልከቻ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቶቹ ተከታታይነት ያላቸው መሆናቸውን ሲያምን ማመልከቻውን ተቀብሎ ተከታታይ አድርጎ ይመዘግባቸዋል፡፡

## 50.ተከታታይነት ያላቸው የንግድ ምልክቶች ማመልከቻን ስለመከፋፈል

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 49 መሠረት ተከታታይነት ያላቸው የንግድ ምልክቶችን ለማስመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን የማሳተም ዝግጅቱን ከማጠናቀቁ በፊት በማንኛውም ጊዜ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከቻው በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የተለያዩ ማመልከቻዎች እንዲከፋፈል ማመልከት ይችላል፡፡
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 46(2) የተደነገገው ሁኔታ ከተሟላ ጽሕፈት ቤቱ ጥያቄውን ተቀብሎ ማመልከቻውን ይከፋፍለዋል፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ
## ስለንግድ ምልክት ወኪሎች

## 51.ምዝገባ

1. ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ሂደት ጋር በተያያዘ የንግድ ምልክት ባለቤቶችን የመወከል አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በንግድ ምልክት ወኪልነት መመዝገብ አለበት፡፡
2. በንግድ ምልክት ወኪልነት በጽሕፈት ቤቱ ለመመዝገብ የሚፈልግ አመልካች፤-
   ሀ) መኖሪያ አድራሻው በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ፤
   ለ) ዕድሜው ቢያንስ 21 ዓመት የሞላው፤
   ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው ጠበቃ ወይም አግባብ ባለው ዘርፍ ቢያንስ መካከለኛ የትምህርት ደረጃ ያለው፣ ከንግድ

ምልክት ጋር የተያያዘ ከሦስት ዓመት ያላነሰ ልምድ ያለውና በጽሕፈት ቤቱ የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ያለፈ ሰው፤ እና

መ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል የተሰጠ የወንጀል ወይም የሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ውሳኔ ሪከርድ የሌለበት፤

መሆን አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በመፈፀም ለንግድ ምልክት ወኪሎች የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ መውሰድ ይችላል፡፡
4. ጽሕፈት ቤቱ ለንግድ ምልክት ወኪሎች የሚስጠውን የብቃት መመዘኛ በመመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰጣል፡፡

52.<u>የምዝገባ ምስክር ወረቀት</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ የምዝገባ ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ 51 የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል የአመልካቹን ስም በንግድ ምልክት ወኪሎች መዝገብ በማስፈር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
2. የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ፡-

ሀ) የንግድ ምልክት ወኪሉን ሙሉ ስም፣ ዜግነት እና የመኖሪያና የሥራ አድራሻ፤

ለ) የምዝገባውን ቀን፤ እና

ሐ) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሰጪውን ኃላፊ ስምና ፊርማ፤

የሚያካትት ይሆናል፡፡

3. የንግድ ምልክት ወኪል የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ይሆናል፡፡

53.<u>የምዝገባ ዕድሳት</u>

1. የንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት ምዝገባው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለጽሕፈት ቤቱ መቅረብ አለበት፡፡

2. ጽሕፈት ቤቱ የእድሳት ማመልከቻ ሲቀርብለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 51(2) ተራ ፊደል (ሀ) እና (መ) የተመለከቱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ምዝገባዉን አድሶ የዕድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
3. የእድሳት ማመልከቻው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረበ በሚቀጥሉት 30 ቀናት ውስጥ ሊቀርብና በዚህ ደንብ አንቀጽ 56(3) መሠረት የሚወሰነው ተጨማሪ ክፍያ ተፈጽሞ ሊታደስ ይችላል፡፡

54.<u>የተመዘገቡ የንግድ ምልክት ወኪሎችን ዝርዝር ስለማሳተም</u>

ጽሕፈተ ቤቱ የተመዘገቡ የንግድ ምልክት ወኪሎችን ዝርዝር በየዓመቱ ያሳተማል፡፡

<u>ክፍል አሥራ ሁለት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

55.<u>መረጃ ስለመጠየቅና ማግኘት</u>

ማንኛውም የሚመለከተዉ ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ መሠረት የተወሰነውን ክፍያ ለመፈጸም፡-

1. የንግድ ምልክት ፍለጋ ተደርጎ የፍለጋ ሪፖርቱ እንዲሰጠው፤ ወይም
2. የንግድ ምልክቶች መዝገብን ወይም በጽሕፈት ቤቱ ለሕዝብ ክፍት የተደረጉ ሌሎች ሪከርዶችንና ሰነዶችን ለመመልከትና ቅጂዎቻቸዉ እንዲሰጡት፤

በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

56.<u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ጽሕፈት ቤቱ ለሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከቱት ተመኖች መሠረት ይከፈላሉ።
2. የሚሰጠዉ አገልግሎት ምድባቸዉ ከአንድ በላይ የሆነ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸፍን የንግድ ምልክት የሚመለከት ሲሆን ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ምድብ በሠንጠረዡ የተመለከተዉ ክፍያ 50 በመቶ በተጨማሪነት ይከፈላል፡፡
3. በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ የተወሰነው መደበኛው የማሳደሻ ጊዜ ካለፈ በኃላ ዘግይቶ ለሚፈፀም ማንኛውም የምዝገባ እድሳት በሰንጠገጡ የተመለከተው አግባብ ያለው ክፍያ 50 በመቶ በተጨማሪነት ይከፈላል፡፡

57.<u>ስለጊዜ ገደቦች አቆጣጠር</u>

በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ በተመለከተ የጊዜ ገደብ ያበቃበት ቀን በስራ ቀን ላይ ያልዋለ እንደሆነ ገደቡ የሚያበቃዉ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን ይሆናል፤

58.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን በፊት ቀርበዉ በመታየት ላይ ያሉ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻዎች ሲሠራበት በቆየው ስርዓት መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ፤ ሆኖም ገና ያልተፈፀሙ የአገልግሎት ክፍያዎችን በሚመለከት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ የተወሰኑት ሰነዶች ተፈፃሚ ይሆናሉ።
2. ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን በፊት የተመዘገቡ የንግድ ምልክት ወኪሎች ጽሕፈት ቤቱ በመመሪያ በሚወስነዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልተዉ እንደገና መመዝገብ አለባቸው።

59.<u>መመሪያ የማዉጣት ስልጣን</u>

ጽሕፈት ቤቱ አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

60.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክጠቅላይ ሚኒስትር**

## ሰንጠረዥ

## የአገልግሎት ክፍያዎች

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| 1 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ | 1750.00 |
| 2 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ማሻሻያ | 350.00 |
| 3 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ መቃወሚያ | 1500.00 |
| 4 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ | 3000.00 |
| 5 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ዕድሳት ማመልከቻ | 1300.00 |
| 6 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ዕድሳት | 2200.00 |
| 7 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማሻሻያ ማመልከቻ | 350.00 |
| 8 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማሻሻያ | 360.00 |
| 9 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ምትክ የምስክር ወረቀት | 495.00 |
| 10 | ለንግድ ምልክት ምዝገባ የማሰረዝ ወይም ፈራሽ የማስደረግ ማመልከቻ | 2600.00 |
| 11 | ለንግድ ምልክት ባለቤትነት መተላለፍ ምዝገባ | 1300.00 |
| 12 | ለንግድ ምልክት የፍቃድ ውል ምዝገባ | 1300.00 |
| 13 | ለንግድ ምልክት ፈቃድ ውል መሠረዝ ምዝገባ | 450.00 |
| 14 | የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻዎችን ለመከፋፈል (የክፍፍሉ ውጤት ለሆነው ለእያንዳንዱ ማመልከቻ) | 350.00 |
| 15 | የንግድ ምልክት ምዝገባዎችን ወይም የምዝገባ ማመልከቻዎችን ለማዋሀድ<br>(ለእያንዳንዱ ምዝገባ ወይም ማመልከቻ) | 350.00 |
| 16 | ለንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባ ማመልከቻ | 315.00 |
| 17 | ለንግድ ምልክት ወኪሎች ብቃት መመዘኛ | 270.00 |
| 18 | ለንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባ | 1350.00 |
| 19 | ለንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባ ዕድሳት | 1125.00 |
| 20 | ለጊዜ ገደብ ማራዘሚያ ማመልከቻ | 500.00 |

## የፍትህ ሚኒስቴር

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| 21 | ለተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች የማጣራት ፍለጋ | 450.00 |
| 22 | የጽሕፈት ቤቱን ሪኮርዶችና ሰነዶች ለመመልከት | 150.00 |
| 23 | ለሪኮርዶችና ሰነዶች ቅጂ (በገጽ) | 10.00 |

**ሐ/ ጥራትና ደረጃዎች**

## የመንግሥት ማስታወቂያ ቁጥር 6/1934 ዓ.ም

## አዲሱን ደንበኛ ሰዓት በኢትዮጵያ ስለመከተል የወጣ ማስታወቂያ

ሦስት ሰዓት ከሚቀድመው ከደንበኛ ከግሪኒቢች የሰዓት አቆጣጠር ጋር የተስማማ እንዲሆን ከነሐሴ 11 ቀን 1934 ዓ.ም ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዓቶች ሁሉ ከቀድሞው ልክ ሩብ ሰዓት እንዲቀድሙ መደረጉን እናስታውቃለን፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 10 ቀን 1934 ዓ.ም**

**ጸ.ት.ወ.ጊዮርጊስ**

**የጽሕፈት ሚኒስትር**

## የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 431/1965 ዓ.ም

## የሚዛንና የመሥፈሪያ ደንብ

1. **አውጭው ባለሥልጣን**

የንግድ፣ እንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስትር በቁጥር 208/1955 ዓ.ም (እንደተሻሻለ) በወጣው የሚዛንና የመሥፈሪያ አዋጅ (ከዚህ ቀጥሎ አዋጅ እየተባለ በሚጠራው) በአንቀጽ 13 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በደረጃዎች ምደባ ቦርድ አሳሳቢነት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር አርእስት**

ይህ ደንብ "የ1965 ዓ.ም የሚዛንና የመሥፈሪያ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **የተሻረ ደንብ**

በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 333/1960 ዓ.ም የወጣው የሚዛንና የመሥፈሪያ ደንብ ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል፡፡

4. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፣

1. "ድርጅት" ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ድርጅት ነው፡፡[124]
2. "ኢንስፔክተር" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 11 በተመለከተው መሠረት የእንስፔክተር ተግባር እንዲያከናውን በድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣን የተሰጠው ማናቸውም ሰው ነው፡፡[125]
3. "የመሥፈሪያ መሣሪያ" ማለት የክብደት፣ የርዝመት፣ የይዞታ፣ የጉልበት፣ የጊዜ፣ የሙቀት ልክ ወይም የሌሎች ድርጅቱ የሚወስናቸው መጠኖች መሥፈሪያ መሣሪያ ነው፡፡
4. "ማመሳከሪያ መደበኛ መሣሪያዎች" ማለት ድርጅቱ የሚኖሩትና የሚጠብቃቸው መደበኛ መሥፈሪያዎች ወይም የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ናቸው፡፡

---

[124] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 22/9/ መሰረት "የስነ ልክ ስርዓት ይዘረጋል" ተብሎ ስልጣኑ ለንግድ ሚኒስቴር የተሰጠው በመሆኑ "ድርጅት" የሚለዉ "ንግድ ሚኒስቴር" በሚል ይነበብ፡፡

[125] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 22/9/ መሰረት "የስነ ልክ ስርዓት ይዘረጋል" ተብሎ ስልጣኑ ለንግድ ሚኒስቴር የተሰጠው በመሆኑ "ሚኒስቴሩ ለኢንስፔክቴሩ ስልጣን ይሰጣል" በሚል ይነበብ፡፡

5. “የመቆጣጠሪያ መደበኛ መሣሪያዎች” ማለት ለመገበያያ የሚያገለግሉትን የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ትክክለኛነት ለመመርመርና ለማረጋገጥ ድርጅቱ የሚኖሩትና እንስፔክተሮች የሚጠቀሙባቸው መደበኛ የመሥፈሪ መሣሪያዎች ናቸው፡፡
6. “የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ሻጭ” ማለት ሥራው አድርጎ ትርፍ ለማግኘት የመሥፈሪያ መሣሪያዎችን ለተጠቃሚዎች የሚሸጥ ወይም በሌላ አኳኋን የሚያስተላልፍ ማናቸውም ሰው ነው፡፡
7. “ተጠቃሚ” ማለት በንግድ ሥራ ላይ በመሥፈሪያ መሣሪያ የሚጠቀም ወይም ለዚሁ ጉዳይ የሚያገለግል የመሥፈሪያ መሣሪያ በቁጥጥሩ ሥር ያለው ማናቸውም ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ለግል ቤት አገልግሎት ጉዳይ በመሥፈሪያ መሣሪያ የሚጠቀመውን ሰው አይጨምርም፡፡
8. “ምርመራ” ማለት ማናቸውም የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ትክክለኛነታቸውና ሌሎችም ግዴታዎች ሁሉ ከተገቢዎቹ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር ለመስማማታቸው በእንስፔክተር የሚመረመርበት ሥርዓት ነው፡፡
9. “ማረጋገጥ” ማለት እንስፔክተር ማናቸውንም የመሥፈሪያ መሣሪያ መርምሮ ትክክለኛና ከተገቢዎች የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር የሚስማማ ሆኖ ካገኘው በኋላ በመሥፈሪያው መሣሪያ ላይ የደረጃዎች ማኅተምን የሚያትምበት ሥርዓት ነው፡፡

5. ***የመጀመሪያ ምርመራና ማረጋገጫ***

የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ሠሪ፣ አስመጪ ወይም ሻጭ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 11 እና 12 በተመለከተው መሠረት ማናቸውም የመሥፈሪያ መሣሪያ በእንስፔክተር ተመርምሮ ካልተረጋገጠ በስተቀር የተባለውን የመሥፈሪያ መሣሪያ ለማናቸውም ተጠቃሚ መሸጥ ወይም በማናቸውም አኳኋን ማስተላለፍ አይችልም፡፡

6. ***በመሥፈሪያ መሣሪያዎች የሚነግዱ ሰዎች ግዴታ***

1. ማናቸውም የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ሠሪ፣ አስመጪ ወይም ሻጭ፣ የሸጣቸውን ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፋቸውን የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ዝርዝር ሁሉ መዝገቦ መያዝ አለበት፡፡
2. ማናቸውም የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ሠሪ፣ አስመጪ ወይም ሻጭ፣ መስከረም፣ ታኅሣሥ፣ ሚያዝያና ሰኔ በገባ በሰባት ቀን ውስጥ ባለፉት ሦስት ወሮች በእጁ

የነበሩትን የሸጣቸውን ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፋቸውን የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ሁሉ የሚያስረዳ መግለጫ ለድርጅቱ ማቅረብ አለበት፡፡

7. **የምርመራ ማስታወቂያ**

1. ድርጅቱ አስፈላጊ መስሎ እንደታየው ተጠቃሚዎች የመሥፈሪያ መሣሪያዎቻቸውን የሚያስመረምሩበትንና ማረጋገጫ የሚያገኙበትን ቀበሌ ወይም ቀበሌዎች እንዲሁም የምርመራውንና የማረጋገጡን ሥራ ለማከናወን እንስፔክተር የሚገኝባቸውን ቀኖችና ሥፍራዎች በመግለጽ በብዛት በሚሰራጭ ጋዜጣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ማስታወቂያ ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚወጣው ማስታወቂያ ድርጅቱ የሚያስታውቀው ጊዜ ከማለፉ በፊት በተወሰነው ቀበሌ ወይም ቀበሌዎች የሚገኝ ተጠቃሚ ሁሉ በእጁ የሚገኙትን የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ብዛትና ዓይነት በመግለጽ የመሥፈሪያ መሣሪያዎቹ እንዲመረመሩለትና እንዲረጋገጡለት ለእንስፔክተር ማመልከት አለበት፡፡

8. **የመሥፈሪያ መሣሪያዎችን ያላስመረመሩ ተጠቃሚዎች**

1. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ድርጅቱ የወሰነው ጊዜ ካለፈ በኋላ እንስፔክተር ማናቸውም ያልተረጋገጠ የመሥፈሪያ መሣሪያ በተወሰነው ቀበሌ ወይም ቀበሌዎች ውስጥ ለንግድ ሥራ ሲያገለግል ያገኘ እንደሆነ በዚህ ደንብ መሠረት እስኪረጋገጥ ድረስ በመሥፈሪያ መሣሪያው እንዳይሠራበት ይከለክላል፡፡ እንስፔክተሩም ጉዳዩን ለድርጅቱ ያስታውቃል፤ ድርጅቱም በተጠቃሚው ላይ ክስ እንዲቀርብበት ማዘዝ ይችላል፡፡
2. የንግድ ሥራ በሚከናወንበት ማናቸውም ቀበሌ በእንስፔክተር የተገኘ ማናቸውም የመሥፈሪያ መሣሪያ ለተባለው የንግድ ሥራ አገልግሎት የሚውል ሆኖ ይቆጠራል፡፡

9. **የተጠቃሚዎች ግዴታ**

1. የመሥፈሪያ መሣሪያ ለምርመራ የሚያቀርብ ማናቸውም ተጠቃሚ፤
   ሀ) የመሥፈሪያ መሣሪያውን በንጹሕ ሁኔታ ማዘጋጀት፤
   ለ) እንስፔክተሩ የመሥፈሪያ መሣሪያውን ልዩ ልዩ ክፍሎች መመርመር እንዲችል የመሥፈሪያ መሣሪያውን በሚገባ ማዘጋጀት፤ እና

ሐ) የመሥፈሪያ መሣሪያውን በመመርመር ረገድ መደረግ የሚገባውን ማናቸውንም ተግባር በፍጥነትና በሚገባ ለማከናወን እንዲቻል በቂ ሠራተኛ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ማናቸውም የመሥፈሪያ መሣሪያ ከተመረመረና ከተረጋገጠ በኋላ ትክክለኛነቱን የሚያፋልስ ጉድለት በማናቸውም ጊዜ የደረሰበት እንደሆነ የመሥፈሪያ መሣሪያው እንዲታደስ፣ እንዲመረመርና እንደገና እንዲረጋገጥ የተባለው የመሥፈሪያ መሣሪያ ተጠቃሚ ሁኔታውን ለእንስፔክተር ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት፡፡

10.**የመመርመሪያ መደበኛ መሣሪያዎች**

1. እንስፔክተር የመሥፈሪያ መሣሪያዎችን በሚመረምርበት ጊዜ ሁሉ በመቆጣጠሪያ መደበኛ መሣሪያዎች መጠቀም አለበት፡፡
2. ማናቸውም ተጠቃሚ በመቆጣጠሪያ መደበኛ መሣሪያዎች ተጠራጥሮ ክርክር ቢያነሣ የማመሳከሪያ መደበኛ መሣሪያዎች የመጨረሻ ማስረጃ ይሆናሉ፡፡
3. ድርጅቱ የመቆጣጠሪያ መደበኛ መሣሪያዎችን ሁሉ ከማመሳከሪያ መደበኛ መሣሪያዎች ጋር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በማነጻጸር እንዲረጋገጡ ያደርጋል፡፡

11.**የምርመራ ውጤቶች**

1. የመሥፈሪያ መሣሪያ ተመርምሮ ትክክለኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንስፔክተሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 በተመለከተው መሠረት ይፈጽማል፡፡
2. የመሥፈሪያ መሣሪያ ተመርምሮ ትክክለኛ ሳይሆን ቢገኝ የመሥፈሪያ መሣሪያውን ተጠቃሚ ጉድለቱን እንስፔክተሩ በሚወስነው ተገቢ ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክልና እንደ አስፈላጊነቱ የመሥፈሪያ መሣሪያውን በማሸግ ወይም ትክክለኛ አለመሆኑን ለመግለጽ በመሥፈሪያ መሣሪያ ላይ በማተም ወይም በላዩ ላይ የማይሠራበት የሚል ማስጠንቀቂያ በመለጠፍ የተባለው ትክክለኛ ያልሆነ የመሥፈሪያ መሣሪያ እንዳይሠራበት ያደርጋል፡፡ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ ጉድለቱ ያልተስተካከለ እንደሆነና እንስፔክተሩ ትክክለኛ ያልሆነው የመሥፈሪያ መሣሪያ የንግድ ሥራ ሲሠራበት ያገኘ እንደሆነ ትክክለኛ ያልሆነውን የመሥፈሪያ መሣሪያ ይይዝና ይህንኑ ሁኔታ ለድርጅቱ ያስታውቃል፡፡

3. ትክክለኛ ሆኖ ያልተገኘና እንስፔክተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ምልክት ያደረገበት የመሥሪያ መሣሪያ ከተስተካከለ በኋላ በእንስፔክተሩ ተመርምሮ ትክክለኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንስፔክተሩ በተባለው የመሥፈሪያ መሣሪያ ላይ የተደረገውን እሽግ፣ ማኅተም ወይም ማስጠንቀቂያ ያነሳና በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 መሠረት የመሥፈሪያ መሣሪያውን ያረጋግጣል፡፡

12.<u>የመሥፈሪያ መሣሪያዎች መረጋገጥ</u>

1. እንስፔክተሩ የመረመራቸውንና ያረጋገጣቸውን የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ተጠቃሚዎች ስምና አድራሻ፣ ምርመራና ማረጋገጫ የተከናወነበትን ቀንና እንዲሁም የተመረመሩትን የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት የሚመዘግብበት የምርመራና የማረጋገጫ መዝገብ ይይዝና ስለእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚያሰፍረውን ማስረጃ ሁሉ በፊርማው ያረጋግጣል፡፡
2. እንስፔክተሩ፤
   ሀ) የመሥፈሪያው መሣሪያ ተጠቃሚ በዚህ ደንብ በሠንጠረዥ (1) የተወሰነውን ተገቢ ያገልግሎት ዋጋ የከፈለ መሆኑን፤ እና
   ለ) የመሥፈሪያው መሣሪያ ድርጅቱ ካወጣቸው ከተገቢዎቹ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር የሚስማማ መሆኑን ሲረዳ፤

ድርጅቱ ያወጣውን የደረጃዎች ማኅተም በመሥፈሪያ መሣሪያው በተገቢ ሥፍራ ላይ በማተም የተባለውን የመሥፈሪያ መሣሪያ ያረጋግጣል፡፡

3. በተጨማሪ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የዓመተ ምሕረቱን የመጨረሻ ሁለት አኃዞች በክብ ውስጥ አድርጎ በመሥፈሪያ መሣሪያው ላይ በማመልከት የመሥፈሪያ መሣሪያው የተረጋገጠበት ዓመተ ምሕረት መገለጽ አለበት፡፡

13.<u>የመሥፈሪያ መሣሪያዎች እንደገና መረጋገጥ</u>

1. ድርጅቱ የተረጋገጡት የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ሁሉ እንደ ዓይነታቸውና እንደየአገልግሎታቸው መጠን ከዓመት ባላነሰና ከሶስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አንድ ጊዜ እንዲመረመሩና እንደገና እንዲረጋገጡ ያደርጋል፡፡
2. ድርጅቱ የመሥፈሪያ መሣሪያዎች በንግድ ሥራ ወደሚያገለግሉበት ሥፍራ በማናቸውም ጊዜ በድንገት እንስፔክተር ለመላክ ይችላል፡፡

3. የመሥፈሪያ መሣሪያ እንደገና በሚመረመርበት ጊዜ ትክክለኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንስፔክተሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን ከፈጸመ በኋላ የመሥፈሪያ መሣሪያውን እንደገና ያረጋግጣል፡፡
4. የመሥፈሪያ መሣሪያ እንደገና በሚመረመርበት ጊዜ ትክክለኛ ሳይሆን የተገኘ እንደሆነ እንስፔክተሩ ከዚህ ቀደም የተደረጉትን የማረጋገጫ ማኅተሞች ሁሉ ከመሥፈሪያ መሣሪያው ላይ ያነሳና በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት አስፈላጊውን ይፈጽማል፡፡

14.<u>የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

የመሥፈሪያ መሣሪያ ከተረጋገጠ በኋላ የመሥፈሪያ መሣሪያው ተጠቃሚ ሲጠይቅ እንስፔክተሩ በዚህ ደንብ በሠንጠረዥ 2 በተወሰነው ቅጽ ለተጠቃሚው የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡

15.<u>የአገለግሎት ዋጋ</u>

1. ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 መሠረት የመሥፈሪያ መሣሪያ መጀመሪያ በሚረጋገጥበት ጊዜ የመሥፈሪያ መሣሪያውን ሠሪ፣ አስመጪ ወይም ሻጭ፤ እና

   ለ) ለንግድ አገልግሎት የሚውል የመሥፈሪያ መሣሪያ በሚመረመርበትና በሚረጋገጥበት ጊዜ ተጠቃሚው፤

   ለእያንዳንዱ የተረጋገጠ የመሥፈሪያ መሣሪያ በዚህ ደንብ በሠንጠረዥ 1 የተወሰነውን የአገለግሎት ዋጋ መክፈል አለበት፡፡
2. ስለተከፈለውም የአገልግሎት ዋጋ ደንበኛ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡

16.<u>ቅጣት</u>

የዚህን ደንብ ውሳኔዎች የተላለፈ በአዋጁ አንቀጽ 12 መሠረት ይቀጣል፡፡

17.<u>ደንቡ የሚጸናበትን ቀን</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 30 ቀን 1965 ዓ.ም**

**ከተማ ይፍሩ**

**የንግድ እንዱስትሪና የቱሪዝም ሚንሰትር**

## ሠንጠረዥ 1

## የመሥፈሪያ መሣሪያዎችን ለማስመርመርና ለማረጋገጥ የሚከፈለውን ልክ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

1. **የርዝመት መሥፈሪያዎች**

ሀ/ ተራ መሥፈሪያዎች — የኢ.ት.$

| | |
|---|---|
| ለእያንዳንዱ መሥፈሪያ እስከ 2 ሜትር | 0.25 |
| ከ2 ሜትር በላይ እስከ 5 ሜትር | 0.50 |
| ከ5 ሜትር በላይ እስከ 10 ሜትር | 1.00 |
| ከ10 ሜትር በላይ እስከ 50 ሜትር | 3.00 |
| ከ50 ሜትር በላይ | 5.00 |

ለ/ የአውቶማቲክ መሥፈሪያዎች፣

| | |
|---|---|
| ለእያንዳንዱ መሥፈሪያ መሣሪያ | 50.00 |

2. **ክብደት ማነጻጸሪያዎች**

ሀ/ ተራ የንግድ ክብደት ማነጻጸሪያዎች

ለእያንዳንዱ ክብደት ማነጻጸሪያ፡-

| | |
|---|---|
| ከ1 ግራም እስከ 1 ኪሎ ግራም | 0.25 |
| ከ1 ኪሎ ግራም በላይ እስከ 10 ኪሎ ግራም | 0.50 |
| ከ10 ኪሎ ግራም በላይ እስከ 50 ኪሎ ግራም | 2.00 |
| ከ50 ኪሎ ግራም በላይ | 3.00 |

ለ/ ረቂቅና ሜትሪክ ካራት ክብደት ማነጻጸሪያዎች

| | |
|---|---|
| ለእያንዳንዱ የክብደት ማነጻጸሪያ | 1.00 |

3. **ሚዛኖች፣**

ሀ/ ከአውቶማቲክ መመዘኛ መኪናዎችና ባለማቋረጥ በመሥራት ከሚጀምሩ መመዘኛ መኪናዎች በስተቀር ሌሎች ሚዛኖች እንዲሁም በሙሉ ወይም በከፊል በራሳቸው አማካይነት የሚያመለክቱ ሚዛኖች፣ — የኢ.ት.$

| | |
|---|---|
| እስከ 10 ኪሎ ግራም | 6.00 |
| ከ10 ኪሎ ግራም በላይ እስከ 50 ኪሎ ግራም | 8.00 |
| ከ50 ኪሎ ግራም በላይ እስከ 1 ቶን | 10.00 |

ለ/ ለከፍተኛ ንግድና የእንዱስትሪ ሥራ የሚያገለግሉ፣

| | |
|---|---|
| ከ1 ቶን በላይ እስከ 5 ቶን | 20.00 |
| ከ5 ቶን በላይ እስከ 10 ቶን | 50.00 |
| ከ10 ቶን በላይ እስከ 50 ቶን | 70.00 |
| ከ50 ቶን በላይ | 100.00 |

ሐ/ አውቶማቴክ ሚዛኖች፣

| | |
|---|---|
| እስከ 5 ኪሎ ግራም | 10.00 |
| ከ5 ኪሎ ግራም በላይ እስከ 50 ኪሎ ግራም | 20.00 |
| ከ50 ኪሎ ግራም በላይ እስከ 1 ቶን | 30.00 |
| ከ1 ቶን በላይ እስከ 5 ቶን | 50.00 |
| ከ5 ቶን በላይ እስከ 10 ቶን | 70.00 |
| ከ10 ቶን በላይ | 100.00 |

መ/ ባለማቋረጥ በመሥራት የሚደምሩ መመዘኛ መኪናዎች፣

ማናቸውም ይዞታ ላለው ለእያንዳንዱ መመዘኛ መኪና 100.00

ሠ/ ማናቸውም ሚዛን በተጨማሪ ዋጋን በገንዘብ አስልቶ እንዲያመለክት የተሠራ ከሆነ፣ ዋጋ አመልካቹን ክፍል ለመመርመርና ለማረጋገጥ የኢ.ት/$ 2.00 የአገልግሎት ዋጋ መክፈል አለበት፡፡

4. ***የፈሳሾች መሥፈሪያ መሣሪያዎች***

***ሀ/ የይዞታ መሥፈሪያዎች፣***

1. ***ተራ የንግድ የይዞታ መሥፈሪያ***

ለእያንዳንዱ መሥፈሪያ፡-

| | |
|---|---|
| እስከ 20 ሊትር | 3.00 |
| ከ2 ሊትር በላይ እስከ 100 ሊትር | 5.00 |
| ከ100 ሊትር በላይ እስከ 500 ሊትር | 10.00 |
| ከ500 ሊትር በላይ እስከ 1000 ሺህ ሊትር | 20.00 |

ከ1000 ሊትር በላይ ለሆነ፣ ለተጨማሪው
በ1000 ሊትር የኢ.ት. 5 ብር ሒሳብ መሠረት፡፡

2. ***ረቂቅ የይዞታ መሥፈሪያዎች፣***

ማናቸውም ይዞታ ያለው፣ እያንዳንዱ 5.00

3. **ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) የፈሳሽ ማጓጓዣዎች**

ለእያንዳንዱ 100.00

ለ/ **የፈሳሽ ሜትሮች**

ለእያንዳንዱ መሣሪያ፡-

1. የነዳጅ ፓምፖች 25.00
2. ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ከፍተኛ የፈሳሽ ሜትሮች 50.00
3. ለእንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ የፈሳሽ ሜትሮች 100.00

**ሠንጠረዥ 2**

**የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቅጽ**

**በኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ድርጅት**

**የሚዛንና መሥፈሪያ መቆጣጠሪያ ክፍል**

**የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**

ስም፡ -----------------------------------------------------------------------

አድራሻ፡ -------------------------------------------------------------------

የፖስታ ሳጥን ቁጥር፡ --------------------- የቴሌፎን ቁ/ --------------

ሕጋዊ አቋም፡ -------------------------------------------------------------

የንግድ ሥራ፡ -------------------------------------------------------------

የአገር ውስጥ ወይም የውጪ አገር ንግድ ፈቃድ ቁጥር ወይም የንግድ መዝገብ ቁጥር

ቁጥሮች፡ ------------------------------------------------------------------

ለንግድ ሥራ የሚጠቀምባቸው ቀጥሎ የተዘረዘሩት የመሥፈሪያ መሣሪያዎች፡ ---------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

በቁጥር 208/1955 ዓ.ም በወጣው የሚዛንና መሥፈሪያ አዋጅና እንዲሁም በቁጥር 431/1965 ዓ.ም በወጣው የሚዛንና መሥፈሪያ ደንብ መሠረት ተመርምረው ትክክለኛ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

## የፍትህ ሚኒስቴር

ቀን -------------------------- ቀን --------------------------

ፊርማ ---------------------- ፊርማ --------------------------

(እንስፔክተር) (ስለ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ)

(ኦፊሴል ማኅተም)

## የደንብ ቁጥር 13/1982

## የደረጃዎች ማኅተም እና የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

**"ኢትዮጵያ ትቅደም"**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የመስተዳድሩን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 8/1980 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የደረጃዎች ማኅተም እና የአገልግሎት ዋጋ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 13/1982" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፣

   1. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን ነው፣[126]
   2. "ደረጃ" ማለት የዕቃዎችን፣ የአሠራሮችንና የአዘገጃጀቶችን ጥራት፣ ደኅንነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የዕቃዎችን የዓይነት ብዛትና የአመራረት ዘዴ ወይም አሠራሮችንና አዘገጃጀቶችን ሥርዓት ለማስያዝ የሚያገለግል መመዘኛ ነው፣[127]
   3. "የኢትዮጲያ ደረጃዎች" ማለት ማናቸውም ባለሥልጣኑ አጽድቆ የሚያወጣቸው ደረጃዎች ናቸው፣
   4. "ዕቃዎች" ምርቶችን፣ ሸቀጦችንና መሣሪያዎችን ይጨምራል፣
   5. "ነጋዴ" ማለት አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ፈቃድ ተሰጥቶት ወይም በሕግ ተቋቁሞ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ሲሆን የኅብረት ሥራ ማኅበራትንም ይጨምራል፣
   6. "አምራች" ማለት አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ፈቃድ ተሰጥቶት ወይም በሕግ ተቋቁሞ በማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ሲሆን የኅብረት ሥራ ማኅበራትንም ይጨምራል፡፡

---

[126] በ17/13 (2003) ደ. 193 መሠረት ስራዉ የሚከናወነዉ በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ በመሆኑ "ኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ" በሚል ይነበብ፡፡

[127] በ17/13 (2003) ደ. 193 አንቀፅ 2 (3) የተሰጠዉን ትርጓሜ ተመልከት፡፡

7. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
8. “ማኅተም” ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተመለከተው የደረጃዎች ማኅተም ነው፣
9. “የማኅተሙ ተጠቃሚ” ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው አምራች ወይም ነጋዴ ነው፣
10. “ምርመራ” ማለት ዕቃዎች ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ የሚያካሂደው ምርመራና የሚያደርገው ፍተሻ ነው፣
11. “የመሸጫ ዋጋ” ማለት የማኅተሙ ተጠቃሚ ዕቃዎቹን የሚሸጥበት እንደነገሩ ሁኔታ የጅምላ ወይም የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ነው፣
12. “ፈቃድ” ማለት በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም በዚህ ደንብ መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ነው፡፡

3. <u>**የደረጃዎች ማኅተም**</u>

በባለሥልጣኑ ውሳኔ በማኅተሙ ዙሪያ ተገቢው ሐተታ ሊቀረጽበት የሚችል ይህ የደረጃዎች ማኅተም  የባለሥልጣኑ የግል ንብረት ስለሆነ በዚህ ደንብ መሠረት ከባለሥልጣኑ በቅድሚያ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር በማናቸውም ዕቃ ረገድ በማኅተሙ መጠቀም አይቻልም፡፡

4. <u>**በደረጃዎች ማኅተም መጠቀም ግዴታ ስለመሆኑ**</u>

ባለሥልጣኑ ልዩ ሁኔታ መኖሩን አረጋግጦ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ተፈጻሚነታቸው ለጊዜው እንዲታለፍ ካልፈቀደ በስተቀር፣ ማንኛውም አምራች ወይም ነጋዴ የኢትዮጵያ ደረጃዎች በወጣላቸው ዕቃዎች ላይ በዚህ ደንብ መሠረት በደረጃዎች ማኅተም የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

5. <u>**በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም ስለሚቀርብ ማመልከቻ**</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 መሠረት በደረጃዎች ማኅተም የመጠቀም ግዴታ ያለበት ማንኛውም አምራች ወይም ነጋዴ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ 1 የተመለከቱትንና ባለሥልጣኑ እንዳስፈላጊነቱ የሚወስናቸውን ተጨማሪ ዝርዝሮች የያዘ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ማመልከቻው ሲቀርብ ብር 10 (አስር ብር) ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት፡፡

6. **<u>በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም ስለሚሰጥ ፈቃድ</u>**
   1. የአመልካቹ ዕቃ ከተገቢዎቹ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ በዕቃው ላይ ተቀዳሚ ምርመራ ያደርጋል፡፡
   2. አመልካቹ በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈለጉትን ሁኔታዎች ማሟላቱንና ዕቃው ከተገቢው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር መስማማቱን ባለሥልጣኑ ሲያምንበት በደረጃዎች ማኅተም እንዲጠቀም ይፈቅድለታል፡፡
   3. ባለሥልጣኑ የቀረበለትን ማመልከቻ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት ገልጾ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አመልካቹን በጽሑፍ ያሳውቀዋል፤ በዕቃው ላይ የተደረገው ተቀዳሚ ምርመራ ውጤትም ለአመልካቹ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡
7. **<u>የደረጃዎች ማኅተም አጠቃቀም</u>**
   1. የማኅተሙ ተጠቃሚ በፈቃዱ ውስጥ በተወሰነው ዕቃ ላይ በማኅተሙ መጠቀም አለበት፡፡ እንዲሁም ስለዕቃው በሚያወጣው የንግድ ማስታወቂያ ላይ በማኅተሙ መጠቀም ይችላል፡፡
   2. የማኅተሙ ተጠቃሚ በዕቃው ላይ ማኅተሙን የሚያደርገው ባለሥልጣኑ በፈቃዱ ውስጥ በወሰነው አኳኋን ይሆናል፡፡
   3. ባለሥልጣኑ በዕቃው ላይ ከማኅተሙ ሌላ አስፈላጊ መስለው የታዩትን ተጨማሪ መግለጫዎች እንዲያመለክት የማኅተሙን ተጠቃሚ ሊያስገድደው ይችላል፡፡
8. **<u>የማኅተሙ ተጠቃሚ ግዴታዎች</u>**

   የማኅተሙ ተጠቃሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፣
   1. ለምርመራ የሚፈለገውን ናሙና ለባለሥልጣኑ የመስጠት፣
   2. የሚያመርታቸው ዕቃዎች ከተገቢዎቹ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር መስማማታቸውን ለማረጋገጥ በቂ ውስጣዊ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የማቋቋም፣
   3. ዕቃው ከተገቢው የኢትዮጵያ ደረጃ ጋር ያለማቋረጥ መስማማቱን የማረጋገጥ፣
   4. ዕቃው ከተገቢው የኢትዮጵያ ደረጃ ጋር መስማማቱን ያቋረጠ ወይም በዕቃው ላይ ማናቸውም ለውጥ የተደረገ እንደሆነ ይህንኑ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ የማሳወቅ፣
   5. በዚህ ደንብ መሠረት የሚወስነውን የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ ለባለሥልጣኑ የመክፈል፣

6. ዕቃው ከምርመራ በኋላ ተገቢውን የኢትዮጵያ ደረጃ ያልጠበቀ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ለምርመራ ያወጣውን ወጭ የመክፈል፣
7. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና ባለሥልጣኑ በፈቃዱ ውስጥ የወሰናቸውን ግዴታዎች የማክበር፣

9. <u>በየጊዜው ስለሚደረግ ምርመራ</u>

1. የማኀተሙ ተጠቃሚ ዕቃ ምንጊዜም ከተገቢው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ በየጊዜው ምርመራ ያደርጋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚያደርገው ምርመራ ከማኀተሙ ተጠቃሚ በተወሰደ ወይም ከገበያ በተገዛ የዕቃው ናሙና ላይ ይሆናል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ከማኀተሙ ተጠቃሚ ዕቃ ላይ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ምርመራ ካላደረገ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10/3/ መሠረት የሚከፈለውን የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ ሊጠይቅ አይችልም፡፡

10. <u>የምርመራና</u>

11.<u>የእትማት አገልግሎት ዋጋ</u>

1. ለማናቸውም ዕቃ የአንዱ የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 3 የተመለከተው ይሆናል፡፡
2. የማኀተሙ ተጠቃሚ ለባለሥልጣኑ ሊከፍል የሚገባው የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ የሚታሰበው በሠንጠረዥ 3 ውስጥ ለአንዱ የተወሰነውን የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ የማኀተሙ ተጠቃሚ በዕቃዎቹ ላይ በተጠቀመው የእትማት መጠን በማባዛት ይሆናል፡፡
3. የማኀተሙ ተጠቃሚ አምራች ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚወሰነው የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ በየሩብ ዓመቱ ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት፡፡
4. የማኀተሙ ተጠቃሚ ነጋዴ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚወሰነው የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ ነጋዴው በዕቃዎቹ ላይ ማኀተሙን በተጠቀመበት ጊዜ ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት፡፡
5. የማኀተሙ ተጠቃሚ የምርመራና የእትማት አገልግሎት ክፍያውን በዚህ አንቀጽ የተወሰነው ጊዜ ካለፈ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ ላዘገየበት ለእያንዳንዱ

ወር የምርመራና የእትማት አገልግሎት ክፍያውን አንድ በመቶ (1%) የሚሆን መቀጫ ይከፍላል፡፡

12. **ስለመዝገብ**

ባለሥልጣኑ ፈቃዶችንና አስፈላጊ መስለው የታዩትን የፈቃዱን ሁኔታዎች የሚመዘግብበት መዝገብ ያቋቁማል፣ መዝገቡም ሕዝብ እንዲመለከተው ክፍት መሆን አለበት፡፡

13. **ስለ ፈቃድ መሰረዝ**

1. የማኅተሙ ተጠቃሚ፣

   ሀ) የሚያመርተው ወይም የሚነግደው ዕቃ ተገቢውን የኢትዮጵያ ደረጃ ያልጠበቀ መሆኑን ባለሥልጣኑ ከምርመራ በኋላ የተረዳ እንደሆነ፣

   ለ) በዚህ ደንብ ወይም በፈቃዱ ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልፈጸመ እንደሆነ፣ ወይም

   ሐ) ሥራውን ያቆመ ወይም ሂሳቡን ያጣራ እንደሆነ፣

   ባለሥልጣኑ በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም የሰጠውን ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

2. ፈቃዱ እንደተሠረዘ የማኅተሙ ተጠቃሚ ለባለሠልጣኑ ሊከፍል የሚገባውን ክፍያ ወዲያው መክፈልና በሚመለከተው ዕቃ ረገድ በማኅተሙ መጠቀሙን ማቆም አለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ የሕዝቡን ጥቅም ለመጠበቅ አስፈላጊ መስሎ በሚታየው በማናቸውም አኳኋን የፈቃዱን መሠረዝ ለሕዝብ ያስታውቃል፡፡

14. **በደረጃዎች ማኅተም ያለመጠቀም ስለሚያስከትለው ውጤት**

1. በዚህ ደንብ መሠረት በደረጃዎች ማኅተም የመጠቀም ግዴታ ያለበት አምራች ወይም ነጋዴ በማኅተሙ ሳይጠቀም ዕቃዎች ሲያመርት ወይም ሲነግድ የተገኘ እንደሆነ ወይም በማኅተሙ ለመጠቀም የተሰጠው ፈቃድ በአንቀጽ 12/1/ሀ/ መሠረት የተሠረዘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የተባለውን ዕቃ ማምረቱን ወይም መነገዱን ወዲያውኑ እንዲያቆም ለማድረግ ይችላል፡፡

2. በዚህ ደንብ መሠረት የደረጃዎች ማኅተም ሊደረግበት የሚገባ ዕቃ የደረጃዎች ማኅተም ሳይኖረው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዳይገባ ወይም ከኢትዮጵያ ግዛት እንዳይወጣ ለመከልከል የጉምሩክ ባለሥልጣኖች በዚህ ደንብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

3. በዚህ ደንብ መሠረት በደረጃዎች ማኅተም መጠቀም ግዴታ የሆነባቸውን ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ለማስመጣት የኢትዮጵያ ብሔራዋ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ሲጠየቅ ፈቃዱን ከመስጠቱ በፊት ዕቃዎቹ ተገቢውን የኢትዮጵያ ደረጃ የሚያሟሉ ለመሆኑ ባለሥልጣኑ ማረጋገጡን የሚገልጽ ሰነድ እንዲቀርብለት የመጠየቅ ሥልጣን በዚህ ደንብ ተሰጥቶታል፡፡

15.<u>የተሻረ ሕግ</u>

የደረጃዎች ማኅተምና የአገልግሎት ዋጋ ደንብ ቁጥር 434/1965 ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል፡፡

16.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥቅምት 30 ቀን 1983 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 30 ቀን 1982 ዓ.ም**

**ኃይሉ ይመኑ**

**የኢሕዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ሠንጠረዥ 1

## በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም የሚቀርብ ማመልከቻ

በደረጃዎች ማኅተምና የአገልግሎት ዋጋ ደንብ ቁጥር 13/1982 መሠረት በኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን የደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

1. የአመልካቹ ስምና አድራሻ ------------------------------------------------------------------
2. ሕጋዊ አቋም ------------------------------------------------------------------------------------
3. የንግድ መዝገብ ቁጥር ----------------------------------------------------------------------------
4. የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ፈቃድ ቁጥር -----------------------------------------------------
5. ፋብሪካው ወይም የንግድ ሥራው የሚገኝበት ሥፍራ ----------------------------------------
6. የደረጃዎች ማኅተም የሚደረግበት ዕቃ ዓይነት መጠንና ጥራት -------------------------
7. አግባብ ያለው የኢትዮጵያ ደረጃ መለያ ቁጥር----------------------------------------------
8. የተገመተው የዓመቱ ጠቅላላ የምርት ወይም የንግድ እንቅስቃሴ ውጤት መጠን -----

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------
9. የዕቃው የመሸጫ ዋጋ ----------------------------------------------------------------------------
10. በዕቃው ላይ የሚደረገው የአምራቹ ልዩ ስም ወይም ምልክት ----------------------------

    -----------------------------------------------------------------------------------------------------

    ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ማስረጃዎች በማምነውና በማውቀው መጠን እውነተኛና የተሟሉ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

----------------------------------- --------------------------

(ቀን) (ፊርማ)

ማኅተም ማዕረግ

## ሠንጠረዥ 2

## በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም የሚሰጥ ፈቃድ

የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን ------- በደረጃዎች ማኅተምና የአገልግሎት ዋጋ ደንብ ቁጥር 13/1982 ድንጋጌዎችና በሚከተሉት ሁኔታዎች መሠረት በደረጃዎች ማኅተም እንዲጠቀምበት ይህን ፈቃድ ሰጥቶታል፡፡

1. ፈቃዱ የሚመለከተው ዕቃ ዓይነት ---------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------

2. የዕቃው መጠንና ጥራት -------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
3. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ዕቃ ከሚከተለው ወይም ከሚከተሉት የኢትዮጵያ ደረጃ ወይም ደረጃዎች ጋር መስማማት አለበት -----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
4. ማኅተሙ በሚከተለው ሥፍራ ላይ እና አኳኋን መደረግ አለበት -----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
5. የሚከተለው የማኅተሙ ተጠቃሚ ልዩ ስም ወይም የንግድ ምልክት ከማኅተሙ ጋር መደረግ አለበት --------------------------------------------------------------------------------
6. ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዕቃ ላይ የሚከተለው ተጨማሪ መግለጫ መደረግ አለበት ----------------------------------------------------------------------------------------------------
7. በዚህ ፈቃድ ባለሥልጣኑ ከሰጠው ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ሊጠቀምበት አይችልም፡፡
8. የማኅተሙ ተጠቃሚ ሊከፍል የሚገባውን የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ ለመተመን ባለሥልጣኑ የሚልክለትን የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ መተመኛ ሰነድ እየሞላ ለባለሥልጣኑ መላክ አለበት፡፡

----------------------------------- --------------------------

(ቀን) (ፊርማ)

ማኅተም ማዕረግ

**ሠንጠረዥ 3**

**የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ**

| የኢትዮጵያ ደረጃ | በደረጃዎች ማኅተም ለመጠቀም | |
|---|---|---|
| አርዕስት የደረጃ መለያ | የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ (የዕቃው የመሸጫ ዋጋ ከመቶ) | |
| የዘይት ፍሬ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ. ለ 1.001 | 0.2 |

| | | |
|---|---|---|
| ጥራጥሬ የባቄላ ወይም የአደንጓሬ አመዳደብ | ኢ.ደ ለ. ለ 1.104 | 0.2 |
| ጥራጥሬ የምስር አመዳደብ | ኢ.ደ ለ. ለ 1.105 | 0.2 |
| ጥራጥሬ የሽምብራ አመዳደብ | ኢ.ደ ለ. ለ 1.106 | 0.2 |
| ጥራጥሬ የአተር አመዳደብ | ኢ.ደ ለ. ለ 1.107 | 0.2 |
| ያልተለፋ ቆዳና ሌጦ ያልተለፋ የቀንድ ከብት ቆዳና የጥጃ ሌጦን በመልክና በግዘፍና መመደብ | ኢ.ደ ለ. ቸ 6.007 | 0.2 |
| ያልተለፋ ቆዳና ሌጦ የበግና የፍየል ሌጦ በመልክ በግዘፍና በመጠን መመደብ | ኢ.ደ ለ. ቸ 6.008 | 0.2 |
| የጐመን ዘር የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ. ነ 1.002 | 0.2 |
| የበቆሎ የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ. ነ 1.003 | 0.2 |
| የሰሊጥ የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ነ 1.004 | 0.2 |
| የለውዝ የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ነ 1.005 | 0.2 |
| የፈረንጅ ሱፍ የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ነ 1.006 | 0.2 |
| የተልባ የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ነ 1.007 | 0.2 |
| የጥጥ ፍሬ የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ነ 1.008 | 0.2 |
| የኑግ የመብል ዘይት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ነ 1.009 | 0.2 |
| የዘይት ፋጉሎ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ነ 3.001 | 0.2 |
| ጥሬ የቡና ፍሬ አመዳደብ | ኢ.ደ. ለ.ከ 1.002 | 0.05 |

## የፍትህ ሚኒስቴር

| አርዕስት የደረጃ መለያ | የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ (የዕቃው የመሸጫ ዋጋ ከመቶ) | |
|---|---|---|
| ኮረት መደበኛ የቤቶን ኮረት | ኢ.ደ መ.ሠ 3.201 | 0.5 |
| የቤቶን ብሎኬት፣ ውስጠ ክፍት የቤቶን ብሎኬትና የወለል መሙያ | ኢ.ደ መ.ሠ 3.301 | 0.5 |
| የቤቶን አሸንዳ፣ የቤቶን የፍሳሽ አሸንዳ | ኢ.ደ መ.ሠ 3.326 | 0.4 |
| የአስቤስቶስ ሲሚንቶ ልሙጥ ሉኮች | ኢ.ደ መ.ሠ 3.501 | 0.4 |
| የአስቤስቶስ ሲሚንቶ የፍሳሽና የቦይ አሸንዳ | ኢ.ደ መ.ሠ 3.551 | 0.4 |
| የሸክላ ጡብ ድፍን የሸክላ ጡብ | ኢ.ደ መ.ሠ 4.001 | 0.5 |
| የሸክላ ጡብ ውስጠ ክፍት የሸክላ ጡብና የወለል መሙያ | ኢ.ደ መ.ሠ 4.026 | 0.5 |
| ፖርትላንድ ሲሚንቶ የጥራት ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ መ.ሠ 5.201 | 0.5 |
| አረብ ብረት ቆርቆሮ ዚንጐ ንክር ልሙጥ አረብ ብረት ቆርቆሮ | ኢ.ደ መ.ሠ 7.001 | 0.8* |
| አረብ ብረት ቆርቆሮ ዚንጐ ንክር ሽንሽን አረብ ብረት ቆርቆሮ | ኢ.ደ መ.ሠ 7.026 | 0.8 |
| ጥብቅ ክብሪት ባለ ሣጥን ክብሪት | ኢ.ደ ሠ.ሠ 4.201 | 0.02 |
| የአረብ ብረት ሽቦ ለምስማር መሥሪያ የሚሆን በቀዝቃዛነቱ የተዠመገገ ልዝብ አረብ ብረት ሽቦ | ኢ.ደ ቀ.ለ 4.031 | 0.5** |
| ምስማር የአረብ ብረት ሽቦ ምስማር | ኢ.ደ ቀ. ለ 4.120 | 0.5 |
| ባለሾክ የአጥር ሽቦ ዚንጐ ንክር ልዝብ አረብ ብረት | ኢ.ደ ቀ. ለ 4.060 | 0.5 |
| ወረቀት ያልተቀፈፈ የወረቀት ክምችት | ኢ.ደ ወ. ለ2.021 | 0.8*** |

| | | |
|---|---|---|
| ወረቀት የተቀፈፈ ወረቀት | ኢ.ደ ወ.ለ 2.030 | 0.8 |
| ወረቀት የደብዳቤ አምቦልክና ማጎደር መጠን፣ | ኢ.ደ ወ.ለ 2.040 | 0.8 |

*ለ “ዚንጐ ንክር ሽንሽን አረብ ብረት ቆርቆሮ” የአገልግሎት ዋጋ ከተከፈለ የተመለከተው የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ አይጸናም፡፡

**ለ “አረብ ብረት ሽቦ ምስማር” የአገልግሎት ዋጋ ከተከፈለ የተመለከተው የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ አይጸናም፡፡

*** “የተቀፈፈ ወረቀት” የአገልግሎት ዋጋ ከተከፈለ፣ የተመለከተው የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ አይጸናም፡፡

| **አርዕስት የደረጃ መለያ** | **የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ (የዕቃው የመሸጫ ዋጋ ከመቶ)** | |
|---|---|---|
| ፋይል ማድረጊያ መሣሪያ የክላሴርና የአቃፊ መጠን | ኢ.ደ ወ. መ1.050 | 0.8 |
| ሙዝ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 2.601 | 0.2 |
| ካሮት ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 6.002 | 0.2 |
| ድንች ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 6.003 | 0.2 |
| ቲማቲም ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 6.200 | 0.2 |
| አደንጓሬ እሸት (ሎሩቃ) ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 6.300 | 0.2 |
| አተር እሸት (ሎሩቃ) ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 6.301 | 0.2 |
| አናናስ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 2.602 | 0.2 |
| ወይን ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 2.700 | 0.2 |
| ሰላጣ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 6.100 | 0.2 |
| ጣሳ የታሸገ ፍራፍሬና ቅጠላ ቅጠል፣ በሙቀት የተጠበቀ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.በ 5.001 | 0.2 |
| ትኩስ አፕል ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 2.001 | 0.2 |
| ትኩስ አፕሪኮት (የቻይና ፍሬ) ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ለ 2.100 | 0.2 |

| | | |
|---|---|---|
| ትኩስ ኮክ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 2.101 | 0.2 |
| ብርቱካን ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 2.200 | 0.2 |
| ፖራዲስ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 2.201 | 0.2 |
| መንደሪን ታንጀሪን ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 2.202 | 0.2 |
| ሎሚ (የፈረንጅ) ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 2.203 | 0.2 |
| ሎሚ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 2.204 | 0.2 |
| እንጆሪ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 2.606 | 0.2 |
| ቀይ ሽንኩርት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 6.008 | 0.2 |
| **አርዕስት የደረጃ መለያ** | **የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ (የዕቃው የመሸጫ ዋጋ ከመቶ)** | |
| ባሮ ሽንኩርት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 6.009 | 0.2 |
| ነጭ ሽንኩርት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 6.010 | 0.2 |
| ስሪት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 6.101 | 0.2 |
| ካያር ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 6.202 | 0.2 |
| የፈረንጅ ቃሪያ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ለ.ለ** 6.203 | 0.2 |
| አሞንየም ሰልፌት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.001 | 0.2 |
| አሞኒየም ሰልፌት ናይትሬት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.002 | 0.2 |
| ዩሪያ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.003 | 0.2 |
| ሱፐር ፎስፌት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.004 | 0.2 |
| ትሪፕል ሱፐርፎስፌት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.005 | 0.2 |
| ፖታሲየም ክሎራይድ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.006 | 0.2 |
| ፖታሲየም ሰልፌት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.007 | 0.2 |
| ዳይአሞኒየም ፎስፌት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.008 | 0.2 |
| አሞኒየም ፎስፌት ሰልፌት ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.009 | 0.2 |
| ውሑድ የመሬት ማዳበሪያዎች ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.010 | 0.2 |
| የአጥንት መኖ፣ ጥሬ የሆነ ዝርዝር ሁኔታ | **ኢ.ደ ሠ.ለ** 1.011 | 0.2 |

| | | |
|---|---|---|
| ቢራ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 3.001 | 0.2 |
| ወይን ጠጅ (ቪኖ) ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 3.100 | 0.4 |
| ቬርሙጥ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 3.102 | 0.4 |
| በካርቦን ዳይኦክሳይድ የተጠበቀ ለስላሳ መጠጥ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 4.001 | 0.3 |
| የፍራፍሬ (ሀብሀብ፣ ሎሚ፣ ትርንጎ፣ መንደሪን፣ ብርቱካን) ጭማቂ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 4.002 | 0.3 |
| **አርዕስት የደረጃ መለያ** | **የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ (የዕቃው የመሸጫ ዋጋ ከመቶ)** | |
| የፍራፍሬ መጠጥ ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 4.003 | 0.3 |
| በሚገባ ተጠብቆ የተሰናዳ ያልተበረዘ የብርቱካን ጥሉል ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 4.004 | 0.3 |
| ተፈጥሯዊ የፍራፍሬ ጥሉል ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.አ 4.005 | 0.3 |
| የመብል ጨው ዝርዝር ሁኔታ | ኢ.ደ ለ.ኸ 2.001 | 0.2 |
| የጥጥ ጭረት ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ተ.ለ 1.001 | 0.3**** |
| የጥጥ ፈትል ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ተ.ቀ 0.001 | 0.3 |
| የጥጥ መስፊያ ክር ጠቅላላ ተፈላጊ ነገሮች | ኢ.ደ ተ.በ 0.001 | 0.3 |
| ፖርት ላንድ ፖዞላና ሲሚንቶ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ መ.ሠ 5.202 | 0.5 |
| ደረጃ የወጣለት አሸዋ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ መ.ሠ 2.301 | 0.5 |
| የአስቤስቶስ ሲሚንቶ ሽንሽን ሉክ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ መ.ሠ 3.526 | 0.4 |
| አንኳር ኖራ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ መ.ሠ 5.002 | 0.5 |
| ደቃቅ ኖራ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ መ.ሠ 5.003 | 0.5 |
| ሳሙና ማጠቢያ (የልብስ) ሳሙናዎች ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ረ 1.001 | 0.2 |

| | | |
|---|---|---|
| ሳሙና መጸዳጃ (የገላ) ሳሙናዎች ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ሪ 1.010 | 0.2 |
| ሳሙና ካርቦላዊ ሳሙና ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ሪ 1.016 | 0.2 |
| የዱቄት ማጽጃ የቤት ዕቃ ማጽጃዎች ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ሪ 1.051 | 0.2 |
| ፒቪሲ የአትክልት ማጠጫ ጐማ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.በ 6.061 | 0.5 |

****ለ "ጥጥ ፈትል" የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ ከተከፈለ የተመለከተው የአንዱ የምርመራና የእትማት አገልግሎት ዋጋ አይጸናም፡፡

| አርዕስት የደረጃ መለያ | | የአንዱ የምርመራና እትማት አገልግሎት ዋጋ (የዕቃው የመሸጫ ዋጋ ከመቶ) |
|---|---|---|
| ባለ ዝቅተኛ ዝፈት ፖሊኤትሊን ፊልም ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.በ 2.001 | 0.5 |
| የተለፋ ቆዳ ርጥብ-ሰማያዊ ክሮም ያለው የተለፋ ቆዳ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.በ 4.001 | 0.2 |
| የተለፋ ቆዳ ላዩ ክሮም የሆነ የተለፋ ቆዳ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ከ 4.002 | 0.2 |
| የተለፋ ቆዳ ርጥብ-ሰማያዊ ላዩ ክሮም የሆነ ፈር ያለው የተለፋ ቆዳ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ከ 4.003 | 0.2 |
| የተለፋ ቆዳ ለጫማ የሚሆን የተለፋ ቆዳ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ከ 4.004 | 0.2 |
| የተለፋ ቆዳ የጫማ ሶል የተለፋ ቆዳ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ከ 4.005 | 0.2 |
| የተለፋ ቆዳ ለገበር የሚሆን የተለፋ ቆዳ ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ከ 4.007 | 0.2 |

## የፍትህ ሚኒስቴር

| | | | |
|---|---|---|---|
| የምግብና የመጠጥ ውጤቶች መያዣ ጠርሙሶች ካርቦንዳይኦክሳይድ የታመቁ መጠጦች መያዣ ጠርሙሶች ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ዘ | 0.004 | 0.2 |
| የምግብና የመጠጥ ውጤቶች መያዣ ጠርሙሶች የቢራ ጠርሙሶች ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ዘ | 0.005 | 0.2 |
| የምግብና የመጠጥ ውጤቶች መያዣ ጠርሙሶች የወይንጠጅ ጠርሙሶች ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች | ኢ.ደ ሠ.ዘ | 0.006 | 0.2 |
| ኢንዱስትሪያዊ መድኖች በዓይን ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነፀብራቆችን መከላከያዎች | ኢ.ደ ደ.�septies | 2.002 | 0.5 |
| ኢንዱስትሪያዊ መድኖች የዓይን ደኅንነት መጠበቂያ ቤዛዎች | ኢ.ደ ደ.�septies | 2.004 | 0.5 |

## የፍትህ ሚኒስቴር

### ደንብ ቁጥር 476/13

### የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ም/ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 1097/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

   1. "አክሬዲቴሽን"፣ "የተስማሚነት ምዘና" "የተስማሚነት ምዘና አካል" "የክትትል አሰስመንት" እና "ባለሙያ" በኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 421/2010 አንቀጽ 2 የተሰጣቸው ትርጎሜ ይኖራቸዋል፣
   2. "ሰነድ ምርመራ" ማለት ለመስክ ግምገማ የሚሆኑ የተስማሚነት ምዘና አካል ሰነዶችን ተስማሚነት፣ ብቁነትና ውጤታማነት ማረጋገጥ ነው፤
   3. ቅድመ ግምገማ" ማለት ተስማሚነት ምዘና አካል ለአክሬዲቴሽን መስፈርቶች ያለውን ዝግጁነትና መቀራረብ ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ ነው፤
   4. "መነሻ ግምገማ" ማለት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚደረግ ግምገማ ነው፤
   5. "መስፈርት ምርመራ" ማለት የተስማሚነት ምዘና አካል በተስማሚነት ምዘና ሥራ ለመሰማራት የሚያበቁትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ ነው፤
   6. "መሪ ገምጋሚ" ማለት የተወሰኑ የግምገማ ክንዋኔዎችን በበላይነት የሚመራ ነው፤
   7. የቴክኒክ ገምጋሚ" ማለት በአንድ አክሬዲቴሽን አካል ተመድቦ ብቻውን ወይም የአንድ ቡድን አካል ሆኖ የተስማሚነት ምዘና አካልን የሚገመግም ሰው ነው፣

8. “ኤክስፐርት” ማለት በአንድ አክሬዲቴሽን አካል ተመድቦ የሚገመገመውን የአክሬዲቴሽን ወሰን በሚመለከት የተለየ እውቀት ወይም ሙያ የሚያበረክት ሰው ነው፤
9. “ቡድን መሪ” ማለት የተወሰኑ የግምገማ ክንዋኔዎችን በበላይነት የሚመራ ነው፤
10. “መስክ ግምገማ" ማለት ቡድን መሪው የሰነድ ግምገማ ካጠናቀቀ በኋላ ጽ/ቤቱና ተቋሙ በተስማሙበት ቀን በተቋሙ በመገኘት ሙሉ የትግበራ ሥራው የሚፈተሸበት ሥራ ነው፤
11. “አሰልጣኝ” ማለት በመስኩ እውቀትና ክህሎት ያለው ለሠልጣኞች ሥልጠና የሚሰጥ ሰው ነው፡፡

3. <u>**የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ**</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 421/2010 መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

4. <u>**የተሻረ ደንብ**</u>

የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ቁጥር 275/2005 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 27 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# የፍትህ ሚኒስቴር

## ሰንጠረዥ

## የአገልግሎት ክፍያዎች

| ተ.ቁ | አገልግሎት | ክፍያ(ብር) | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሰነድ ግምገማ | 6000 | |
| 2 | ቅድመ ግምገማ | 3000 | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ ለአንድ ቀን፡፡ ምርመራው ከዚህ በላይ የሰው ኃይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ጊዜና የሰው ኃይል ተባዝቶ ይሆናል |
| 3 | የመነሻ ግምገማ | 7500 | የሚላከው የአንድ መሪ ገምጋሚ፣ አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ እና እንዳስፈላጊነቱ አንድ የቴክኒክ ኤክስፐርት ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ኃይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜና የሰው ኃይል መጠን ከፍ ይደረጋል፡፡ |
| 4 | ዝቅተኛ መስፈርት | 4000 | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚና አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ኀይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜ እና የሰው ኃይል መጠን ከፍ ይደረጋል፡፡ |
| 5 | የክትትል ግምገማ | 6000 | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ፣ አንድ የቴክኒክ ገምጋሚና እንደአስፈላጊነቱ አንድ የቴክኒክ ኤክስፐርት ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ኃይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜና የሰው ኃይል መጠን ከፍ ይደረጋል፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | ተጨማሪ ዩኒት ለሚፈልጉ ሰፋፊ ላቦራቶሪዎች ገምጋሚ | 2500 | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ፣ አንድ የቴክኒክ ገምጋሚና አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ አንደአስፈላጊነቱ አንድ ኤክስፐርት ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ኃይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ጊዜና የሰው ኃይል ተባዝቶ ይሆናል፡፡ |
| 7 | በግምገማ ወቅት መሰረታዊ ጉድለት ያሳየ መልሶ መስተካከሉን ማረጋገጥ | 2500 | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ ወይም አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ኃይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ጊዜና የሰው ኃይል ተባዝቶ ይሆናል፡፡ |
| 8 | ዳግም ግምገማ | 7500 | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ፣፤ አንድ የቴክኒክ ገምጋሚና እንደአስፈጊነቱ አንድ የቴክኒክ ኤክስፐርት ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ኃይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜና የሰው ኃይል መጠን ክፍያ ይደረጋል፡፡ |
| 9 | ስልጠና | 2000 | የሚላከው አንድ አሰልጣኝ ለአንድ ቀን፡፡ ሥልጠናው ከዚህ ጊዜ በላይ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜ መጠን ክፍ ይደረጋል፡-፡ የሥልጠና ወጪዎችን ተቋሙ የሚሸፍን ከሆነ ክፍያው የአጠቃላዩን ክፍያ 30% ብቻ ይሆናል፡፡ |

## ክፍል ሃያ አንድ

## የባንክ እና መድህን ስራ

### ሀ/ የባንክ ስራ

## አዋጅ ቁጥር 97/1990 ዓ.ም

## በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ

በባንኮች በዋስትና የተያዙ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዲሸጡ ለፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰንና ውሳኔውንም ለማስፈጸም የሚወስደው ጊዜ በጣም ረጅም በመሆኑ፣

በቁጠባ ሂሣብ መልክ ከሕዝብ የሰበሰቡትንና ከተለያዩ ምንጮች ያገኙትን ገንዘብ በማበደር በሚገኘው የወለድ ገቢ የሚተዳደሩ ባንኮች ሥራ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ በማሳደሩ፣

ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴው አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ባንኮች ለተለያዩ የንግድና የልማት እንቅስቃሴ የሚሰጧቸው ብድሮችን በተቀላጠፈ መንገድ ለመሰብሰብ እንዲችሉና ለወደፊቱ ጥሩ የንግድ አሰራር ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ለባንክ ብድር በመያዣ የተሰጡ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሽያጭ በሚመለከት በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎች ማሻሻልና አዲስ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ቁጥር 97/1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ "ሬጅስትራር" ማለት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ መብትን በተመለከተ የማይንቀሳቀስ ንብረት የመመዝገብ ኃላፊነት ያለው የክልል ወይም የከተማ አካል ወይም በሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ መብትን በተመለከተ የስምምነቱን መፈረም የሚያረጋግጠውና ስምምነቱን የሚያስቀምጠው የክልል ወይም የከተማ አካል ነው፡፡

3. **የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ስምምነት**

   የ1952 የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 2851 እና አንቀጽ 3060 ድንጋጌ ቢኖርም የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና የያዘ ባለገንዘብ ባንክ የሚፈልገው

እዳው እንዲከፈል በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈለው ቢቀር ከሠላሳ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ ለባለዕዳው በመስጠት በመያዣ የያዘውን የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ለመሸጥና የባለቤትነት መብቱንም ለገዢው ለማዛወር ወይም ለሁለተኛ ጊዜ በወጣ የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት ገዥ ካልቀረበ ንብረቱን ለመጀመሪያው የጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሠረት ለመውሰድና የባለቤትነት መብቱ በስሙ እንዲዛወርለት ለማድረግ ከባለዕዳው ጋር የሚያደርገው ስምምነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።[128]

4. **በማይንቀሳቀስ ወይም በሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ የመያዣ መብት**

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ የያዘና ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነው ጊዜ ያልተከፈለው ባለገንዘብ ባንክ ለባለዕዳው ከሠላሳ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በመያዣ የያዘውን የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ለመሸጥና የባለቤትነቱንም መብት ለገዢው ለማዛወር ወይም ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት ገዢ ካልቀረበ ንብረቱን በብድር ውሉ ውስጥ በሰፈረው የዋጋ ግምት መሠረት ለመውሰድና የባለቤትነት መብቱ በስሙ እንዲዛወርለት ለማድረግ ይችላል፡፡

5. **በባንክና በባለዕዳው መካከል ስለሚኖር ግንኙነት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት በባንክ የተደረገ ሽያጭ ባለዕዳውን በመወከል እንደተፈጸመ ይቆጠራል።

6. **በሐራጅ ሽያጭ ላይ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚነት**

ባንክ በመያዣ የያዘውን የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ የመሸጥ ሥልጣን በሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከቁጥር 394 - 449 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

7. **ስለባንክ ተጠያቂነት**

ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተጠቀሱትን አግባብ ያላቸውን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ሽያጩን በመፈጸሙ በባለዕዳው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

8. **የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መዝጋቢ ሥልጣንና ኃላፊነት**

   1. ሬጅትራሩ ለማይንቀሳቀስ ወይም ለሚንቀሳቀስ ንብረት የሐራጅ ሽያጭ አፈጻጸም የሚረዱ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል።

[128] በ6/46 (1992) አ. 216 አንቀፅ 2 (1) ተሻሻለ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሬጅስትራሩ ለሚወስደው እርምጃ የፖሊስ ኃይል መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ፖሊስን ማዘዝ ይችላል።

9. <u>በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ስላሉ ጉዳዮች</u>

የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና በያዘ ባለገንዘብ ባንክ አመልካችነት ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ ክስ ወይም አፈጻጸም ተቋርጦ በዚህ አዋጅ መሠረት ባንክ ንብረቱን ለመሸጥና የባለቤትነቱንም መብት ለገዢ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

10. <u>የተሻረ ሕግ</u>

የፍትሐብሔር ሕግ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 65/1989 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

11. <u>መሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የፍትሐብሔር ሕግ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 65/1989 መሠረት በአፈጻጸም ላይ ያሉ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት ይመራሉ፡፡

12. <u>ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

13. <u>አዋጁ የሚፀናበት</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 12 ቀን 1990 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 592/2000[129]

## ስለባንክ ሥራ የወጣ አዋጅ

ባንኮች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር ገንዘብ በማሰባሰብ በተለያዩ የልማት ዘርፎች እንዲውል በማድረግ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው፤

ባንኮች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ የክፍያና የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸው በመሆናቸው፤

የባንክ ሥራ በተገቢው ሥርዓት አለመመራት በፋይናንስ ሥርዓቱና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ጎጂ የሆነ ያለመረጋጋት ሁኔታን የማስከተል ባህሪያት ያሉት በመሆኑ፤

በፋይናንስ ሥርዓቱና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ የሚደርሰው አለመረጋጋት በሕዝብና በመንግሥት ላይ የሚያስከትለውም ጉዳት በቀላሉ የሚገመት ባለመሆኑ፤

የባንክ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን በሚመለከት ሁለ አቀፍ ሕግ በማውጣት የባንክ ሥርዓቱ ለአደጋ ያልተጋለጠ፣ አስተማማኝና የተረጋጋ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "'ባንክ" ማለት የባንክ ሥራ እንዲሠራ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም የመንግሥት ባንክ ነው፣
   2. "የባንክ ሥራ" ማለት የሚከተሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል፣

      ሀ) ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አለው ብሎ በፈቀደው የገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመቀበል፤

[129] 25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(26) መሰረት በአዋጁ በተለያዩ ቦታዎች "ቁጥጥር/ የቁጥጥር ሥራ"፣ "ተቆጣጣሪ"፣ "ቁጥጥር እንዲያካሂዱ" እና "ቁጥጥሩ በተደረገበት" ተብለው የተጠቀሱት "የምርመራ ሥራ"፣ "መርማሪ" እና "የምርመራውን ሥራ እንዲያካሂዱ" እና "ምርመራው በተደረገበት" በሚሉት ተተክተዋል፡፡

ለ) የባንክ ሥራ በሚሠራው ሰው ሂሣብና ኃላፊነት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል(ሀ) የተመለከተውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ በብድሮች ወይም በኢንቨስትመንቶች ላይ የማዋል፤

ሐ) በገንዘብ መልክ ያልተቀረፀ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የመግዛትና የመሸጥ፤

መ) በባንኮቹ በራሳቸውም ሆነ በደንበኞቻቸው ስም ለሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ሰዎች ገንዘብ የማስተላለፍ፤

ሠ) በገንዘብ ማስከፈያ፣ በሐዋላና በተስፋ ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች የዕዳ ማረጋገጫ ሰነዶች አማካኝነት በቅናሽ የማበደርና የማስተላለፍ፤

ረ) በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የመስጠት፣[130]

ሰ) የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት የመስጠት፣

ሸ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሰ" በተመለከቱት ተግባራት የተሰማራ ባንክ እንዲሠራቸው በብሔራዊ ባንክ የሚፈቀድለት በተለምዶ እንደባንክ ሥራ የሚታወቁ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፣

3. "የካፒታል ወጪ" ማለት በመቋቋም ላይ ባለ ባንክ የሚከፈል የቅድሚያ ወጪ፣ የአክሲዮን ሽያጭ ኮሚሽን፣ የድለላ አገልግሎት ክፍያና በቋሚ ንብረት መልክ የማይታይ ሌላ ወጪ ነው፤

4. "ዋና የሥራ አስፈጻሚ" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የአንድን ባንክ የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፣

5. "ኩባንያ" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጉም የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ፡-[131]

ሀ) በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸዉ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም በኢትዮጵያውያን እና የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸዉ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጋራ የተያዘ ወይም

ለ) ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸዉ ትውልደ በኢትዮጵያዊያን ወይም በኢትዮጵያዊያን እና የዉጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው

[130] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(1) መሰረት አንቀጽ 2(2) (ረ) ተሰርዞ አዳዲስ ፊደል ተራ (ረ)፣ (ሰ) እና (ሸ) ተጨምረዋል፡፡
[131] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ ፤በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፤

6. “ዳይሬክተር” ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፤

7. “ሠራተኛ” ማለት የባንክ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን እንዲያካሂድ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፤

8. “የአደራ ተግባር” ማለት አብዛኛውን ጊዜ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል በባንክ የሚከናወን ንብረትን ተቀብሎ በአደራ የማስቀመጥ ወይም በሌሎች ሰዎች ስም ገንዘብ የማስተዳደር ተግባር ነው፤

9. “የፋይናንስ ድርጅት" ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት፣ በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት፣ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ነው፤[132]

10. “የሂሣብ ዓመት” ማለት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ከጁላይ 1 ቀን ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት ጁን 30 ቀን የሚያበቃ የባንክ የሂሣብ ዓመት ነው፤

11. “ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማናቸውም ባንክ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው፣

12. “ዕዳ መክፈል የማይቻልበት ወሰን” ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የማናቸውም ባንክ ጠቅላላ ዕዳ ከጠቅላላ ሀብቱ የበለጠ የሚሆንበት ጊዜ ነው፤

13. "ብድር" ወይም "ቅድሚያ ክፍያ" ማለት በተወሰነ ቀን ወይም ቀኖች ወይም በተጠየቀ ጊዜ በተለምዶ ከወለድ ጋር ተመልሶ እንዲከፈል ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ወይም ግዴታ በማስገባት በቀጥታ፣ ወይም እንዳልታቀደ ኦቨርድራፍት፣ ከሌላ አበዳሪ ጋር በትብብር በሚሰጥ ብድር እንደመሳተፍና ከሌላ አበዳሪ ብድር እንደመግዛት በመሳሰሉት በተዘዋዋሪ፣ ለማንኛውም ሰው ገንዘብ ከመስጠት ወይም ገንዘብ ለመስጠት ቃል ከመግባት የሚመነጭ ማንኛውም የአንድ ባንክ የፋይናንስ

[132] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

ሀብት ሲሆን ማናቸውም ባንክ ለማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በስሙ ብድር ለመስጠት፣ ባንኩ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት አከራይ በሆነበት የሊዝ ፋይናንስ ስምምነት ማስረጃነት የይገባኛል መብትን ለማስተናገድና በተበዳሪው ስም የኦቨርድራፍት አገልግሎት ለመስጠት በውል ላይ ተመሥርቶ የተገባን ግዴታ ያጠቃልላል፤[133]

14. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
15. “የችሎታ መመዘኛ” ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ የብቃትና የሥነ-ምግባር መመዘኛ ነው፣
16. “ሞግዚት” ማለት ብሔራዊ ባንክ ወይም ችግር ያለበትን ባንክ በመረከብ አሠራሩን እንደገና በማዋቀር ጤናማ ለማድረግ ወይም ሕልውናው እንዲያከትም ለማድረግ በብሔራዊ ባንክ የተሾመ ሰው ነው፣
17. “በዋስትና የተጠበቀ የይገባኛል ጥያቄ” ማለት በንብረት መያዣነት ወይም በውል መሠረት በሌሎች ንብረቶች ላይ ተፈጻሚ በሚሆን ዋስትና የተደገፈ የማናቸውም ባንክ የይገባኛል ጥያቄ ነው፣
18. “ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚ” ማለት የዋና ሥራ አስፈጻሚ ምክትል የሆነ ወይም ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ ማንኛውም የባንክ የሥራ ኃላፊ ነው፣
19. “ብሔራዊ ባንክ” ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው።
20. "ዋስትና" ማለት ግዴታ ያለበት ሰው ግዴታውን በአጥጋቢ ሁኔታ ሳይወጣ ቢቀር የጉድለቱን ተመጣጣኝ ክፍያ ራሱ እንደሚሸፍን ባንኩ ለደንበኛው በጽሑፍ የሚሰጠው ማረጋገጫና የተሰፋ ሰነድ ነው፤[134]
21. "በዲጂታል ዘዴዎች የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት" ማለት በዲጂታል ዘዴዎች የሚሠጡ የክፍያ፣ የሐዋላ እና የመድን አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፤
22. "የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ" ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 ላይ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፤

---

[133] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

[134] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(3) አንቀጽ 2(19) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (20)፣ (21)፣ (22)፣ (23)፣ (24)፣ (25) እና (26) ተጨምረዋል፤

23."የገንዘብ አከል ንብረት እጥረት ሲያጋጥመው" ማለት ባንኩ የአጭር ጊዜ ግዴታውን መወጣት ወደማይችልበት የፋይናንስ ቁመና ሲደርስ ማለት ነው፤

24."በተዘዋዋሪ ከባንክ የአክሲዮን ድርሻ ያለው" ማለት በቀጥታ በባንኩ የአክሲዮን ድርሻ ባለው ድርጅት የአክሲዮን ድርሻ መያዝ ማለት ነው፤

25."መደበኛ የሥራ ሂደት" ማለት የባንኩን ፖሊሲና መመሪያ በመከተል ያለአንዳች መድልኦ እንዲሁም ከሌሎች ደንበኞች ባልተለየ አሠራርና ሁኔታ አገልግሎት ማግኘት ነው"፤

26.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተነገረው ድንጋጌ ሴትንም ይጨምራል፤

**ክፍል ሁለት**

**ስለባንክ ሥራ ፈቃድ**

3. **ፈቃድ የማውጣት አስፈላጊነት**

1. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ የባንክ ሥራ ፈቃድ ወይም በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የመስጠት ፈቃድ ወይም ይሁንታ ሳያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሥራ ማካሄድ ወይም በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡[135]

2. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ "ባንክ" የሚለውን ወይም ተዛማጅ የሆነ ስያሜ የማናቸውም የፋይናንስ ተቋም ስም አካል አድርጎ መጠቀም አይችልም።

3. ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በቀር ማንኛውም ባንክ፣

ሀ) ብሔራዊ ባንክ ከፈቀደው ቦታ ውጭ የባንክ ሥራ ማካሄድ ወይም ነባር የሥራ ቦታን መዝጋት፣

ለ) አዲስ የባንክ አገልግሎት መጀመር፤

ሐ) ከሌላ ባንክ ጋር መቀላቀል ወይም የሌላ ባንክን ሥራ በባለቤትነት መያዝ፣

መ) በመቀላቀልም ሆነ በሌላ መንገድ የባንኩን መሸጥ ወይም የባለሀብትነት መተላለፍ የሚያስከትሉ ማናቸውንም ዓይነት ስምምነቶች ወይም ውሎች ማድረግ ወይም የተፈቀደለትን የባንክ ንግድ ሥራ ዓይነት መቀየር፤

[135] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(4) ተሻሻለ፡፡

ሠ) በመደበኛ የሥራ ተግባሩ አፈጻጸም ሳቢያ ካልሆነ በቀር የንብረት ባለቤትነቱን በሙሉም ሆነ በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ማስተላለፍ ወይም በሌላ መንገድ ማዛወር፣

ረ) ባንኩ ራሱ ያወጣውን አክሲዮን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በቀር ካፒታሉን መቀነስ፣

ሰ) የተሻሻለዉን የመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማስመዝገብ፤ ወይም[136]

ሸ) የባንክ ሥራ እንዲያካሂድ ፈቃድ ያገኘበትን ስም መቀየር፤ አይችልም።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የአጭር ጊዜ ቁጠባን ለማሰባሰብ የሚደረግ ዘመቻ እና/ወይም ወደ ደንበኛው የሥራ ቦታ በመሄድ ጥሬ ገንዘብ የማሰባሰብን አገልግሎት በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ[137]

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን በመተላለፍ ማንኛውም ሰው ተቀማጭ ገንዘብ ለመቀበል በማስታወቂያ ወይም በማግባቢያ ዘዴ መጠቀሙን ወይም የባንክ ሥራ እያካሄደ መሆኑን ብሔራዊ ባንክ ለማመን ምክንያት ሲኖረው ይህንኑ ሁኔታ ለማጣራት ባንኩ በዚሁ ሰው ይዞታ ሥር የሚገኙትን የንግድ መዝገቦች፣ ቃለ-ጉባኤዎች፣ ሂሣቦች፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነዶች፣ ማስታወሻዎች፣ የገንዘብ ማዘዣዎችና ሌሎች ሰነዶች እንዲያቀርቡለት ማድረግና መመርመር ወይም ማስመርመር ይችላል፡፡

6. ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ የባንክ ሥራ በማካሄድ በዚህ ድርጊት አማካኝነት የተቀበለው ገንዘብና ሌላ ንብረት በእጁ የሚገኝ ከሆነ ብሔራዊ ባንክ ይኸው ገንዘብና ንብረት ለአስቀማጮቹ ወይም ለባለንብረቶቹ በአፋጣኝና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲመለስ አስፈላጊው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

---

[136] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(5) ተሻሻለ፡፡

[137] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(6) መሰረት አንቀጽ 3 (3) ቀጥሎ የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) ተጨምሮ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤ (አርፍተ ነገሩ ያላለቀ ሲሆን እንግሊዘኛው issue ይላል፡፡)

4. **የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች**

1. የባንክ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣
   - ሀ) በሚገባ የተሞላ የፈቃድ መጠየቂያ ቅጽና ብሔራዊ ባንክ የሚጠይቃቸው ሌሎች አባሪ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፣
   - ለ) ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ መከፈል አለበት፣
   - ሐ) ማመልከቻው ለብሔራዊ ባንክ እንደቀረበ ባንኩ በሚወስነው ቅጽ መሠረት መሥራቾቹ በባንክ ሥራ ለመሰማራት መፈለጋቸውን ለአራት ተከታታይ ሳምንታት ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በስፋት በሚሠራጩ ጋዜጦች ላይ አሳትመው ማውጣት አለባቸው፣
   - መ) ባንኩ በኩባንያ መልክ መቋቋምና የመመሥረቻ ጽሑፉና የመተዳደሪያ ደንቡ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ  መጽደቅ አለበት፣
   - ሠ) ያወጣቸው አክሲዮኖች በሙሉ የተፈረሙ ሆነው ከእነዚሁም ውስጥ ቢያንስ ሩቡ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መሆን አለበት፣
   - ረ) በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ መከፈልና በምሥረታ ላይ ባለው ባንክ ስም በዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፣
   - ሰ) የባንኩ ዳይሬክተሮች፣ ዋናው ሥራ አስፈጻሚና ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን የችሎታ መመዘኛ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡
   - ሸ) ተደማጭነት ያላቸው ባለአክሲዮኖች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን የተገቢነትና ሥነ-ምግባር መመዘኛ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፣
   - ቀ) የባንኩ ሕንፃና ግቢ፣ የጥበቃ ሥርዓትና የገንዘብ ማስቀመጫ ቮልት ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን መስፈርቶች አሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡
2. ሊቋቋም በታሰበው ባንክ ውስጥ የማንኛውንም መሥራች ባለአክሲዮን መሆን የሚቃወም ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/ በተመለከተው መሠረት የመጨረሻው ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከማስረጃ ጋር በጽሑፍ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይችላል፡፡ ብሔራዊ ባንክ ተቃውሞውን ለመመርመር የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል።

የምርመራው ውጤት በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ተደርጎ ፈቃዱን ለመስጠት ወይም ለመከልከል ታሳቢ ይደረጋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የባንክ ሥራ ፈቃድ ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

5. **ፈቃድ ስለመስጠት**

1. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉ 90 ቀናት ውስጥ በባንክ ሥራ ፈቃድ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ ይሰጣል።
2. ፈቃዱ የሚሰጠው በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ ሲከፈል ይሆናል፡፡
3. በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ የባንክ ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የመጨረሻው ፈቃድ ይሆናል፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የፈቃድ ሁኔታዎችን ሲያሻሽል ማሻሻያው በሥራ ላይ እንዲውል ከታሰበበት ጊዜ ሠላሳ ቀን ቀደም ብሎ የሚመለከታቸው ባንኮች እንዲያውቁት ያደርጋል።

6. **የባንክ ሥራ ስለመጀመር፤**

ፈቃድ የተሰጠው ባንክ፣

1. ሥራ ከመጀመሩ በፊት በብሔራዊ ባንክ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ብቃት ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት፣ የመረጃ ፍሰት ሥርዓት፣ የሪስክ ማኔጅመንት ፖሊሲና ደንቦች፣ እንዲሁም የሰው ኃይል አደረጃጀትና የመሳሰሉትን የባንክ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ግዴታዎችን ማሟላት፤ እና
2. ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 12 ወራት ውስጥ ሥራ መጀመር፣ አለበት።

7. **የፈቃድ እድሳት**

ብሔራዊ ባንክ የባንክ ሥራ ፈቃድ የሚታደስበትን ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

8. **ፈቃድ የተሰጣቸውን ባንኮች ስለማስታወቅ**

ብሔራዊ ባንክ በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸውን ባንኮች ዝርዝር አትሞ ያወጣል። እንዲሁም በዚሁ ዝርዝር ላይ የተጨመሩትን ወይም ከዝርዝሩ የተሰረዙትን ባንኮች ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች ላይ ወዲያውኑ አሳትሞ ያወጣል።

## 9. የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በባንክ ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ[138]

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 (1)(እንደተሸጋሸገው) የተደነገገዉ ቢኖርም የውጭ ሀገር ዜግነት ያለዉ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም ሙሉ በሙሉ የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸዉ ትውልደ ኢትዮጵያውን ባለቤትነት ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያን የጋራ ባለቤትነት የተቋቋመ ድርጅት በኢትዮጵያ ዉስጥ በተቋቋመ ባንክ የአክሲዮን ባለቤት መሆን ወይም ባንክ ማቋቋም ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው አግባብ የዉጭ ሀገር ዜግነት ያለዉ ትውልደ ኢትዮጵያዊ በቀጥታ የአንድ ባንክ ባለአክሲዮን ሲሆን ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የአክሲዮን ባለቤት የሆነበት ሌላ ድርጅት የአንድ ባንክ ባለአክሲዮን ሲሆን የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም እርሱ ባለአክሲዮን የሆነበት እና በባንኩ ባለአክሲዮን የሆነ ድርጅት በባንኩ የሚኖረዉ የአክሲዮን ድርሻ ዋጋ በሙሉ ተቀባይነት ባለዉ የውጭ ምንዛሪ ብቻ የሚከፈል ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ግዴታ ቢኖርም፡-

   ሀ) ከአክሲዮን ባለቤትነት የሚያገኘውን የትርፍ ድርሻ፤

   ለ) የአክሲዮን ድርሻውን ለሌላ ሰው ሲያዛውር፤

   ሐ) ባለአክሲዮን የሆነበት ባንክ ሲሸጥ ወይም ፈርሶ ሂሳቡ ሲጣራ፤ ወይም

   መ) ሌሎች ከአክሲዮን ባለቤትነት ጋር በተያያዘ፤የውጭ ሀገር ዜግነት ላለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም እሱ ባለአክሲዮን ለሆነበት ድርጅት እና በባንኩ ውስጥ አክሲዮን ላለው የሚከፈሉ ማናቸውም ዓይነት ክፍያዎች በሙሉ በብር የሚከፈሉ ይሆናል፤ እንዲሁም በዚህ አግባብ የሚያገኘውን ሀብት ወይም ጥቅም ወደ ውጭ ማዛወር አይፈቀድለትም፡፡
4. የውጭ ሀገር ዜግነት ያለዉ ትውልደ ኢትዮጵያዊ በባንክ ዘርፍ መዋዕለ ንዋዩን በሥራ ላይ ስለሚያውልበት ተጨማሪ ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለአክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች ጉባዔ

## 10. ስለአክሲዮኖችና የአክሲዮን መዝገብ

[138] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(7) ተሻሻለ፡፡

1. የባንክ አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው፣ አንድ ዓይነት የሆኑና የተመዘገቡ ተራ አክሲዮኖች ይሆናሉ።
2. ማናቸውም ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝርና ድምጽ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የአክሲዮን መዝገብ ይይዛል።
3. ማንኛውንም ሰው ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ሊያደርግ የሚችል የአክሲዮን ዝውውር በአክሲዮን መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት።
4. በአክሲዮን መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ ማናቸውም የአክሲዮን ዝውውር ዋጋ አይኖረውም።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው የአክሲዮን መዝገብ በባንኩ መደበኛ የሥራ ሰዓት ሕዝብ ያለክፍያ ማየት በሚችልበት ሁኔታ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ይቀመጣል።

11. <u>አክሲዮኖች የመያዝ ገደብ</u>

1. ከኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት በስተቀር፣ ማንኛውም ሰው ብቻውንም ሆነ ከባለቤቱ ወይም እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ በአንደኛ ደረጃ ከሚዛመዳቸው ሰዎች ጋር በመሆን የማናቸውም ባንክ የተፈረመ ካፒታል ከአምስት በመቶ በላይ አክሲዮን ሊኖረው አይችልም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወደ ባንክ ባደገ ኩባንያ ውስጥ ማናቸውም የክልል መንግሥት ሊኖረው የሚችለው የአክሲዮን መጠን ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. በማንኛውም ባንክ ውስጥ አክሲዮን ያላቸው ሰዎች በከፊል ወይም በሙሉ በባለቤትነት የያዙት ኩባንያ በባንኩ ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን የአክሲዮን መጠን ብሔራዊ ባንክ ይወስናል።
4. በአንድ ባንክ ውስጥ ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን በሌሎች ባንኮች አክሲዮን መያዝ አይችልም።
5. ማንኛውም ሰው ከባንክ በተገኘ ብድር የባንክ አክሲዮን ሊገዛ አይችልም።
6. [139]

12. <u>የባለአክሲዮኖች ጉባኤ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ፣

[139] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(8) ተሰረዘ፡፡

ሀ) በማንኛቸውም የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በታዛቢነት የሚሳተፍ ሰው ሊመድብ፣ እና

ለ) የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የባለአክሲዮኖችን ጥቅም ለማስከበር ወይም የባንክ ክፍለ ኢኮኖሚውን መረጋጋትና ጤናማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት ባንኩን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ አወያይቶ ውሳኔ ማሰጠት፣ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ በተመለከተው መሠረት ብሔራዊ ባንክ የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የጠራ እንደሆነ፣

ሀ) የስብሰባውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣

ለ) የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም በባንኩ የተሰየመ ሌላ ሰው ስብሰባውን ይመራል፣

ሐ) የባለአክሲዮኖችን ጠቅላላ ጉባኤ ምልዐተ ጉባኤ እና በጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በሚመለከት በንግድ ሕጉ ስለአክሲዮን ማኅበራት የተደነገጉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፣

መ) ከጉባኤው መካሄድ ጋር የተያያዙ ወጪዎች ጉዳዩ በሚመለከተው ባንክ ይሸፈናሉ።

13. <u>ድምጽ የመስጠት ገደብ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም የባለአክሲዮኖች ስብሰባ፣

ሀ) ማንኛውም ሰው ለሌላ ባለአክሲዮን እንደራሴ ሆኖ የሚሰጠውን የድምጽ መጠን፣ እና

ለ) ከባንኩ የተበደረ ማንኛውም ባለአክሲዮን የሚኖረውን ድምጽ፣

ሊገደብ ይችላል፡፡

2. ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ባንኩ በመመሪያ የሚወስናቸውን የሥነ-ምግባርና ተገቢነት መስፈርቶች ማሟላት ያልቻለ እንደሆነ ድምጽ የመስጠት መብቱን ሊገድብበት ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለባንክ ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች

### 14. ስለዳይሬክተሮችና ሥራ አስፈጻሚዎች ሹመት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15/2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ዳይሬክተር ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ በሚወስናቸው የችሎታ መመዘኛዎች መሠረት ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ ጠንቃቃና መልካም ዝና ያለው መሆን አለበት፡፡[140]
2. የባንክ ሥራ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜም ሆነ በሌላ ማናቸውም ጊዜ የሚደረግ የማናቸውም ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሹመት በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ካልጸደቀ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. ብሔራዊ ባንክ አዲስ የተመረጡ የባንክ ዳይሬክተሮችን ሹመት በጽሑፍ እስኪያጸድቅ ድረስ የነባር ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ መቀጠል አለበት፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ፣
   ሀ) ዳይሬክተሮች ማሟላት ስለሚገባቸው የችሎታ መመዘኛዎች፣
   ለ) የአንድ ባንክ የቦርድ አባሎች ሆነው የሚሠሩትን ዳይሬክተሮች ዝቅተኛ ቁጥር፣
   ሐ) የባንክ ዳይሬክተሮች ቦርድን ተግባራት፣ ኃላፊነት፣ ግዴታዎችንና መልካም የኩባንያ ሥራ[141]
   መ) አንድ ዳይሬክተር በማንኛቸውም ባንክ ሊያገለግል የሚችልበትን ከፍተኛ የሥራ ዘመንና እንደገና ለመመረጥ የሚያበቁትን ሁኔታዎች፣
   ሠ) ለዳይሬክተሮች የሚደረገውን የክፍያ ጣሪያ፣ እና
   ረ) በማናቸውም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ተመርጠው ሊያገለግሉ የሚችሉ የዚያው ባንክ ሠራተኞችን ቁጥር በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 15. ክልከላ

1. የውጭ ሀገር ዜጎች ወይም በከፊልም ሆነ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት ሥር ያሉ ድርጅቶች ወይም የውጭ ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሥራ ማካሄድ ወይም

---
[140] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(9) ተሻሻለ፡፡
[141] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(10) ተሻሻለ፡፡

የባንክ ሥራ የሚያካሂድ ቅርንጫፍ ሊያቋቁሙ አይችሉም፤በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ባንክ የአክሲዮን ድርሻም መያዝ አይችሉም::[142]

2. ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከስሶ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ሰው የባንክ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ መሆን አይችልም።
3. ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሚገኝ በማናቸውም በፈረሰ ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የነበረ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንኩ ሥራ አመራር የተሳተፈ ሰው በባንክ ዳይሬክተርነት፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚነት ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንክ ሥራ አመራር መሳተፍ አይችልም።
4. የፋይናንስ ድርጅት ዳይሬክተር በተመሳሳይ ጊዜ የባንክ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡ በተጨማሪም ዳይሬክተሩ ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚው አሥር በመቶና ከዚያ በላይ የባለቤትነት ድርሻ የያዘበት የንግድ ድርጅት የባንክ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡[143]
5. ማናቸውም የባንክ ሠራተኛ የዚያው ባንክ ቦርድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ወይም በማናቸውም ሌላ ባንክ ዳይሬክተር ሆኖ ሊመረጥ አይችልም።

16. <u>ከባንክ ሥራ አመራር ራስን ስለማግለል</u>

ማንኛውም የባንክ ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንክ ሥራ መሪነት የሚሳተፍ ሰው፣

1. ራሱ ወይም ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚሠራበት ኩባንያ ከስሬአለሁ ብሎ ያመለከተ ወይም በፍርድ ቤት የኪሣራ ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ወይም በኪሣራ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ንብረቱ በቁጥጥር ሥር የዋለበት ወይም ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በባንክ የተወረሰበት እንደሆነ፣
2. የባንክም ሆነ ሌላ ብድር ወይም ታክስ ባለመክፈሉ ተከስሶ የተፈረደበት እንደሆነ፣

[142] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(11) መሰረት አንቀፅ 15 አዲስ ንዑስ አንቀፅ (1) ተጨምሮ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3) እና (4) ንዑስ አንቀፅ (2)፣ (3)፣ (4) እና (5) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡
[143] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(12) ተሻሻለ፡፡

3. ራሱ ወይም ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚሠራበት ኩባንያ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የመክፈያ ጊዜያቸው ላለፈባቸው ብድሮች ለማናቸውም ባንክ ባለዕዳ የሆነ እንደሆነ፣ ወይም
4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወሰናቸውን የችሎታ መመዘኛዎች ያላሟላ እንደሆነ፣ ራሱን ከባንክ ሥራ አመራር ማግለል አለበት፡፡

17.**በብሔራዊ ባንክ ስለሚወሰድ የማገድና የማሰናበት እርምጃ**

1. ብሔራዊ ባንክ በቂ ነው ብሎ በሚያምንበት ምክንያት ማንኛውንም የባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ለማገድ ወይም ለማሰናበት ይችላል።
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ዓላማ ሲባል "በቂ ምክንያት" የሚከተሉትን ያካትታል፤
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 እና 16 የተደነገጉትን አለማክበር፣
   ለ) ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የፈመው የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚውን መረጋጋት ጤናማነት፣ኢኮኖሚውን ወይም የሕዝብን ጥቅም አደጋ የሚጥል ማንኛውም ድርጊት፡፡[144]
3. ብሔራዊ ባንክ የአንድን ባንክ ዳይሬክተሮች ከሥራ በሚያሰናብትበት ጊዜ የዳይሬክተሮቹ ቁጥር በሕግ ከሚፈቀደው በታች ከሆነ ወዲያውኑ የቦርዱን ኃላፊነት ተረክቦ በ30 ቀናት ውስጥ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ በመጥራት በተሰናበቱት ዳይሬክተሮች ምትክ ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ የአንድን ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ሲያሰናብት፣ የዚያ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ በብሔራዊ ባንክ የወጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሰው ወዲያውኑ መተካት አለበት፡፡

## **ክፍል አምስት**

## **የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች**

18.**ተፈላጊውን ካፒታል ስለመያዝ**

1. ባንኮች መያዝ ያለባቸው አነስተኛ የካፒታል መጠንና መጠባበቂያ እንዲሁም እነዚህ የሚሰሉባቸው ቀመሮች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።

[144] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(13) ተሻሻለ፡፡

2. ብሔራዊ ባንክ ባንኮች ለአደጋ የተጋለጡበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የካፒታልና የመጠባበቂያ ግዴታዎችን ለተለያዩ ባንኮች ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡
3. ብሔራዊ ባንክ የማናቸውም ባንክ ካፒታል ከተወሰነው አነስተኛ መጠን በታች ነው ብሎ ሲያምን ባንኩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. ማናቸውም ባንክ በካፒታሉ ላይ የደረሰው መሸርሸር መወገዱ በብሔራዊ ባንክ ሳይረጋገጥ የትርፍ ክፍፍል ማድረግ፣ በባለ አክሲዮኖች ሂሣብ ውስጥ ማስገባት ወይም መክፈል አይችልም።

19. <u>ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ ስለመያዝ</u>

1. ማናቸውም ባንክ በሂሣብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ካገኘው የተጣራ ትርፍ ቢያንስ 25 በመቶ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣቡ ያዛውራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም፣ መጠባበቂያ ሂሣቡ ከባንኩ ካፒታል ጋር እኩል ሲሆን ከተጣራ ትርፉ በየዓመቱ የሚያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. ብሔራዊ ባንክ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ ዝቅ የሚደረግባቸውን ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

20. <u>በቂ ገንዘብ-አከል ንብረትና የመጠባበቂያ ሂሣብ ስለመያዝ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እያንዳንዱ ባንክ በቂ ገንዘብ-አከል ንብረቶችን መያዝ አለበት።
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አፈጻጸም "ገንዘብ-አከል ንብረት" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

   ሀ) ጥሬ ገንዘብ፣

   ለ) በብሔራዊ ባንክና በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው ሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባንኮች ያለ ተቀማጭ ገንዘብ፣

   ሐ) በብር ወይም በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሪ የተገለጹና በቀላሉ ወደ ጥሬ ገንዘብ ተቀይረው ወዲያውኑ ተከፋይ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ንብረቶች፤

መ) በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ተቀባይነት አላቸው ተብለው የሚወሰኑ ሌሎች ገንዘብ-አከል ንብረቶች።

3. እያንዳንዱ ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በብሔራዊ ባንክ በተከፈተ ሂሣብ መጠባበቂያ በጥሬ ገንዘብ ማስቀመጥ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የገንዘብ-አከል ንብረትና የመጠባበቂያ ገንዘብ ሂሣብ ግዴታዎችን ያላሟላ ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መቀጫ ይከፍላል።

21. <u>ፕሮቪዥንና የእርጅና ቅናሽ የመያዝና ኪሣራ የመሸፈንና የማጣጣት ግዴታዎች</u>

1. ማንኛውም ባንክ ለሚከተሉት ጉዳዮች የፕሮቪዥን ሂሣብ መያዝ አለበት፤

ሀ) ለብድሮች፣ ቅድሚያ ክፍያዎችና ለማይከፈሉ ወይም አጠራጣሪ ለሆኑ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣

ለ) ባንኩ የካፒታልና መጠባበቂያ ግዴታዎቹን ማሟላቱን ለማረጋገጥ ስሌት ሲሠራ ከግምት ውስጥ ላልገቡ ዕዳዎችና ሊያጋጥም ለሚችል የዕዳ ተጠያቂነት ጭምር በዋስትና ለተሰጡና በዋስትናው መሠረት ባንኩ ከሕዝብ ለሚፈለግበት ዕዳ ሊያገለግሉ ለማይችሉ ንብረቶች ዋጋ፣ እና

ሐ) ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚወስኑ ሌሎች ጉዳዮች።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚያዘው ፕሮቪዥን መጠንና የሚሰላበት ዘዴ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. ማናቸውም ባንክ ለቋሚ ንብረቶች የሚይዘውን የእርጅና ቅናሽ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ማስላት አለበት፡፡

4. ማናቸውም ባንክ የካፒታል ወጪዎችን ቢበዛ በአምስት ዓመት ውስጥ ማጣጣት አለበት፡፡

5. ማናቸውም ባንክ በሥራ ሂደት የደረሱና የተጠራቀሙ ኪሣራዎችን በየዓመቱ በሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነት ኪሣራዎች ሙሉ በሙሉ እስከሚሸፈኑ ድረስ ባለአክሲዮኖች ትርፍ አይከፋፈሉም፡፡

6. ብሔራዊ ባንክ ማናቸውም ባንክ የካፒታልና የመጠባበቂያ ሂሣብ ግዴታዎቹን ማክበሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነውን ስሌት በሚሠራበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/፣ /3/ እና /4/ መሠረት የተያዘውን ፕሮቪዥንና የቋሚ ንብረቶች

የእርጅና ቅናሽ ሂሣብና የተደረገውን የካፒታል ወጪዎች ማጣጣት በቂነት ታሳቢ በማድረግ አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

7. ማናቸውም ባንክ፣

ሀ) የባንኩ ማናቸውም ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል የሚያደርሰውን እንዲሁም በማናቸውም ባልተጠበቀ ሁኔታ የሚደርሰውን ኪሣራ ለመሸፈን የሚያስችልና ለዚሁ ጉዳይ ብቻ የተያዘ የመጠኑ በቂነት በብሔራዊ ባንክ የተረጋገጠ ልዩ የመጠባበቂያ ሂሣብ ይይዛል፣ ወይም

ለ) የዚህ ዓይነቱን ኪሣራ ለመሸፈን ብሔራዊ ባንክ የዋስትና መጠኑን በቂነት እንዲሁም የሁኔታውን አግባብነት በተቀበለው ዓይነት የመድን ውል ይገባል፡፡

22. <u>በአንዳንድ የባንክ አገልግሎቶች ላይ ስለሚጣሉ ገደቦች</u>[145]

1. ማንኛውም ባንክ በሚያደርገው ኢንቨስትመንትና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማንኛውም ሰው በሚሰጠው ብድር፣ የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሌላ የብድር አገልግሎት፣ ዋስትና ወይም ባንኩ በሚገባቸው ሌሎች ግዴታዎችና ውሎች ላይ ለሚጣሉ ገደቦችና ሁኔታዎችን በሚመመለከት ባንኩ መመሪያ ያወጣል፡፡"

2. ብሔራዊ ባንክ ከወለድ ነፃ ተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የባንክ ሥራዎችን ለመቆጣጠር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

3. ማናቸዉም ባንክ የራሱን አክሲዮን በመያዝ ብድር መስጠት አይችልም፡፡[146]

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለፋይናንስ መዝገቦችና ስለውጭ ኦዲት ምርመራ</u>

23. <u>ስለፋይናንስ መዝገቦች</u>[147]

1. ማናቸውም ባንክ፣

ሀ) የባንኩን ሁኔታ በግልጽና በትክክል በሚያሳይ፣

ለ) የባንኩን ሥራና የገንዘብ አቋሙን በሚያስረዳ፣ እና

ሐ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሥራውን እያካሄደ ስለመሆኑ ብሔራዊ ባንክ ማረጋገጥ በሚያስችለው፣ ሁኔታ መዝገቦቹን መያዝ አለበት፡፡

[145] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(14) ተሻሻለ፡፡
[146] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(15) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡
[147] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(16) መሰረት አንቀጽ 23 (1) ተሰርዞ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

2. ማናቸውም ባንክ እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴ ዓይነት የሚመዘገብበት የተለየ መዝገብና ሰነዶች መያዝ አለበት። የእነዚህን ሰነዶች አቀራረብና በውስጣቸውም የሚመዘገቡትን ጉዳዮች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

24. <u>ኦዲተሮች ስለመሾም</u>[148]

1. ማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተሮች ይሾማል። የኦዲተሮቹ ሹመትም በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፡፡
2. የሚከተሉት ሰዎች የማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተር ሆነው መሾም አይችሉም፤
   ሀ) የባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፣
   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ የሚሸፈን ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም በአንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ፣
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ ወይም /ለ/ የሚሸፈን ሰው የሥራ ባልደረባ ወይም ሽሪክ የሆነበት የኦዲት ተቋም፡፡
3. ማናቸውም ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የውጭ ኦዲተር ያልሾመ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ኦዲተር ይሾምለታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ኦዲተር የተሾመለት ማንኛውም ባንክ ለተሾመው ኦዲተር የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ ብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መፈጸም አለበት፡፡

25. <u>የኦዲተሮች የሹመት ዘመን</u>

1. የባንኮችን የኦዲት ሥራ ለማካሄድ ስለሚሾሙ የውጭ ኦዲተሮች የሹመት ዘመን ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24/4/ መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሾመ የውጭ ኦዲተር የአገልግሎት ዘመን እስከ የሚቀጥለው የባንኩ ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ድረስ ይሆናል፡፡
3. የማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተር የተሾመበት የአገልግሎት ጊዜ ሳያበቃ በማናቸውም ምክንያት ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ፣ ባንኩ ይኸንኑ ሁኔታ ለብሔራዊ ባንክ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

[148] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(17) መሰረት አንቀጽ 24 (3) ተሰርዞ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

## 26.የኦዲተሮች ተግባር

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 መሠረት የተሾመ የውጭ ኦዲተር ተግባሮች፣ ሌሎች በሕግ የተጣሉበት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባገኙ የኦዲት ደረጃዎች መሠረት የባንኩን ሂሣብ መርምሮ ያገኛቸውን ውጤቶችና የደረሰባቸውን ድምዳሜዎች ለባንኩ ባለ አክሲዮኖችና ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይሆናል፡፡[149]
2. ብሔራዊ ባንክ በውጭ ኦዲተሮች የሚሠራውን የኦዲት ሥራ ጥልቀትና ሽፋንን በሚመለከት ተጨማሪ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
3. በማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተር ሆኖ የተሾመ ሰው፣ በመደበኛ የሥራ ሂደትና ለሌላ ለማንኛውም ሰው ከሚሰጠው አገልግሎት ባልተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ በዚያው ባንክ ሂሣብ መያዝ ወይም ከባንኩ ማናቸውንም ዓይነት ብድር፣ የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሌላ አገልግሎት ማግኘት አይችልም፡፡

## 27. የኦዲት ሪፖርት

1. ብሔራዊ ባንክ የአንድ ባንክ የሂሣብ ዓመት ከተጠናቀቀ በኋላ በምን ያህል ጊዜ የኦዲት ሪፖርት መውጣት እንዳለበት በመመሪያ ይወስናል፡፡
2. የማንኛውም ባንክ ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተመረመሩትን የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም የኦዲት ግኝትና አስተያየት ያካተተ ሙሉ የኦዲት ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ብሔራዊ ባንክ የቀረበውን የኦዲት ሪፖርት ካላመነበት ድጋሚ የሂሣብ ምርመራ እንዲካሄድ ማዘዝ ወይም ሌላ የውጭ ኦዲተር በመሾም ሂሣቡ እንደገና እንዲመረመር ማድረግ ይችላል፡፡ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አዲስ የተሾመውን የውጭ ኦዲተር የአገልግሎት ክፍያ መሸፈን አለበት፡፡
4. የማንኛውም ባንክ የውጭ ኦዲተር የሂሣብ ምርመራ ተግባሩን በሚያካሂድበት ጊዜ፣
   ሀ) የዚህ አዋጅ፣ የሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎች በከፍተኛ ደረጃ መጣሳቸውን ወይም ያለመከበራቸውን፣
   ለ) በባንኩ ወይም በማናቸውም የባንኩ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ የማጭበርበር ወይም ሌላ የእምነት ማጉደል ወንጀል መፈጸሙን፣

[149] ለ20/81 (2006) አ. 847 አላማ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

ሐ) የባንኩን ካፒታል 25 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ መጠን የሚቀንስ ኪሣራ የደረሰ መሆኑን፣

መ) ባንኩ እንደቀጣይ ድርጅት ሥራውን ለማካሄድ ያለውን አቅም የሚጎዳ ወይም የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ከባድ የሆነ የአሠራር ጉድለት የተከሰተ መሆኑን፣ ወይም

ሠ) ሌሎች ከባድ የአሠራር ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች ተከስተው መገኘታቸውን፣

ሲደርስበት ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

5. ብሔራዊ ባንክ ማንኛውንም የባንክ የውጭ ኦዲተር ኦዲት የሚያደርገውን ባንክ የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ በማንኛውም ጊዜ ጠርቶ ውይይት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## መረጃ ስለመስጠትና በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ቁጥጥር

### 28. መረጃ ስለመስጠት

1. ማናቸውም ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚገባ የተፈረሙ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ሪፖርቶችን ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።

2. ማናቸውም ባንክ፣

   ሀ) በኦዲተር የተመረመረና የሥራ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎችን በሁሉም ባንኩ የሥራ ቦታዎች፣ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች ግልጽ በሆነ ቦታ ዓመቱን በሙሉ እንዲታዩ ማድረግ አለበት፤[150]

   ለ) የሂሣብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ማብራሪያ ጽሑፎችን አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ አሳትሞ ያወጣል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የፋይናንስ መግለጫዎችን ለሕዝብ እይታ ዝግጁ የማድረጉና በጋዜጣ አሳትሞ የማውጣቱ ተግባር የባለ አክሲዮኖች ዓመታዊ ጉባኤ በተካሄደ በሁለት ሣምንታት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ የዓመቱን ሂሳብ በዘጋ በአራት ወራት ውስጥ የፋይናንስ

[150] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(18) መሰረት ተሻሻለ፡፡

መግለጫዎቹን ለማጽደቅ መሰብሰብ ያለበት ሲሆን የፋይናንስ መግለጫዎችን ለሕዝብ እይታ ዝግጁ የማድረጉና በጋዜጣ አሳትሞ የማውጣቱ ተግባር የዳይሬክተሮች ቦርድ የፋይናንስ መግለጫዎችን ባጸደቀ በሁለት ሳምንታት ዉስጥ መፈጸም አለበት፡፡[151]

5. ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ከባንኮች መጠየቅና ማግኘት ይችላል፤ ሆኖም፦[152]

   ሀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም ሲባል፤

   ለ) የባንኮችን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ፤

   ሐ) በሕግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች፤

   መ) ብሔራዊ ባንክ ተጠሪ ለሆነለት አካል

   ሠ) በፍርድ ቤት በታዘዙ፤ ወይም

   ረ) ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ለመወጣት ሲባል፤ ካልሆነ በቀር እነዚህ መረጃዎች ለማንኛውም ሰው ተላልፈው አይሰጡም፡፡

6. የማናቸውም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሁኔታዎች በባንኩ ሲከሠቱ ወይም ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ ሲገምት ሁኔታውን በጋራም ሆነ በተናጠል ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፤

   ሀ) ለገንዘብ አሰቀማጮችና ለሌሎች አበዳሪዎች ያለበትን ግዴታ መወጣት የማይችል ሲሆን፣ ወይም

   ለ) ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች ክፍያዎችን በወቅቱ ለመፈጸም ሊሳነው የሚችል ከሆነ።

## 29. <u>በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ቁጥጥር፤</u>

1. ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ወይም በማናቸውም ጊዜ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማናቸውም ባንክ ላይ በቦታው ተገኝቶ ቁጥጥር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል።

2. ከጠቅላላው ገንዘብ አስቀማጮች በቁጥር አንድ አምስተኛ ወይም በባንኩ ዘንድ ካለው ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ አንድ ሦስተኛ አስቀማጭ የሆኑ አመልካቾች በአንድ ባንክ ላይ ቁጥጥር ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዳ መረጃ አያይዘው ጥያቄ

---

[151] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(19) መሰረት ከአንቀጽ 28 (3) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) ተጨምሮ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

[152] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(20) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ካቀረቡ፣ ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ የቀረበበት ባንክ በጤናማ ሁኔታ መገኘቱንና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ በመምራት ሂደት ውስጥ መከበራቸውን ለማረጋገጥ በሚስጥር ቁጥጥር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ለማድረግ ይችላል፡፡

3. በባንኮች ላይ የሚካሄድ የቁጥጥር ሥራ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በብሔራዊ ባንክ ባለሥልጣኖች ወይም ለዚህ ዓላማ ሲባል ብሔራዊ ባንክ በሚቀጥራቸው ሌሎች እምነት በሚጣልባቸውና ብቃት ባላቸው ሰዎች ሊካሄድ ይችላል፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር እንዲያካሂዱ የሚመድባቸው ሰዎች ቁጥጥሩን በሚገባ ለመፈጸም የሚያስችሏቸው የባንኩን መዝገቦችና አሠራሮች የሚመለከቱ መረጃዎችና መግለጫዎች የባንኩ ሠራተኞች እንዲሰጧቸው የመጠየቅ ሥልጣን ይኖራቸዋል።
5. በባንክ ቁጥጥር ሥራ ሂደት የተሰበሰቡ መረጃዎች ቁጥጥሩን ባካሄዱት ሰዎች በሚስጢር መጠበቅ አለባቸው።

## 30. <u>የቁጥጥር ሪፖርት</u>

1. የቁጥጥሩ የመጨረሻው ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት ለተመርማሪው ባንክ እንዲደርሰው ተደርጎ በሪፖርቱ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል።
2. ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የቁጥጥር ሪፖርት ይዘት፣
   ሀ) ቁጥጥሩን ባካሄዱት ሰዎች እንዲሁም ቁጥጥሩ በተደረገበት ባንክ ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች፣ እና
   ለ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም ወይም የሕዝብን ጥቅም ለማስከበር ሲባል ካልሆነ በቀር በብሔራዊ ባንክ፣ በምስጢር መጠበቅ አለበት፡፡

## 31. <u>የማስተካከያ እርምጃዎች</u>

በተደረገው ቁጥጥር ተመርማሪው ባንክ አግባብ ያላቸው ሕጎችና መመሪያዎችን ያልተከተለ ወይም በተሰጠው የባንክ ሥራ ፈቃድ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልፈጸመ መሆኑ፣ የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም በሚጎዳ ማናቸውም ተግባር ላይ ተሠማርቶ መገኘቱ ወይም በባንኩ ሥራ አመራር ላይ ከባድ ድክመት የተከሰተ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ፣

1. ከቁጥጥሩ የሚነሱ ወይም የተያያዙ ማናቸውንም ጉዳዮች በሚመለከት ለመነጋገር የባለአክሲዮኖች ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እንዲጠራ ወይም የዚህ

ባንክ የሥራ ኃላፊዎች ምርመራውን በሚመለከት የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችን እንዲያነጋግሩ ለማዘዝ፣

2. አንድ ወይም ከዚያ በላይ ኃላፊዎቹን በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በቦርዱ በተሰየመ ማናቸውም ኮሚቴ ወይም ሌላ አካል ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ለመወከልና አስተያየታቸው በስብሰባዎቹ ላይ እንዲሰማ ለማድረግ፣
3. ባንኩ ሊወስድ የሚገባውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በጽሑፍ ለማዘዝ፣
4. የባንኩን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች፣ ዋና የሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚዎች ከሥራ ለማገድ ወይም ለማሰናበት ወይም ለዚሁ ሲባል ባወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በነዚሁ ላይ የገንዘብ መቀጫ ለመወሰን፣
5. ባንኩ አዲስ ቅርንጫፎችን እና ንዑስ ቅርንጫፎችን እንዳይከፍት ለመከላከል፣[153]
6. የባንኩን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ለመገደብ፣ ለማዘግየት ወይም ለመከልከል፣
7. ባንኩ ለተወሰነ ጊዜ በከፊልም ሆነ በሙሉ የባንክ ሥራ እንዳይሠራ ለማዘዝ፣ ወይም
8. ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዲሆን ለማድረግ፣

ይችላል።

## ክፍል ስምንት

## ፈቃድ ስለመሠረዝ፣ ስለሞግዚት አስተዳደርና ስለመፍረስ

### 32. ፈቃድ ስለመሠረዝ

1. ብሔራዊ ባንክ በሚከተሉት ምክንያቶች የማናቸውንም ባንክ ፈቃድ ወዲያውኑ ሊሰርዝ ይችላል፣
   ሀ) የባንኩ ፈቃድ የተሰጠው በሀሰት ወይም በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመሥርቶ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም
   ለ) ባንኩ ፈቃዱ በተሰጠው በ12 ወራት ውስጥ ሥራውን ያልጀመረ እንደሆነ፣
   ሐ) ባንኩ የገንዘብ አከል ንብረት እጥረት ሲያጋጥመው፣[154]
   መ) ባንኩ ዕዳ መክፈል ወደማይችልበት ወሰን ሲደርስ፤ ወይም
   ሠ) ባንኩ ሕግንና መመሪያን አክብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፤

[153] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(21) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[154] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(22) መሰረት አንቀጽ 32(1)(ለ) ቀጥሎ አዳዲስ ፊደል ተራ (ሐ)፣(መ) እና (ሠ) ተጨምረዋል፤

2. ብሔራዊ ባንክ የማናቸውንም ባንክ ፈቃድ እንዲሰረዝ ሲወስን ፈቃዱ የተሰረዘበት ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ በሰፊው በሚሠራጭ ጋዜጣ ውሳኔውን አሳትሞ ያወጣል።
3. ፈቃድ የመሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ወይም ብሔራዊ ባንክ ከሚወስነው ማናቸውም ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።
4. ፈቃዱ የተሰረዘበት ባንክ የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ማናቸውንም ዓይነት የባንክ ሥራ መሥራት አይችልም።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /1//ለ/ መሠረት ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለመሰረዝ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለከት ይችላል፡፡

33. <u>ሞግዚት ስለመሾም</u>

1. ብሔራዊ ባንክ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች በአንድ ባንክ መኖራቸውን ሲያምን ባንኩን ተረክቦ የሚቆጣጠር ሞግዚት ይሾማል፣
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት የባንኩ ፈቃድ የተሰረዘ ከሆነ፣
   ለ) ባንኩ ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን የደረሰ ከሆነ፣
   ሐ) ሕግን፣ መመሪያን በመተላለፍ ወይም ጥንቃቄ በጎደለው አሠራር ምክንያት በቀላሉ የማይገመት የሀብት ወይም የገቢ ብክነት የተከሠተ እንደሆነ፣[155]
   መ) ባንኩ ሥራውን እያካሄደ ያለው የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም አደጋ ላይ ሊጥል በሚችል ጤናማ ባልሆነና ጥንቃቄ በጎደለው የአሰራር ሁኔታ ከሆነ፣
   ሠ) በብሔራዊ ባንክ የተጣለውን ማናቸውንም ገደብ ባንኩ ሆነ ብሎ የጣሰ ከሆነ፣
   ረ) ባንኩ የሂሳብ መዝገቦችን፣ ሰነዶችን ወይም ሪከርዶችን ሥልጣን ለተሰጠው የብሔራዊ ባንክ ተቆጣጣሪ ወይም ወኪል ለቁጥጥር ተግባር ለማቅረብ እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፣
   ሰ) ባንኩ በመደበኛ የሥራ ሂደት ግዴታዎቹን ለመወጣት ወይም የገንዘብ አስቀማጮችን ጥያቄ ለማሟላት አይችልም የሚል ጠንካራ ግምት ሊኖር ከቻለ፣
   ሸ) ባንኩ ካፒታሉን በሙሉ ወይም የካፒታሉን አብዛኛውን ክፍል የሚያመናምን ኪሳራ የደረሰበት ወይም እንደሚደርስበት የሚገመት ከሆነ፣

[155] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(23) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ቀ) ባንኩ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነውን አነስተኛ የካፒታል መጠን የማያሟላ ከሆነ፣

በ) ባንኩ በቂ ካፒታል የሌለውና ወደፊትም ካፒታሉን በሚያስፈልገው መጠን ለመጨመር አቅም እንደማይኖረው የሚገመት ከሆነ፣

ተ) ባንኩ በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ካፒታሉን በሚያስፈልገው በቂ መጠን መጨመር ያልቻለ እንደሆነ ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካፒታሉን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ዕቅድ ያላቀረበ እንደሆነ፣

ቸ) ባንኩ ለብሔራዊ ባንክ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ካፒታልን መልሶ የመገንባት ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣

ነ) ባንኩ ተገቢ ያልሆነ፣ ሕገወጥ ወይም ጥንቃቄ የጎደላቸው ተግባሮችን በማከናወን የሃገሪቱን ወይም የሕዝቡን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥሉ ፖሊሲዎች የተከተለ ከሆነ፣

ኘ) ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ከሌላ ባንክ ጋር የተቀላቀለ እንደሆነ፣

አ) በብሔራዊ ባንክ የወጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዳይሬክተሮችን፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎችን መሾም ያልቻለ እንደሆነ፣

ከ) በባለአክሲዮኖች ውሳኔ ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዲሆን ከተጠየቀ ወይም ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት የባንኩ ባለሀብቶች ባንኩን ለማፍረስ የወሰኑ እንደሆነ፣ ወይም

ወ) ባንኩ እንደ አንድ ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ሕጋዊ ተቋም መቀጠል የተሳነው እንደሆነ።

2. ብሔራዊ ባንክ ለአንድ ባንክ ሞግዚት መሾሙን፣ ለሹመቱ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ፣ የሞግዚቱን ስም፣ ሹመቱ የሚፀናበትን ቀንና ማናቸውንም ሌሎች አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በመጥቀስ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ላይ አሳትሞ ያወጣል።

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሾመ ማንኛውም ሞግዚት ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ባንክ ይሆናል፡፡

4. ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እራሱ በሞግዚትነት ሊሰራ ይችላል፡፡

## 34. ለሞግዚትነት የሚያበቁ መስፈርቶች

1. በብሔራዊ ባንክ የሚሾም ማንኛውም ሞግዚት በብሔራዊ ባንክ አስተያየት ከፍተኛ የሙያ ብቃትና ታማኝነት ያለው ሰው መሆን አለበት።
2. ሞግዚቱ የንግድ ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ፤
   ሀ) የሞግዚት አስተዳደሩን በበላይነት የሚመራው ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን መስፈርት ማሟላት፣ እና
   ለ) ድርጅቱ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ወይም ባንክ ማቅረብ፣ አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም በሞግዚትነት የሚሾም ሰው ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣቸውን ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

## 35. የሞግዚት የአገልግሎት ክፍያዎች

1. ለሞግዚት የሚፈጸም የአገልግሎት ክፍያ መጠን በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል፡፡
2. የሞግዚት የአገልግሎት ክፍያ በሞግዚት አስተዳደር ሥር በሆነው ባንክ እጅ በሚገኝ ገንዘብ ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የባንኩ ንብረት ተሸጦ በሚገኝ ገቢ ይሸፈናል፡፡

## 36. የሞግዚትነት አስተዳደር የሚቆይበት ጊዜ

1. ብሔራዊ ባንክ የማንኛውም ባንክ የሞግዚትነት አስተዳደር የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም፣ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም የባንክ ሞግዚት የተጣለበትን ኃላፊነት አጥጋቢ በሆነ መንገድ አልተወጣም ብሎ ሲያምን በማናቸውም ጊዜ ከሥራ ሊያሰናብተው ይችላል።
3. ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳደር የሥራ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ወይም ሞግዚቱ ከሥራ እንደተሰናበተ ወዲያውኑ ይህንኑ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ አሳትሞ ያወጣል።

## 37. የሞግዚት አስተዳደር ስር መዋል የሚያስከትለው ውጤት

ማንኛውም ባንክ ሞግዚት እንደተሾመለት ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33/2/ መሠረት በጋዜጣ እንዳስታወቀ፣

1. ከሞግዚት ቅድሚያ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር በሞግዚት አስተዳደር ሥር በዋለው ባንክ ስም ምንም ዓይነት እርምጃ ሊወሰድ አይችልም፣
2. የባለአክሲዮኖች፣ የዳይሬክተሮችና የሌሎች የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች ሥልጣን ታግዶ ለሞግዚቱ ይተላለፋል፣
3. የባንኩ መብትና ሥልጣን እንዲሁም ማንኛውም ገንዘብ አስቀማጭ ወይም አበዳሪ በባንኩ ወይም በባንኩ ንብረቶች ላይ ያለው መብትና ሥልጣን ወዲያውኑ ወደ ሞግዚቱ ይተላለፋሉ፣
4. ሞግዚቱ የባንኩን ንብረቶችና መዛግብት በሙሉ ተረክቦ ባለአክሲዮኖች፣ ዳይሬክተሮችና ሥራ አስፈጻሚዎች በነበራቸው ሥልጣን መሠረት ባንኩን ያስተዳድራል፤ የባንኩንም ሥራ አጠቃልሎ ይሠራል፤[156]
5. የባንኩን የክፍያ ጥያቄ ወይም መብት በይርጋ ሊያሳግድና ሊያስቀር የሚችል ማንኛውም በሕግ፣ በውል ወይም በሌላ ሁኔታ የተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሚያበቃበት ጊዜ ጀምሮ ለስድስት ወራት ይራዘማል፣
6. ማናቸውም በባንኩ ንብረትና ሀብት ላይ የተጣለ የፍርድ ቤት እግድ ወይም በባንኩ የተሰጠ ዋስትና ይሻራል፣ እንዲሁም ባንኩ በሞግዚት አስተዳደሩ ሥር በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ በባንኩ ንብረት ላይ አዲስ የፍርድ ቤት እግድ ሊተላለፍ ወይም ዋስትና ሊሰጥ አይችልም፣ ሆኖም ይህ ድንጋጌ፤
   ሀ) ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ከዋለበት ቀን ከስድስት ወራት በፊት፣ ወይም ለባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ ጥቅም ከሆነ ከ12 ወራት በፊት፣ በተሰጠ የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ወይም ዋስትና፣
   ለ) በሞግዚት ጥያቄ በፍርድ ቤት በተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ወይም በሞግዚቱ በተሰጠ ዋስትና፣ እና
   ሐ) መጠኑ ብሔራዊ ባንክ ለዚሁ ዓላማ ሲባል ባወጣው መመሪያ ከተወሰነው ጣሪያ በላይ እስካልሆነ ድረስ የሞግዚት አስተዳደሩ ከፀናበት ቀን በፊት በፍርድ ቤት ተወስኖ የአፈጻጸም ትዕዛዝ በተሰጠበት ጉዳይ፣ ላይ ተፈጻሚ  አይሆንም።
7. የሞግዚት አስተዳደሩ ከጸናበት ቀን አስቀድሞ ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ፣ ወይም ለባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ሰራተኛ ወይም ሸሪክ ከሆነ በ12 ወራት ውስጥ፣ የተፈጸመ ማናቸውም ክፍያ ወይም የንብረት ማስተላለፍ ከሌሎች የባንኩ አበዳሪዎች

[156] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(24) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ወይም አስቀማጮች የተለየ ጥቅም የሚያስጥ ከሆነ ሊጸና አይችልም፣ ሆኖም ይህ ድንጋጌ፤

ሀ) መጠኑ በብሔራዊ ባንክ ለዚሁ ዓላማ ሲባል ባወጣው መመሪያ ከተወሰነው ጣሪያ በማይበልጥ ለእያንዳንዱ አስቀማጭ በተከፈለው የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ፣

ለ) የንብረቱን የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ተመጣጣኝ ጥቅም ለባንኩ ለማስገኘት በተደረገ የንብረት ማስተላለፍ፣ እና

ሐ) የቦነስንና ሌሎች ልዩ ክፍያዎችን ሳይጨምር፣ ለባንኩ ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች በተፈጸመ መደበኛ ክፍያና ጥቅማጥቅም፣

ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 38. የሞግዚት መሾምን በመቃወም ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 /2/ መሠረት ሞግዚት ስለመሾሙ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ከባንኩ አክሲዮኖች ቢያንስ 25 በመቶ የመምረጥ መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች የሞግዚቱን መሾም በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት አቤቱታ ከቀረበ፤

   ሀ) ፍርድ ቤቱ በአቤቱታው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የሞግዚት አስተዳደሩ ይቀጥላል፣

   ለ) ፍርድ ቤቱ አቤቱታው በቀረበ በ10 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ይሰማል፣ ምርመራውም በተጠናቀቀ በ20 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብ በፍርድ ቤቱ መታየት የሚችለው ጭብጥ ብሔራዊ ባንክ ሞግዚቱን የሾመው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 ከተደነገጉት መስፈርቶች አንጻር ሲታይ በዘፈቀደና በግዴለሽነት መሆን አለመሆኑ ብቻ ነው።
4. ፍርድ ቤቱ ብሔራዊ ባንክ ሞግዚቱን የሾመው፤

   ሀ) በዘፈቀደና በግዴለሽነት ነው ብሎ ከወሰነ የሞግዚቱ ሹመት እንዲቋረጥ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ ወይም

   ለ) በዘፈቀደና በግዴለሽነት አይደለም ብሎ ከወሰነ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ የሞግዚት አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጥላል።

## 39. የሞግዚት ሥልጣንና ተግባር

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 መሠረት የተሾመ ሞግዚት በሞግዚት አስተዳደር ሥር የዋለውን ባንክ የማስተዳደርና የመቆጣጠር ሙሉና ብቸኛ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሞግዚቱ ሥልጣን የሚከተሉትን ይጨምራል፤
   - ሀ) ማናቸውንም የባንኩን ሥራ የመቀጠል ወይም የማቋረጥ፣
   - ለ) የባንኩን ንብረቶች የመሸጥ፣
   - ሐ) ብሔራዊ ባንክ ስለጉዳዩ በሚያወጣው መመሪያ የሚጥላቸው ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የባንኩን ንብረት በማስያዝም ሆነ ሳያሲዝ ገንዘብ የመበደር፣
   - መ) ባንኩ ያለበትን ማናቸውንም የክፍያ ግዴታዎች የማቋረጥ ወይም የመገደብ፣
   - ሠ) በባንኩ ዕዳዎች ላይ የሚከፈሉ የወለድ ተመኖች እንደገና የመወሰን ሆኖም ተመኖቹ በጊዜው አግባብ ባለው ገበያ ላይ ካሉት የወለድ ተመኖች ያነሱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡
   - ረ) በማናቸውም የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብና ሌሎች ዕዳዎች ላይ ወለድ መታሰብ የሚቋረጥበትን ቀን የመወሰን፣
   - ሰ) ማንኛውንም አስፈላጊ የሆነ ባለሙያ ወይም አማካሪ የመቅጠር፣
   - ሸ) ባንኩ ተዋዋይ ወገን የሆነባቸውን የሥራ ወይም የአገልግሎት ወይም የኪራይም ወይም ሌሎች ውሎችን የማቋረጥ፣
   - ቀ) ባንኩንና የሥራ እንቅስቃሴዎቹን በተመለከተ ለወትሮው በሚስጥር ሊያዙ ይችሉ የነበሩ መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ መረጃ ይፋ ሊደረግ የሚችለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 ወይም 41 የተገለጹትን እርምጃዎች ለመውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፣
   - በ) በባንኩ ስም ማናቸውንም ክፍያ መፈጸምና የክፍያ ሰነድ ማውጣት፣ ማናቸውንም ክስ መመስረት ወይም መከላከልና ማናቸውንም ሌላ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ፣
3. ብሔራዊ ባንክ ሞግዚት ሲሾም ሞግዚቱ በቅድሚያ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ ሊወስዳቸው የማይችላቸውን እርምጃዎችና ሞግዚቱ እንዲህ ዓይነቱን ፈቃድ ሲጠይቅ ባንኩ መልስ የሚሰጥበትን የጊዜ ገደብ ሊወስን ይችላል።

40. **<u>የሞግዚት አስተዳደርን ለማጠናቀቅ ስለሚወሰዱ አማራጭ እርምጃዎች</u>**

1. ማንኛውም የባንክ ሞግዚት፤

   ሀ) የባንኩ ሥራ መቀጠል አዋጪ ሆኖ ካገኘው የሞግዚት አስተዳደሩ ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ የባንኩ መደበኛ ሥራ እንዲቀጥል በማድረግ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው ሁኔታና ግዴታ መሠረት ባንኩን ለቀድሞ ባለቤቶቹና ወይም ለቀድሞ ባለቤቶቹና ለሸሪኮቻቸው እንዲመለስ ማድረግ፣ ወይም

   ለ) የባንኩ ሥራ መቀጠሉ አዋጪ ሆኖ ካላገኘው ባንኩን በመሸጥ፣ ከሌላ ባንክ ጋር በመቀላቀል ወይም በማፍረስ የባንኩ ሥራ እንዲቋረጥ ማድረግ፣ ይችላል፡፡

2. በሞግዚቱ የተወሰደው አማራጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ የተመለከተው ከሆነ፣ ብሔራዊ ባንክ የባንኩን የሥራ ፈቃድ ወዲያውኑ ይሰርዛል፤ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46 መሠረት የሞግዚት አስተዳደሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ባንኩ በስሙ በስተመጨረሻው ላይ "በመፍረስ ላይ ያለ" የሚል ሐረግ ተጨምሮበት ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቆያል፡፡

41. **<u>የባንኩ ስራ መቀጠል አዋጪ ሳይሆን ሲቀር በሞግዚቱ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>**

1. የባንኩ ስራ መቀጠል አዋጪ ሳይሆን ሲቀር ሞግዚቱ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው ግዜ ውስጥ፤

   ሀ) አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሌሎች ባንኮች የባንኩን ንብረቶችና ግዴታዎች በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወስዱ ያደርጋል፣ ወይም

   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 42 እስከ 45 በተደነገገው መሰረት የባንኩን ንብረቶች ሸጦ ያከፋፍላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው መሰረት ሞግዚቱ ከሁለቱ አማራጮች አንዱን እርምጃ ለመውሰድ በሚወስንበት ግዜ በእርሱ አስተያየት የባንኩ ሀብት ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጣ የሚችልበትንና የገንዘብ አስቀማጮችንና የሌሎች አበዳሪዎችን ጥቅም ለማስከበር የተሻለውን አማራጭ መውሰድ አለበት፡፡

3. ሞግዚቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የመረጠውን እርምጃ ከመውሰዱ በፊቱ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለማግኘት በፅሁፍ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ ብሔራዊ ባንክም ጥያቄው በቀረበ በአስር ቀናት ውስጥ የተመረጠውን እርምጃ መፍቀዱን ወይም አለመፍቀዱን ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ሞግዚቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ መሰረት የባንኩን ንብረቶችና እዳዎች ሲያስተላልፍ፤
   ሀ) በራሱ አስተያየት ማንኛውም የባንኩ ገንዘብ አስቀማጭ ወይም ሌላ አበዳሪ የሚያገኘው የገንዘብ ድርሻ በዚህ አዋጅ ከአንቀፅ 42 እስከ 45 በተደነገገው መሰረት የባንኩ ንብረት ተሽጦ ከሚደርሰው ገንዘብ የማያንስ ሆኖ ከተገኘ የባንኩን ዕዳዎች ዋጋ ሊቀንስ፣ እና
   ለ) ማንኛውም ገንዘብ አስቀማጭ በባንኩ ያለውን ተቀማጭ ገንዘብ ከባንኩ ለተበደረውና ላልከፈለው ገንዘብ ማቻቻያ ሊያደርገው፣ ይችላል፡፡

42.<u>ባንክ ሲፈርስ በቅድሚያ ስለሚፈጸሙ ሥርዓቶች</u>

ማንኛውም ባንክ ሲፈርስ ሞግዚቱ በቅድሚያ፤

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41/1/ መሠረት ወደ ሌላ ባንክ የሚተላለፉትን ወይም በማጣሪያ የሚሸጡትን የባንኩን ሀብቶች የሚያሳይ ዝርዝር አዘጋጅቶ የዝርዝሩን ቅጂ ለሕዝብ ዕይታ ክፍት ያደርጋል፣
2. በአደራ የተቀመጡ ሀብቶችን ለባለቤቶቻቸው ለመመለስና የባንኩን የአደራ ሂሣቦች ለመዝጋት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣
3. በባንኩ መዛግብት መሠረት ማንኛውም ሰው ከባንኩ ስለሚፈልገው ዕዳ የሂሳብ መግለጫ አዘጋጅቶ ይሰጣል፣ ከዚሁ ጋር በማያያዝ በሂሣብ መግለጫው ላይ ተቃውሞ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞውን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ ጊዜ ውስጥ ለሞግዚቱ ማቅረብ እንደሚችል ማሳሰቢያ ይሰጣል።

43.<u>በይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42/3/ ከተመለከተው የተቃውሞ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በኋላ ባሉት ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሞግዚቱ፤
   ሀ) በቀረበው የይገባኛል ጥያቄ አግባብነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው የይገባኛል ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፣
   ለ) የእያንዳንዱ ገንዘብ አስቀማጭና ሌላ አበዳሪ ሊከፈለው የሚገባውን የገንዘብ ልክና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 ድንጋጌ መሠረት የክፍያውን ቅደም ተከተል ይወስናል፣
   ሐ) የተፈቀዱትን የይገባኛል ጥያቄዎች የሚያሳይ ፕሮግራም ያዘጋጃል።

2. ሞግዚቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/ የተጠቀሰው ፕሮግራም ለዕይታ የሚቀርብበትን ቀንና ቦታ እንዲሁም በፕሮግራሙ ላይ ተቃውሞ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ ማንኛውም የባንኩ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ባለበት አካባቢ በሰፊው በሚሰራጭ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጋዜጦች ላይ በሣምንት አንድ ጊዜ ለሦስት ተከታታይ ሣምንታት አሳትሞ ያወጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ በተጠቀሰው ማስታወቂያ የሚገለጸው ተቃውሞ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ የመጨረሻው ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ20 ቀናት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡
4. የይገባኛል ጥያቄው ሙሉ በሙሉ ያልተመለሰለት ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተጠቀሰው መረጃ በቀጥታ እንዲደርሰው ሞግዚቱ የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል፡፡

44. <u>ስለተፈቀዱ የይገባኛል ጥያቄዎች የመጨረሻ ፕሮግራምና ድልድል</u>

1. ማንኛውም የባንኩ ገንዘብ አስቀማጭ ወይም አበዳሪ ወይም ባለአክሲዮን የተፈቀዱ የይገባኛል ጥያቄዎች ፕሮግራም ይዘትን በተመለከተ የሚኖረውን ተቃውሞ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43/2/ መሠረት ይፋ ከተደረገው ተቃውሞዎችን የማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በፊት በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ሞግዚቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ተቃውሞ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በተቃውሞው ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
3. ሞግዚቱ ተቀባይነት ያገኙ ተቃውሞዎችን መሠረት በማድረግ የመጨረሻውን ፕሮግራም ያዘጋጃል። የመጨረሻውን ፕሮግራም ቅጅም ለብሔራዊ ባንክ ያቀርባል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የመጨረሻው ፕሮግራም ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ሞግዚቱ በተቻለ ፍጥነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የመጨረሻውን ድልድል ማድረግ አለበት፡፡

45. <u>የይገባኛል ጥያቄዎች አከፋፈል ቅደም ተከተል</u>

1. በማናቸውም የባንክ ንብረት የማጣራት ተግባር በዋስትና የተጠበቁ የይገባኛል ጥያቄዎች ካሉ በተገባላቸው ግዴታ መሠረት መከፈል አለባቸው። ሌሎች በባንኩ ጠቅላላ ሀብት ላይ የሚቀርቡ የይገባኛል ጥያቄዎች አከፋፈል በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

ሀ) ለሞግዚቱ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያና ሞግዚቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም ያወጣቸው አስፈላጊና አግባብ ያላቸው ወጪዎች፣ ሆኖም ብሔራዊ ባንክ ሞግዚት ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ የሞግዚትነት ተግባሩን ለመፈጸም ያወጣው ወጪ ብቻ ታስቦ ተመላሽ ይሆንለታል፣

ለ) ሞግዚቱ ከተሾመ በኋላ ለባንኩ አዲስ ብድር የሰጡ አበዳሪዎች፣

ሐ) የሞግዚቱ ሹመት ከፀናበት ቀን በፊት ባለው የሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ የባንኩን የሥራ አስፈጻሚዎች ሳይጨምር የሌሎች ሠራተኞች ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች፣ ሆኖም የዚህ ዓይነቱ ክፍያ፤

1) ጉርሻን ወይም ከሚጠበቀውና ከመደበኛው በላይ የሆኑ ክፍያዎችን፣ እና

2) ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ይሆናል በሚል ግምት አላግባብ የተጨመሩ ክፍያዎችን፣ አያጠቃልልም፣

መ) ተቀማጭ ገንዘቦች፣

ሠ) ለፌዴራልና ለክልል መንግሥታት መከፈል ያለበት ታክስ፣

ረ) በባንኩ ላይ የሚቀርቡ ሌሎች የይገባኛል ጥያቄዎች፣

ሰ) ሞግዚቱ በሚወስነው ተመን መሠረት በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተመለከቱት የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ የሚከፈል ወለድ።

2. ባንኩ ያለው የሀብት መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተዘረዘሩትን የይገባኛል ጥያቄዎች በሙሉ ለመክፈል በቂ ሆኖ ሲገኝ፣ ቀሪው ሀብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42/3/ መሠረት በጊዜው ማመልከቻ ላልቀረበባቸውና ተቀባይነት ላላቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ክፍያ ይውላል።

3. ያለው ገንዘብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተው በማንኛውም የቅደም ተከተል ደረጃ ሥር ያሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን ሙሉ በሙሉ ለማስተናገድ በቂ በማይሆንበት ጊዜ በዚያ ደረጃ ውስጥ ላሉት የይገባኛል ጥያቄዎች ተመጣጣኝ በሆነ ስሌት መከፈል አለበት፡፡

4. ሁሉም ተቀባይነት ያገኙ የይገባኛል ጥያቄዎች ከተከፈሉ በኋላ ተራፊው የባንኩ ሀብት በባንኩ ውስጥ ባላቸው የባለቤትነት ድርሻ መሠረት ለባለአክሲዮኖች ይከፋፈላል።

46. <u>ስለሞግዚት አስተዳደር መጠናቀቅ</u>

1. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የባንኩ ንብረቶች በሙሉ ተሸጠው ከተከፋፈሉ በኋላ ሞግዚቱ በአስተዳደሩ ወቅት ስለተከናወኑት ሥራዎች ሪፖርት አዘጋጅቶ ለብሔራዊ ባንክ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት። ብሔራዊ ባንክም የጸደቀውን ሪፖርት ወዲያውኑ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ሪፖርት ለሕዝብ ይፋ እንደተደረገ የሞግዚት አስተዳደሩ እንደተጠናቀቀ ይቆጠራል፤ በመፍረስ ላይ የሚገኘው ባንክም ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ ሞግዚቱ ማመልከቻ ያቀርባል።
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 መሠረት ክስ ካልተመሰረተ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ሪፖርት ለሕዝብ ይፋ በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ሞግዚቱና ብሔራዊ ባንክ ከሞግዚት አስተዳደሩ ጋር ከተያያዙ ማናቸውም ግዴታዎች ነፃ ይሆናሉ።
4. ጥያቄ ቀርቦባቸውና ተፈቅደው ያልተከፈሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን የሚመለከት ገንዘብ ካለ በብሔራዊ ባንክ ዘንድ ይቀመጣል። ሆኖም ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳደሩ ካበቃበት ቀን ጀምሮ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከተቀመጠው ገንዘብ ጋር ከተያያዘ ማናቸውም የይገባኛል ጥያቄ ነፃ ይሆናል፡፡

47. <u>በሞግዚት እርምጃዎች ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>

1. ማንኛውም የባንክ ሞግዚት በወሰደው እርምጃ ላይ እርምጃው በተወሰደ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት የሚከተሉት ሰዎች ብቻ ናቸው፤
   ሀ) ከጠቅላላው ተቀማጭ ገንዘብ ቢያንስ 25 በመቶ ድርሻ ያላቸው ሰዎች፣
   ለ) ገንዘብ አስቀማጮችን ሳይጨምር ከጠቅላላው የይገባኛል ጥያቄ ካላቸው ሰዎች ቢያንስ 50 በመቶ ያህል ድርሻ ያላቸው አበዳሪዎች፤ ወይም፣
   ሐ) ከጠቅላላው የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ቢያንስ 25 በመቶ ድርሻ የያዙ የባንኩ ባለአክሲዮኖች።
3. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ ሲመረምር ሊያይ የሚችለው ጭብጥ ሞግዚቱ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተግባሩን ሲፈጽም በፍጹም ግዴለሽነትና በዘፈቀደ የሠራ መሆን አለመሆኑን ብቻ ይሆናል፡፡

4. ሞግዚቱ ተግባሩን ያከናወነው በፍጹም ግዴለሽነትና በዘፈቀደ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲወስን ሞግዚቱ ካሣ እንዲከፍል ሊያዘው ይችላል፣ ሆኖም ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው የሞግዚቱ ድርጊት የሚለወጥ አይሆንም፡፡
5. ሞግዚቱ ተግባሩን ያከናወነው በፍጹም ግዴለሽነትና በዘፈቀደ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ ሞግዚቱ ክሱን ለመከላከል ያወጣቸውን ወጪዎች አቤቱታ አቅራቢዎቹ እንዲከፍሉ ያዛል።

48. <u>ስለሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

የንግድ ሕግና አግባብ ያላቸው ሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ በሞግዚት አስተዳደርና የባንክ መፍረስ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

49. <u>ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ ስለደረሰ ባንክ</u>

ማናቸውም ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ የደረሰ ባንክ ተቀማጭ ገንዘብ መሰብሰብ አይችልም።

50. <u>የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ስለመሠማራት</u>

ባንኮች የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ላይ ሊሠማሩ የሚችሉበት ሁኔታ በብሔራዊ ባንክ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

51. <u>ስለቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ</u>

ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር የሚያካሂድባቸው ባንኮች ቁጥጥሩን ለማካሄድ የወጣውን ወጪ እንዲሸፍኑ ለዚህ ጉዳይ ሲባል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሊያዝ ይችላል፡፡

52. <u>የይገባኛል ጥያቄ ስላልቀረበባቸው ተከፋይ ሂሳቦች[157]</u>

1. ለ15 ተከታታይ ዓመታት የይገባኛል ጥያቄ ያልቀረበበትን፣ በዋና ገንዘቡ ላይ የመጨመር ወይም የመቀነስ እንቅስቃሴ ያልታየበትን፣ የባንክ ደብተር ወይም ሌላ የጽሑፍ መረጃ ያልቀረበበትን ወይም የደብዳቤ ልውውጥ ያልተደረገበትን ተከፋይ ሂሣብ የያዘ ማንኛውም ባንክ በዚሁ ሂሣብ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ለብሔራዊ ባንክ ማስተላለፍ አለበት፡፡

[157] በ25/88(2011) አ. 1159 አንቀፅ 2(25) መሰረት ከአዋጁ አንቀጽ 52 ቀጥሎ አዲስ አንቀጾች፣ 53፣ 54፣ 55፣ 56፣ 57፣ 58 እና 59 ተጨምረው ከአንቀጽ 53 እስከ 61 ያሉት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 59 እስከ 67 ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

2. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሊተላለፍለት የሚገባውን ዝቅተኛ የገንዘብ መጠንና ባንኮች የዚህ ዓይነቱን ገንዘብ ሲያስተላልፉ ሊከተሉ የሚገባቸውን ሥርዓት በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡
3. ማናቸውም ባንክ የይገባኛል ጥያቄ ያልቀረበበትን ተከፋይ ሂሳብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለብሔራዊ ባንክ ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ በዕዳው ከመጠየቅ ሙሉ በሙሉ ነፃ ይሆናል፡፡
4. ማንኛውም ሕጋዊ ባለመብት ጥያቄ ከአቀረበ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተላለፈውን ሙሉውን ገንዘብ ለባለመብቱ መከፈል አለበት፣ ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ብሔራዊ ባንክ ወለድ አይከፍልም።
5. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተላለፉትንና በሕጋዊ ባለመብቶቹ ጥያቄ ያልቀረበባቸውን ሂሣቦች አጠቃቀም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

53. <u>የደህንነት ደረጃዎች</u>

ባንኮች ማሟላት ስለሚገባቸው የደህንነት ደረጃዎች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

54.<u>ማስታወቂያ ስለማዉጣት</u>

ማናቸዉም ባንክ በማንኛውም ጊዜ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሐሰተኛ፣ አሳሳች፣ አደናጋሪ ወይም የሌላውን ጥቅም የሚጎዳ የተከፈለበትን የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ማስታወቂያ፣ ፖስተር፣ ቢል ቦርድ፣ በራሪ ወረቀት፣ ሠርኩላር ወይም ሌላ ሰነድ እና የተከፈለበትን የጋዜጣና የመጽሔት ማስታወቂያ አውጥቶ ቢገኝ ባንኩ ማስታወቂያውን እንዲያቋርጥ፣ እንዲያሻሽል ወይም ከማስተዋወቅ እንዲቆጠብ ብሔራዊ ባንክ ሊያዘው ይችላል፡፡

55.<u>ዋናና ወሳኝ ሥራን በዉጭ አካላት ስለማሠራት</u>

ባንኮች ዋናና ወሳኝ ሥራቸውን በውጭ አካላት ስለሚያሠሩበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ዋናና ወሳኝ ሥራ" ማለት ተቀማጭ ማሰባሰብን፣ ብድር መስጠትን፣ ሐዋላን፣ ዓለም አቀፍ የባንክ አገልግሎትን እና በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑትን ሌሎች ሥራዎች ያጠቃልላል፡፡

56.<u>የባንክ አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ስለማድረግ</u>

1. ባንኮች የሚያቀርቡት አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆን አለበት፡፡

2. ባንኮች የሚያቀርቡት አገልግሎት አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ ስለሚሆንበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ እንደ አስፈላጊነቱ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

57.**ስለ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ**

የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል መመሪያ ብሔራዊ ባንክ ሊያወጣ ይችላል፡፡

58.**በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት**

በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት ስለሚሰጥበት ሁኔታ በብሔራዊ ባንክ መመሪያው ይወሰናል፡፡

59.**ከወለድ ነጻ የባንክ ስራ**

1. በዚህ አዋጅ የባንክ ስራ ለመስራት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ብሔራዊ ባንክ ከወለድ ነጻ ባንክ ለማቋቋም፣ ፈቃድ ስለሚሰጥበትና ቁጥጥር ስለሚካሄድበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡ለዚህ ንዑስ አንቀጽ "ወለድ ነጻ ባንክ" ማለት ከወለድ ነጻ የባንክ ስራ ብቻ እንዲሰራ በብሄራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛው የባንክ ስራ ጋር ከወለድ ነጻ ተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር የተያያዘ የባንክ ሥራዎችን ለመቆጣጠር መመሪያ ያወጣል።

60.**የደንበኞችን ማንነት ስለማወቅ**

ባንኮች የደንበኞቻቸውን ማንነት በትጋት ተከታትለው የሚያውቁባቸውንና አጠራጣሪ የሂሣብ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት የሚያደርጉባቸውን መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

61. **የባንኮችና የመድን ኩባንያዎች ግንኙነት**

1. ብድር መስጠትን፣ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበልንና የባንክና የመድን አገልግሎቶችን ጨምሮ በባንኮችና በመድን ኩባንያዎች መካከል የሚደረጉ የሥራ ግንኙነቶች በማናቸውም ረገድ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር ከሚደረጉት የሥራ ግንኙነቶች ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ሁኔታዎች መደረግ አለባቸው።
2. ብሔራዊ ባንክ በባንኮችና በመድን ኩባንያዎች መካከል የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት የሚመለከቱ መመሪያዎችን በየጊዜው ሊያወጣ ይችላል፡፡

62. <u>መረጃዎችን እንዲታተሙ ስለማድረግ</u>

ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበን ወይም የተሰበሰበን ማናቸውንም መረጃ ወይም ስታትስቲካዊ አሐዞች በከፊልም ሆነ በሙሉ አግባብ ነው ብሎ በአመነበት አቀራረብና ጊዜ አሳትሞ ሊያወጣ ይችላል፣ ሆኖም የጉዳዩ ይፋ መሆን የባንክ ሥርዓቱን ጤናማነት ለማጠናከር ሲባል የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር፣ የማናቸውንም ባንክ ወይም ደንበኛ ዝርዝር መረጃ ወይም ስታትስቲካዊ አሐዞች ይፋ ሊያደርግ አይችልም።

63. <u>የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችና ተጠሪዎች ከግል ተጠያቂነት ስለመጠበቃቸው</u>

ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሲባል የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችና ተጠሪዎች በቅን ልቦና ለሚፈጽሙት ማናቸውም ድርጊት በግል በዕዳ ሊጠየቁ፣ ሊከሰሱ ወይም ማናቸውም ሌላ ጥያቄ ሊቀርብባቸው አይችልም።

64. <u>የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት</u>

ብሔራዊ ባንክ በባንኮች መካከል የሚደረግ የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ስለሚደራጅበት ሁኔታ፣ ስለአሠራሩና የወጪ መጋራት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

65. <u>ቅጣት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3/1/ የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው የጥፋት ድርጊቱ ለቀጠለበት ለእያንዳንዱ ቀን በብር 20,000 መቀጫ እና ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3/4/ የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንዲያቀርብ በብሔራዊ ባንክ ተጠይቆ ያላቀረበ ወይም እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ከብር 20,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጫ እና ከ7 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ የተመለከተው ጥፋት የተፈጸመው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት ከሆነ የእሥራት ቅጣቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ድርጅቱን በኃላፊነት በሚመራው ሰው ላይ ይሆናል፡፡
4. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ወይም አንቀጽ 17 ድንጋጌዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጫ እና ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

5. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 28/5/ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማናቸውም የባንክ ዳይሬክተር ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጫ እና ከ7 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።
6. ማንኛውም የባንክ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፣
   ሀ) ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተጣለበትን ግዴታዎች መፈጸም እንዳይችል ወይም በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በባንኩ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዳያካሂድ እንቅፋት ከሆነ፣ ወይም
   ለ) ለማታለል በማሰብ የሐሰት ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ ወይም በባንኩ መዝገብ፣ ሂሣብ፣ ሪፖርት ወይም መግለጫ ውስጥ የመዘገበ እንደሆነ ወይም መመዝገብ የነበረበትን መግለጫ ወይም መረጃ ሳይመዘግብ የቀረ እንደሆነ፣
   ሐ) ባንኩ ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ተቀማጭ ገንዘብ የተቀበለ ወይም ሌላ ሰው እንዲቀበል ያዘዘ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፣ ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጫ እና ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።
7. ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈፃፀማቸውን ያስናከለ እንደሆነ እስከ ብር 10,000 በሚደርስ መቀጫና እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

66. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል።

67. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የባንክ ሥራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 84/1986 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በንግድ ሕግ፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች መሠረት ሊፈጸሙ ከሚገባቸው ግዴታዎች ይህ አዋጅ ባንኮችን ነፃ አያደርጋቸውም።

68. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ፣**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 19 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 626/2001

## አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ[158]

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በገጠር በግብርና እና በሌሎች መሰል ሥራዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ፤

የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ዕድገትና ጤናማነት ይበልጥ እንዲጎለብት ተስማሚ የሆነ ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር 626/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ፈቃድ የተሰጠው ተቋም" ማለት በብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ማናቸውም የፋይናንስ ተቋም ነው፣
   2. "ዋና ሥራ አስፈፃሚ" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራም ቢሆን የአንድን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፣
   3. ‹‹ኩባንያ›› ማለት በንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጉም የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ:-[159]

      ሀ) በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም በኢትዮጵያውያን እና የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጋራ የተያዘ፣ ወይም

[158] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(10) መሰረት በአዋጁ በተለያዩ ቦታዎች ‹‹ተቆጣጣሪ›› ወይም ‹‹የቁጥጥር ሥራ›› የሚለው እንደ ቅደም ተከተላቸው ‹‹መርማሪ›› ወይም ‹‹የምርመራ ሥራ›› በሚል ተተክቷል፡፡
[159] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ለ) ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም በኢትዮጵያውያን እና የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጋራ ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ፤ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፣

4. ‹‹የግዴታ ቁጠባ›› ማለት ገንዘቡን የሚቆጥቡት ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ወይም የንግድ ድርጅቶች ፈቃድ ከተሰጠው ተቋም ብድር ለመውሰድ ብቁ ለመሆንና ለሚያገኙት ብድር በመያዣነት እንዲያገለግል በግዴታ የሚያስቀምጡት የቁጠባ ገንዘብ ነው፤[160]
5. "ዳይሬክተር" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፣
6. ‹‹የፋይናንስ ተቋም›› ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት፣ በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ነው፣[161]
7. "የፋይናንስ ኪራይ" ማለት አክራዩ

   ሀ) ቀደም ሲል ይዞት የሚገኘውን የካፒታል ዕቃ፣ ወይም

   ለ) በተከራዩ መራጭነት አቅራቢ ተብሎ ከሚጠራው ሦስተኛ ወገን የሚገዛውን የካፒታል ዕቃ፣

   ተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ ዓይነት ነው፣

[160] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[161] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሻሻለ፡፡

8. “የሂሳብ ዓመት” ማለት እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከጁላይ 1 ቀን ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት ጁን 30 ቀን የሚያበቃ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሂሣብ ዓመት ነው፣
9. “የቡድን ዋስትና” ማለት የቡድን ተበዳሪዎች ከመካከላቸው አንዳቸው ፈቃድ ከተሰጠው ተቋም የተበደረውን ያልከፈለ እንደሆነ ብድሩን መልሶ ለመክፈል በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ የሚሆኑበት የዋስትና አሰራር ነው፣
10. “አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ” ማለት ፈቃድ በተሰጠው ተቋም አማካይነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3/2/ ላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎችና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ተግባራትን የሚያጠቃልል የንግድ ሥራ ነው፡፡
11. “አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም” ማለት በገጠርም ሆነ በከተማ በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3/2/ በተጠቀሱት ሌሎች ሥራዎች ለመሰማራት በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ነው፤
12. “ብሔራዊ ባንክ” ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤
13. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
14. “የችሎታ መመዘኛ” ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ የብቃትና የሥነ-ምግባር መመዘኛ ነው፤
15. “ሞግዚት” ማለት ብሔራዊ ባንክ ወይም በብሔራዊ ባንክ የተሾመ ሰው ሲሆን ተግባሩም ችግር ያለበትን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በመረከብ አሰራሩን እንደገና በማዋቀር ተቋሙን ጤናማ ማድረግ ወይም ማፍረስ ነው፤
16. “የውዴታ ቁጠባ” ማለት በባለሂሣቡ በማናቸውም ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ሊወጣ የሚችል ፈቃድ በተሰጠው ተቋም ውስጥ ተቀማጭ የሆነ ገንዘብ ነው፤
17. “ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ” ማለት የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆነ ወይም ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ ማንኛውም የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሥራ ኃላፊ ነው፣

18.“በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት” ማለት በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰጡ የክፍያ፣ የሐዋላ እና የመድን አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡[162]

19.‹‹የውጭ ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ›› ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 ላይ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

20.‹‹ገንዘብ አከል ንብረት›› ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፣

ሀ) ጥሬ ገንዘብ፣

ለ) በሀገር ውስጥ ባንኮች እና በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ያለ ተቀማጭ ገንዘብ፣

ሐ) በቀላሉ ወደ ጥሬ ገንዘብ ተቀይረው ወዲያውኑ ተከፋይ ሊሆኑ የሚችሉ ንብረቶች፤ እና

መ) በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ተቀባይነት አላቸው ተብለው የሚወሰኑ ሌሎች ገንዘብ አከል ንብረቶች፡፡

21. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተነገረው አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ዓላማና ተግባር</u>

1. የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም ዋና ዓላማ ገንዘብ መሰብሰብና በገጠርና በከተማ በግብርና፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች እንዲሁም በሌሎች መሰል ሥራዎች ለተሰማሩ ሰዎች ጣሪያው በብሄራዊ ባንክ የሚወሰን ብድር መስጠት ይሆናል፡፡

2. በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያከናውን ይችላል፡-[163]

ሀ) የውዴታም ሆነ የግዴታ ቁጠባ፣ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭ መቀበል፣

ለ) በገጠር እና በከተማ በግብር እና በሌሎች ሥራዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች ብድር መስጠት፤

[162] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(2) መሰረት ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (17) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጾች (18)፣ (19) እና (20) ተጨምረው ንዑስ አንቀጽ (18) ንዑስ አንቀጽ (21) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

[163] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(3) መሰረት የአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሰ)፣ (ቀ) እና (ተ) ተሻሽለዋል፡፡

ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፈሉ የሃዋላ ሰነዶችን ማውጣትና መቀበል፤

መ) ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አነስተኛ የመድን ሥራ መሥራት፤

ሠ) ዓላማቸው ገቢ ማስገኘት የሆነ እንደ ግምጃ ቤት ሰነዶችን እና ሌሎች የአጭር ጊዜ የንግድ ወረቀቶችን ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት መግዛት፤

ረ) ሥራውን የሚያከናውንባቸውን ሕንፃዎች ጨምሮ ማናቸውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤትነት መያዝ መንከባከብና ለሌሎች ማስተላለፍ፤

ሰ) በከተማና በገጠር በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ወይንም በሌሎች ምርታማ ተግባራት ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚያካሂዱቸውን ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶች ማገዝ፤

ሸ) ለደንበኞች የአመራር፣ የገበያ፣ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ምክር መስጠትና በእነዚህም መስኮች አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲችሉ ማገዝ፤

ቀ) ለጥቃቅንና ለአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ወይም መሰል ምርታማ ተግባራት ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስተዳደር፤

በ) የሀገር ውስጥ ሐዋላ አገልግሎት መስጠት፤

ተ) የፋይናንስ ኪራይ አገልግሎት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 እና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 807/2005 መሠረት ለተከራዮች መስጠት፤ እና

ቸ) "በዲጅታል ዘዴዎች የዲጅታል ፋይናንስ አገልግሎት፣[164]

ኀ) የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት መስጠት፤ እና

ነ) ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አገልግሎት መስጠት፣

ኘ) ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች በሚወሰኑ ሌሎች ሥራዎች መሰማራት።

[164] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(4) መሰረት ከአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ተ) ቀጥሎ አዲስ ፊደል ተራ (ቸ)፣ (ኀ) እና (ነ) ተጨምረው ነባሩ ፊደል ተራ (ቸ) ፊደል ተራ (ኘ) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ

4. **ፈቃድ የማውጣት አስፈላጊነት**

   1. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር፣ በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፤ ሆኖም አግባብ ባለው ሕግ ፈቃድ የተሰጣቸው ባንኮች የተለየ የሥራ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ።
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገውን በመተላለፍ ማናቸውም ሰው ተቀማጭ ገንዘብ ለመቀበል በማስታወቂያ ወይም በማግባቢያ ዘዴ መጠቀሙን ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እያካሄደ መሆኑን ብሔራዊ ባንክ ለማመን ምክንያት ሲኖረው ይህንኑ ሁኔታ ለማጣራት ባንኩ በዚሁ ሰው ይዞታ ሥር የሚገኙትን የሂሳብ መዝገቦች፣ ቃለ ጉባኤ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነዶች፣ የገንዘብ ማዘዣዎች እና ሌሎች ሰነዶች እንዲቀርቡለት ለማድረግና ለመመርመር ወይም ለማስመርመር ይችላል፡፡

5. **የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች**

   1. አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡
      - ሀ) በሚገባ የተሞላ የፈቃድ መጠየቂያ ቅጽና ብሔራዊ ባንክ የሚጠይቃቸው ሌሎች አባሪ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፤
      - ለ) ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ መከፈል አለበት፤
      - ሐ) ተቋሙ በኩባንያ መልክ መቋቋምና የመመሥረቻ ጽሑፉና የመተዳደሪያ ደንቡ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፤
      - መ) ተቋሙ ያወጣቸው አክሲዮኖች በሙሉ የተፈረሙ ሆነው ከእነዚሁም ውስጥ ቢያንስ ሩቡ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መሆን አለበት፤
      - ሠ) በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ መከፈልና በምሥረታ ላይ ባለው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ስም በዝግ የባንክ

ሂሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፤

ረ) የተቋሙ ዳይሬክተሮችና ዋናው ሥራ አስፈጻሚ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን የችሎታ መመዘኛ የሚያሟሉና ሹመታቸው በብሔራዊ ባንክ የፀደቀ መሆን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

6. <u>**ፈቃድ ስለመስጠት**</u>

1. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ፈቃዱ የሚሰጠው በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ ሲከፈል ይሆናል።
3. በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የመጨረሻው ፈቃድ ይሆናል።
4. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የፈቃድ ሁኔታዎችን ሲያሻሽል ማሻሻያው በሥራ ላይ እንዲውል ከታሰበበት ጊዜ ሰላሳ ቀን ቀደም ብሎ የሚመለከታቸው አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ተቋሞች እንዲያውቁት ይደረጋል።
5. ብሄራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ቅርንጫፎችን መክፈት ይችላሉ።

7. <u>**የፈቃድ ዕድሳት**</u>

ብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ የሚታደስበትን ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

8. <u>**ፈቃድ ስለመሰረዝ**</u>

1. ብሔራዊ ባንክ የማንኛውንም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሥራ ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ለመሰረዝ ይችላል፦

ሀ) ለተቋሙ ፈቃድ የተሰጠው በተሳሳተ ወይም በሀሰት መረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ለ) ተቋሙ ፈቃድ በተሰጠው በ12 ወራት ውስጥ ሥራ ሳይጀምር የቀረ እንደሆነ።

ሐ) ተቋሙ የገንዘብ አከል ንብረት እጥረት ሲያጋጥመው፣[165]

መ) ተቋሙ ዕዳ መክፈል ወደማይችልበት ወሰን ሲደርስ፣ ወይም

ሠ) ተቋሙ ህግንና መመሪያን ተቀብሎ ለመስራት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፤

2. ብሔራዊ ባንክ የማናቸውንም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ፈቃድ እንዲሰረዝ ሲወስን የተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ውሳኔውን አሳትሞ ያወጣል።

3. ፈቃድ የመሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ወይም ብሔራዊ ባንክ ከሚወስነው ማናቸውም ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. ፈቃዱ የተሰረዘበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ማናቸውንም ዓይነት አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ መሥራት አይችልም።

5. ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለመሰረዝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

## ክፍል ሶስት

## የአሠራርና የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች

### 9. አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ስለመጀመር

ፈቃድ የተሰጠው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣

1. ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ማሟላት የሚገባውን ሁኔታዎች ማሟላት፣ እና

2. ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 12 ወራት ውስጥ ሥራ መጀመር፣ አለበት፡፡

### 10. አክስሲዮኖች የመያዝ ገደብና የአክሲዮን መዝገብ ስለመያዝ

1. አንድ ባለአክሲዮን በማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ስለሚኖረው የአክሲዮን መጠን ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

---

[165] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(5) መሰረት ከአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) ቀጥሎ አዲስ ፊደል ተራ (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) ተጨምረዋል፡፡

2. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝርና ድምፅ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የአክሲዮን መዝገብ ይይዛል፡፡ በዚህም መዝገብ የተመዘገበ ማንኛውም የአክሲዮን ዝውውር የህግ ውጤት ይኖረዋል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው መዝገብ በአነስኛ የፋይናንስ ተቋሙ መደበኛ የሥራ ሰዓት ሕዝብ ያለ ክፍያ ማየት በሚችልበት ሁኔታ በተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት ይቀመጣል።

11. <u>አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም አመራር ቦታ ስለሚይዙ ሰዎች፣</u>

1. የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ የተወሰኑትን የችሎታ መመዘኛ መስፈርቶች ያሟሉ መሆኑና ሹመታቸውም በብሔራዊ ባንክ የፀደቀ መሆን አለበት፡፡
2. አንድ ሰው በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ በቦርድ አባልነት ቢበዛ ለስንት ዓመታት ማገልገል እንደሚችልና እንደገና የሚመረጥበትን ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡
3. የሌላ የማናቸውም ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሥራ መሪነት የሚሳተፍ ሰው፤

   ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፣ ወይም

   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል የተፈረደበት ከሆነ፤ ራሱን ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም አመራር ማግለል አለበት፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተሮች ቦርድን ተግባራት፣ ኃላፊነት፣ ግዴታዎችንና መልካም የኩባንያ ሥራ አመራርን በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

12. **የውጭ ኦዲተር ስለመሾም**

1. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው የውጭ ኦዲተር መሾም አለበት፡፡ የውጭ ኦዲተር የሌለው ከሆነም ይህንኑ ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የውጭ ኦዲተር ያልሾመ እንደሆነ እስከሚቀጥለው የተቋሙ ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ ድረስ የሚያገለግል የውጭ ኦዲተር ብሔራዊ ባንክ ይሾምለታል፡፡ ለተሾመው ኦዲተር የሚደረገው የአገልግሎት ክፍያም በተቋሙ ይሸፈናል።
3. በማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ኦዲት ሥራ ለማካሄድ የሚሾሙ የውጭ ኦዲተሮች፣

   ሀ) [166]

   ለ) የምርመራ ይዘትና ጥልቀት፣ እና

   ሐ) የኦዲተሮች የሹመት ዘመን፣

   በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
4. የሚከተሉት ሰዎች የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር ሆነው መሾም አይችሉም፤

   ሀ) የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ሠራተኛ፤

   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ የተመለከተ ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም አንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ፤

   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ ወይም /ለ/ የተመለከተ ሰው ሠራተኛ ወይም ሽሪክ የሆነበት የኦዲት ተቋም፡፡

13. **የውጭ ኦዲተር ተግባሮችና ሪፖርቶች**

1. የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር የኦዲት ግኝቶችን፣ ድምዳሜዎችን እና አስተያየቶችን ያካተተ የተሟላ የኦዲት ሪፖርት እና የውጭ ኦዲተር ዝርዝር ግኝቶችን በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡ በተጨማሪም የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር

[166] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(9) መሰረት ተሰረዘ፡፡

የተቋሙን ሂሳብ መርምሮ ያገኛቸውን ውጤቶች እና የደረሰባቸውን ድምዳሜዎች ለተቋሙ ባለአክሲዮኖች ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡[167]

2. ብሔራዊ ባንክ የቀረበውን የኦዲት ሪፖርት ካላመነበት ድጋሚ የሂሣብ ምርመራ እንዲካሄድ ማዘዝ ወይም ሌላ የውጭ ኦዲተር በመሾም ሂሣቡ እንደገና እንዲመረመር ማድረግ ይችላል፡፡ በብሔራዊ ባንክ አዲስ ለተሾመው የውጭ ኦዲተር የሚደረገው ክፍያ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ የሚሸፈን ይሆናል፡፡
3. የማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር የሂሣብ ምርመራ ተግባሩን በሚያካሂድበት ጊዜ፤
   ሀ) የዚህ አዋጅ ወይም የሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በከፍተኛ ደረጃ መጣሳቸውን ወይም ያለመከበራቸውን፣
   ለ) በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወይም በማናቸውም የተቋሙ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ የማጭበርበር ወይም ሌላ የእምነት ማጉደል ወንጀል መፈጸሙን፣
   ሐ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ካፒታል 25 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ መጠን የሚቀንስ ኪሣራ የደረሰ መሆኑን፣
   መ) የአስቀማጮችን ወይም የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ከመደበኛው ወይም ከተለመደው አሠራር ውጭ ከባድ የሆነ የአሠራር ችግር መከሰቱን፣ ወይም
   ሠ) የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የገንዘብ ጠያቂዎችን የገንዘብ ጥያቄዎች በተቋሙ ንብረቶች ሊሸፈኑ መቻላቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉን፣

   ሲደርስበት ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር ሆኖ የተሾመ ሰው በመደበኛ የሥራ ሂደትና ለሌላ ለማንኛውም ሰው ከሚሰጠው አገልግሎት ባልተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ በዚያው ተቋም ሂሣብ መያዝ ወይም ከተቋሙ ማንኛውንም ዓይነት አገልግሎት ማግኘት አይችልም።

---

[167] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(6) መሰረት ተሻሻለ፡፡ (ማስታወሻ የማሻሻያ አዋጁ ቁጥር 1146/2012 ምንም እንኳን በአንቀፅ 2(6) ይህን ድንጋጌ በማሻሻል አዲስ ያስገባ ቢሆንም በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 2(9) ላይ የተሰረዘ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ ሆኖም ድንጋጌው ሳይሰረዝ በተሻሻለው መሰረት እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡)

5. ብሔራዊ ባንክ የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሂሣብ ዓመት ከተጠናቀቀ በኋላ በምን ያህል ጊዜ የኦዲት ሪፖርት መውጣት እንዳለበት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

14. <u>የፋይናንስ ግዴታዎች</u>

1. አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሊኖረው የሚገባው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል መጠን ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ የሚከተሉትን በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣
   ሀ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ለማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ሊሰጥ ስለሚችለው ከፍተኛ የብድር መጠንና ችግር ላለባቸው ብድሮች ስለሚይዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ፤
   ለ) በሥራ ላይ ያለ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሊኖረው ስለሚገባው የካፒታል መጠንና ገንዘብ-አከል ሀብቶች፤
   ሐ) [168]
   መ) ስለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የፋይናንስ አፈጻፀም ደረጃ፤ እና
   ሠ) ስለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሂሣብ አያያዝ፣ የሥራ አመራር መረጃ ፍሰት፣ የውስጥ ቁጥጥርና በየጊዜው መቅረብ ስላለባቸው ሪፖርቶች።
3. ብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ለአደጋ የተጋለጡበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የካፒታልና ገንዘብ-አከል ንብረቶች ግዴታዎችን ለተለያዩ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

15. <u>ስለፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች ስለመስጠት</u>

1. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፡-
   ሀ) የሂሣብ መግለጫዎቹን ተቀባይነት ባላቸው የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች መሠረት ማዘጋጀት፤
   ለ) የተቋሙን ሁኔታ በግልጽና በትክክል የሚያሳይ፣ የተቋሙን ሥራና የገንዘብ አቋሙን የሚያስረዳ እና ተቋሙ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ሥራውን እያካሄደ ለመሆኑ ብሔራዊ ባንክ ማረጋገጥ በሚችልበት ሁኔታ መዝገቦቹን መያዝ፤ እና

[168] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(9) መሰረት ተሰረዘ፡፡

ሐ) ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴ ዓይነት የሚመዘግብበት የተለየ መዝገብና ሰነዶች መያዝ፤

አለበት፡፡

2. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣-

   ሀ) ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚገባ የተፈረሙ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ሪፖርቶችን ለባንኩ ማቅረብ፣ እና

   ለ) በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫዎችን በሁሉም የተቋሙ ቅርንጫፎች ግልፅ በሆነ ቦታ ዓመቱን ሙሉ እንዲታዩ ማድረግ፣

   አለበት፡፡

3. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣-

   ሀ) ለገንዘብ አስቀማጮቹና ለሌሎች አበዳሪዎች ያለበትን ግዴታ ማሟላት እንደማይችል፣ ወይም

   ለ) ለገንዘብ አስቀማጮችና ለሌሎች አበዳሪዎች ክፍያዎችን በወቅቱ ለመፈፀም እንደሚሳነው፣

   ሲገመት ሙሉውንና ትክክለኛውን ሁኔታ ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፤ በተጨማሪም ብሔራዊ ባንክ የሚጠይቃቸውን ሌሎች ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

4. ብሔራዊ ባንክ አግባብ አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም መጠየቅና ማግኘት ይችላል፣ ሆኖም፣

   ሀ) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም ሲባል፣

   ለ) የተቋሙን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ፣

   ሐ) በሕግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች፣

   መ) ብሔራዊ ባንኩ ተጠሪ ለሆነለት አካል፣

   ሠ) በፍርድ ቤት በመታዘዙ፣ ወይም

   ረ) ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ለመወጣት ሲባል፣

   ካልሆነ በቀር እነዚህ መረጃዎች ለማንኛውም ሰው ተላልፈው አይሰጡም።

16. <u>የብድር አገልግሎት አሰጣጥ</u>

ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ለቡድኖችም ሆነ ለግለሰቦች ብድር መስጠት ይችላል፡፡ ተቋሙ እንደ አግባብነቱ በራሱ ውሳኔ ያለመያዣ፣ በመያዣ፣ በንብረት ወይም በቡድን ወይም በግለሰብ ዋስትና ብድር መስጠት ይችላል፡፡

17. **ክልከላ**

ከብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን መፈጸም አይችልም፤

1. የተቋሙን ሥራ ወይም ተቋሙን ከሌላ ለማቀላቀል ወይም ለመሸጥ ማንኛውንም ውል መዋዋል፣
2. በመደበኛ የሥራ አፈፃፀም ተግባሩ ካልሆነ በቀር ንብረቱን በሙሉም ሆነ በከፊል ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም በሌላ መንገድ ማዛወር፣
3. በኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የተቋሙን ካፒታል መቀነስ፣
4. የተሻሻለውን የመመሥረቻ ጽሁፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ማስመዝገብ ወይም ፈቃድ ያገኘበትን ስም መለወጥ፤[169]
5. ከተፈቀደለት አካባቢ ውጭ መሥራት።

18. **በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥርና የማስተካከያ እርምጃዎች**

1. ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ወይም በማናቸውም ጊዜ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ላይ በቦታው ተገኝቶ ቁጥጥር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል፡፡
2. ከጠቅላላው ገንዘብ አስቀማጮች በቁጥር አንድ አስረኛ ወይም በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ዘንድ ካለው ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ አንድ ስድስተኛ አስቀማጭ የሆኑ አመልካቾች በተቋሙ ላይ ምርመራ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዳ መረጃ አያይዘው ጥያቄ ካቀረቡ፣ ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ የቀረበበት ተቋም በጤናማ ሁኔታ መገኘቱንና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቋሙን የሥራ እንቅስቃሴ በመምራት ሂደት ውስጥ መከበራቸውን ለማረጋገጥ በሚስጥር ምርመራ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ለማድረግ ይችላል፡፡
3. አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትን የመቆጣጠሩ ተግባር በብሔራዊ ባንክ አንድ ባለሙያ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ባለሙያዎች ወይም በሌሎች እምነት

[169] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(7) መሰረት ተሻሻለ፡፡

በሚጣልባቸውና ለዚህ ጉዳይ በብሔራዊ ባንክ በተቀጠሩ ባለሙያዎች ወይም ድርጅቶች ሊካሄድ ይችላል፡፡

4. አነስተኛ የፋይናንስ ተቋምን እንዲቆጣጠሩ በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ቁጥጥር ከሚደረግበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሠራተኞች የቁጥጥሩን ተግባር ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ስለተቋሙ ሁኔታ የሚገልፁ መዛግብትና የሥራ እንቅስቃሴ ማብራሪያዎች ለመጠየቅ ሥልጣን አላቸው፡፡

5. የቁጥጥር ሪፖርት ለሚመለከተው ተመርማሪ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ በቀረበው ሪፖርት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ተመርማሪው ተቋም በሪፖርቱ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል።

6. ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የቁጥጥር ሪፖርት ይዘት፡-

ሀ) ቁጥጥሩን ባካሄዱት ሰዎች እንዲሁም ቁጥጥሩ በተደረገበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች፣ እና

ለ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም ወይም የሕዝብን ጥቅም ለማስከበር ሲባል ካልሆነ በቀር በብሔራዊ ባንክ፣ በምስጢር መጠበቅ አለበት፡፡

7. በተደረገው ቁጥጥር ተመርማሪው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በኢትዮጵያ ፀንተው የሚገኙትን ሕጎች፣ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ያልተከተለ መሆኑ ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እንዲሠራ በተሰጠው የሥራ ፈቃድ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልፈፀመ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም በማናቸውም አኳኋን የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የሕዝብን ጥቅም በሚጎዳ በማናቸውም ተግባር ላይ የተሰማራ እንደሆነ ወይም በሥራ አመራሩ ላይ ከባድ ድክመት የተከሰተ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ፡-

ሀ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙን ማናቸውም ተግባር በተመለከተ ለመነጋገር የባለአክሲዮኖች ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እንዲጠራ ወይም የዚህ ተቋም ኃላፊዎች ምርመራውን በተመለከተ የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችን እንዲያነጋግሩ ለማዘዝ፣

ለ) አንድ ወይም ከዚያ በላይ ኃላፊዎቹን በተመርማሪው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዲሬክተሮች ቦርድ ወይም በእርሱ በተሰየመ በማናቸውም ኮሚቴ

ወይም ሌላ አካል ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ለመወከልና የተወካዮቹ አስተያየትም በተጠቀሱት ስብሰባዎች ላይ እንዲሰማ ለማዘዝ፣

ሐ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ሊወሰድ የሚገባውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በጽሑፍ ለማዘዝ፣

መ) በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ሌሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ላይ የገንዘብ መቀጫ ለመወሰን ወይም ከሥራ እንዲታገዱ ወይም እንዲሰናበቱ ለማዘዝ፣

ሠ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ አዲስ ቅርንጫፎችን እንዳይከፍት ለመከልከል፣

ረ) የተቋሙን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ለመገደብ፣ ለማዘግየት ወይም ለመከልከል፣

ሰ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙን ለተወሰነ ጊዜ በከፊልም ሆነ በሙሉ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እንዳይሰራ ለማዘዝ፣ ወይም

ሸ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙን ፈቃድ ለመሰረዝና ተቋሙን የማፍረስ ሂደት እንዲጀመር ለማድረግ፣

ይችላል፡፡

19. <u>ስለሞግዚት አስተዳደርና መፍረስ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች በአንድ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም መኖራቸውን ሲያምን ተቋሙን ተረክቦ የሚቆጣጠር ሞግዚት ሊሾም ወይም ራሱ እንደሞግዚት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት የባንኩ ፍቃድ የተሰረዘ ከሆነ፤

ለ) የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ ሀብት ለአስቀማጮችና ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ከገባቸው ግዴታዎች ያነሰ ከሆነ፤

ሐ) ሕግን ወይም መመሪያን በመተላለፍ ወይም ጥንቃቄ በጎደለው አሰራር ምክንያት በቀላሉ የማይገመት የሀብትና የገቢ ብክነት የተከሰተ ከሆነ፤

መ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ሥራውን የሚያካሂደው ጤናማ ባልሆነ እና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ከሆነ፤

ሠ) በብሔራዊ ባንክ የተጣለ ማንኛውም ገደብ ሆን ተብሎ የተጣሰ ከሆነ፤

ረ) ተቋሙ የሂሣብ መዝገቦችን፣ ሰነዶችን፣ ሬኮርዶችን ወይም ንብረቶችን የደበቀ ወይም ለቁጥጥር ተግባር ሥልጣን ለተሰጠው የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም ወኪል ያላቀረበ ከሆነ፤

ሰ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ በመደበኛ የሥራ ሂደት ግዴታዎቹን ወይም የገንዘብ አሰቀማጮቹን ጥያቄ ማሟላት አይችልም የሚል ጠንካራ ግምት ከኖረ፣

ሸ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ካፒታሉን በሙሉ ወይም የካፒታሉን አብዛኛውን ክፍል የሚያመናምን ኪሳራ የደረሰበት ወይም እንደሚደርስበት የሚገመት ከሆነ፤

ቀ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ውጪ ከተሰማራ፣

በ) ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ከማናቸውም ሌላ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወይም ባንክ ጋር የተቀላቀለ ከሆነ፤

ተ) አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ፤

1) በብሔራዊ ባንክ የሚጠየቀውን አነስተኛ የካፒታል መጠን የማያሟላና ወደፊትም ካፒታሉን በሚያስፈልገው መጠን ለመጨመር አቅም እንደማይኖረው የሚገመት፣

2) በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ካፒታሉን በሚያስፈልገው በቂ መጠን መጨመር ያልቻለ ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካፒታሉን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ዕቅድ ያላቀረበ፣ ወይም

3) ለብሔራዊ ባንክ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ካፒታልን መልሶ የመገንባት ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ ያልቻለ፣ ከሆነ፤

ቸ) ባለአክሲዮኖች ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት ተቋሙን ለማፍረስ የወሰኑ እንደሆነ ወይም ተቋሙ እንደ አንድ ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ሕጋዊ ሰው ሆኖ መቀጠል የተሳነው ከሆነ፤

ኀ) በባለአክሲዮኖች በተላለፈ ውሳኔ ተቋሙ በሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲውል የተጠየቀና በብሔራዊ ባንክ የጸደቀ ከሆነ።

2. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለተሾመ ሞግዚት የሚከፈለውን ክፍያ ይወስናል፡፡

3. አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሞግዚት አስተዳደርና የማፍረስ ሂደት አግባብ ባላቸው የባንክ ሥራ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይከናወናሉ፣

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. ፈቃድ የተሰጣቸውን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ስለማስታወቅ

ብሔራዊ ባንክ በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸውን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ዝርዝር አትሞ ያወጣል። እንዲሁም በዚሁ ዝርዝር ላይ የተጨመሩትን ወይም ከዝርዝሩ የተሰረዙትን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች ላይ ወዲያውኑ አሳትሞ ያወጣል።

### 21. አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወደ ባንክ ወይም ወደ ሌላ የፋይናንስ ተቋምነት ስለሚሸጋገርበት ሁኔታ

1. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን መስፈርቶች አሟልቶ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣ ባንክ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ሆኖ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲሰራ ብሔራዊ ባንክ እንደገና ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት እንደገና ፈቃድ ከተሰጠው፣ ብሔራዊ ባንክ ተቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራን እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ አድርጎ እንዲቀጥል ሊያዘው ይችላል፡፡

### 22. ድጋፍ ስለማግኘት

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ለማበደር ወይም ካፒታላቸውን ለመገንባት ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ምንጮች ዕርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

### 23. ከትርፍ ገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን

ማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ከሥራው ያገኘውን ትርፍ፤

1. ለባለአክስዮኖቹ ከአከፋፈለ እንደማንኛውም የንግድ ተቋም የትርፍ ገቢ ግብር ይከፍላል፣
2. በሙሉ ለተቋሙ ሥራ ካዋለው ከትርፍ ገቢ ግብር ነጻ ይሆናል።

24.**<u>የደንበኞች ማንነት ስለማወቅ</u>**

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የደንበኞቻቸውን ማንነት በትጋት ተከታትለው የሚያውቁባቸውንና አጠራጣሪ የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት የሚያደርጉባቸውን መስፈርቶች ብሄራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

25.**<u>ክልከላ</u>**

ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ ወይም ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ለማቋቋም ወይም ቅርንጫፍ ለመክፈት ወይም የውጭ ሀገር አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ተቀጽላ በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ለመሥራት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የአክሲዮን ባለቤት ለመሆን አይፈቀድለትም፡፡

26.**<u>የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ</u>**[170]

የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት እና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል መመሪያ ብሔራዊ ባንክ ሊያወጣ ይችላል፡፡

27.**<u>የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት</u>**

ብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትን ጨምሮ በፋይናንስ ተቋማት መካከል የሚደረግ የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ስለሚደራጅበት፣ ስለአሰራሩና የወጪ መጋራትን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

28.**<u>የማስታወቂያ ይዘትን ስለመቆጣጠር</u>**

ማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በማንኛውም ጊዜ በብሔራዊ ባንክ እምነት ሀሰተኛ፣ አሳሳች፣ አደናጋሪ ወይም የሌላውን ጥቅም የሚጎዳ የተከፈለበት የሬድዮ ወይም የቴሌቪዥን ማስታወቂያ፣ ፖስተር፣ ቢልቦርድ፣ በራሪ ወረቀት ወይም ሌላ ሰነድ እና የተከፈለበት የጋዜጣና የመጽሄት ማስታወቂያ አውጥቶ ቢገኝ ተቋሙ ማስታወቂያውን እንዲያቋርጥ፣ እንዲያሻሽል ወይም ከማስተዋወቅ እንዲቆጠብ ብሔራዊ ባንክ ሊያዘው ይችላል፡፡"

[170] በ26/7(2012) አ.1164 አንቀፅ 2(8) መሰረት ከአዋጁ አንቀጽ 25 ቀጥሎ አዲስ አንቀጾች 26፣27፣28፣29፣30፣31 እና 32 ተጨምረው ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ያሉት አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 33 እስከ 37 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

**29.ዋናና ወሳኝ ሥራን በውጭ አካላት ስለማሰራት**

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወሳኝ ሥራቸውን በውጭ አካላት ስለሚያሰሩበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ‹‹ዋናና ወሳኝ ሥራ›› ማለት ቁጠባ መሰብሰብን፣ ብድር መስጠትን፣ የሀገር ውስጥ ሀዋላን፣ የአነስተኛ የመድን ሥራ እና ብሔራዊ ባንክ የሚወስነውን ሌሎች ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡"

**30. በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት**

በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ይወስናል፡፡"

**31.ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አገልግሎት ስለመስጠት**

1. በአዋጁ የተጠቀሱ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ብሔራዊ ባንክ ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት ለሚቋቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ፈቃድ ስለሚሰጥበትና ቁጥጥር ስለሚያካሂድበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዴታዎች ለመደንገግ መመሪያ ያወጣል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ "ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ የሚሠራ ተቋም" ማለት ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ብቻ እንዲሠራ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛው የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ጋር የወለድ ነፃ ተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራዎችን ለመቆጣጠር መመሪያ ያወጣል፡፡

**32.የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በአነስተኛ የፋይናንስ ዘርፍ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 25 የተደነገገው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም ሙሉ በሙሉ የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለቤትነት ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያን የጋራ ባለቤትነት የተቋቋሙ

ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የአክስዮን ባለቤት መሆን ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ማቋቋም ይችላሉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው አግባብ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ቀጥታ የአንድ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም ባለአክስዮን ሲሆን ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የአክስዮን ባለቤት የሆነበት ሌላ ድርጅት የአንድ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ባለአክስዮን ሲሆን የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም እሱ ባለአክስዮን የሆነበት እና በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ ባለአክሲዮን የሆነ ድርጅት በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ የሚኖረው የአክስዮን ድርሻ ዋጋ በሙሉ ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሪ ብቻ የሚከፈል ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ግዴታ ቢኖርም:-

ሀ) ከአክስዮን ባለቤትነት የሚያገኘው የትርፍ ድርሻ፣

ለ) የአክስዮን ድርሻውን ለሌላ ሰው ሲያዛውር፣

ሐ) ባለአክስዮን የሆነበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሲሸጥ ወይም ፈርሶ ሂሳቡ ሲሰራ፣ ወይም

መ) ሌሎች ከአክሲዮን ባለቤትነት ጋር በተያያዘ፤

የውጭ ሀገር ዜግነት ላለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም እሱ ባለአክሲዮን ለሆነበት ድርጅት እና በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ አክሲዮን ላለው የሚከፈሉ ማናቸውም ዓይነት ክፍያዎች በሙሉ በብር የሚከፈለው ይሆናል፣ እንዲሁም በዚህ አግባብ የሚያገኘውን ሀብት ወይም ጥቅም ወደ ውጭ ሀገር ማዛወር አይፈቀድለትም፡፡

4. የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአነስተኛ የፋይናንስ ዘርፍ መዋዕለ ንዋያቸውን በሥራ ላይ ስለሚያውሉበት ተጨማሪ ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

## 33.ቅጣት

1. ማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ፣

   ሀ) ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መፈጸም እንዳይችል ወይም በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዳያካሂድ እንቅፋት ከሆነ፣ ወይም

   ለ) ለማታለል በማሰብ የሐሰት ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ ወይም በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ መዝገብ፣ ሂሣብ፣ ሪፖርት ወይም መግለጫ ውስጥ የመዘገበ እንደሆነ ወይም መመዝገብ የነበረበትን መግለጫ ወይም መረጃ ሳይመዘግብ የቀረ እንደሆነ፣

   ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጫ እና ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ እስከ ብር 10,000 በሚደርስ መቀጫና እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል።

## 34. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

## 35. ተፈጻሚነት ስለሚኖራቸው ሌሎች ሕጎች

1. የባንክ ሥራ ሕጎች በዚህ አዋጅ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ላይ እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2. በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣው አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና ስለንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣው አዋጅ ቁጥር 98/1990 በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በመያዣ የተያዘ ንብረት ላይ እንደአግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

36. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. ሰለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ ስለመስጠትና ሥራቸውን ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 40/1988 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

37.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 718/2003

## የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ

ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት የሀገሪቱ ፋይናንስ መሠረተ ልማት ዋነኛ አካል በመሆኑ የሥርዓቱ ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋትን የኢኮኖሚ ዕድገትንና የፋይናንስ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ፤

የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓቱን ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ለማረጋገጥ ሥርዓቱ ስለሚቋቋምበት፣ ስለሚተዳደርበት፣ አሰራሩ ስለሚመራበት እንዲሁም ቁጥጥርና ክትትሉ ስለሚካሄድበት ሁኔታ ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "መዝገብ፣ ሪከርድ፣ ሂሳብ፣ ሰነድ ወይም መረጃ" ማለት በወረቀት ወይም በኢሌክትሮኒክ፣ በኦፕቲካል፣ በማግኔቲክ ወይም በማናቸውም መልክ የተቀረፀን ወይም የተከማቸን መዝገብ፣ ሪከርድ፣ ሂሣብ፣ ሰነድ ወይም መረጃ ነው፤
   2. "ካርድ" ማለት በየጊዜው ከሂሳብ ውስጥ ገንዘብ ለማግኘት ወይም ክፍያ ለመፈፀም የሚያገለግል ማንኛውም ካርድ ወይም ሂሣብ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ኮድ ወይም ሌላ ዘዴ ወይም መሳሪያ ሲሆን የዴቢት፣ የክሬዲት እና የተከማቸ እሴት ካርድን ይጨምራል፤
   3. "የግብይት ማዕከል" ማለት በሂሣብ ማወራረድ ሥርዓት ውስጥ ከእያንዳንዱ ሻጭ ገዢ እና ለእያንዳንዱ ገዢ ሻጭ የሆነ አካል ነው፤
   4. "ማዕከላዊ የዋስትና ሰነዶች ግምጃ ቤት" ማለት የዋስትና ሰነድ ወይም ሌላ የፋይናንስ መሳሪያን አካላዊ እንቅስቃሴ በመግታት በመዝገቡ መዝግቦ የሚይዝና

ሰነዱ ከአንዱ ወደ ሌላው ሰው በዚሁ መዝገብ ላይ በሚደረግ የስመ ባለቤትነት ዝውውር ማስተካከያ ብቻ እንዲተላለፍ የሚያደርግ አካል ነው፤

5. "ሂሳብ ማጣራት" ማለት ሂሣብ ከማወራረድ አስቀድሞ የሚሰራውን የገንዘብ ወይም የዋስትና ሰነዶችን የማስተላለፍ ትእዛዞች የመላክ፣ የማስታረቅ እና የማረጋገጥ ሂደት ሆኖ ሂሣብ ለማወራረድ እንዲያስችል የክፍያ ትዕዛዞችን ማቻቻልና የተጣራ የመጨረሻ ተከፋይ ሂሳብ ማሳወቅን ያካትታል፤
6. "የሂሳብ ማጣሪያ ተቋም" ማለት ብሔራዊ ባንክ ወይም ማናቸውም በብሄራዊ ባንክ የሂሳብ ማጣራት አገልግሎት እንዲሰጥ የተፈቀደለት አካል ሲሆን በሌላ ህግ እውቅና የተሰጠውን የሂሳብ ማጣሪያ ተቋም አይጨምርም፤
7. "የሂሣብ ማጣሪያ ሥርዓት" ማለት ተሳታፊዎች ከገንዘብ፣ ከዋስትና ሰነዶች ወይም ሌሎች የፋይናንስ መሳሪያዎች ጋር በተያያዘ በተማከለ ሁኔታ ወይም በአንድ በተወሰነ ሥፍራ እርስ በርሳቸው መረጃ የሚያቀርቡበት እና የሚለዋወጡበት ስርዓት ሲሆን ተሳታፊዎች ግዴታቸውን የማወራረድ ሂደት ለማመቻቸት በሁለትዮሽ ወይም በብዙዮሽ ሆነው በሂሣብ መጠናቸው ላይ ለመድረስ የሚጠቀሙበትን የስሌት አሰራር ይጨምራል፤
8. "ኤሌክትሮኒክ" ማለት ከብሔራዊ የክፍያ ስርዓት ጋር በተያያዘ አገልግሎት ላይ የሚውል ኤሌክትሪካል፣ ዲጂታል፣ ማግኔቲክ፣ ኦፕቲካል፣ ባዮሜትሪክ፣ ኤሌክትሮ ኬሚካል፣ ሽቦ አልባ፣ ኤሌክትሮ ማግኔቲክ ቴክኖሎጂ ወይም ሌላ ማንኛውም ቴክኖሎጂ ነው፤
9. "ኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽን" ማለት ወጥ በሆነ ፎርማት፡-
   ሀ) በማየት ወይም በማዳመጥ በግልጽና በቀላሉ ለመረዳት፤ እና
   ለ) በመልዕክቱ ውስጥ ያለውን መረጃ በማተም፣ በመቅዳት ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ለማግኘትና በቀጣይ ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ፤

   መልዕክት በኤሌክትሮኒክ መለዋወጥ ነው፤
10. "ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ" ማለት የኤሌክትሮኒክ ተርሚናል ሲሆን ኮምፒውተር፣ የሽያጭ ነቁጥ፣ ራስ ሠር የክፍያ ማሽን፣ ስልክ እና ሌሎች ተመሳሳይ መገልገያዎችን ይጨምራል፤
11. "የኤሌክትሮኒክ ፊርማ" ማለት መልዕክቱ ከያዘው መረጃ ጋር በተያያዘ፣ የፈራሚውን ትክክለኛነት እና ማንነት ለመለየትና በመልዕክቱ የተካተተው መረጃ

በፈራሚው የፀደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከመረጃ መልዕክት ጋር የተቆራኘ ወይም ከመልዕክቱ ጋር ምክንያታዊ በሆነ አኳኋን የተያያዘ በኤሌክትሮኒክ መልክ ያለ መረጃ ነው፤

12. "የፋይናንስ ተቋም" ማለት ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የፖስታ ቁጠባ፣ የሐዋላ ድርጅት፣ መድን ሰጪ ኩባንያ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፤

13. "ገንዘብ ማስተላለፍ" ማለት በማናቸውም ሰው አነሳሽነት በፋይናንስ ተቋም ከተቀመጠ ሂሳብ ላይ ገንዘብ ወጪ ወይም ገቢ እንዲደረግ ለተቋሙ በሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ሥልጣን ወይም በቀረበ ጥያቄ መሠረት በክፍያ ወይም በሀዋላ የሚደረግ ማናቸውም የገንዘብ ማስተላለፍ ሆኖ በሽያጭ ነቁጥ ወይም በራስ ሠር የክፍያ ማሽን የሚፈፀም ክፍያን፣ በተቋሙ በቀጥታ የሚከናወን ገቢ ወይም ወጪን፣ በስልክ፣ በኢንተርኔት፣ በካርድ ወይም በሌሎች መገልገያዎች አማካኝነት የሚደረግ ማስተላለፍን ያጠቃልላል፤

14. "ከፍተኛ ዋጋ ያለው ገንዘብ የማስተላለፍ ሥርዓት" ማለት የገንዘብ መጠኑ በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሆኖ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ገንዘብ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማስተላለፍ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ባንክ ለባንክ የሚደረግ የገንዘብ ማስተላለፍ ስርዓትን፤

ለ) ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠውንና አጣዳፊ የሆነን የመንግሥት ገንዘብ ማስተላለፍን፤

ሐ) የዋስትና ሰነዶችን ማጣራት እና ማወራረድን፤ ወይም

መ) ብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ብሎ የሚወስነው ማናቸውም የገንዘብ ማስተላለፍ ስርዓትን።

15. "ብሔራዊ ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

16. "ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ቀጥሎ የተመለከቱትን ያካትታል፡-

ሀ) የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ገንዘብ ወይም የክፍያ ትዕዛዞችን መላክ፣ መቀበል፤ ክፍያ ማካሄድ ወይም ማስተላለፍን፤

ለ) የክፍያ መፈፀሚያ ሰነዶችን ማውጣትና ማስተዳደርን፤

ሐ) የክፍያ፣ የሂሣብ የማጣራትና የማወራረድ ስርዓቶችን፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተራ ፊደል (ሐ) ስር ከተመለከቱት ስርዓቶች ጋር የተያያዙ ስምምነቶች እና የአሰራር መመሪያዎችን፤ እና

ሠ) የክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ፣ ኦፕሬተሮች፣ ተሳታፊዎች፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪዎች እና በእነዚህ ስም በውክልና ወይም አገልግሎትን በሶስተኛ ወገን ለማሰራት በሚደረግ ስምምነት በሙሉ ወይም በከፊል በሃገር ውስጥ የሚሰሩ ማናቸውም ሶስተኛ ወገኖችን፤

17.“ማቻቻል” ማለት ግዴታን ለማወራረድ በአንድ የክፍያ ስርዓት ስር ባሉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የስርዓቱ ተሳታፊዎች መካከል ያሉትን የክፍያ ግዴታዎች በማጣጣት ወይም በማስተካከል የተጣራ የክፍያ ግዴታ ወይም የተጣራ የሂሣብ መዝጊያ ዋጋ መወሰን ነው፤

18.“ኦፕሬተር” ማለት ብሔራዊ ባንክ፣ የገንዘብ ተቋም ወይም በብሔራዊ ባንክ ኦፕሬተር እንዲሆን ፈቃድ የተሰጠው ሌላ ማናቸውም አካል ነው፤

19.“ተሳታፊ” ማለት በክፍያ፣ በሂሣብ ማጣራት ወይም በማወራረድ ሥርዓት ውስጥ የሚሳተፍ አካል ሲሆን ይህም በብሔራዊ ባንክ ወይም በሌላ ማናቸውም ሂሳብ የማወራረድ ስራ በሚሰራ አካል ዘንድ የማወራረጃ ሂሳብ የሚከፍትና የሚይዝ ቀጥተኛ ተሳታፊ ወይም በቀጥተኛ ተሳታፊ የማወራረጃ ሂሣብ በኩል ብቻ ግዴታውን ለማወራረድ የሚችል ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳታፊ ሊሆን ይችላል፤

20.“የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ” ማለት አንድ ሰው ገንዘብ፣ ዕቃ ወይም አገልግሎት እንዲያገኝ ወይም ክፍያ እንዲፈፅም ወይም ገንዘብ እንዲያስተላልፍ የሚያስችለው ግዙፍነት ያለውም ሆነ የሌለው ማናቸውም ሰነድ ሲሆን ቼክን፣ ድራፍትንና ካርድን ይጨምራል፤

21.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

22.“አነስተኛ ገንዘብ የማስተላለፍ ሥርዓት” ማለት በብሔራዊ ባንክ የሚከናወነውንና የሚተዳደረውን የቼክ ማጣራት እና በብሔራዊ ባንክ የተፈቀደ ማናቸውም ዓይነት አነስተኛ ገንዘብ ማስተላለፍ ስርዓት የሚይዝ የገንዘብ ማስተላለፍ ሥርዓት ነው፤

23.“ሂሣብ ማወራረድ” ማለት ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነድ ወይም የፋይናንስ ሰነድን በማስተላለፍ በሁለት ወይም ከዚህ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል ያለን ግዴታ የመወጣት ድርጊት ነው፤

24.“የሂሣብ ማወራረድ ደንብ” ማለት የክፍያ ግዴታዎች የሚሰሉበት፣ የሚቻቻሉበት ወይም የሚወራረዱበትን ሁኔታ የሚደነግግ ደንብ ነው፤

25.“ሂሣብ ማወራረድ ሥርዓት” ማለት የክፍያ እና የሂሣብ ማወራረድ ግዴታዎችን ለመወጣት እንዲያስችል በብሔራዊ ባንክ የተቋቋመና የሚከናወን ወይም በብሔራዊ ባንክ የተፈቀደለት ማናቸውም ሂሳብ ለማወራረድ የተቋቋመ ሥርዓት ነው፤

26.“የተከማቸ እሴት” ማለት ለክፍያ እንዲጠቅም ሆኖ በገንዘብ የተመደበ ወይም ያልተመደበ ዋጋ የሚወክል በኮምፒውተር ቺፕ ወይም በሌላ ማናቸውም መገልገያ መጠኑ የተመዘገበ የእሴት ክምችት የሚያካትት ነው፤

27.“የተከማቸ እሴት ካርድ” ማለት የገንዘብ መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊደረግ የሚችል የቅድሚያ ክፍያ ካርድ ነው፤

28.“ሥርዓት” ማለት የክፍያ፣ የሂሣብ ማጣራት እና የሂሳብ ማወራረድ ሥርዓትን ያጠቃልላል፤

29.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴት ጾታንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ የብሔራዊ ክፍያ ሥርዓትን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ስለብሔራዊ ባንክ ሥልጣንና ተግባር እና ፈቃድ ስለመስጠት</u>

4. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ብሔራዊ ባንክ፦

ሀ) ከፍተኛ ዋጋ ያለው ገንዘብ እና አነስተኛ ገንዘብ የማስተላለፍ ስርዓቶችን የያዘ የተቀናጀ የክፍያ ሥርዓት፤ እና

ለ) ማዕከላዊ የገንዘብ ሰነዶች ግምጃ ቤትን፤

ያቋቁማል፣ በባለቤትነት ይይዛል፣ ስራውን ያከናውናል፣ በስርዓቱ ይሳተፋል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 5(15) ከተሰጠው ስልጣን በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) ሰዎች፦

1) ስርዓትን እንዲያቋቁሙና እንዲያከናውኑ፤ እና

2) የክፍያ መፈፀሚያ መሳሪያዎችን እንዲያወጡ፤

ፈቃድ የመስጠት።

ለ) በሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነዶችን የመሰየም እና እነዚህን በሚመለከት ገደቦችን፣ ሁኔታዎችን እና ደረጃዎችን የመወሰን፤

ሐ) ለስርዓቶች አስተዳደር፣ አሰራርና አመራር ገደቦችን፣ ደንቦችን፣ የአሰራር መመሪያዎችንና ደረጃዎችን የማውጣትና መከበራቸውን በየጊዜው የማረጋገጥ፤

መ) ተሳታፊዎችና ኦፐሬተሮች፦

1) የሥርዓት መሠረተ ልማቶችን ለመገንባትና እርስ በርሳቸውም ተናባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ኢንቨስትመንት፤

2) ወጪ ስለሚጋሩበት ሁኔታ፤

3) ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉትን ክፍያ፤ እና

4) በአንድ ጊዜ በጥሬ ገንዘብ መክፈል የሚችሉትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን፤

የመወሰን።

ሠ) ኦፐሬተሮች፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪዎች ዳይሬክተሮችና ዋና ስራ አስፈፃሚዎች ማሟላት የሚገባቸውን መሠረታዊ መስፈርቶች የማውጣት፤

ረ) ለተሳታፊዎች ወይም ለግብይት ማዕከል የአጭር ጊዜ ብድር የመስጠት፤

ሰ) ለፌዴራል መንግሥት የዋስትና ሰነዶች የግብይት ማዕከል የመሆን፤

ሸ) ለተሳታፊዎች የባለአደራነትና የሂሣብ የማወራረድ አገልግሎት የመሥጠት፤

ቀ) ብሔራዊ የክፍያ ስርዓት የተሳለጠ እንዲሆን ለማስቻል በዋስትና የሚያዙ ንብረቶችን ባህሪ፣ ፎርም፣ ተፈፃሚነት እና ሽጦ ዕዳን የመሰብሰብ ዘዴን በተመለከተ የመወሰን፤

በ) ኦፐሬተር፣ ተሳታፊ ወይም ሂሣብ ማጣሪያ ተቋም፦

1) ሥጋትን ስለመጋራትና የመቆጣጠሪያ ስልቶች፤
2) የሂሣብ ማጣሪያ ተቋማት አሰራር ስርዓትና የፋይናንስ አቋም አስተማማኝነት፤ እና
3) ለፋይናንስ ሥርዓቱ ሥጋት ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ ስለሚገምታቸው ሌሎች ጉዳዮች፤

ትዕዛዝ የመስጠት ወይም ከእነዚሁ ጋር ማናቸውም ዓይነት ስምምነት የመፈፀም።

ተ) ብሔራዊ ክፍያ ስርዓትን በተመለከተ የፖሊሲና የጋራ ጉዳዮች የምክክር መድረክ የመሆን፤

ቸ) የክፍያ ስርዓትን በተመለከተ የቁጥጥርና የክትትል ሥልጣን ካላቸው ከሌሎች ሃገራት የገንዘብና አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የመተባበር፤ እና

ኀ) ከብሔራዊ ክፍያ ስርዓት ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ሌሎች ተግባራት የማከናወን።

5. <u>ፈቃድ ስለመስጠት እና ስለክልከላ</u>

1. ከብሔራዊ ባንክ በስተቀር ሌላ ማንኛውም ሰው ከባንኩ ፈቃድ ሳያገኝ የአንድ ሥርዓት ኦፕሬተር መሆን አይችልም።
2. የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 165/2002 ለሚያከናውነው የፋይናንስ አገልግሎት ተግባር በዚህ አዋጅ መሠረት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የማግኘትና ባንኩ በዚህ ረገድ ለሚያካሂዳቸው አስፈላጊ የቁጥጥርና ክትትል ሥራዎችም ተገዢ መሆን አለበት፡
3. ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ማናቸውም ኦፕሬተር፡-

ሀ) አዲስ ስርዓት በስራ ላይ ማዋል፤

ለ) ከሌላ ኦፕሬተር ጋር መዋሃድ ወይም የሌላ ሰው ሥርዓት ባለቤትነት መረከብ፤

ሐ) በመቀላቀልም ሆነ በሌላ መንገድ የኦፕሬተሩን ሥራ መሸጥ ወይም ባለቤትነትን የሚያስቀሩ ማናቸውንም ዓይነት ስምምነቶች ወይም ውሎች መፈፀም ወይም በሥራ ዘርፉ ላይ ዓይነተኛ ለውጥ ማድረግ፤

መ) አክሲዮኑን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ካፒታሉን መቀነስ፤

ሠ) የመመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል፤ ወይም

ረ) ስርዓቱን የሚያካሂድበትን የንግድ ስም መቀየር፤

አይችልም።

4. ብሔራዊ ባንክ በፅሁፍ በተሰጠ ማስታወቂያ፦

ሀ) አንድ ስርዓት ለብሔራዊ የክፍያ ስርዓቱ አስተማማኝነት፣ ደህንነት፣ የተቀላጠፈ መሆን እና መሣለጥ ጎጂ ከሆነ፤ ወይም

ለ) ክልከላው የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

የማናቸውም ኦፐሬተር ሥርዓት እንዳይሰራ መከልከል ይችላል።

6. <u>ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. ሥርዓትን ለማቋቋምና ለማካሄድ ፈቃድ ለማግኘት ለብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ መቅረብ አለበት።
2. ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው በብሔራዊ ባንክ የሚወሰነውን የፈቃድ ማውጫ ክፍያ መክፈል አለበት።
3. ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻው እንደደረሰው በጥያቄው ላይ መወሰን እንዲያስችለው አመልካቹ ስላቀረበው ዝርዝር መረጃ ትክክለኛነት፣ ሥርዓቱን ለማከናወን ስላለው ብቃት፣ የሥርዓቱ ተሳታፊዎች ስላቀረቧቸው የብቃት ማረጋገጫዎች፣ እንዲሁም ስለሌላ ማናቸውም ከማመልከቻው ጋር ስለተያያዘ ጉዳይ አስፈላጊ የመሰለውን ማጣራት ሊያደርግ ይችላል።
4. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀፅ ንውስ አንቀፅ (3) የተመለከተውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የቀረበው ማመልከቻ የተሟላና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በባንኩ በወጡ መመሪያዎችን የተከተለ መሆኑን ሲያምንበት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ለሥርዓቱ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፦

ሀ) ኦፐሬተሩ ለማቋቋም ያቀደው ሥርዓት ወይም ለመስጠት ያቀደው አገልግሎት ተፈላጊነት፤

ለ) የታቀደው ሥርዓት የቴክኒክ ደረጃና የአሠራር ንድፍ፤

ሐ) የደህንነት መመሪያዎችን ጨምሮ የታቀደው ሥርዓት የሚመራባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች፤

መ) የሂሣብ ማጣራትና ማቻቻል ዝርዝር ሁኔታዎችን ጨምሮ በሥርዓቱ ገንዘብ የሚተላለፍበትን ሁኔታ፤

ሠ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቋም፣ የማስተዳደር ልምድ እና ታማኝነት፤

ረ) የተገልጋዮች ጥቅም የሚከበርበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከኦፕሬተሩ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚገዛበት ዝርዝር ሁኔታ፤

ሰ) በገንዘብና ብድር ፖሊሲ ላይ ስለሚኖረው ፋይዳ፤ እና

ሸ) ከብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት ጋር በተያያዘ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ሌሎች ሁኔታዎች።

5. ብሔራዊ ባንክ ከአመልካቹ የሚፈለጉ መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6. ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለማግኘት ከአመልካች ስለሚያስፈልጉ መረጃዎችና ሌሎች ተጨማሪ ሁኔታዎች መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

7. <u>ፈቃድን ስለማገድ</u>

1. ማናቸውም ኦፕሬተር፦

ሀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ከተላለፈ፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚጠይቃቸውን መረጃዎች በትክክልና በወቅቱ ካላቀረበ፤

ሐ) ከብሔራዊ ባንክ የተላለፈለትን ትዕዛዝ ካላከበረ፤ ወይም

መ) ብሔራዊ ባንክ በአንቀጽ 9(1) መሠረት ፈቃዱ እንዲሰረዝ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የኦፕሬተሩ በሥራ መቆየት በሀገሪቱ የክፍያ ሥርዓት ደህንነት አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ወይም የፋይናንስ መረጋጋት ላይ አደጋ ያደርሳል ብሎ ካመነ፤

ብሔራዊ ባንክ ጉድለቶቹ እስኪስተካከሉ ወይም የማጣራቱ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ ፈቃዱን አግዶ ማቆየት ይችላል፡፡

2. ፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ሲታገድ ብሔራዊ ባንክ ፈቃዱ የታገደበትን ምክንያት እና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ጉድለቶቹን ለማስተካከል ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ለኦፕሬተሩ በጽሁፍ ያስታውቃል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የጽሁፍ ማስታወቂያ የደረሰው ኦፕሬተር በማስታወቂያው በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ጉድለቱን የማስተካከል ግዴታ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ያሉት ድንጋጌዎች ቢኖሩም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተዘረዘሩት ጥፋቶች መከሰታቸው በሀገሪቱ የክፍያ ሥርዓት ደህንነት አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ወይም የፋይናንስ መረጋጋት ላይ አደጋ ያደርሳል ብሎ ካመነ ብሔራዊ ባንክ የኦፐሬተሩን ፈቃድ ሊሰርዘው ይችላል፡፡

8. <u>**የፈቃድ ማገድ ውጤት**</u>

ፈቃዱ የታገደበት ማንኛውም ኦፐሬተር በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲያከናውን የተፈቀደለትን ማንኛውንም ሥራ መፈጸም አይችልም።

9. <u>**ፈቃድን ስለመሰረዝ**</u>

1. ማናቸውም ኦፐሬተር፡-
   ሀ) ፈቃዱ የተሰጠው ሐሰተኛ ወይም የተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
   ለ) ፈቃዱ ከተሰጠባቸው ዓላማ ወይም ሁኔታዎች ተጻራሪ በሆነ አኳኋን ሥርዓቱን ካካሄደ፤
   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት የእርምት እርምጃ የተወሰደበትን ጉድለት ደግሞ ከፈፀመ፤
   መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ጉድለቱን ካላስተካከለ፤
   ሠ) ፈቃድ በተሰጠው በ12 ወራት ውስጥ ሥራ ካልጀመረ፤
   ረ) ከከሰረ፣ ከፈረሰ ወይም ሥራውን ካቆመ፤ ወይም
   ሰ) የንግድ ፈቃዱ ከተሰረዘ፤

   ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለፁት ምክንያቶች ፈቃዱ እንዲሰረዝ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ብሔራዊ ባንክ እንደ አስፈላጊነቱ ኦፐሬተሩ በፅሁፍ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም ኦፐሬተሩ ጥያቄው

ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሠላሳ ቀናት ውስጥ አስተያየቱን በጽሁፍ ያላቀረበ ወይም ያቀረበው አስተያየት በቂ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ ፈቃዱን ይሰርዛል።

10.<u>**በወኪል ስለመስራት**</u>

1. ከክፍያ መፈፀሚያ ሰነዶች ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በተወካይ አማካይነት የሚሰጥ ሰው፦

   ሀ) የተወካዩን ስምና አድራሻ፤

   ለ) በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ድርጊትን ከመቆጣጠር ጋር በተያያዘ የተቀመጡትን ግዴታዎች ለመፈፀም እንዲያስችለው ተወካዩ የዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስልት ዝርዝር መግለጫ፤ እና

   ሐ) አገልግሎቱን በመስጠት ሂደት የተወካዩን ስራ ለመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች ማንነት፣ እንዲሁም ባንኩ ባወጣው መመሪያ መሠረት ሰዎቹ ብቁና ተገቢ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፤

   ለብሔራዊ ባንክ ወዲያውኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት መረጃዎች በደረሱት ጊዜ ለሕዝብ ክፍት በሆነ መዝገብ ላይ የተወካዩን ስም ማስፈር አለበት።

3. ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ተወካዩን በመዝገቡ ላይ ከማስፈሩ በፊት የቀረበውን መረጃ ትክክለኛነት ማጣራት ይችላል፡፡

4. ብሔራዊ ባንክ ወኪሉ ብቁና ተገቢ ሆኖ ካላገኘው በመዝገቡ ውስጥ ላለመመዝገብ ይችላል፡፡ ባንኩ ወኪሉን ላለመመዝገብ ከወሰነ ወካዩ ከተወካዩ ጋር ያለውን የውክልና ውል አቋርጦ ለደንበኞቹ ማስታወቅ ይኖርበታል።

5. ብሔራዊ ባንክ ለኦፐሬተርና ለክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ወኪል ለመሆን መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

11.<u>**ተፈጻሚነትን የማረጋገጥ ግዴታ**</u>

ኦፕሬተሮች ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ስነድ አውጪዎች ሥራዎቻቸውን ለማከናወን ሶስተኛ ወገኖችን ወይም ወኪሎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ፣ እነዚህ አካላት የዚህን

አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማክበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

## ክፍል ሶስት

## ሂሳብ ማወራረድ፣ ማቻቻል እና ፍፃሜ ክፍያ

12. **የማወራረጃ ሂሳብና ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳትፎ**

1. እያንዳንዱ ቀጥተኛ የሥርዓት ተሳታፊ ዝቅተኛ ተቀማጭ ገንዘብን ጨምሮ በብሔራዊ ባንክ ወይም በተፈቀደለት የሂሳብ ማወራረድ ስርዓት ኦፕሬተር በሚወሰኑ ውሎችና ሁኔታዎች መስረት በባንኩ ወይም በኦፕሬተሩ ዘንድ ሂሳብ መክፈትና መያዝ አለበት።
2. እያንዳንዱ ቀጥተኛ ያልሆነ የሥርዓት ተሳታፊ የበሰሉ ግዴታዎቹን እንደወኪል ሆኖ የሚያወራርድለት ቀጥተኛ የሥርዓት ተሳታፊ መሰየም አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳታፊ ቀጥተኛ ተሳታፊን እንደወኪል በሚሰይምበት ጊዜ ተወካዩ ከወካዩ የተሰጠውን የፅሁፍ ማረጋገጫ አባሪ በማድረግ ለኦፕሬተሩ በፅሁፍ ማስታወቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተሰጠውን ውክልና ለማቋረጥ የፈለገ ተወካይ ውክልናው ከሚያበቃበት ቢያንስ 15 ቀን አስቀድሞ ለኦፕሬተሩ በፅሁፍ ማስታወቅ አለበት።

13. **ክፍያዎችን ስለማወራረድ**

1. በሥርዓት ተሳታፊዎች መካከል የሂሣብ ማወራረድ ግዴታ መወጣት የሚቻለው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት በተከፈተ የማወራረጃ ሂሳብ ውስጥ ብሔራዊ ባንክ ወይም የተፈቀደለት የሂሣብ ማወራረድ ሥርዓት በሚፈፅመው ገቢ ወይም ወጪ ምዝገባ ነው፡፡
2. የብሔራዊ ባንክ ወይም የተፈቀደለት የሂሣብ ማወራረድ ሥርዓት ደንቦች እንደአግባቡ በኦፕሬተር፣ በሂሣብ ማጣሪያ ተቋም፣ በተሳታፊ፣ በግብይት ማዕከል፣ በብሔራዊ ባንክ በራሱ እና በሥርዓቱ በሚሳተፍ ሌላ ማናቸውም አካል ላይ ተፈፃሚና አስገዳጅ ይሆናሉ።

14. **ስለፍፃሜ ክፍያ**

1. ማናቸውም ስርዓት በአሠራሩ ፍፃሜ ክፍያ ላይ ስለሚደርስበት ሁኔታ ደንብ ማውጣት አለበት። ይህም የክፍያ ትዕዛዞች አንዴ በሥርዓቱ የሂሳብ መዝገብ ውስጥ ከስፈሩ በኋላ ሊሻሩ እንደማይችሉ የሚወስኑትን ደንቦች ማካተት አለበት፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በወጣው ደንብ መሠረት በሂሣብ መዝገብ የገባ ወይም የተፈፀመ ክፍያ የመጨረሻ ሲሆን ዕዳን ለመክፈል ባለመቻል ወይም በመክሰር ወይም ተመሳሳይ ዓላማና ውጤት ባለው ማናቸውም ሕግ ወይም ልማድ ምክንያት ሊሻር፣ ሊቀለበስ፣ ወይም ሊሰረዝ ወይም በማናቸውም ሕግ ወይም የአስተዳደር ትዕዛዝ መሠረት የተሰጠ የአስተዳደር ወይም የፍርድ ዕግድ ሊጣልበት አይችልም።
3. ብሔራዊ ባንክ ስለፍፃሜ ክፍያ፣ ሂሳብ ስለማወራረድ፣ ስለማቻቻል እንዲሁም ኪሳራ ስለመጋራትና ስለመከፋፈል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

15.<u>ስለማስታወቅ</u>

1. ማንኛውም በብሔራዊ ክፍያ ስርዓት ውስጥ ያለ ኦፕሬተር፣ ተሳታፊ ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ከከሰረ፣ በመጠበቂያ ስምምነት ሥር እንዲውል ከተደረገ ወይም ከፈረሰ ጉዳዩን በሚመለከት የተወሰነውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ቅጂ ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።
2. የመክሰር፣ የመፍረስ ወይም በመጠበቂያ ስምምነት ሥር እንዲውል የተሰጠን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ያቀረበ ማናቸውም ኦፕሬተር፣ ተሳታፊ ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ በማናቸውም ስርዓት ሊሰራ ወይም ሊሳተፍ አይችልም።

16.<u>የተሳታፊ መፍረስ ወይም በመጠበቂያ ስምምነት ሥር መሆን</u>

ዕዳን መክፈል ስላለመቻል ወይም መክሰርን አስመልክቶ በወጡ ማናቸውም ሕጎች ላይ በተቃራኒው የተመለከተ ድንጋጌ ቢኖርም የተሳታፊ መፍረስ ወይም በመጠበቂያ ስምምነት ሥር መዋል ስለጉዳዩ ትዕዛዝ ለብሔራዊ ባንክ ከመድረሱ በፊት ፍፃሜ ክፍያ አግኝተው የመጨረሻ እና የማይሻሩ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት በተመዘገቡ ክፍያዎች ላይ ውጤት አይኖረውም።

17.<u>በሒሳብ አጣሪዎች ላይ አስገዳጅነት ያላቸው ስምምነቶችና ደንቦች</u>

ዕዳን መክፈል ስላለመቻል ወይም መክሰርን አስመልክቶ በወጡ ሌሎች ህጎች በተቃራኒ የተመለከተ ማናቸውም ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ተሳታፊ ከፈረሰ

ወይም በመጠበቂያ ስምምነት ሥር እንዲውል ከተደረገ ወይም በፍርድ ቤት የመክሰር ውሳኔ ከተሰጠ ተሳታፊው ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓትን በሚመለከት ተዋዋይ የሆነባቸው ስምምነቶች፣ የማቻቻል ደንቦች ወይም የስርዓቱ ልምዶች በሒሳብ አጣሪው ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

18.<u>ለክፍያና ለሂሣብ ማወራረድ ግዴታዎች ስለሚሰጥ መያዣ</u>

ክፍያን ለመፈጸም ወይም ግዴታን ለመወጣት ሲባል ከተሰጠ መያዣ ጋር በተያያዘ የሚኖሩ የኦፐሬተር፣ የተሳታፊ፣ የሂሳብ ማጣሪያ ተቋም እና የግብይት ማዕከል መብቶች እና ማካካሻዎች ዕዳን ለመክፈል ባለመቻል ወይም በመፍረስ ሥነ-ሥርዓቶች ወይም ተመሳሳይ ዓላማና ውጤት ባለው ማናቸውም ሌላ ሕግ ሊጣበቡ አይችሉም። በተለይም እነዚህ ወገኖች በመያዣው ላይ ያላቸውን መብቶችና ማካካሻዎች ለማስፈፀም የሚኖራቸውን ችሎታ የሚያጣብብ ማናቸውም ዕግድ ሊሰጥ አይችልም።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ስለማስተላለፍ</u>

19.<u>የውል ግዴዎች</u>

1. ማናቸውም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ከኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ማስተላለፍና ከተከማቸ እሴት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ለሁሉም ተገልጋዮች በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆን ግልጽና ወጥ የሆነ ናሙና የውል ግዴታዎች ተገልጋዮቹ መርምረው መስማማት እንዲችሉ አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከቱት ወጥ ሆነው የተዘጋጁ ናሙና የውል ግዴታዎች እንዲሁም በየጊዜው የሚደረጉባቸው ማሻሻያዎች በብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ መጽደቅ አለባቸው።
3. ብሔራዊ ባንክ በኤሌክትሮኒክ የሚተላለፍ ገንዘብንና የተከማቸ እሴት አገልግሎትን በሚመለከት በተዋዋይ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መሠረታዊ የውል ግዴታዎችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

20.<u>የቅሬታ አፈታት</u>

1. ኦፐሬተሮች፣ ተሳታፊዎችና የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪዎች በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ከማስተላለፍና ከተከማቸ እሴት አገልግሎት ጋር በተያያዘ

የተጠቃሚዎችን ቅሬታ የሚያስተናግዱበት የውስጥ አሰራር መዘርጋትና ቅሬታው የሚቀርብበትን ስርዓት ለተጠቃሚዎች ማሳወቅ አለባቸው።

2. ብሔራዊ ባንክ ከኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ማስተላለፍና ከተከማቸ እሴት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ስለሚመረመሩበትና ስለሚስተናገዱበት ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

21.<u>የኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽን</u>

1. ማናቸውም መረጃ ወይም ጉዳይ በጽሑፍ እንዲሆን የሚያስገድድ ሕግ ወይም ስምምነት ሲኖር ይህ መረጃ ወይም ጉዳይ በኤሌክትሮኒክ መልክ ከቀረበ ወይም ከተቀመጠ እና በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል የሚችል ከሆነ የመረጃውን አቀራረብ አስመልክቶ የተጠየቀው ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል።

2. ማናቸውም ተቃራኒ የሆነ ሕግ ወይም የተለመደ አሰራር ቢኖርም በሕግ ወይም በውል በኦፕሬተር ወይም ተሳታፊ በፅሁፍ ወይም በሌላ መንገድ እንዲሆን የተደነገገ መረጃ በሚከተለው አኳኋን እንዲሰጥ ተጠቃሚው ከተስማማ፦

   ሀ) በተጠቃሚው የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ወይም ተጠቃሚው በመረጠው የኤሌክትሮኒክ አድራሻ፤ ወይም

   ለ) ኦፕሬተሩ ወይም ተሳታፊው፦

      1) ተጠቃሚውን በተፋጠነ ሁኔታ በኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽን እስካስታወቀ፤ እና

      2) ተጠቃሚው መረጃውን በኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽን ማግኘት እንዲችል አድርጎ እስካዘጋጀው ድረስ፤

   በኦፕሬተሩ ወይም በተሳታፊው የኤሌክትሮኒክ አድራሻ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

22.<u>የጋራ ሥርዓት አጠቃቀም</u>

1. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል የጋራ ስርዓት አባላት ማለት በአንድ ሥርዓት ውስጥ ታቅፈው በኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽን ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ለደንበኞች የሚሰጡትን ኦፕሬተሮች፣ ተሳታፊዎች፣ ቸርቻሪዎች፣ ሌሎች ነጋዴዎች፣ የመገናኛና አገልግሎት ሰጪዎች እና ሌሎች በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን ይጨምራል።

2. የጋራ ስርዓት አባላት መብትና ኃላፊነት አባላቱ እርስ በርስ በሚያደርጉት የሁለትዮሽ ወይም የብዙዮሽ ስምምነት ይወስናል፤ ሆኖም ብሔራዊ ባንክ

ስምምነቶቹ ማካተት የሚገባቸውን መሠረታዊ መብቶችና ኃላፊነቶች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

3. ኦፕሬተሮች፣ ተሳታፊዎች ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪዎች የጋራ ስርዓት አባል መሆናቸውንና ግዴታቸውን ያልተወጡት በሌላ አባል ጥፋት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ለተጠቃሚው ካለባቸው ግዴታ ሊያመልጡ አይችሉም፡፡
4. ማናቸውም ኦፕሬተር፣ ተሳታፊ ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ከኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ማስተላለፍ ስርዓት ወይም ከተከማቸ እሴት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከተገልጋዮቹ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ወይም የሚነሱ አለመግባባቶችን በተፋጠነ ሁኔታ በውስጡ በመሠረተው ሥርዓት መፍታት አለበት፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ሰዎች ተገልጋዮች ጉዳያቸውን ለሌላ የጋራ ሥርዓት አባል እንዲያቀርቡ ወይም ቅሬታቸውን ወይም አለመግባባቶቹን በሌላ አካል እንዲያስመረምሩ ሊጠይቁ አይችሉም፡፡

23.<u>**የኤሌክትሮኒክ መረጃ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ**</u>

1. በሌላ ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በሌላ አኳኋን የተደነገገ ቢኖርም በማናቸውም ሥርዓት የተላለፈን ክፍያ በሚመለከት በሰነድ፣ በኮምፒውተር ሕትም፣ በወረቀት ቅጂ፣ በማይክሮ ፊልም፣ በፍሎፒ ወይም ሀርድ ዲስክ ወይም በማናቸውም የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም መልክ የሚገኝ መረጃ ለማንኛውም ፍርድ ቤት ከቀረበ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
2. በፊልም፣ በማይክሮ ፊልም፣ በማይክሮፊሽ ወይም በኮምፒውተር የተያዙ የቼክ፣ የዋስትና ሰነዶች፣ የተቀማጭ ገንዘብ ምስክር ወረቀቶች፣ የሂሳብ መዝገቦች፣ የመንግሥት የዋስትና ሰነዶች ወይም የሌሎች የክፍያ መፈፀሚያ ሰነዶች የፎቶግራፍ ምስሎች በኦርጅናል ሰነዶቹ ላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች ወይም የሂሣብ እንቅስቃሴዎች ትክክለኛነት ለማስረዳት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡፡
3. የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ጨምሮ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የመነጨ፣ የተካሄደ ወይም የተፈፀመ የክፍያ ትዕዛዝ፣ መልዕክት ወይም ገንዘብ ማስተላለፍ የተከናወነውን ጉዳይ ወይም የሂሣብ እንቅስቃሴ ትክክለኛነት ለማስረዳት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

4. ብሔራዊ ባንክ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ስለሚተላለፍበት መንገድ እና የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ጨምሮ ስለ ኤሌክትሮኒክ ሰነዶች አያያዝ ደረጃዎች፣ ፎርማቶችና ሁኔታዎች መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

24.<u>ምስልን ለክፍያ ስለማቅረብ</u>

1. ቼክን ወይም ሌላ በወረቀት ላይ የሰፈረ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድን ምስሉንና ተዛማጅ መረጃውን ወደ ኤሌክትሮኒክ መረጃ በመለወጥና በማከማቸት ኦርጅናሉን የክፍያ ሰነድ እንዲተካ ማድረግ ይቻላል፡፡
2. በአንድ ሥርዓት አማካኝነት የተላለፈ የቼክ ወይም በወረቀት መልክ የተዘጋጀ ማናቸውም የክፍያ መፈጸሚያ ስነድ ምስል የወከለውን ሰነድ ያህል ተቀባይነት ይኖረዋል።
3. ምስሉን በመጠቀም ክፍያ አንድ ጊዜ ከተፈፀመ በኋላ ዋናው ወረቀት ለድርድር የማይቀርብና ሊወገድ የሚችል ነው።
4. በምስሉ አማካይነት በማናቸውም ምክንያት ክፍያ ካልተፈፀመ ዋናው ወረቀት ለክፍያ ሊቀርብ ይችላል።
5. ብሔራዊ ባንክ የወረቀት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነዶች ወደ ምስል ስለሚለወጡበት ሁኔታና አሰራሩ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ስለቁጥጥር እና ክትትል</u>

25.<u>የተፈቀደለት ሥርዓት ደንቦች</u>

1. እያንዳንዱ ኦፕሬተር የሚያካሂደውን ሥርዓት በተመለከተ የአስተዳደር፣ የአመራርና አሠራር ደንቦችን በፅሁፍ ማዘጋጀትና በሥራ ላይ ማዋል አለበት።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተመለከቱት ደንቦች በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለባቸው።
3. ብሔራዊ ባንክ፦

ሀ) መሻሻሉ ወይም መሻሩ ለሕዝብ የሚሰጠውን ጥቅም፤

ለ) የሥርዓቱ ተሳታፊ የሆኑትን ጥቅም፤

ሐ) ወደፊት የሥርዓቱ ተሳታፊ ለመሆን ለሚያስቡ ሰዎች ያለውን ፋይዳ፤ እና

መ) ሌሎች ለሥርዓቱ መሳለጥ፣ አስተማማኝነት እና ደህንነት አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ጉዳዮች፤

ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የወጣውን ማናቸውንም የኦፕሬተሩን ደንብ ለማሻሻል ወይም ለመሻር ይችላል፡፡

4. በተፈቀደለት ሥርዓት ተዘጋጅተው በሥራ ላይ የዋሉ ደንቦች፦

ሀ) በደንቡ ላይ ተመልክቶ እንደሆነ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ ሲያበቃ፤

ለ) ደንቡ በብሔራዊ ባንክ ሲሻር፤

ሐ) ኦፕሬተሩ በፈቃዱ ስራውን ሲያቆም፤ ወይም

መ) የኦፕሬተሩ ፈቃድ ሲታገድ ወይም ሲሰረዝ፤

ተፈፃሚነታቸው ቀሪ ይሆናል።

## 26.<u>በስርዓት ላይ ስለሚደረግ ለውጥ</u>

ማንኛውም ኦፕሬተር፦

1. ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ፤ እና
2. ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ካገኘ በኋላ ከ30 ቀናት ለማያንስ ጊዜ ለሥርዓቱ ተሳታፊዎች ሳያሳውቅ፤

የሥርዓቱን መዋቅር፣ አሰራር ወይም አስተዳደር መለወጥ አይችልም።

## 27.<u>ስለፋይናንስ መዝገቦች</u>

1. ብሔራዊ ባንክ የተፈቀደላቸው ኦፕሬተሮች፣ ተሳታፊዎች፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪዎች እና የግብይት ማዕከሎች የሂሳብ መግለጫቸውን በዓለም አቀፍ የሂሣብ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች ተከትለው እንዲያዘጋጁ መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰ ማናቸውም ተቋም፦

ሀ) ያለበትን ሁኔታ በግልፅና በትክክል በሚያሳይ፤

ለ) የሥራ እንቅስቃሴውንና የፋይናንስ አቋሙን በሚገልፅ፤ እና

ሐ) ሥራውን በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት እያካሄደ ስለመሆኑ፤

ብሔራዊ ባንክ ማረጋገጥ በሚያስችለው ሁኔታ መዝገቦቹን መያዝ አለበት፡፡

3. ኦፕሬተሮች፣ ተሳታፊዎችና የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪዎች የሚያከናውኑትን እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴ ዓይነት መዝግበው ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል። የእነዚህን ሰነዶች ፎርምና በውስጣቸውም የሚመዘገቡትን ጉዳዮች ብሔራዊ ባንክ ሊወስን ይችላል፡፡

4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መፃሕፍት አዋጅ ቁጥር 179/1991 ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ አፐሬተሮች፣ ተሳታፊዎች፣ የግብይት ማዕከሎች እና የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪዎች በሚያከናውኑት ተግባር እና የአስተዳደር እንቅስቃሴ የያዙትን ስነድና መረጃ በሙሉ ሰነዱ ወይም መረጃው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ለ10 ዓመት ጠብቀው ማቆየት አለባቸው።
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) ላይ የተመለከተው መረጃ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊያዝ ይችላል።

28.<u>ኦዲትና ምርመራ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ የማናቸውንም ኦፐሬተር፣ ተሳታፊ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የግብይት ማዕከል ሂሳብ፣ መዝገብ፣ ሰነዶችና ሌሎች ማናቸውንም ረኮርዶች ለመመርመር ወይም በገለልተኛ ኦዲተሮች ለማስመርመር ይችላል፡፡ ለዚህም ሲባል ተመርማሪ ወገኖች ብሔራዊ ባንክ ወይም ኦዲተሮቹ ስራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ አለባቸው፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በቅድሚያ አሳውቆ ወይም ሳያሳውቅ የኦፐሬተርን፣ የተሳታፊን፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪን ወይም የግብይት ማዕክልን የሥራ ቦታዎች፣ የሥራ መገልገያዎች፣ የሥራ መሳሪያዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ ማሽነሪዎች፣ መዝገቦች ወይም ሌሎች ሰነዶች፣ ሂሳቦች ወይም የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገቦች መመርመር ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ኦፐሬተር፣ ተሳታፊ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የግብይት ማዕከል በብሔራዊ ባንክ በተጠየቀ ጊዜ መዝገቦችን፣ ቃለ ጉባኤዎችን፣ የሂሳብ መዝገቦችን፣ የፋይናንስ ሰነዶችን፣ የዋስትና ሰነዶችን፣ የክፍያ ደረሰኞችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውም ከራሱ ወይም ከሥራ ሸሪኩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች በብሔራዊ ባንክ ለተመረጠ ማንኛውም መርማሪ ወይም ኦዲተር ባንኩ፣ መርማሪው ወይም ኦዲተሩ በሚወስነው ጊዜ እና ሁኔታ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ያገኘውን መረጃ፦

ሀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም፤

ለ) የክፍያ ስርዓቱን አስተማማኝነት፣ ውጤታማነትና ደሕንነት ለማረጋገጥ፤

ሐ) በህግ ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት፤

መ) በፍርድ ቤት ሲታዘዝ፤

ሠ) ባንኩ ተጠሪ ለሆነለት አካል፤ ወይም

ረ) ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ግዴታዎች ለመወጣት፤

ካልሆነ በስተቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሌላ ማንኛውም ሰው መግለጽ የለበትም።

29.<u>የውጭ ኦዲተሮች ሹመትና ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ኦፕሬተር፣ ተሳታፊ ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ የውጭ ኦዲተር ይሾማል። የኦዲተሩም ሹመት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፡፡
2. ኦፕሬተሩ፣ ተሳታፊው ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪው በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው የውጭ ኦዲተር ለመሾም ያልቻለ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ ኦዲተሩን ይሾምለታል። በዚህ ሁኔታ የተሾመው ኦዲተር ክፍያም በብሔራዊ ባንክ ተወስኖ ኦዲተሩ በተሾመለት ሰው የሚከፈል ይሆናል፡፡
3. ብሔራዊ ባንክ የውጭ ኦዲተሮች ለመሾም ብቁ የሚያደርጓቸውን መሠረታዊ መስፈርቶችና የአገልግሎት ዘመን ይወስናል።
4. የውጭ ኦዲተሩ ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ፦
   ሀ) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ማስታወቂያ ወይም ትዕዛዝ መጣሱን ወይም ያለመከበሩን፤ ወይም
   ለ) የማጭበርበር ወይም ሌላ የዕምነት ማጉደል ወንጀል ስለመፈፀሙ የሚያረጋግጥ ማስረጃ መኖሩን፤

   ሲደርስበት ጉዳዩን ወዲያውኑ ኦዲት ለሚደረገው ሰው፣ ለብሔራዊ ባንክ እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው የህግ አስፈፃሚ አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡
5. ብሔራዊ ባንክ በውስጥም ሆነ በውጭ ኦዲተሮች በኦዲት ተደራጊው ላይ የቀረበውን ማናቸውንም ሪፖርት ቅጂ ማግኘት ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) ወይም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የተሾመ ኦዲተር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) ወይም (5) የተደነገገውን ወይም በብሔራዊ ባንክ የቀረበውን የመረጃ ጥያቄ በማክበሩ ምክንያት አይጠየቅም።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**30.ስለአገልግሎት ክፍያ**

ብሔራዊ ባንክ ከኦፕሬተሮች፣ ከተሳታፊዎች እና ክክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪዎች የአገልግሎት ዋጋ ሊሰበስብ ይችላል፡፡

**31.አለመግባባትን ስለመፍታት**

1. በዚህ አዋጅ የተሸፈነ የብሔራዊ የክፍያ ስርዓት ጉዳይን አስመልክቶ በሥርዓቱ ተዋናዮች መካከል የሚነሳ ማናቸውም የፍትሐብሔር አለመግባባት በእርቅ ይፈታል፡፡
2. አለመግባባቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተደነገገው በእርቅ ለመፍታት ያልተቻለ እንደሆነ ጉዳዩ በሽምግልና ዳኝነት ይፈታል።
3. ስለይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት በሽምግልና ዳኝነት የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና በተከራካሪ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
4. ብሔራዊ ባንክ ከብሔራዊ የክፍያ ስርዓት ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች በዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች መሠረት ስለሚፈቱበት ሁኔታ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**32.ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት ምክር ቤት**

መንግሥት ብሔራዊ የክፍያ ስርዓትን በሚመለከት ብሔራዊ ባንክን የማማከር ሚና የሚኖረው ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት ምክር ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**33.በቅን ልቦና ለተፈፀመ ድርጊት የተሰጠ ጥበቃ**

ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ትዕዛዝ ወይም የአሠራር ሥርዓትን ለማስፈፀም ሲባል ብሔራዊ ባንክ ወይም ማንኛውም የብሔራዊ ባንክ ኃላፊ፣ ሠራተኛ ወይም ወኪል በቅን ልቦና ለሚፈፅመው ማናቸውም ድርጊት ሊከሰስ አይችልም።

34.<u>ሕግን ስለመጣስ እና ስለአስተዳደራዊ እርምጃ</u>

ብሔራዊ ባንክ ኦፕሬተር፣ ተሳታፊ ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ፣ ትዕዛዝ ወይም የአሠራር ሥርዓት መጣሱን ካረጋገጠ እንደአግባቡ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት አንድ ወይም ከዚያ በላይ አስተዳደራዊ ዕርምጃዎችን መውሰድ ይችላል፦

1. ለጥፋተኛው የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣
2. በጥፋተኛው ላይ ገደብ መጣል ወይም ጥሰቱ ለቀጠለበት ለእያንዳንዱ ቀን እስከ ብር 20,000 የሚደርስ ገንዘብ መቅጣት፤
3. የጥፋተኛውን ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች ከስራቸው ማገድ ወይም ማሰናበት፤ ወይም
4. የጥፋተኛውን የሥራ ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ።

35.<u>ስለ ጥፋትና ቅጣት</u>

1. በሌላ ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር የዚህን አዋጅ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ (1) ወይም አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ የጣሰ ማንኛውም ሰው ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና የጥሰት ድርጊቱ ለቀጠለበት ለእያንዳንዱ ቀን ብር 20,000 መቀጫ ይቀጣል።
2. የኦፕሬተር፣ የተሳታፊ ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ዳይሬክተር፣ ስራ አስኪያጅ ወይም ስራተኛ፦
   ሀ) ኦዲተር ወይም በብሔራዊ ባንክ በአግባቡ የተወከለ ኢንስፔክተር በዚህ አዋጅ መሠረት ስራውን በተገቢው ሁኔታ እንዳያከናውን መሰናክል ከሆነ፤
   ለ) የኦፕሬተሩ፣ የተሳታፊው ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ሂሳብ፣ መዝገብ ወይም ሪከርድ ላይ ጉዳት ያደረሰ፣ ያወደመ፣ የቀየረ ወይም ወደ ሃሰተኛ ሰነድነት ወይም መረጃ የለወጠ ከሆነ፤ ወይም
   ሐ) በተፈቀደ ስርዓት ሂሳብ መዝገብ ውስጥ ሃሰተኛ ሪከርዶች ያሰፈረ ወይም መሠረታዊ መረጃዎችን ሳያሰፍር የቀረ ከሆነ፤ ወይም
   መ) በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት መስጠት ያለበትን መረጃ ሳይሰጥ ከቀረ ወይም ሃሰተኛ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ከሰጠ፤ ወይም

ሠ) ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት፣ ህግ ወይም መረጃውን ለመቀበል ህጋዊ ስልጣን ያለው ሰው ወይም ብሔራዊ ባንክ ካልጠየቀ ወይም ካላዘዘ በስተቀር በሚስጥር ጠብቆ ሊይዝ የሚገባውን የማንኛውንም ሰው መረጃ አሳልፎ ከሰጠ፤

ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

3. ማናቸውንም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ ያለህጋዊ ፈቃድ የሰራ ወይም አስመስሎ የሰራ ወይም የለወጠ ማንኛውም ሰው ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

4. ማናቸውንም በማስመሰል የተሰራ፣ የሌለ፣ የተለወጠ፣ የጠፋ፣ የተሰረቀ፣ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት፣ የተሰረዘ ወይም በተጨበረበረ መንገድ የተገኘ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ መሆኑን እያወቀ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ፣ ወደ ውጪ ሀገር የላከ፣ የገዛ፣ የያዘ፣ በባለአደራነት የተቀበለ፣ የሸጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ ወይም በስጦታ የለገሰ ማንኛውም ሰው ከ 5 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

5. ሀሰተኛ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ ለመስራት በማሰብ ማንኛውም መሣሪያ፣ ቅርፅ ማውጫ፣ ወረቀት፣ ብረታ ብረት ወይም ማናቸውም ሌላ ቁስ ይዞ የተገኘ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር የላከ ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈ ማንኛውም ሰው ከ7 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

6. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የቀረበለት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ በማስመሰል የተሰራ፣ የሌለ፣ የተለወጠ፣ የጠፋ፣ የተሰረቀ፣ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት፣ የተሰረዘ ወይም በተጭበረበረ መንገድ የተገኘ መሆኑን እያወቀ ሸቀጥ፣ አገልግሎት ወይም ማናቸውንም ዋጋ ያለው ጥቅም ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አምጪው የሰጠ ከሆነ፤ ወይም

ለ) በማስመሰል የተሰራን፣ የሌለን፣ የተለወጠን፣ የጠፋን፣ የተሰረቀን፣ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበትን፣ የተሰረዘን ወይም በተጭበረበረ መንገድ የተገኘን የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ በመጠቀም የተገኘ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም አገልግሎት

መሆኑን እያወቀ የተቀበለ፣ የደበቀ፣ የተጠቀመ፣ ያስተላለፈ ወይም ያጓጓዘ ከሆነ፤

ከ 2 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ እስራት እና በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

7. ማንኛውም ሰው፦

ሀ) የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ ወይም ወኪሉ ሳይሆን የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ የሸጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) ከክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪው ወይም ከወኪሉ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ሰው የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ የገዛ እንደሆነ፤

እስከ 3 ዓመት በሚደርስ እስራት እና እስከ ብር 5 ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

8. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ ንዑስ አንቀፅ (7) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደ ተጠበቁ ሆነው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ ወይም አፈፃፀማቸውን ያሰናከለ ማንኛውም ሰው እስከ 3 ዓመት በሚደርስ እስራት እና እስከ ብር 10,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

9. የሦስተኛ ወገኖች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ የተመለከተን የወንጀል ድርጊት በመፈጸም የተገኘ ማንኛውም ሀብት በመንግሥት ይወረሳል።

36.<u>የመሸጋገሪ ድንጋጌ</u>

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች አዋጁ በመጽናቱ ጊዜ በሥራ ላይ ባሉ ኦፐሬተሮች፣ ተሳታፊዎች፣ የክፍያ መፈፀሚያ ስነድ አውጪዎች እና የእነዚሁ ወኪሎች ላይ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

37.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን ማውጣት ይችላል፡፡

38. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ትዕዛዝ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

39. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ለ/ የመድህን ስራ**

**አዋጅ ቁጥር 746/2004**

**የመድን ሥራን አዋጅ**

የመድን ዘርፍ ባልታሰበ አደጋ ለሚደርሱ ጉዳቶች ሽፋን በመስጠት፣ ለገንዘብ ቁጠባ አንድ አማራጭ በመሆንና ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ገንዘብ በማሰባሰብ ለኢኮኖሚ ልማት ጉልህ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

የመድን ዘርፍ አስተማማኝና የተረጋጋ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ መኖር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

   1. "አስሊ" ማለት በመድን በተለይም ከሕይወት መድንና ከጡረታ ዋስትና ጋር በተያያዙ የፋይናንስ ጥያቄዎችና ታሳቢ ግምቶች ላይ ምክር የሚሰጥ ሰው ነው፤
   2. "ተቀባይነት ያለው ሀብት" ማለት እዳ የመክፈል ህዳግን ለማስላት የሚወሰድ የሀብት መጠን ነው፤
   3. "ተቀባይነት ያለው ዕዳ" ማለት እዳ የመክፈል ህዳግን ለማስላት የሚወሰድ የዕዳ መጠን ነው
   4. "ባንክ" ማለት የባንክ ሥራ እንዲሠራ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም የመንግስት ባንክ ነው፡፡
   5. "የካፒታል ወጪ ማለት" በመቋቋም ላይ በሚገኝ መድን ሰጪ የሚደረግ የቅድሚያ ወጪ፣ የአክስዮን ሽያጭ ኮሚሽን ክፍያ፣ የድለላ አገልግሎት ክፍያና እንደ ግዙፍ ንብረት ሊቆጠር የማይችል ሌላ ወጪ ነው፤
   6. "ዋና ሥራ አስፈጻሚ" ማለት በማንኛውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የአንድን መድን ሰጪ የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የሚመራ

ሰው ነው፤

7. "የመድን ሥራ ዓይነት" ማለት አንድ መድን ሰጪ እንደ አንድ የመድን ሥራ ዓይነት ለማካሄድ ፈቃድ ያገኘበት የመድን ሥራ ዓይነት ነው፤
8. “ኩባንያ” ማለት በንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጉም የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች ወይም በኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች በጋራ የተያዘ ወይም ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች የተያዘ ወይም በኢትየጵያውያን እና የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች በጋራ ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ፣ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፤[171]
9. "መመሪያ" ማለት በብሔራዊ ባንክ የወጣ መመሪያ ነው፤
10. "ዳይሬክተር" ማለት በማንኛውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የመድን ሰጪው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ ሰው ነው፤
11. "ሠራተኛ" ማለት የመድን ሰጪውን የዕለት ተዕለት ሥራዎች እንዲያካሂድ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ማንኛውም ሌላ ሠራተኛ ነው፤
12. “የፋይናንስ ድርጅት” ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት፣ በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት በዚህ ዘርፍ ሥር የሚመደብ ሌላ ድርጅት ነው፤[172]
13. "የሂሳብ ዓመት" ማለት እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከጁላይ አንድ ቀን ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት ጁን ሰላሳ ቀን የሚያበቃ የማንኛውም መድን ሰጪ የሂሳብ ዓመት ነው፤
14. "ጠቅላላ መድን ሥራ" ማለት በረጅም ጊዜ መድን ሥራ ውስጥ ሊካተት የማይችል ማንኛውም ዓይነት የመድን ሥራ ነው፤

---

[171] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

[172] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

15."ተደማጭነት ያለው ባለአክስዮን" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማናቸውም መድን ሰጪ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የአክስዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው፤

16."መድን" ማለት አንድ መድን ሰጪ ከመድን ገቢው አረቦን በመቀበል በመድን ውል ውስጥ በግልፅ በተቀመጡና መድን ገቢው ተጋላጭ የሆነበት የአደጋ ሥጋቶች ለሚያደርሱት ጉዳት፣ ጥፋት፣ ኪሳራ ወይም ሕጋዊ ኃላፊነትን ተከትሎ የካሣ ክፍያ ለመፈፀም የሚገባው ግዴታ ወይም በውለታው በግልፅ የተቀመጡ ሁኔታዎች የተከሠቱ እንደሆነ የተወሰነውን ገንዘብ ወይም ዋጋ ያለው ሌላ የካሣ ክፍያ ለመክፈል የሚያደርገው ስምምነት ነው፤

17."የመድን ወኪል" ማለት ኮሚሽን በማስከፈል፡-

ሀ) በመድን ሰጪው ስም በቀጥታ ከሕዝብ ጋር በመገናኘት የመድን ገበያን የሚያፈላልግ፣ እና

ለ) የመድን ውል ለመዋዋል የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶችን የሚያመቻችና የመድን ውል ቀጣይ አስተዳደርና ዕድሣትን በሚመለከት እገዛ የሚያደርግ፤

ሰው ነው፡፡

18."የመድን ረዳት" ማለት የመድን ወኪል፣ የመድን ደላላ፣ የጉዳት ገማች ወይም የመድን መርማሪ ነው፤

19. "የመድን ደላላ" ማለት ኮሚሽን በማስከፈል:-

ሀ) በመድን ገቢው ሰው ስም የመድን ውል ለማዋዋል የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶችን የሚያመቻች፤

ለ) የመድን ውል ለመዋዋል የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶችን የሚያመቻችና የመድን ውል ቀጣይ አስተዳደርና ዕድሣትን በሚመለከት ዕገዛ የሚያደርግ፤ እና

ሐ) በመድን ውለታና በካሣ ክፍያ ጥያቄ ላይ ለመድን ገቢው የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ፤

ሰው ነው፡፡

20."የመድን ፖሊሲ" ማለት ማንኛውም መድን ሰጪ አረቦን በመቀበል በመድን ውል ውስጥ የተጠቀሰው ሁኔታ የተሟላ እንደሆነ ወይም አደጋ ተከስቶ ጉዳት ወይም ጥፋት ያስከተለ እንደሆነ ለመድን ገቢው በውል የተወሰነውን ጥቅም

ወይም ካሳ ለመክፈል የገባውን ግዴታ የሚያረጋግጥ ሰነድ ሲሆን የመድን ውል የምስክር ወረቀት፣ ክፍያ የተፈፀመበት ጊዜያዊ ሠነድ፣ የመድን ሽፋን ዕድሣት ደረሰኝና የመድን ውሉን የሚያረጋግጥ ሌላ ሠነድን ይጨምራል፤

21. "የመድን መርማሪ" ማለት የአደጋ ስጋት ተጋላጭነትን በማጥናት የአረቦን ምጣኔንና በጠቅላላ መድን ውል ውስጥ የተቀመጡ ግዴታዎችንና ሁኔታዎችን በተመለከተ የማማከር አገልግሎት የሚሰጥና የአደጋ ስጋት ተጋላጭነትን ለመቀነስ መወሠድ የሚገባውን ቅድመ አደጋ ጥንቃቄን በተመለከተ ሃሳብ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

22. "መድን ሰጪ" ማለት የመድን ፖሊሲ የሚሰጥ ወይም የመድን ፖሊሲ ለመስጠት እና የመድን ፖሊሲው የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ለመፈፀም ስምምነት የሚያደርግ ሰው ነው፤

23. "የሕይወት መድን" ማለት መድን ሰጪው አረቦን በመቀበል የመድን ገቢው በሕይወት የመኖር ወይም ሞት ላይ ተመስርቶ በተፈፀመ ውል ለመድን ገቢው ወይም ለሌላ ተጠቃሚ አስቀድሞ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል የሚገባው የመድን ውል ዓይነት ነው፤

24. "የረጅም ጊዜ የመድን ሥራ" ማለት፡-

ሀ) የሕይወት መድን፤

ለ) የተወሰነ ገንዘብ በተወሰነ ግዜ የመክፈል ግዴታ፤

ሐ) የጡረታ ዋስትና፤

መ) ዘላቂ የጤና መድን፤

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (መ) ከተመለከቱት የመድን ሥራዎች ጋር በማጣመር በመድን ሰጪው የሚሰጥ የአካል ጉዳት ወይም የህመም መድን ሽፋን፤ ወይም

ረ) በመመሪያ የሚወሰን ሌላ የመድን ስራ ዓይነት ነው፤

25. "ጉዳት አስተካካይ" ማለት የካሣ ጥያቄ የቀረበባቸውን ጉዳቶች በመመርመር አግባብ ባላቸው ሕጎችና በመድን ፖሊሲው መሠረት ድርድር በማድረግ የካሣ ጥያቄዎቹ እንዲስተካከሉና እልባት እንዲያገኙ የማድረግ ተግባር የሚያከናውን ሰው ነው፤

26. "ጉዳት ገማች" ማለት በጠቅላላ መድን ፖሊሲዎች ላይ የቀረቡ የካሣ ጥያቄዎችን

በመድን ሰጪው ወይም በመድን ገቢው ስም የደረሰውን ጉዳት መንስኤ የሚመረምርና የጉዳቱን ልክ የሚገምት ሰው ነው፤

27."አብይ የመድን ሥራ ዓይነት" ማለት እንደነገሩ ሁኔታ የረጅም ጊዜ የመድን ሥራ ወይም ጠቅላላ የመድን ሥራ ነው፤

28. "ዕዳን መክፈል የሚያስችል ህዳግ" ማለት በእያንዳንዱ አብይ የመድን ሥራ ዓይነት ተቀባይነት ያለው ሀብት ተቀባይነት ካለው ዕዳ ሊበልጥበት የሚገባው ህዳግ ነው፤

29."የመድን ፖሊሲ ባለይዞታ" ማለት የመድን ፖሊሲ ባለቤት ወይም የመድን ፖሊሲው የሚያስገኘውን ጥቅም የመጠየቅ ሕጋዊ መብት ያለው ሰው ነው፤

30."የብቃት መመዘኛ" ማለት በመመሪያ የሚወሰን ተፈላጊ የትምህርት፣ የሥራ ልምድና የስነ ምግባር ደረጃ ነው፤

31."ሞግዚት" ማለት ብሔራዊ ባንክ ወይም ችግር ያለበትን መድን ሰጪ በመረከብ አሠራሩን እንደገና በማዋቀር ጤናማ እንዲሆን ወይም ሕልውናው እንዲያከትም ለማድረግ በብሔራዊ ባንክ የተሾመ ሰው ነው፤

32."የጠለፋ መድን" ማለት አንድ ሰው አንድ መድን ሰጪ ለሚቀበለው የአደጋ ተጋላጭነት በውል የሚሰጠው የመድን ዋስትና ስምምነት ነው፤

33. "የጠለፋ መድን ሰጪ" ማለት የጠለፋ መድን ውል በመሸጥ የጠለፋ መድን ሽፋን የሚሰጥ ሰው ነው፤

34. "የጠለፋ መድን ደላላ" ማለት የጠለፋ መድን ለመድን ሰጪ የሚያመቻች ሰው ነው፡፡

35."ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ" ማለት በማንኛውም ስም ቢጠራም የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆነ ወይም ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ ማንኛውም የመድን ሰጪው የሥራ ኃላፊ ነው፤

36. "ቴክኒካዊ መጠባበቂያ" ማለት ከውለታ ለሚመነጩ ግዴታዎች ማስፈፀሚያ የሚያዝ መጠባበቂያ ሲሆን የሚከተሉትን ይይዛል፡-

ሀ) በአስሊ የተወሰኑ የረጅም ጊዜ መድን ሥራ መጠባበቂያ ሂሳቦች፤

ለ) ጥያቄ ለቀረበባቸውና ላልተከፈሉ የካሣ ጥያቄዎችና ለካሣ ክፍያ ማስተካከያ ወጪዎች የሚያዝ መጠባበቂያ ሂሳብ፤

ሐ) የውለታ ጊዜያቸው ላላለቀ የጠቅላላ መድን ሽፋኖች የተከፈለ አረቦን መጠባበቂያ ሂሳብ፤

መ/ አስቀድመው ለደረሱና ለመድን ሰጪው ሪፖርት ላልተደረጉ የካሣ ክፍያ ጥያቄዎች መጠባበቂያ ሂሳብ፤ እና

ሠ) ሌሎች በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት በመድን ሰጪው መያዝ ያለባቸው ሂሳቦች፡፡

37. "የኢንቨስትመንት-መድን ቁርኝት" ማለት በመድን ሰጪው ላይ የሚያስከትለው የግዴታ መጠን መድን ገቢው የሚከፍለውን አረቦን በተመረጡ የኢንቨስትመንት መስኮች በማዋል በሚገኘው ውጤት ላይ የሚመሠረት ሆኖ በውለታው የተወሰነው ጊዜ ሲያልቅ ወይም መድን የገባው ሰው በሞተ ጊዜ ቢያንስ አስቀድሞ የተወሰነውን ዝቅተኛ የዋስትና መጠን የሚያስገኝ በረጅም ጊዜ የመድን ሥራ ላይ የተሠማራ የመድን ሰጪ የሚሰጠው የመድን ፖሊሲ ነው፤

38.“በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰዋ የፋይናንስ አገልግሎት” ማለት በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰጡ የክፍያ፣ የሐዋላ እና የመድን አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፤[173]

39.“ታካፉል” ማለት ሰዎች የተወሰነ የገንዘብ መዋጮ ከማህበራቸው አባሎች በመሰብሰብ በአባሎቻቸው ላይ ለሚደርስ ጥፋት (loss) ወይም ጉዳት(damage) ቀደም ብሎ በተወሰነ የገንዘብ ልክ ለመርዳት የሚያቋቁሙት ኅብረት ነው፤

40.“የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ” ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 ላይ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፣

41.“መድን ሰጪ ኩባንያ” ማለት የመድን ሥራ እንዲሰራ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ መድን ሰጪ ነው፤

[173] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(2) መሰረት አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (37) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጾች (38፣ 39፣ 40፣ 41፣ 42፣ 43፣ 44፣ 45፣ እና 46) ተጨምረው ከንዑስ አንቀጽ 38 እስከ 40 ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከ47 እስከ 49 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

42.“አነስተኛ መድን” ማለት መሰረታዊ የመድን መርሆዎችን የሚከተል፣ በአረቦን ክፍያ ላይ የተመሰረተ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ሊጠቀሙበት የሚያስችል፣ እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከማንኛውም ስጋት ለመከላከል እንዲያስችል የተቀረጸ እና በተለያዩ አነስተኛ መድን ሰጪዎች የሚቀርብ የመድን ሽፋን ነው፤

43.“አነስተኛ መድን ወኪል” ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው እና አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አነስተኛ መድን ሰጪዎች ስም የሚሰራ እና አነስተኛ መድን ገቢዎችን እና አነስተኛ መድን ሰጪዎችን የማገናኘት ስራ የሚሰራ ሰው ነው፤

44.“አነስተኛ መድን ሰጪዎች” ማለት የአነስተኛ መድን ሥራን ለመስራት ብቻ የተቋቋሙትን ጨምሮ መድን ሰጪ ኩባንያዎች እና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ናቸው፤

45.የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ (ፕሪሚየም)” ማለት በመድን ፖሊሲ ውስጥ የተገለጸውን ሽፋን ለመስጠት መድን ሰጪ የሚያስከፍለው ገንዘብ ነው፤

46."ዕዳን መክፈል የሚያስችል ወሰን" ማለት በእያንዳንዱ አብይ የመድን ሥራ ዓይነት ተቀባይነት ያለው ሀብት ተቀባይነት ካለው ዕዳ ሊበልጥበት የሚገባው ወሰን ነው፤

47. "ብሔራዊ ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

48."ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

49.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመድን ሥራ ፈቃድ

### 3. ፈቃድ የማውጣት አስፈላጊነት

1. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ሳያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የመድን ሥራ መሥራት አይችልም፡፡

2. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ ‘‘መድን’’ ወይም ‘‘መድን ሰጪ’’ የሚለውን ወይም ከዚህ ጋር ተዛማጅ የሆነ ስያሜ የማናቸውም የፋይናንስ ንግድ ሥራ ስም አካል አድርጎ መጠቀም አይችልም፡፡
3. ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛውም መድን ሰጪ፡-
   ሀ) ብሔራዊ ባንክ ከፈቀደው ቦታ ውጪ የመድን ሥራ ማካሄድ ወይም ነባር የሥራ ቦታን መዝጋት፤
   ለ) አዲስ ዓይነት የመድን ሽፋን አገልግሎት መስጠት፤
   ሐ) ከሌላ መድን ሰጪ ጋር መቀላቀል ወይም የሌላ መድን ሰጪ ሥራ በባለቤትነት መያዝ፤
   መ) ሁሉንም ሆነ ከፍተኛ መጠን ያለውን የመድን ፖሊሲውን ማስተላለፍ፣ ከሌላ ኩባንያ ጋር በመዋሃድ ወይም በሌላ መንገድ ሥራውን ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ መስማማት ወይም በሥራ ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማድረግ፤
   ሠ) በመደበኛ የሥራ አፈፃፀም ሂደት ካልሆነ በቀር የንብረት ባለቤትነቱን በሙሉም ሆነ በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ማስተላለፍ ወይም በሌላ መንገድ ማዛወር፤
   ረ) የራሱን አክስዮን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ የሥራ ሂደት በተከሠተ ኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በቀር ካፒታሉን መቀነስ፤
   ሰ) የመመስረቻ ጽሑፉን ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል፤ ወይም
   ሸ) የመድን ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ ያገኘበትን ስም መቀየር፤

   አይችልም፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን በመተላለፍ ማንኛውም ሰው የመድን ሥራ ለማካሄድ ማስታወቂያ ያወጣ ወይም የመድን ሥራ እያካሄደ መሆኑን ብሔራዊ ባንክ ለማመን ምክንያት ሲኖረው ይኸንኑ ሁኔታ ለማጣራት በዚሁ ሰው ይዞታ ሥር የሚገኙትን የንግድ መዝገቦች፣ ቃለጉባኤዎች፣ ሂሳቦች፣ የዋስትና ሠነዶች፣ ማስታወሻዎች፣ የገንዘብ ማዘዣዎችና ሌሎች ሠነዶች እንዲቀርቡለት ማድረግና መመርመር ወይም ማስመርመር ይችላል፡፡
5. ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳያገኝ የመድን ሥራ በማካሄድ በዚህ ድርጊት አማካኝነት አረቦን የተቀበለ ወይም የመድን ሽፋን በመስጠት በውል ግዴታ ውስጥ ገብቶ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ ይኸው አረቦን በአፋጣኝና በተቀላጠፈ

መንገድ እንዲመለስ ወይም ግዴታው እንዲፈፀም አስፈላጊው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

4. <u>የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

1. የመድን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት፡-

ሀ) በሚገባ የተሞላ የፈቃድ መጠየቂያ ቅጽና በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት መቅረብ የሚገባቸው ሌሎች አባሪ ሠነዶች መቅረብ አለባቸው፤

ለ) ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የሠነድ መመርመሪያ ክፍያ መከፈል አለበት፤

ሐ) ማመልከቻው ለብሔራዊ ባንክ እንደቀረበ ባንኩ በሚወስነው ቅጽ መሠረት መሥራቾቹ በመድን ሥራ ለመሠማራት መፈለጋቸውን ለአራት ተከታታይ ሣምንታት ቢያንስ በሣምንት አንድ ጊዜ በስፋት በሚሠራጩ ጋዜጦች ላይ አሳትመው ማውጣት አለባቸው፤

መ) መድን ሰጪውን በኩባንያ መልክ ማቋቋምና የኩባንያውን የመመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ከመመዝገባቸው በፊት በብሔራዊ ባንክ ዘንድ አቅርቦ ማስፀደቅ ያስፈልጋል፤

ሠ) በኩባንያው የወጡት አክስዮኖች በሙሉ የተፈረሙ ሆነው ከዚሁ ውስጥ ቢያንስ ሩብ ያህሉ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መሆን አለበት፤

ረ) በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ መከፈልና በምሥረታ ላይ ባለው መድን ሰጪ ስም በዝግ የባንክ ሂሳብ መቀመጥ አለበት፤

ሰ) የመድን ሰጪው ዳይሬክተሮች፣ ዋናው ሥራ አስፈፃሚና ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች በመመሪያ የተወሰነውን የብቃት መመዘኛ ማሟላት አለባቸው፤

ሸ) ተደማጭነት ያላቸው ባለአክስዮኖች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን የሥነ-ምግባር መመዘኛ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፤

ቀ) መድን ሰጪው የጠለፋ መድንን ጨምሮ የአደጋ ስጋት ተጋላጭነት መጠን የሚቆጣጠርበት ሥርዓት፣ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲሁም የመድን ሰጪውን ሥራ ስፋትና ጥልቀት መሠረት ያደረገ ፖሊሲ እና የሥራ መመሪያ የሚያመለክት የተሟላ ቅድመ ጥናት መቅረብ አለበት፤

በ) በቂና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የመድን ሰጪውን የወደፊት ሥራ አካሄድና አደረጃጀት የሚያመለክት ዕቅድ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት፤

ተ) የመድን ሰጪው ስም ፈቃድ ከተሰጣቸውና በሥራ ላይ ካሉ ሌሎች መድን ሰጪዎች ስም ጋር ተመሣሣይ ያልሆነ ወይም ሊያደናግር በሚችል ሁኔታ ከፍተኛ ተመሣሣይነት የሌለው መሆን አለበት፤

ቸ) መድን ሰጪው ሥራውን የሚያካሂድበት ሕንፃና የቢሮ ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን መስፈርቶች ያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

2. ሊቋቋም በታሰበው መድን ሰጪ ውስጥ የማንኛውንም መሥራች ባለአክስዮን መሆን የሚቃወም ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) በተመለከተው መሠረት የመጨረሻው ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሠላሣ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከማስረጃ ጋር በጽሑፍ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይችላል፡፡

3. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበውን ተቃውሞ ለመመርመር የሚያስችል ተገቢ እርምጃ ይወስዳል፡፡ በምርመራው የተገኘውን ውጤትም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ በማድረግ ፈቃዱን ለመስጠት ወይም ለመከልከል በሚሰጠው ውሣኔ ታሣቢ ይደረጋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ የመድን ሥራ ፈቃድ ለመስጠት መሟላት የሚገባቸው ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ብሔራዊ ባንክ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን ከመረመረና ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ተሟልተዋል ብሎ ሲያምን ፈቃዱን ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ወይም ገደብ፣ ወይም በቅድመ ሁኔታ ወይም በገደብ ሊሰጥ ይችላል::

2. በመድን ሥራ ፈቃድ ላይ የሚጣሉ ቅድመ ሁኔታዎች ወይም ገደቦች ከሌሎች መካከል የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

ሀ) በሚሰጠው የመድን ሥራ ዓይነት ላይ የሚጣል ገደብ፤

ለ) ፈቃዱ ፀንቶ ሊቆይ የሚችልበት ጊዜ ገደብ፤

ሐ) መድን ሰጪው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወይም በማንኛውም የመድን ሥራ አይነት ላይ ሊሰበስብ በሚችለው የአረቦን ገቢ መጠን ላይ የሚጣል ገደብ፤ እና

መ) መድን ሰጪው ሌሎች ድርጅቶችን በባለቤትነት መያዝን ወይም ልዩ ኩባንያን ማቋቋምን መከልከል ጨምሮ በኢንቨስትመንት ላይ የሚጣል ገደብ፤ እና

ሠ) የአደጋ ሥጋቶችን ለጠለፋ መድን ሰጪዎች ማስተላለፍ ስለሚገባበት ሁኔታ፡፡

3. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ የመድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት በቀረበው ማመልከቻ ላይ ውሣኔ ይሠጣል፡፡
4. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ባለፈቃዱ ሊሠማራ የሚችልበትን የመድን ሥራ ዓይነቶች መግለፅ አለበት::
5. ፈቃዱ የሚሰጠው በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ ሲከፈል ነው፡፡
6. በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ የመድን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል የመጨረሻው ፈቃድ ይሆናል፡፡
7. ብሔራዊ ባንክ በማንኛውም ጊዜ ለመድን ሰጪ በተሰጠ ፍቃድ ላይ ግዴታዎችን በመጨመር ወይም ገደብ በመጣል ፈቃዱን ማሻሻል ይችላል፡፡
8. ብሔራዊ ባንክ ለጠለፋ መድን ሰጪ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለፈቃድ አሰጣጡም ሁኔታ በመመሪያ ሲወሰን ይችላል፡፡
9. የጠለፋ መድን ደላላ ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
10. ብሔራዊ ባንክ ለአነስተኛ መድን ሰጪና ለአነስተኛ መድን ወኪል ስለሚሰጥበትና ቁጥጥር ስለሚካሄድበት ሁኔታ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡[174]

6. <u>የንግድ ዓላማዎች</u>

1. በፈቃዱ ላይ የተጣለው ቅድመ ሁኔታ ወይም ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ መድን ሰጪው በፈቃዱ ላይ በተዘረዘሩት የመድን ሥራ ዓይነቶች መሠማራት ይችላል፡ በተጨማሪም በብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በሚሰጥ ፈቃድ መድን ሰጪው ሌሎች ከመድን ሥራ ጋር ቁርኝት ያላቸው ተቀጥላ ሥራዎችን ማካሄድ ይችላል፡
2. የረጅም ጊዜ መድን ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ለተሰጠው መድን ሰጪ ተቀጥላ

[174] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(3) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

ሥራዎች የሚከተሉትንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በኢንቨስትመንት የማማከርና ሀብት የማስተዳደር አገልግሎቶችን መስጠት፤

ለ) በሪል እስቴት የድለላ አገልግሎት መስጠት፤

ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙና መድን ሰጪው ከፍተኛ የባለቤትነት ድርሻ ለያዘባቸው ድርጅቶች መረጃ የማጠናቀር አገልግሎት የመስጠት፤

መ) መድን ሰጪው ከሚያራምደው የመድን ሥራ አይነት ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎችና ለመድን ደላሎች ዕገዛ ማድረግ፤

ሠ) ንብረት በአደራ የማስቀመጥ ተግባር ማከናወን፤ እና

ረ) የኢንቨስትመንት-መድን ቁርኝት አገልግሎት መስጠት፡፡

3. የጠቅላላ መድን ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ለተሰጠው መድን ሰጪ ተቀጥላ ሥራዎች የሚከተሉትንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡-

ሀ) መድን ሰጪው ከሚያካሂዳቸው የመድን ሥራዎች ጋር በተያያዘ የአደጋ ሥጋት አስተዳደርና ጉዳት የማስተካከል ምክር አገልግሎቶች መስጠት፤

ለ) መድን ሰጪው ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎችና ለመድን ደላላዎች መረጃዎችን የማጠናቀር አገልግሎት የመስጠት፤

ሐ) መድን ሰጪው ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ዓይነት ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎችና ለመድን ደላሎች እገዛ የማድረግ፤ እና

መ) መድን ሰጪው ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ጋር በተያያዘ የባለሞተር ተሽከርካሪ ጥገናና ጉዳት ግምት አገልግሎት የሚሰጥበት ጋራጅ ማቋቋምና ማካሄድ፡፡

4. የረጅም ጊዜ የመድን ሥራ ለመሥራት በዚህ አዋጅ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም መድን ሰጪ በቅድሚያ ከብሔራዊ ባንክ በተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ የኢንቨስትመንት-መድን ቁርኝት ሥራ ተግባራትን ሊያካሂድ ይችላል፡፡

5. ኢንቨስትመንት-መድን ቁርኝት ሽፋን አሠጣጥ እና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሀብቶች ከሌሎች ሀብቶች ተለይተው ስለሚቀመጡበት አኳኋን በመመሪያ ይወሰናል፡፡

7. **የመድን ሥራ ስለመጀመር**

ፈቃድ የተሰጠው መድን ሰጪ፡-

1. ሥራ ከመጀመሩ በፊት በመመሪያ በተወሰነው መሠረት ተገቢው የመረጃ ፍሰት ስርዓት፣ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት፣ የአደጋ ሥጋት አስተዳዳር ፖሊሲና ደንቦች፣ እንዲሁም የሰው ኃይል አደረጃጀትና የመሳሰሉትን ጨምሮ የመድን ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ግዴታዎችን ማሟላት፤ እና
2. ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 12 ወራት ውስጥ ሥራ መጀመር፤ አለበት፡፡

8. **የፈቃድ ዕድሳት**

የመድን ሥራ ፈቃድ የሚታደስበት ሁኔታ በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

9. **ፈቃድ የተሰጣቸውን መድን ሰጪዎች ስለማስታወቅ**

ብሔራዊ ባንክ በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸውን መድን ሰጪዎች ዝርዝር አትሞ ያወጣል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ዝርዝር ላይ የተጨመሩትን ወይም ከዝርዝሩ የተሠረዙትን መድን ሰጪዎች ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች ላይ ወዲያውኑ አሳትሞ ያወጣል፡፡

10. **ክልከላ**[175]

የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በመድን ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ የተጣለው ክልከላ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፡-

1. የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም ሙሉ በሙሉ የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለቤትነት ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያን የጋራ ባለቤትነት የተቋቋመ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ መድን ሰጪ ኩባንያ የአክሰዮን ባለቤት ወይም መድን ሰጪ ኩባንያ ማቋቋም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው አግባብ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በቀጥታ በመድን ሰጪ ኩባንያ የአክስዮን ባለቤት ሲሆን ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የአክስዮን ባለቤት የሆነበት ሌላ ድርጅት የመድን ሰጪ ኩባንያ ባለአክስዮን ሲሆን የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ

[175] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(4) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ኢትዮጵያዊ በድርጅቱ የሚኖረው የአክስዮን ድርሻ ዋጋ በሙሉ ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሪ ብቻ የሚከፈል ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ( 2) የተደነገገው ግዴታ ቢኖርም:-

ሀ) ከአክስዮን ባለቤትነት የሚገኝ የትርፍ ድርሻ፤

ለ) የአክስዮን ድርሻውን ለሌላ ሰው ሲያዛውር፤

ሐ) ባለአክስዮን የሆነበት መድን ሰጪ ኩባንያ ሲሸጥ ወይም ፈርሶ ሲጣራ፤ ወይም

መ) ሌሎች ከአክስዮን ባለቤትነት ጋር በተያያዘ፤

የውጭ ሀገር ዜግነት ላለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሚከፈሉ ማናቸውም ዓይነት ክፍያዎች በሙሉ በብር የሚከፈለው ይሆናል፤ እንዲሁም በዚህ አግባብ የሚያገኘውን ሀብት ወይም ጥቅም ወደ ውጭ ማዛወር አይፈቀድለትም፡፡

4. የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በመድን ሰጪ ኩባንያ ውስጥ መዋዕለ ንዋያቸውን በሥራ ላይ ስለሚያውሉበት ተጨማሪ ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለአክስዮኖችና የባለ አክስዮኖች ጉባኤ

### 11. ስለአክስዮኖችና የአክስዮን መዝገብ

1. የመድን ሰጪ አክስዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው አንድ ዓይነት የሆኑና የተመዘገቡ ተራ አክስዮኖች ይሆናሉ፡፡
2. ማንኛውም መድን ሰጪ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የባለአክስዮኖችን ስም ዝርዝርና ድምፅ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የአክስዮን መዝገብ ይይዛል፡፡ በዚህ መዝገብ ውስጥ የሠፈረ ማንኛውም የአክስዮን ዝውውር አክስዮኖችን ባስተላለፈውና በተላለፈለት ሰው መካከል አክስዮኖችን የማስተላለፍ ሕጋዊ ስምምነት ስለመኖሩ እንዲሁም የአክስዮኖቹ ስመ-ባለቤትነት ስለመዘዋወሩ የመጨረሻ ማረጋገጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
3. በአክስዮን መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ ማንኛውም የአክስዮን ዝውውር ዋጋ አይኖረውም፡፡

4. ማንኛውንም ሰው ተደማጭነት ያለው ባለአክስዮን ሊያደርግ የሚችል የአክስዮን ዝውውር በአክስዮን መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የአክስዮን መዝገብ በመድን ሰጪው መደበኛ የሥራ ሰዓት ሕዝብ ያለ ክፍያ ማየት በሚችልበት ሁኔታ በመድን ሰጪው ዋና መሥሪያ ቤት ይቀመጣል፡፡

12.<u>አክስዮኖችን የመያዝ ገደብ</u>

1. ከኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት በስተቀር ማንኛውም ሰው ብቻውንም ሆነ ከባለቤቱ ወይም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ በአንደኛ ደረጃ ከሚዛመዳቸው ሰዎች ጋር በመሆን ከማናቸውም መድን ሰጪ የተፈረመ ካፒታል ከአምስት በመቶ በላይ አክስዮን ሊይዝ አይችልም፡፡
2. በማንኛውም መድን ሰጪ ውስጥ አክስዮን ያላቸው ሰዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የያዙት ድርጅት በመድን ሰጪው ውስጥ ሊኖረው የሚችለው የአክስዮን መጠን በመመሪያ ይወሰናል፡፡
3. በአንድ መድን ሰጪ ውስጥ ተደማጭነት ያለው ባለአክስዮን በሌሎች መድን ሰጪዎች አክስዮን መያዝ አይችልም፡፡
4. ማንኛውም ሰው ከባንክ በተገኘ ብድር የመድን ሰጪ አክስዮን ሊገዛ አይችልም፡፡
5. [176]

13.<u>የባለ አክስዮኖች ጉባኤ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ፡-
   ሀ) በማንኛውም የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በታዛቢነት የሚሳተፍ ሰው ሊመድብ፤ እና
   ለ) የመድን ገቢዎችን ወይም የባለአክስዮኖችን ጥቅም ለማስከበር ወይም ለመድን ክፍለ ኢኮኖሚው መረጋጋትና ጤናማነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት መድን ሰጪውን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ አወያይቶ ውሣኔ ማሰጠት፤

   ይችላል፡

[176] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(5) መሰረት ተሰረዘ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) በተመለከተው መሠረት ብሔራዊ ባንክ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የጠራ እንደሆነ፡-
   ሀ) የስብሰባውን አጀንዳ ያዘጋጃል፤
   ለ) ስብሰባውን እንዲመራ የባንኩን ሠራተኛ ወይም ሌላ ባለሙያ ሊሰይም ይችላል፤
   ሐ) የባለአክስዮኖችን ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤና በጉባኤው የሚተላለፉ ውሣኔዎችን በሚመለከት በንግድ ሕጉ ስለ አክስዮን ማህበራት የተደነገጉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፤
   መ) ከጉባኤው ጋር የተያያዙ ወጪዎች ጉዳዩ በሚመለከተው መድን ሰጪ ይሸፈናሉ፡፡

14.ድምፅ የመስጠት ገደብ

1. ብሔራዊ ባንክ በማንኛውም የባለአክስዮኖች ስብሰባ ማንኛውም ሰው የባለአክስዮን እንደራሴ ሆኖ መስጠት የሚችለውን ድምፅ ሊገድብ ይችላል::
2. ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ተደማጭነት ያለው ባለአክስዮን በመመሪያ የተወሰነውን የሥነ-ምግባር መስፈርት ማሟላት ያልቻለ እንደሆነ ድምፅ የመስጠት መብቱን ሊገድብበት ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለመድን ሰጪ ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች

15.ስለዳይሬክተሮችና ሥራ አስፈፃሚዎች ሹመት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ በብሔራዊ ባንክ እምነት ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ ጠንቃቃና መልካም ዝና ያለው መሆን አለበት፡፡
2. መድን ሥራ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜም ሆነ በሌላ በማንኛውም ጊዜ የሚደረግ የማንኛውም መድን ሰጪ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሹመት በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ካልጸደቀ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3. ብሔራዊ ባንክ አዲስ የተመረጡ የመድን ሰጪ ዳይሬክተሮችን ሹመት በጽሑፍ እስካላፀደቀ ድረስ የነባር ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ ይቀጥላል።
4. ብሔራዊ ባንክ፦
   ሀ) የመድን ሰጪ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎች ማሟላት ስለሚገባቸው የብቃት መመዘኛዎችን፤
   ለ) የአንድ መድን ሰጪ የቦርድ አባላት ሆነው የሚሠሩ ዳይሬክተሮች ዝቅተኛ ቁጥርን፤
   ሐ) የመድን ሰጪ ዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነትና ግዴታዎችን እና የመድን ሰጪ ኩባንያን መልካም የኩባንያ ሥራ አመራርን፤[177]
   መ) አንድ ዳይሬክተር በማናቸውም መድን ሰጪ ሊያገለግል የሚችልበትን ከፍተኛ ሥራ ዘመንና እንደገና ለመመረጥ የሚያበቁትን ሁኔታዎች፤
   ሠ) ለዳይሬክተሮች የሚደረገውን የክፍያ ጣሪያ፤ እና
   ረ) በማናቸውም መድን ሰጪ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ተመርጠው ሊያገለግሉ የሚችሉ የዚያው መድን ሰጪ ሠራተኞችን ቁጥር፤
   በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

16.<u>ክልከላ</u>

1. ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ሰው የመድን ሰጪ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ መሆን አይችልም።
2. ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሚገኝ በማናቸውም በፈረሰ መድን ሰጪ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የነበረ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመድን ሰጪው ሥራ አመራር የተሳተፈ ሰው በመድን ሰጪ ዳይሬክተርነት፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚነት ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመድን ሰጪ ሥራ አመራር መሳተፍ አይችልም።

---
[177] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(6) መሰረት ተሻሻለ፡፡

3. ማናቸውም መድን ሰጪ ዳይሬክተር በተመሳሳይ ጊዜ የሌላ ፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡ በተጨማሪም ዳይሬክተሩ አሥር በመቶና ከዚያ በላይ የባለቤትነት ድርሻ የያዘበት የንግድ ድርጅት የመድን ሰጪ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡[178]
4. ማንኛውም መድን ሰጪ ሠራተኛ የዚያው መድን ሰጪ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ወይም የማንኛውም ሌላ መድን ሰጪ ዳይሬክተር ሆኖ ሊመረጥ አይችልም።
5. የውጭ ሀገር ዜጎች ወይም በከፊልም ሆነ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች ወይም የውጭ መድን ሰጪ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የመድን ሥራ ማካሄድ ወይም የመድን ሥራ የሚያካሂዱ ቅርንጫፎች ማቋቋም እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ መድን ሰጪዎች የአክስዮን ባለቤት መሆን አይችሉም፡፡[179]

17.<u>ከመድን ሰጪ ስራ አመራር ራስን ስለማግለል</u>

የማንኛውም መድን ሰጪ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመድን ሰጪ ሥራ አመራር የሚሳተፍ ሰው፣

1. ራሱ ወይም ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚሠራበት ኩባንያ ከስሬአለሁ ብሎ ያመለከተ ወይም በፍርድ ቤት የኪሣራ ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ወይም በኪሣራ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ንብረቱ፣ በንብረት ጠባቂ ቁጥጥር ሥር የዋለበት ወይም ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት የራሱ ወይም የኩባንያው ንብረት በባንክ የተወረሰበት እንደሆነ፤
2. ማንኛውንም ብድር ወይም ታክስ ባለመክፈሉ ተከሶ የተፈረደበት እንደሆነ፤ ወይም
3. ብሔራዊ ባንክ የወሰናቸውን የብቃት መመዘኛዎች ያላሟላ እንደሆነ፤

   ራሱን ከመድን ሰጪ ሥራ አመራር ማግለል አለበት፡፡

[178] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(7) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[179] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(7) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

18.<u>በብሔራዊ ባንክ ስለሚወሰድ የማገድና የማሰናበት ርምጃ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ የማንኛውንም መድን ሰጪ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ በበቂ ምክንያት ከሥራ ለማገድ ወይም ለማሰናበት ይችላል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ በቂ ምክንያት የሚከተሉትን ያካትታል፣

   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ወይም አንቀጽ 17 የተደነገጉትን አለማክበር፣

   ለ) በብሔራዊ ባንክ እምነት በመድን ሰጪ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የፈጸመው የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚውን መረጋጋት ወይም ጤናማነት፣ ኢኮኖሚውን ወይም የሕዝብን ጥቅም ወይም መድን ሰጪውን የሚጎዳ ማናቸውም ድርጊት፡፡
3. ብሔራዊ ባንክ የአንድን መድን ሰጪ ዳይሬክተሮች ከሥራ በሚያሰናብትበት ጊዜ የዳይሬክተሮቹ ቁጥር በሕግ ከሚፈቀደው በታች ከሆነ ወዲያውኑ የቦርዱን ኃላፊነት ተረክቦ በ30 ቀናት ውስጥ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ በመጥራት በተሰናበቱት ዳይሬክተሮች ምትክ ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ የአንድን መድን ሰጪ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ያሰናበተ እንደሆነ መድን ሰጪው የዳይሬክተሮች ቦርድ በመመሪያ የተወሰኑትን የብቃት መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው ወዲያውኑ መተካት አለበት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች</u>

19. <u>ተፈላጊውን ካፒታል ስለመያዝ</u>

1. መድን ሰጪዎች መያዝ የሚገባቸው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን በመመሪያ ይወሰናል፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ የመድን ሰጪዎች አጠቃላይ የአደጋ ሥጋት ተጋላጭነት መጠንን ግምት ውስጥ ያስገባ የተለያየ የካፒታልና መጠባበቂያ ህዳግ የመያዝ ግዴታዎች ለተለያዩ መድን ሰጪዎች ሊያስቀምጥ ይችላል::

3. ብሔራዊ ባንክ የማናቸውም መድን ሰጪ ካፒታልና መጠባበቂያ ህዳግ ከተወሰነው ዝቅተኛ መጠን በታች ነው ብሎ ሲያምን መድን ሰጪው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያስችል እርምጃዎች እንዲወስድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

20.**ሕጋዊ ተቀማጭ ገንዘብ**

1. ማንኛውም መድን ሰጪ ለሚያካሂደው ለእያንዳንዱ አብይ የመድን ሥራ ዓይነት መጠኑ በመመሪያ የሚወሰን ህጋዊ ተቀማጭ ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ ወይም በመንግሥት የግዴታ ሰነድ በብሔራዊ ባንክ ማስቀመጥ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተወሰነው ተቀማጭ ገንዘብ በመድን ሰጪው ስም የሚያዝ ሆኖ የመድን ሰጪው ሃብት እንደሆነ ይቆጠራል፤ ሆኖም ተቀማጩ ገንዘብ በሙሉም ሆነ በከፊል ብሔራዊ ባንክ በፅሑፍ ካልፈቀደ በቀር ወጪ ሊደረግ ወይም ለማንኛውም ብድር መያዣ ወይም ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቀማጭ ከሆነው ገንዘብ ውስጥ ማንኛውም ክፍል የመድን ሰጪውን ግዴታ ለመፈፀም የዋለ እንደሆነ ጉድለቱን ለማሟላት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ገንዘብ መድን ሰጪው ተቀማጭ ገንዘቡ ወይም ከተቀማጭ ገንዘቡ ውስጥ ማንኛውም ክፍል ግዴታውን ለመፈፀም ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ ወይም በመንግሥት የግዴታ ሰነድ ማስቀመጥ አለበት፡፡
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱትን ግዴታዎች ለመፈፀም ካልሆነ በቀር ተቀማጩ ገንዘብ ወይም ከተቀማጩ ገንዘብ ማናቸውንም ክፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው አኳኋን እንዲውል አይፈቀድም፡፡

21. **ሕጋዊ ተቀማጭ ገንዘብ አጠቃቀም ላይ የተጣሉ ገደቦች**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 በተመለከተው መሠረት ተቀማጭ የሆነ ገንዘብ በመድን ውሎች መድን ሰጪው ከገባቸው የገንዘብ ግዴታዎች ውስጥ ሳይፈጸሙ የቀሩትን ለመፈፀም ካልሆነ በቀር የመድን ሰጪውን ማንኛውንም ሌላ ግዴታ ለማስፈፀሚያ ሊመደብ ወይም ወጪ ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲሁም መድን ገቢው በመድኑ ውል መሠረት ከመድን ሰጪው ሊከፈለው ስለሚገባ ዕዳ የተሰጠን ውሣኔ

ለማስፈፀም ካልሆነ በቀር ማንኛውንም ሌላ የፍርድ ቤት ውሣኔ ለማስፈፀም ሊውል አይችልም፡፡

2. ለእያንዳንዱ አብይ የመድን ሥራ ዓይነት ተቀማጭ የሆነ ገንዘብ በዚያው አብይ የመድን ሥራ በተፈፀሙ የመድን ውሎች ምክንያት ለሚመጣ ግዴታ ካልሆነ በቀር ሌላ ማንኛውንም ግዴታ ለመፈፀም ሊውል አይችልም፡፡

22. ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ስለመያዝ

1. ማንኛውም መድን ሰጪ በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ካገኘው የተጣራ ትርፍ ከአሥር በመቶ የማያንሰውን ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም መጠባበቂያ ሂሳቡ ከመድን ሰጪው የተከፈለ ካፒታል ጋር እኩል ሲሆን በየዓመቱ ወደ መጠባበቂያው ሂሳብ ገቢ የሚደረገው የተጣራ ትርፍ መጠን በመመሪያ ይወሰናል፡፡
3. ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ሊቀንስ የሚችልበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡

23. ዕዳ መክፈል የሚቻልበት ህዳግ

1. ማንኛውም መድን ሰጪ በማንኛውም ጊዜና በመመሪያ በሚወሰነው መሰረት፡-
   ሀ) በቂ ካፒታል፣ መጠባበቂያ እና ግዴታውን ለመክፈል የሚያስችለው ህዳግ፣
   ለ) በቂ ጥሬ ገንዘብና ከጥሬ ገንዘብ ጋር የተቀራረበ ሌላ ሀብት፣
   
   መያዝ ይኖርበታል፡፡
2. በመመሪያ በተወሰነው መሠረት ዕዳ መክፈል የሚቻልበት ህዳግ የሚጠይቀውን ሀብት መያዝ ያልቻለ ማናቸውም መድን ሰጪ ችግሩ መወገዱ በብሔራዊ ባንክ እስከሚረጋገጥ ድረስ የትርፍ ክፍፍል ማሳወቅ፣ በባለአክስዮኖች ሂሳብ ውስጥ ማስገባት ወይም መክፈል አይችልም፡፡
3. ዕዳ መክፈል የሚቻልበት ህዳግ የሚሠላበት ቀመርና ለዚሁ ዓላማ የመድን ሰጪው ተቀባይነት ያላቸው ሃብቶችና ዕዳዎች የሚገመቱበት አኳኋን በመመሪያ ይወሰናል፡፡

24. ቴክኒካዊ መጠባበቂያዎች፣ የእርጅና ቅናሽና የካፒታል ወጪዎችን ስለማጣጣት

1. ማንኛውም መድን ሰጪ ቴክኒካዊ መጠባበቂያዎች መያዝ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መያዝ የሚገባቸው መጠባበቂያዎች መጠንና የሚሠሉበት አኳኋን በመመሪያ ይወሠናል፡፡

3. መድን ሰጪው የረጅም ጊዜ መድን ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ የተሰጠው ከሆነ በዓመታዊ የሂሳብ መግለጫው የሚታየው ዕዳ በአስሊ የተገመተውን የረጅም ጊዜ መድን ግዴታን ለመሸፈኛ የተቀመጠን ቴክኒካዊ መጠባበቂያዎች እንዲሁም ለመድን ፖሊሲ ግዴታዎችና ለሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የተያዘውን መጠባበቂያ ያካተተ መሆን አለበት፡፡
4. የረጅም ጊዜ መድን ቴክኒካዊ መጠባበቂያዎች የረጅም ጊዜ መድን ፖሊሲ ግዴታዎችን ለመፈፀም ከሚያስፈልገው ገንዘብ መጠን ማነስ የለበትም፡፡
5. ማንኛውም መድን ሰጪ፡-
   ሀ) አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚይዘውን የእርጅና ቅናሽ ማስላትና የካፒታል ወጪዎችን ማጣጣት አለበት፤
   ለ) በሥራ ሂደት የደረሱና የተጠራቀሙ ኪሣራዎችን በየዓመቱ የሚያገኘውን የተጣራ ትርፍ በመጠቀም ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነት ኪሣራዎች ሙሉ በሙሉ እስከሚሸፈኑ ድረስ ለባለአክስዮኖች የትርፍ ክፍፍል ማድረግ የለበትም፡፡
6. ብሔራዊ ባንክ ማናቸውም መድን ሰጪ የካፒታልና ዕዳ መክፈል የሚቻልበት ህዳግ ግዴታዎቹን ማክበሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነውን ስሌት በሚሠራበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (3) እና (5)(ሀ) መሠረት የተያዙትን መጠባበቂያዎች፣ የቋሚ ንብረቶች የእርጅና ቅናሽ ሂሳብና የተደረገውን የካፒታል ወጪ ማጣጣት ተገቢነት ታሳቢ በማድረግ አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል፡፡
7. ማንኛውም መድን ሰጪ በብሔራዊ ባንክ ዕምነት በቂ የሆነና በተለይ፡-
   ሀ) የመድን ሰጪው ማንኛውም ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ በቸልተኝነት ወይም ዕምነት በማጉደል የሚያደርሰውን ኪሣራ፤ እና
   ለ) ባልተጠበቁ ወይም አስከፊ በሆኑ አደጋዎች ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን፤ ለመሸፈን ልዩ የመጠባበቂያ ሂሳብ ይይዛል ወይም የመድን ወይም የጠለፋ መድን ፖሊሲ ይገዛል፡፡

25.<u>አጠቃላይ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ የመድን ሰጪዎችን ኢንቨስትመንት በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

2. ማንኛውም መድን ሰጪ፡-

ሀ) በኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ሰው ተገቢ ያልሆነ ኪሣራን ለማስወገድና ኢንቨስትመንቱ ተመጣጣኝ ገቢ ሊያስገኝ መቻሉን በማረጋገጥ ረገድ የሚያደርጋቸውን ጥንቃቄዎች ሁሉ ያካተተ፤

ለ) የግዴታዎቹን ይዘት የሚያንፀባርቅ፤ እና

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን የተከተለ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መቅረፅና መተግበር አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## የሂሳብ ሪፖርት፣ የውጪ ኦዲትና በአስሊ ስለሚደረግ ምርመራ

### 26.የሂሳብ ሪፖርት

1. [180]

2. ማናቸውም መድን ሰጪ፡-

ሀ) ሁኔታውን በግልጽና በትክክል በሚያሳይ፤

ለ) ሥራውን፣ የገንዘብ አቋሙንና ሁኔታውን በሚስረዳ፤ እና

ሐ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሥራውን እያካሄደ ስለመሆኑ ብሔራዊ ባንክ ማረጋገጥ በሚያስችለው፤

አግባብ መዝገቦቹን መያዝ አለበት፡፡

3. ማንኛውም መድን ሰጪ እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴ ዓይነት የሚመዘግብበት የተለየ መዝገብና ሠነዶች መያዝ አለበት፡፡ የእነዚህን ሠነዶች ዓይነት፣ በውስጣቸው ስለሚመዘገቡ ዝርዝር ጉዳዮች እና ፎርማቸው በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

### 27.ሂሳቦችን ስለመለየት

1. መድን ሰጪው የረጅም ጊዜና ጠቅላላ መድን ሥራዎች የሚያካሂድ ከሆነ፡-

ሀ) የእያንዳንዱን አብይ የመድን ሥራ ወጪና ገቢ የሚያሳይ የተለያየ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት፤

ለ) ለእያንዳንዱ አብይ የመድን ሥራ በየራሱ ስም ሂሳብ ከፍቶ የተለያየ ቴክኒካዊ መጠባበቂያዎች ማስቀመጥ አለበት፤

---

[180] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(8) መሰረት ተሰረዘ፡፡

ሐ) ለረጅም ጊዜ የመድን ሥራ የተቀመጠ ቴክኒካዊ መጠባበቂያ፡-

1) መድን ሰጪው ከዚህ የመድን ሥራ ዓይነት ውጪ ሌላ የመድን ሥራ እንደማያከናውን ተቆጥሮ ይህን ዓይነቱን መድን ለገቡ ሰዎች ብቻ ዋስትና ይሆናል፤

2) መድን ሰጪው በሌላ ውል መሠረት የሚመጣበት ግዴታን ለማስፈፀም ሊያውለው አይችልም፤

3) መድን ገቢው በረጅም ጊዜ መድን ውል መሠረት ከመድን ሰጪው ሊከፈለው ስለሚገባ ዕዳ የተሰጠን ውሣኔ ለማስፈፀም ካልሆነ በስተቀር ማናቸውንም ሌላ የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለማስፈፀም ሊውል አይችልም፡፡

መ) የረጅም ጊዜ መድን ሥራ ሃብቶችና ቴክኒካዊ የመጠባበቂያ ሂሳቦች ከመድን ሰጪው ሌሎች ሃብቶች ተለይተው ለብቻ መያዝ አለባቸው፡፡

2. በረጅም ጊዜ መድን ወይም በጠቅላላ መድን ሥር የሚመደቡ የተለዩ የመድን ሥራ ዓይነቶችን የሚመለከቱ ሂሳቦችና ቴክኒካዊ መጠባበቂያዎች ተለይተው የሚያዙበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡፡

3. ብሔራዊ ባንክ የረጅም ጊዜ መድንና የጠቅላላ መድን ሥራዎች የየራሳቸው የሕግ ሰውነት ባላቸው የተለያዩ ኩባንያዎች እንዲካሄዱ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

28.<u>**ኦዲተሮች ስለመሾም**</u>

1. ማንኛውም መድን ሰጪ የውጭ ኦዲተሮችን መሾም አለበት፤ ሆኖም ሹመቱ በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፡፡

2. የሚከተሉት ሰዎች የማንኛውም መድን ሰጪ የውጪ ኦዲተር ሆነው መሾም አይችሉም፡-

ሀ) መድን ሰጪው ባለአክስዮን፣ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የሚሸፈን ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም በአንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ወይም (ለ) የሚሸፈን ሰው የሥራ ባልደረባ ወይም ሸሪክ የሆነበት የኦዲት ተቋም፡፡

3. የመድን ሰጪዎችን የኦዲት ሥራ ለማካሄድ የሚሾሙ የውጭ ኦዲተሮች ደረጃ በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡
4. ማንኛውም መድን ሰጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የውጭ ኦዲተር ያልሾመ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ኦዲተር ይሾምለታል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ኦዲተር የተሾመለት ማንኛውም መድን ሰጪ ለተሾመው ኦዲተር የሚከፈለውን የኦዲት አገልግሎት ክፍያ ብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ይፈፅማል፡፡

29.<u>የኦዲተሮች የሹመት ዘመን</u>

1. መድን ሰጪዎችን የኦዲት ሥራ ለማካሄድ ስለሚሾሙ የውጭ ኦዲተሮች የሹመት ዘመን ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያውጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሾመ የውጭ ኦዲተር የአገልግሎት ዘመን እስከሚቀጥለው የመድን ሰጪው ዓመታዊ ባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ድረስ ይሆናል፡፡
3. የማንኛውም መድን ሰጪ የውጭ ኦዲተር የተሾመበት የአገልግሎት ጊዜ ሳያበቃ በማንኛውም ምክንያት ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ መድን ሰጪው ይህንኑ በፍጥነት ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፡፡

30.<u>የኦዲተሮች ተግባር</u>

1.[181]

2.በውጭ ኦዲተሮች የሚሠራውን የኦዲት ሥራ ጥልቀትና ሽፋንን በተመለከተ መመሪያ ሊወጣ ይችላል፡፡

3.በማንኛውም መድን ሰጪ የውጭ ኦዲተር ሆኖ የተሾመ ሰው በመደበኛ የሥራ ሂደትና ለሌላ ለማንኛውም ሰው ከሚሰጠው አገልግሎት ባልተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመድን ሽፋን፣ ማንኛውንም ዓይነት ብድር፣ የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሌላ አገልግሎት ከዚያው መድን ሰጪ ሊያገኝ አይችልም።

[181] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(9) መሰረት ተሰረዘ፡፡

31. <u>የኦዲት ሪፖርት</u>

1.የአንድ መድን ሰጪ የሂሣብ ዓመት ከተጠናቀቀ በኋላ በምን ያህል ጊዜ የኦዲት ሪፖርት መውጣት እንዳለበት በመመሪያ ይወሰናል፡፡[182]

2.የማንኛውም መድን ሰጪ ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተመረመሩትን የሂሣብ መግለጫዎች እንዲሁም የኦዲት ግኝትና አስተያየት ያካተተ ሙሉ የኦዲት ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡

3.ብሔራዊ ባንክ የመድን ሰጪው ኦዲተር የመድን ሰጪውን ዓመታዊ የሂሳብ መዛግብት ለመመርመር ስለሚከተለው ስልትና የኦዲት ሥራው ሽፋንና ጥልቀት በተመለከተ ኦዲተሩ ሪፖርት እንዲያቀርብለት ማድረግና ኦዲተሩ የምርመራውን ሽፋንና ጥልቀት እንዲያሰፋ በፅሁፍ ሊያዝ ይችላል።

4.ብሔራዊ ባንክ የቀረበውን የውጭ ኦዲት ሪፖርት አጥጋቢ ሆኖ ያላገኘው እንደሆነ በድጋሚ የሂሣብ ምርመራ እንዲካሄድ ማዘዝ ወይም የተለየ ነፃ የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብለት ሌላ የውጭ ኦዲተር ወዲያው በመሾም ሂሣቡ እንደገና እንዲመረመር ማድረግ ይችላል፡፡ መድን ሰጪው በብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አዲስ የተሾመውን የውጭ ኦዲተር የአገልግሎት ክፍያ መሸፈን አለበት፡፡

5.ማንኛውም መድን ሰጪ የውጭ ኦዲተር ሂሣብ ምርመራ ተግባሩን በሚያካሂድበት ጊዜ፦

ሀ) የዚህ አዋጅ፣ ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎች በከፍተኛ ደረጃ መጣሳቸውን ወይም ያለመከበራቸውን፤

ለ) በመድን ሰጪው ወይም በማንኛውም መድን ሰጪው ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ የማጭበርበር ወይም ሌላ እምነት ማጉደል ወንጀል መፈጸሙን፤

ሐ) ከወትሮው የተለየ ወይም ሊደርስ ይችላል ተብሎ ባልተጠበቀ ጉዳት ምክንያት የመድን ሰጪው ካፒታል በከፍተኛ መጠን ቀንሶ መድን ሰጪው ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን ላይ የደረሰ መሆኑን፤

[182] ለ20/81 (2006) አ. 847 አላማ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

መ) መድን ሰጪው እንደ አንድ ቀጣይ ድርጅት ሥራውን ለማካሄድ ያለውን አቅም የሚጎዳ ወይም ለመድን ገቢዎች ወይም ለሌላ ገንዘብ ጠያቂዎች የተገባ ግዴታን መፈፀም የሚያስችል በቂ የፋይናንስ አቅም ሊኖረው እንደማይችል ከፍተኛ ግምት ላይ የተደረሰ እንደሆነ፣ ወይም

ሠ) ሌሎች ከፍተኛ የአሠራር ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች ተከስተው መገኘታቸውን፤

ሲደርስበት ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

6. ብሔራዊ ባንክ የማንኛውንም መድን ሰጪ የውጪ ኦዲተር በማንኛውም ጊዜ በመጥራት መድን ሰጪውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውይይት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

32. <u>የአስሊ ምርመራ</u>

1. የረጅም ጊዜ መድን ሥራ የሚያካሂድ ማንኛውም መድን ሰጪ በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት በቂ ልምድ ያለው አስሊ መሾም አለበት፡፡
2. የአስሊ ምርመራ ስለሚደረግበት ጊዜና ድግግሞሽ እንዲሁም ሪፖርቱ ለብሔራዊ ባንክ ስለሚቀርብበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
3. አስሊው የመድን ሰጪውን ሥራ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኙ የስሌት መርሆዎችና ይህንኑ በተመለከተ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ይገመግማል፡፡
4. አስሊው የምርመራ ሥራውን በሚያካሂድበት ጊዜ የመድን ሰጪውን የፋይናንስ አቋም በከፍተኛ ደረጃ ሊያናጋ የሚችል የአሠራር ጉድለት ወይም ሁኔታ መከሰቱን ለማመን የሚያስችለው ምክንያት ሲኖር ይህ ሁኔታ በመድን ሰጪው ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ቢካተትም ባይካተትም ለብሔራዊ ባንክ ወዲያውኑ በጽሑፍ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
5. ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የረጅም ጊዜ መድን ሥራ የሚያካሂድ መድን ሰጪ ከሾመው ሌላ አስሊ የመድን ሰጪውን ሥራ እንዲገመግም ሊሾም ይችላል።
6. አስሊ ማሟላት ስለሚገባው የብቃት መመዘኛዎች እንዲሁም የስሌት ሥራ የሚሠራበት አኳኋን በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## መረጃ ስለመስጠትና በመድን ሰጪዎች ላይ ስለሚካሄድ ምርመራ

### 33.መረጃ ስለመስጠት

1. ማንኛውም መድን ሰጪ በመመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ፡-
   ሀ) በሚገባ የተፈረሙ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች ሪፖርቶችን ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጁ ቅጾች፤
   ለ) ስለ ሥራ ጉዳዩ ለባለአክስዮኖች የሚያቀርበውን ሪፖርት ትክክለኛ ቅጂ፤ እና
   ሐ) የእያንዳንዱን ጠቅላላ የባለ አክስዮኖች ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ትክክለኛ ቅጂ፤ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም መድህን ሰጪ፦
   ሀ) በኦዲተር የተመረመረ እና የስራ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎችን በሁሉም የስራ ቦታዎችና ቅርንጫፎች ግልፅ በሆነ ቦታ ዓመቱን ሙሉ እንዲታዩ ማድረግ፤ እና
   ለ) የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና የኦዲተሩን መግለጫ አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ማሳተም፤
   አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት የፋይናንስ መግለጫዎች ለህዝብ እይታ ዝግጁ የማድረጉና በጋዜጣ አሳትሞ የማውጣቱ ተግባር የባለአክስዮኖች ዓመታዊ ጉባኤ በተካሄደበት በሁለት ሳምንታት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ አግባብ አላቸው ብሎ የሚያምንባቸው መረጃዎች ከመድን ሰጪዎች መጠየቅና ማግኘት ይችላል፤ ሆኖም
   ሀ) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈፀም፤
   ለ) የመድን ሰጪዎችን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ፤
   ሐ) በሕግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች፤
   መ) ብሔራዊ ባንክ ተጠሪ ለሆነለት አካል፤
   ሠ) በፍርድ ቤት ሲታዘዝ፤ ወይም

ረ) ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ለመወጣት ሲባል፤ ካልሆነ በቀር እነዚህ መረጃዎች ለማንኛውም ሰው ተላልፈው አይሰጡም፤

5. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው መግለጫ በማናቸውም ሁኔታ ትክክል ያልሆነ ወይም በማናቸውም አኳኋን ጉድለት ያለበት መስሎ ከታየው ብሔራዊ ባንክ፡-
   ሀ) የመግለጫውን ጉድለት ለማረም ወይም ለማሟላት እንደ አስፈላጊነቱ በኦዲተር ወይም በአስሊ የተረጋገጠ ሌላ ተጨማሪ መረጃ መድን ሰጪው እንዲያቀርብ ለመጠየቅ፤ ወይም
   ለ) መድን ሰጪው ማናቸውንም የሂሳብ መዝገብ፣ ወይም በማዘገየ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተ ሌላ ሠነድ አቅርቦ እንዲያስመረምር ሊያዝ፤ ይችላል፡፡

6. የማንኛውም መድን ሰጪ ዳይሬክተሮች መድን ሰጪው ለመድን ገቢዎችና ለሌሎች አበዳሪዎች፡-
   ሀ) ያለበትን ግዴታ መወጣት እንደማይችል፤ ወይም
   ለ) ክፍያዎችን በወቅቱ መፈፀም ሊሳነው እንደሚችል፤
   ሲገምት ሁኔታውን በጋራም ሆነ በተናጠል ወዲያውን ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

34.<u>በመድን ሰጪዎችላይ ስለሚደረግ ምርመራ</u>

1. ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ወይም በማናቸውም ግዜ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማንኛውም መድን ሰጪ ላይ በመድን ሰጪው ሥራ ቦታ በመገኘት ወይም በውጭ ሆኖ ምርመራ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በአንድ መድን ሰጪ ላይ ምርመራ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ በቂ መረጃ አያይዞ ቅሬታ ካቀረበ ብሔራዊ ባንክ ቅሬታ የቀረበበት የመድን ሰጪ በጤናማ ሁኔታ ላይ መገኘቱንና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የመድን ሰጪውን የሥራ እንቅስቃሴ በመምራት ሂደት ውስጥ መከበራቸውን ለማረጋገጥ በሚስጥር ምርመራ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ለማድረግ ይችላል፡፡

3. በመድን ሰጪዎች ላይ የሚካሔድ የምርመራ ሥራ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በብሔራዊ ባንክ ሰራተኞች ወይም ለዚህ ዓላማ ሲባል ብሔራዊ ባንክ በሚቀጥራቸው ሌሎች እምነት በሚጣልባቸውና ብቃት ባላቸው ሰዎች ሊካሄድ ይችላል፡፡
4. ብሔራዊ ባንክ ምርመራ እንዲያካሄዱ የሚመድባቸው ሰራተኞች ወይም ሌሎች ሰዎች ምርመራውን በሚገባ ለማካሄድ ያስፈልጋሉ ብለው በማመን ሲጠይቁ የመድን ሰጪው የቀድሞም ሆነ የወቅቱ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ስራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚዎች፣ ሰራተኞች ወይም ሌሎች ወኪሎች የመድን ሰጪው ሪከርዶች፣ ሃብቶችና የዋስትና ሰነዶች እንዲታዩ መፍቀድና የመድን ሰጪውን ስራ የሚመለከቱ መረጃዎችን መስጠት አለባቸው፡፡
5. በመድን ሰጪ ምርመራ ስራ ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎች ቁጥጥሩን ባካሄዱት ሰዎች በሚስጥር መጠበቅ አለባቸው፡፡

35.<u>**የምርመራ ሪፖርት**</u>

1. የምርመራ የመጨረሻ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት ለተመርማሪ መድን ሰጪ እንዲደርሰው ተደርጎ በሪፖርቱ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል፡፡
2. ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የምርመራ ሪፖርት ይዘት፦
   ሀ) ምርመራውን ባካሄዱት ሰዎችና ምርመራው በተደረገበት መድን ሰጪ ዳይሬክተሮችና ሰራተኞች፤ እና
   ለ) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈፀም ወይም የሕዝብ ጥቅምን ለማስከበር ሲባል ካልሆነ በቀር በብሔራዊ ባንክ፤

   በሚስጥር መጠበቅ አለበት፡፡

36.<u>**የማስተካከያ እርምጃዎች**</u>

በተደረገው ምርመራ ተመርማሪው መድን ሰጪ በብሔራዊ ባንክ እምነት አግባብ ያላቸው ሕጎችና መመሪያዎችን ያልተከተለ ወይም በተሰጠው የመድን ስራ ፍቃድ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልፈፀመ እንደሆነ ወይም የመድን ገቢዎችን ጥቅም በሚጎዳ ማናቸውም ተግባር ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ ወይም በመድን ሰጪው ስራ አመራር ላይ ከባድ ድክመት የተከሰተ እንደሆነ ባንኩ፦

1. ከምርመራው የሚነሱ ወይም የተያያዙ ማናቸውንም ጉዳዮች በሚመለከት ለመነጋገር መድን ሰጪው የባለአክሲዮኖች ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እንዲጠራ ማዘዝ፤
2. ስለሚመረምረው ጉዳይ ማንኛውም የመድን ሰጪ ዳይሬክተር ወይም ሰራተኛ የፅሁፍ መተማመኛ እንዲሰጥ መጠየቅ፤
3. አንድ ወይም ከዚያ በላይ ኃላፊዎቹን በመድን ሰጪው ባለአክሲዮኖች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በቦርዱ በተሰየመ ማናቸውም ኮሚቴ ወይም ሌላ አካል ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ለመወከልና አስተያየታቸው በስብሰባዎቹ ላይ እንዲሰማ ዕድል እንዲሰጣቸው ማዘዝ፤
4. ተገቢ ሆነው የተገኙ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መድን ሰጪውን በጽሁፍ ማዘዝ፤
5. የመድን ሰጪውን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚዎች ከስራ ማገድ ወይም ማሰናበት ወይም ለዚሁ ዓላማ በወጡ መመሪያዎች መሰረት የገንዘብ መቀጫ መወሰን፤
6. መድን ሰጪው አዲስ የመድን ውሎች እንዳይዋዋል ማገድ ወይም ሊያካሂድ በሚችለው የመድን ሥራ ዓይነቶች ላይ ገደብ መጣል፤
7. መድን ሰጪው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሊሰበስብ በሚችለው የአረቦን ገቢ መጠን ወይም በጠለፋ መድን አማካይነት ለጠለፋ መድን ሰጪዎች ሊያስተላልፍ በሚችለው የአደጋ ስጋት ተጋላጭነት መጠን ላይ ገደብ መጣል፤
8. መድን ሰጪው ሌላ ተቋም በባለቤትነት እንዳይዝ መከልከልን ጨምሮ ሃብቱን በሥራ ላይ የሚያውልበትን ሁኔታ መገደብ፤
9. የመድን ሰጪውን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል መገደብ፣ ማዘግየት ወይም መከልከል፤ ወይም
10. መድን ሰጪው በሞግዚት አስተዳደር ስር እዲሆን ማድረግ፤

ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለፈቃድ ማገድ ወይም መሠረዝና ስለሞግዚት አስተዳደርና መፍረስ

**37. ፈቃድ የማገድ ወይም የመሰረዝና በሞግዚት አስተዳደር ስር የማዋል እርምጃ የሚያስወስዱ ምክንያቶች**

1. ብሔራዊ ባንክ ከሚመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ከተከሰተ የማንኛውንም መድን ሰጪ ፈቃድ በመሰረዝ መድን ሰጪው በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዲውል ያደርጋል፡-
   ሀ) ለመድን ሰጪው ፈቃድ የተሰጠው በከፍተኛ ደረጃ የተዛባ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሆነ እንደሆነ፤
   ለ) መድን ሰጪው ፈቃድ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሥራ ያልጀመረ ወይም ሥራውን ለአንድ ዓመት ያቋረጠ እንደሆነ፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ወይም ከዚያ በላይ በአንድ መድን ሰጪ መኖራቸውን ሲያምን የመድን ሰጪውን ፈቃድ በማገድ በሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲውል ማድረግ ይችላል፡-
   ሀ) መድን ሰጪው ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን የደረሰ እንደሆነ ወይም በብሔራዊ ባንክ እምነት መድን ሰጪው ያለው ሀብት ለመድን ገቢዎችና ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በቂ ከለላ መስጠት የማይችል ከሆነ፤
   ለ) ህግን በመተላለፍ ወይም ጥንቃቄ በጎደለው አሠራር ምክንያት ከፍተኛ የሀብት ወይም የገቢ መመናመን የተከሠተ እንደሆነ፤
   ሐ) መድን ሰጪው ሥራውን እያካሄደ ያለው በመድን ገቢዎች ጥቅም ላይ ከፍ ያለ አደጋ ሊያስከትል በሚችል ጤናማ ባልሆነና ጥንቃቄ በጎደለው የአሠራር ሁኔታ ከሆነ፤
   መ) መድን ሰጪው ሆነ ብሎ በብሔራዊ ባንክ የተጣለን ማንኛውንም ገደብ የጣሰ እንደሆነ፤
   ሠ) መድን ሰጪው የሂሳብ መዝገቦችን፣ ሠነዶችን ወይም ሪኮርዶችን ሥልጣን ለተሰጠው የብሔራዊ ባንክ ተቆጣጣሪ ወይም ወኪል ለቁጥጥር ተግባር ለማቅረብ እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፤

ረ) መድን ሰጪው የክፍያ ጊዜያቸው ደርሶ መከፈል የሚገባቸው ግዴታዎችን መፈፀም የተሳነው እንደሆነ ወይም እንደነዚህ ዓይነት ዕዳዎችን መክፈል እንደማይችል በብሔራዊ ባንክ ሲገመት፤

ሰ) መድን ሰጪው፡-

1) በብሔራዊ ባንክ የተወሰነውን አነስተኛ የካፒታል መጠን የማያሟላ ከሆነ፤

2) በቂ ካፒታል የሌለውና ወደፊትም ካፒታሉን በሚያስፈልገው መጠን ለመጨመር አቅም እንደማይኖረው የሚገመት ከሆነ፤

3) በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ካፒታሉን በሚያስፈልገው በቂ መጠን መጨመር ያልቻለ እንደሆነ ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካፒታሉን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ዕቅድ ያላቀረበ እንደሆነ፤ ወይም

4) ለብሔራዊ ባንክ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ካፒታልን መልሶ የመገንባት ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ::

ሸ) መድን ሰጪው ተገቢ ያልሆኑ፣ ሕገወጥ የሆኑ ወይም ጥንቃቄ የጎደላቸው ተግባራትን በማከናወን የአገሪቱን ወይም የሕዝቡን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥሉ ፖሊሲዎች የተከተለ እንደሆነ፤

ቀ) ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ከሌላ መድን ሰጪ ጋር የተቀላቀለ እንደሆነ፤

በ) በብሔራዊ ባንክ የወጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ዳይሬክተሮችን፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎችን መሾም ያልቻለ እንደሆነ፤

ተ) በባለአክስዮኖች ውሣኔ መድን ሰጪው በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዲሆን ከተጠየቀ ወይም ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት ባለአክስዮኖቹ መድን ሰጪውን ለማፍረስ የወሰኑ እንደሆነ፤

ቸ) መድን ሰጪው እንደ አንድ ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ሕጋዊ ወይም ነፃ ተቋም መቀጠል የተሳነው እንደሆነ፤

ነ) መድን ሰጪው ገንዘቡን ወይም ሃብቱን ወይም ከእነዚህ ማንኛውንም ክፍል በሕግ የተከለከለ ሥራ ላይ ያዋለ እንደሆነ፤

ኘ) መድን ሰጪው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ ከመድን ሥራ ውጭ በሌላ ማንኛውም ሥራ ላይ የተሠማራ እንደሆነ ወይም ፈቃድ ከተሰጠው የመድን ሥራ ዓይነት ሌላ የመድን ሥራ ሲሠራ ከተገኘ፡፡

3. ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በማንኛውም መድን ሰጪ ላይ እርምጃ ሲወስድ እርምጃውን ከነምክንያቱ ወዲያውኑ ለመድን ሰጪው በፅሑፍ ማስታወቅ አለበት፡

4. ብሔራዊ ባንክ የማንኛውንም መድን ሰጪ ፈቃድ እንዲሰረዝ ሲወስን ፈቃዱ የተሰረዘበት መድን ሰጪ ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ውሳኔውን አሳትሞ ያወጣል፡፡

5. ፈቃድ የመሰረዝ ውሳኔው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ወይም ብሔራዊ ባንክ ከሚወስነው ማንኛውም ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

6. ፈቃዱ የተሰረዘበት መድን ሰጪ የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ማንኛውም ዓይነት የመድን ሥራ መስራት አይችልም፡፡

38.**ተፈጻሚነት የሚኖረው ሕግ**

የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 ከአንቀፅ 34 እስከ 48 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለመድን ሰጪ በሞግዚት አስተዳደር ሥር መዋልና መፍረስም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## በመድን ረዳቶች፣ በጉዳት አስተካካዮች እና በአስሊዎች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

39.**የፈቃድ አስፈላጊነት**

1. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ካልተሰጠው በቀር የመድን ረዳት ሆኖ መሥራት አይችልም::

2. የመድን ረዳት ሆኖ ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ የብቃት መመዘኛ መስፈርቶች በመመሪያ ይወሰናሉ::

3. የመድን ረዳት ሆኖ ለመሥራት የሚቀርብ የፈቃድ ማመልከቻ በመመሪያ በተወሰነው ቅጽ መሠረት ይቀርባል::

4. የመድን ረዳት ሆኖ ለመሥራት የፈቃድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በብሔራዊ ባንክ የተወሰነውን የሠነድ ምርመራና የፈቃድ ክፍያ መክፈል አለበት::
5. ማንኛውም መድን ሰጪ ፈቃድ ያልተሰጠውን ወይም የተሰጠው ፈቃድ ያልታደሰለትን ወይም የተሰረዘበትን ሰው የመድን ረዳት ሆኖ እንዲሠራ የፈቀደ ወይም አበል እንዲከፈለው ያደረገ እንደሆነ ሕገወጥ ድርጊት እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡

40.<u>የመድን ረዳቶች ፈቃድ ዕድሣት</u>

የመድን ረዳቶች ፈቃድ ስለሚታደስበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

41.<u>ፈቃድ ስለ ማገድና ስለመሠረዝ</u>

የመድን ረዳቶች ሥራቸውን የሚያካሂዱበት አኳኋን እንዲሁም ፈቃዳቸውን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች በመመሪያ ይወሠናሉ፡፡

42.<u>ክልከላ</u>

ማንኛውም የመድን ወኪል ከአንድ በላይ ለሆኑና ተመሣሣይ አብይ የመድን ሥራ ዓይነት ለሚያካሂዱ መድን ሰጪዎች በወኪልነት ሊሠራ ወይም ወኪል እንደሆነ በማስመሰል መቅረብ ወይም በሌላ መንገድ ሥራውን ለሕዝብ ማስተዋወቅ አይችልም፡፡

43.<u>ጉዳት አስተካካዮች እና አስሊዎች</u>

1. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ በጉዳት አስተካካይነት ወይም በአስሊ ሙያ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም፡፡
2. ለጉዳት አስተካካዮች እና አስሊዎች ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታና የብቃት መመዘኛ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አሥር</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

44.<u>የንግድ ሥነ-ምግባር</u>

መድን ሰጪዎች የመድን ሥራ የሚያካሂዱበት አኳኋን፣ ለመድን ገቢዎችና ለመድን ረዳቶች የሚኖርባቸው ኃላፊነቶች፣ የደንበኞችን ቅሬታ ለመስማትና መፍትሔ ለመስጠት መዘርጋት የሚገባቸው ሥርዓቶችና ሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮች በመመሪያ ይወሰናሉ፡፡

## 45.ከውጭ አገር መድን ሰጪዎች ጋር መዋዋል የተከለከለ ስለመሆኑ

1. ብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ካልፈቀደ በቀር ውሉ የሚፃፍበት ወይም የሚፈረምበት ሥፍራ የትም ቢሆን ስለአደጋ ወይም ስለሰው ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኝ ንብረት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀም ለተገባ ግዴታ ወይም ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡ ዕቃዎች የሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት የመድን ወይም የጉዳት ካሣ ውል በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ካልተሰጠው መድን ሰጪ ጋር መዋዋል አይፈቀድም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

## 46.መድን ሰጪው በሚሰጠው ብድርና የገንዘብ ዋስትና ላይ ስለሚጣል ገደብ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር መድን ሰጪው ለማንኛውም ዳይሬክተር፣ ባለአክስዮን፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ኦዲተር፣ አስሊ ወይም ለማንኛውም የመድን ረዳት ወይም ከነዚህ ሰዎች ጋር ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሰው ለመድን ሰጪው ኩባንያ ሰራተኞች ሁሉ ከተፈቀደ የሰራተኞች ጥቅማጥቅም በስተቀር ማናቸውንም ዓይነት ብድር ወይም የገንዘብ ዋስትና ሊሰጥ አይችልም፡፡ ሆኖም ይህ ገደብ መድን ሰጪው የገባውን የሕይወት መድን ውል ዋጋ መጠን ሳያልፍ ለሕይወት መድን ገቢዎች የሚሰጠውን ብድር አይጨምርም፡፡[183]
2. ማንኛውም መድን ሰጪ የራሱን አክስዮን በዋስትና በመያዝ ማናቸውንም ዓይነት ብድር ወይም የገንዘብ ዋስትና ሊሠጥ አይችልም፡፡

## 47.ከፈቃድ ማመልከቻ ጋር በቀረቡ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ስለሚያጋጥም ለውጥ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መድን ሰጪው ፈቃድ ለማግኘት ካቀረበው ማመልከቻ ጋር አባሪ በሆኑት ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ለውጥ ካጋጠመ መድን ሰጪው ያጋጠመውን ለውጥ ሙሉ ዝርዝር ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡

[183] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(10) መሰረት ተሻሻለ፡፡

2. የተደረገው ለውጥ የአረቦን ምጣኔን፣ የመድን ገቢውን ጥቅሞች ወይም መድን ገቢው እንዲያደርግ የሚጠየቀውን ስምምነት ወይም እንዲገባ የሚጠየቀውን ግዴታ የሚነካ ሲሆን በአስሊ ወይም ሌላ አግባብ ባለው ባለሙያ የተሰጠ የምስክር ወረቀት አብሮ መቅረብ አለበት፡፡

48.**<u>የመድን ሽፋን በዱቤ መስጠት ስለ መከልከሉ</u>**

1. በከፊል ወይም በሙሉ በዱቤ የተሸጠ የመድን ፖሊሲ ዋጋ አይኖረውም፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ በፌደራል ወይም በክልል መንግስት አካላት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተጨማሪ ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

49.**<u>የደንበኞችን ማንነት ስለማወቅ</u>**

መድን ሰጪዎች የደንበኞቻቸውን ማንነት በትጋት ተከታትለው የሚያውቁበትንና አጠራጣሪ የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት የሚያደርጉበትን ሥርዓት ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

50.**<u>የመድን ሰጪዎችና የባንኮች ግንኙነት</u>**

1. የመድን ሽፋን መስጠትን፣ ብድር መስጠትን፣ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበልንና ሌሎች የመድንና የባንክ አገልግሎቶች መስጠትን ጨምሮ በመድን ሰጭዎችና በባንኮች መካከል የሚደረጉ የስራ ግንኙነቶች በማናቸውም ረገድ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር ከሚደረጉት የስራ ግንኙነቶች ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ሁኔታዎች መደረግ አለባቸው፡፡
2. በመድን ሰጪዎችና በባንኮች መካከል የሚኖረውን የስራ ግንኙነት የሚገዙ ተጨማሪ ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

51.**<u>መረጃዎችን እንዲታተሙ ስለማድረግ</u>**

ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ መሰረት የቀረበን ወይም የተሰበሰበን ማናቸውንም መረጃ ወይም ስታትስቲካዊ አሐዞች በከፊልም ሆነ በሙሉ አግባብ ነው ብሎ ባመነበት አቀራረብና ጊዜ አሳትሞ ሊያወጣ ይችላል፤ ሆኖም የጉዳዩ ይፋ መሆን የፋይናንስ ዘርፉን ጤናማነት ለማጠናከር የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር የማናቸውም መድን ሰጪ ወይም ደንበኛ ዝርዝር መረጃ ወይም ስታትስቲካዊ አሃዞች ይፋ ሊያደርግ አይችልም፡፡

**52.የብሔራዊ ባንክ ሰራተኞችና ወኪሎች ከግል ተጠያቂነት ስለመጠበቃቸው**

1. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ሲባል የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞችና ወኪሎች በቅን ልቦና ለሚፈፀሙት ማናቸውም ድርጊት በግል ሊጠየቁ አይችሉም፡፡
2. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ሲባል ማንኛውም የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ ሰው በቅን ልቦና በፈፀመው ድርጊት ምክንያት በፍርድ ቤት የቀረበ ክስ ለመከላከል የሚያስፈልገውን ወጪ ጨምሮ በሌሎች ማናቸውም ዕዳዎች ተጠያቂ ቢሆን ብሔራዊ ባንክ ወጪውን ወይም ዕዳውን ይሸፍናል፡፡

**53.ስለ ቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ**

1. በብሔራዊ ባንክ ትዕዛዝ በማንኛውም መድን ሰጪ ላይ የአስሊ ምዘና፣ ልዩ ምርመራ፣ ሙያዊ ዳሰሳ ወይም ኦዲት ከተካሄደ ወይም እንዲካሄድ ከተደረገ ለሥራው የወጣውን ወጪ ጉዳዩ የሚመለከተው መድን ሰጪ እንዲሸፍን ባንኩ ሊያዝ ይችላል፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ ምርመራ ለማካሄድ ያወጣውን ወጪ ለዚህ ዓላማ ባወጣው መመሪያ መሠረት ምርመራው የተካሄደበት መድን ሰጪ እንዲሸፍን ባንኩ ሊያዝ ይችላል፡፡

**54.የጠለፋ መድን**

የጠለፋ መድን የሚካሄድበት ሁኔታና መስፈርት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**55.የጠለፋ መድን ሰጪን ስለመቆጣጠር [184]**

1. ብሔራዊ ባንክ የጠለፋ መድን ሰጪን ይቆጣጠራል፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ የጠለፋ መድን ሰጪን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆነ መመሪያ ያወጣል፡፡
3. ከአንቀጽ 6(2-5)፣ 27(3)፣ 34(2)፣39-45፣ 48-50፣ 58 እና 59 (እንደተሸጋሸገው) በስተቀር ሁሉም የአዋጁ ድንጋጌዎች በጠለፋ መድን ሰጪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

---

[184] በ26/6(2012) አ.1163 አንቀፅ 2(11) መሰረት ከአዋጁ አንቀጽ 54 ቀጥሎ አዲስ አንቀጽ 55፣ 56፣ 57፣ 58፣ 59፣ 60 ተጨምረው ከአንቀጽ 55 እስከ 60 ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 61 እስከ 66 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

56.<u>በዲጅታል ዘዴዎች የመድን አገልግሎት ስለመስጠት</u>

በዲጅታል ዘዴዎች የመድን አገልግሎት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ይወስናል፡፡

57.<u>የማስታወቂያ ይዘትን ስለመቆጣጠር</u>

ማናቸውም መድን ሰጪ በማናቸውም ጊዜ በብሔራዊ ባንክ እምነት ሐሰተኛ፣ አሳሳች፣ አደናገሪ ወይም የሌላውን ጥቅም የሚጎዳ የተከፈለበትን የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ማስታወቂያ፣ ፖስተር፣ ቢልቦርድ፣ በራሪ ወረቀት፣ ሰርኩላር ወይም ሌላ ሰነድ እና የተከፈለበትን የጋዜጣ እና የመጽሄት ማስታወቂያ አውጥቶ ቢገኝ መድን ሰጪው ማስታወቂያውን እንዲያቋርጥ፣ እንዲያሻሽል ወይም ከማስተዋወቅ እንዲቆጠብ ብሔራዊ ባንክ ሊያዘው ይችላል፡፡

58.<u>የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ (ፕሪሚየም) ስለመወሰን</u>

ብሔራዊ ባንክ ዝቅተኛ የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ ለመወሰን ይችላል፡፡ ዝቅተኛ የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ ስለሚወሰንበት ሁኔታ በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

59.<u>የመድን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ</u>

የመድን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት እና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል መመሪያ ብሔራዊ ባንክ ሊያወጣ ይችላል፡፡

60.<u>ስለታካፉል መድን ሰጪ ኩባንያ ፈቃድ ስለመስጠት እና ስለመቆጣጠር</u>

1. በአዋጁ የመድን ሥራን ለመሥራት እና ለመቆጣጠር የተደነገጉ ድንጋጌዎች እና መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ብሔራዊ ባንክ የታካፉል መድን ሥራ ለሚሰራ መድን ሰጪ ፈቃድ ስለሚሰጥበት እና ቁጥጥር ስለሚያካሄድበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ መመሪያዎችን ያወጣል፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛው የመድን ሥራ ጋር የታካፉል አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመቆጣጠር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

61.<u>የመረጃ መጋራት ስርዓት</u>

ብሔራዊ ባንክ መድን ሰጪዎች መረጃ የሚለዋወጡበት ሥርዓት አደረጃጀትን፣ አሠራሩንና ወጪ የሚጋሩበትን ሁኔታ በተመለከተ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

62.<u>መድን ሰጪዎች ስለሚይዟቸው መዝገቦች</u>

በመድን ሰጪዎች መያዝ የሚገባቸው የመዝገብ ዓይነቶችና በመዝገቦቹ ውስጥ መመዝገብ የሚገባቸው መረጃዎች በመመሪያ ይወሰናሉ፡፡

63.<u>ቅጣት</u>

በወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና የጥፋት ድርጊቱ ለቀጠለበት ለእያንዳንዱ ቀን በብር 20,000 መቀጫ ይቀጣል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ (4) የተዘረዘሩትን ሠነዶች እንዲያቀርብ በብሔራዊ ባንክ ተጠይቆ ያላቀረበ ወይም እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ከሰባት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት ከሆነ የእስራት ቅጣቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ድርጅቱን በኃላፊነት በሚመራው ሰው ላይ ይሆናል፡፡
4. የዚህን አዋጅ አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) ወይም አንቀፅ 17 ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጫ ይቀጣል፡፡
5. የዚህን አዋጅ አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ (6) ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም የመድን ሰጪ ዳይሬክተር ከሰባት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጫ ይቀጣል፡፡
6. ማንኛውም የመድን ሰጪ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፡-

   ሀ) ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መፈፀም እንዳይችል ወይም በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በመድን ሰጪው ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዳያካሒድ እንቅፋት ከሆነ፤

ለ) ለማታለል በማሰብ የሐሰት ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ ወይም በመድን ሰጪው መዝገብ፣ ሂሳብ፣ ሪፖርት ወይም መግለጫ ውስጥ የመዘገበ እንደሆነ ወይም መመዝገብ የነበረበትን መግለጫ ወይም መረጃ ሳይመዘግብ የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) መድን ሰጪው ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የመድን ውለታ የተዋዋለ ወይም ሌላ ሰው እንዲዋዋል ያዘዘ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፤

ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 50,000 እስከ 100,000 በሚደርስ መቀጫ ይቀጣል፡፡

7. ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈፃፀማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ እስራትና እስከ ብር 10,000 በሚደርስ መቀጫ ይቀጣል፡፡

## 64.ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 65. የተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

1. የመድን ስራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1996 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ህግ፣ በመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች መሰረት ሊፈፀሙ የሚገባቸው ግዴታዎች ይህ አዋጅ መድን ሰጪዎችን ነፃ አያደርጋቸውም፡፡

66. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 16 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 799/2005

## ስለተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የወጣ አዋጅ

በተሽከርካሪ ምክንያት እየደረሰ ያለው አደጋ በየጊዜው እየጨመረ በመምጣት ላይ በመሆኑ፤ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት የሚደርሰው የሰው ሞት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ኪሣራ ማህበራዊ ችግር የሚያስከትል በመሆኑ፤

የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበትን ስርዓት ማመቻቸትና የተሽከርካሪ ባለንብረቶች የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በነባሩ የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ አፈፃፀም የተለዩ ችግሮችና ያልተካተቱ ጉዳዮች በመኖራቸው እነዚህን እና ሌሎች ተያያዥ ድንጋጌዎችን ያካተተ ህግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "የመድን ምስክር ወረቀት" ማለት የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ህጋዊ ግዴታ ያለበት ሌላ ሰው ተሽከርካሪው በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው አደጋ በዚህ አዋጅ መሠረት መድን የገባለት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፤
   2. "የመድን ኩባንያ" ማለት አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ጠቅላላ የመድን ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ነው፤
   3. "መድን ገቢ" ማለት ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው አደጋ በዚህ አዋጅ መሠረት መድን የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፤

4. “መድን ሰጭ” ማለት ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርስው አደጋ በዚህ አዋጅ መሰረት ተገቢውን የመድን ሽፋን የሰጠ የመድን ኩባንያ ነው፤
5. “ተሽከርካሪ” ማለት ከአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ ሠረገላና ከብስክሌት በስተቀር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት የባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሳቢ ወይም ተሳቢ ነው፤
6. “ባለሞተር ተሽከርካሪ” ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል በመንገድ ላይ እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ነው፤
7. “ተሳቢ” ወይም “ግማሽ ተሳቢ” ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ኅታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችል ተሽከርካሪ ነው፤
8. “የመድን ፖሊሲ” ማለት የመድን ገቢው ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው የሞት አደጋ፣ የአካል ጉዳት ወይም የንብረት ኪሣራ ካሣ ለመክፈል እና የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ክፍያን ለመፈጸም መድን ሰጪው ውለታ የሚገባበት ሰነድ ነው፤
9. “መንገድ” ማለት ማናቸውም አውራ ጎዳና፣ የከተማ ወይም የገጠር መንገድ፣ የተሽከርካሪዎች ማቆሚያ ወይም ማራገፊያና መጫኛ፣ ድልድይ ወይም ተሽከርካሪ የሚጠቀምበት ማናቸውም ሌላ መተላለፊያ ነው፤
10. “ሦስተኛ ወገን” ማለት በመድን ፖሊሲ መሠረት ኃላፊነት ያስከተለ የተሽከርካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ ከመድን ገቢው፣ ከመድን ገቢው ቤተሰብ፣ ከአሽከርካሪው ወይም ከመድን ገቢው ተቀጣሪ ሰራተኛ በስተቀር የመድን ፖሊሲው ተፈፃሚነት የሚመለከተው ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፤
11. “ቢጫ ካርድ” ማለት የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድንን በሚመለከት በምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ አባል አገሮች በተፈረመው ፕሮቶኮል መሠረት የሚሰጥ ካሣ ለመክፈል የሚያስችል የምስክር ወረቀት ነው፤
12. “ሚኒስቴር” ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ነው፤
13. “ቤተስብ” ማለት የመድን ገቢው የትዳር ጓደኛ፣ ልጅ፣ አባት፣ እናት ወይም መድን ገቢው የሚያስተዳድረው ማንኛውም ሰው ነው፤

14. "የአረቦን ተመን" ማለት በመንግስት የሚወሰንና በዚህ አዋጅ የተደነገገውን የመድን ፖሊሲ ለመግዛት በመድን ገቢው ለመድን ሰጪው የሚፈፀም ክፍያ ነው፤
15. "የፈንድ ተመን" ማለት በመንግሥት ተወስኖ ከሚሰበሰበው አረቦን ተመን ላይ ተጨማሪ በመቶኛ ወይም በሌላ አግባብ በማስላት ለመድን ፈንዱ ገቢ የሚሆን የገንዘብ መጠን ነው፤
16. "አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት" ማለት በመንገድ ላይ በደረሰ የተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት የተጐዳ በአደጋው ቦታ፣ ወደ ሕክምና ተቋም በሚጓጓዝበት ወቅት እና በሕክምና ተቋሙ ድንገተኛ ክፍል ውስጥ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ነው፤
17. "ካሣ" ማለት እንደ አግባብነቱ በመድን ሰጪው ኩባንያ ወይም በኤጀንሲው ለተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂው የሚከፈል ክፍያ ነው፤
18. "የአካል ጉዳት" ማለት በተሽከርካሪ አደጋ የደረሰበት ግለሰብ በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሯዊ እንቅስቃሴ ላይ የደረሰ ጉዳት ሲሆን ጊዜያዊ፣ ከፊል ቋሚ ወይም ሙሉ ቋሚ የአካል ጉዳትን ያካትታል፣
19. "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋመው የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
20. "ቦርድ" ማለት የኤጀንሲው ቦርድ ነው፤
21. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
22. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን አስፈላጊነት</u>

   1. ማንኛውም ሰው ተሽከርካሪው በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው አደጋ የጸና የመድን ሽፋን ሳይኖረው ተሽከርካሪውን በመንገድ ላይ መንዳት፣ መጠቀም ወይም ሌላ ሰው እንዲነዳ ወይም እንዲጠቀም ማድረግ ወይም መፍቀድ አይችልም።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስቴሩ የመድን ሽፋን ሳይኖራቸው በመንገድ ላይ ሊነዱ ወይም ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን ሊወስን ይችላል፣ ተጎጂዎች የጉዳት ካሣ የሚያገኙበትን የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመድን ፖሊሲ

### 4. የሶስተኛ ወገን መድን ፖሊሲ ስለመስጠት

1. የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ፖሊሲ ሊሰጥ የሚችለው በመድን ኩባንያዎች ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠ የመድን ፖሊሲ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ ለሚያደርሰው የሰው ሞት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ኪሳራ መከፈል የሚገባውን ካሣና የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ወጪን የሚሸፍን መሆን አለበት፡፡
3. ጠቅላላ የመድን ሽፋን የሚሰጥ የመድን ኩባንያ በዚህ አዋጅ የተደነገገውን የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ፖሊሲ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
4. ለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን የመድን ፖሊሲ የሚከፈለው የአረቦን ተመን ኤጀንሲው በሚያቀርበው ጥናት ላይ ተመስርቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ ቢኖርም ተደጋጋሚ የተሽከርካሪ አደጋ የሚያደርሱ መድን ገቢዎችን እና አሽከርካሪዎችን በተመለከተ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ኤጀንሲው በሚያደርገው ጥናት ላይ ተመስርቶ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል።

### 5. በመድን ፖሊሲ ተፈጻሚነት ላይ ስለሚደረጉ ገደቦች

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የመድን ምስክር ወረቀት ቀጥሎ የተመለከቱትን ምክንያት በማድረግ ጉዳት ለደረሰበት ሰው መድን ሰጭው ካሣ እንዳይከፍል ለመገደብ አያስችሉትም፡-

1. ተሽከርካሪውን የሚያንቀሳቅሰውን ሰው ዕድሜ ወይም የአካል ወይም የአእምሮ ሁኔታ፤
2. የተሽከርካሪውን ሁኔታ፣ የፈረስ ጉልበት፣ የሲሊንደር ችሎታ ወይም ዋጋ፤

3. ተሽከርካሪው የሚይዘውን ሰው ብዛት፣ የሚጫነውን ዕቃ ክብደት ወይም አካላዊ ባህሪ ወይም ልዩ መዣሪያ፤ ወይም
4. ተሽከርካሪው በአገልግሎት ላይ የሚውልበትን ጊዜ ወይም አካባቢ፡፡

6. <u>የመድን ፖሊሲ የውል ሁኔታዎች</u>

1. በመድን ፖሊሲው ውስጥ፡-
   ሀ) ፖሊሲው ተጠያቂነትን አያስከትልም የሚል፤ ወይም
   ለ) በፖሊሲው መሠረት ለካሣ ክፍያ ጥያቄ መነሻ የሚሆነው ክስተት ከደረሰ በኋላ የተወሰነ ድርጊት ከተፈጸመ ወይም ሳይፈጸም ከቀረ ኃላፊነቱ ቀሪ ይሆናል የሚል፤

   የውል ሁኔታ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው በመድን ፖሊሲው መሠረት መድን ሰጭው ለሦስተኛ ወገን እንዲከፍል የሚደረገው ካሣ መድን ገቢው መልሶ ለመድን ሰጭው እንዲከፍል ለማድረግ የሚደነግገውን የውል ሁኔታ የሚሽር አይሆንም።

7. <u>በመድን ፖሊሲ ስለማይሸፈኑ ሁኔታዎች</u>

የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ፖሊሲ የሚከተሉትን በሚመለከት ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡-

1. በመድን ገቢው ወይም ቤተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የሞት አደጋ ወይም የአካል ጉዳት ወይም የንብረት ጉዳት፤
2. በመድን ገቢው ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው በሥራው ላይ የሚደርስ የግጭት አደጋ ወይም የሞት አደጋ ወይም የአካል ጉዳት ወይም የንብረት ጉዳት፤
3. መድን በተገባለት ተሽከርካሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት፤
4. መድን በተገባለት ተሽከርካሪ ላይ በኪራይ ወይም በክፍያ በሚጓጓዝ ንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት የሚያስከትለውን ሃላፊነት፤
5. ማንኛውም በመድን ፖሊሲ ሽፋን የተሰጠው የመድን ገቢ የግል ንብረት ወይም በርሱ ቁጥጥር ወይም ሃላፊነት ወይም በአደራ የሚገኝ ንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት፤
6. ከኢትዮጵያ ግዛት ክልል ውጪ የደረሰ የተሽከርካሪ አደጋ ተከትሎ የመጣ ሃላፊነት፡፡

8. **ክልከላ**

ማንኛውም ሰው የተሽከርካሪ መድን ፖሊሲ ለማግኘት ሲል የፖሊሲውን ተፈጻሚነት ሊያስቀር የሚችል ሀሰተኛ መግለጫ መስጠት ወይም በፖሊሲው ላይ ያለውን መብት ሊያስቀር የሚችል ማናቸውንም ድርጊት መፈጸም አይችልም።

**ክፍል ሶስት**

**ስለመድን ምስክር ወረቀት**

9. **የመድን ምስክር ወረቀት ስለመስጠት**

1. የመድን ኩባንያ ለመድን ገቢው የመድን ፖሊሲ በሚሰጥበት ጊዜ የመድን ምስክር ወረቀትም አብሮ መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ የመድን ምስክር ወረቀት፡-
   ሀ) የመድን ገቢውን ስምና አድራሻ፣
   ለ) የተሽከርካሪውን የሠሌዳ፣ የሞተርና የሻሲ ቁጥሮች፣
   ሐ) የመድን ፖሊሲው የሚጀምርበትና የሚያበቃበት ጊዜ፣
   መ) የመድን ፖሊሲው የተሰጠባቸውን ሁኔታዎች፣
   ሠ) በመድን ፖሊሲው ተጠቃሚ የሚሆኑትን ሰዎች ወይም ወገኖች፣ እና
   ረ) የመድን ሰጭውን ስምና አድራሻ፣
   መያዝ አለበት፡፡
3. በመድን ምስክር ወረቀቱ ላይ መድን ሰጭውን የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት የመድን ፖሊሲ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. የመድን ሽፋን ውል ሲቋረጥ ወይም የውል ዘመኑ ሲያልቅ መድን ገቢው የመድን ምስክር ወረቀቱንና የመድን ተለጣፊውን ወዲያውኑ ለመድን ሰጭው መመለስ አለበት፡፡

10. **የመድን ምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የተሰጠ የመድን ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ የሚፀና መሆን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በበቂ ምክንያት ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ለሚሰጥ የመድን ፖሊሲ የውል ዘመኑን መሰረት ያደረገ የመድን ምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፡፡ አፈጻጸሙን እንደአስፈላጊነቱ ኤጀንሲው በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ሚኒስቴሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

11.**መረጃ ስለመስጠት**

1. መድን ገቢው የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው መብት ባለው ሰው ወይም በእርሱ ስም ጥያቄ ሲቀርብለት፡-

   ሀ) ተሽከርካሪው መድን ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን፤ እና

   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት በተሰጠው የመድን ምስክር ወረቀት ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች፤

   በመግለጽ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መድን ሰጭው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን መረጃ ለኤጀንሲው የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3. በማንኛውም የህግ አስከባሪ አካል ወይም የህክምና ተቋም የመድን ሰጭው በሰጠው የመድን ምስክር ወረቀት ላይ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ተገቢውን መረጃ ከ24 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

12.**ስለመድን ተለጣፊ ምልክት**

1. ማንኛውም መድን ሰጪ የመድን ተለጣፊ ምልክት ተናባቢ ከሆነው ምስክር ወረቀት ጋር ለመድን ገቢው መስጠት አለበት፡፡

2. ከፊት ለፊት የንፋስ መከላከያ መስታወት ላለው ተሽከርካሪ የተሰጠው የመድን ተለጣፊ ምልክት ሙሉ ለሙሉ በግልፅ እንደሚታይ ሆኖ በዚሁ መስታወት ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

3. ለተሳቢ ወይም የንፋስ መከላከያ መስታወት ለሌለው ተሽከርካሪ የተሰጠ የመድን ተለጣፊ ምልክት ሁልጊዜም ተሽከርካሪዉን በሚነዳው ሰው እጅ መቀመጥ አለበት፡፡

13.**የመድን ተለጣፊ ምልክት አለመያዝ ወይም አለመኖር**

1. የመድን ተለጣፊ ምልክት አለመያዝ ተሽከርካሪው የመድን ሽፋን እንደሌለው ስለሚያስቆጥረው የመድን ምስክር ወረቀት እስኪመጣ ድረስ ፖሊስ እንዲህ ያለውን ተሽከርካሪ ይዞ የማቆየት ሥልጣን ይኖረዋል።
2. ወቅታዊ የሆነ የመድን ተለጣፊ ምልክት አለመኖር ተሽከርካሪው በመንገድ ላይ ሲነዳ ወይም ጥቅም ላይ ሲውል የፀና የመድን ፖሊሲ የሌለው መሆኑን ስለሚጠቁም ተገቢው የመድን ምስክር ወረቀት እስካልቀረበ ድረስ እንደሁኔታው የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም በህግ ሃላፊነት ያለበት ወገን ወይም ተሽከርካሪው በመንገድ ላይ እንዲነዳ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል ያደረገ ወይም የፈቀደ ወይም ተሽከርካሪውን ሲነዳ ወይም ሲጠቀም የነበረ ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተላለፈ ይቆጠራል።

14. **ምትክ ስለመስጠት**

የመድን ምስክር ወረቀት ወይም የመድን ተለጣፊ ምልክት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ መድን ገቢው ይህንኑ ገልጾ ሲጠይቅ መድን ሰጭው ምትክ መስጠት አለበት፡፡

**ክፍል አራት**

**በመድን የመሸፈን ሃላፊነት**

15. **የመድን ገቢው ግዴታዎች**

መድን ገቢው ከሚከተሉት ምክንያቶች የሚመነጩ ሀላፊነቶች በሚገባው መድን እንዲሸፈኑ የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል፡-

1. መድን የተገባለት ተሽከርካሪ የሚያደርሰው ግጭት፣ የእሳት ቃጠሎ ወይም ፍንዳታ፤
2. የተሽከርካሪው ጭነት፣ አካል ወይም የሚገለገልበት መሣሪያ ወድቆ የሚያደርሰው ጉዳት፤ እና
3. ከተሽከርካሪው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የሚደርስ ማንኛውም ጉዳት፡፡

16. **የሃላፊነት መጠን**

1. በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ መድን ፖሊሲ የሚሸፈነው የካሣ መጠን፡-
   ሀ) በአንድ ሰው ላይ ለሚደርስ የሞት አደጋ ከብር 5,000 ያሳነሰና ከብር 40,000 ያልበለጠ፣
   ለ) በአንድ ሰው ላይ ለሚደርስ የአካል ጉዳት ከብር 40,000 ያልበለጠ፡፡

ሐ) በንብረት ላይ ለሚደርስ ኪሳራ ከብር 100,000 ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

2. ለህክምና እና ሌሎች ከጉዳቱ ጋር ተያያዥነት ኖሯቸው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ለሚከፈል ካሣ የተፈፀመ ወጪ ተጎጂው ቋሚ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ሲደርስበት ከሚከፈለው የካሣ መጠን ላይ የሚታሰብ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተወሰነው መጠን በላይ ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ሰው ይህንኑ ተጨማሪ ክፍያ መድን ገቢው ወይም በህግ ሃላፊነት የተጣለበት አካል እንዲከፍለው አግባብ ባለው ህግ መሠረት የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
4. በማንኛውም ተሽከርካሪ የደረሰ ቋሚ የአካል ጉዳት መጠን በህክምና ቦርድ መረጋገጥ ይችላል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን የሃላፊነት መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት የማሻሻል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

17. **<u>አደጋን ስለማስታወቅና ስለካሳ ክፍያ ጥያቄ</u>**

1. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካልኖረ በስተቀር መድን ገቢው መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ ማድረሱን ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ በ10 ቀን ውስጥ ለመድን ሰጭው ማስታወቅ አለበት፡፡
2. ካሣ የመጠየቅ መብት ያለው ማንኛውም ሦስተኛ ወገን ካሉት ማስረጃዎች ጋር የካሣ ጥያቄውን ለመድን ሰጭው በቀጥታ ማቅረብ ይችላል፡፡

18. **<u>የፍርድ ቤት ውሳኔን ስለመፈጸም</u>**

1. በመድን ፖሊሲ የተሸፈነ ኃላፊነትን በሚመለከት በመድን ገቢው ላይ የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሲኖር መድን ሰጭው በፖሊሲው ላይ ያለበትን ተጠያቂነት ለማስቀረት ወይም ለመሰረዝ መብት ቢኖረውም ወይም ፖሊሲውን አስቀርቶት ወይም ሰርዞት ቢሆንም እንኳ ለፍርድ ባለመብቶቹ በውሳኔው የተመለከተውን ገንዘብ ወጪና ወለድን ጨምሮ መክፈል አለበት፡፡
2. ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የመድን ፈንድ

19.**መቋቋም**

የመድን ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ) ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚከፈት ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

20.**የፈንዱ ዓላማ**

1. የፈንዱ ዓላማ መድን ባልተገባለት ወይም ባልታወቀ ተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት፡-

   ሀ) ጉዳት የደረሰበት ሰው አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ፣

   ለ) የአካል ጉዳት ለደረሰበት ሰው ካሣ እንዲከፈለው ማድረግ፣ እና

   ሐ) ለሞተ ሰው ቤተሰብ አባላት ካሣ እንዲከፈል ማድረግ፣

   ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ከፈንዱ የሚከፈለው የገንዘብ መጠን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት በተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ፖሊሲ በሚሸፈነው የሃላፊነት መጠን ድረስ ይሆናል፡፡

3. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ያወጣውን ወጪ ለጉዳቱ በሃላፊነት ተጠያቂ ከሆነው ሰው ላይ የማስመለስ መብት ይኖረዋል።

21. **የፈንዱ አስተዳደር**

ፈንዱ በኤጀንሲው ይተዳደራል፡፡

22. **የሚኒስቴሩ ስልጣንና ተግባር**

ሚኒስቴሩ፡-

1. የዚህ አዋጅ ዓላማ እንዲሳካ ለማድረግ ኤጀንሲውን በበላይነት ይከታተላል፣ እንደአስፈላጊነቱም መመሪያ ያወጣል፤

2. የኤጀንሲውን ተግባር በየወቅቱ ይገመግማል፡፡

23. **የፈንዱ የገንዘብ ምንጭ**

1. የፈንዱ የገንዘብ ምንጭ ከፈንዱ ተመን የሚሰበሰብ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ሌላ ተጨማሪ ገቢ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰበሰበው የፈንድ ተመን በኤጀንሲው ጥናት ላይ ተመሥርቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል፡፡

24. **ስለፈንዱ ክፍያዎች**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ለተመለከቱት ዓላማዎች ከፈንዱ ሂሳብ ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚከፈለው ቦርዱ በሚያወጣው የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

25. **ስለኦዲት**

የፈንዱ ሂሳብ ቦርዱ በሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**ክፍል ስድስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

26. **በውጭ አገር ስለተመዘገበ ተሽከርካሪ**

1. በውጭ አገር የተመዘገበና በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ ለመንቀሳቀስ ፈቃድ የተሰጠውን ተሽከርካሪ የሚያሽከረክር ሰው የፀና የመድን ምስክር ወረቀትና የመድን ተለጣፊ ምልክት መያዝ ወይም የመድን ፖሊሲው በአገር ውስጥ የመድን ኩባንያ የተሰጠ ካልሆነ ቢጫ ካርድ ወይም ተመሳሳይነት ያለው የመድን ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በውጭ አገር የተመዘገበ ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ ለሚያደርሰው አደጋ የሚኖረው የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ከተደነገገው የሃላፊነት መጠን ማነስ የለበትም፡፡

27. **ስለአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት**

1. የተሽከርካሪ አደጋ የደረሰበት ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ለሦስተኛ ወገን በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈን ሆነም አልሆነም ወጪው እስከ ብር 2,000 የሚደርስ አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት ይኖረዋል።
2. ማናቸውም የህክምና ተቋም የተሽከርካሪ አደጋ ደርሶበት ወደ ህክምና ተቋሙ ለመጣ ማንኛውም ተጎጂ አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3. ማንኛውም ተሽከርካሪ በሚያደርሰው ጉዳት የህክምና ተቋሙ ለአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ያወጣውን ወጪ በኤጀንሲው አቅራቢነት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የክፍያ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት እንዲከፈለው ሊጠይቅ ይችላል።
4. መድን ያልተገባለት ወይም ያልታወቀ ተሽከርካሪ ለሚያደርሰው ጉዳት የህክምና ተቋሙ ለህክምና አገልግሎት ያወጣውን ወጪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 መሠረት በቀጥታ ከፈንዱ እንዲከፈለው ለመጠየቅ ይችላል።

28. **ተፈጻሚነት ስለሚኖራቸው ሕጎች**

መድንን የሚመለከቱ የንግድ ሕግና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

29. **ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒሰቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

30. **ቅጣት**

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብን ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ከብር 3,000 እስከ ብር 5,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል፡፡

31. **የተሻረ ሕግ**

የተሽከርካሪ አደጋ ሦስተኛ ወገን መድን ዋስትና አዋጅ ቁጥር 559/2000 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

32. **መብትና ግዴታ መተላለፍ**

በአዋጅ ቁጥር 559/2000 የተቋቀመው የመድን ፈንድ ጽሕፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል፡፡

33. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**